ሁሉም ሁሉን ይወቅ

ከ(ተደሰ) ዓለማየሁ ሞገስ ደረሱ፡

ስለ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሃይማኖታችን በዙሪያችን በእየጊዜው እየተነሡ ለሚፈታተኑን መናፍቃንና በውስጣችንም በዕጪተትም ሆነ ያለዕጪተት ለሚያደናግሩ ረቂአን የሳጥናኤል ካድሬዎች የተሰጠ ተዋሥአ (ከርከር፡ መልስ፡ ተጋሕዶ)።


1987 ዓ.ም.
አዲስ አበባ

መግቢያ

የሃይማኖት መሠረትና ፍጻሜ ወልደ እግዚአብሔር ኢየሱስ ክርስቶስ ነው፤

ከእሱ ሌላ መናፍቃን በሚያወሩት፥ ከሓድያን በሚያመጡት፥ የጸሐፍት ፈሪሳውያን ርዝራዦች፥ አንዳንድ የልማድ ገበሮች በሚዘሩት ተረት፥ ጥሩ ሊት እንኾተው በደንብ ባልተግሩት ትምህርት፥ ጎሊናዎ በሚያወጣው፥ በሚያወርደው፥ አእምሮዎ በሚያሰላስለው ሐሳብ ይቸገራሉ ወይ? ለዚህ ሁሉ መልስ <u>በሙሉ ቃሉን ይወቅ</u> ቁልጭ ብሎ ተመልሶልዎልና እንበው ያስተውሉ፥ አስተውለውም ለወገንዎና ለልጆችዎ ያስተምሩ። ለሀገር መውደድና የፈጠረን አምላክ ለማገልገል ከዚህ የተሻለ መሥዋዕት የለምና።

የደራሲው መብት በሕግ የተጠበቀ ነው



እኛስ የተሰቀለውን ክርስቶስን እንሰብካለን (1ቆሮ. 1:23)

መቅድመ መቅድም

በዚህ ርእስ ከመቅድሙ በፊት የተጻፉት አናትጽ ቢታሪክ ሳይሆን በአነጋገር ምርጥ ጥቅሶች የመጽሐፉን ይዘት ያስፈሳሉና ውድ አንባቢ ሆይ አተኩረህ እንድታነባቸው ትጠየቃለህ።

1. <u>ንሕነስ ንሰብክ ክርስቶስሃ (እኛ ግን፥ እኛማ፥ እኛስ የተሰበክነውን ክርስቶስን እንሰብካለን)</u>። (1ቆሮ. 1:23)
የቤተ ክርስቲያን መሥራች ክርስቶስ ነው። ሥጋ ለብሶ ዓለምን ያዳነ ወልደ እግዚአብሔር ክርስቶስ ነው። ሥጋ በመልበሱ ከአብና ከሰው መካከል ሁኖ ሊያስታርቅ፥ ሊያግልድ የሚኖረው ሊቀ ካህናት ክርስቶስ ነው። ይህን ያላመተ ጎጋ ከመድኀኔ ዓለም ቤተ ክርስቲያን ተክለ ሃይማኖትን ይደርባል፥ ለምን ቢሉት አቡየ እንዲያግልዱን ነው አለ ይባላል። የአማላጆች አለቃ ክርስቶስ መሆኑን ባለግወቁ፤ በክርስቶስ በኩል በቀር ወደ አብ የሚገባ የለም (ዮሐ.14:6)። አሪት የክርስቶስን መምጣት ትናገራለች፤ ሐዋርያት ደግሞ ክርስቶስ መጥቶ፥ አስተምሮ፥ ዓለምን አድኖ፥ ትንቢትን ፈጽሞ ወደ አባቱ መመለሱን፥ ግሬትን፥ ከሱ በኋላ ሐሳዊ መስሕ እንጂ ነቢይ እንደሌለ፥ እንደማይመጣ ይናገራሉ። ይህን ሁሉ ይህ መጽሐፍ ያስረዳልና ወንድሜ ሆይ ቀስ ብለህ አንበው።

2. <u>የክርስትና መሥራች፥</u>
የክርስትናን ሃይማኖት ራሱ አምላክ ሥጋ ለብሶ፥ እንደኛ ሰው ሁኖ ለሰው ልጅ የገለጠው ነው። እግዚአብሔር ሃይማኖትን ለሰው የገለጠው በብሉይና በአዲያት በመንፈስ ቅዱስ፥ በሐዲስ፥ በወንጌል ደግሞ ራሱ ወልደ እግዚአብሔር ሥጋ ለብሶ፥ እኛን መስሎ ነው። ስለዚህ ክሊቃውንት ጠይቆ ከምሁራን ተምሮ፥ መጻሕፍትን በተንታቄ አንብቦ የሚረዱት፥ ከተረዱትም በኋላ በመታዘዝ፥ ታዝዞ የሚከተሉት እንጂ በራሴ ፍልስፍና እጀሳለሁ ብሎ የሚተማጅሩበት አይደለም፥ ሃይማኖት እምነት እንጂ ፍልስፍና አይደለምና። ከወልደ እግዚአብሔር እኔ አበልጣለሁ ግለትም ከቂልነት አልር ፅዘደት ነው። በዚህ ዓለም ምስት ሥርዓቶች አሉ፥ እነሱም ሃይማኖት፥ ፍልስፍና፥ ሳይንስ ናቸው፤ መጠናትም ያለባቸው እንደየሥርዓታቸው ነው።

3. <u>ይህን መጽሐፍ ዳር እስክዳር</u>፥ አንበው፥ ተረድተውም ሆነ፥ እንዲያውሳይረዱ ለጥቅማቸው፥ ስገንዘብ፥ ለዘመት ለሥጋዊ ክብር ብለው፥ ገዝተንዋል ሪገመንዋል የሚሉ ሐሰውተ መሲሕ ክርስቶስ እንደሚነሡ

ይዘህ በመሬ ተነድተህ ወግነህ፥ በሐሰት አትመስክር የሚለውን አምላካዊ ቃል እንዳትተላለፍ አደራ!!!
በዚህም ከአለቆች ደግሞ ብዙዎቹ በእሱ አመኑ ግን ፈሪሳውያን ከምኩራብ እንዳያስወጧቸው አልመሰከሩለትም፥ ከእግዚአብሔር ክብር ይልቅ የሰውን ክብር ወደዋልና። (ዮሐ. 12:42-43)

4. <u>ወደኔ ቅረቡ</u>፥ ይህንም ስሙ፥ እኔ ከጥንት ጀምሬ በስውር አልተናገርሁም፥ በድብቅም ቦታ፥ ከሆነበት ዘመን ጀምሮ እኔ ከዚያ ነበርሁ፥ አሁንም እግዚአብሔርና መንፈሱ ልከውኛል። (ኢሳ. 48:16)።
5. <u>መጨረሻቸው ጥፋት</u>፥ አምላካቸው ሆዳቸው፥ ክብራቸው ጎላራቸው፥ ሐሳባቸው ምድራዊ የሆኑ ሰዎች ይህን መጽሐፍ አይተበሉም። (ፊል. 3:14)
ሆዱን ካላመለከና ፍቅረ ንዋይና ዝሙት ካላታለለው በቀር ከዚህ መጽሐፍ ጋራ የግይስማማ ሊቅና አስተዋይ ሰው አይናርም።
6. <u>የበሰበሰ ዝናም አይፈራም</u>፥ ነውና በእየሃይማኖቱ ድርጅት ያለውን ስሕተት ቅዱሳት መጻሕፍት በሚናገሩት፥ ነቢያት፥ ሐዋርያት፥ ሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያን ባስተማሩት መሠረት ገልጦ፥ ክርስቶስ ያስተማራትን ርትዕት ሃይማኖት አስተምሬ ሩጫዬን ጨርሼ ወደ መድኀኔ ዓለም ልገባ ቆርጫለሁና ቆራጥ ሁሉ ይህን እንድትከተል በዚህ መጽሐፍ ዐዋጅ ነጋሪነት ተጋብዘሃል። የሚከተለውም እውነትን የሚወድ ብቻ ነው።
7. <u>ትምህርት ቀናን ያሻሽላል</u>፥ እንጂ ጠማማን አያቃናም። ይህ መጽሐፍ የተዘጋጀውም መሻሻል ለሚፈልጉ ለቀና ሰዎች ነው።
8. <u>ክርስቲያን ምንድር ነው</u>? ማንነው? ማንን ይመስላል?
ክርስቲያን ክርስቶስን ይመስላል፥ ክርስቶስን ይከተላል። በምን በምን ለሚል፤ ከእግዚአብሔር በጸጋ በመወለድ፥ በማብር ክርስቶስን ለመምሰል በመሞከር፥ መንግሥቱን በመውረስ።
እሱም ወደ ወገኖቹ መጣ፥ ወገኖቹ ግን አልተቀበሉትም። ለተቀበሉት ሁሉ ግን በስሙ ለሚያምኑት ለእነርሱ የእግዚአብሔር ልጆች ይሆኑ ዘንድ ሥልጣንን ሰጣቸው። እነርሱም ከእግዚአብሔር ተወለዱ እንጂ ከደም ወይም ከሥጋ ፈቃድ ወይም ከወንድ ፈቃድ አልተወለዱም። (ዮሐ. 1:10-13)
9. <u>በእምነት ሁላችሁም</u>፥ በክርስቶስ ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጆች ናችሁና፥ ከክርስቶስ ጋራ አንድ ትሆኑ ዘንድ የተጠመቃችሁ ሁሉ

ክርስቶስን ለብሳችኋል። በአሁም ዘንድ አይሁዳዊ ወይም ግሪክ ሰው የለም። ባሪያ ወይም ጭፃ ሰው የለም፤ ወንድም ሴትም የለም÷ ሁላችሁም በክርስቶስ ኢየሱስ አንድ ናችሁና። (ገላ. 3:26-28)

10. <u>በእግዚአብሔር መንፈስ የሚመሩ</u>÷ ሁሉ የእግዚአብሔር ልጆች ናቸውና። አባ! አባት! ብለን የምንጮህበትን የልጅነት መንፈስ ተቀበላችሁ እንጂ እንደገና ለፍርሃት የባርነትን መንፈስ አልተቀበላችሁምና። የእግዚአብሔር ልጆች መሆናችንን ያ መንፈስ ራሱ ከመንፈሳችን ጋር ይመሰክራል። ልጆች ከሆንን ወራሾች ደግሞ ነን። የእግዚአብሔር ወራሾች ከክርስቶስ ጋራ ተወራራሾች (ማለት ከክርስቶስ ጋራ የእግዚአብሔርን መንግሥት እንወርሳለን)። (ሮሜ. 8:14-17፤ ዮሐ. 5:1-5፤ ኤፌ. 4:6፤ ገላ. 4:5-7)
በግብር ክርስቶስን ለመምሰል፤ እኔ ክርስቶስን እንደምመስል እኔን ምሰሉ። (1 ቆሮ. 11:1)

11. <u>የልጅነቱና የወንድምነቱ ታል ኪዳንና ተስፋስ በግብር</u>÷ ተገልጧል ወይ?
እንዴታ! እውነት እውነት እላችኋለሁ በእኔ የሚያምን እኔ የምሠራውን ሥራ አሁም ይሠራል፤ ከዚህም የሚበልጥ ይሠራል። (ዮሐ. 14:12፤ ግብ. 5:1-11፤ 12-16፤ 9:32-43፤ 19:11-20፤ 20:7-12፤ 28:1-9)

12. <u>በእግዚአብሔር መንፈስ የተጻፈ</u> መጽሐፍ ሁሉ ለተግሣጽም ለማሪምም በጽድቅ ለማሠልጠንም ይጠቅማል። (2 ጢሞ.3:17)
ስለዚህ ቅዱሳት መጻሕፍት መጠናት እንጂ እንዲህ እንበለው በማለት መታረም የለባቸውም። እኔ ያዘዝኋችሁን የአምላካችሁን የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ትጠብቃላችሁ እንጂ÷ ባዘዝኋችሁ ታል አትጨምሩም ከአሁም አታጎድሉም። (ዘዳ. 4:2)
በዚህ መጽሐፍ የተጻፈውን የትንቢት ታል ለሚሰማ ሁሉ እኔ እመሰክራለሁ፤ ማንም በዚህ ላይ እንዳች ቢጨምር እግዚአብሔር በዚህ መጽሐፍ የተጻፉትን መቅሠፍቶች ይጨምርበታል÷ ማንም በዚህ በትንቢት መጽሐፍ ከተጻፉት ታላት እንዳች ቢያጎድል÷ በዚህ መጽሐፍ ከተጻፉት ከሕይወት ዛፍና ከቅድስቲቱ ከተማ እግዚአብሔር ዕድሉን ያጎድልበታል። (ራእ. 22:18-19)
ስለዚህ ወንድሜ እንባቢ ሆይ ቅዱሳት መጻሕፍትን ከሚደልዝና ከሚሠርዝ ሐሳዊ ጋራ አትስማማ።

መቅድም

ይህ መጽሐፍ 3 እርእስት ተርበውበት ነበር፥

ሀ. የኢትዮጵያ ተዋሕዶ አርቶዶክስ ሃይማኖት፥

ለ. አርቶዶክስ ሃይማኖት

ሐ. እኛስ የተሰቀለውን ክርስቶስን እንሰብካለን

መ. አርቶዶክሳዊት ሃይማኖት ይህች ናት

ሠ. ርትዕት ሃይማኖት ይህች ናት

ረ. ሁሉም ሁሉን ይወቅ

የመጀመሪያው ርእስ የኢትዮጵያ ተዋሕዶ አርቶዶክስ ሃይማኖት የሚለው ባስተሳሰቡ ልክ በትምህርቱ ተጥተኛ ሳለ፥ ቤተ ክርስቲያኗ የመንግሥት ጥገኛ ሁና በመናርዋ ምክንያት ካህናቱ የንጉሡ አገልጋይ በመሆናችው፥ ከሃይማኖት ይልቅ ስርብትና (መላ) ስለሚቀናችው እነሱ ያልደረሱበት፥ የማያውቁት ወይንም የማይወዱት፥ ጥቅማችውን የሚነካ፥ ራሳችውን ዝቅ የሚያደርግ፥ ፈሪሳዊነታቸውን የሚያጋልጥ መስሎ ከታያቸው፥ ምንም ትምህርቱ ክርስቶስን በተጥታ የሚገልጥ፥ ሃይማኖትን የሚያስረዳ ቢሆንም፥ እይሁድ በሐሰት አድማ ክርስቶስን እንደሰቀሉት፥ የእይሁድ ልጅ ይመስል በግብር መስለው፥ ሁነው ሊቁን ወይንም አስተማሪውን የሐሰት ስም እየሰጡ ሲያባርሩ፥ ሲያሳድዱ ስለኖሩ፥ አውንም ከመጻሕፍት ቅዱሳት ጠቅሶ የሚያስተምር ሰው ሲያገኙ በጹላ እንበለው እንጂ፥ መጽሐፍ ጠቅሰው ተከራክረው ለመሰለ ስለማይፈልጉና ስለማይችሉ፥ ይህን ያመጠኞች መሸሻኒያና መደበቂያ ዋሻ የሆነ ስም ለዚህ ቅዱስና ርቱዕ መጽሐፍ ርእስ ግድረት መልካም ስላልመሰለ ተዘለለ።

በዚ ያለው ሁለተኛው አርቶዶክስ ሃይማኖት ደግሞ፥ ሁላችንም እንደምናውቀው አርቶዶክስ የግሪክ ቃል፥ አርሰስ ርቱዕ ተጥተኛ ዶክሳ ሐሳብ ግለት ነው፤ ሁለቱ ሲገናኙ አርቶዶክስያ፥ አርቶዶክስ ይሆናል፤ ይህም ተጥተኛ ሐሳብ ወይንም እምነት ግለት ይሆናል። ይህ ርእስ ለዚህ መጽሐፍ ተስማሚ ነበር፥ ግን በመላ ዓለም ስለሚጠራበትና ሃይማኖቱ ነኝሎ፥ እምነቱ ስሑት፥ ሐሳዌ ወልጋዳ፥ አካሄዱ ጠማማ ነው የሚል ስለሌለ እንዚን ከማደናገርና በመልስም ከመጋራት አማራጭ መሬለግ ይሻላል ተብሎ ታስቦ።

በሌ የተጻፈው እኛስ የተሰቀለውን ክርስቶስን እንሰብካለን የሚለው ደግሞ ከሁሉ ቢሻልም፥ ይህም መጽሐፍ የተጻፈ ስለሱ ቢሆንም ለኢትዮጵያ ብዙ ካህናት የክርስቶስ ስም ስለማይጣፍጣቸው፥ በመጽሐፉ ይገለጥ እንጂ ርእስ መሆን ይትር ተብሎ ተዘሏል።

ለ፥ መ፥ ሠ፥ ተመሳሳይ ናቸው፤ የቀሩበትም ምክንያት አንድ ነው። በ ረ የተነገረው ሁሉም ሁሉን ይወቅ ግን፥ መጽሐፉ የተዘጋጀው ምስጢር ነው እየተባለ፥ ካህናት የሚያድበሰብሱትን ልጅ ነገር ሁሉ ግልጥልጥ፥ ፍርጥርጥ አድርጎ ለማቅረብ ስለሆነ ሁሉንም ረቶ ቀሚ ሁኗል፥ የእግዚአብሔር ለመሆን የመድኀኒቱ ቁልፍ ጥምቀት ነው። ስለዚህም ጌታችን መድኀኒታችን አስታራቂያችን፥ አማላጃችን ኢየሱስ ክርስቶስ የአመነ የተጠመቀ ይዳን (ማር. 16:16) ብሏል። የዚህን ሙሉ ትርጉም በውስጡ እስከናየው ለጊዜው መግር ከጥምቀት ይቀድማል።

ወደ ወገኖቹ መጣ ወገኖቹ ግን አልተቀበሉትም፥ ለተቀበሉት ግን የእግዚአብሔር ልጆች ይሆኑ ዘንድ ሥልጣንን ሰጣቸው (ዮሐ. ም, 1:12-13)። በዚህም ተወልዶ ብልጫ፥ አንክሶ ሩጫ እንደሌለ እናውቃለን። ቀጥሎም ከአባቱ የሰማሁትን ሁሉ ነገርኋችሁ ብሏል። አንዳንድ ግብዞች እንደሚያደርጉት ምስጢር (ሰውር) የሚባል ድብብቆሽ ነገር የለም። በቤተ ክርስቲያን የምስጢርን ትርጉም የሚያዛቡ ሰዎች አሉ። ምስጢር የግሪክ ቃል ነው። አሁም ከዚህ ላይ ስውር ማለት ሳይሆን፥ ዕፁብ ድንቅ የሚገርም የሚደንቅ ማለት ነው። እሱም ለምሳሌ ሰው በውሃ ይጠመቃል፥ በዚህ ጊዜ በውሃው ላይ መንፈስ ቅዱስ አድሮ የእግዚአብሔር ልጅ ያደርገኛል፥ ፈኑ መንፈስከ ቅዱስ ይረሰዮ ሥጋ ወልድከ (የልጅህን ሥጋ እንዲያደርገው ቅዱስ መንፈስህን) ላክ ብሎ ቄሱ ሲጸልይበት ጎብስቱ አማናዊ ሥጋ መለኮት፥ ወይኑ አማናዊ ደመ መለኮት ይሆናል፥ እኔንም ከኃጢአቴ አንጽቶ መድኀኒተ ሥጋ ወነፍስ ወመንፈስ ቢሆነኝ ይችላል፤ ይሆነኛል ብሎ ማመን ነው። ምስጢር የሚባለው እንጂ ካህን የሚያውቀው መሃይምን የማያውቀው ነገር በነገረ መለኮት አለ ለማለት አይደለም። ስለዚህ ለመላው አንባቢ ሁሉ ምስጢር የሚባል ነገር እንዳይኖር ይህ መጽሐፍ ተጽፏል፤ መጽሐፉ የሚጠቅመውም በመጀመሪያ በመላ ክርስቲያንን፥ ከዚያም እውነትን ለሚፈልግ አይሁድ፥ ኽላም፥ አረማዊ፥ ኢአማኒ ሁሉ ነው። ክርስቲያን ኢስላም ይሁዲ አረሚ ሳይል የሚያነበው ሁሉ እንደሚጠቀምበት ይታመናል።



ደራሲው ከ35 ዓመት በፊት



ደራሲው ዛሬ

ስለ ደራሲው ባጭሩ፡

ለመሆኑ አንተ ማን ነህ? ምንስ አገባህና እንደዚህ ግልጥልጥ አድርገህ ትጽፋለህ? ለሚለኝ ጠያቂ፡ ስለራሴ የሚከተለውን መግለጫ መስጠት ግዴታው ደግሞ እውነትን ለሚፈልግ ሁሉ የተጣለ መሆኑን ለአንባቢ እገልጣለሁ። ከዚህ በታች ያለውን የተናገርሁት በአጣብቂኝ ተይዤ ስለሆነ ከመከራዬ ሁሉ ያዳነኝ እግዚአብሔር አምላኬ በኔ አድሮ የሠራውን ለአንባቢዬ ስል ብናገር ከትምክሕት እንደማይቆጥርብኝ አምናለሁ፡ ንግሩ ለእግዚአብሔር ምሕረቱም ይላልና የእሱን ምሕረት ከማንም በማንስ በእኔ አድሮ መሥራቱን በመናገሬም ለሌሎች ጥብአትን ይሰጣል ብዬ አምናለሁ። ውዳሴ ከንቱ እንዳያደርግብኝም ለእሱ የምጋደልለትን ኢየሱስ ክርስቶስን አለምነዋለሁ። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስም ሆነ ቅዱስ ጳውሎስ ስለራሳቸው ይናገሩ የነበሩት ጳሕፍት ፈሪሳውያን ቢጽ ሐሳውያን ሲያስገድዷቸው ነው። እኔም የክርስቶስና የጳውሎስ ደካማ ተከታይ በመሆኔ አምላኪዬ በእኔ አድሮ የሠራውን በአጭሩ ለመዘርዘር ለአንባቢ ስል ተገድጃለሁ። (ዮሐ. 10:24-29፤ ግብ. 22:1-16፤ ገላ. 1:13፤ 19፤ 2ቆሮ. 11:16-33፤ 12:1-10)

እኔ በኢትዮጵያ ተዋሕዶ አርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን በዘራቸው፡ በሃይማኖታቸው፡ በብቃታቸው፡ በትንቢታቸው ከታወቁ ቤተሰቦች ተወልጄ ያደግሁ፡ ብዙዎቹ ተግርነ የሚሉት ዘመናችውን በቅኔና በዜማ አሳልፈው መጻሕፍትን ባለመግራቸው፡ ቢግሩም በልጅነታቸው በማይገባቸው በማዕዝ ቋንቋ በመግራቸው፡ ሳይረዱ በቃል ግጥናት እንጂ መመራመር ስለሚጎድላቸው፡ የሚያውቁትና የተረዱትም ስለሚፈሩ በደንብ አያስተምሩት እንጂ የኔን ሃይማኖት የመሰለ ርትዕት (የቀና የረታ) ሃይማኖት የለም ብዬ የማምን ነኝ። ከዚህ የደረስሁትም በወላጆቼ እምነትና አመራር ብቻ ተመርቼ ሳይሆን ዐሥራ ሁለት ዓመት በልዩ ልዩ ቋንቋ የተጻፉ ብዙ የሃይማኖት መጻሕፍት ካነበብሁ በኋላ ነው። ዘመናዊውን ትምህርት ከመከታተሌ በፊት የቅኔ መምህር ሁኜ መጻሕፍት ሐዲሳትን አጥንቼ ነበር። ከዚያም በኋላ የሃይማኖት ትምህርቴን ለማጣራት ዘጠኝ ቋንቋ አጥንቼ ነበር፡ አሁን ግን በእርጅናና በብቸኝነት ምክንያት ስለማልጠቀምባቸውም ከጥቂቶቹ በስተቀር ወደየሀገራቸው መመለስ ጀምረዋል። በማስተማር፡ በሃይማኖት በቋንቋ 3 ድግሪ አለኝ።

ከ 34 ዓ.ም. ጀምሬ ለ 57 ዓመት በዘመትሩ ሥጋዊ መተዳደሪያ ተግባሬን እያከናወንሁ እሑድና ቅዳሜ ያለማቋረጥ ሃይማኖቴን ሳስተምር ኑሬአለሁ። መማሩንስ ተማር፡ ማወቁንም ዕወቅ ታዲያ ምን ያስቀባጥርሃል? ለሚለኝ ጠያቂ ደግሞ መልሴ የሚከተለው ነው። ጎብረተ ሰብእ የሚከፈለው በሦስት ነው፡

ሠ) ጅቦች፥ ተኩላዎች፥ ቀማኞች እንስሳቱን የሚተራመቱ አራዊት ሲሆኑ፥
ል) ብዙዎች ደግሞ ከአራዊት የሚከላከሉበት ጥርስ ይሉ ጥፍር የሌላቸው በጎችና አህዮች፥ በመንፈሳዊና በሥጋዊ ሊከፈሉ ይችላሉ።
ሐ) በጣም ጥቂቶቹ ደግሞ በጎችንና አህዮችን በጠቅላላ እንስሳትን አራዊት እንዳይበሏቸው የሚከላከሉ ረኞች ናቸው። የኔ ጠባዕይ በሐ ካሉት ጋራ ነው። በሌላም አነጋገር ከቡር አቶ ሐዲስ ዓለማየሁ በፍቅር አስከ መታበር ካተረፏቸው ገጸ ባሕርያት ቱጹ ካሣንና አበጀ በለው ይመስላል (ም. 18)።

ከዚህም በላይ ዕዳ ያመጣል ብዙ ሳላስበው ስለተግርሁ፥ ተምሬ ላስተምር የወቀቶ አጥሬ ግዲታ ስለአለብኝ ከርስትናም ካወቋት በኋላ ባያስተምሯት ዕዳ ስለምትሆን ነው። (ሉታ. 12:47፤ ያዕ. 4:17)

ስለዚህ ቢሆን አምላኬ መንፈሱን ልኮ ቢረዳኝ በመላ ዓለምን፥ በተቀረ ራሴን ለግዳን አፍጨረጨራለሁ። ለምን ቢሉ የእግዚአብሔር የጸጋ ልጅ በመሆኔ አምላኬ አዝዟልና። (ሕዝ. 3:16)

ከሰባትም ቀን በኋላ የእግዚአብሔር ቃል ወደኔ እንዲህ ሲል መጣ። የሰው ልጅ ሆይ! ለእስራኤል ቤት ጠባቂ አድርጌሃለሁ፤ ስለዚህ የአፌን ቃል ስማ፥ ከኔም ዘንድ አስጠንቅቃቸው። ኃጢአተኛን በርግጥ ትሞታለህ ባልሁት ጊዜ፥ አንተ ባታስጠነቅቀው፥ ነፍሱም ትድን ዘንድ ከክፉ መንገዱ እንዲመለስ ለኃጠአተኛው አስጠንቅቀህ ባትነግረው፥ ያ ኃጢአተኛ በኃጢአቱ ይሞታል፥ ደሙን ግን ከጅህ እፈልጋለሁ። ግን አንተ ኃጢአተኛውን ብታስጠነቅቅ፥ እርሱም ከኃጢአቱና ከክፉ መንገዱ ባይመለስ፥ በኃጢአቱ ይሞታል፥ አንተ ግን ነፍስህን አድነሃል። (20ና 22ንም ተጥለህ አንብ፥ ምዕራፍ 33:1-20ንም ጨምር)።

ዳግመኛም ጌታችን ራሱ፤ የጌታውንም ፈቃድ ዐውቆ ያልተዘጋጀ እንደ ፈቃዱም ያላደረገ ያ ባሪያ እጅግ ይገረፋል። (ሉታ. 12:47)። በጎ ማድረግን ዐውቆ ለማይሠራት ኃጢአት ትሆንበታለች። (ያዕ. 4:17)

እንግዲህ ልጄ ሆይ! አንተ በክርስቶስ ኢየሱስ ባለው ጸጋ በርታ። ብዙ ሰዎች የመሠከሩለትን ከኔም የሰማኸውን፥ ሌሎችን ለማስተማር ሰሚችሉ ለታመኑ ሰዎች አደራ ስጥ። (2 ጢሞ. 2:1-7)

ከዚሁ መልእክት 4:2 ደግሞ ቃሉን ስበክ በጊዜውም ያለጊዜውም ጽና፥ ፈጽመህ አየታገሥህና አያስተግርህ ዝለፍና ገሥጽ ምክርም ይላል።

ስለዚህ በጥምቀት በመንፈስ ቅዱስ ከግዚአብሔር በጸጋ የተወለድህ ሁሉ የጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ወንድም በመሆንህ የጌታን ስም ለማስተግር

እግዚአብሔር ይጠራሃልና ይህን መጽሐፍ ይዘህ ተነሣ እያልሁ እውነትን ለማውጣት ተነሣሁ። በሕይወቴ እርቆ በማየት እየተናገርሁ የተፈጸመው እጅግ ብዙ ነው። ብቻ ገሌ ገሌውን ለማያውቁኝ አንባቢያን መጽሐፉን ማነው የጻፈው? መግሩንስ ይግር ግን እሱ በተግባር ምን ያደረገ ነው? ለሚሉ ጠያቂዎች ባጭሩ የሚከተለውን እትታለሁ።

1. በ36 ዓ.ም. ወሎ መርጦ ከብሉዴ ተክሌ ብሉይ አነብ ነበር። በዚህ ጊዜ የወያኔ ጦር እንዳለፈ ነበርና ደን ይጨፈጭፍ፥ ካንቻ ይመታ ጀመረ፥ እኔም ደኑ ከጠፋ ዝናም ይጠፋል፥ ሀገር ምድረ በዳ ይሆናል እያልሁ ብሰብክ መንግሥት የደኑን መጥፋት ይፈልግ ስለነበር፥ እንዳልሰብክ ተከለከልሁ፥ እኔም እናንተም ትሞታላችሁ፥ ልጆቻችሁም ይለደዳሉ ብዬ ሄድሁ። ወደ አዲስ አበባ እንደመጣሁም መስበክ ጀመርሁ።
2. ከዚህ ጊዜ ጀምሮ እስከ 50 ዓ.ም. ቤተ ክርስቲያን ራሷን እንድትችል፥ በአላፊዎች ነገሥታትና መኳንንት እንዳትመካ ሰበክሁ። በዚህም የንጉሥ ጠላትም ተባልሁ። በቁርኮውም መጻሕፍቱ ትምህርት ቤት እንዳይገቡ ተከለከሉ፥ ተቃጠሉ፥ ወዲያውም ጥብቅ ቁጥጥር እንዲደረግብኝ ለማስታወቂያ ሚኒስቴር ትእዛዝ ተላለፈና የጻፍሁት የግዕዝ መዝገበ ቃላትም ከማተሚያ ቤት ታገደ፥ ታግዶም ቀረ።
3. በ1940 ዓ.ም. በመጋቢት ሊቀ ሥልጣናት መልእክቱን የመጀመሪያው ከዚህ ከቅድስት ሥላሴ ይደልው ብለን የምንሾመው ፓትሪያርክ አንተ ነህ አልኋቸው፥ ምንም እሳቸው በጊዜው ባይቀበሉትም፥ ትንቢቱ ግን ተፈጸመ። ለጊዜውም ብፁዕ ወቅዱስ በሥርዓት ቀዳሚ፥ በቴራ ሣልሳዊ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ተባሉ። ለፍጻሜው ግን የመጀመሪያው ኢትዮጵያዊ ሰማዕት ወቅዱስ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ወፓትርያርክ ዘኢትዮጵያ ሆኑ፥ ተባሉ።
4. በ40 ዓ.ም. የግንቦት መድኀኔ ዓለም ዕለት ገነተ ልዑል ተጠርቼ ብዙ ከተናገርሁ በኋላ ጃንሆይ በትምህርት ሚኒስቴር ሥርዓተ ትምህርት ቢያናድዱኝ ይህ ከሆነ እግዚአብሔር ለመንግሥቱ ቀናዒ ነውና 46 ዓመት ገዝተሽ ሁለት ዓመት ታሰሪኝ ገሃነም ትወርጃለሽ ብዬ ወጣሁ።
5. በ42 የብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ባስልዮስን መታወርና የቅዱስ

ቱምፍሉስን መታሰር ነገርሁ።

6. በ1945 ዓ.ም. ቁስጥንጥንያ በሃልኪ የግሪክ መንፈሳዊ ኮሌጅ በነበርሁበት ዘመን ለመጀመሪያ ጊዜ ከኬልቄዶን (451 ዓ.ም.) ጉባኤ ወዲህ በሁለቱ ባህሪያት አተረጓጎም፥ እንዱ ሌላውን እንዲህ ይላል እያለ ሌላው ወንድሙ የማይለውን እያወራ ተለያይቶ ሊናር፥ ወልደ አብ በመለኮቱ ወልደ ማርያም በትስብእቱ ሁለት ልደት በተዋሕዶ ከበረ ብለን የምናምን እንጂ እንደ አውጣኪስ በጎደረትም ሆነ በጥፍአተ ትስብእት የምናምን አይደለንም ብዬ በሰፊው ለኮሌጁ ቤተ ሰብእ አስረዳሁ፥ በዚህም ምክንያት ራሳችን ቀድሰን የምንቆርብበት ቤተ መቅደስ ተሰጠን። ወዲያውም የኬልቄዶን ጉባኤ መቶኛ ዓመት ሲከበር የቁስጥንጥንያው ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ቅዱስ ቅዱሳን አተናጎራስና የሮማው ቅዱስ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት በእያሉበት በእየቋንቋቸው በአንድ ቀን በመንፈስ ቅዱስ ተመርተው የኬልቄዶን ጉባኤ የሥነ ሥርዓት እንጂ የሃይማኖት ልዩነት የለውም ብለው ጋዜጣዊ መግለጫ ሰጡ። በእኔ በደካማው አድሮ ይህን የተናገረ አምላኬ ለዘለዓለም ይመስገን።

7. በ1950 ዓ.ም. የሰው ዘር የተፈጠረው መጀመሪያ በኢትዬጵያ እንጂ የዚያን ጊዜው ሰው እንደሚያምነው በኢየሩሳሌም እስያ አደለምና በዐባይ ሸለቆና በእየቆላው ይፈለግ ብል የቂል መሣቂያ ሁኜ ለብዙ ቀን ቆየሁ። ይህ በተነገረ ከ30 ዓመት በኋላ ሉሲ ተገኘች። የዐባይን ሸለቆ ግን ከመሪዎች ብዙዎቹ ስለማይወዱት እስካሁን አጥኝ ቡድን ባለመላኩ ቀኑን እንደኔ ትንቢቱን ይቆጥራል። የግብፅን መንግሥት የመሠረቱ ጠቢባንም ያስተማሩ ኢትዮጵያዊያን ናቸው በሚል ርእስ ተነሥቼ ለመተግበር ከዘሬ 22 ዓመት በፊት የውጭ ርዳታ ጠይቄ ከዩኒቨርሲቲህ ድጋፍ ካገኘህ እንረዳሃለን የሚል መልስ በማግኘቴ የኛን ዩኒቨርሲቲ ብጠይቅ መሪዎቹ በቅናትና በጥመት ተጠምደው የድጋፍ ደብዳቤ ባለመጻፋቸው ሳላረጋጠው አረጀሁ፥ ይህም ለኔ ስምና ድካም ቀረብኝ እንጂ በጊዜው ይረጋገጣል።

8. በ1953 ዓ.ም. ንጉሠ ነገሥቱን የንግግር ነጻነት ይልቀቁ የጋላ ገበር የሚባለውን ሀገር በግርማዊነትዎ 10 ጋሻ፥ በግርማዊት 10፥ በልዑላን ልጆችዎ 5:5 በምኒስትሮችዎ 3:3 አስቀርተው ላራሹ

በልዑላን ልጆችም 5:5 በምኒስትሮችም 3:3 አስቀርተው ላራሹ ያካፍሉ፥ ይህን ያደረጉ እንደሆነ እኔና አቤ ጉበኛ በአየጋዜጣው ለሚወጣው መልስ አለን ብላቸው፥ እምቢ ስላሉ፥ ሀገር ምንድር ናትን ጻፍሁና በተንሁ፥ ያዘው ተባለ፥ ይህን የሰሙ ሀገር ወዳድ ሰዎች ደብቀው ጊዜው ሲያልፍ ወጣሁ፥ መጽሐፏ ተቃጠለች። ያዘለችው ትንቢት ግን ሁሉም ተፈጸመ። ራሳቸውም አጉል ሞት ሞቱ፥ መንግሥታቸውንም ባዕድ ወረሰው፥ ልጆቻቸውም ተሰደዱ፥ ከሀገራቸው ድኃ እየቀሙ ወደ ውጭ የላኩት ገንዘብም በቀሰበት ቀረ።

9. ደርግም እስከ 7 ዓመት በሰላም እንደሚቆይ ከዚያ በኋላ ግን ችግር እንደሚያጋጥመው ያውም ከራስ መኮንን እስራሽ ለዩኒቨርሲቲው ቤተ ሰብእ ነግሬ ነበር።

አሁን ወደ ተነሣሁበት ወደ ቤተ ክርስቲያን ልዙርና፥

10. ዶክተር አባ አየለ ተክለ ሃይማኖት፥ ካቶሊካዊ ቄስ፥ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ሰለ ክርስቶስ ባሕርያት አካላዊ ተዋሕዶ የምታምነው ትምህርት በሚል ርእስ የአብያተ ክርስቲያናትን ዝምድና ለማቀራረብ ቢጽፉ አንድ ባሕርይን ለማጽደቅ ሲሉ በቤተ ክርስቲያኒቱ ስም፥ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ከእስክንድርያ እናቷ፥ ከግርቆስ አባቷ በተቀበለችው መሠረት ወልድ በሥጋው የአብ የባህርይ ልጅ ነው (ወልደ አብ በሥጋሁ) የሚል ጽሑፍ ለማስጠንቀቂያ ብለው፥ መጽሔት አይሉት ጋዜጣ አወጡ። እኔም መምህረ ኮነ በበድወሉ፥ ሬደላተ ዘፈጸመ ኩሉ በሚል ርእስ ጽፌ በትኜ ሕዝቡን ከዚህ ታላቅ ስሕተት ከብዙ ክርክር በኋላ አዳንሁ። ጸሐፊውም ከቤተ ክህነት ማተሚያ ቤት ተባረረ።

11. ግንበር ከጠማችሁ፥ ጽዋዕ ከቀመሳችሁ፥ ሳልናከ ከበላችሁ እንደ ሥጋው ደሙ ይቆጠርላችኋል የሚለውን የወንፈል ስብከት ዛሬ ወደ አለበት ደረጃው ያመረድሁት እኔ ነኝ።

12. የመር በዓላትንና ለቅሶን ለማቃለልም ብዙ ደክሜአለሁ።

13. ሠርግና ልግድ በሚል መጽሐፍም ብዙ ዝባዙኬ አስቀርቻለሁ።

14. ያለቁርባን የሚደረግ ተክሊልም ዋጋ እንደሌለው በመጀመሪያ ያስረዳሁ እኔ ነኝ፥ አሁን ግን እነሱም ሊቀበሉት ጀምረዋል። (ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን ከሊቀ ካህናት ክንፈ ገብርኤል

አልታየ፥ ገጽ 129)

15. ሳጃም እንዳይገባ፥ ወባይን እንዳይሸገር፥ መጽሐፍ ቅዱስ ታግዶ ሲኖር፥ የተሻገረው በእኔ ትከሻና ስም ነው፥ ይህንንም በኔ የሠራ አምላክ ይክበር ይመስገን። በዚህ ቁርኾም በዘመነ ደርግ በቀበሌ አግካይነት ከቤቴ ጽላት ወስደው ይጠነቁላል ብለው በመገናኛ ብዙኃን የእውነት ጠላቶች በሐሰት አስነገሩ። ዓለምም ሣቀ።

16. በቦታው እንደምናየው ጌታ ለሥርየተ ኃጢአት ብሎ የሰጠውን ቁርባን፥ ሳትበቁ፥ በቅታችሁ ሳትነጹ ነጽታችሁ ብትቀበሉት ሥጋው እሳት ሁኖ ይበላችኋል፥ ደሙ ባሕረ እሳት ሁኖ ያሰጥማችኋል ይላል ቃለ ወንጌል እያሉ ቅዱሱን ክርስቲያን፥ አምላክ የሞተለትን ሥጋውን ደሙን ተቀብሎ መድኀኒተ ነፍስ ወሥጋ እንዳያገኝ በግድረግ የዲያብሎስ አሽከር፥ የሳጥናኤል ሉሌ፥ የጥበልያኮስ አገልጋይ በመሆን ብዙ ካህናት ኑረዋል፥ አሁንም አሉ።

እኔ በበተነሁት ክታብ ምክንያት ቁረቡ ግለት የጀመሩትም በደንብ አሰረድተው ሳይሆን እንዲያው በደፈናው ቁረቡ እያሉ ነው እንጂ በማሰረዳት አይደለም። ይህንም አስተግረ ብለው መንግሥትን በማወናበድ፥ ራጉኤልን ለመሰረቅ ሲሞክሩ የሰበካው ሕዝብ ቢይዛቸው፥ ባልዋልሁበት አላሰሩኝ፤ እኔ ድርጊቱ ዐርብ የተፈጸመ ግክሰኛ ነው የሰማሁ። አሁንም የተለመደ ውሸታቸውን እንደሚያቀነባብሩ አምናለሁ፥ እኔም እንደ አበው ሰማዕታት እውነቷን ትናግሬ አክሊለ ሰምዕ እደፋለሁ ብዬ አምናለሁ፥

17. በመስቀል ተሰቅሎ ሙቶ፥ ራሱን ሠውቶ ከአባቱ ከአግዚአብሔር አብ ጋራ አስታርቆናል አግልዶናል ብዬ ምስካዬ ሕዙናን መድኀኔ ዓለም ላይ የጸራቅሊጦስ ፅስት ሠኔ ሚካኤል ድርብ ሁኖ ሠኔ 12: 1986 ዓ.ም. ብሰብክ ስሜን ሳይጠሩ ሐምሌ 4: 1986 ዓ.ም. ከሐሰተኞች መምህራን ተጠበቁ በሚል ርእስ አሁን ደግሞ ጌታችን መድኀኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ አላግለደንም፥ አያመልድም አሉና ዐረፉ፤ ግግስዱን በቦታው እናየዋለን፥

18. ከ 36 ዓ.ም. ጀምሬ በዐላውያን ነገሥታት፥ በመናፍቃን ካህናት፥ በአድርባዮች ሊቃውንት፥ በሰው በሚነገዱ ነገር አመላላሾች ስታደን ከሀገር በራት ያለ ጊዜው ሕግ ስወረስ፥ መሬቴን ስነቀል፥ መጽሐፌን ስወረስ፥ አልክበር እንጂ የዓመት ልብስ፥ የዕለት

ይህን ሁሉ ከእሁኑ ሲናዶስ ውስጥ ያሉት አበው ሁሉ ግጥም አድርገው ያውቃሉና እውነትን ከደፈሮት ሊመሰክሩ ይችላሉ። በእነሱም ካልተመለሱ አምላክ የሚፈርድ መሆኑን ነግሬአለሁ፥ እምቢ ካሉ መልሱን ይጠብቁ።

19. አሁን ደግሞ በዙሪያችን ያሉት ሰባኪያን የክርስቶስን አማላጅነት፥ አዳኝነት ቤዛዊነት እያጋነኑ ሲያስተምሩ ጊዜ ከእነሱ ለመሸሽ ለጸሎት ከተጻፈው በቀር የጌታችንን የኢየሱስ ክርስቶስን ሥራና ስም ለማንሣት የሚቀፋቸው ካህናት ብዙ ናቸው። በቀደም ለት ስሙ ይቅርና አንድ ሰባኪ ሰለጋብቻ ሲሰብክ ሰማሁ፤ እሱም ጋብቻን የመሠረተች ቤተ ክርስቲያን ናት ብሎ በለፈው ከ30 ደቂቃ በላይ ለፈለፈ። እኔም ሰብኩቱን እንደ ጨረሰ፥ ጥሩ ሰበክህ፥ ግን ጋብቻን የመሠረተ ክርስቶስ የሚያገባም እግዚአብሔር አብ ነው፥ ቤተ ክርስቲያን ግን ምስክር እንጂ መሥራችም አጋቢም አይደለችም ብለው ገና ሰብኩቱን ሲጀምር በጻድቃን፥ በሰማዕታት በማርያም በአብርሃም ስም ስለነበረ ክርስቶስ በመነሣቱ ፊቱ ተጨማደደ፥ ብዙም ለፈለፈ፥ እንዲህ ያሉት ናቸው የቤተ ክርስቲያንን ልጆች የሚያባርሩ።

ይህ ሁሉ አነሰና አሁን ደግሞ ግን አለብን ብለው የመንደር ወሬ ይመሰል ከቅዱሳት መጻሕፍትም የፈለጉትን ከኪሳቸው እያወጡ ይጨምሩ ከእነሱ ግምት ጋራ የማይስማማውንም ይፍቁ ጀመር፤ ለራሳችን ጥቅም ከተስማማ ቃለ እግዚአብሔር ገደል ይግባ አሉና ቁጭ አሉ።

20. በ1961 ዓ.ም. ደግሞ ሐተታ ዘርአ ያዕቆብ በሚል ርእስ ዘርዐ ያዕቆብ አኩስማዊ ፈላሰፋና ወልደ ሕይወት እንፍራንዛዊ ደቀ መዝሙሩ የጻፉትን ፍልስፍና ኮንቲ ሮሲኒና መሰሎቹ፥ በዐድዋ ላይ በዐፄ ምኒሊክ መሪነት ኢትዮጵያውያን ያደረሱባቸውን የታሪክ ጠባሳ ለመመለስ፥ ጁስቶ ዳ ዑርቢኖ የሚባል ሚሲዮናዊ ቀሲስ መነኮሰ ነው የጻፉቸው ብለው፥ ሰተው፥ አሰተው ዓለምን ካሳመኑ በኋላ፥ መንደረኞቻቸው ትግሮችና ጎንደሮች ዝም ሲሉ እኔ ነኝ ስለ እውነትና ሀገሬ ቁሚ፥ ኢትዮጵያውያን መሆናቸውን ያረጋገጥሁ። በዚህም ፈረንጅ ሰድበሃል ተብዬ ስድስት ዓመት ከእድገት ታገድሁ።

ከጻፍኋቸው መጻሕፍት ሁሉ ብዙ ጠላት ያፈራልኝ ለፈላሰፋው ኢትዮጵያዊ አክሱማዊ ዘርዐ ያዕቆብና ወልደ ሕይወት ጥብቅና መቆሜ ነው። እንደምን? ቢሉ በኢትዮጵያ ሥነ ጽሑፍ ውስጥ የነበሩት መምህራን ሁሉ ከኔ በቀር

ዚሱ በኢትዮጵያ ሥነ ጽሑፍ ውስጥ የነበሩት መምህራን ሁሉ ከኔ ከቀር የተማሩት በውጭ መምህራን ስለሆነና አጣቶቻቸውም ጭዋዎች ስለነበሩ ስለኢትዮጵያ ሥልጣኔ ያላቸው ግምት በጣም ዝቅተኛ በመሆኑ የሚያስተምሩትም ከዚያው ከውጭ ሰዎች ያገኙትን ፍርፋሪ ነውና ዘርዐ ያዕቆብ ኢትዮጵያዊ አይደለም እያሉ ሲያስተምሩ ስማሁና፡ ይህን ስሕተት ተው ፈረንጅ በትቂት ቀን ዝጉን ባህላችንን አጥንቶ እንዲህ ያለ ጽሑፍ ሊያበረክት አይችልም ብል የማይቀበሉኝ ሆነ። እኔም መልስ እጽፋለሁ አልሁ፡ በዚህ ጊዜ ስድስቱ ጓደኞቼ በእየክፍሉ አቶ ዓለማየሁ እድነኞለሁ ብለዋል እያሉ ስተማሪ መሣቂያ አደረጉኝ፡ እኔም ይህን ሰሰማ ግድ የለም፡ ለጊዜው ሥራ ይበዛብኛልና መንፈቅ ይወስድብኝ ይሆናል፡ ከዚያ በኋላ ግን እንኳን በእኔ የሚቀልድበት እንደቡትና የሚሥቅቡት ጥርስ የሚገጥበት ድድ የለውም አልሁና በመንፈቁ አዘጋጅቼ አቀረብሁ፤ ጥናቱንም በግድ ተቀበሉት። ተማሪም የያዙት ድግሪ እንጂ ዕውቀት እንዳልሆነ ተረዳ። እነሱም እትመልሱም ወይ ሲሏቸው ራሳቸውን እየወዘወዙ መረጃ ቀርቧል እያሉ ለጊዜው ዝም አሉ። በኋላ ግን ከኢትዮጵያ ጥናት ውስጥ ስለኢትዮጵያ ጥናት በደንብ የሚያውቀው ዓለማየሁ ነው እያለ ተማሪ ሲያወራ ጊዜና በጻፈው መጽሐፍ የሚያስተምርም ዓለማየሁ ነው ሲባል ጊዜ ቅናት ያዛቸውና ስድስት ሁነው ጽፈው አንዱን እያስፈረሙ የሰም ማጥፋት ዘመቻ እደረጉብኝ በመጻሕፍቴ ላይ ያደረጉት ሂስ ሳይዝላቸው ጊዜ ደግሞ ንጉሠን አይወድም፡ የንጉሠ ጠላት ነው እያሉ፡ የማስተምርበትን ዐረፍተ ነገር ሁሉ ለመረጃ ክፍል ያቀብሉ ጀመር፤ ማጎደሬን ያቁ ሲነግሩኝ ከሰንክሳር ቢበልጥ እንጂ አያንስም ይላሉ። ንጉሠ ሲወርዱ ደግሞ ወዲያው የንጉሠ ወዳጅ ነበር እሉና ዐረፉ።

ይህ ሁሉ እኔን ምንም አላደረገኝም ነበር፡ እኔን የጎዳኝ በእየክፍሉና ለሚያገኙት ሁሉ አቶ ዓለማየሁ ዘረኛ ናቸው፡ ትግሬ አይወዱም፡ ጋላ ይንቃሉ እያሉ ባልዋልሁበት ከወንድሞቼ ጋራ ያጣሉኝ ነው። ከዚህ ወሬ ወዲህ ትግሬና የዚያን ጊዜው ጋላ ያሁኑ ወረሞ እንደርግጠኛ ጠላቱ ያየኛል። ያላልሁትን ያወራል፡ ያላደረግሁትን ይናገራል። ዘረኛ አይደለሁም እንጂ ዘረኛ እንኳ ብሆን፡ ዘሬ፡ ጋሉት፡ አገው፡ ትግሬ ጋላ ስለሆነ የገዛ ዘራን አልጠላም። ለዚህም እውነቱን ለማወቅ ለሚፈልግ ከአባቶቼ በብራና ተጽፎ የተሰጠኝን የዘር መዝገብ ለማሳየት ዝግጁ ነኝ። ለትግሬና ለጋላ ሲና ዲ እነሰው ወይ? ይላል እየተባለ ለሚወራውም የ24 ዓመት ደብተር ስላለኝ እውነትን ለሚፈልግ ሁሉ በደስታ አስነብባለሁ። ይህን ሁሉ ለእንባቢ

ለማሳወቅ በእንግሊዝኛ የየካቲት መጽሔት በመጋቢት ወር በ1985 በወጣው ምክንያት መልስ ጽፌ፡ በእየመጽሔቱ ሥራ የተሰገሰጉት በወሬ የጠሉኝ ስለሆኑ ሳይተበሉኝ ቀሩ። አሁን ግን ይህን ሁሉ የዘረዘርሁ ከቡር አንባቢ ሆይ! በውሼት ወሬ አትጥላኝ አንበህ ፍረድ ለማለት ነው።

የእነዚያ ርዝራዦች አሁንም እንዳልሰብክ ወልድ ፍጡር ይላል እያሉ ስሜን ያጠፉቡ፤ ይህ ግን በዚህ ጽሑፍ ተመልሷልና አያሳስበኝም።

አሁንም እውነትን ይዤ ስለመድኀኔ ዓለም አመሰክራለሁ። ዕድሌ ምን እንደሆነ ግን ከሰማዕትነት በቀር ምንም አላውቅም። ይህን ሲያዩ በትኔና በዚግ የኖሩ ደባትር፡ መጽሐፉን ስለማያውቁት፡ በአድማቸው መጻሕፍትን ሲያጣጥሙ የኖሩ ሊታውንተ መጻሕፍት፡ ብዙ ጊዜ ተጥተኛውን መንገድ ስለማይረዱት ወደ ግዝቱና በትሩ፡ ስም ማጥፋቱ፡ አድማው እንደሚዘሩ የታወቀ ነው። ምን ይሁን ሕልም ፈርቶ ሳይተኙ አይታደር።

በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን በኩል፡ ሁኔታው ይህ ሲሆን በትርቡ የመጡት የሃይማኖት ድርጅቶች ደግሞ፡ ያለ መምህር መጽሐፍ ቅዱስን ብቻ አንብበው መንፈስ ቅዱስ ገለጠልኝ እያሉ፡ ብዙ አስቸጋሪ ጉድለትና ስሕተት ይዘው መጡ። ከእጅ አይሻል ማጭድ። በዚህ ሁሉ መሃል የእኔ ዝምታ ምን ይባላል?

ወልደ እግዚአብሔር ሕያው፡ ወልደ ማርያም ሥጋው፡ በቅዱስ መንፈሱ እየመራ ያስተማራትን መንጌል በዚህ መጽሐፍ አጋዥነት ለኔም ሆነ ለአንባቢዎች እንዲገልጥልን ግለጻ ግለጻ ተምበርክኬ እለምናለሁ። አንባቢዎቼንም እንድትተባበሩኝ በትሕትና በኢየሱስ ክርስቶስ ስም እጠይቃችኋለሁ።

ከዚህ ቀጥሎ፡ መጽሐፉን አንብቦ፡ ሂሰ ወይም እርማት ለሚከተለው ጎትመት ለመላክና ከስብራት በቀር በባህል መድኀኒት ለመፈወስ ለሚፈልግ ሁሉ የደራሲውና የሀገር ባህሉ ሐኪም አድራሻ የሚከተለው መሆኑን በትሕትና እንገልጻለን፤

ዓለማየሁ ሞገስ
ፖ.ሣ.ቁ. 30143
አዲስ አበባ
ቴሌ. 18-23-20
<u>አድራሻ</u>
የቤት ቁጥር 442፡ ተበሌ 10፡ አውራጃ 16፡ የካ፡ ኢ.አ.

እስከዚህ ያለው ስለደራሲው ግንኙት ባጭሩ ይብቃንና ወደ መጽሐፉ ዓላማና ታሪክ ደግሞ እንመለስ። ዐላማው ሃይማኖታችንን ለማያውቁ ለመንገር፥ ላያውቁ እናውቃለን እያሉ የሚያጭበረብሩትን ለማሪምና ለማስተማር፥ ምስጢር ያልገባቸው እነደርሶ ካህን በሚስጥር ሰም የሚያድበሰብሱትን ግልጥልጥ አድርጎ ለመሃይምናን ለማሳየት፥ ክርስቲያን በጥምቀት በጸጋ ከእግዚአብሔር የተወለደ ሁሉ እኩል እንደሆነ ለማስረዳት፥ የሚበላለጠው በግብሩና፥ በሥራው እንጂ በክርስቶስ ዘንድ ከእግዚአብሔር የተወለደ ሁሉ እኩል እንደሆነ ለማሳወቅ። በሌላም አነጋገር ይህን መጽሐፍ ላነበበ ሁሉ የቤተ መቅደስ ምስጢር የሚባል ነገር እያጋጥመውም፥ እባክህ ሊቁ አብራራልኝ፥ ንገረኝ የሚለው ነገርም እይኖረውም።

ታሪኩ ደግሞ ሁላችንም እንደምናውቀው ከ332 ዓ.ም. ገደማ ጀምሮ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ለገዢዎች፥ ለነገሥታቱ መሣሪያ ስለሆነች ሊታውንት በተናገሩ ቁጥር ንጉሡና ጳጳሱ ስለሚያሳድዷቸው፥ የተናገሩትና ያስተማሩት ሲሰደዱ፥ የፈሩት ደግሞ ጭጭ ብለው ኑረዋል። ግመቅስ እናውቃለን፥ ብንናገር እናልቃለን እያሉ፥ ሲሾሙ፥ ሲሽለሙ፥ ሆዳቸውን ሲሞሉ ኑረው አልፈዋል። አሁንም እነዚህን የመሰሉ ለሹመት ዕውቀታቸውን ሸጠው ሃይማኖታቸውን ለውጠው የሚኖሩ ከኔ ይልቅ እንባቢያን የሚያውቋቸው እጅግ ብዙ ናቸው። ይህን ሁሉ እያየሁ እኔም ባልሾም፥ ባልሽለምም ከሰው ጋራ እኖራለሁ ብዬ ዝም ብል በየጊዜው በቤተ ክርስቲያኒቱ ስም እየተጻፈ የሚወጣው ስሕተትና ዐዋጅ እየበዛ በመሄዱ፥ ደጎና የሚያስተምሩት ሰባክያንና ባሕታውያንም በመታገዳቸው፥ ከዚህ በፊት ብዙዎችን ተናገሬ፥ የታረሙት ታረሙ፥ ያልታረሙት ግን በህገር ላይ ጥፋት አምጥተዋል፤ ስለዚህ ክርስቶስን የሚወዱ ለእውነት ቅንዓት ያላቸው፥ ሃይማኖታቸውን ጥርት ባለች መልኳ ግመቅ ለሚፈልጉ፥ ነባይያን እንባቢዎች ይጠቅማል በሚል ይህን ጽሑፍ ለማቅረብ መሰንሁ፥ ክርስቶስን ለሚወድ ሁሉ ጥሩ መብራት ነው። አሜን።

መግቢያ

ተደጋግመው የሚጠቀሱ መጻሕፍት ሁሉ ምሕጻረ ቃል አላቸውና ግጥናት ያስፈልጋል። ለማጎተም ስለሚያስቸግር የግርጌ ማስታወሻ የለንም። የሚጠቀሰው ሁሉ በቅንፍ ተከልሎ ከዚያው ከዘሩ ውስጥ ነው የሚገኝ። አንዳንድ ከባድ የመጽሐፍና የቅኔ ቤት ቃላት ሁሉ በመጀመሪያ ሲገቡ በቅንፍ ይተረጎማሉ፡

በመጨረሻ ደሞ በፊደል ተራ ተጽፈው ተገልጠው ይገኛሉ፡ የተባለውን ላለመደጋገም ምዕራፎች በሙሉ ቁጥር ተሰጧቸዋልና ሲጠቀሱም ያንን ግየት ነው።

አቀራረቡም እንደሚከተለው ነው፤ መጀመሪያ አምስቱ አዕማደ ምስጢር ከዚያ ሰብዓቱ ሀብታት ከዚያ እንደ ትምህርቱ ተቀራራቢነት በተጠየቅ ዘዴ ይከታተላሉ። እሱም የሚከተለው ነው።

አምስቱ አዕማደ ምስጢር

ምስጢረ ሥላሴ
ምስጢረ ሥጋዌ
ምስጢረ ጥምቀት
ምስጢረ ቁርባን
ምስጢረ ትንሣኤ ሙታን።

ሰብዓቱ ሀብታተ ቤተ ክርስቲያን፤

ሀብተ ጥምቀት
ሀብተ ሜሮን (ቅብዐት)
ሀብተ ቁርባን
ሀብተ ክህነት
ሀብተ ተክሊል
ሀብተ ንስሓ
ሀብተ ቀንዲል

አዕማድና ሀብታት የሚለያዩት፡ አዕማድ ትምህርተ ሃይማኖትን ሲያሳዩ፡ ሀብታት ግን በእያንዳንዱ ሀብት አማካይነት ለሰው የተሰጠውን ጸጋ እግዚአብሔር ነው።

በእነዚህ መሠረትነት ትምህርቱ ይቀጥላልና አንባቢ ሆይ ጠንከረህ እንድትከታተል ትጋበዛለህ።

የግሡ ጸታ ብዙ ጊዜ የሚነገረውም በሁለተኛ ሰው ተባዕታይ ነው። ይህ የሆነበት ደግሞ ሌላውን ቁጥርና ጸታ ለማቃለል ሳይሆን በሃይማኖትና በግዕዝ፡ በተለይ ለማሳየት ካልሆነ በቀር፡ ሁለተኛና ሦስተኛ ሰው ጸታና ነጠላ ቁጥር፡ ተባታይ መደብ የተለመደ ስለሆነ በጠቅላላ በመናገር ማደናገርን ለማስወገድ ነው።

ዛሬ ወረቀት በተወደደበት፡ ሠራተኛ በተጓደደበት ጊዜ በስፊው ጽፌ የማሳትምበት ገንዘብ ስለሌለኝ እያንዳንዱ ርእስ ለመጠቆም እንጂ ለመፈጸም ስለማይሠራ አንባቢ ይህን እንደ መግቢያ አድርጎ በዚህ ትምህርት የተጻፉትን መጻሕፍት ይልቁንም ቅዱሳት መጻሕፍትን እንዲያጠናና እንዲያነብ ይጠቁማል።

ከዳግማዊ ምኒልክ ወዲህ የተነሡት ያገሯ መሪዎች አንደኛ ቋንቋውን በደንብ ባለማወቃቸው ሁለተኛ ደሞ አዲስ ነገር አመጣን፥ ከራተኞቹ እኛ እንሻላለን እያሉ ጎጋውን ለግጭበርበር፥ ስርብትና ግስመሰልና ግጭበርበር ግወናበድ ነውና በእየጊዜው ልዩ ልዩ ቃላት ሲያገቡ ኑረዋልI ይኖራሉም። እኔ ግን ስርብትናን ከጠላሁ ብዙ ጊዜዬ ሁኗል። ስለዚህ ቢያንስ በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ስለ ስርብትና (ፖለቲካ) በርቱዕም ሆነ በኢርቱዕ አልናገርምI አልጽፍም። ፖለቲካ ከመጨረሻው ንጉሥ በራት መላና ስርብትና እንደነበረ ግንም ያውቀዋል። ስለዚህ መላ ነባር ስርብትና ግን ዘር በመሆኑ ሰረበተ፥ መሰርበት ስርባቹ ከሚለው ግሥ የሚያደርስ ስለሆነ በሰረበተ ዘር በስርብትና ነው የምሠራው። ይህ ቃል በሌለበት ከፖለቲካ ገባ የሚል ሰው ሁሉ ጠግግ፥ ነገር አጣግሚ ነው።

ከዚህ ሌላ ለአንባቢው አስቸጋሪ ቃላት ያጋጠሙት እንደሆነ አንደኛ በመጀመሪያ ሲመጡ ትርጉማቸው በቅንፍ ይገለጣልና ከዚያ ላይ ግጥናት ሁለተኛ ደግሞ ከመጨረሻ የሚገኘውን ምዕላደ ቃላት ወይም መፍትሔ ቃላት ግግከር ይበሻል።

<u>መዘክር</u>I ጎራጆች በኮምፒተሩ ባለመለመዳቸው አልተጻፉምና እንባቢ እያሰተካከለ እንዲያነባቸው በትሕትና እንጠይቃለን።



ፅሩያን አጋእዝተ ዓለም ሥላሴ

ምዕርፍ 1

ምስጢረ ሥላሴ

የሥላሴን ምስትነት፡ አንድነት፡ ባሕርይ፡ ህላዌ፡ መለኮት፡ ጊዜ፡ ዘመን፡ ሥልጣን የሚያስተምረን ክፍል ምስጢረ ሥላሴ ይባላል። እነሱም በስም፡ በግብር፡ በገጽ፡ በአካል ምስት ሲሆኑ በመለኮት፡ በባሕርይ፡ በሥልጣን፡ በህላዌ፡ በጊዜ፡ በዘመን አንድ ናቸው።

1. የሥላሴ አንድነት ምስትነት

<u>በስም</u> አብ፡ ወልድ፡ መንፈስ ቅዱስ ይባላሉ። <u>በግብር</u> አብ ይወልዳል፡ ያሠርጻል፡ ወልድ ይወለዳል፡ መንፈስ ቅዱስ ይሠርጻል። ስለዚህም አብ ወላዲ፡ ወልድ ተወላዲ መንፈስ ቅዱስ ሠራጺ ይባላሉ። ለአብ ከወልድና ከመንፈስ ቅዱስ የተለየ ፍጹም አካል ፍጹም ገጽ አለው። ለወልድም ከአብና ከመንፈስ ቅዱስ የተለየ ፍጹም አካል ፍጹም ገጽ አለው። ለመንፈስ ቅዱስም እንዲሁ። በመለኮት፡ በባሕርይ፡ በሥልጣን፡ በህላዌ፡ በጊዜ፡ በዘመን ግን ሁሉም አንድ ናቸው። አብ በአባትነቱም ሆነ በአሥራጺነቱ ወልድንም ሆነ መንፈስ ቅዱስን አይቀድምም፤ በዘመንና በክብር ሁሉም እኩል (ዕሩያን) ናቸው። በምንም ምን አይበልጥም አይበላለጡም። አብ ባለበት ሥራ ወልድም መንፈስ ቅደስም አሉ። የአብ ቃሉ ወልድ፡ አስትንፋሱ መንፈስ ቅዱስ፡ የወልድ ልቡ አብ ሕይወቱ አስትንፋሱ መንፈስ ቅዱስ፡ የመንፈስ ቅዱስ ልቡ አብ፡ ቃሉ ወልድ ሁነው በጎብረት በሥላሴነትና ባንድነት ሊሠለሱ ኑረዋል፡ አሉ፡ ይኖራሉ። በዚህ ሁኔታ እየኖሩ አብ አጋዜ ኩሉ ዓለም ፈጣሪ ሰግያት መምድር፡ ወልድ መድኀኔ ዓለም፡ መንፈስ ቅዱስ መጽንዔ ዓለም ጰራቅሊጦስ ይባላሉ። ቅዳሴው ቡሩክ እግዚአብሔር አብ አጋዜ ኩሉ ዓለም ወቡሩክ ወልድ ዋሕድ እግዚእን ኢየሱስ ክርስቶስ መድኀኒነ ወቡሩክ ጰራቅሊጦስ መንፈስ ቅዱስ መድንዒ ወመንጽሔ ኮልነ (ዓለምን ሁሉ የያዘ አምላካችን እግዚአብሔር አብ ቡሩክ ነው። ጌታችን መድኀኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ አንድያ ልጅም ቡሩክ ነው። ሁላችንን የሚያጸና የሚያነጻ አማላጅ መንፈስ ቅዱስም ቡሩክ ነው)። የወልድንና የመንፈስ ቅዱስን አማላጅነት ከቦታው እናየዋለንና ይህን ለጊዜው ትተን ወደ አሁኑ ርእሳችን እንመለስ። (መ.ቅ.ገጽ 42)

2. ምስጢረ ሥላሴ በሐዲስ ኪዳን፡ በጌታ ትምህርት፤

ምንም እንኳ በዘመነ አሪትም በምሳሌና ባንዳንድ ጥቅስ ቢነገርም ምስጢረ ሥላሴን ፍርጥርጥ አድርጎ ያስተማረን ጌታችን መድኀኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ወልደ እግዚአብሔር ሕያው ወልደ ግርያም ሥግው ከሰማየ

ሰማያት ወርዶ ከድንግል ሥጋ ለብሶ፥ ተወልዶ ነው። ስለዚህ ስምስጢረ ሥላሴ መሠረቱ እሱ ነው። ስምን ቢሉ ከራሱ የበለጠ ምስክር የለምና ነው። ሲያስተምርም በትእዛዝ በትምህርት በተግባር ነበረ።
በትእዛዝ ሑሩ ወመህሩ ኮሎ አሕዛበ እንዘ ታጠምቅዎሙ በስመ አብ ወልድ ወመንፈስ ቅዱስ (በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቃችሁ በመላ አሕዛብን ሂዱና አስተምሩ ብሎ ሐዋርያትን አዝዟል። (ማቴ. 28:19)።
በትምህርቱ፥ እኔ ከአብ ዘንድ የምልክላችሁ ከአብ የሚወጣ አራቅሊጦስ (አማላጅ፥ አጽናኝ) የእውነት መንፈስ በመጣ ጊዜ እሱ ስለኔ ይመሰክራል (ዮሐ. 15:26)።
በሕይወቱ፥ በሥራው፥ በድርጊቱ፥ በተግባሩ፥ በግብሩ፥ ይሸውም ሲጠመቅ፥ ኢየሱስም ተጠምቆ ወዲያው ከውሃ ወጣ፥ እነሆም ሰማያት ተከፈቱ የእግዚአብሔር መንፈስም እንደ ርግብ ወርዶ ሲቀመጥበት ዐየ። እነሆም ድምፅ ከሰማያት መጥቶ በርሱ ደስ የሚለኝ የምወደው ልጄ ይህ ነው አለ። (ማቴ. 3:17)። ከዚህም በላይ አባቴ አብ ላከኝ መንፈስ ቅዱስም ይመጣል እያለ አስተምሯል። ከወደዳችሁኝስ ትእዛዜን ጠብቁ፥ እኔም አብን ሌላ አማላጅ (አራቅሊጦስ አማላጅ አጽናኝ ጠባቂ ተብሎ ሊተረጎም ይችላል) ከእናንተ ጋራ ይኖር ዘንድ እንዲልክላችሁ አስምነዋለሁ።

3. ምስጢረ ሥላሴ በሐዋርያት

በአባቱ ፈቃድ በእሱ በራሱና በመንፈስ ቅዱስ ሥምረት ተልኮ መምጣቱንም በእየጊዜው ተናግሯል። ይህን ግን በሰፈው ከዐቃው እናየዋለን። ሐዋርያትና ሲቃውንትም ይህን ተቀብለው ሲያስተምሩ ኑረዋል። በሰማይ የሚመሰክሩ ሦስት ናቸውI እነሱም አብና ቃል መንፈስ ቅዱስI እነዚህ ሦስቱም አንድ ናቸው። (1:ዮሐ. 5:6-8)።

4. ምሥጢረ ሥላሴ በመዝገበ ሃይማኖት

መዝገበ ሃይማኖት በግዕዝ

በመዝገበ ሃይማኖት የተጻፈውን መረብዓን ሃይማኖትን ካጠፉ በኋላ ሰምእመናን ማስተማሪያ ይሆን ዘንድ ከቅዱስ ግርቶስ መንበር የወጣውን የሃይማኖት መግለጫ ከዚህ ቀጥለን መጀመሪያ ግዕዙን በኋላ አማርኛውን እስከ ቁጥር 10 መቱን ከዚያ 13ን:14ን. 38ን:39ን እንጽፋለን አንባቢም ትርጉሙን በቁጥሩ ለማስተያየት ይችላል።

ነአመን በአብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ ቅድስት ሥላሴ።
አብ በገጹ ወበአካሉ ወበመልክኡ ፍጹም ውእቱ።ወልድ በገጹ ወበአካሉ ወበመልእክኡ ፍጹም ውእቱ። መንፈስ ቅዱስ በገጹ ወበአካሉ ወበመልክኡ ፍጹም ውእቱ። ሠለስቱ ገጽ ወአሐዱ ሥምረትI ሠለስቱ አካል ወአሐዱ አርአያI ሠለስቱ አሰግት ወአሐዱ ጽምረትI ሠለስቱ ንባብ ወአሐዱ ቃል ሥሉስ እንዘ ኢይትፈልጥ ወአሐዱ እንዘ ኢይቶሳሕ።
አብ ብርሃን ውእቱ ለሊሁ ወብርሃን ለወልድ ወብርሃን ለመንፈስ ቅዱስI አሐዱ ውእቱ ብርሃን። ወልድ ቃል ውእቱ ለሊሁ ወቃል ለአብ፥ ወቃል ለመንፈስ ቅዱስI አሐዱ ውእቱ ቃል። ወመንፈስ ቅዱስ ለሊሁ ውእቱ መንፈስI ወመንፈስ ለአብI ወመንፈስ ለወልድI አሐዱ ውእቱ መንፈስ።
አሐዱ ህላዌ ዲበ አሐዱ እንዘ ኢይትከፈል። አሐቲ ጥበብ፥ ወአሐቲ ምክር፥ አሐቲ መንግሥት፥ ወአሐቲ ሥልጣን፥ አሐዱ መለኮት: ወአሐዱ ምኩናን።
አብ አምላክ፥ ወልድ አምላክ፥ መንፈስ ቅዱስ አምላክI ኢይትበሀሉ ሠለስቱ አማልክት ዘእንበለ አሐዱ አምላክ። አብ እግዚእ፥ ወልድ እግዚእI መንፈስ ቅዱስ እግዚእI ኢይትበሃሉ ሠለስቱ አጋእዝት ዘእንበለ አሐዱ እግዚአብሔር።
ኢየፀቢ አብ እምወልድ በከሢነ አብ፥ ወኢይንእስ ወልድ እምአብ በከሢነ ወልድ፥ ወመንፈስ ቅዱስኒ ከማሁ ውእቱI ኢየፀቢ ወኢይንእስ እምአብ ወወልድ። ዕሩያን እሙንቱ እንበለ ተውሳክ ወኢንትጋ።
ነአምን በአብ ከመ አብ ውእቱ ሕይወት ወመለኮት ውእቱ፥ ወፈናዊ ውእቱ፥ አምላክ ውእቱ ለሓኪ ወፈጣሪ ውእቱ በቃሉ ወበመንፈሱ።
ወነአምን በወልድ ከመ አምላክ ውእቱ ዘእምአምላክ፥ ብርሃን ዘእምብርሃን፥ ባሕርይ ዘእምባሕርይ፥ ግሕየዊ ዘእምሕይወት፥ መድኀን ዘእመድኀኒት፥ መለኮት ዘእመለኮት ህልው ምስለ አቡሁ ወመንፈሱ።
እምቅመ ያስተርኢ ኩሉ ዘአስተርእየ ወዘኀቡዕ ዘተወልደ እምአብ ዘእንበል እም በምስጢረ ልደት ዘእምንቤሁ ኀቡዕ ወቅዱስ ወስቡሕ ወአልቦ ዘየአምሮ ዘእንበለ አቡሁ ወመንፈሱ ከመ ማእዜ ውእቱ ወከመ አይ ውእቱ ኀሊና መዋቲ ወኢዘ መላእክት አእምሮ።

4.1.10 በእንተ መድኀኒተ ሰብእ ወረደ እምሰማያት በፈቃደ አቡሁ ወመንፈስ ቅዱስ፡ ወተሰብአ እመንፈስ ቅዱስ ወእግርያም እምቅድስት ድንግል በእንበለ ዘርዐ ብእሲ እንዘ ኢይግሰን ድንግልናሃ። ኮነ ፍጹመ ሥጋ በእንበለ ቶስዓ ወኢትድምርት፡ እንበለ ፍልጠት ወኢውላጢ፣ በቤተ ልሔም ተወልደ ወእምድኀረ ወለደት ድንግልናሃ ተረክበ (ማቴ. 1:20፣ 2:1)፣

4.1.13 ወግብረ መስኮት ገብረ በሥጋሁ፡ ወፈወሰ ዱያነ፡ ወእንሥአ ሙታን ወከሠተ አፅይንተ ዕውራን። ወግየ ረስየ ወይነ፡ ወሰረየ ኀጢአተ ብዙኃን ወበደብረ ታቦር ወለጠ አርአያሁ በመስኮት በቅድመ አርዳኢሁ እንዘ ኢይትዌለጥ እምሥጋሁ ኢአሐተ ሰዓተ ወኢከመ ቅጽበተ ፀይን እምድኀረ አሐዱ ከሮን።

4.1.14 ወተሰብሐ ካዕበ እምኀበ አቡሁ ወእመንፈሱ ወለሊሁ እምኔሁ።

4.1.38 ወነአምን በመንፈስ ቅዱስ እግዚእ መሕየዊ፡ ዘወረደ እምአብ እንዘ ኢይትድም ወኢይድኀር፡ እንዘ ኢየሐጽጽ ወኢይትዌሰክ፡ እንዘ ኢይዐቢ ወኢይንእስ እንዘ ኢይበዝኅ ወኢይነትግ፡ እንዘ ኢይፈደፍድ ወኢይውኅድ፡ እንዘ አሐደ ይሴባሕ፡ ወአሐደ ይሰገድ ምስለ አብ ወወልድ፡ ወመንክር ሥላሴ ውእቶ።

4.1.39 ወውእቶ ፍጻሜ ሥላሴ፡ ውእቶ እስትንፋሰ እግዚአብሔር፡ ዘነበበ በአሪት ወበነቢያት፡ ውእቶ ዘይነገር በእነተ ደኃሪ፡ ውእቶ ዘይፈጽሞ ለተዳግሞ፡ ውእቶ ዘተደሳ ወአንጽሖ ለእግዚእትነ ግርያም ወላዕሌሃ ክሡተ ምስጢረ ሥላሴ። ወአመ ኀደረ ላዕሌሃ ቃል መለኮት ኮነ ሥጋ እምሥጋሃ እንበለ ተምያጥ፡ ወኢተውላጥ፡ ወእኮ እምለዲ ወከሉ።

4.1 <u>መዝገበ ሃይማኖት በአግርኛ</u>

<u>ከዚህ በላይ በግዕዝ የተጠቀሰው ትርጉም በአግርኛ</u>

4.1.1 በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ በቅድስት ሥላሴ እናምናለን።

4.1.2 ለአብ ፍጹም ገጽ፡ ፍጹም አካል፡ ፍጹም መልክ፡ ለወልድ ፍጹም ገጽ፡ ፍጹም አካል፡ ፍጹም መልክ፡ ለመንፈስ ቅዱስ ፍጹም ገጽ፡ ፍጹም አካል፡ ፍጹም መልክ አላቸው። ምስት ገጽ አንድ ፈቃድ፡ ምስት አካል አንድ አርአያ፡ ምስት ስም አንድ ተዋሕዶ፡ ምስት ገባብ አንድ ቃል ናቸው። የማይለያይ ምስትነት የማይተላለቅ አንድነት አላቸው።

4.1.3 አብ ራሱ ለራሱ ብርሃን ነው፥ ለወልድም ብርሃን ነው፥ ለመንፈስ ቅዱስ ብርሃን ነው። አንድ ብርሃን ነው። ወልድ ራሱ ለራሱ ቃል ነው። ለአብም ቃል ነው።
ለመንፈስ ቅዱስም ቃል ነው። አንድ ቃል ነው። መንፈስ ቅዱስ ራሱ ለራሱ እስትንፋስ ነው። ለአብም እስትንፋስ ነው፥ ለወልድም እስትንፋስ ነው። አንድ መንፈስ ነው።

4.1.4 በአንድ መንበር ላይ ሳይከፈል፥ አንድ ህላዌ አለ። አንዲት ጥበብ አንዲት ምክር፥ አንዲት መንግሥት፥ አንዲት ሥልጣን፥ አንድ መለኮት አንድ አገዛዝ አላቸው።

4.1.5 አብ አምላክ ነው፥ ወልድ አምላክ ነው፥ መንፈስ ቅዱስ አምላክ ነው። አንድ አምላክ እንጂ ሦስት አማልክት አይባሉም። አብ ጌታ ነው፥ ወልድ ጌታ ነው፥ መንፈስ ቅዱስ ጌታ ነው። አንድ እግዚአብሔር እንጂ ሦስት ጌቶች አይባሉም።

4.1.6 አብ አባት በመሆኑ ከወልድ አይበልጥም፥ ወልድም ልጅ በመሆኑ ከአብ አያንስም፥ መንፈስ ቅዱስም እንዲሁ ከአብና ከወልድ አይበልጥም፥ አያንስም፥ ያለጉድለትና ጭማሪ ትከክል ናቸው።

4.1.7 አብ አባት እንደሆነ፥ ሕይወትም እንደሆነ፥ ገዥም እንደሆነ ወላጅም እንደሆነ፥ በቃሉና በመንፈሱ አምላክ ሠሪና ፈጣሪም እንደሆነ እናምናለን።

4.1.8 ወልድም ከአምላክ የተገኘ አምላክ፥ ከብርሃን የተገኘ ብርሃን፥ ከባሕርይ የተገኘ ባሕርይ፥ ከሕይወት የተገኘ አዳኝ፥ ከመድኀኒት የተገኘ መድኀን፥ ከገዥ የተገኘ ገዥ፥ ከአብና ከመንፈስ ቅዱስ ጋራ አንድ ህላዌ እንደሆነ እናምናለን።

4.1.9 ከሚታየውና ከማይታየው ከመታየቱ በፊት ከርሱ በተገኘ የልደት ምስጢር ያለ እናት ከአብ የተወለደ ያለአብና ያለመንፈስ ቅዱስ መቼ እንደሆነ፥ ምን እንደሆነ፥ የመዋቲ ጎሊናና የመላእክት አእምሮ ሊያውቀው የማይችል፥ የተሠወረ የተመሰገነ ቅዱስ ነው።

4.1.10 ለዉን ለማዳንም በአባቱ ፈቃድ በራሱና በመንፈስ ቅዱስ ሥምረት (ፈቃድ) ከለማያት ወረደ፥ ከቅድስት ድንግል ማርያም በመንፈስ ቅዱስ ያለወንድ ዘር ድንግልናዋ ሳይለወጥ ሰው ሆነ። ያለ መለወጥ፥ ያለመለየት፥ ያለመቀላቀል፥ ያለ መጨመር ፍጹም ሰው ሆነ። በቤተ ልሔም ተወለደ። (ማቴ. 1:20:2:1)

4.1.13 በሥጋውም የመለኮት ሥራ፥ ሠራ፥ ድውያንን ፈወሰ፥ ሙታንንም አስነሣ፥ የዕውራንን ዐይን አበራ፥ ውሃውን ወይን አደረገ። የብዙዎቹን ኃጢአት ይቅር አለ፥ ከተዋሕዶ በኋላ የዐይን ጥቅሻና የአንዲት ሰዓት ስንኳ ያህል ከሥጋው መለወጥ ሳይኖርበት ከተማሪዎች ፊት በደብረ ታቦር ተለወጠ የመለኮቱን አርአያ አሳየ። (ማቴ. 17-:1-4)

4.1.14 ከአባቱና ከመንፈስ ቅዱስም ከራሱም ዳግመኛ ተመለገነ። በታልና በትእዛዝም ብዙ ተአምራት አደረገ። አስመ ሦስት ዓመትም የመንግሥት ወንጌልን አስተማረ።

4.1.38 ሳይተድም፥ ወደ ኋላ ሳይል፥ ሳይነድል ሳይጨምር፥ ሳይበልጥ፥ ሳያንስ፥ ሳይበዛ ከአብና ከወልድ ጋራ በአንድነት የሚሰግዱለት፥ በአንድነት በሚመሰገን ከአብ በተገኘ በሚያድን ጌታ በመንፈስ ቅዱስ እናምናለን። አሱም የሚያስደንቅ ሦስትነት ነው።

4.1.39 እርሱ የሦስትነት መጨረሻ ነው። በአሪትና በነቢያት የተናገረ የእግዚአብሔር አስትንፋስ ነው። እርሱ የቀድሞውን የሚፈጽም የኋለኛውን የሚናገር ነው። አሱ እመቤታችን ማርያምን የተደሳት ያነጻት፥ በላይዋም የሥላሴን ምስጢር የገለጠ ነው። መለኮት ቃል በላይዋ ባደረ ጊዜ፥ ከመዲያ ወዲህም ሳይሆን፥ ያለመመላለስ ያለመለየወጥ ከሥጋዋ ሥጋ ሆነ።

ከዚህ ተጥሎ ደግሞ የሠለስቱ ምእትን ጸሎተ ሃይማኖት በግዕዝና በአማርኛ አታጠን ተርጉመን እናቀርባለን፤ ከዚህ በፊት በአማርኛ የተተረጎሙት ሦስቱም ስሕተት ስላለባቸው ከዚህ ጋራ ማስተያየት ያሻል።

5. ጸሎተ ሃይማኖት በግዕዝ

አአምን በአሐዱ አምላክ እግዚአብሔር አብ አኃዜ ኩሉ ገባሬ አማያት ወምድር ዘያስተርኢ ወዘኢያስተርኢ።

ወአአምን በአሐዱ እግዚእ ኢየሱስ ክርስቶስ ወልደ አብ ዋሕድ ዘህልው ምስሌሁ አምቅድመ ይትፈጠር ዓለም፤ ብርሃን ዘአምብርሃን፥ አምላክ ዘአምአምላክ ዘበአማን፤ ዘተወልደ ወአኮ ዘተገብረ፥ ዘፅሩይ ምስለ አብ በመለኮቱ፤ ዘቦቱ ኩሉ ኮነ ወዘአንበሌሁስ አልቦ ዘኮነ ወኢምንትኒ እምዘኮነ፥ ወዘበምድርኒ፤ ዘበአንቲአነ ለሰብእ ወበአንተ መድኀኒትነ ወረደ አምሰማያት፥ ዘተሰብአ ወተሠገወ አመንፈስ ቅዱስ ወአማርያም ቅድስት ድንግል፥ ዘኮነ ብእሴ ወተሰቀለ በአንቲአነ በመዋዕለ ጲላጦስ አንጢናዊ፥

ዘሐመ ወሞተ ወተቀብረ ወተንሥአ እሙታን አመ ሣልስት ዕለት በከመ ጽሑፍ ውስተ ቅዱሳት መጻሕፍት። ዘወረገ በሰብሐት ውስተ ሰማያት ወነበረ በየማነ አቡሁ። ወዘዳግመ ይመጽእ በስብሐት ይኮንን ሕያዋነ ወሙታነ ወአልቦ ግንለቅት ለመንግሥቱ።

ወአምን በመንፈስ ቅዱስ እግዚእ ግሕየዊ ዘሠርጸ እምአብ ዘይሰገድ ሎቱ ምስለ አብ ወወልድ ወይሴብሕ ኀቡረ። ዘነበበ በነቢያት።ወአአምን በአሐቲ ቅድስት ቤተ ክርስቲያን እንተ ላዕለ ኩሉ። ጉባኤ ዘሐዋርያት።

ወአአምን በአሐቲ ጥምቀት ለስርየተ ኀጢአት።

ወእሴር ትንሣኤ ሙታን ወሕይተ ዘይመጽእ ለዓለመ ዓለም። አሜን።

አባቶቻችን ጸሎተ ሃይማኖትን በብዙ የተረጎሙበት ምክንያት ከአቡነ ዘበሰማይት ጋራ ለማመሳሰል ነው። አይሆንም። አቡነ ዘበሰማያት የማኅበር ጸሎት ነው። ጸሎተ ሃይማኖት ለእያንዳንዱ የእምነት መግለጫ ስለሆነ በነጠላ መሆን አለበት ብለው ነው ሠለስቱ ምእት በነጠላ ያደረጉት።

6. ጸሎተ ሃይማኖት በአማርኛ

ሁሉን በያዘ ሰማይና ምድርን፥ የሚታየውንና የማይታየውን በፈጠረ በአንድ አምላክ በእግዚአብሔር አብ አምናለሁ።

ዓለም ሳይፈጠር ከርሱ በተወለደ የአብ አንድያ ልጅ በሚሆን ባንድ ጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ከብርሃን በተገኘ ብርሃን፥ ከእውነተኛ አምላክ። በተገኘ፥ እውነተኛ አምላክ። በተወለደ እንጂ ባልተፈጠረ፥ በመለኮቱ ከአብ ጋራ እኩል በሚሆን፥ ሁሉ በርሱ በሆነ፥ ስለኛ ስለሰዎች እኛን ለማዳን ከሰማያት በወረደ በመንፈስ ቅዱስ ከቅድስት ድንግል ማርያም ሰው በሆነ፥ በጴንጤናዊ ጲላጦስ ዘመንም ስለእኛ በተሰቀለ፥ በታመመ፥ በሞተ በተቀበረ በሦስተኛው ቀን ከሙታን ተለይቶ በተነሣ፥ በቅዱሳት መጻሕፍት እንደ ተጻፈ በክብር ወደ ሰማይ ባረገ፥ በአባቱም ቀኝ በተቀመጠ፥ ዳግመኛም በሕያዋንና በሙታን ይፈርድ ዘንድ በጌትነት በሚመጣ፥ ለመንግሥቱም ፍጻሜ በሌለው አምናለሁ። ሕይወትን በሚሰጥ ጌታ ከአብ በሠረጸ፥ ከአብና ከወልድ ጋራ በሚሰገድለትና በሚመሰገን በነቢያት በተናገረ በመንፈስ ቅዱስም አምናለሁ። በአንዲት ቅድስት ከሁሉ በላይ በሆነች ሐዋርያዊት ቤተ ክርስቲያን አምናለሁ።

ኃጢአትን ለማስተሥረይ (በምትሰጥ) በአንዲት ጥምቀት አምናለሁ።

በትንሣኤ ሙታንና በሚመጣው ሕይወት ተስፋ አደርጋለሁ። አሜን።

7. ጸሎተ ሃይማኖት የት መጣ?

ሠለስቱ ምእት ጸሎተ ሃይማኖትን ያዘጋጁት ከቅዱሳት መጻሕፍት አወጣትተው ነው፤

7.1 ሰማይንና ምድርን በፈጠረ በአንድ እግዚአብሔር አብ አምናለሁ፤ (ዘፍ. 1:1-፤ ዘፀ. 20:11፤ 1 ዜና. መዋ. 16:26፤ ዕብ. 1:10፤ መዝ. 102:25 ምሳ .8:27፤ ኢሳ. 40:22፤ 42:5፤ 45:12 ኤር. 32:17፤

7.2 በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ አምናለሁ፤ (ሉቃ.5:5፤ 6:5፤ 8፥24፥ 45፤ 9:33-49፤ 17:13፤ 24:50-51፤ ግብ. 2:26፤ 5:31፤ 1:9፤ ሮሜ 10:9፤ 1ቆሮ. 1:9፤ 8:6፤ 12:3፤ ኤፌ. 4:5፤ ዮሐ. 1:1-2፤ 3:16-21፤ ማቴ. 3.17፤ 17:5፤ ምሳ. 8:23-31፤ 1 ጢሞ. 6:16፤ ያዕ. 1:17፤ 1 ዮሐ.1:5-6፤ 5:20-21፤

7.3 ከአብ ያለ እናት ከእመቤታችን ያለ አባት በግብረ መንፈስ ቅዱስ የተወለደ እንጂ ያልተፈጠረ። ማቴ. 1:18-25፤ 3:16-17 17:5፤

7.4 የሞተ፥ የተሰቀለ፥ ከሙታን ተለይቶ የተነሣ፤ (ማቴ. 26፥ 27፥ 28፥ ማር. ከ13-16 ምዕራፍ፤ ሉቃ. 22:47፤ 23-24፤ ዮሐ.ም. 18-21 አንብ።

7.5 ዳግመኛም በክብር ይመጣል፤ (ማቴ. 25:31-24:29-25-46፤ 1 ተሰ. 4:13-18፤ ለመንግሥቱ ፍጻሜ የለውም፥ (ሉቃ. 1:32-33።

በመንፈስ ቅዱስም አምናለሁ፥ (ማቴ. 28:19፤ 12:28፤ ሉቃ. 1:35)፤ ዮሐ. 14:15-26፤ 16:8-15፤ ግብ. 2:1-4 ሮሜ 5:5፤ 8:15-17፤ ገላ. 5:25፤ 1 ቆሮ. 12:3፤ 2 ቆሮ. 13:13)

7.6 <u>ለቃሉአት ግለተሰረያ በአንዲት ጥምቀት፥ አምናለሁ፤</u> ጥምቀት የሚደረገውም ጥንተ አብሶን አጥፍቶ የእግዚአብሔርን ልጅነት ለማግኘት ነው። የሚደረገውም በሕይወት አንድ ጊዜ ብቻ ነው። ቃሉአትም ቢሠራ ንስሐ ገብቶ ይመለሳል እንጂ፥ እንደ <u>ሥርዐተ ረበናት በቴድርም አይጠመቁም</u>። (ማቴ. 28-19-20፤ ማር. 16:16፤ ዮሐ. 3:3-12፤ ኤፌ. 4:5፤ ቆላ. 2:12፤ 1 ጴጥ. 3:21-22)

7.7 <u>ሁሉም በእሱ የሆነ</u>፥ (ዮሐ. 1:1-5፤ ምሳ. 8:22-31)

7.8 <u>በአንዲት ቅድስት ቤተ ክርስቲያን አምናለሁ፤</u>

(ማቴ. 16:18፤ ኤፌ. 5:21-29)

7.9 <u>በትንሣኤ ሙታን በሚመጣው ዘመን ሕይወትም አምናለሁ፤ ተስፋ አደርጋለሁ</u>። (ማቴ. 25:31-፤ 1 ቆሮ. 15:12-፥ 1 ተሰ. 4:13-5:1-11)

በዚሁ በጸሎተ ሃይማኖት መሥመር የዓለም አርቶዶክሳውያን ሊቃውንትንና መምህራን ሲያስተምሩ ኑረዋል አሁንም ያስተምራሉ።

8. ሥላሴ በብሉይ ኪዳን

የሐዲስ ኪዳኑ ይህ ሲሆን በብሉይ ኪዳን ደግሞ እግዚአብሔር አንድ ገጽ፥ አንድ አካል ብቻ ሳይሆን ሦስትነቱን የሚያመለክቱም ብዙ ክፍሎች አሉ። ግን እንደ ሐዲስ ኪዳኑ ፍርጥርጥ አድርገው አይናገሩም፤ ምክንያቱስ ቢሉ፥ እስራኤል በዙሪያቸው የነበሩትን የአሕዛብ አማልክት ለመከተል ዝንባሌ ስለነበራቸው እነሱን እስኪሠለጥኑ ድረስ ከዚያ ሰግራቅ፥ ብዙትንም አንድነትንም በሚያሳይ አጣልል ይነገር ነበር፥ ሦስትነትን የሚያሳዩ ብዙ ጥቅሶች አሉ፤

ሰብዓ ሊቃናትም መጻሕፍተ ብሉያትን ከዕብራይስጥ ወደ ጽርእ ሲተረጉሙ ከእስራኤል ዝንባሌ ለመሸሽ ብዙውን ነጠላ እያደረጉ ተርጉመዋል። ስምለሌ፥ በመጀመሪያ እግዚአብሔር (ኤሎሂም) ሰማይና ምድርን ፈጠረ ያለው ቃል ለቃል ሲተረጎም ኑር ኤሎሂም አማልክት መሆን ነበረበት፥ ጽሑም አንዳንድ ጊዜ ብዙውን ስም ነጠላ ግሥ ስለሚከተለው በመጀመሪያ አማልክት ሰማይና ምድርን ፈጠሩ ቢል ይሰድ ነበር፤ ተርጓሚዎች ግን ነጠላን መርጠዋል። አውንም አማልክት የሚለው ቃል ሁለትም አራትም ሊያሳይ ይችላል፥ ግን በሐዲስ ኪዳን ስለተመሰነ ሊያደናግረን አይችልም። (ዘፍ. 1:1)።

ቀጥሎም ሰውን በመልካችንና በአምሳያችን እንፍጠር (ዘፍ. 1:26)። ይህ ጥቅስም ምንም ብዛትን ቢያመለክትም፥ ንቱማዊ አነጋገር ነው የሚሉ አሉ። ንጉሣዊ አነጋገር ከ 16ኛው መቶ ዘመን በፊት በማንም ሀገር ያለተለመደ፥ ይልቁንም በመካከለኛው ምሥራቅ ያልታወቀ ስለነበረ ጉንጫ አልፋ ቄትቄት ከመሆን በቀር ሩይዳ የለውም። በብሉይ ኪዳን ታሪክ እየመሩ ያሉ ነገሥታት ሁሉ፥ እንፈርያን፥ እነዳርዮስ፥ እነዳሢት እነአስቴርን ጨረ ስንቱን፥ ሲናገሩ የንበረ በነጠላ ነው። እሱም ራሱ እግዚአብሔርም ልእክርሃም፥ ለሙሴ፥ ለሳሙኤል በነጠላ ሲናገር ስለኖረ ይህ ነገር የሚያከራክር አይደለም።

ብዙትን ከሚያመለክቱ ጥቅሶችም፥ እግዚአብሔር አምላክም አለ፤ እነሆ አዳም መልካምንና ክፉን በማወቅ ከእኛ እንዳንዱ ሆነ። (ዘፍ. 3:22) ከእኛ እንዳንዱ ምስትነትን ብዙትን፥ እግዚአብሔር አምላክም አለ እንድነትን ያሳያል። ዘፍ. ምዕራፍ 18ም የተጻፈው በአንድና ብዙ ስለሆነ አንጫጪ ልብ እድርጎ እንዲያነበው ይጠቁማል።

የሚከተለው ጥቅስም ብዙነትን ያሳያል፤ ኑ እንውረድና ቋንቋቸውን እንደባልተው (ዘፍ. 11:7)

ኢሳያስም ስለሥስትነት ሲጠቁም፥ ንጉሥ የዚያን በሞተበት ዓመት፥ እግዚአብሔርን በረጅምና ከፍ ባለ ዙፋን ላይ ተቀምጦ ወየሁት.....ሱራፌልም አንዱ ለአንዱ ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ፥ የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር ምድር ሁሉ በክብርህ ተሞልታለች፥ እያሉ ሲጮኽ ነበር ብሎ ሥስትነቱንም አንድነቱንም ተናግሯል። (ኢሳ 6:1-3)

ከቡር ዳዊትም የእግዚአብሔርን ሥስትነት እንደሚከተለው ገልጿል፤

ሣሁሉ ለእግዚአብሔር መልአ ምድረ
ወበታለ እግዚአብሔር ጸንዓ ለማያት
ወእምእስትንፋሰ አፉሁ ኩሉ ጎይሎሙ።

(የእግዚአብሔር ኖርነት መሬትን ሞላ፥ በእግዚአብሔር ቃልም ሰማያት ጸኑ፥ በአፉ እስትንፋሱም ጎይላቸው ሁሉ) በዚህም እግዚአብሔር አብን፥ ቃለ እግዚአብሔር ወልድን፥ እስትንፋሰ እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስን ገልጿል። (መዝ. 32:5-6)

9. ሥላሴ በሊቃውንት

ሥሉስ ቅዱስ ዕሩያን ለመሆናቸው፥ በአየጊዜው የተነሡ ሊቃውንት የሚከተለውን ምሳሌ ዘየሐጽጽ (ጎደሎ ምሳሌ) እየሰጡ ሲያስተምሩ ኑረዋል፤ አብ ፀሐይ፥ ወልድ ፀሐይ፥ መንፈስ ቅዱስ ፀሐይ፥ በዚህም በፀሐይ አካል በፍሕሙ አብ፥ ብሙቀቱ ወልድ፥ በብርሃኑ መንፈስ ቅዱስ ይመሰላሉ። ከፍሕሙ ከሙቀቱ ከብርሃኑ ማነው የሚቀድም? ሙቀትና ብርሃን ከፍሕም እንደተገኙ ግን ርግጥ ነው።

እንደዚሁም አብ አሳት ወልድ አሳት መንፈስ ቅዱስ አሳት፥ ይህም እንደሌይኛው ነው። አሁንም አብ ሐሊብ (ወተት) ወልድ ሐሊብ፥ መንፈስ ቅዱስ ሐሊብ ይላሉ፤ ከወተት ቅቤ፥ አይብ፥ አጓት ይገኛሉ፥ ከእነዚህ በማንተ ተፈጥሮ የነበረ ማነው፥ ይህ ይቀድማል፥ ያ ይከተላል እያሉ ጉንጭ ከማልፋትና ጊዜ ከማሳለፍ በቀር የዚህ መልስ የለውም።

ከዚህ ቀጥዬ እኔም የዘመኔን ዕውቀት ተደግፌ የምሰጠው ምሳሌ ዘየሐጽጽ አለኝ፤ ያለ ወሲብ (ሕውስት ተራክቦ) የሚራቡ ትሎች አሉ። እነዚህ ተሐዋስያን (ተላዋሾች) የሚባሉት ከውስትም ከሦስትም እየተቆራረጡ ነው። ከነዚህ ከሦስቱ የትኛው ነው የሚቀድመው ከመሃል ያለው ነው ወይስ በግራና በቀኝ አየበረሩ የሄዱት?

በህላዌ በቅድምናስ የተሰጠውን ጥቅስና ምሳሌ ተቀብለን ዕሩያን (አኩል) ናቸው እንበል፥ በክብር አብ አባት አይደለም ወይ? ስለዚህ አይበልጥም

ወይ? ለሚል ጠያቂ ደግሞ የሚከተለው ይመለስለታል።
ስክብርም አይበላለጡም፥ ከልጁ የሚበልጥ አባት፥ ከአባቱ የሚበልጥ ልጅ አለና። ለምሳሌም ሰናክሬም፥ ናቡከደነጸር፥ እስክንድር፥ አውግስጦስ ቄሳር፥ ናፖልዮን፥ ዐፄ ቴዎድሮስ፥ ዐፄ ዮሐንስ፥ ዐፄ ምኒልክ፥ ዐፄ ኀይለ ሥላሴ፥ መንግሥቱ ኀይለማርያም፥ ኧረ ስንቱን! ሰምሳሌ ያህል ከተጠቀሰ ይበቃል። እም! እንዲህስ ይባላል፥ ታሪኩም እውነት ነው፤ ግን ዐይናቸውን ጨፍነው፥ ጆሮአቸውን ወትፈው፥ አብ ከወልድና ከመንፈስ ቅዱስ ይበልጣል፥ እንዲያውም ወልድንስ ፈጥሮታል፤ መንፈስ ቅዱስም ሕጹጽ ከዚያውም አሳል የሌለው ዝርው ኀይለ እግዚአብሔር ነው የሚሉ አሉ። ለዚህ ሁሉ መልሱ ምንድር ነው ለሚል ጠያቂ፤

10. ሥላሴ በቅዱሳት መጻሕፍት

10.1 ኢየሱስ ክርስቶስ ወልደ እግዚአብሔር ከሦስቱ አካላት አንዱ ነው።

<u>ኢየሱስ ክርስቶስ አምላክ ወልደ አምላክ ነው</u>

አርዮናውያን ኢየሱስ ክርስቶስ ወይም ወልድ አምላክ አይደለም፥ ቢሆንም ትንሽ አምላክ ነው ስለሚሉ የሚከተለው መልስ ተሰጥቷል። እግዚአብሔር በመለኮቱ ቀናዒ ነው፥ ስለዚህም እንደሱ አምላክ ላልሆነ አምልኮቱን አያካፍልም ወኢይሁብ ክብርየ ለባዕድ (ክብሬን ለባዕድ አልሰጥም ብሏል። (ዘፀ. 20:1-7) እግዚአብሔር ዳኛም፥ ፈራጅም ቁጡም ንስሓ በማይገባ ነው፤ በንስሓ በሚመለስ ደግሞ መሐሪ ነው። ዘፍ. 3:1-19፤ ዘጉ. 20:10-13፤ ዘዳ. 3:23፤ በትእዛዙም ጥብቅ ነው። 1 ሳሙ. 15:1-23፤ ለልጁ ግን እውነተኛ እኩያው አምሰክ ስለሆነ ፍጥረት ሁሉ እንዲያመልከውም እንዲሰግድለትም አዝዟል፤ ከመላእክቱስ ለማን ነው እንዲህ ያለው? አንተ ልጄ ነህ፥ እኔም ዛሬ ወለድሁህ፥ እኔ አባት እሆንዋለሁ እሱም ልጅ ይሆነኛል። ልጁንም ወደ ዓለም ሲያገባ የእግዚአብሔር መላእክትም ሁሉም ለእሱ ይስገዱ ብሏል። (ዕብ. 1-10)

10.2 <u>ወልድ ኢየሱስ ክርስቶስ በመለኮቱ ከአባቱ ጋራ ዕሩይ ነው።</u>

አባቱም አምላክ፤ አሱም አምላክ አይበላለጡም፥ እይተናነሱም። አኖን ለማዳን ለማስታረቅ ለማግለድ ግን ሥጋ ለብሶ ብዙ የትሕትና ተግባር ፈጽሟል፥ በሥጋው ተዋርዷል፥ ተሰድቧል፥ ተገርፏል፥ ተገፏል፥ ተሰቅሏል፥ ሙቷል፥ ከዚህም በፊት እናቱ፥ ዮሴፍ፥ የሥጋ ዘመዶቹ ሁሉ አዝዘውታል፥ ልከውታል፥ የደቀመዛሙርቱን እግር አጥቧል፥ የውርደት ውርደት፥ እንደ ባሪያም ተሸጧል ያውም በ30

ብር፥ የመለኮት ኩራትና መጀነን የቀረው ሰውን ለማዳን ሥጋ ለመልበስ በወሰነ ጊዜ ነው። ሰውን ለማዳን ሲወሰን ግን በፈቃዱ እንጂ ያስገደደው የለም። ሁሉንም በቅደም ተከተል እናየዋለን።
ለዚህም ከራሱ ከአባቱ ከእግዚአብሔር አብ ጀምረን
አምላክነቱን፥ልጅነቱን የሚያስረዱ ጥቅሶች እንጠቅሳለን።

10.3 <u>ራሱ እግዚአብሔር አብ</u>፥ ትእዛዙን እናገራለሁ፤ እግዚአብሔርም አለኝ፥ አንተ ልጄ ነህ፥ እኔ ዛሬ ወለድሁህ፥ በመለኮቱ አኩያው ልጁ መሆኑን ለማሳየት ወለድሁህ፥ አለ። ግንም ቢሆን የሚወልደውን አይፈጥረውም፥ የፈጠረውን ደግሞ አይወልደውምና። ሥጋን ሲያይ ደግሞ በሥጋው፥ ሥጋ ለብሶ እኛን እንዳግለደንና እንዳስታረቀን ለማስረዳት አሕዛብን በርስትነት እንድሰጥህ ለምነኝ፥ አሰጥሃለሁ አለው። (መዝ. 2:6) አምላክ ሆይ! መንበርህ ለዓለመ ዓለም ነው። የመንግሥትህ በትር የቅንነት በትር ነው። ጽድቅን ወደድህ ዓመፃንም ጠላህ። (መዝ. 44:6-7)

10.4 <u>በጊዜ ጥምቀትም</u>፥ ኢየሱስም ከተጠመቀ በኋላ ወዲያው ከውኃው ወጣ፥ እነሆም ለግያት ተከፈቱ፥ የእግዚአብሔር መንፈስም እንደርግብ ወርዶ በራሱ ላይ ሲቀመጥ ዐየ፥ እነሆም ድምፅ ከሰማያት መጥቶ የምወደው ልጄ ይህ ነው አለ (ማቴ. 3:16-17) ቀጥሎም በ17ኛው ምዕራፍ ቁጥር 5ም ይህንኑ ደግሞ አጽንቶታል። በርሱ ደስ የሚለኝ የምወደው ልጄ ይህ ነው፥ እሱን ስሙት ብሎ፥ (ማር. 1.11፤ ሉቃ. 3:22) ዳግመኛም፥ እነሆ የመረጥሁት ውድ ልጄ፥ ነፍሴ የተደሰተችበት፥ መንፈሴን በእሱ ላይ የማኖርበት፥ ፍርድን ለአሕዛብ ይነግራል፤ አይከራከርም አይጮኽምም፥ ድምፁንም በአደባባይ የሚሰማ የለም። (ማቴ. 12:18፤ ኢሳ. 42:1-4፤)

ከገናናው ክብር በእሱ ደስ የሚለኝ የምወደው ልጄ ይህ ነው፥ የሚል ድምፅ በመጣለት ጊዜ ከእግዚአብሔር አብ ክብርና ምስጋና ተቀብሏልና። (2ጴ. 1:17፤ 18)

10.5 <u>ራሱ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ስለራሱ አምላክነት የአብ ልጅነቱን የመሰከረው፤</u>
በእሱ የሚያምን ሁሉ የዘለዓለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ፥ እግዚአብሔር እንድያ ልጁን እስኪሰጥ ድረስ ዓለሙን

እንዲሁ ወዲልና። ዓለም በልጁ እንዲድን ነው እንጂ በዓለም እንዲፈርድ እግዚአብሔር ወደ ዓለም አላከውምና። በእሱ በሚያምን አይፈረድበትም፥ በማያምን ግን በአንዱ በእግዚአብሔር ልጅ ስም ስላላመነ አሁኑኑ ተፈርዶበታል። (ዮሐ. 3:16-18)

10.6 እውነት እውነት እላችኋለሁ፥ ሙታን የእግዚአብሔርን ልጅ ድምፅ የሚሰሙበት ሰዓት ይመጣል። አሁም አሁን ነው። (5:22-26)
እውነት እውነት እላችኋለሁ፥ እውነተኛ እንጀራ ከሰማይ የሚሰጣችሁ አባቴ ነው እንጂ ከሰማይ እንጀራ የሰጣችሁ ሙሴ አይደለም...(ዮሐ. 6:32)

10.7 ኢየሱስም ወደ ውጭ እንዳወጡት ሰማ፥ ሲያገኘውም፥ አንተ በእግዚአብሔር ልጅ ታምናለህን አለው? እሱም መልሶ ጌታ ሆይ! በእርሱ አምን ዘንድ ማነው? አለ። አይተኸዋልም፤ ከአንተ ጋራም የሚናገረው እሱ ነው አለው፥ እሱም ጌታ ሆይ! አምናለሁ ብሎ ሰገደለት፤ (ዮሐ. 9:35-38፤ 10:36)
እኔና አብ አንድ ነን፤ (ለክርክሩ ዮሐ. 10:22-30 ያነቧል፤)
(ዮሐ. 14:6-11)

10.8 እኔን የሚጠላ አባቴን ይጠላል። (ዮሐ. 15:23)

10.9 አብ ሙታንን እንደሚያስነሣ ሕይወትም እንደሚሰጣቸው፥ እንዲሁም ወልድ ደግሞ ለሚወዳቸው ሕይወትን ይሰጣቸዋል። (ዮሐ. 5:20)

10.10 እኔ ራሴን ባከብር ክብሬ ከንቱ ነው፥ የሚያከብረኝ እናንተ አምላካችን የምትሉት አባቴ ነው። (ዮሐ. 8.54)

10.11 <u>ዮሐንስ መጥምቅ</u>፥ ኢየሱስም ከተጠመቀ በኋላ ከውሃው ወጣ፥ እነሆም ሰማያት ተከፈቱ የእግዚአብሔር መንፈስም እንደ ርግብ ወርዶ ከራሱ ላይ ሲቀመጥ ዐየ፥ እነሆም ድምፅ ከሰማያት መጥቶ በእርሱ ደስ የሚለኝ ልጄ ይህ ነው አለ። (ማቴ. 3:16፤ ማር. 1:9-11፤ ሉቃ. 3:21-22)

10.12 <u>ዮሐንስ ወንጌላዊ</u>፤ በመጀመሪያ ቃል ነበረ፥ ቃልም በእግዚአብሔር ዘንድ ነበረ፤ ቃልም እግዚአብሔር ነበረ፤ ይህ በመጀመሪያ በእግዚአብሔር ዘንድ ነበረ፤ ሁሉ በእርሱ ሆነ፥ ከሆነውም እንዳች እንኳ ያለ ርእሱ አልሆነም። በእርሱ ሕይወት ነበረች፥ ሕይወትም የሰው ብርሃን ነበረች። ብርሃንም በጨለማ ያበራል፤ ጨለማም አላሸነፈውም። (ዮሐ. 1.1-5)

የእግዚአብሔርም ልጅ እንደመጣ አውነተኛም የሆነውን እናውቅ ዘንድ ልቡናን እንደ ሰጠን እናውቃለንI አውነተኛም በሆነው በእርሱ አለን፥ እርሱም ልጁ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው፥ እርሱ አውነተኛ አምላክና የዘለዓለም ሕይወት ነው። (1ዮሐ. 5:20)

<u>ዮሐንስ በእስያ ላሉት ለሰባቱ አብያተ ክርስቲያናትI</u> ካለውና ከነበረው ከሚመጣውም፥ በዙፋኑም ፊት ካሉት ከሰባቱ መናፍስት ከተአመነውም ምስክር ከሙታንም በኩር፥ የምድርም ነገሥታት ገዥ ከሆነ ከኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋና ሰላም ለእናንተ ይሁንI ለወደደን ከኃጢአትም በደሙ ላጠበን፥ በመንግሥቱም ለአምላኩና ለአባቱ ካህናት እንድሆን ላደረገ፥ ለእርሱ ከዘለዓለም እስከ ዘለዓለም ድረስ ክብርና ኀይል ይሁን፥ አሜን። እነሆ በደመናት ይመጣልI ዐይንም ሁሉ የወጉትም ያዩታልI የምድርም ወገኖች ሁሉ፥ ስለርሱ ዋይ! ዋይ! ይላሉI አዎን፥ አሜን። ያለውና የነበረው የሚመጣው፥ ሁሉንም የሚይዝ (የሚገዛ) ጌታ አምላክ አልፋና አሜጋ እኔ ነኝ ይላል። (ራእ. 1:4-8)

ባየሁትም ጊዜ እንደ ሞተ ለው ሁኜ ከእግሩ በታች ወደቅሁ። ቀኝ እጁን ጭኖ እንዲህ አለኝI አትፍራ ፊተኛውና መጨረሻው ሕያውም እኔ ነኝ፥ ሙቼም ነበርሁ፥ እነሆም ከዘለዓለም እስከ ዘለዓለም ድረስ ሕያው ነኝ። የሞትና የሲኦልም መክፈቻ አለኝ። (ራእ. 1:17)

ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆነ ታምኑ ዘንድ፥ አምናችሁም በስሙ ሕይወት ይሆንላችሁ ዘንድ ይህ ተጻፈ። (ዮሐ. 20:31)

10.13 <u>ቅዱስ ጳውሎስ-</u> በገዛ ደሙ የዋጃትን የእግዚአብሔርን ቤተ ክርስቲያን ትጠብቁአት ዘንድ መንፈስ ቅዱስ እናንተን ጳጳሳት አድርጎ ለሾመባት ለመንጋው ሁሉና ለራሳችሁ ተጠንቀቁ። ግብ. 20:28

ለእኛስ ነገር ሁሉ ከእሱ የሆነ እኛም ለእርሱ የሆንን አንድ አምላክ አብ አለን፥ ነገር ሁሉ በእሱ በኩል የሆነ አንድ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ አለን። (1ቆሮ. 8:6) በእርሱ የመለኮት ሙላት ሁሉ በስውነት ተገልጦ ይኖራልI (ቆላ. 2:9)

10.14 <u>ሌሎች ሐዋርያት፥</u> ቶማስም ጌታዬ አምላክዬም ብሎ መለሰለት። (ዮሐ. 20:28)

ጴጥሮስም አንተ ክርስቶስ የሕያው እግዚአብሔር ልጅ ነህ። (ማቴ. 16:17)

ሐዋርያው ይሁዳ፡ አስቀድመው ለዚህ ፍርድ የተጻፉ ሰዎች በስውር ገብተዋልና፡ እነሣቸውም እግዚአብሔርን የማይፈሩ የአምላካችንንም ጸጋ በርኩሰት የለወጡ ብቸኛውንም አምላካችንንና ጌታችንን ኢየሱስ ክርስቶስን የካዱ ናችው። (ይሁዳ. 1:4)

10.15 መናፍስት፡ እነሆም፡ ኢየሱስ ሆይ! የእግዚአብሔር ልጅ ከእንተ ጋራ ምን አለን? ጊዜው ሳይደርስ ልትሠቃየን ወደዚህ መጣህን? እያሉ ጮኹ። (ማቴ. 8:29፤)

በዚያን ጊዜ በምኩራባቸው ርኩስ መንፈስ ያደረበት ሰው ነበረ፡ እርሱም፡ የናዝሬቱ ኢየሱስ ሆይ! ከእንተ ጋራ ምን አለን? ልታጠፋን መጣህን? ማን እንደሆንህ ዐውቄአለሁ፡ የእግዚአብሔር ቅዱስ ነህ ብሎ ጮኸ። (ማር. 1:24፤ ሉቃ. 4:34)

10.16 ነቢያት፡ ሕፃን ተወልዶልናልና፡ ወንድ ልጅም ተሰጥቶናልና፡ አለቅነቱም በጫንቃው ላይ ይሆናል፡ ስሙም ድንቅ መካር፡ ኃያል አምላክም፡ የዘለዓለም አባት የሰላም አለቃ ተብሎ ይጠራል። (ኢሳ. 9:6)

11. ሥላሴ በመናፍቃን

እነዚህ አርዮሳውያንና መቅዶንዮሳውያን ናቸው። በመጀመሪያ አርዮሳውያንን እናስ ቀድማለን። የጆሐባ ምስክሮች ነን እያሉ መቅደስ ሠርተው፡ ቤተ ክርስቲያን አንጸው ሳይሆን ቤት ለቤት እየተሽሎከሎኩ ሕፃናትንና ያልተማሩ ሽማግሎችን የሚያታልሉ ሐሳውያን ነቢያት የጆሐባ ምስክሮች ተሸክመውት ከሚዞሩት መጽሐፍ ቅዱስ አንዱን ነጥብም አይቀበሉም። እንዴታ! ለሚል፡

መጀመሪያ ከእግዚአብሔር አብ እንጀምር፡ የሚታየውንና የማይታየውን፡ ሰማይንና ምድርን የፈጠረ አብን አያምኑትም። እንዴታ! እሱንማ እግዚአብሔር ብቻ እውነተኛ ይሁን ብለው ጽፈው የለ፡ ይባል ይሆናል፡ እግዚአብሔር እውነተኛ ይሁን አሉ እንጂ መቼ እግዚአብሔር እውነተኛ ነው አሉ? እንዲህ ያለ ነገር ካፋቸው መቼ ወጣ? በእንዱ አምላክ በእግዚአብሔር አብም አያምኑም፡ መጽሐፍ ቅዱስን ተሸክመው የሚዞሩም መጀመሪያ እንደ ምድራዊ መንግሥት ሠራዊቱን ጨርሰው፡ በኋላ ወልድንና መንፈስ ቅዱስን ከሱ ለይተው፡ እሱም የለ ሰማለት ያዘጋጁት ዕቅድ ነው። ይህ ባይሆን ኑሮ

እግዚአብሔር አብ የምወደው ልጄ ይህ ነው ስሙት እያለ፥ እየሮኸ፥ የለም ካንተ ይበልጥ እኛ እናውቃለን፥ ፍጡርህ እንጂ ልጅህ አይደለም ባላሉት ነበር። (ማቴ. 3:17፤ 12:18፤ 17:5፤ ማር. 1:11፤ 9:7፤ ሉቃ. 9:35፤) ማመን መቀበል ማለት ነው እሱም የሚናገረውን ማመን፥ የሚያዝዘውን መቀበል ነው፥ እነሱ ግን የሚመሰክረውንም አያምኑ፥ የሚያዝዘውንም አይቀበሉ። <u>የምወደው ልጄ ይህ ነው</u> ምስክርነት፥ <u>እሱን ስሙት</u> ትእዛዝ ነው፥ ከሁለቱ አንዱንም አይቀበሉትም። አትገደል ብሏልና የሀገር ጠላት ሲመጣ አንዘምትም ይላሉ፤ ለመብቷ ግን ዘምቶ ሀገሩን ከሚያስጠብቀው ጋራ እኩል ነን ሲሉ አያፍሩም። አትገደል አትዝመት ማለት አይደለም፥ መገደል ያለ ሕግ ጎረቤትን፥ ጓደኛን፥ ያለ በላይ ሥልጣን ያለ ትእዛዝ ያለ ፍርድ፥ በቅናት፥ በምቀኝነት በጥላቻ መገደል፥ ነፍስ ማጥፋት ነው፥ ይህ ባይሆን ኑሮ አትገደል ብሎ ካዘዘ በኋላ እስራኤልን በአካባቢያቸው ካሉት አሕዛብ ጋራ በመሪነት፥ በጀኔራልነት በለው እያለ ሲያዋጋ የኖረ እግዚአብሔር የዝንጀሮ ገመር፥ ራሱ ያፈርስ፥ ራሱ ይከምር እንዲሉ ሕግ ሲሠራ ሲያፈርስ ኑሯል ማለት ነው። እንደነሱ አባባል አትገደል ያለው አትዝመት ቢሆን ኑሮ፥ በኋላ ልጁ የእግዚአብሔርን ለእግዚአብሔር የቄሳርን ለቄሳር ብሎ ያጠናው ሥርዓተ ምድራዊ መንግሥት ይጥፋ ማለት ነበር። (ሉቃ. 20:25) በኦሪት ዘፀአት 20:13 አትገደል ያለው አምላክ በመሪነት እስራኤልን ሲያዋጋ እንደኖረ የሚከተሉትን ጥቅሶች ያነቧል፤ (ዘፍ. 17:8-16፤ ዘዳ. 25:17-19፤ ዘኁ. 21:10-15፤ 31-35፤ 23:1-10፤ 33:50-56፤ ዘዳ. 1:4-8፤ 19-45፤ 2:13-37፤ 3:1-7፤ 20:1፤ ኢያሱ፥ 8:1...፤ 10:8-11፤ 32፤ 6:1) ከዚህ በላይ የተጠቀሱትን ጥቅሶች እያወጡ መላልሶ አንቦ አትገደል አትዝመት እንዳልሆነ ይረዱል። ኢየሱስ ክርስቶስ ወልደ እግዚአብሔር ሕያውና ሕይወቱ መንፈስ ቅዱስ ደግሞ የእግዚአብሔር አብ እኩያ (ዕሩያን) በመለኮት እንደሆኑ ለማሰረዳት የሚከተለው መልስ ተሰጥቷል።

ይህ ሁሉ ምስክር እያለ የእግዚአብሔር አብን የእግዚአብሔር ወልድን የእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስን (ይህን በቦታው እናየዋለን) የሦስቱ ሥላሴን ምስክርነት አሽቀንጥረው ጥለው፥ ዐይንም የለኝ ጮፋና ነኝ፥ ጀሮም ዳባ ልበስ ብለው ሰውን ለማታለል ሲፈልጉ ራሳቸው ተታለው ይኖራሉ። በመለኮቱ እምቅድመ ዓለም ወእስከ ዓለም ከአብ እኩል እንደሆነ ዐይተናል፥ እነሱ የሚጠቅሷቸው ጥቅሶች ግን የተነገሩት ሥጋ ለብሶ፥ ሥጋ በመልበሱ፥

ንጉሥ፡ ነቢይ፡ ካህን፡ ሊቀ ካህናት፡ ሊቀ ሰማዕት፡ ሊቀ ሐዋርያት ያለኵትንና የተሰኘባቸውን ነው። እነሱንም ቢሆን ከርእሱና ከጎዳኑ ለይተው ለራሳቸው እንደሚመቻቸው አጣመው ነው የሚፈቷቸው።

ለሁሉም መጻሕፍት የሚሉትን ከነትርጉማቸው ከዚህ ቀጥለን ለአንባቢያን እናቀርባለን።

ሀ) ምሳ. 8:20-36፤ 20 እኔ በጽድቅ መንገድ እሄዳለሁ፡ በፍርድም ጎዳና መካከል

ለ) 21 ለሚወዱኝ ርስት አወርሳቸው ዘንድ፡ ቤተ መዛግብታቸውንም እሞላ ዘንድ፡

22 እግዚአብሔር የመንገዱ መጀመሪያ እደረገኝ በቀድሞ ሥራው መጀመሪያ፡

23 ከጥንቱ ከዘለዓለም ጀምሮ ተሾምሁ ምድር ከመፈጠርዋ አስቀድሞ፤ 24 ቀላያት ገና ሳይኖሩ እኔ ተወለድሁ፡ የውኃ ምንጮች ገና ሳይፈልቁ፡ 25 ተራሮች ገና ሳይመሠረቱ፡ ከኮረብቶች በፊት እኔ ተወለድሁ፤ 26፡ ምድሪቱን ሜዳውን ገና ሳይፈጥር የመጀመሪያውንም የዓለም አፈር። 27፡ ሰማዮችን በዘረጋ ጊዜ አብሬ ነበርሁ፡ በቀላያት ፊት ክበብን በደነገገ ጊዜ፡ ደመናትን ከላይ ባዘጋጀ ጊዜ፡ የቀላይን ምንጮች ባጸና ጊዜ፡ 28 ለባሕርም ዳርቻን በወሰነ ጊዜ ውኃ ከትእዛዙ እንዳያልፍ የምድርን መሠረት በመሠረተ ጊዜ፡ 29 በዚያ ጊዜ እኔ በእርሱ ዘንድ፡ ዋና ሠራተኛ ነበርሁ፡ በእየዕለቱም ደስ አሰኘው ነበርሁ፡ 30 ደስታዬም በምድር ተድላዬም በለው ልጆች ነበረ።

ይህ አንቀጽ የሚናገረው ስለ ጥበብ ነው፡ መጽሐፈ ምሳሌም የተጻፈው በመጀመሪያው ምዕራፍ ቁጥር አንድ እንደተጻፈው፡ በምሳሌ ጥበብንና ተግሣጽን ለማወቅ እንጂ ምስጢረ ሥላሴ ለማስተማር አይደለም። ይህንም ምዕራፍ ስምንትን ከመጀመሪያው እስከ መጨረሻው ብናነብ በደንብ ልንረዳ እንችላለን። አርዮስ ግን የተሰሳተው ቁጥር 22 ላይ የተጻፈውን (ቀናኒ) በጽርእ <u>ሜኤክትሲ</u> ብዙ ትርጉም ያለውን ቃል ፈጠረኝ ብሎ ተርጉሞ ያንንም ለእግዚአብሔር ወልድ ሰጥቶ ነው። ቀናኒን (ክቲዚን) ብዙ ተርጓሚዎች ይህ ቃል ግልጽ አይደለም ጭፍን ነው እያሉ የመሰላቸውን ይዘው ይሄዱና በኋላ በትርጓሜ ያቃኑታል።

አርዮስ በተከራከረበት ቋንቋ በጽርእ (ግሪክ) ከትዚን ስድስት ትርጉም አለው፡ ሀ) አደረገ፡ ለ) አበጀ፡ ሐ) ወለደ፡ መ) አከናወነ፡ ሠ) አዳበለ፡

አጓደኑ፡ ረ) ፈጠረ። ለምን ቢሉ ዝቅ ብሎ 24 ና 25 ቀላያት ገና ሳይኖሩ እኔ ተወለድሁ፡ የውኃ ምንጮች ገና ሳይፈልቁ፡ ተራሮች ገና ሳይመሠረቱ፡ ከኮረብቶች በፊት እኔ ተወለድሁ ይላልና፡ ቢፈጠር ኑሮ ወዲያው አንድ ገጽ ሳይዘል ለምን ተወለድሁ፡ ነበርሁ አሰ?
ከዚህም በላይ እግዚአብሔር አብ የምወደው ልጄ ይህ ነው እያለ እየመሰከረ ራሱም አባቴ ላከኝ እያለ እያስተማረ መንፈስ ቅዱስም በዚህ ተግባር እየመሰከረ፡ ሦስታችሁም ሥላሴ ልክ አይደላችሁም ማለት አምላክን ማስተባበል ነው።

12. የምስጢረ ሥላሴ መደምደሚያ

የምስጢረ ሥላሴ ትምህርት በዚህ አንቀጽ ይደመደማል። በአካል፡ በስም፡ በግብር፡ ሦስት በመለኮት፡ በባሕርይ በህልውና አንድ የሆነ፡ አንድ አምላክ ሥላሴ ተብሎ ይጠራል። በስም አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ ይባላሉ፤ በግብር፡ አብ ወላዲ አሥራጺ፡ ወልድ ተወላዲ፡ መንፈስ ቅዱስ ሠራጺ ይባላሉ። በአካል አንዱ ከሌላው አይደባለቁም ለእያንዳንዳቸውም ፍጹም ፍጹም አካል አላቸው። ወልድ፡ ሥጋ በመልበሱ ምንም ከተዋሕዶ በኋላ ልዩነት ባይኖረውም፡ ሰውም አምላክም ነው፡ ሥጋ ለብሶ ከአባቱ አስታረቀን፡ አማለደን፤ እንደ ሰውነቱ ያማልዳል፡ እንደ አምላክነቱ ይማለዳል። መንፈስ ቅዱስም ልክ እንደ አብና ወልድ አካላዊ መንፈስ ሲሆን ለሦስቱ ሥላሴም ጎይል ስለሆነ፡ አብ ወልድ ራሱ መንፈስ ቅዱስ በአንድነት የጀመሩትን ነገር ሁሉ ይፈጽማል፡ ያከናውናል፤ ስለዚህ ነው ከጰራቅሊጦስ ወዲህ የቤተ ክርስቲያን መሪ የሚባለው። ወልድ በሦስቱም ፈቃድ ሥጋ ሰብሶ ጥንተ አብሶን አጠፋ፡ ከትንሣኤ ይልቁንም ከርደተ ጰራቅሊጦስ ወዲህ በጎብረት እያንዳንዱን ኃጢአተኛ ያስታርቃሉ፡ ከአብ ጋራ ማለት ከመለኮታዊ ባሕርያቸው ጋራ።
ሥላሴ፡ አብ ሠራው፡ ወልድ አደረገው፡ መንፈስ ቅዱስ ፈጸመው የሚባለውን ሁሉ የሚያከናውኑት በጎብረት ነው። ለምሳሌ በመጀመሪያ እግዚአብሔር ሰማይና ምድርን ፈጠረ ዘፍ. በምዕራፍ አንድ ቁጥር አንድ በሁለተኛው፡ በሦስተኛው ደግሞ የእግዚአብሔርም መንፈስ በውኃ ላይ ሰፍ ነበር፡ እግዚአብሔርም ብርሃን ይሁን አለ ብርሃንም ሆነ ትላለች አሪት። በዚህም እግዚአብሔር አብን፡ ቃለ አብ እግዚአብሔር ወልድን፡ መንፈስ እግዚአብሔር እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስን መናገሯ ነው። ስለዚህ ፍጥረትን ሁሉ በፈጠረ ቁጥር እግዚአብሔር አለ ስትል በኋላ ዮሐንስ

ወንጌላዊ በመጀመሪያ ቃል ከእግዚአብሔር ነበረ ...ያለ እሱም የሆነ የለም ባለው ቃል ዓለም መፈጠሩን ያሳያል። (ዘፍ. 1:1-3፤ 7፤ 9፤ 11፤ 14፤ 20) ዓለምን ሲፈጥሩ ሦስት ሁነው (በአካል) ለአብርሃምም የይሥሐቅን መወለድ ተስፋ ሲሰጡ ሦስት ሁነው፥ በኋላም ከእመቤታችን የጌታን ትስብእት ለማመቻቸት ሦስት ሁነው፤ ለዚህም ቅድስት ድንግል ማርያምን አብ መርጧታል፥ ወዷታል፥ በኩር ልጁን ችላ እንድትፀንሰው አሸንቷታል፥ መንፈስ ቅዱስ ፈጽሞ ቀድሷታል፥ አንጽቷታል፤ ወልድ ደግሞ ከነፍሷ ነፍስ ከሥጋዋ ሥጋ ነሥቶ፥ ሥጋ ለብሶ ፍጹም እንደኛ ሰው ሁኗል። (ሉቃ. 1:26-38)

መጽ.ቅ. ቁጥር 115ን ካየህ በኋላ ይህን አንብ፤ ቅዱስ እግዚአብሔር አብ ዘሠምረ ኪያኪ፥ ወቅዱስ ወልድ ዋሕድ ዘጎደረ ውስተ ከርሥኪ ወቅዱስ መንፈስ ቅዱስ ጸራቅሊጦስ መንፈስ ቅዱስ ዘአጽንዐኪ አንቺን የወደደ እግዚአብሔር አብ ቅዱስ ነው፥ በግሕፀንሽ ያደረ ወልድ ዋሕድም ቅዱስ ነው፥ ያጸናሽ የጽድቅ መንፈስ ቅዱስም ቅዱስ ነው። (መ.ቅ. 214:24-26)

ያዕቆብ ዘሥሩግም፥ አእግዚኦ ኪያከ ይመስል በአርአያ ወበጸዳል ዘወለደከ ወፍጉው አንተ እምጎቤሁ ለአቡከ፥ ነቅዕ ዘእምነቅዕ ዘውሕዘ እምአርያም። ፈትል ነዊኅ ዘኢይትበተከ እም አብ ፈጣሬ ለግያት ወምድር፥ እምለግይ ወረድከ በፈቃድከ፥ ግሕፀነ ድንግል አግመሪከ፥ ንስቲት ወለት ወለቶሙ ለነዳያን ያረተከ፥ ገሊላዊት ሐቀፈተከ፥ ነፍሳ ቀደስከ፥ ወሥጋሃ አንጻሕከ፥ አጽናዕካ ወኢደንገጸት ብከ=አቤቱ የወለደህ በመልከና በብርሃን አንተን ይመስላል፤ አንተ ከአባትህ ዘንድ ተልከሃል፤ ከአርያም ከፈሰሰ ምንጭ የተገኘ ምንጭ፤ ከአብ የማይለይ፥ የማይቆረጥ ረጅም ፈትል፥ ሰማይና ምድርን የፈጠርህ በፈቃድህ ከሰማይ ወረድህ፥ የድንግል ማሕፀን ወሰነህ፤ የድኖች ልጅ ትንሽ ብሳቴና አቀፈችህ፤ ነፍሷን አከበርህ ሥጋዋንም አነጻህ፥ አጸናሃት በአንተም አልደነገጠችም። (መ.ቅ. 438:20-21) ሥላሴ በሥራ ይተባበራሉ፥ አንዱ ባለበት ሁሉም ይገኛሉ። (ዮሐ. 10:39፤ 14:23) አንዱ በሌለበት ሌላው የለም። (ዮሐ. 15:23)

ሥላሴ የሚል ቃል በቅዱሳት መጻሕፍት ስለሌለ ቃሉንም ሆነ ትርጉሙን አንቀበልም የሚሉ አርዮሳውያን ስላሉ፥ እግረ መንገዳችን የሥላሴን ቃል ከዚህ እንናገራለን።

ሥላሴ ሠለሰ ሦስት አደረገ ከሚለው የግዕዝ ግሥ የመጣ የግሪኩ ትርያስ ተነጻጻሪ (ተወዳዳሪ) ቃል ነው። እሱም ሦስትነት ግለት ነው። ቅዱሳት መጻሕፍት ለክርስቲያን የሕገ መንግሥት መጻሕፍት እንጂ የሕግ መጽሐፍ

እይደሉም። ሕገ መንግሥት የሚዘረዘረው በሕግ ነው። የሥላሴ ሦስትነትና አንድነት ከዚህ በላይ በተጠቀሱት መጻሕፍት በማያጠራጥር መንገድ ተገልጧል። መሰየሙ ግን ያስተዋይ ሊቅ ፈንታ ነው። የሰዋሰው ደራሲና ሳይንቲስት ግኝታቸውን እየሰየሙ እንዲሄዱ፥ ለምሳሌ የሰዋሰው ጸሓፊ ለማስረዳት እንዲመቸው፥ እንደቋንቋው ከስምንት አስከ ፀሥር የቋንቋውን ቃላት በወገን በወገን ስሎ ስም፥ ቅጽል፥ ተውላጠ ስም ወዘተ እያለ ያወጣል። እንደዚሁም ወላጅ ለልጁ ልጅ ለወላጁ ስም ያወጣል። የቤተ ክርስቲያን ሊቃውንትም ለማስተማር እንዲመች በሦስት አካላት፥ አስግት፥ ግብራት በአንድ ባሕርይ፥ ሥልጣን፥ ህላዌ፥ ፈቃድ ሲሠለስ ለሚኖር አምላክ ሥላሴ ብለው ሰይመዋል።

እንዱም ስለዚህ ነው ከፍ ብሎ አርዮሳውያን ቅዱሳት መጻሕፍትን ለማታለያ ይሸከሟቸዋል እንጂ አይረዱቸውም እይቀበሏቸውም የተባለው።

የቀረውን ደግሞ ከአርዮስ፥ ከመቅዶንዮስ፥ ከሁለት ባሕርይ እናመልጣለን ሲሉ፥ ሊቅነት ከሚያመጣው መናፍቅነት ሳይሆን፥ ሳያውቁት ድንቁርና ከማሰው ጉድጓድ የተዘፈቁ የኢትዮጵያ አርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን አባቶች ነን የሚሉ፥ ከመንበረ ፓትርያርኩ ለምእመናን የተዘጋጀ ትምህርት በሚል የበተኑ፤ የዚያን መልስ በሚደረገው ርእስ እናየዋለን።

ምዕራፍ 2

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ አግላጅም ተግላጅም ነው፥

ክርስቶስ· አላግለደም ለምን ተባለ?

በምስጢረ ሥላሴ እግዚአብሔር ወልድ ከአባቱ ከእግዚአብሔር አብና ከባሕርይ ሕይወቱ ከእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስም ጋራ እኩል ነው ከተባለ በኋላ አሁን ደግሞ በዘመናችን ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከአባቱ ጋራ አስታርቆናል አግልዶናል የሚሉ ሰዎች ስለተነሡ ቤተ ክርስቲያናችን ክርስቶስ ተግላጅ እንጂ አግላጅ አይደለም በሚል ንኡስ ርእስ፥ ተዐቀቡኬ እምሐሳውያን ነቢያት (ከሐሰተኞች መምህራን ተጠበቁ) በሚል ርእስ አ/አ ሐምሌ 4 ቀን 1986 ዓ.ም. አውጥታለች። እሱም ከኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን መንበረ ፓትርያርክ ሰምእመናን የተዘጋጀ ትምህርት ይላል። የዚች ቤተ ክርስቲያን አባል ነኝ የሚል ሁሉም ይህን ዐዋጅ መከተል አለበት ስሚል ይህ ምዕራፍ በጠቅላላው እንደመልስ ሁኖ ይቀርባል። እንዲያውም ለዚህ መጽሐፍ መደረስ ምክንያት የሆነው በቤተ ክርስቲያናችን ሳያውቁ፥ ሳይማሩ በስመ ካህን የሚነግዱትን አወናባጆች ለመገሠጽ ለማረም ነው ለማለት ይቻላል።

ክርስትና ወደ ኢትዮጵያ ከገባ ጀምሮ ብዙ ጊዜ ሲሸሙ ሲሸለሙ የኖሩ ሃይማኖቱን ያልተማሩ፥ ወይም ተምረው ሹማምቱን እያወደሱ ሊቃውንቱን የሚያስገድሉ፥ የሚያሳድዱ ሰዎች ነበሩ። በዘመናችን በቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ ላይ እንደተደረገው። ይህም በብዙ ጋዜጣዎች ስለወጣ፥ ግንም የሚያውቀው ሐቅ ነው። ለእንድ ሽህ ስድስት መቶ ዘመን ግብጻውያን ቋንቋውን በማያውቁት ሕዝብ መካከል በአስተርጓሚ ተሸፍነው፥ ሊቃውንቱን ሲገዝቱ፥ ያልተማረውን አገልጋያቸውን ሲሾሙ፥ ሲሸልሙ ኑረው አልፈዋል። ኢትዮጵያውያን ከተሾሙ፥ ወዲህም የቤተ ክርስቲያኗ መሪ ንጉሡ ስለነበሩና የንግግር ነጻነትም ባለመኖሩ ያም ዘመን፥ በሃይማኖት በኩል ምንም ውጤት ሳይሠራበት አልፏል። በዚህ ረጅም ዘመን በትውፊት ስም የተደፈደፈውን፥ እንደ ወንጌል ቃል የሚታየውን የባልቴት ተረት ለማንሣት ብንፍጨረጨር በቤተ ክርስቲያኒቱ ስም አስመሳዮች ግምታቸውን ሲነዙ፥ ተረታቸውን ሲሰብኩ ኑረዋል። አብዛኛው እንደ ወንጌል የሚቆጠረው የባልቴት ተረት የመጣበት አይታወቅም፤ የእንዳንዱ በክርስቶስ ሞት ያለፈው ሥርዓተ ረበናት ነው ምንጩ፥ የሌላው ደግሞ ቤት ሠርቶ ምሽት አግብቶ መኖር ያቃተው፥ ውስጡ ሰቄስ ይሁንና መናኝ ነኝ ባይ አታላይ፥ እንዲህ ብዬ ብሰብክ ሰው ቅዱስ ይለኛል፥ እቦ! እቦ! እባላለሁ እያለ ከልቡ አንቅቶ የሚያወራው መብለታቱ ተቀብለው የሚበትኑት

ከቅዱሳት መጻሕፍትም ሆነ ከአዋልድ የማይገኝ ነው። ሁሉንም በዚህ መጽሐፍ በቅደም ተከተል እስከናየው: በዘመናችን በቤተ ክርስቲያን የሚደረገውን ስሕተት (በመቅድሙ የተገለጠውን) አስቀድመን: ቀሪውን ደግሞ በቅደም ተከተል እንዘረዝራለን።

በቅድሚያ የዚህ መጽሐፍ ደራሲ ከ36 ዓ.ም. ጀምሮ እንዲሻሻሉ የታገለባቸው አርእስት፡

ሀ) የግኅበር ጽዋ እንደታዩት ይሰገድልታል: አይሰገድለትም፤

ለ) ለአልናከ እንደ ሥጋሁ ወደሙ ይቆጠራል? ለአልናከ ጸሎተ ግዕድ እንጂ ከዚያ አያልፍም። ጌታችንም: ሐዋርያትም ግዕድ ይባርኩ: ከግዕድ በኋላም ይዘምሩ ወይም ያመሰግኑ ነበር ይህም እንደዚያ እንጂ ሌላ አይደለም። (ማር. 14:26)

ሐ) ተአምረ ማርያምን ያዳመጠ እንደ ሥጋሁ ወደሙ ይቆጠርለታል፡ ነገሩ ግራ የሚያጋባ ነው፤ በአንድ በኩል ከቦታው እንደምናየው ብትቆርቡ ትከነናላችሁ: ሥጋው አሳት ሁኖ ይፈጃችኋል: ደሙ ባሕረ አሳት ሁኖ ያስጥማችኋል: እያሉ: ለውን ወደ መሐሪው እምላኩ እንዳይቀርብ ያደርጋሉ: በሌላው ደግሞ ማንኛቸውንም የቅዱስ ሥጋውና የክቡር ደሙ ተነጻጻሪ: እኩያ ያደርጋሉ።

መ) ጌታ በወንጌል የከለከለውን የወንፈል ምግብ በግኅበር ስም ይጸድቃል ይላሉ። በእግዚአብሔር ስምም ሆነ በወዳጆቹ ለነዳያን ለመስጠት ከሆነ ረድኤት ነው: ጥሩ በተቀረ ግን በሙሴ ዳኝነት ለወሩ ሊከፍል ዋስ ጠርቶ በልቶ ዋሱ እንዳይታገትበት በከፊለ እንዴት ነው የሚጸደቀው? (ሉቃ. 14:7-14)

በመቅድሙ እንደተገለጠው በ1954 ዓ.ም. ደግሞ ከሮማዊ ቀሲስ ዶክተር አባ አየለ ተክለ ሃይማኖት ዘዐቢይ: ዓዲ: የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን: ስለ ክርስቶስ ባሕርያት አካላዊ ተዋሕዶ የምታምነው ትምህርት ብለው ቢጽፉ: ከአሳቸው ትምህርት ለመራቅ ሲሉ: የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን: ከእስክንድርያ እናቴ: ከግርቆስ አባቴ ብላ በምታምነው ሃይማኖቷ መሠረት: ከጥንት ጀምራ እግዚአብሔር አብ የእግዚአብሔር ወልድ <u>በሥጋው የባህርይ</u> አባቱ ነው ብላ ታምናለች ብለው ለምእመናን ማስጠንቀቂያ በቤተ ክርስቲያኒቱ ስም በተኑ። በዚህም እንደኛ እምቅድመ ዓለም ከአብ ያለናት: ድኅረ ዓለም ከእመቤታችን ያለአባት: ወልደ አብ በመለኮቱ: ወልደ ማርያም በትስብእቱ የሚለው በመፍረሱ: አብና ማርያም በመጋባታቸውም የማርያም ድንግልና ፈረሰ: አታመንዝር ብሎ ያዘዘው የእግዚአብሔር

አብ ሕግም በራሱ በሠሪው በመጣሱ፡ ስብሐት ሎቱና ክርስቶስም አይሁድ እንዳሉት ሁሉ ዲቃላ፡ የአመንዝራ ልጅ በመሆኑ ብዙ ሊቃውንት ተቆረቆሩ፡ ተናደዱ። አንዳንዶችም ከሠርጉ ባለመጠራታቸው አዘኑ። ብዙዎች ሊቃነ ጳጳሳትም ልክ ነው ከተዋሕደ ምን ልዩነት አለበት ብለው መለሱ። በኋላ ግን ለብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ባስልዮስ ለቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ ለብፁዕ አቡነ ዮሐንስ ተነግሮ እነዚህ በዘመኑ የነበሩት ዋና ዋናዎቹ ስለደገፉኝ አንድ ሰው ነው የጻፈው ብለው ከቤተ ክህነት አስወጡና ነገሩ በረደ። የበረደውም ብዙ ክታባት እየተጻፉ ከተበተኑ በኋላ ነው። አላዋቂዎች ግን አሁንም ውስጥ ውስጡን እንዳሉ ይታመናል።

የዚያን ጊዜ ከተበተኑት እንጉርጉሮች አንዱና አንድ መወድስ ከዚህ ቀጥለው ተጽፈዋል፤

ከኢየሩሳሌም መጽሐፍ ቤት
መጡ ብለውኝ ሊቃውንት (ተናብልት)
የግርያምን ዜና ብጠይቅ
ታዝናለች አሉኝ በጥብቅ
በግብር ሳያውቃት ግንም ወንድ
በድንግልና ብትወልድ፡
ታስብ ነበረ በእውነት
የሥጋ አባቱ ጠፍታት
ነቢያት ሐዋርያት ሊቃውንት
ብዙ የጻፉ መጻሕፍት
ታሪኩን ነግረው በእየረድፉ
ሁሉን ዘርዝረው አለፉ
አባት በምድር የለውም
እንዲሁም እናት በአርያም
ይህን አመነ ዓለምም
ድንግል ናት ብሎ ዘለዓለም።
በድንግልናም ከሆነ
ድንግል ናት ብሎ ሁሉ አመነ።
ተግሮች መጡ ትላንትና
ከሁሪት ሀገር ድንቁርና
አረጋገጥነ ወሬውን
የሥጋ አባቱን አገኘን።

ወልደ አብ መሆኑን በትስብእቱ
ነገረን እሉን አባቱ።
ወሬውም ሁሉ ቀባጀረ
እንግዲህ እውነት ማመን ቀረ።
በጣም አዘነ ነደደው
ሠርግ የቀረበት ብዙ ሰው።

<u>መወድስ</u>

አንፍር አንሰ በጊዜ ተሠይሙ፡
መምህራነ አሚን አርድእት እንበለ ለፊደል እምረቱ
እስመ ኢያእምሮ ጥንቁቀ መሠረተ እበው ነሡቱ።
ወእንዘ ይጎይዩ ዐርከ አሚን
ርትዕተ ፍናተ እበው ሃይማኖተ ሰሕቱ።
አመ ይክዱ በትስብእቱ
ወልደ ማርያም ድንግል ወወልደ አብ በመለኮቱ።
ይቤሎሙሂ መጽሐፎሙ ለእመ ሐተቱ
ወልድ ለእመ ኮነ ወልደ አብ በትስብእቱ
ትምህርተ አበው ተሰዕረ ድንግለ ፍናው ክልኤቱ
እምጣነ ማርያም መርዓተ አብ ወለወልድ ወላዲቱ።

<u>ስለቁርባን</u>

በዝርዝሩ ከቦታው ከዚህ በፊት ተጽፎ የተበተነውን እናቀርባለን። ከዚህ ግን ምቀኝነት ይሉ ጥመት ወይንም ንፍገት በምን ምክንያት እንደሆነ አይታወቅም፡ ከማንም መጽሐፍ ሳያገኙ ከሥርዓተ ቅዳሴ ለጥፈው፡ ብትቆርቡ ትከነናላችሁ እያሉ ሕዝቡን እያሳርሩ፡ ባለማቁረባቸው ሕዝቡን ገሃነም እንዲወርድ በማድረጋቸው ዲያቢሎስን ሲረዱ መኖራቸውን እንገልጣለን።
ከአለፈው አረሚ መንግሥት ጋራ በሥርዓተ አሕዛብ ተስማምተው፡ ተመሳጥረው ፓትርያርካቸውን አስገደሉ። ይህ አንሷቸው በቀን የፈለጉትን ያህል ታቦት መባረክ ሲችሉ፡ የቅዱስ ራጉኤልን ታቦት መርካቶ እንሰርቃለን ብለው ሕዝቡ ቢነቃባቸው ሰው አስገድለው አመለጡ።
ስለዚህም ከተበተኑት ብዙ መወድሶች አንዱ ከዚህ ቀጥሎ ተጽፏል፤

<u>መወድስ</u>

እሙነ ኮነ ምላሌ አበው
እንተ ለመደ ልመድ ያስርቅ ማዕዳተ
ለጠይቆ ዝ ንነጽር ኤጲስቆጶሳተ

ሊቃነ ጳጳሳት ቅዱሳነ
ታቦተ እለ ይባርኩ ሰረቁ ታቦተ
እንበለ ይክህሉ አንብቦተ
ዘህለምሙ መጽሐፈ ይቀስጡ መጻሕፍተ
በክብርሂ ድኅረ ተሠይሙ ዘቤተ ክርስቲያን ዐቀብተ
ይሠይጡ ቀሚጠሙ ንዋያተ ቅዱሳተ
ወከመ ብእሲ ኀጥአ ዐስበ ዕለታዊ ሲሲተ
በነሢአ ወርቅ ይሠይጡ ጥምቀተ ወክህንተ
ከመ ስመ እምላክ ነገዱ ለረኪበ ንዋይ ሚመተ
በንሢአ ወርቅ ይሠይጡ ክህንተ ወጥምቀተ።
በዚህም ብናጠፉ ለምን ታርሙናላችሁ ስንሰርቅስ ዐይታችሁ ለምን ዐየናችሁ ትላላችሁ ብለው ሰው አሳስረዋል። ይህ ሁሉ ሁኖም ቀጭና ገሣጭ ስለሌለባቸው፥ ዛሬ ግተሚያ ቤቱ በበዛበት ቅዱሳት መጻሕፍት በእየቤቱ በተዳረሱበት ዘመን እንደ ቀድሞው እንደብራናው ዘመን መሰሏቸው፥ መጻሕፍቱን የት አግኝቶ ያነባቸዋል ብለው ከአተቱት ሐተታ ጋራ የግይስግሙ ጥቅሶች ደርድረው፥ ክርስቶስ ተግላጅ እንጂ አግላጅ አይደለም አሉና ዐረፏ! ዐረፉ። እንዲህ ነው የግን አለብኝ ቤት! ክርስቶስ አያግልድም፥ አያስታርቅም፥ ከአባቱ ከአብ ተልኮ ወደዚህ ዓለም መጥቶ ተገር፥ ተገርፎ፥ ተሰቅሎ ሙቶ አላዳነንም የሚሉ በአግርኛ አፋቸውን ያልፈቱ፥ የፈቱ እንዳሉም ሹመት ይቀርብኛል፥ የበላይ ተግሣጽ ይደርስብኛል፥ ደመወዝ ይቀነስብኛል ብለው የሠጉ የፈሩ ለምች መሆን አለባቸው።

የግስታረቅና የግግለድ መግለጫ

ግስታረቅና ግግለድ ከሁለት ተጣዮች መሃል ገብቶ በመገላገል ሁለቱም አንድ ናቸው። የሚለያዩት ግን በግስታረቅ ሦስቱም ሰዎች እኩል ሲሆኑ፥ በግግለድ ግን አግልጹኝ ባዩ ያንሳል። ለምሳሌም አቶ ሰና አቶ መ ተጣሉ እንበል፥ ይህን የሰግ አቶ ሀ አንተም ተው አንተም ተው ብሎ ያስታርቃል፤ ሦስቱም በግዕረግም ይሁን በዕድሜ እኩል ናቸው። በግግለድ ደግሞ አግላጅና ተግላጅ አሁንም እኩል ናቸው። ከዚህም አግላጅና ተግላጅ አብና ወልድ እኩል ናቸው፥ የሚያንሰው አግላጅ ፈላጊው አዳም ነው፤ አዳም ንስሓ ገባ፥ ተጠጠተ ፈጣሪውን በመበደሉ አዘነ፥ ወልደ እግዚአብሔር ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በተለየ አካሉ ከሰግየ ሰግያት ወርዶ፥ ሥጋ ለብሶ በመለኮቱ እኩያው ከሚሆን ከባሕርይ አባቱና ከራሱ ከመንፈስ ቅዱስም ሕይወቱ አግልዶ፥

ሰምና፥ ጸልዮ ራሱን ሠውቶ አስታርቆታል። በመሰቀሉ አዳም የሠራውን ጥንተ አብሶ አስወግዷል፤ ከዚያ በኋላ ደግሞ በአባቱ ቀኝ ቁሞ የሰው ልጅ እያንዳንዱ በሚሠራው በደል ሲያግልድ፥ ሲከራከር ይኖራል።

ላከውም አግለደም፥ አስታረቀም ቢባል ከአባቱ በመለኮቱ በምንም አያንስም። ለዚህም የባህላችንን ምሳሌ እንመልከት፤ በቀድሞ ሥርዓት ሴት ልጅ የፈለገ ሰው ነገሩ እንዲከብድለት ደጃዝማች ወደ ደጃዝማች ወይም ፊታውራሪ ይልካል፤ ደጃዝማችም ሂደው ይለምናሉ፤ በዚህም የለማኙ ያግላጁ የደጃዝማች ማዕረግ ከሚሾሙት ከፊታውራሪ አያንስም። ማስታረቅም ግግለድም ክብር አይቀንስም፥ ማዕረግ አያዋርድም።

የጌታችንን የክርስቶስን አግላጅነት ለመካድ የተበተነ ክታብ

ከዚህ በላይ በተጠቀሰው ክታብ ክርስቶስ ተግላጅ እንጂ አግላጅ አይደለም ብለው ለማስረዳ ያቀረቡትን አንቀጽ ከዚህ በታች ጽፈን ለአንባቢ እናቀርባለን።

በቅዱሳት መጻሕፍት ስለጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የተጻፈው ሁሉ የማስታረቅን እንጂ የግግለድን ተግባር አያመለክትም። ጌታ ከፅንስ እስከ ትንሣኤው ድረስ በቃልም በግብርም የፈጸመው ሁሉ የማስታረቅ ተግባር ነው።

ምልጃ የሚል ቃል ለጌታ አይነገርም፤ ማስታረቁም ቢሆን እስከ መሰቀል ድረስ ብቻ ነው። በመሰቀሉ ዕርቅ ስለተፈጸመ ከመሰቀሉና ከትንሣኤው በኋላ ለእያንዳንዱ እንደ ሥራው ፍርድ ይሰጠዋል፥ ዋጋ ይከፍላል እንጂ የማስታረቅ ሥራ አይኖርም። መናፍቃኑ ለተነሣሡበት የማሳሳት ትምህርት ይረዳናል ብለው (1ጢሞ. 2:5፤ 1ጴ. 2:1፤ ማቴ. 11:28፤ ዮሐ. 7:37) የደረደሯቸው ጥቅሶች በእየመልኩ ሲተረጎሙ በ1 ጢሞ. 2:5 የተጠቀሰው በእግዚአብሔርና በሰው መካከል የፈጸመውን የአስታራቂነት ሥራ እንጂ አግላጅነትን አይደለም። ግግለድና ማስታረቅ የተለያዩ ናቸው።

ይህ አንቀጽ በግን አለብኝና በግደየለሽእነት የተሠራ ለመሆኑ (ማሰቡና መግሩስ ይቅርና) የሚከተሉት ምክንያቶች ተሰጠዋል። አንደኛ የታተተው ሐተታ እንኳን ከቅዱሳት መጻሕፍትና ከአዋልድም መረጃ የለውም። ሁለተኛ የተጠቀሱት ጥቅሶች ጠቀሱ ለመባል የተደረደሩ እንጂ ከአንቀጹ ጋራ ዝምድና የላቸውም። መቼም አንባቢ መጠቀሱን እንጂ መጽሐፍ ቅዱስ አውጥቶ አያይም ተብሎ የተደረደሩ

ናቸው፤ ስለዚህ አንባቢ እንዲያገናዝባቸው ጥቅሶቹ ከዚህ በታች ተጽፈዋል፤

ሀ) 1ጢሞ. 2:5፥ ደግሞም በጭቁታ የሚታገል ግንም ቢሆን፥ እንደሚገባ አድርጎ ባይታገል የድሉን አክሊል አያገኝም።

ለ) 1ጴ. 2:1፥ ስሁንም ክፉ ነገርን ሁሉ ጣሉ፤ ተንኮልንም ሁሉ፥ ግብዝነትንም፥ ቅንዓትንም፥ ሐሜትንም ሁሉ።

ሐ) ማቴ. 11:28፥ እናንተ ደካሞች ሸክማችሁ የከበዳችሁና የተጫናችሁ ሁሉ ወደ እኔ ኑ፡ እኔም አሳርፋችኋለሁ። ዮሐ. 7:37፤ በበዓሉም በመጨረሻው ታላቁ ቀን ኢየሱስ ቁሞ ግንም ቢጠማ ወደኔ መጥቶ ይጠጣ ብሎ ጮኸ።

ፍየል ወደያ ቅንዝምዝም ወዲህ፤ ላም ባልዋለበት ኩበት ለቀማ ሆነ ነገሩ ሁሉ። አሁን የትኛው መናፍቅ ነው ይህን ለማማለድና ለማስታረቅ ማስረጃ ይሆነኛል ብሎ የሚጠቅስ? የእሱስ ጓደኛ ሕፃን አእምሮ ካልሆነ በቀር። አንደኛውንና ሁለተኛውን አናቅጽ ካየን ሦስተኛውንና አራተኛውን ደግሞ እናስከትል።

በ 1ዮሐ. 2:1፥ በመናፍቃኑ ትርጉም ጠበቃ (አግላጅ) አለ? የሚለው ከቃሉ ውጭ የተተረጎመ ነው፤ ቃሉ የሚለው ወእመኒቦ ዘአበሰ ጸራቅሊጦስ ብነ ኀበ አብ ኢየሱስ ክርስቶስ..."ነው ይህም ሲተረጎም ልጆቼ ሆይ እንዳትበድሉ ይህን እጽፍላችኋለሁ፥ የበደለም ቢኖር ጸራቅሊጦስ ከአባት ኢየሱስ ክርስቶስ ዘንድ አለን። ኃጢአታችን ያስተሰርይልን ዘንድ ቸር ነው" ግለት ነው።

አቤት ድፍረትና ስሕተት! ይህስ ሀገር አስጥሎ ያስመንናል። አቤት መዝረጥረጥ! አለመጻፋቸው ጥሩ፥ ብዙ ቢጽፉ ምን ያደርጉ ነበር ይሆን? ያንተ ያለህ አውጣኝ!

ከዚህ በላይ የጠቀሱት አጣመው እንደ ጻፉትና አወላግደው እንደተረጎሙት ሳይሆን በግሪክም ሆነ በግዕዝ የተጻፈው እንደሚከተለው ነው፤

ደቂቅየ ዘንተ እጽሕፍ ለክሙ ከመ ኢተአብሱ፥ ወእመኒቦ ዘአበሰ ጸራቅሊጦስ ብነ ኀበ አብ ኢየሱስ ክርስቶስ ጻድቅ ወውእቱ መስተሰርየ ኃጣውኢነ። (ልጆቼ ሆይ ኀጢአትን እንዳትሠሩ ይህን እጽፍላችኋለሁ፤ ከአብ ዘንድ አግላጅ (ጠበቃ) ጻድቅ ኢየሱስ ክርስቶስ አለን) ነው። እሱም የኃጢአታችን ማስተሰርያ ነው። ማቴ. 11:28ንም ወደኔ ኑ ለማለት ጥሪ እንጂ ለአግላጅነት የሚጠቅሰው ስለሌለ ይህም የጤነኛ ጥቅስ ስለማይመስል ለአንባቢ ትዝብት ትተነው እናልፋለን።

ዮሐ. 6:37ም ስለ ሥጋውና ደሙ የተነገረ እንጂ ስለአግላጅ

የጠቀሰውም ሆነ የሚጠቅሰው ሰው ስለሌለ አሁንም የኛ ሊቃውንትንም ሆነ አባቶች ከዐይን ያድናችሁ ብሎ ከግለፍ በቀር ምን ይደረጋል? ዛሬ ምእመናኑ መጻሕፍትን በእየቤታቸው ይዘው እያነበቡ በተራቀቁበት ጊዜ ያልተግራችሁ መቼ ይሆን የምትግሩ?

<u>የክርስቶስ አግላጅነት ምስክር፤</u>

ለዚህ ርእስ መግቢያ እስከዚህ የተናገርነው ይብቃንና የእነሱንም የባልቴት ተረት ትተን፡ ስለ ክርስቶስ አዳኝነት፡ አስታራቂነት፡ ለደቂቀ አዳም ጠበቃነት፡ አግላጅነት፡ ጸላይነት በለበለው ሥጋ ከአባቱና ከኛ መካከል ሁኖ ዘለዓለም ተከራካሪነት፡ አብ፡ አባቱ፡ ራሱ፡ መንፈስ ቅዱስ ሕይወቱ፡ ነቢያት፡ ሐዋርያት፡ ሊቃውንት፡ መጻሕፍት የሚሉትን እንስማ፡ እንይ፡ እንግር።

<u>እግዚአብሔር አብ አባቱ፡</u> እኔ ግን ንጉሤን ሾምሁ፡ በተቀደሰው ተራራዬ በጽዮን ላይ። ትእዛዙን እናገራለሁ፡ እግዚአብሔር አለኝ፡ አንተ ልጄ ነህ፡ እኔም ዛሬ ወለድሁህ፣ ለምነኝ አሕዛብን ለርስትህ የምድርንም ዳርቻ ለግዛትህ እሰጥሃለሁ። (መዝ. 2:6-8)።
እንደ መልከ ጸዴቅ ሥርዓት አንተ ለዘለዓለም ካህን ነህ ብሎ እግዚአብሔር ማለ አይጸጸትምም። (መዝ. 109:4፡) እንዲሁ ክርስቶስ ደግሞ ሊቀካህናት ሊሆን ራሱን አላከበረም ነገር ግን አንተ ልጄ ነህ፡ እኔ ዛሬ ወለድሁህ፡ ያለው እርሱ ነው፡ እንዲሁም በሌላ ስፍራ ደግሞ፡ አንተ እንደ መልከጼዴቅ ሹመት ለዘለዓለም ካህን ነህ ይላል። እስከዚህ እግዚአብሔር አብ የተናገረው ነው፡ ከዚህ አያይዞ ደግሞ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ እንዲህ ብሏል፣ እርሱም በሥጋው ወራት ከሞት ሊያድነው ወደሚችል ከብርቱ ጩኸትና ከእንባ ጋራ ጸሎትና ምልጃን አቀረበ፣ እግዚአብሔርም ስለመፍራቱ ሰማለት። (ዕብ. 5:5) ታዲያስ የእኛ ሊቃውንት የሊቀ ካህናት ሥራ ምን ይሆን?

<u>ራሱ ወልደ እግዚአብሔር ኢየሱስ ክርስቶስ፡</u>

ብትወዱኝ ትእዛዜን ጠብቁ፡ እኔም አብን እለምናለሁ ለዘለዓለም ከእናንተ ጋራ እንዲኖር ሌላ አግላጅ (አጽናኝ) ይሰጣችኋል። (ዮሐ. 14:15-16) የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ አግላጅነት፡ ስለ ሰው ልጅ ጸላይነት፡ ከአብ ስለመላኩ ራሱ የተናገረውን ለመረዳት የዮሐንስ ወንጌልን ም.17ን በሙሉ መላለሶ ያነቧል።

ስለካማ ያግልዳል፥ ይጸልያል፥ ጸልዮአልም፤
ሰምያን ሆይ! እነሆ ሰይጣን እንደ ስንዴ ሊያበጥራችሁ ለመነ፤ እኔ ግን እምነትህ እንዳይጠፋ ስለእንተ አግለድሁ አንተም በተመለስህ ጊዜ ወድሞችህን አጽና አለ። (ሉቃ. 22:32)
ለጠላቶቹም ያግልዳል፤
ኢየሱስም አባት ሆይ! የሚያደርጉትን አያውቁምና ይቅር በላቸው አለ፤ (ሉቃ. 23:34)
ለመንፈስ ቅዱስ መላክም ይለምናል ያግልዳል፤ ብትወዱኝ ትእዛዜን ጠብቁ፥ እኔም አብን እለምነዋለሁ ከእናንተ ጋራ ለዘለዓለም ይኖር ዘንድ ሌላ አግላጅ (አጽናኝ) ይሰጣችኋል። (ዮሐ. 14:15-16)
ለቤተ ክርስቲያንም ይጸልያል፥ ያግልዳል፤ (እኔ ስለነዚህ እለምናለሁ፥ ስለዓለም አለምንም፥ ስለሰጠኸኝ እንጂ የአንተ ናቸውና...። ዮሐ. 17:9)
ነቢያት፥ ከነፍሱ ብርሃን ያያል ደስም ይለዋል፤ ጻድቅ ባሪያዬም በዕውቀቱ ብዙ ሰዎችን ያጸድቃል፥ ኃጢአታቸውንም ይሸከማል። ስለዚህም እርሱ ብዙዎችን ይወርሳል፥ ከኀያላንም ጋራ ምርኮን ይከፋፈላል፥ ነፍሱን ለሞት አሳልፎ ሰጥቷልና፥ ከዐመፀኞችም ጋራ ተቆራኝቷልና፥ እሱ ግን የብዙ ሰዎችን ኃጢአት ተሸክሞ፥ ስለዐመፀኞችም ማለደ (ኢሳ. 53:11-12)
ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ፥

ሀ) ጠላቶቹ ሳለን ከእግዚአብሔር ጋራ በልጁ ሞት ከተራረቅን፥ ይልቁንም ከተራረቅን በኋላ በልጁ ሞት እንድናለን፤ ይህም ብቻ አይደለም፥ አሁን መታረቁን ባገኘንበት በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል በእግዚአብሔር ደግሞ እንመካለን።
ይህ ቁጥር እንዲህ እንበለው በግስትና በምስል አፍሳሽ ተበላሽቶ ነው እንጂ የግሪኩ ቀጥተኛ በግዕዝ ትርጉም እንደዚህ ነው፥
መሰበ እንዘ ፀሩ ንሕነ ተዐረቅነ ምስለ እግዚአብሔር በሞተ ወልዱ፥ እፎ እንከ እምከመ ተዐረቅነ ፈድፋደ ነሐዩ በሕይወተ ወልዱ። አኮ በእንተ ዝንቱ በሕቲቱ ዓዲ ንትሜካሕ በእግዚአብሔር በእንተ እግዚእነ ኢየሱስ ክርስቶስ ዘበእንቲአሁ ረከብነ ዕርቀነ። (ሮሜ 5:9-10) ቁጥር. 9 በመጀመሪያ እንዲህ ነበረ የተተረጎመው፤ (መሰበ እንዘ ፀሩ ንሕነ ተሣህልነ ምስለ እግዚአብሔር በሞተ ወልዱ፥ እፎ እንከ እምከመ ተሣህልነ ፈድፋደ ነሐዩ በሕይወተ ወልዱ)
ለ) እግዚአብሔር የመረጣቸውን ማን ይከሳቸዋል? የሚያጸድቅ እግዚአብሔር ነው፥ የሚኮንንስ ማነው? የሞተው ይልቁንም

ከሙታን የተነሣው፥ በእግዚአብሔር ቀኝ ያለው ስለኛ የሚማልደው ክርስቶስ ኢየሱስ ነው፤ (ሮሜ 8:34) ከሞተ በኋላ አያማልድም የሚሉትን የባልቴት ተረት ይህ የቅዱስ ጳውሎስ አነጋገር ብትንትንን ያወጣዋል። ምክንያቱስ ቢሉ በመንፈስ ቅዱስ አየተቃኘ የሚጽፈው ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ በእግዚአብሔር ቀኝ ያለው ስለኛ የሚማልደው ኢየሱስ ክርስቶስ ነው ብሎ የዘለዓለም አማላጅ መሆኑን አስተምሯል፥ ገልጧል፥ ጽፏል። መቼ በዚህ ብቻ ይበቃና! ገና ይቀጥላል እንጂ።

ሐ) ወውእቱሰ ይነብር ለዓለም አስሙ ኢያስዐር ክህነቱ ወይክል እድጎኖቱሙ ለዝሉፉ ለእለ ይቀርቡ ጎበ እግዚአብሔር እንተ መንገሌሁ እስመ ለግሙራ ሕያው ውእቱ ወይተነብል ሎሙ። (ዕብ. 7:25)=እሱ ግን ለዘለዓለም የሚኖር ስለሆነ የማይለወጥ የማይሻር ክህነት አለው፥ ስለእነሱም ለማማለድ በሕይወት ይኖራል፤ ስለዚህ ደግሞ በእርሱ ወደ እግዚአብሔር የሚመጡትን ፈጽሞ ሊያድናቸው ይችላል። ክርስቶስ በእጅ ወደ ተሠራች የእውነተኛይቱ ምሳሌ ወደምትሆን ቅድስት አልገባምና፥ ነገር ግን በእግዚአብሔር ፊት ስለኛ አሁን ይታይ ዘንድ (ይከራከር፥ ያማልድ ዘንድ) ወደ አሷ ወደ ሰማይ ገባ። (ዕብ. 9:15)

መ) የሚኮንንስ ማን ነው? ስለኛ የሚማልደው ኢየሱስ ክርስቶስ ነው፤ ሮሜ 8:34)

ሠ) ስለእነሱ ሊያማልድ በሕይወት ስለለዓለም ይኖራልና፤ (ዕብ. 7:25)

ሀ) <u>ሊቃውንት</u>፥ አበው አባቶቻችን በመጽሐፉ ቅዳሴ እንደገለጡት ወናሁ ደመ መሲሕክ ንጹሕ ዘተክዕወ በእንቲያየ በቀራንዮ ይኬልህ ሀየንቴየ (እነሆ በቀራንዮ የፈሰሰው ንጹሕ የልጅህ ደም ስለኔ ይጮኽል) (መ.ቅ. ገ.134፥ ቁ. 104- 5)።

ለ) <u>አባ ሕርያቆስም</u>፥ እንቃዕደወ ሰማየ ጎበ አቡሁ ወአስተምሐረ ወለዲሁ ወአግሕፀነ አርዳኢሁ ከመ ይዕቀቦሙ እምኩሉ እኩይ። (መ.ቅ.ገ.229:103)

ወደ ሰማይ ወደ አባቱ ቀና ብሎ አየ፥ የወለደውንም ግለደ፥ ደቀ መዛሙርቱንም ከክፉ ሁሉ ይጠብቃቸው ዘንድ አደራ አለ።

ሐ) <u>ቅዱስ አትናቴዎስም</u>፥በል አባ! ወአቡየ! መሐር ወተሣህል እለ በልዑ ሥጋየ ወእለ ስትዩ ደምየ (መ.ቅ.ገ. 304: ቁ. 142) አባ አባቴ ሆይ ሥጋዬን የበሉትን፥ ደሜንም የጠጡትን ማራቸው ይቅር በላቸው በል ብሏል።

ሙ) <u>ቅዱስ ባስልዮስም፥</u>
ወበእንተ ዝንቱ መድኀኒነ ይኬልሕ እንዘ ይብል እስመ ሥጋየኒ መብልዐ ጽድቅ ዘበእማንን ወደምየኒ ስቴ ሕይወት ዘበአማንን...(መ.ቅ.ገ.338 ቁ. 119) ስለዚህ መድኀኒታችን ሥጋዬ እውነተኛ የጽድቅ መብል ደሜም እውነተኛ የሕይወት መጠጥ ነውና እያለ፥ ይመሸል።

ሙ) <u>ቅዱስ ዮሐንስ አፈ ወርቅም</u>I
አንቃዕደወ ሰማየ ጎቤከ ጎበ አበሁ እግዚአብሔር ወእግዚእ ኩሉ ዘመልዕልተ ኩሉI (መ. ቅ.ገ. 398 ቁ. 40) የሁሉ በላይና የሁሉ ጌታ ወደ ምትሆን እግዚአብሔር ወደ አንተ ወደ አባቱ እንጋጦ አየ።

ረ) <u>ቅዱስ ዲዮስቆሮስም፥</u>
አንቃዕደወዕ ሰማየ ጎቤከ ጎበ አቡሁ=ወደልንተ ወደ አባቱ አንጋጦ አየ፥ አይቶ ባረከ ፈተተ ብሏልI (መ.ቅ.ገ.460: ቁ.29) አይጣል፥ ይህስ በጣም እጅግ ይገርማል ቅዳሴ የተጻፈው በግዕዝም በአግርኛም ነው። እንዴት ከሁለት አንዱ ላይገባቸው ቀድሰው ያቆርባሉ? እንጃ! ምን አልባት የአይሁድ ተከታዮች ናቸውና ነቢዩ ኢሳያስ ያለው ደርሶባቸው እንዳይሆንI እሱም፥ ሂድ፥ ይህን ሕዝብ መስማትን ትሰማላችሁ፥ አታስተዉሉም ማየትም ታያላችሁ አትመለከቱም በላቸው። በዐይናቸው እንዳያዩ፥ በጆርአቸውም እንዳይሰሙ፥ በልባቸውም እንዳያስተውሉ፥ ተመልሰውም እንዳይፈወሱ፥ የዚህን ሕዝብ ልብ አደንድን፥ ጆሮአቸውንም አደንቁር ዐይናቸውንም ጨፍን አለኝ። (ኢሳ. 6:9-10) ለእነሱም የእግዚአብሔር ምሳሌ የሆነ የክርስቶስ የክብሩ ወንጌል ብርሃን እንዳያበራላቸው፥ የዚህ ዓለም አምላክ የማያምኑትን አሳብ አሰወረ። (2 ቆሮ. 4:4) በእውነቱ በእነዚህ ጥቅሶች የተነገረው ደርሶባቸው ነው እንጂ በቃላቸው በአግርኛና በግዕዝ አጥንተው የሚያንበለብሉት ቅዳሴ እንዴት አይገባቸውም ወይስ አይረዳቸውም ለማለት ይቻላል። ከዚህ ላይስ አቤቱ አባት ሆይ! የሚሠሩትን አያውቁምና ይቅር በላቸው ብለህ ለጠላቶችህ ለአይሁድ የጸለይህ ጌታ ለእነዚህ ካህናትም ግለጥ ብሎ መጸለይ ይገባል።
አስተዋይ ባለቅኔና መሃይምንም እንዲህ ብለዋልI
በዘበልዐት ሔዋን እንጸዋ ሕማም፥
ተቀጥቅጠ ኢየሱስ ገዳም=(የሕማም አይጥ ሔዋን በበላች ኢየሱስ ዳዋ ተመታ)።

አዳም በበደለ መድኀኔ ዓለም ከሦ
ቁጿል ቀራንዮ ከለሚዳ ለብሶ
ግዕዝና አማርኛ ከገባችሁ ይህስ ምን ማለት ነው።
ለዚህ አንቀጽ መደምደሚያ፡ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ፡
እግዚአብሔር ሕያው ወልደ ማርያም ሥጋው፡ ሰውን ለማዳን
ለብሶ፡ ሥጋ በመልበሱ ሰው በመሆኑ፡ ለማኝም፡ አስታ
ታራቂም፡ አማላጅም፡ ተማላጂም ነው። በዚህም በመለኮቱ በሥ
ከአብ ከባሕርይ አባቱ፡ ከመንፈስ ቅዱስ ከባሕርይ ሕይወቱ አያ
በባሕርይ ዕሩያን ናቸውና። በአለፈው ዘመን በእኛ ሀገር ሥ
ማኅበር፡ ያፍ ዕውቀት ለሹመት፡ የእጅ ዕውቀት ለውርደት አ
እየተተረተ የእጅ ሠራተኛና ዐዋቂ ይዋረድበት እንደነበረ
በቀር መሥራትም ከማረግ አያዋርድም ከክብርም ዝቅ አያደርግ
እንደ አምላክነቱ ይግለጻል፡ እንደ ሰውነቱ ይግልጻል፡ ይለም
ወደ አብ ወደ አባቱም ይጸልያል፡ ጸልዮግል፡ በጥንተ አብሶ ከ
የመጣውን ኃጢአታችን በመስቀሉ ደምሷል። ለእያንዳንዳችን
አሁንም ይከራከራል።

ምዕራፍ 3

ጎሩይ ማእከለ እግዚአብሔር ወሰብእ=ክሰውና ከእግዚአብሔር መካከል

ይህ ቃል በግዕዝ ጎሩይ ውሉድ (ጠብቆ) በግሩክ ሚሲቲስ በእንግሊዝ mediator ይባላል፥ መካከለኛ ግለት ነው። በለበሰው ሥጋ ከእግዚአብሔርና ከፍጡር ሁሉ መካከል ሁኖ ሲያስታርቅ፥ ሲያግልድ፥ የአግላጆች አለቃም ከባሕርይ ሕይወቱ ከመንፈስ ቅዱስ በቀር ሁኖ የሚኖር ጌታችንI መድኀኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። ሰዚህም እንደገና በመዝሙር 2:6 የተነገረውን የእግዚአብሔር አብ ቃል፥ ለምነኝ አሕዛብን ለርስትህ፥ የምድርንም ዳርቻ ለግዛትህ አሰጥሃለሁን እንጠቅሳለን።

ዳንኤል፥ በሌሊት ራእይ አየሁI እነሆም፥ የሰው ልጅ የሚመስል ከሰማይ ደመናት ጋራ መጣ በዘመናት ወደ ሸመገለውም ደረሰ፥ ወደፊቱም አቀረቡት። ወገናችና አሕዛቡም በልዩ ልዩ ቋንቋም የሚናገሩ ሁሉ ይገዙለት ዘንድ፥ ግዛትና ክብር መንግሥትም ተሰጠው። ግዛቱም የማያልፍ የዘለዓለም ግዛት ነው፥ መንግሥቱም የማይጠፋ ነው። (ዳን. 7:13-14)

ራሱ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ፥

ኢየሱስም እኔ መንገድና እውነት ሕይወትም ነኝ፥ በእኔ በኩል በቀር ወደ አብ የሚመጣ የለም አለው። (ዮሐ 14:6)

ቅዱስ ጳውሎስ፥ አሐዱ እግዚአብሔር ወአሐዱ ጎሩይ ማእከለ እግዚአብሔር ወሰብእ፥ ኢየሱስ ክርስቶስ ዘከነ ሰብእ ወመጠወ ርእሶ ቤዛ ኩሉ። (1ጢሞ. 2:5) አንድ እግዚአብሔር አሰና፥ በእግዚአብሔርና በሰው መካከል ያለው መካከለኛው ደግሞ አንድ አለI እሱም ሰው የሆነ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው ራሱን ለሁሉ ቤዛ የሰጠ። ስለዚህም የፊተኛው ኪዳን ሲጸና፥ ሕግ የተላለፉትን ከሞት የሚቤዥ ስለሆነ፥ የጠፉት የዘለዓለምን ርስት የተሰፋ ቃል እንዲቀበሉ እርሱ የሐዲስ ኪዳን መካከለኛ ነው። (ዕብ. 9:15) የሐዲስ ኪዳንም መካከለኛ ወደሚሆን ወደ ኢየሱስ ክርስቶስ ...ደርሳችኋል። (ዕብ. 12:24) የእግዚአብሔር ሙላት ሁሉ በእሱ እንዲኖር፥ በእሱም በኩል በመስቀሉ ደም ሰላም አድርጎ በምድርና በሰማያት ያሉትን ሁሉ ለራሱ እንዲታረቅ ፈቅዷልና (ቆላ. 1:20) መካከለኛው ግን ያንድ አይደለም እግዚአብሔር ግን አንድ ነው። (ገላ. 3:20)

ምዕራፍ 4

ሥጋ ለብሷል፥

ትሰብእቱን (ሥጋ መልበሱን) የሚያሳዩትን ክፍሎች ብዙ ሰዎች ምስጢሩን ሳያስተውሉ ይሠርዛሉ፥ ይደልዛሉ፥ ከነአካቴውም ዘለዋቸው ይሄዳሉ። ኢየሱስ ክርስቶስ ሎቱ ስብሐትና በአባቱ ፍጹም አምላክ በእናቱም ፍጹም ሰው ነው። ሰው ሁኖ፥ ሰው በመሆኑ፥ ከኃጢአት በቀር የሰው ልጅ የሚሠራውን ሁሉ ሠርቷል። ስለዚህም ወልደ አብ በመለኮቱ ወልደ ማርያም በትስብእቱ፤ ወኮነ ሰብአ ከማነ ዘእንበለ ኃጢአት ባሕቲታ እየተባለ ይነገራል። ከዚህ በታች የተጠቀሱት ጥቅሶችም ከነመሰሎቻቸው የሚያሳዩት ትስብእትን ነው። ሥጋ በመልበሱ ለትስበእት የተጠቀሱትን ነው።

ከሁሉም አስቀድመን ጌታ ድኅረ ትንሣኤ ለማርያም መግደላዊት ታይቶ ያላትንና በአንድም ቤት ሊቃውንት እንዴት እንደሚተረጉሙት አሳይተን ሌሎችን ደግሞ በተጠየቅ ቅደም ተከተል እናቀርባለን።

ø) ወይቤላ እግዚእ ኢየሱስ ኢትልክፍኒ እስመ ዓዲ ኢዐረጉ ኀበ አቡየ ወሑሪ ባሕቱ ኀበ አኀውየ ወበልዮሙ አዐርግአ ኀበ አቡየ ወአቡክሙ፥ ኀበ አምላኪየ ወአምላክክሙ (ጌታ ኢየሱስም ገና ወደ አባቴ አላረግሁምና አትንኪኝ ወደ ወንድሞቼ ሂደሽ ግን ወደ አባቴ ወደ አባታችሁ ወደ አምላኪየ ወደ አምላካችሁ አርጋለሁ በያቸው አላት፥ ዮሐ. 20:17) ይህን ሲተረጎሙ=የተግሣጽ አነጋገር፥ ወደ አባቴ አልወጣሁም ማለት ገና አላመንሽብኝምና አትንኪኝ አላት። አንድም የመሰናበቻ ጊዜ የደረሰ መስሏት ቀርባለች፥ የማርግበት ጊዜ ገና ነውና አትንኪኝ አላት። ካህናት ልብሰ ተክህኖ ለብሰው ሳሉ ሊነኳቸው እንዳይገባ ለማጠየቅ (ከርእሰ ውጭ ዋጋ የለሽ አንድም)። ወደ ወንድሞቼ ሂደሽ ወደ አባቴ ወደ አባታችሁ፥ ወደ አምላኪየ ወደ አምላካችሁ (ፈጣሪዬ ፈጣሪያችሁ) አርጋለሁ ብለሽ ንገሪያቸው አላት። አቡየ ብሎ የእሱን ልደት ተናገረ። አቡየ ያለው የሱ የባሕርይ ነው፥ አቡክሙ ያለው የእኛ የጸጋ ነው። አምላኪየ አለው በሥጋ ይፈጥረዋልና፥ አምላክክሙ አለ በጥንተ ተፈጥሮ በሐዲስ ተፈጥሮ ይፈጥረናልና። አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ በአካል ሦስት (ይሜለሱ በአካላት) (ወይትወሐዱ በመለኮት እንዲል) አንድ ናችው። ለዚህም ማስረጃ ወልድ የአብም የራሱ የወልድም፥ የመንፈስ ቅዱስም ቃል ነው ብለናል። (ዮሐ. 1:1-5) በጥንተ ተፈጥሮ እግዚአብሔር አብ ዓለምን ሲፈጥር ሳይወጣ ሳይወርድ እንዲያው ከሰማያዊ ዙፋኑ ላይ ሁኖ እንዲህ ይሁን ሲል ይሆን

ነበር፥ ኩሉ በእሱ ሆነ፥ ያለ እሱም የሆነ የለም እንዳለ ዮሐንስ ወንጌላዊ በወንጌሉ (ዘፍ. 1:3፤ 6፤ 9፤ 11፤ 14፤ 20፤ 24፤ 29፤) ከዚህም በመለኮት አንድ በአካል ሦስት ወደሆነው አምላኪየና አባቴ አርጋለሁ። ሥጋን የመረጡት ሦስቱ ሲሆኑ ቅድመ ተዋሕዶ ያከበረው ግን የሦስቱም ኀይልና ክብር ሰጭ መንፈስ ቅዱስ ነው። ስለዚህ በመለኮቱ ከአብ ያንሳል የሚል ሁሉ ስሑት ነው፤ ሥጋን ግን የፈጠሩት በአንድ ሥልጣን ሦስቱም ናቸው፥ ያከበረውም የጋራ ኀይላቸው መንፈስ ቅዱስ ነው ከተዋሕዶ በፊት።

የሚከተሉት ጥቅሶችም የተጻፉት በዚህ መንፈስ ነው።

ለ) <u>ራሱ ጌታና ነቢዩ ኢሳያስ</u>፥ የጌታ የእግዚአብሔር መንፈስ በኔ ላይ ነው፤ ለድኆች የምሥራችን እሰብክ ዘንድ እግዚአብሔር ቀብቶኛልና፥ ልባቸው የተሰበረውን እጠግን ዘንድ፥ ለተማረኩትም ነጻነትን፥ ለታሰሩትም መፈታትን እናገር ዘንድ ልኮኛል፤ የተወደደችውን የእግዚአብሔርን ዓመት፥ አምላካችንም የሚበቀልበትን ቀን እናገር ዘንድ፥ የሚያለቅሱትንም ሁሉ እጽናና ዘንድ፥ እግዚአብሔር ለከብሩ የተከላቸው የጽድቅ ዛፎች እንዲበሉ ለጽዮን አልቃሾች አደርግላቸው ዘንድ፥ በአመድ ፈንታ አክሊልን፥ በልቅሶ ፈንታ የደስታን ዘይት፥ በሐዘንም ፈንታ የምስጋናን መጎናጸፊያ እሰጣቸው ዘንድ ልኮኛል። (ኢሳ. 61:1-3፤ ሉቃ. 4:18-19)

ሐ) <u>ጌታችን</u>፥ የምትወዱኝስ ብትሆኑ ከኔ አብ ይበልጣልና ወደ አብ በመሄዴ ደስ ባላችሁ ነበር። (ዮሐ. 14:28)

መ) አምላኬ! አምላኬ! ለምን ተውኸኝ? እኔን ከማዳንና ከጩኸቴ ቃል ሩቅ ነህ (መዝ. 21:1፤ ማቴ. 27:46)

ሠ) ስለዚያች ቀን ወይም ስለዚያች ሰዓት ግን የሰማይ መላእክትም ሆኑ ወልድም ቢሆን ከአብ በቀር የሚያውቅ የለም። (ሉቃ. 13:32)

ከዚህም አላዋቂ ሥጋን መልበሱን ለማጠየቅ ወልድም ቢሆን አለ እንጂ በመለኮቱ ከአብ ተለይቶ የማያውቀው ነገር አለ ለማለት አይደለም። ሁለተኛው ደግሞ ለአጽንዖተ ነገር ነው፤ ማንም ከአሳወቅሁ እያለ እንድይቸገር። ይህም ሁኖ አሁንም ብዙ ሰዎች ቁጥር ቆጥረን ሱባዔ ገብተን ደርሰንበታል፥ እግኝተነዋል እያሉ ይለፈልፋሉ፤ በዚህ እንዲያውም መጽሐፍ ቅዱስን ቃል ለቃል እንከተላለን ባዩዮች የጆሆባ ምስክሮችና አደበንቲስቶች ይብላሉ።

በእየጊዜው በዚህ ዕለት በዚህ ሰዓት ይመጣል ብለው ይናገራሉ: ግን ቀጠሮአቸውን አክብሮ እስካሁን አልመጣም: ከእንግዲህም በእነሱ ቁጥር አይመጣም። የሚከተሉት ደግሞ ከላይ ከተጠቀሰው ከጌታ ቃል ከወንጌሉ ጋራ ይስማማሉ: ተርጓሚዎች ግን ጎጋውን ሕዝብ ፈርተው እምላኩ ለእግዚእነ የሚለውን እየዘለሉት ይሄዳሉ። በዚህም ከጌታ ከራሱ እንበልጣለን: ከሐዋርያት ያውም ከጴጥሮስና ጳውሎስ እኛ እንሻላለን: እነሱንም እናርማለን: እናስተምራለን ብለው መነሣታቸውን ያሳያል። እንዲህ ነው: ከተማሩ ላይቀር ጌታን ተሳስተሃል: ሐዋርያትን መናፍቃን ናቸው ወይንም አታውቁም ብሎ ማረም: ግስተግር።

<u>ጳውሎስ</u>:

ሬ) ይትባረክ እግዚአብሔር አምላኩ ወአቡሁ ለእግዚእነ ኢየሱስ ክርስቶስ እቡሃ ለምሕረት ወአምላካ ለኩላ ትፍሥሕት። (2 ቆሮ. 2:3) የርኅራኄ አባት የመጽናናትም ሁሉ አምላክ የሆነ የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ አምላክና አባት ይባረክ።

ለ) ከመላእክት ይልቅ በጥቂት አሳነስኸው: የክብርና የምስጋና ዘውድ ጫንህለት: በእጆችህም ሥራ ላይ ሾምኸው: ሁሉን ከእግሮቹ በታች አስገዛህለት። (ዕብ. 2:7 መዝ. 8:5) ከመላእክት ጥቂት አሳነስኸው አለ: ከመላእክት እንደጌታ የተሰደበ የተዋረደ: የተገፈፈ: በመስቀል የተሰቀለ የሞተ የለምና።

ሸ) ለዘለዓለም የተባረከ የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ አምላክና አባት እንዳልዋሸ ያውቃል። (2ቆሮ. 11:31)

ቀ) በክርስቶስ በሰማያዊ ሥፍራ በመንፈሳዊ በረከት ሁሉ የባረከን የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ አባትና አምላክ ይባረክ። ኤፌ.1:3

በ) የክብር አባት: የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ አምላክ እሱን በማወቅ የጥበብንና የመገለጥን መንፈስ እንዲሰጣችሁ እለምናለሁ። (ኤፌ. 17)

ተ) በቀጥታ ከግሪኩ ወደ ግዕዝ የተተረጎመ ፊልጵስዮስ (2:6-10:6) ዘውእቱ እርእያሁ ለእግዚአብሔር: ኢኅለየ ሐይዶ ከሞነ ዕሩይ ምስለ እግዚአብሔር: 7 አዕረቀ ርእሶ ወነሥአ እርእያ ገብር ወተመስለ ሰብእ ወተረክበ በርእየተ ዕጓለ እመሕያው። 8 አትሐተ ርእሶ ወተአዘዘ እስከ ለሞት ወሞተሂ ዘበመስቀል። 9 ወበእንተዝ አዕበዮ እግዚአብሔር ጥቀ ወጸገዎ ስመ ዘየዐቢ እምኩሉ ስም። 10 ከመ ለስሙ ለኢየሱስ ይስግድ ኩሉ ብርክ ዘበሰማያት ወዘበምድር

ወዘታሕተ ምድር=6 እሱም በእግዚአብሔር መልክ ሳለ ቀምቶ ከእግዚአብሔር ጋራ እኩል መሆንን አልፈልግም። 7 ነገር ግን የባርያ መልክ ይዞ በሰው አምሳል ሁኖ ራሱን አራቆተ። እስመ ሞት ድረስ ያውም በመስቀል ላይ ሞት ታዘዘ። ስለዚህ እግዚአብሔርም ያለልክ ከፍ አደረገው፤ ስምም ከስም ሁሉ የሚበልጥ ሰጠው። ከሰማያትና ከምድር ከዚያም በታች ያለ ጉልበት ሁሉ ለኢየሱስ ስም ይበረከክ ዘንድ።

<u>ጴጥሮስ</u> በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ትንሣኤ ለሕያው ተስፋ ዳግመኛ የወለደን።የጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ አባትና አምላክ ይመስገን። (1ጴ. 1:3)

ቸ) እግዚአብሔር ግን የሞትን ጦር አጥፍቶ አስነሣው (ግብ. 2:24)

ኀ) በእርሱ ደስ የሚለኝ የምወደው ልጄ ይህ ነው የሚል ያ ድምፅ በመጣለት ጊዜ ከእግዚአብሔር አብ ክብርና ምስጋና ተቀብሏልና፥ እኛም በቅዱሱ ተራራ ከእሱ ጋራ ሳለን ይህን ድምፅ ከሰማይ ሲወርድ ሰማነ። (2ጴ. 1:17-18)

ነ) <u>ዮሐንስ</u> ለወደደን ከኃጢአታችንም በደሙ ላጠበን በመንግሥትም ለአምላኩና ለአባቱ ካህናት እንድንሆን ላደረገ፥ ለእሱ ከዘለዓለም እስከ ዘለዓለም ድረስ ክብርና ኀይል ይሁን። (ራእ. 1:6)

ኘ) ሥራህን በአምላኬ ፊት ፍጹም ሁኖ አላገኘሁትምና የነቃህ ሁን። (ራእ.3:2) ድል የነሣው በአምላኬ መቅደስ ዐምድ እንዲሆን አደርገዋለሁ፥ ወደፊትም ከዚያ ከቶ አይወጣም፤ የአምላኪዬን ስምና፥ የአምላኪዬን ከተማ ስም፥ ማለት ከሰማይ ከአምላኪዬ ዘንድ የምትወርደውን አዲሲቱን ኢየሩሳሌምን፥ አዲሱን ስሜን በእሱ ላይ እጽፋለሁ። (ራዕ. 3:12)

አ) <u>መዝሙር</u>፥ 2:6-9ም ከዚህ ላይ ይጠቅሳል፥ በእግዚአብሔር አብ ምስክርነት። እግዘአብሔር ጌታዬን ጠላቶችህን ለእግርህ መቀመጫ እስካደርግልህ ድረስ በቀኜ ተቀመጥ አለው። መዝ.109

ከ) ምሳ. 8:21-36ም ከዚህ ላይም ስለሚያስፈልግ ተመልሶ መመልከት ያሻል።

ወ) ከዚህም በላይ የተጠቀሱትን ቁጥሮች የሚመስሉ ብዙ ጥቅሶች አሉ፥ እነዚህ የተጠቀሱበት ምክንያት ትስብእትን የሚያዩ መሆናቸውን ለማስረዳትና እንደ አርዮስ በመለኮት ላይ የማይጠቀሱ መሆናቸውን ለማሳየት ነው። እነዚህ የተጠቀሱት ለትስብእት መሆናቸውን መላልሶ እንቦ ተረድቶ ቢጤዎቻቸውንም በዚሁ አቅጣጫ ይተረጉሟል፥ ይፈቷል።

ምዕራፍ 5

አዳምን ለማዳን ከአብ ተልኳል፥ ታዝዟል

መለኮት በመላ ዓለም ምሉእ እንደሆነ እናምናለን፥ እናውቃለን፤ ሥጋ ግን ከትንሣኤ በፊት ውሱን ነው። ውሱን ሥጋን ተዋሕዶ ሰው ሁኖ ለዘጠኝ ወር ከአምስት ቀን በማሕፀነ ማርያም አደረ፥ እንደ ሕፃናት አለቀሰ፥ ጥቂት በጥቂት አደገ፥ ከኃጢአት በቀር የሰው ልጅ የሚሠራውን ሁሉ ሠራ፤ በላ፥ ጠጣ፥ ሄደ፥ ተጓዘ፥ ደከመ፥ ተኛ፥ ፈራ፥ ሞተ በሥጋው። በሥጋው ይህን ሁሉ ያደረገውን የፍቅርን አባት የትሕትናን ጌታ፥ ጌታችንን አምላካችንን መድኀኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስን፥ አባቱ ላከው ብንል መላኩ ከአባቱ ያሳንሰዋል ብለው፥ ከውሰጣችን አብ ወልድ መንፈሰ ቅዱስ በኅብረት በከርሠ ማርያም አድረዋል የሚሉ አሉ፤ ባይጽፉ ነው እንጂ ነገ መጻፋቸው ስለማይቀር፥ እኔም ጨርሼ ሳላረጅ፥ ነገርን ነገር ያነሣዋል እንዲሉ፥ አሁኑኑ በነካ እጄ፥ ለጌታችን መናገሬ ካልቀረ በጥቂቱ ልጠቅስ እወዳለሁ። የኛ ሰዎች የሚሰሳቱት ሁልጊዜም ያልሰሙት ነገር ሲመጣባቸው ለማሰፈራት ሲፈልጉ ነው፤ ለኃጢአት ግንጫ የተሰጠውን ቁርባን፥ አዛውረው ብትቆርቡ ትኮነናላችሁ ሲሉ የኖሩ ለማስፈራራት፤ እግዚአብሔር አብ ለእግዚአብሔር ወልድ በሥጋው የባሕርይ አባቱ ነው ብለው የበተኑ ሁለት ባሕርይ የሚለውን ካቶሊክ ለማራቅ፤ አሁንም ደግሞ የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስን አዳኝነትና አማላጅነት ከደጉ ቁጭ ያሉ ከተሐድሶ ለመሸሽ ነው።

ያስበረገጋቸው ተሐድሶ ግን ምን እንደሚል አላውቅም።

በግድ ሳይሆን በሦስቱም ፈቃድ (እስመ በፈቃዱ ወበሥምረተ አቡሁ ወመንፈስ ቅዱስ መጽአ ወአድኀነነ እንዳለ ቅዱስ ኤፍሬም) አብ ልኮት በተለየ አካሉ ከሰማየ ሰማያት ወርዶ ሥጋ ለብሶ ሰው ሁኖ በመስቀል ላይ ተሠውቶ አድኖናል። ለአባቱ ከተላከ መላክ ዝቅ ያደርገዋል የሚሉ አሉ። በሀገራችው ሥርዓተ ማኅበር አያሰቡ። ክብሪትና ኩራት ከአባቱ ጋራ በሰማያዊ ዙፋኑ ሁኖ በመመሰገን ፈንታ አዳምን ለማዳን ሥጋ ሲለብስ እሰከ ትንሣኤ በመለኮት እንጂ በሥጋ ርቆ ተጠቅሎ የተቀመጠ ነገር ነው። በመላክ ምክንያት ከአባቱ ካነሰ፥ እናቱ ልካዋለች፥ ዮሴፍ ልኮታል፥ ከዚያም አልፎ ተርፎ በጥንታዊ ሥርዓተ ማኅበር እንደሚደረገው ጎረቤቱ ሁሉ አንተ ልጅ ና እንዲህ አድርግልኝ እያለ ሲልከው ኑሯል። ለዚህም ምስክሮች፤

ሀ) <u>እሱ ራሱ፤</u> ከእነሱም ጋራ ወርዶ ወደ ናዝሬት መጣ ይታዘዛቸውም ነበር። (ሉቃ. 2:51) ከጎረቤቶቹም ሌላ በዚህ ዓለም ላይ ሳለ ግንኙም ሲያገለግል ነው የኖረው። መሲሕ ሲነግሥ እንነግሣለን፥

ራስ ደጃዝማች: እንባላለን ሚኒስቴር እንሆናለን እያሉ እስከ ጳራቅሊጦስ ድረስ በቀድሞ ሥርዓት ያስቡ የነበሩ ሐዋርያትም የጌታ መንግሥት ከላይ በመከፈስ የሚሰጥ መስሏቸው በዘብዴዎስ ልጆች ቢቆጡ የመላክን የማገልገልን ትልቅነት ነግሯቸዋል።

ለ) ዐሥሩም ሰምተው በሁለቱ ወንድማማች ተቆጡ። ኢየሱስ ግን ወደ እሱ ጠርቶ እንዲህ አላቸው: የአሕዛብ አለቆች እንዲገዟችው: ታላላቆችም በላያቸው እንዲሠለጥኑ ታውቃላችሁ። በእናንተስ እንዲህ አይደለም: ነገር ግን ማንም ከእናንተ ታላቅ ሊሆን የሚወድ የእናንተ አገልጋይ ይሁን: ከእናንተ ማንም ትልቅ ለመሆን የሚፈልግ: የእናንተ አገልጋይ ይሁን: ከእናንተ ማንም አንደኛ ለመሆን የሚፈልግ የእናንተ ባሪያ ይሁን። የሰው ልጅ ሊያገለግል እንጂ ሊገለገል እንዳልመጣ (ሊላክ እንጂ ሊልክ እንዳልመጣ)። (ሉቃ. 20:24-28)

ሐ) ከዚህም በላይ በቤተ እስራኤል እግር ማጠብ የውርደት ውርደት ነው: ለማጠብ ቢገደድም ከራት በፊት እንጂ ከራት በኋላ አይደለም። ጌታ ግን ከራት ላይ ተነሥቶ ነው የራሱን የበታቾቹን የደቀ መዛሙርቱን እግር ያጠበ: ታዲያ ከዚህ ሁሉ አብ ያንሳል ብለው ነው አላስተዋዮች የሚዘባርቁ? ለሁሉም ይህን የባልቴት ተረት ከዚህ ላይ እንነልትና እንደ ልማዳችን መጻሕፍቱና ሊቃውንቱ: ቅዱሳን አበው የሚሉትን እንይ። ለዚህም ለሌሎች አብያተ ክርስቲያን ተከታዮች ቅዱሳት መጻሕፍትን: ለኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ተከታይ ግን አዋልዱን ሁሉ: ቅዳሴውን: ሰዓታቱን: ኪዳኑን: ውዳሴ ማርያሙን: መልካ መልኩን ሁሉ እንጠቅሳለን: ለምን? ቢሉ: ትደግማለህ እንጂ አትረዳም ለማለት: እንቦ የሚረዱ ቢሆን ኑሮ ከዚህ በፊት በአማላጅነት ያደረጉትን ስሕተት አያደርግም ነበርና ነው። ከአብ መላኩን የሚያስረዱ ጥቅሶች:

በመጀመሪያም ቅዱሳት መጻሕፍት:

ምስክሮች:

ሀ) <u>ራሱ ጌታችን ኢየሱስ</u>: ዮሐ. 3:17: 61 ቁጥርን እይ: በዓለም እንዲፈርድ እግዚአብሔር ልጁን አላከውምና ይልሃል።

ለ) ነገር ግን አብን እንድወድ ዓለም እንዲያውቅ: አብ እንዳዘዘኝ እንዲሁ አደርጋለሁ። (ዮሐ. 14:31)

ሐ) ሕያው አብ እንደላከኝ: እኔም ከአብ የተነሣ ሕያው እንደምሆን

እንዲሁ የሚበላኝ ደግሞ ከኔ የተነሣ ሕያው ይሆናል። (ዮሐ. 6:57)

መ) ኢየሱስም ዳግመኛ ሰላም ለእናንተ ይሁን፡ አብ እንደላከኝ፡ እኔ ደግሞ እልካችኋለሁ አላቸው። (ዮሐ. 20:21)

ሙ) አብ የሚሰጠኝ ሁሉ ወደኔ ይመጣል፥ ወደኔም የሚመጣውን ከቶ ወደ ውጭ አላወጣውም፥ ፈቃዴን ለማድረግ እይደደለም እንጂ የላከኝን ፈቃድ ለማድረግ ከሰማይ ወርጃለሁና። ከሰጠኝም ሁሉ አንድም እንኳ እንዳላጠፋ፥ በመጨረሻው ቀን እንዳስነሣው እንጂ፥ የላከኝ የአብ ፈቃድ ይህ ነው። (ዮሐ. 6:37-39)

ረ) እኔ ግን ከሱ ዘንድ ነኝ እርሱም ልኮኛልና አውቀዋለሁ ብሎ ጮኸ። (ዮሐ. 7:29)

ሰ) አብ የቀደሰውንና ወደ ዓለምም የላከውን (ዮሐ. 1:36)

ሸ) ኢየሱስም አላቸው። እግዚአብሔርስ አባታችሁ ከሆነ በወደዳቸሁኝ ነበር፥ እኔ ከእግዚአብሔር ወጥቼ መጥቻለሁና፡ እርሱ ላከኝ እንጂ ከራሴ አልመጣሁምና። (ዮሐ. 8:42)

ቀ) ቀን ሳለ የላከኝን ሥራ ላደርግ ይገባኛል። (ዮሐ. 9:4)

በ) እሱ ግን ስለዚህ ተልኬአለሁና ለሌሎች ከተማዎች ደግሞ የእግዚአብሔርን መንግሥት አስብክ ዘንድ ይገባኛል አላቸው። (ሉቃ. 4:43)

<u>ቅዱስ ጳውሎስ</u>፥

ተ) ነገር ግን የዘመኑ ፍጻሜ በደረሰ ጊዜ እግዚአብሔር ከሴት የተወለደውን ከሕግም በታች የተወለደውን ልጁን ላከ። (ገላ. 4:4)

ቸ) <u>ቅዱስ ዮሐንስ ወልደ ነጎድጓድ ሐዋርያው</u> በዚህም፡ የእግዚአብሔር ፍቅር በእኛ ዘንድ ተገለጠ፥ በእርሱ በኩል በሕይወት እንኖር ዘንድ እግዚአብሔር አንድ ልጁን ወደ ዓለም ልኮታልና። (ዮሐ. 4:9)ከቅዱሳት መጻሕፍት እንደዚህ ያሉ፡ ብዙ ለቁጥር የሚያደናግሩ ጥቅሶች መጥቀስ ይቻላል፡ ግን ወረቀትና ጊዜ እንዳይፈጅ የእነሱው እስከዚህ ይብቃንና ሊቃውንትንና አዋልድን ደሞ እንይ፣

<u>ሐዋርያት</u>፥

ኀ) ወዐረገ ሰማያተ ኀበ አብ ዘፈነም ወደ ላከው ወደ አብ ወደ ሰማይ ዐረገ (መ.ቅ. 103)

ከ) ነአኩተከ እግዚኦ በፍቁር ወልድከ እግዚእነ ኢየሱስ ዘበደኃሪ መዋዕል ፈናከ ለነ ወልደከ መድኀነ ወመቤዝወ መልእከ

ምክርከ=አቤቱ በተወደደ ልጅህ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ እናመሰግንሃለን፥ በኋለኛው ዘመን የምክርህን አበጋዝ፥ መድኀኒትና ቤዛ የሚሆን ልጅህን ልከህልናልና። (መ.ቅ. 110:4)

ሠ) ሰአሉኒ ወለኮሎሙ አዕርፍ ነፍሶሙ ወተሣህሎሙ ዘፈናከ እምስግይ ወልደከ ውስተ ግሕፀነ ድንግል ተዐቁረ በክርሥ ሥጋ ኮነ ወወልድከ ተዐውቀ እመንፈስ ቅዱስ የኢህንም የሁሉንም ነፍሳቸውን እሳርፍ ይቅርም በላቸው ልጅህን ከሰግይ ወደ ድንግል ግሕፀን የላክኸው፥ በግሕፀን ተወሰነ፥ ሥጋም ሆነ ልጅህም በመንፈስ ቅዱስ ተዐወቀ፤ (መ.ቅ. 115:23)

ወ) ወልድከ መጽአ ወእምድንግል ተወልደ ወሕዝበ ሰከ ይገብር=ልጅህ መጣ ከድንግልም ተወለደ ፈታድህን ይፈጽም ሕዝብንም ለእንተ ያደርግ ዘንድ (117:33)

<u>አባ ሕርያቆስም</u>፥

ዘ) በእግን ነጸረ እግዚአብሔር አብ ምሥራቀ ወምዕራብ ሰሜነ ወደቡበ ወውስተ ኩሉ አጽናፍ፥ አስተንፈሰ ወአጸነወ ወኢረከበ ዘከግኪ ወሠምረ መዓዛ ዚአኪ ወእፍቀረ ስነኪ ወፈነወ ኀቤኪ ወልዶ ዘያፈቅር=እግዚአብሔር አብ ከሰግይ ሁኖ ምሥራቅንና ምዕራብን ሰሜንና ደቡብን ዳርቻዎችንም ሁሉ በእውነት ተመለከተ፥ ተነፈሰ፥ አሸተተም፥ እንዳንቺ ያለ ግን አላገኘም፥ ያንችን መዓዛና ደምግባትም ወደደ፥ የሚወደውን ልጁንም ወዳንቺ ላከ። መ.ቅ.ገ. (214:24) ከዚህ ለይ አባ ሕርያቆስና ቅዱስ ኤፍሬም ተባብረዋል።

<u>ቅዱስ ኤፍሬም</u>፥

የ) ነጸረ አብ እም ሰግይ ወኢረከበ ዘከግኪ፥ ፈነወ ዋሕዶ ወተሰብአ እምኔኪ አብ ከሰግይ አየ፥ እንዳንቺ ያለ ግን አላገኘም፥ ባያገኝ አንድያ ልጁን ወዳንቺ ልኮ ሰው ሆነ ብሏል። (ውዳሴ ዘረቡዕ)

ደ) ዳግመኛም ይሸው አባ ሕርያቆስ፥ ነአምን አበ ፈናዊ ከመ አብ ውእቱ በህላዌሁ ወነአምን ወልደ ተፈናዊ ከመ ወልድ ውእቱ በህላዌሁ ወነአምን መንፈሰ ቅዱሰ ግሕየዊ ከመንፈስ ቅዱስ ውእቱ በህላዌሁ፥ ሠለስቱ ስም አሐዱ እግዚአብሔር=የላከ አብ በህላዌው አባት እንደሆነ እናምናለን፥ የተላከ ወልድ በህላዌው ወልድ እንደሆነ እናምናለን ግሕየዊ መንፈስ ቅዱስም በህላዌው መንፈስ ቅዱስ እንደሆነ እናምናለን ምስት ስም፥ አንድ እግዚአብሔር። (መ.ቅ. 220:54)

ሠለስቱ ምእትም፡

ጀ) እግዚአብሔር አብ ዘፈነወ ወልዶ ዋሕደ ከመ ይጎድር ውስተ ሥጋ ወለት እንተ ኢተአምር ምተ=እግዚአብሔር አብ አንድያ ልጁን የላከው ወንድ ከማታውቅ ልጅ ሥጋ እንዲያድር ነው።

ገ) ተሐፅነ እኮ በትርሲት ወክብር አላ ከመ ውሉደ ነዳያን፡ ልህቀ በዐቢይ ተግሣጽ እንዘ ይትኤዘዝ ለእዝማዲሁ፡ በጌጥና በክብር እይደለም፡ እንደ ድኆች ልጆች ለዘመዶቹ እየታዘዘ በብዙ ተግሣጽ እደገ እንጂ። (መ.ቅ. 259:77)

ወእምዝ ሶበ ርእየ ከመ ኢበቁዐ ለእድጎኖተ ዓለም ደመ ነቢያት ቅዱሳን እም ደመ አቤል ጻድቅ እስከ ደመ ዘካርያስ ወልደ በራክዩ፡ ፈነወ ለነ ወልዶ መድኀነ ወመቤዝወ ከመ ይባልሕ ወይቤዙ ወያብእ ቅድሜሁ ተዝካረ ሕያዋን ወሙታን=ከዚህ በኋላ ከጻድቁ ከአቤል ደም ጀምሮ እስከ በራክዩ ልጅ ዘካርያስ ደም ድረስ የቅዱሳን ነቢያት ደም ዓለምን ለማዳን እንዳልጠቀመ ባየ ጊዜ መድኀኒትና ቤዛ የሚሆን ልጁን ፈጽሞ ያድን ዘንድ ላከልን፣ በፊቱም የሕያዋንና የሙታንን መታሰቢያ ያገባ ዘንድ። (መ.ቅ. 375:43)

ጠ) በሚከተሉት ገጾችና ቁጥር የሚገኙትም ከዚህ በላይ የተጠቀሱትን ይመስላሉ፣ (መ.ቅ. 394:17፣ 395:24፣ 396:29፣ 415:16፣ 416:22፣ 419:35፣ 458:15)

ጨ) ጎርጎርዮስም፣ ወነአምን አበ ፈናዌ ወነአምን ወልደ ተፈናዌ ወነአምን መንፈስ ቅዱስ ማሕያዌ=ላኪ አብን እናምናለን፡ ተላኪ ወልድን እናምናለን፡ ማሕያዊ (አዳኝ) መንፈስ ቅዱስን እናምናለን ብሏል። (መ.ቅ. 470:13፣ 472:26)።

ይህን ሀሉ እያነበቡ ነው እጣመው እየተረጎሙ፡ ዐይኔን ግምባር ያድርገው ጆሮዬን ይድፈነው ብለው የሚከዱ።

ጸ) ርእየ ኢሳይያስ ነቢይ በመንፈሰ ትንቢት፡ ምስጢሮ ለዐማኑኤል ወበእንተዝ ጸርሐ እንዘ ይብል ሕፃን ተወለደ ለነ ወልድ ተውህበ ለነ ሕፃን ተወለደልን፡ ልጅ ተሰጠልን ብሎ ኢሳይያስ በትንቢት መንፈስ ጮኸ። ተፈሣሕ ወተሐሠይ አ ዘመደ ዕጓለ እመሕያው እስመ አፍቅሮ እግዚአብሔር ለዓለም፡ ፈነወ ለነ መዝራዕቶ ልዑለ=የሰው ልጅ ሆይ! በጣም ደስ ይበልህ፡ እግዚአብሔር ዓለሙን ወዶ አንድያ ልጁን በእሱ የአመነ ሁሉ ይድን ዘንድ ሰጥቷልና ከፍተኛ ክንዱንም ልኮልናልና። ነጸረ አብ እምሰማይ ወኢረከበ ዘከማኪ፡ ፈነወ ዋሕዶ ወተሰብአ እምኔኪ=አብ ከሰማይ

ወይቶ እንዳንቺ ያለ ባያገኝ አንድያ ልጁን ልኮ ካንቺ ሰው ሆነ፡ ሥጋ ለበሰ። ታዲያ አሁን ውዳሴ ማርያም መጠቀሱ፡ የእኛ ካህናት መጀመሪያ በቃል በቁጥር ከዚያ በዜማ ያውም በአራራይና በዕዝል፡ ቀጥሰው በነጠላ በአንድም ትርጓሜ አጥንተው ዕለት በዕለት ሲደግሟት የሚኖሩትን አታውቁትም ለማለት ነው ወይ? አታውቋትም ለማለት ሳይሆን ሸመደዳችኋት እንጂ አልተረዳችኋትም ለማለት ነው።

<u>መልክአ ኢየሱስም</u>፡

፬) እምሥራቀ ፀሐይ እስከነ ዐረብ ይትአኮት ስሙ ለእግዚአብሔር አምላክነ፡ ኪያከ ወልዶ ዘፈነወ ለነ። ኢየሱስ ክርስቶስ ሊቀ ካህናቲነ አስተጋብ አነ ኀበ ትረፍቅ መካነ፡ እስመ ዝርዋን አግብርቲከ ንሕነ።

<u>የጥምቀት ድጓም</u>፡ ክርስቶስ አስተርአየ ውስተ ዓለም እምድንግል ተወልደ፡ ክሡተ ኮነ እንዘ ይትኤዘዝ ለአዝማዲሁ ከሞኖ ሰብአ በዮርዳኖስ ተጠመቀ ብሏል።

ይህ አዲስ አይደለም የእኛ ሰው በግዕዝ አቡነ ዘበሰማያትን በቃሉ አጥንቶ እንደበቀቀን ሲያነበንብ ይኖራል፡ ይህም ከዚያ ልዩነት የለውም። እንደዚህ ላሰው ልብ ወለድ መሳይ ታሪክ የሚጠቅሱ ሰዎች አሉ። ሰውዬው ሊቀሰ ወደ ጳጳስ ይሄዳል፡ አቡነ ቀሲሱ ሊፈትኑት ሥላሴ ስንት ናቸው? ይሉታል። እሱም በአካባቢው ያሉትን የሥላሴ አብያተ ክርስቲያን ቆጥሮ አምስት ናቸው ብሎ መለሰ ይባላል። ሰው በባልንጀራው ስለሚገመት እንደነዚህ ካሉት ጋራ መዋል ያስገምታል ብለው የሚያፍሩ አሉ።

ብዙ ካህናት መድገም እንጂ አንብቦ መረዳት አይችሉም: ስለዚህ ቅዱሳት መጻሕፍትን ሊቃውንትን፡ የሚደግሙትን መልክአ መልክ: የሚያነቡትን ገድላ ገድል፡ የሚያዜሙትን ድጓ፡ ቅኔ ግጥም መጥቀስ ጊዜ መፍጀት ብራና መጨረስ ነው እንጂ ቀለሙ እንደ ስርብትናው ቢቀናቸው ኑሮ ጥቂቱ በበቃ ነበር።

የኛ ሊቃውንት በትዕቢት ተወጥረው አንበው ስለማይረዱ ጥቅስ ግብዛት ከንቱ ነውና አስከዚህ ይብቃን።

የዚህ ርእሰ ማጠቃለያ እንደ ሰው አባት በግድ አይደለም እንጂ በሦስቱ ፈቃድ አባቱ ልኮት ወደዚህ ዓለም መጥቶ እንደኛ ከኃጢአት በቀር ሰው ሁኖ አድኖናል። ተልኳል፡ ይላካል፡ አገልግሏል፡ ያገለግላል፡ ይምራል፡ ያስምራል፡ ይከራከራል፡ ስለኛም ይሟገታል፡ ይዳኛል፡ ይፈርዳል።

ምዕራፍ 6

ክርስቶስ ቤዛና መድኀኒታችን ነው፡

የቤዛና የመድኀኒት መግለጫ፡

የቤዛና መድኀኒት ልዩነት ምንድር ነው ለሚል፡ ቃላቱን እንገልጣለን። መድኀኒት አድኀነ ካለው ግሥ የመጣ ነው። ገዳይ ሲደርስ አዳኝ ይደርስ እንዲሉ ማዳን በጉልበት ተከላክሎ፡ ወይም ገንዘብ ሰጥቶ፡ ወይም ዋስ ሁኖ ችግረኛን ከጠላቱ እጅ ማውጣት ነው። ቤዛ ግን ቤዘወ ተበዥ ካለው ግሥ የመጣ ስለሆነ ከመድኀኒት ትርጉም በላይ ራስን ለያዥ ወይም በተያዥ ፈንታ ሰጥቶ እስረኛን ወይም ምርኮኛን ማዳን ነው። ስለዚህ ክርስቶስ በማስተማርና በሞት ከግብርናተ ዲያብሎስ ስላወጣን ቤዛችንም መድኀኒታችንም ነው።

ጌታችን ወደዚህ ዓለም የመጣበት ምክንያት፡

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ወደዚህ ዓለም የመጣውና ሥጋ የለበሰው ስለሁለት ነገር ነው፡ ለአርአያ፡ ለቤዛ። አርአያውን በትምህርቱና በሕይወቱ ሂደት አሳይቶናል፡ ምግባር በሚለው ርእስ እናየዋለን። ቤዛነቱንና መድኀኒትነቱን ግን ከዚህ ቀጥለን እንጽፋለን። ዋነኛው የመጣበት ዓላማም ይህ ነው ይባላል፡ ነውም። ይህንም በአይሁድ ሴራ፡ በጲላጦስ አደባባይ ተሰድቦ፡ ተገፎ፡ ተገርፎ፡ የሰማዕት ሥቃይ ተቀብሎ በመስቀል ተሰቅሎ ሙቶ፡ ሦስት መዓልት ሦስት ሌሊት በከርሠ መቃብር አድሮ፡ ለአባቱ ለእግዚአብሔር አብ ለኃጢአታችን ፍጹም ዘለዓለማዊ መሥዋዕት፡ ለአዳም ቤዛ፡ ለእግዚአብሔር ካሣ ራሱን አድርጎ ተበዥቶናል። በዚህም ለዘለዓለም ከአባቱ ጋራ አስታርቆናል፡ አግልዶናል። ይህንም ለማስረዳት ከዚህ በታች ያሉት ጥቅሶች ተጽፈዋል።

ሀ) ኃጢአታቸውንም ይሸከማል፡ ስለዚህ እሱ ብዙዎችን ይወርሳል፡ ከኀያላንም ጋራ ምርኮን ይካፈላል፡ ነፍሱን ለሞት አሳልፎ ሰጥቷልና፡ ከዐመፀኞችም ጋራ ተቆጥሯልና፡ እሱ ግን የብዙ ሰዎችን ኃጢአት ተሸክሞ። ስለ ዐመፀኞችም ማለደ። (ኢሳ. 53:12፡ ሉቃ. 23:34)

ከሰማይም ከወረደው በቀር ወደ ሰማይ የወጣ ማንም የለም፡ እሱም በሰማይ የሚኖረው የሰው ልጅ ነው። ሙሴ በምድረ በዳ እባብን እንደሰቀለ እንዲሁ በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘለዓለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ የሰው ልጅ ሊሰቀል ይገባዋል። በእሱ የሚያምን ሁሉ የዘለዓለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ፡ እግዚአብሔር አንድያ ልጁን እስኪሰጥ ድረስ ዓለሙን እንዲሁ ወዷልና። ዓለም በልጁ እንዲድን ነው እንጂ

በዓለም እንዲፈርድ እግዚአብሔር ልጁን ወደ ዓለም አላከውምና። በሱ በሚያምን አይፈረድበትም፥ በማያምን ግን በአንዱ በእግዚአብሔር ልጅ ስም ስላላመነ አሁኑኑ ተፈርዶበታል። (ዮሐ. 3:13-19)

በዚህም የእግዚአብሔር ፍቅር በእኛ ዘንድ ተገለጠ፤ በእሱ በኩል በሕይወት እንኖር ዘንድ እግዚአብሔር አንድ ልጁን ወደ ዓለም ልኮታልና። (ዮሐ. 4:9-10)።

እኔ መንገድና እውነት ሕይወትም ነኝ፤ በእኔ በኩል በቀር ወደ አብ የሚመጣ የለም (ዮሐ. 14:6)

መዳንም በሌላ በማንም የለም፤ እንድንበት ዘንድ የሚገባን ለሰዎች የተሰጠ ስም ከሰማይ በታች ሌላ የለምና። (ግብ. 4:12)

ገና ደካሞች ሳለን፥ ክርስቶስ ዘመኑ ሲደርስ ስለ ኃጢአተኞች ሞቷልና። (ሮሜ 5:6)

መሞትን አንድ ጊዜ ፈጽሞ ለኃጢአት ሞቷልና በሕይወት መኖርን ግን ለእግዚአብሔር ይኖራል (ሮሜ 5:6)

<u>መደምደሚያ</u>፥ በቤዛነቱ ከአባቱ ጋራ አስታርቆናል፤ አማልዶናል ያማልደናል። ከግብርናተ ዲያብሎስም አድኖናል።

ምዕራፍ 7

ክርስቶስ ብርሃነ ዓለም፥ አርአያ፥ አብነት፥ መምህር ነው፤

ክርስቶስ የዓለም ብርሃን ነው፥ የሚያምኑበትን ሁሉ በመንፈስ ቅዱስ እየመራ ወደ አባቱ መንግሥት ወደ መንግሥተ ሰማያት ያገባል። ለዚህም እንዴት ለሚል ጠያቂ የሚከተሉት ጥቅሶች ተሰጠዋል።

የዓለም ብርሃንነቱን የሚያሰረዱ ጥቅሶች፤

እሱ ራሱ ኢየሱስ ክርስቶስ፥

ሀ) እኔ ውእቱ ብርሃኑ ለዓለም ዘይተልወኒ ኢየሐውር ውስተ ጽልመት አላ ይረክብ ብርሃነ ሕይወት=የዓለም ብርሃን እኔ ነኝ፥ የሚከተለኝም ወደ ጨለማ አይሄድም የሕይወትን ብርሃን ያገኛል እንጂ፤ (ዮሐ. 8:12)

ለ) እንዘ ሀሎኩ ውስተ ዓለም እነ ውእቱ ብርሃኑ ለዓለም በዓለም ሳለሁ የዓለም ብርሃን እኔ ነኝ፤ (ዮሐ. 9:5)

ሐ) በእሱ ሕይወት ነበረች፤ ሕይወትም የሰው ብርሃን ነበረች። ብርሃንም በጨለማ ያበራል፥ ጨለማም አላሸነፈውም። (ዮሐ. 1:4-5)

እምን እሱስ ለራሱ ብርሃን ነው፥ ግን ለሰው ምን ሰጠ? ለሚል ጠያቂ ደግሞ በአጻም በደል የሄደውን ልጅነታችንን መልሶ በጸጋ የእግዚአብሔር ልጆች፥ የእሱ ታናሽ ወንድሞች፥ የአባቱን መንግሥት ከሱ ጋራ ተወራራሾች አድርጎናል። ይህ ሁሉ ከብርና ጸጋም በሚከተሉት ጥቅሶች ይረጋገጣል፤

ወደ ወገኖቹ መጣ፥ ወገኖቹ ግን አልተቀበሉትም፥ ለተቀበሉትና በስሙ ላመኑት ግን የእግዚአብሔር ልጆች ይሆኑ ዘንድ ሥልጣን ሰጣቸው፤ እነሱም ከእግዚአብሔር ተወለዱ እንጂ ከደም ወይም ከሥጋ ፈቃድ አልተወለዱም (ዮሐ. 1:11-13)

ከዚህም አልፎ ተርፎ እንደሱ ወደሱ እንዲያማልዱ፥ ኃጢአት እንዲያስተሰርዩ፥ ሙት እንዲያነሡ፥ ለምጽ እንዲያነጹ ሥልጣን ሰጥቷቸዋል፤ ይህን በሰፊው ዝቅ ብለን የክርስቶስ ተከታዮችም ያግልጻሉ በሚለው ርእስ እናየዋለን፤ ለአሁኑ ግን፤

እውነት እውነት እላችኋለሁ በእኔ የሚያምን እኔ የምሠራውን ሥራ እሱም ይሠራል፤ ከዚህም የሚበልጥ ይሠራል (ዮሐ. 14:12) ይህም በሥራና በተግባር ሲታይ ሲገለጥ የኖረ ዛሬም እስከ ዕለተ ምጽአት ሲደረግ የሚኖር እንጂ የሰርብትና ወሬ እንዳይደለ በሰፊው ከቦታው እናየዋለን።

በእግዚአብሔር መንፈስ የሚመሩ ሁሉ የእግዚአብሔር ልጆች ናቸውና፥ አባ! አባት! ብለን የምትጮኽበትን የልጅነት መንፈስ ተቀበላችሁ እንጂ እንደገና ለፍርሃት የባርነት መንፈስ አልተቀበላችሁምና። የእግዚአብሔር ልጆች መሆናችንን ያ መንፈስ ራሱ ከመንፈሳችን ጋራ ይመሰክራል። ልጆች ከሆን ወራሾች ደግሞ ነን፥ ማለት የእግዚአብሔር ወራሾች፥ የክርስቶስ ደግሞ የጋራ ተወራራሾች ነን (ሮሜ 8:14-17)

ኢየሱስ ክርስቶስ ነው ብሎ የሚያምን ሁሉ ከእግዚአብሔር ተወልዷልI (1 ዮሐ. 5:1)

በእምነት ሁላችሁም በክርስቶስ ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጆች ናችሁና (ገላ. 3:26)

ከርሱ ጋር ከሞትን ከርሱ ጋር ደግሞ በሕይወት እኖራለን፥ ብንጸና ከእሱ ጋራ ደግሞ እንነግሣለን። (2 ጢሞ. 2:11)

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ አርአያና መምህር ነው።

በቤዛነት እንዳየነው የቤዛነቱ ጓደኛ አርአያነቱ ነው። አርአያነት በሁለት ይከፈላልI በምሳሌነት እየሠሩ በሕይወት ሂደት ማሳየትና በቃል ማስተማር። አርአያነቱ በዚህ ርእስ ከዚህ ታይቶ ትምህርቱ ደግሞ በእየምዕራፉ ይቀጥላል። እሱ በአርአያነት ያልፈጸመው በጠቅላላ ለሰው ልጅ የሚያስፈልግ ትሩፋት የለም። ለባሕርዩ የሚሰግግውን በምሳሌነት እየሠራ አሳይቷል፥ የማይሰግግውን ደግሞ በቃል እንዲህ አድርጉ፥ አታድርጉ እያለ አስተምሯል። ታዘዙ ለማለት በአባቱ ቃልነት የሠራትን ሕገ አሪትን ፈጽሟል። ትሕትናን ለማሳየትም ለእናቱ ዘመዶች እየታዘዘ አድጓል፥ የደቀ መዛሙርቱን እግር አጥቧል፥ ትልቅ ለመሆን የሚፈልግ ሁሉ አገልጋይ ይሁን ብሎ አዝዟል።

እኔ ጌታና መምህር ሆኜ እግራችሁን እንዳጠብሁ እናንተ ደግሞ እርስ በርሳችሁ እግራችሁን ትተጣጠቡ ዘንድ ይገባችኋል። እኔ ለእናንተ እንዳደረግሁ እናንተም ታደርጉ ዘንድ ምሳሌ ሰጥቻችኋለሁና። (ዮሐ. 13:14-15)

ለሕፃናት አርአያ ለመሆን ለእናቱና ለአሳዳጊው አባቱ ለዮሴፍ እየታዘዘ ለዘመዶቹ እየተላከ አድጓልI (ሉቃ. 2:51)

የአሪት ጌታ እሱ ሲሆን ለአርአያ ሕገ አሪትን ፈጽሟልI ባርባ ቀኑ ዋሊያና ርግብ ይዘውለት በሕጉ መሠረት ቤተ መቅደስ ገብቷልI ከዚህ በኋላም በጥምቀቱና በመስቀሉ የሻረውን ግዝረትን ፈጽሟል። (ሉቃ. 2:21-52)

እንዲህ እያለ አድጎ በ30 ዓመቱ አርአያውን ሊሰጠን ለእኛ ልጅነትንና ስርየተ ኃጢአትን የሚያሰጠንን ጥምቀት በፈለገ ዮርዳኖስ፥ በእደ ዮሐንስ ተጠመቀ። ጥምቀት ለእኛ ልጅነትንና ስርየተ ኃጢአትን ያሰጣል፥ ለእሱ ግን አርአያ ከመሆን በቀር የሚጠቅመው ነገር የለም። (ማቴ. 3:13-17፤ ማር. 1:9:11፤ ሉቃ. 3:21-22) ይህም ወደ እግዚአብሔር ቤተ ሰብእ መግቢያ፥ የእግዚአብሔርን ልጅነት ማግኛ፥ የጥንተ አብሶ ማስተስረያ እንዲሆን ሕግ አድርጎ አዘዘ። (ዮሐ. 3:3-9፤ ማር. 16:15-18፤ ግብ. 2:38፤ ኤፌ. 4:4)

<u>መደምደሚያ</u>፥ ኢየሱስ ክርስቶስ ብርሃን፥ አርአያ፥ መምህር ነው ብለን ካመንን እርስ በርሳችሁ ተፋቀሩ የምትል የብርሃንን ትእዛዝ ይዘን በብርሃን እንጓዝ (1ዮሐ. 2:8-9)



ጥምቀት

ምዕራፍ 8

ጥ ም ቀ ት፡

ወደ ቤተ ክርስቲያን (ማኅበረ ክርስቲያን) መግቢያው በሩ ጥምቀት ነው። በግሪክም ሆነ በግዕዝ የጥምቀት ትርጉም አንድ ነው። እሱም ማለል: ቀለም ማግባት: መንከር: መዘፍዘፍ: በቀለም መልከን መለወጥ ማለት ነው።

ሰው አምኖ በመጠመቁ በጥንተ አብሶ በአዳም ምክንያት የሄደች ልጅነቱን በጸጋ እግዚአብሔር ያስመልሳል: ኃጢአቱን ያስርያል: በዚህም ወደ ማኅበረ ክርስቲያን ይገባል። ሰው ከተወለደበት ቀን አንሥቶ እስከ ዕለተ ሞቱ ሲጠመቅ ይችላል። አንዳንድ ሰዎች ላሠራሩ: ሰሥርዓቱ እንዲመች ብለው: ወንድ ልጅ በአርባ ቀን ሴት ልጅ በሰማንያ ይጠመቁ የሚሉ አሉ: ሌሎች ደግሞ ጌታ ያመነ የተጠመቀ ይዳን ነውና ያሰው ከመጠመቅ ማመን ይቅደም: ስለሚቀድም ሕፃናትን አናጠምቅም ይላሉ። ሰሁለቱም በዘመነ ሐዋርያት ይደረግ የነበረውን ግየት ያሻል በዚያ ዘመን አባወራው ሲጠመቅ: ሴት ወንድ: ሕፃን ሽማግሌ ሳይለይ ይጠመቅ ነበር። (ግብ. 10:48: 16:14-15: 33: 1ቆሮ. 1:16)

ከዚህ በላይ የተጠቀሱትን መላልሶ አንብቦ በመላ ቤተ ሰቡ መጠመቁን ይረዱል።

ከዚህም በላይ በብሉይ ኪዳንም ሕፃናት በወላጆቻቸው አማካይነት ተገርዘው የእግዚአብሔር ቤተ ሰቦች: የእስራኤል ማኅበሮች ሆነው እስከ 12 ዓመታቸው ይቆያሉ። (ዘፀ. 17:9-15) በ12 ዓመታቸው በወኪል የነበረውን ኀላፊነት ራሳቸው ተቀብለው ያጸድቃሉ። ይህን ተከትለው አሁንም ብዙ አብያተ ክርስቲያናት በሕፃንነቱ በወኪል በዘመዶቹ ወይም በክርስትና አባቶቹ ዋስትና አጥምቀው: በዐሥራ ሁለተኛ ዓመቱ ራሱ : አምናለሁ ጥምቀቴንም ተቀብያለሁ ብሎ እንዲያጸድቅ ያደርጋሉ። ጥሩ ዘዴ ነው። ከዐሥራ ሁለት ዓመት በፊት የሞተ እንደሆን: ሳይጠመቅ እንዳይሞት: ከዚያ በኋላ ደግሞ ሳይማር: ሳያውቅ: እንዲያው በልግድ በልጅነቴ ተጠምቄ ነበር አሉ እያለ በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ ሳያምን: ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስም ወደዚህ ዓለም መጥቶ: ሙቶ እንዳዳነው ሳያውቅ: እንዲያው በግብረ አረመኒ እንዳይሞት።

በሕፃንነት በመጠመቃቸው በጸጋ እግዚአብሔር በመንፈስ ቅዱስ ያድጋሉ። እንኳንስ ተወልደውና ገና በማሕፀን ሳሉ የተመረጡም አሉ። እግዚአብሔርም: ራሱ ተመራጩ እንደነሳኦል: ይሁዳ: ዴማስ አቋርጦ ካላደነከረ በቀር በሆድ ሳሉ ይመርጣል: በሕፃንነቱም እንደነ

ምዕራፍ 9

ሜ ሮ ን

ሀብተ ሜሮን ከጥምቀት በኋላ በጥምቀት ጊዜ የተቀበልነውን ሀብተ ወልድናና ሀብተ መንፈስ ቅዱስን ለማጽናት የሚሰጥ ምስጢር ነው። ሜሮን ከወንጌልም በፊት የእስራኤል ነገሥታትና ካህናት ይቀቡት ነበር። በሐዲስም የእግዚአብሔር ልጅ ሁኖ ሀብተ ክርስትና ለማግኘቱ ምሳሌ ሁኖ ተሰጧል። በጥምቀት ከእግዚአብሔር የተወለደም ሁሉ ይቀባዋል።

መሠረቱም ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የሚያማልድ የሚያጽናና መንፈስ ጽድቅ ጰራቅሊጦስን እልክላችኋለሁ ያለው የተስፋ ቃል ነው። (ዮሐ. 14:16፤ 26፤ 15፤ 26፤ 16:7)

በመጀመሪያ ይሁን ሀብት የሚሰጡት በአንብሮ እድ ጳጳሳት ነበሩ፡ በኋላ ግን ሜሮኑን ባርከው በእየደብሩ እየላኩ፡ ሥልጣኑን ለቀላውስት ሰጡት።

አሰጣጡም ከጥምቀት በኋላ ስለሆነ የተጠመቁ ሁሉ ዕለቱን የሚቀበሉትም አሉ። አንዳንዶቹ ደግሞ ተጠማቂው ሕፃን የሆነ እንደሆነ ዘግይተው ነፍስ ሲያውቅ፡ ጥምቀቱን በእምነቱ ሲያጸድቅ ይቀቡታል። ለዚህም ሕፃኑ ነፍስ ከማወቁ በፊት ድውይ አይፈውስ፡ ሰሰው አይጸልይ፡ ምን ያደርግለታል? ብለው ይመልሳሉ፡ እንደዚሁም ቁርባንንም ጌታ ለኃጢአት ማስተስረያ ብሎ ነው የሰጠው፡ ቅዱስ ጳውሎስም የጌታ ሥጋ መሆኑን ካላወቀ ነው ያለው፡ ከዐሥራ ሁለት ዓመት በፊት መለየትም ሆነ ኃጢአት መሥራት ስለማይቻል ብለው፡ ከዚያ በኋላ ያደርጉታል።

ምዕራፍ 10

ተ ክ ሊ ል

ከቡር አውሰቦ በኩለሄ=ጋብቻ በማናቸውም መልኩ ክቡር ነው: ክቡር ይሁን ነው ቅዱስ ጳውሎስ ያለው:
በጋብቻ ሁለት ለዎች: ሴትና ወንድ ተፋቅረው አንድነት ለመኖር ሲሰማሙ አንድ አካል የሚያደርጋቸው ሀብተ እግዚአብሔር ተክሊል ይባላል። በዚህ ጊዜ አጋቢው እራሱ እግዚአብሔር: ተጋቢዎች ሁለቱ ጓደኞች የመጭው ባልና ምሽት ሲሆኑ: ቤተ ክርስቲያን ደግሞ በካህናቱ ተወክላ ምስክር ናት። ስለዚህ ከእግዚአብሔር በቀር ለማፋታት ሥልጣን ያለው ማንም የለ: አንድ ሥጋ ናቸው እንጂ ከእንግዲህ ሁለት አይደሉም: እግዚአብሔር ያጣመረውን ሰው አይለይ....ከማመንዘር በቀር ምሽቱን ፈቶ ሌላ ያገባ አመነዘረ እላችኋለሁ (ማቴ. 19:6-9፤ 1ቆሮ. 6:16፤ 7:10-11)
የዚህን ምስጢር ታላቅነት በመንፈስ ቅዱስ እየተመራ የጻፈው ቅዱስ ጳውሎስ በክርስቶስና በቤተ ክርስቲያን መስሎ ተናግሮታል፣...ይህ ምስጢር በጣም ትልቅ ነው፤ እኔ ግን በክርስቶስና በቤተ ክርስቲያኑ እመስለዋለሁ፤ (ኤፌ. 5:21-33)
ስለዚህ በሕገ ቤተ ክርስቲያን በቁርባን በእግዚአብሔር አጋቢነት የተፈጸመ ጋብቻ በማንኛቸውም መልኩ ፍጹም ቅዱስ ነው። የሚንቁትም ሆነ የሚያቃልሉት አላዋቂዎች ናቸው። በድንግልና አንድ ልብ ሁነን አምላካችን እናገልግል ከሚሉ በቀር: ብለው ፅሙዳን ከሚሆኑ በቀር አውሰቦን የሚንቁ ሁሉ ሕገ እግዚአብሔርን ይንቃሉ: አምላካቸውን ያርማሉ። ከዚህም አልፈው ተርፈው: በዚህ ተገናኙ በዚህ ቀን አትገናኙ እያሉ ምእመናንን የሚያሰቃዩማ የሐሳዊ ምህርነታቸውን ፍዳ ያገኝዋታል። እንደሚያገኝዋት ርግጥ ነው። ቅዱሳት መጻሕፍት ለጸሎት ካልሆነ በቀር አትለያዩ ጸሎታችሁን ትጨርሱም ተመልሳችሁ አብራችሁ ተኙ: ስለ ሥጋችሁ ደካማነት ይጣን እንዳይፈታተናችሁ። እንዳታመነዝሩ ሰው ሁሉ ምሽት ትሩፈው፤ በባልዮው አካል ሴቷ፤ በሴቷ አካል ወንዱ ያዝዝ፤ እምቢ ትበባሉ ይላል፤ የእግዚአብሔር ትእዛዝ ይህ ሲሆን: ጋብቻን ማክበድ: እግዚአብሔርን ለማስጠላት ታጥቀው የቆሙ ሐሳውያን ግን ሐሳቸው አውጥተው ለአውሰቦ ቀን አለው እያሉ ያደናግራሉ፤ ታዲያ ንዲህ ካሉት መሸሽ ነው የሚያዋጣውና ንስሐ አባት አለማድረግ ው።(ዕብ. 13:14)

ምዕራፍ 11

ሀብተ ቀንዲል፦

ሕሙም ከደዌ ሥጋና ከደዌ ነፍሰ ወመንፈስ የሚድንበት በዘይት ተጸልዮ የሚቀባ ጸሎት ቀንዲል ይባላል። በዚህም ሕመምተኛ ኃጢአቱን ተናዞ ይደረግለትና ከደዌው ይፈወሳል፥ የሠራውም ኃጢአት ቢኖር ይፋቅለታል። የመሠረተውም ራሱ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው፤ ሌሎቹን ሀብታተ ቤተ ክርስቲያን፤ ጥምቀትን፥ ንስሓን፥ ቁርባንን፥ ክህነትን ወዘተ.እንደመሠረተ ሁሉ፥ የቀሩትማ በወንጌል ይገኛሉ ይህ አይገኝ እንዴት ነው? ለሚል ጠያቂ መልሱ የሚከተለው ነው። ጌታ በወንጌል ያልተጻፈ ብዙ ሠርቷል። ከዚህም በላይ መጻሕፍተ ሐዲሳት የተጻፉት በአጋጣሚ በአንዳንድ ጠያቂ ምክንያት ነው እንጂ በጠቅላላ ጌታ የሠራውን ሁሉ ልጻፍ ተብሎ ዐቅድ ወጥቶ የተጻፉ አይደሉም። (ዮሐ. 21:25)

ጌታ ሐዋርያትን ጠርቶ የግስተግር ሕግ አስጠንቶ፥ አዝዞ በሁለት በሁለት ይልካቸዋል፥ እነሱም እንደታዘዙት እየሄዱ ሲያስተምሩ ድውይ ወይም ሕሙም ጋኔን የያዘው፥ መንፈስ የሚያስጨንቀው ሲያጋጥማቸው በዘይት ጸልየው ያድኑ ነበር፤ ይህንም ለእሱ መልሰው ዘገባውን ገልጠዋል።

...እነሱም ከዚያ ወጥተው ሰዎች ሁሉ ንስሓ እንዲገቡ አስተማሩ ብዙ አጋንንትንም አስወጡ፥ ብዙ ሰዎችንም ዘይት እየቀቡ ፈወሱ (ማር. 6:7-13)

የዚህን ምስጢር (ሀብት) ፍርጥ አድርጎ የነገረን ሐዋርያው ያዕቆብ ነው። እንዲህ ብሎ ከእናንተ መካከል ችግር የደረሰበት ሰው ቢኖር ይጸልይ፥ ደስ ያለው ሰውም ቢኖር እግዚአብሔርን በማመስገን ይዘምር። ከእናንተ መካከል የታመመ ሰው ቢኖር የቤተ ክርስቲያንን ቀሳውስት (ሽማግሌች) ወደሱ ይጥራ እነሱም በሽተኛውን በጌታ ስም ዘይት ቀብተው ይጸልዩለት። እንዲህ ዐይነቱ በእምነት የተመሠረተ ጸሎት በሽተኛውን ያድነዋል፥ ጌታም ከበሽታው ይፈውሰዋል፥ የሠራው ኃጢአትም ይቅር ይባልለታል። ስለዚህ እንድትፈወሱ ኃጢአታችሁን እርስበርሳችሁ ተናዘዙ፥ እያንዳንዱም ለሌላው ይጸልይ የጻደቅ ሰው ጸሎት ብዙ ኀይል አላትና (ያዕ. 5:13-16) እንዳንድ ሰዎች ይህ ሀብት (ምስጢር ቀንዲል) መደረግ ያለበት በጊዜ ሞት ወይም በሞት ዋዜማ በሕይወት መጨረሻ ነው ይላሉ፥ መጽሐፉ ግን ሰው ሲታመም ቀሳውስትን ይጥራ እነሱም ይጸልዩለት ስለሚል ባስፈለገ ጊዜ ሁሉ ማድረግ ይቻላል።



ለኛ ዱሚል ጸልዮአልም (ማቴ. 4:1-11: ዮሐ. 17:1-26)

ምዕራፍ 12

ጸምና ጸሎት፥ ምጽዋት፥ በአጠቃላይ

ከመንፈስ ቅዱስ የጌታችን ሥራ የቀደመበቱ ምክንያት፥ አንደኛ ጌታችን ሥጋ ለብሶ የሠራውን ሥራ ለማከታተል፥ ሁለተኛ ደግሞ መንፈስ ቅዱስ ጌታ የሠራውን ሥራ ሁሉ ፈጻሚና አስፈጻሚ ስለሆነ፥ ሦስተኛው ደግሞ ጌታችን የድኀነት ሥራ ፈጽሞ፥ ተሰቅሎ፥ ሙቶ፥ ተነሥቶ ካረገ በኋላ ተልኮ የመጣ ስለሆነ የሥሉስ ቅዱስ የድኀነት ሥራ ፈጻሚና የቤተ ክርስቲያን ጠባቂ በመሆኑ በመጨረሻ ሁኗል።
ጸም፥ ጸሎት፥ ምጽዋት ከጌታ በፊትም በመላው ዓለም ይልቁንም በቤተ እስራኤል ነበሩ። ግንኛቸውም ሕዝብ ሲቸግረው ይጸግል፥ ለእየአምላኩም ይጸልያል። ለዚህስ ለቁጥር የሚያስቸግር መጥቀስ ይቻላል። ከጌታ በፊት የነበረው አፍአዊ፥ የጌታው ውስጣዊ፥ የእስራኤሉ ግብዝ፥ የጌታው ግን ሐቅ በመሆኑ ነው። ጸሐፍት ፈሪሳውያን ሲጸሙ ፊታቸውን ያጨማድዱ፥ እመድ ይለብሱ፥ ይመስሉ ነበር፥ ጸሙ እንዲባሉ። ሲጸልዩ ደግሞ ሰው በተሰበሰበበት በቤተ መቅደስ ዙሪያ ወይም ምኩራብ ያለዚያም ከመስቀለኛ አውራ መንገድና ከማዕዘን ላይ ቁመው ነበር። ድጋማቸውን ሲያጅጎደጉዱ፥ ጻዊታቸውን ሲደግሙ በተቻለ መጠን ብዙ ሰው ማየት አለበት። ምጽዋት ሲሰጡ ደግሞ ዛሬ እቶ እገሌ ምጽዋት ይሰጣሉ ተብሎ በዘመኑ መገናኛ ተነግሮ፥ እምቢልታ ተነፍቶ፥ ነጋሪት ተመቶ መሆን ነበረበት፥ አለበት፥ አሁንም በአየምኩራቡ እንዲህ ያደርጋሉ። (ይቺንስ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ሕዝብም ይወዳታል፥ በቦታው ትታያለች) ምክንያቱስ ቢሉ ሰው አላያቸውም ነበርና ነው። ስለዚህ አምላክ ውላጣዊ ልብን የሚመረምር እንጂ አፍአዊ አለመሆኑን ለማስረዳት ግብዝነትንም ለመዋጋት የሚከተለውን ዐውጅዋል። ማቴ. 6:1 ሰውም ትታዩ ዘንድ፥ ምጽዋታችሁን በፊታቸው እንዳታደርጉ ተጠንቀቁ፥ ያለዚያ በሰማያት ባለው አባታችሁ ዘንድ ዋጋ የላችሁም። 2 እንግዲህ ምጽዋት ስታደርግ ግብዞች በሰው ዘንድ ሲከበሩ በምኩራብ በመንገድ እንደሚያደርጉ፥ በፊትህ መለከት አታስነፋ፥ እውነት እላችኋለሁ ዋጋቸውን ተቀብለዋል። 3:4 አንተ ግን ምጽዋት ስታደርግ ምጽዋትህ በስውር እንዲሆን ቀኝህ የምትሠራውን ግራህ እትወቅ በስውር የሚያይ አባትህም በግልጥ ይሰጥሃል። 5 ስትጸልዩም እንደ ግብዞች እትሁኑ፥ ለሰው ይታዩ ዘንድ በምኩራብና በመንገድ ማዕዘን ቁመው መጸለይን ይወዳሉና፥ እውነት እላችኋለሁ ዋጋቸውን ተቀብለዋል። 6 አንተ ግን ስትጸልይ ወደ እልፍኝ ግባ፥ መዝጊያህንም ዘግተህ በስውር ላለው አባትህ ጸልይ፥ በስውር የሚያይ አባትህም በስውር ይሰጥሃል።

7 አሕዛብም በመናገራቸው ብዛት የሚሰሙ ይመስላቸዋልና ስትጸልዩ እንደእነሱ በከንቱ አትድገሙ። 16 ስትጦሙም እንደ ግብዞች አትጠውልጉ፥ ለሰዎች ጾመኛ መስለው ለመታየት ፊታቸውን ያጠወልጋሉና፥ እውነት እላችኋለሁ ዋጋቸውን ተቀብለዋል። አንተ ግን ስትጸም በስውር ላለው አባትህ እንጂ ጾመኛ መስለህ ለሰዎች እንዳትታይ ራስህን ተቀባ ፊትህንም ታጠብ፥ በስውር የሚያይ አባትህም በግልጥ ይሰጥሃል።

በዚህም አምላክ በስውር የምንሠራውን ሁሉ የሚያይ ልቡና ያሰበውን፥ ኩላሊት ያመላሰሰውን የሚያውቅ መሆኑን አስረድቷል። አይሁድ ምጽዋት ሲመጸውቱ ምስክር ያጡ እንደሆነ ከእሑድ እስከ ቅዳሜ በመንገድም ሆነ ከቤታቸው የሰጡትን ቅዳሜ ከቤተ መቅደስ ወይም ከምኩራብ፥ ድምፀ መልካም ሰው ተመርጦ ያ እያዜመ አንድ ባንድ ድኃ አግኝቼ ስለአምላክ ሙሴ ላንዲት ምስኪን መበለት አንድ ብር ሰጥቻለሁ እያለ በጆሮው ለተመሪው ይነገረዋል፥ እሱም ያዜምለታል፤ ይጮኽለታል። ጸሎቱና ጾሙም እንዲሁ ነው። የእኛን ባለቅኔና ተመሪ ይመስላሉ። የኛስ መሪና ተመሪ ከዚያ እንደሆነ የመጣ ግን ያውቃል?

ጌታችን ማስተማር ከመጀመሩ በፊት ከሥራ በፊት ጹሙ ጸልዩ ለማለት እንደ ተጠመቀ፥ ተጠምቆ ጹሟል፥ ጸልዮአል፥ ይህንም ለእርእያ። ጸምና ጸሎት አይለያዩም የሚጸም ይጸልያል፥ ሁልጊዜም ባይሆን በተወሰነ ጊዜ የሚጸልይ ይጾማል። የእሱን ዱካ ተከትለን ጸምን እናስቀድማለን።

ጸ ም

እንደ ብዙ እብያተ ክርስቲያናት ከዚህ እስከዚህ ብሎ ወስኖ ባይሆንም ጾምን በግብርም በትምህርትም ሠርቷል። በግብር ከላይ እንደተባለው እርባ መዓልት እርባ ሌሊት ሰው ከግይደርስበት ገዳም ገብቶ እኹን ከዘረጋ ሳያጥፍ፥ ከቆመ ሳያርፍ ጹሟል። በዚህም ለይጣንን ፊታኹን በትዕቢት፥ በሥሥት፥ በፍቅረ ንዋይ ድል ነሥቷል። ድል ከነሣ በኋላ መላእክት መጥተው ተልከውታል። ይህም እብዛኛው ሥራው ለእርእያ ነውና እናንተም በጸም በጸሎት ጸላኤ ሠናያትን (ለይጣንን) ድል ብታደርጉ መላእክት ይቀርቧችኋል፥ ይላኳችኋል ለማለት ነው።

ከዚያ ወዲያ ኢየሱስ ከዲያብሎስ ሊፈተን በመንፈስ ወደምድረ በዳ ተወሰደ፥ እርባ ቀንና እርባ ሌሊትም ከጸመ በኋላ ተራበ... ። (ማቴ. 4:1:1-11፤ ማር. 1:12:13፤ ሉቃ. 4:1-13)

ሰአርአያ የዚህ በላዩ ሲሆን፥ በቃል ደግሞ፥ ብዑዓን አሰ ይርጎቡ ወይጸምው በእንተ ጽድቅ አስመ እሙንቱ ይጸግቡ ሰለጽድቅ የሚራቡና የሚጸሙ ብዑዓን ናቸው። ከዚህ ላይ ስለጽድቅ የሚራቡ የሚሰውን ጽድቅን የሚራቡ ብለው ጸም የማይወዱ ሰዎች አጣመው ይተረጉሙታል፤ አሱም የተሳበው በግሪክ ተሳቢ (ኤትያቲኪ) ስለሆነ ነው። ተሳቢ በግሪክ ልክ እንደኛ እነዳግርኛና ግዕዝ ብዙ ልዩ ልዩ ትርጉም አለው፤ ን፣ ል፤ በ፤ ስለ፣ ጋራ፤ ወደ። ሰምሳሌ ሐጸበ እግሮ=እግሩን አጠበ ን፤ ዘበጦ በትረ በብትር መታው። አምላክ ሞተ ሰብአ አምላክ ስሰለው ሞተ። ሐረ እኅሁ መወንድሙ ጋራ ሄደ። ዐርገ ደብረ ወደ ተራራ ወጣ። በከየት እኅሃ። ተሳቢ በአግርኛም እንደዚሁ ያገለግላል፤ ልብሱን ሰበሰ። ዘመዱን ጠየቀ። ሀገሩን ሄደ። ጠሙን ዋለ። ዕራቁቱን ነው። መድኀኔ ዓለምን ይዘክራል። ብቻውን ሄደ...ወዘተ።

ከዚህ በቀር የተቀረውን አብዛኛውን በተሳቢ (ኤትያቲክ) የተጻፈውን በን ብቻ ሳይሆን በልዩ ልዩ አገባብ ነው የሚተረጉሙት፥ ሰምሳሌም፥ አንተ ግብዝ አሰቀድመህ ከዐይንህ ምሰሶውን አውጣ ከዚያም በኋላ ከወንድምህ ዐይን ጉድፉን ታወጣ ዘንድ አጥርተህ ታያለህ። ከዚህ ላይ አሰቀድመህ በአግርኛ በግዕዝ ቅደመ ተብሎ የተተረጎመው በግሪክ በተሳቢ መጀመሪያን ተብሎ ነው የተጻፈው። (ማቴ. 7:5) ዕለት ዕለትም (ቀኑን፥ በቀን ቀናቹን) በመቅደስ ያስተምር ነበር፥ ሌሊት (ሌሊቱን፥ ሌሊቶቹን) ግን ደብረ ዘይት ወደሚባል ተራራ ወጥቶ ያድር ነበር። (ሉቃ. 21:37)

ተገበሩ እንከሰ አኮ ለመብልዕ (ዘይጠፍእ) ኀላፊ አላ ሰመብልዕ ዘይነብር ለሕይወት ዘለዓለም ለሚጠፋ (ለኀላፊ) ምግብ ሳይሆን ለዘለዓለም ሕይወት ለሚሆን ምግብ ሥሩ። ከዚህም ላይ የተጻፈው በተሳቢ ነው፤ እኒያ ጸምን የሚጠሉ ሰዎች ታማኝና በያዙት መንገድ የሚገፉ ቢሆኑ ኑሮ አሁንም የማትጠፋ ምግብን ሥሩ ማለት ነበረባቸው። (ዮሐ. 6:27) ወኢያእመሩ ከመ በእንተ አብ ይቤሎሙ ስለ አብ እንደነገራቸው አላወቁም፤ ከዚህም አብን እንደነገራቸው አላወቁም ማለት ነበረባቸው። (ዮሐ. 8:27)

አንተ ግን ነህ አሉት፥ ኢየሱስም በመጀመሪያ የነገርኋችሁ ነኝ አላቸው፥ ከዚህም መጀመሪያን የነገርኋችሁ ነኝ ማለት ነበረባቸው፤ (ዮሐ. 8:25)

የእግዚአብሔርን ጽድቅ ሳያውቁ በራሳቸው ጽድቅ ሊቆሙ ሲፈልጉ ለእግዚአብሔር ጽድቅ አልተገዙም። ከዚህም የራሳቸውን ጽድቅ ሊቆሙ ነው እንጂ በ አይደለም። (ሮሜ 10:3) ወኢትኅፈር እንከ

በእንተ ስምዑ ወኢታስጎፍረኒ ኪያየ ሙቁሐ እንግዲህ በጌታችን ምስክርነት ወይም በእስረኛው በእኔ አትፈር። አሁንም የጌታችንን ምስክርነት ወይም እኔን እስረኛውን አትፈር ነበር (2ጢሞ. 1:8)
ከሁሉም በፊት ወንድሞቼ ሆይ በሰማይም ቢሆን በምድርም ቢሆን በሌላም መሐላ ቢሆን በምንም አትማሉ። ከዚህም ሰማይንም ቢሆን ምድርንም ቢሆን ሌላም ማንኛቸውንም መሐላ አትማሉ ነበር። (ያዕ. 5:12)
ዘኮነ ስምዐ በእንተ ቃለ እግዚአብሔር ወበእንተ ስምዑ ለኢየሱስ ክርስቶስ ወበእንተ ኩሉ ዘርእየ=አሱም ለእግዚአብሔር ቃልና ለኢየሱስ ክርስቶስ ምስክር ላየውም ሁሉ መሰከረ። ከዚህም በተሳቢ ቢተረጎም ኑሮ የእግዚአብሔርን ቃልና የኢየሱስ ክርስቶስን ምስክር ያየውንም ሁሉ መስከረ ይሆን ነበር። (ራእ. 1:2)
ወሶበ ጸርሐ ተናገሩ ሰብዓቱ ነጎድጓድ በበ ቃላቲ ሆሙ=በጮኸም ጊዜ ሰባቱ ነጎድጓድ በእየቃላቸው ተናገሩ። ይህም ቃላቸውን ተናገሩ ነበር። (ራእ. 10:3)
ለመረጃም ያህል የተጠቀሰው ይበቃል እንጂ: እንደ ልማዴ ለወረቀት ባልሣሣም ኑሮ ዕጥፍ መጥቀስ ይቻል ነበር። ይህ ሁሉ እያለ ከዚያ ላይ ብቻን ብሎ መተርጎሙ ለምን ይበጃል?? መንፈሳዊ ጎይል የሚገኘውም በጸምና በጸሎት እንደሆነ ተናግሯል። ይህ ዐይነት ግን ከጸሎትና ከጸም በቀር አይወጣም አላቸው። (ማቴ. 17:21)
በሚያስተምርበት ዘመን ቤት ስለሌለው ተከታዩም ብዙ ስለሆነ የተገኘውን እየበላ ሀገር ላገር እየዞረ ያስተምር ነበር: ይህም መንገደኛና: በግዳጅ ላይ ያለ ወታደር: አራስ እይጹም ብሎ ፈቃድ ለመስጠት እንጂ ጸምን ለመሻር አይደለም። የዮሐንስ ደቀ መዛሙርትና የፈሪሳውያን ደቀ መዛሙርት ይጦሙ ነበር። መጥተውም: የዮሐንስና የፈሪሳውያን ደቀ መዛሙርት የሚጸሙት የእንተ ደቀ መዛሙርት ግን የማይጸሙት ስለምንድር ነው? አሉት። ኢየሱስም ሙሽራው ከእነርሱ ጋራ ሳለ ሚዜዎች ሊጸሙ ይችላሉን? ሙሽራው ከእነሱ ጋራ ሳለ ሚዜዎች ሊጸሙ አይችሉም። ነገር ግን ሙሽራው ከእነሱ የሚወሰድበት ወራት ይመጣል: በዚያ ወራትም ይጦማሉ። በዚህም ለሙሽራና ለሚዜ እርባ ቀን መብላት ተፈቅዷል። ግን አንዳንድ ባሕታዊያን ነን ባዮች እኛ ካልበላን ብለው ያደናግራሉ። (ማቴ. 9:14-17: ማር. 2:18-20: ሉቃ. 5:33-39) ጸም መኖሩንና ያልሻረው መሆኑን ለማስረዳትም: ስትጸሙም እንደ ግብዞች አትጠውልጉ: ለሰዎች እንደጸሙ ሊታዩ ፊታቸውን ያጠፉሉና: (ማቴ. 6:16)

<u>ቅዱስ ጳውሎስም</u> ጸም ከትሩፋት አንዱ እንደሆነ፥ ለሁሉም እንደ እግዚአብሔር አገልጋዮች ራሳችንን እናሳጥናለን በብዙ መጽናናት፥ በመከራ፥ በችግር፥ በጭንቀት፥ በመገረፍ፥ በወኅኒ፥ በሁከት፥ በድካም፥ እንቅልፍ በማጣት፥ በጸም፥ በንጽሕና...ብሎ አስተምሯል፤ (2ቆሮ. 6:4-8)

ጸም ጸሎት ምጽዋት ከክርስቶስ በፊት በዘመነ አሪትም ነበሩ። በጸሎት ከፍል እንደምናየው ጸሙ ለይስሙላ፥ ጸሎቱ ድጋሞ፥ ምጽዋቱ ለተርእዮ ነበር። የክርስቶሱ ግን የዚህ ሁሉ ተቃራኒ ሁኖ ከቂም ከበቀል ርቅ፥ የበደሉትን ክሦ፥ የቀሙትን መልሶ፥ ከተጣሉት ታርቆ ነው። በዚህም በኢሳያስ ከተነገረው ጸም ጋራ ይመሳሰላል።

ኢሳ. 58፥ 1፥ በጎይልህ ጩኽ፥ አትቆጥብ፥ ድምፅህን እንደ መለከት አንሣ፥ ለሕዝቤ መተላለፋቸውን፥ ለያዕቆብ ቤትም ኃጢአታቸውን ንገር። 2፥ ነገር ግን ዕለት ዕለት ይሹኛል፥ መንገዴንም ያውቁ ዘንድ ይወዳሉ፥ ጽድቅን እንዳደረጉ፥ የአምላካቸውን ፍርድ እንዳልተው ሕዝብ እውነተኛውን ፍርድ ይለምኑኛል፥ ወደ እግዚአብሔርም ለመቅረብ ይወዳሉ፤ 3፥ ስለምን ጸምን አንተም አልተመለከትኽንም? ሰውነታችንንስ ስለምን አዋረድን? እንተም አላወቅኽም? ይላሉ። እነሆ፥ በጸማችሁ ቀን ፈቃዳችሁን ታደርጋላችሁ፥ ሠራተኞቻችሁን ሁሉ ታስጨንቃላችሁ፤ 4፥ እነሆ ለጥልና ለክርክር ትጸማላችሁ፥ በግፍ ጡንቻም ትማታላችሁ፥ ድምፃችሁንም ወደ ላይ ታሰሙ ዘንድ፥ ዛሬ እንደምትጸሙት አትጸሙም፥ 5፥ እኔ የመረጥሁት ጸም ይህ ነውን? ሰውስ ነፍሱን የሚያወርደው እንደዚህ ባለ ቀን ነውን? በጪኑ ራሱን እንደ ግራምጣ ዝቅ ያደርግ ዘንድ ማቅና አመድም በበታቹ ያነጥፍ ዘንድ ነዉን? በጪኑ ይኽን ጸም በእግዚአብሔር ዘንድ የተወደደ ቀን ነው ትለዋለህን? 6፥ እኔስ የመረጥሁት ጸም ይህ አይደለምን? የበደልን እስራት ትፈቱት ዘንድ፥ የቀምበርንስ ጠፍር ትለቁ ዘንድ የተገፉትንስ አርነት ታወጡ ዘንድ፥ ቀምበሩንስ ሁሉ ትሰብሩ አይደለምን? 7፥ እንጀራንስ ለተራበ ትቆርሱ ዘንድ፥ ስደተኞቹን ድኆች ወደ ቤትህ ታስገባ ዘንድ፥ የተራቆተውንስ ብታይ ታለብሰው ዘንድ ከሥጋ ዘመድህ እንዳትሸሸግ አይደለምን? 8፥ የዚያን ጊዜ ብርሃንህ እንደ ንጋት ይበራል፥ ፈውስህም ፈጥኖ ይበቅላል፥ ጽድቅህም በፊትህ ይሄዳል፥ የእግዚአብሔርም ክብር በኋላህ ሁኖ ይጠብቅሃል፥ የዚያን ጊዜ ትጠራለህ፥ እግዚአብሔርም ይሰማሃል።

ጌታ እንዲህ አድርጎ በጠቅላላ ጸምን አዝዟል፤ የጸምን ጊዜ የወሰኑ ግን በጎብረት ለመጸም እንዲመች የቤተ ክርስቲያን አባቶች ናቸው።

በፍትሐ ነገሥቱ ክርስቲያን ሁሉ እንዲጾመው የታዘዘው አርባው ቀን፡ የጌታው፡ ዐቢይ ጾም የሚባለው ነው። ቤተ ክርስቲያን በመስነቻቸው አጻዋማት ወቅት፡ ሕመምተኛ፡ ሐራስ፡ መንገደኛ በግዳጅ ላይ ያለ ወታደር ሙሽራና ሚዜዎቹ አይገደዱም፡ አይጠየቁም።

ከዚህ የቀረውን ስለጾም ዝርዝር ከደራሲው ሠርግና ልግድ በሚል ርእስ ገጽ 48 የተሰጠውን ያነቧል።

ጾምና ጸሎት እንደ ጌታ ፈቃድ የተደረጉ እንደሆን ያለምንም ጥርጥር የዚህ በላዩን ቃል ኪዳን ያስፈጽማሉ። ረድኤተ እግዚአብሔርም ያሰጣሉ።

ምዕራፍ 13

ጸ ሎ ት

ከዚህ በፊት እንደተነገረው፡ ጹሞ፡ ጸልዮ፡ ሰምኖ፡ መጽውቶ፡ ንስሓ ገብቶ ከአምላኩ ስርየተ ኃጢአት፡ ረድኤት ከዚህም በላይ ማንኛቸውንም መልስ የሚፈልግ ሁሉ፡ መጀመሪያ ከቂም በቀል መራቅ፡ የበደለውን መካሥ፡ የወሰደው የሰው ገንዘብ እንዳለ መመለስ፡ ከተጣላው መታረቅ አለበት። ለምን ቢሉ ጌታ የቂመኛን ጸሎትና ንስሓ፡ ልመና እይቀበልምና ነው። ይህንም ጌታችን ፍርጥርጥ እድርጎ ተናግሯል። ከዚህ በፊት በተጠቀሰው በኢሳያስም ተገልጧል። እንኳንስ ለምኖ ለማግኘት፡ ቆርቦ ለመጽደቅ ይቅርና፡ ቂም ይዞ ለቤተ ክርስቲያን መባ መስጠትም ክልክል ነው።

እንግዲህ መባህን ከመሠዊያው ላይ ስታቀርብ፡ ወንድምህ እንዳች ነገር ባንተ ላይ እንዳለው ትዝ ቢልህ፡ በመሠዊያው ፊት መባህን ትተህ ሂድና አስቀድመህ ከወንድምህ ጋራ ታርቀህ፡ መጥተህ መባህን አቅርብ።

መባ ለመስጠት እንኳ ቂም ሲከለክል፡ እንዴት ሁኖ ነው የቂመኛ ጸሎት ከአምላክ ቸር መልስ የሚያስጠው? (ማቴ. 5:24)

ለሰዎች ኃጢአታቸውን ይቅር ብትሉ፡ የሰማዩ አባታችሁም እናንተን ደግሞ ይቅር ይላችኋል፡ ለሰዎች ግን ኃጢአታቸውን ይቅር ባትሉ ሰማያዊ አባታችሁም ኃጢአታችሁን ይቅር አይላችሁም፡ (ማቴ. 5:14-15)

በእናንተ ሁለቱ በምድር በማንኛቸውም በሚለምኑት ነገር ቢስማሙ በሰማያት ካለው ከአባቴ ዘንድ ይደረግላቸዋል። ሁለት ወይም ሦስት በስሜ በሚሰበሰቡበት በዚያ በመካከላቸው እሆናለሁ። (ማቴ. 18:19-20)

ጸሎት መልስ፡ ረድኤት፡ ጸጋ፡ ስርየተ ኃጢአት የሚያሰጠው በጌዶ ነው። ጌዶውም ፍቅር ነው፤ ይህንም ከዚህ በላይ የተጠቀሱት ጥቅሶች ያስረዳሉ። ቂም ይዘህ መባህን እልቀበልም እያለ፡ የሰው ሞኝ ራሱን እያታለለ፡ የአርባ ዓመት ቂም ይዞ ፈጣሪውን በአፉ ይለምናል። ፈጣሪ ግን የልብ ያውቃልና አይመልስም። ጸሎት፡ መጀመሪያ መታረቅና መስማማት ይፈልጋል። ተስማምቶም የማጎበር ጸሎት የሆነ እንደሆነ ዛሬ ወይም በዚህ ሳምንት ፈጣሪን የምንጠይቀው ስለዚህ ነው ተብሎ መወሰን አለበት፡ ያለበለዚያ ግን ዓላማውን አይመታም። ዓላማ የለውምና። ለዚህም ትኩስ ምሳሌ መስጠት ይቻላል፡ ለውጡ ከወደቀ ወዲህ ሰው ወደ እግዚአብሔር ተመልሶ፡ ወደ ቤተ ክርስቲያን መጥቶ ሥራውን ትቶ፡ ስለ እግዚአብሔር አስተምሩን ይላል። ካህናቱ ደግሞ

የወደቀው መንግሥት የውስጥ አርበኞች ሁነው የተቀጠሩ ይመስል፡ ወንጌልን እንዳያስተምሩ በምሕላ ጊዜውን ያሳልፋታል። ይህን የውጭ ተንኮልና ቂማቸውን ትተው፡ አሁን ድርቅ ጠንቶ፡ ህገሯ በችግር ላይ ናት፣ ስለዝናም ቢግለሉ ኑሮ ዶልዷሌው አምላክ በእያገሩ እንደሚያዘንም አይጠረጠርም። የምሕላው ዓላማ ስላልተነገረ፡ አንዱ አበበ በድሎኛልና ግደልልኝ፡ ሁለተኛው ደግሞ ገብረ ክርስቶስ ነው፡ የሰጠሽኝን አትንሣኝ፡ አሳይተህ አትቀማኝ፡ ሦስተኛው ደግሞ ምሽቴ በድላኛለች የእጅዋን ስጣት (ኧረ ስንቱን) ሲሉ አምሽተው ይለያያሉ። ይህስ በምን ይታወቃል? ታወቀ? ለሚል ጠያቂም፡ ዓላማና አንድነትማ ቢኖረው አስካሁን መልሱ መጥቶ እናየው ነበር ብሎ ይመልሷል።

ከሁሉም ለመዳን የመሪያችንን የመድኀኒታችንን የጌታችንን ጸሎት እንመልከት፤ የጻሐፍት ፈሪሳውያንን ጸሎት አለመጥቀም ከተናገረ በኋላ እንናንተስ ስትጸልዩ እንዲህ በሉ አለ፤ በሰማይ የምትኖር አባታችን ሆይ! ስምህ ይቀደስ መንግሥትህ ትምጣ ፈቃድህ በሰማይ እንደሆነች እንዲሁም በምድር ትሁን፤ የዕለት እንጀራችንን ስጠን ዛሬ፤ እኛ የበደሉንን ይቅር እንዳልን (ግዕዙም ከመ ንሕነኒ ጎደግነ ለዘአበሱ ለነ ነው መሆን ያለበት) በደላችንን ይቅር በለን ከክፉም አድነን እንጂ ወደፈተናም አታግባን፡ መንግሥት ያንተ ናትና ኀይል ምስጋናም ለዘለዓለሙ፡ አሜን።

አባታችን ሆይ! የተጻፈው በብዙ ነው፡ አንዱ ስለሌላው ይጸልያል፡ ይለምናል፡ ያግልዳል። ይህም ፍቅር ከሌለ ስለግይሆን አባታችን ከግለት በፊት ቂምን ግራቅ ያስፈልጋል። በተቀረ የሽኮከ ጸሎት፡ ያህያ ጩኸት ይሆናል። እኛ የበደሉንን ይቅር እንዳልነ አንተም በደላችንን ይቅር በለን ነው የሚባለው፡ ይህም በደፈናው ሳይሆን ስም ጠርቶ፡ ራስ ቆርጦ፡ ገብረ ክርስቶስን፡ አቶ ወልደ ገብርኤልን፡ አመተ ኢየሱስን እንደ ግርሁ እያሉ ነው። እንደ ጻሕፍት ፈሪሳውያን ይጸልያል ለመባል የሚፈልግ ዝም ብሎ ሊያነበንብ ይችላል። ክርስቶስን ተቀብያለሁ፡ ለጸሎቴም መልስ እፈልጋለሁ የሚል ግን ትእዛዙን ግክበር አለበት።

ጸሎት ምስት ክፍል አለው፡

ስብሐት፡ ልመና፡ ምስጋና፡ ሁሉም በአባታችን ውስጥ ተሰጥቷል። ስብሐት ይህን ዓለም የፈጠርህ የሰማይ አባታችን! እኛንም ስምህን እንድንቀድስ መንግሥትህን እንድወርስ ስለፈጠርኸን እናመሰግንሃለን። ፈጥረህም በዝናም አብቅለህ፡ በፀሐይ አብስለህ

ስለምትመግበን እናመሰግንሃለንን የመሰለ፤ ልመና ደግሞ በሀገራችን ዝናም ጠፍቷል፥ ችግር በዝቷል፥ ፈተና ጠንቷል፥ ከዚህ ሁሉ አድነን ተብሎ። ምስጋና ደግሞ በቅርቡ የተፈጸመ ነገር እያስታወሱ አኩቴት ማቅረብ ነው።

<u>ጊ ዜ</u>፥ ከተቻለ ለጸሎት ጊዜ የለውም። ሃያ አራቱን ጊዜ ሁሉ መጸለይ ማመስገንም ይቻላል። (መዝ. 33:1፤ 118:164፤ ሉቃ. 18:1፤ ግብ. 3:1፤ 16:16፤ 25፤ ሮሜ 1:9-10፤ ፊል. 1:4፤ 1ጢሞ. 1:2፤ ሉቃ. 21:36፤) እግዚአብሔር የተለየ የቢሮና የጽሕፈት ቤት፥ የማስተናገጃ ሰዓት የለውም፤ መሥሪያ ቤቱ ሁል ጊዜም ክፍት ነው።

<u>ቦ ታ</u>፥ ለጸሎት ቦታ የለውም፥ የትም ሁኖ መጸለይ ይቻላል፤ በቤተ መቅደስ፥ በቤት፥ ሰው በማይደርስበት ብቸኛ ቦታ።

በዘጠኝ ሰዓት ጴጥሮስና ዮሐንስ ለጸሎት ወደ ቤተ መቅደስ ወጡ። መቅደስ አሁን ቤተ ክርስቲያን መሆኑ ነው። (ግብ. 3:1-10)

ጌታም በእየጊዜው ወደ ቤተ መቅደስ እየሄደ ያስተምር ነበር። እንደ ተጠመቀ ወዲያው ወደ ገሊላ ተኛ ቦታ ወደ በረሃ ሂዶ ነው የጸመው፥ የጸለየው። በቃሉም ከሳምራዊት ጋራ ባደረገው ቃለ ምልልስ አስረድቷል፤ (ዮሐ. 4:20-25) ዘወትርም ወደ ደብረ ዘይት እየወጣ ሲጸልይ ያድር ነበር። (ማቴ. 14:23፤ ማር. 1:35፤ 6:46፤ ሉቃ. 5:16፤ 6:12)

ጸሎት በግልም በማኅበርም ሠርቷል፤ ይህም በቤተ መቅደስ፥ በቤት እንደሱ በበረሃ፥ በገዳም፥ በተመቸ ቦታ ሁሉ ሊደረግ ይቻላል፤ (ማቴ. 6:5-6)

<u>እንዴት ነው የሚጸለየው</u>?

አፍ ተልብ ከሆኑ ቁምም፥ ተምበርኮም፥ ተቀምጠም፥ በግራ ጎድን ተጋድሞም በማንኛውም ተደፍቶም መጸለይ ይቻላል፤ (ማቴ. 26:36-39፤ ሉቃ. 18:9-14፤ 1ነገ. 8:9-28)

<u>ጸሎትና ድጋም የተለያዩ ናቸው</u>፤ ድጋም የቀድሞ ሰዎች ደርሰው የጻፉትን ቢገባም ባይገባም፥ ብዙ ጊዜ፥ ብዙ ሰዎች እንደሚያደርጉት፥ አፍ የሚለውን ልቡና ባይሰማም አስምቶም ሆነ ሳያስሙ ማነብነብ ነው፤ ለዚህም ዳዊት እደግማለሁ፥ ውዳሴ ማርያም አደርሳለሁ ወይም እደግማለሁ፥ አቁጣሮ አደርሳለሁ ይባላል። ጸሎት ግን ከእግዚአብሔር ጋራ መነጋገር ስለሆነ፥ ቁም ወይንም ተምበርኮ የሚፈልጉትን እንደ ሰልክ ደዋይ ለፈጣሪው መንገር ነው።

ምዕራፍ 14

ንስሓ

ንስሓንም አሳምሮ ሠርቷል። ንስሓ ማለት በበደለው ሥራ ተጠጥቶ መመለስ ነው። ንስሓ ከጌታ በፊት በአሪትም ነበረ። ብቻ እንደ ጌታው በበደሉ ቁጥር አልነገረም። በአሪት ይቅርታ የሚገባው በብዙ ድካም ሲሆን፥ አሁንም የረበናት ተከታዮች አንዳንድ ያልተግሩ ካህናት እንደሚሉት ሳይሆን፥ የጌታው በድያለሁ ማረኝ ካለህ ይቅር በለው ነው። ሐዋርያት ሲሾሙ፥ ድውይ ፈውሱ፥ ለምጣም አንጹ፥ ሙት አንሡ ስለተባሉና እንደነ ኤልያስ ከሰማይ አሳት አውርዶ ጠላትን ግቃጠል፥ እንደ ኤልሳዕ ድብ ጠርቶ ባለጌ ሕፃናትን የማስጨረስ ሥልጣን ስለተሰጣቸው፥ ደስ ሲላቸው፥ ጌታ ግን አሁንም አሁንም ወንድምህ በድሎህ፥ ተጸጽቶ፥ ይቅርታ ቢጠይቅህ፥ ከጠየቀህ ይቅር በለው እያለ አስቸገራቸው፤ እነሱም ጠይቀን እንረዳ ብለው ተማከሩ፥ ተማክረውም አልቀሩ በቅዱስ ጴጥሮስ አፈ ጉባኤነት፥ ዐሥር፥ ዐሥራምስት፥ ካያ ጊዜ ብለው ቢጠይቁ አምን የሚል ስለመሰላቸው ፍጹምነት ባለው ለማስደንገጥ በሰባት ይጠይቁታል። ሰባት በእነሱ ፍጹም ነው፥ ዘለዓለም፥ ሁልጊዜ ማለት ነው፥ ወሰን የለውም፤ ከዚህ ታች ባለው ጥቅስ እስከ ሰባት ጊዜ? ብሎ ሊያሰደነግጠው ይምክራል። ጌታ ግን በአሪት ማንኛቸውም ነገር በሁለት ወይም በሦስት ምስክር ይቁም በሚለው ሕግ ተጠቅሞ ጴጥሮስ ለማስፈራራት ያቀረበውን ሰባት ሦስት ጊዜ መላለሶ ተናግሮ ለንስሓ ቁጥር ይሉ ወሰን እንደሌለው አድርጎ መልሶለታል። በዚህም ይቅር ብሎ መጠየቅ እንጂ ረበናት እነደሚያደርጉት ቁድር ይሉ የንስሓ ጸም እንደሌለ አንረዳለን። ለዚህም ከዚህ በታች የተጠቀሱትን መላልሶ አንቦ ይረዷል።

በዚያን ጊዜ ጴጥሮስ ወደ እሱ ቀርቦ፥ ጌታ ሆይ! ወንድሜ ቢበድለኝ ስንት ጊዜ ልተውለት? እስከ ሰባት ጊዜ? አለው። ኢየሱስም እንዲህ አለው፥ እስከ ሰባ ጊዜ (እስከ ሰባ ሰባት ጊዜም የሚል አብነት አለ) ሰባት እንጂ እስከ ሰባት ጊዜ አልልህም ብሎታል። (ማቴ. 10:1፤ ሉቃ. 9:1፤ 17:4፤ 9:51-56፤ ማቴ. 18:21-22)

በዚህም ከልብ ተጠጥቶ መመለስ እንጂ ንስሓ አንዳንድ ያልተግሩና ወይም ጎጋው ሕዝብ የማያውቅ ነው ይለኛል ብለው ፈርተው ይህን ያህል ጹም ያን ያህል ሰገድ ማለት እንዳልሆነ አስተምሯል። ሰው ቢያጠፋ ይመከራል እንጂ ደርሶ አይገዙትም።

ወንድምህ ቢበድልህ፥ ሂደህ አንተና እሱ ብቻችሁን ሁናችሁ ውቀሰው፥ ቢሰማህ ወንድምህን አተረፍህ፥ ባይሰማህ ግን፥ በሁለት ወይም በሦስት ምስክር አፍ ነገር ሁሉ እንዲጸና፥ ዳግመኛ አንድ


ወይም ሁለት ከእንተ ኃራ ውሰድ፡ እነርሱንም ባይሰማ፡ ለቤተ ክርስቲያን ንገራት፡ ደግሞም ቤተ ክርስቲያንን ባይሰማት፡ እንደ አረመኔና እንደ ቀራጭ ይሁንልህ። (ማቴ. 18:15-17፤) ይህም የሚሆነው በፍትሐ ነገሥት እንደ ተጻፈው በሃይማኖት እንጂ በምግባር፡ በዓል ሻርህ፡ ጸም ገደፍህ ተብሎ አይደለም፡ ግዝት ከቦታው ይታያል።

ከዚህ በላይ ጌታ እግዚአብሔር አብ እንዴት ያለ መሐሪ እንደሆነ፡ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስም ለሰው ዘር፡ ይልቁንም ለኃጢአተኛ እንዴት እንደሚያስብ የሚከተሉትን ጥቅሶች ማንበብ ያሻል፤ አንብቦ፡ ተረድቶ፡ በእየጊዜው የሠሩትን ኃጢአት ለካህን እየነገሩ፡ ኃጢአትን ለማስተስረይ ሥጋውን ደሙን ዘወትር እየተቀበሉ ከፈጣሪ ሳይሰዩ መኖር ነው። (ማቴ. 18:1-፤ 21:28-32፤ ሉቃ. 15:1፤ 17:3)

ንስሓ ከገባሁ፡ ከልቤ ከተመለስሁ፡ የልቤን ፈጣሪዬ ያውቀዋል፡ ባቋራጭ ለጎዳጌ ኃጢአት ለኢየሱስ ክርስቶስ ኃጢአቴን ነግሬ ብቆርብሳ? የሚል ጠያቂ ይኖራል፡ ለዚህ ሃይማኖት መታዘዝ እንጂ በትዕቢት ተነፍቶ መፈላሰፍ አይደለም። ሰው በማያውቀው በማይታረም ፈቃዱና ጠባዩ ኃጢአትህን ለካህን ንገር ብሎ እዝዟል ስለዚህ መናገር አለብን።

እውነት እውነት እላችኋለሁ፡ በምድር የምታስሩት ሁሉ በሰማይ የታሰረ ይሆናል፡ በምድርም የምትፈቱት ሁሉ በሰማይ የተፈታ ይሆናል፡ (ማቴ. 16:19፤ 18:18፤ ዮሐ. 21:23)

በኢየሱስ ክርስቶስ ወንድሜ እንባቢ ሆይ! በዚህ መሠረት ኃጢአትህን በካህን ይቅር ከተባልህ ወዲያውኑ ጊዜ ሳትሰጥ በሥጋው ወደሙ ተለቃለቅ፡ እሱም ስዚሁ ተጋድሎ ሲደረግ የተበተነው ከዚህ ቀጥሎ ይቀርብልሃል።


ቁርባን

ምዕራፍ 15

ቁርባን

የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ሕዝብ ስለ ቁርባን ያለው አስተያየት ከቅዱሳት መጻሕፍት ውጭ ነው፥ ለምን? ቢሉ በምን ምክንያት? ወይንም ማን እንደ ጨመረው ሳይታወቅ፥ ቄሱ ሥርዓተ ቅዳሴውን ከጨረሰ በኋላ ሳትበቁ በቅታቸሁ ሳትነቁ ነቅታችሁ ብትቀበሉት ሥጋው እሳት ሁኖ ይበላችኋል፥ ደሙ ባሕረ እሳት ሁኖ ያሰጥማችኋል ብሎ ስለሚያውጅ፥ ሕዝቡ ሁሉ ይሸሻል። ስለዚህም ያልታዘዘላቸው ነፍስ የማያውቁ ሕፃናትና የጃጁ ሽማግሎች ናቸው የሚቆርቡ፥ የሚሰጠው ምክንያትም እነዚህ ሁለቱም ኃጢአት ለመሥራት ስለማይችሉ ነው፤ ጌታ የሰጠው ለኃጢአት ማስተስረያ ብሎ ስለሆነ ዓላማውን ስቷል። ከኃጢአት ንጹሕ ከሆነ መድኃኒት ለምን አስፈለገው? ጅጁ ሽማግሌና ሕፃን እንዲያውም አያስፈልገውም፥ አያስፈልጋቸውም፤ ምክንያቱስ ቢሉ፤ ጅጁ ኃጢአት ስለማይሠራ፥ ሕፃን ደግሞ፥ ቅዱስ ጳውሎስ የጌታ ሥጋ መሆኑን ካላወቀ ደይኑን መቅሠፍቱን በላ ስላለ፥ እንደ ተራ ምግብ ለሚበላው ሁሉ ደይን መቅሠፍት ነውና። ስለዚህ ከ1939 ዓ.ም. ጀምረን ይህ ስሕተት እንዲታረም ብንታገል ቅዱሳት መጻሕፍትን የማይወዱ ሰዎች ከካህናቱም ከሕዝቡም በማስቸገራቸው በእየጊዜው ከተበተኑት ክታባት አንዱንና ለሮሮ ከተጻፉት መወድሶች ጥቂቶችን እናስከትላለን።

ይኸውም ሐምሌ 15 ቀን 1975 ዓ.ም. የተበተነው ነው።

<u>የሕይወት ምንጭ</u>

ጌታችንና መድኀኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው፥

ከ/ቀደሰ/ ዓለማየሁ ሞገስ

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን አንዳንድ ቀሳውስት በቅዳሴ ጊዜ ምእመናኑን በመጥራት ፈንታ ለማባረር፥ <u>ሳትበቁ በቅታችሁ፥ ሳትነጹ ነጽታችሁ</u>... እያሉ የሚያስተላልፉት የሐሰት ለፈፋ ውሸት እንደሆነ ለማስረዳት ሠኔ 21, 1975 ዓ.ም. ከተሰጠው መግለጫ የሚቀጥል ጽሑፍ።

ሐምሌ 15 ቀን 1975 ዓ.ም.

ልዑል ዘለዓለማዊው እግዚአብሔር ለሰው ዘር እንዴት ያለ ፍቅር እንዳለው የሚያስረዱ የቅዱሳት መጻሕፍት ጥቅሶች ባጭሩ፤

1. እናንተ ሸክማችሁ የከበዳችሁ ደካሞች ወደኔ ኑ፥ እኔም አሳርፋችኋለሁ፥ /ማቴ. 11:28/
2. ከኔ ጋር ያልሆነ ጠላቴ ነው፥ ከኔ ጋር የማይሰበሰብም ይበትነኛል። /ማቴ. 12:30፤ ሉቃ. 11:23/

3. እውነት እውነት እላችኋለሁ በእኔ የሚያምን የዘለዓለም ሕይወት አለው፤ የሕይወት እንጀራ (ኅብስት) እኔ ነኝ...። ሥጋዬን የሚበላ ደሜን የሚጠጣ በእኔ ይኖራል፥ እኔም በእርሱ እኖራለሁ፥ /ዮሐ. 6:35-59/።
4. ሲበሉም ኢየሱስ እንጀራ (ኅብስት) ዳቦ፥ አንሥቶ፥ ባርኮ፥ ቁርሰ እንኩ ብሉ፥ ይህ ሥጋየ ነው ብሎ ሰጣቸው፥ ጽዋውንም አንሥቶ ካመሰገነ በኋላ /አመሰግኖ/ እንኩ ይህ ለሰብዙዎች <u>ኃጢአት ማስተሰርያ</u> የሚፈስ የሐዲስ ቃል ኪዳን ደሜ ይህ ነው ብሎ ሰጣቸው /ማቴ. 26:26-28/።
5. የሰው ልጅ የጠፉውን ሊፈልግና ሊያድን መጥቷልና /ሉቃ. 19:10/
6. የሰው ልጅ ነፍሳትን ሊያድን እንጂ ሊያጠፋ አልመጣምና /ሉቃ. 9:56/።
7. ሕመምተኞች እንጂ፥ ጤነኞች ባለመድኀኒትን አይፈልጉትም፥ ኃጢአተኞችን እንጂ፥ ጻድቃንን ልጠራ አልመጣሁም አላቸው፥ /ማር. 2:17፤ ማቴ. 9:12-13፤ 18:11 ሉቃ. 5:31-32:19:10/።
8. እውነት እውነት እላችኋለሁ በእኔ የሚያምን የዘለዓለም ሕይወት አለው፥ የሕይወት እንጀራ እኔ ነኝ /ዮሐ. 6:47-48/።
9. ሙሴ በምድረ በዳ እባብን ሰቀለ፥ እንዲሁም በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘለዓለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፉ፥ እግዚአብሔር አንድ ልጁን እስኪሰጥ ድረስ ዓለሙን እንዲሁ ወዷልና። ዓለም በልጁ እንዲድን እንጂ፥ በዓለም እንዲፈርድ እግዚአብሔር ወደ ዓለም ልጁን አላከምና፥ በርሱ የሚያምን አይፈረድበትም.../ዮሐ. 3:15-18/።
10. የእግዚአብሔር ጸጋ ስጦታ ግን በክርስቶስ ኢየሱስ የዘለዓለም ሕይወት ነው። /ሮሜ 7:23/።
11. ኢየሱስ ክርስቶስ /መሲሕ/ እንደሆነ የሚያምን ሁሉ ከእግዚአብሔር ተወልዷል። /1ዮሐ. 5:1/።

<u>ምን አገባው? እሱ ምንድር ነው?</u>

የኢትዮጵያ ተዋሕዶ አርቶዶክስ ቅድስት ቤተ ክርስቲያን በዓለም ጥሩ ርቱዓተ ሃይማኖት አርቶዶክሳውያት ከሚባሉት አብያተ ክርስቲያናት ነው ቁጥሯ። ምንም በደንብ ተንትኖ የሚያስተምረው አጥቶ ሃይማኖቷንና ሥርዓቷን ተራው ሕዝብ አይወቀው እንጂ፥ ላወቀው በጣም የሚያኮራ ነው። እኔም በቅኔና በመጻሕፍተ ሐዲሳት ትርጓሜ ከተመረቅሁ በኋላ አራቱን ዐበይት ነቢያትን፤ ሔኖክን ዳዊትን

ከብሉያት አሂጃለሁ፥ ይህንም በጥባኤ ያሄድሁትን ግለቴ ነው እንጂ በግዕዝ የተጻፈ መንፈሳዊ መጽሐፍ ሁኖ ያላነበብሁት ያለ አይመስለኝም። በዘመናዊው ትምህርትም፥ በቋንቋና በታሪክ በሥነ መለኮት ሁለት ድግሪዎች አግኝቼ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የቅኔ፥ የግዕዝ፥ የአግርኛ መምህር ሁኜ ኑሪአለሁ። በቋንቋም በኩል ግዕዝ፥ አግርኛ፥ እንግሊዝኛ፥ ፈረንሳይኛ፥ ጣልያንኛ፥ ግሪክ እናገራለሁ፥ እጽፋለሁ፥ ዐረብኛ፥ ዕብራይስጥ፥ ላቲን አነባለሁ። ይህም የመንፈሳዊውን ትምህርቴን በደንብ እንድረዳና እንዳስተውል ረድቶኛል፥ ይረዳኛል። ከሥጋዊው ሥራዬ ሌላ ቅዳሜ ከሰዓት በኋላና እሑድ እሑድ ከ30 ዓመት በላይ መንፈሳዊ ትምህርት በሰብከት መልክ አስተምሬአለሁ። ከዓለም አብያተ ክርስቲያናትና ከደጋግ ምእመናን እየለመንሁ ከ40,000 በላይ ቅዱሳት መጻሕፍትን መግዛት ስግይችሉ ምእመናን ናኝቻለሁ። በጎጃምም ለመጀመሪያ ጊዜ መጽሐፍ ቅዱስ በአግርኛ ሲሻገር፥ መሻገሪያ ድልድይ በመሆን አገልግያለሁ። በዚህ ተልእኮም 25,551 መጽሐፍ ቅዱስ 600,000 ሐዲስ ኪዳን 1,300,000 ወንጌል በደኅና ተሻግሮ ለምእመናኑ ታድሏል። በዚህም ብዙ አምልኮ ባዕድና አጉል ልማዶች ከሕዝቡ ትከሻ ተወግደዋል።

ቤተ ክርስቲያናችን በእምነቷ ርትዕት ስትሆን አንዳንድ አላዋቂዎች በሚያወሩት ምክንያት ሕዝቡ ከክቡር ሥጋዉና ከቅዱስ ደሙ ተለይቶ ይኖራልɪ ምክንያቱ ግን ታዲያ ቁርባን ሰምን ይፈራል? በሚለው አንቀጽ ይዘረዘራል። ሕዝቡ በቅዳሴ ጊዜ አፍ ተልብ ሁኖɪ በሌሎች ቅዱሳት አብያተ ክርስቲያናት እንደሚደረገው በተመሥጠ ቁሞ ጸሎቱን ከሰማ በኋላ እየቆረበ ወደ ቤቱ እንዲመለስ በእየቤተ ክርስቲያኑ መግለጫዎች ሳድልɪ ባድል[1]ɪ ቁርባን የጌታ አጋ መሆኑ ቀርቶ የራሳቸው አድርገውትɪ እሱ ምንድር ነው? ምን አባው? ቤተ ክህነት አልቀጠረችው? ቄስ አይደል?ɪ ዳዳስ? የራሱን ቆርቦ ቢሄድ አነሰውና ሌላውን ደግሞ ቁረቡ እያለ የሚጋብዝ የሚሉ ቢኖ ሐሳውያን ስለተነሡ፥ ክርስቲያን ሁሉ የእግዚአብሔር ምስክር እንደሆነ ለማስረዳት፥ ወደ ኖናው ርእሴ፥ ከመግባቴ በፊት ተገደድሁ።

ብሉየ መዋዕል ዘለዓለማዊው እግዚአብሔር ልጅ እንዲ የልጅ ልጅ፥ የአክስት፥ የአጎት፥ የወዳጅ፥ የዘመድ ልጅ የለውም፥ የበኩር ልጁን ኢየሱስ ክርስቶስን የተቀበልነ ሁሉ ልጆቹ ነንɪ ልጆቹም ከሆን መንግሥቱን ለመውረስ የሰጠንን ትእዛዝ ተቀብለን ስለ ስሙ መመስከርና ማስተማር አለብንɪ መንግሥቱ በምግባርና በሃይማኖት እንጂ እንዲያው በመወለድ ብቻ የሚወረስ አይደለምና።

1. በእምነት በኩል ሁላችሁም በክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጆች ናችሁና፥ ከክርስቶስ ጋራ አንድ ትሆኑ ዘንድ የተጠመቃችሁ ሁሉ ክርስቶስን ለብሳችኋልና፤ በእሱ ዘንድ አይሁዳዊ ወይም ግሪክ የለም፥ ባሪያ ወይም ጨዋ ሰው የለም፥ ወንድም ሴትም የለም፥ ሁላችሁም በክርስቶስ ኢየሱስ አንድ ሰው ናችሁና፤ እናንተም የክርስቶስ ከሆናችሁ እንኪያስ የአብርሃም ዘር እንደ ተስፋውም ቃል ወራሾች ናችሁ። /ገላ. 3:25-29/።

2. ኢየሱስ ክርስቶስ ነው ብሎ የሚያምን ሁሉ ከእግዚአብሔር ተወልዷል። /1ዮሐ. 5:1/

3. በእግዘአብሔር መንፈስ የሚመሩ ሁሉ እነዚህ የእግዚአብሔር ልጆች ናቸው፤ አባ! አባት! ብለን የምንጮህበትን የልጅነትን መንፈስ ተቀበላችሁ እንጂ እንደገና ለፍርሃት፥ የባርነትን መንፈስ አልተቀበላችሁምና። የእግዚአብሔር ልጆች መሆናችንን ያ መንፈስ ራሱ ከመንፈሳችን ጋራ ይመሰክራል፥ ልጆቹ ከሆን ወራሾቹ ደግሞ ነን፥ ግለት የእግዚአብሔር ወራሾች ነን። /ሮሜ 8:14-17/

4. ለተቀበሉት ግን በስሙ ለሚያምኑት ለእነርሱ የእግዚአብሔር ልጆች ይሆኑ ዘንድ ሥልጣን ሰጣቸው፥ እነርሱም ከእግዚአብሔር ተወለዱ እንጂ፥ ከደም ወይም ከሥጋ ፈቃድ ወይም ከወንድ ፈቃድ አልተወለዱም። /ዮሐ. 1:12-13/

5. በእነዚህም በተሰጡን ነገሮች እጅግ ታላቅ የሆነውን ተስፋ ሰጥቶናል /12 ጴጥ. 1:4/።
ክርስቶስን የተቀበልነ ሁሉ የእግዚአብሔር ልጆችና የመንግሥቱ ወራሾች መሆናችንን የሚያስረዱ ለቁጥር የሚያታክቱ ጥቅሶች ከቅዱሳት መጻሕፍት መጥቀስ ይቻላል። ግን ጽሑፉ ግጠር ስላለበት ስለልጅነታችን እስከዚህ ይብቃንና ለሐዋርያነታችን ደግሞ የሚከተሉትን እንይ፤ ቅዱስ ጴጥሮስ በመላው እስያ ለተበተኑ ምእመናን እንዲህ ሲል ጽፏል፤

1. ወደ ጌታ ኢየሱስ የምትቀርቡትም ሕያዋን ደንጊያዎች በመሆን፥ መንፈሳዊ ቤት ሁናችሁ ለመታነፅ ነው። በዚህ ዐይነት በኢየሱስ ክርስቶስ አማካኝነት ደስ የሚያሰኝ መንፈሳዊ መሥዋዕትን ለእግዚአብሔር ለማቅረብ ቅዱሳን ካህናት ትሆናላችሁ።
እናንተ ግን ከጨለማ ወደ ሚደንቅ ብርሃኑ የጠራችሁን በጎነት እንድትነግሩ የተመረጠ ትውልድ፥ የንጉሥ ካህናት፥ ቅዱስ ሕዝብ፥

ለርስቱ የተለየ ወገን ናችሁ። /1 ጴጥ.2:5-10/

2. መጽሐፉን ትወስድ፥ ማኅተሙንም ትከፍት ዘንድ ለአንተ ይገባሃል፥ ታርደሃልና፥ በደምህም፥ ለእግዚአብሔር ከአሕዛብ፥ ከነገድ፥ ከቋንቋ ከሕዝብ ሰዎችን ዋጅተህ ለአምላካችን ነገሥትና ካህናት አድርገሃልና፥ በምድርም እንነግሣለን እያሉ ሐዲስ መዝሙር ይዘምራሉ። /ራእ. 5:9-10/።

3. የጌታውንም ፈቃድ ዐውቆ እንደፈቃዱ ያላደረገ ባሪያ በጣም ይገረፋል፥ /ሉቃ. 12:47/።

4. ጥሩን ነገር ዐውቆ የማያደርጋት ኃጢአት ትሆንበታለች። /ኩሉ ዘየእምራ ለሠናይት ወኢይገብራ ኃጢአተ ትከውኖ/ ከርሰቶስን የተቀበለ ሁሉ የመመስከርና የማስተማር ግዴታ እንዳለበት ከዚህ በላይ የተጠቀሱት ያስረዳሉ፤ ሥልጣነ ክህነት፤ ቅስና ወይንም ጵጵስና የሚያስፈልገው ቀድሶ ለማቁረብ፥ ታቦት ለመባረክ፥ ለመናዘዝ እንጂ በተቀረው ግን ወንጌልን ማስተማርና ካስፈለገ ጥምቀትም የዲያቆናት ሥራ ነው፤ የመጀመሪያዎቹ ታላላቁ ሰባኪያነ ወንጌል ሊቀ ዲያቆናት፥ ወቀዳሜ ሰማዕት እስጢፋኖስና ፊልጶስ ዲያቆናት ነበሩ፤ ይሰብኩም ያጠምቁም ነበረ። /ግብ. 6:8-15፤ 7:1-60፤ 8:1-40/።

ከነሱም ቀጥለው በእየአደባባዩ እየተሠዉ ወንጌልን ያስተማሩ ታላላቁ ሰማዕታት ድኤመናን ነበሩ። ከእነሱም ጥቂቱን ለመጥቀስ ያህል፥ ቅዱስ ጊዮርጊስ፥ ቅዱስ ፋሲለደስ፥ ቅዱስ መርቆሬዎስ፥ ቅዱስ ገላውዴዎስ፥ ቅዱስ ቂርቆስ፥ ቅዱስ ቴዎድሮስ ወዘተ ኧረ! ስንቱ! እነዚህን የመሳሰሉ ሁሉ ወንጌልን አስተምረው በመጨረሻውም በዐላውያን እደባባይ እንገታቸውን በሰይፍ እየተከለሱ አክሊለ ሰማዕ ደፍተዋል። /ለዚህም ስንከሳርን ያዩአል/

ስለዚህ እሱ ምንድር ነው የሚሉትን ሁሉ፥ ከርሰትና ምን እንደሆነች የማያውቁ ናቸው ብሎ፥ ስለማያውቁ አባት ሆይ! የሚያደርጉትን አያውቁምና ይቅር በላቸው በማለት አልየን /ሉቃ. 23:34/ ተወልዶ ብልጫ፥ እንከሰ ሩጫ አሰመኖሩንም አሰረድተን ወደ ዋናው ወደ ተነሣንበት ርእስ እናልፋለን፥ እንሰፍ።

<u>መሥዋዕት ምንድር ነው?</u>

መሥዋዕት ሰው ሁሉ ከአምላኩ ጋራ ለመገናኘት፥ ላለፈው ኃጢአቱን ይቅር ብሎ እንዲታረቀው፥ ለሚመጣው ደግሞ በመሥዋዕቱ ምክንያት ተዋሕዶት እንዲጠብቀው ለአምላኩ የሚያቀርበው ስጦታ ነው። እሱም ቁርባንና መሥዋዕት ተብሎ በሁለት ሰም ይጠራል፤ ደም የሚያስፈስስ የሆነ እንደሆነ መሥዋዕት፥ በእህል ውኃ የሆነ እንደሆነ ግን ቁርባን

ይባላል። ክርስቲያኖች በጊዜ ቅዳሴ የሚያቀርቡት ግን መሥዋዕትም ቁርባንም ነው። በኅብስትና በወይን ቅርፅ /አምላል/ ስለሚቀርብ ቁርባን ይባላል፤ አማናዊ ሥጋና ደመ መለኮት ስለሆነ ደግሞ መሥዋዕት ይባላል። /1ቆሮ. 11:10/

ዋናው ተግባሩም ኃጢአትን ማስተሰረይ፡ ለውን ከአምላኩ ማስታረቅ እንጂ፡ ያለዕውቀትና በንቀት እንደ ተራ ምግብ ካላደረጉት በቀር፡ መቅሠፍት ሆነ ኩነኔ አያመጣም። የክርስቲያኑስ እንዲያም የዘለዓለም ሕይወት ለማሰጠት ነው የተመሠረተው /ማቴ. 26:26-28፤ ዮሐ. 6:35-70/። ከሦስቱ ታላላቆች ሃይማኖቶች አይሁዳዊነት፡ ክርስትና፡ ሰላም/አሪት፡ ወንጌል፡ ቁርዓን/ ውጭም ግንኛቸውም ሰው የጭዳ መሥዋዕት ለአምላኩ ያቀርባል፤ ከአሪት በፊትም በመላው ዓለም መሥዋዕት በልዩ ልዩ ቅርፅና አምሳል፡ ለልዩ ልዩ አግልክት ሲቀርብ ኑሯል፤ አሁንም በብዙ አሕዛብ ዘንድ አለ። ሐሳቡና ተግባሩ ግን ኃጢአተኛን ከአምላኩ ጋራ ለማስታረቅ ነው። /ዘፍ. 4:3-5/። የሚያስተሰርየው ቀላል ኃጢአትን ይሁን እንጂ መሥዋዕትም ቁርባንም በአሪት ነበረ። ኃጢአተኛው /ሠዊው/ በደሉን ለካህኑ ይናገረና ካህኑ በመሥዋዕቱ ወይም በቁርባኑ ላይ እጁን ከጫነ በኋላ ተሠዊውን ወይም ቁርባኑን ይሠዋል፡ ወይም ያቀርባል፤ በዚህም የሠዊው ኃጢአት ወደ ተሠዊው ይተላለፍና ሠዊው በኃጢአቱ ምክንያት ከሚመጣበት ዕዳ ይድናል። /ሌዋ. 3:8፤ 12-13፤ 4:26:31፤ 35 ዘዕ. 24:4-8/

የአሪት መሥዋዕት በደመ እንሰሳና በእህል ውኃ ስለሆነ አርእስተ ኃጣውእን ለማስተሰረይ አይችልም ነበር፤ /ዘኁልቁ. 15:27-36፤ ዘዳግ. 22:22-25፤ ዘፀ. 21:12፤ ኢያ. 7:15/ መሥዋዕተ አሪት ኃጢአትን ከሰው ለማስወገድ ባለመቻሉ የዓለምን ኃጢአት አንድ ጊዜ ተሠውቶ በደሙ ለማስወገድ የአምላክ ልጅ ወደዚህ ዓለም ለአርአያ፡ ለቤዛ መጣ። አርአያ /አብነትነት/ እየሠሩ በግሳየት ግስተግር ነው፡ በዚህም በባሕርዩ ሊሠራው የሚችለውን እየሠራ በተግባር አሳይቷል፡ አስተምሯል፤ ሊሠራው ያልቻለውን ግን በቃል አስተምሯል፤ ሊሠራው የሚችለውን ለራሱ ምንም ባደረገው፡ እንደ ጥምቀት፡ ጸም፡ ጸሎት፡ ትሕትና፡ውርደት፡ መገረፍ፡ መገፋፍ፡ መሰቀል መታገሥ የመሳሰሉትን እየሠራ አሳይቷል፤ ኃጢአት ሠርቶ ንስሓ መግባትን፡ ግግባትን የመሳሰሉትን ደግሞ አዝዟል። ቤዛው ደግሞ ከወንበዴዎች ጋራ፡ እንደ ወንበዴ ተሰቅሎ፡ ሞቶ፡ ተነሥቶ ዓለምን አድኗል። በዚህም በእሱ ያመነና ኃጢአቱን ተናዝዞ ሥጋውን ደሙን የሚተበል

ሁሉ የዘለዓለም ሕይወት እንዳለው አስረድቷል። አርአያዬን ሰጥቻችኋለሁ ስላለን /ዮሐ. 13:15/ እንደሱ እንኳ ባይሆን እንዳቅማችን እንጸማለን፥ እንጸልያለን፤ ለሰዎችም ርዳታ ያደርግ ስለነበረ የታመመንና የታሰረን እንጠይቃለን፥ ችግረኛን እንረዳለን፥ መርዳት አለብን፤ /ማቴ. 3:13-17፤ 6:3-19፤ 25:32-46፤ 1ቆሮ. 6:4-5/ በተሳሳትንም ቁጥር እንድንናዘዝና ካህኑም ያለምንም ጭቅጭቅ ይቅርታ ሰጥቶ መጨረሻውን ሥርየት ወደሚሰጠው ወደ ሥጋውና ደሙ እንዲያሳልፈን በግልጽ አዝዞናል፤ ካህኑም ታዝዟል። /ማቴ.18:22-23፤ ሉቃ. 17:4/።

እንዲህ ያለው ጸጋም ሰሰው ልጅ የተሰጠው የአምላክ ልጅ ይህን ዓለም በደሙ ለመዋጀት፥ ኃጢአቱንም በሞቱ ለመደምሰስ ስለመጣ ነው። ሰው በእግዚአብሔር ቸርነት እንጂ እንዳንድ አላዋቂ ሰዎች ወይንም አወናባጆች እንደሚሉት፥ በራሱ ግብር ብቻ፥ ሊነጻ፥ ሊበቃ፥ ሊቀደስ ከቶ ምንም ቢሆን አይችልም። /ዮሐ. 1:29፤ 36፥ 3:16-18፤ ዮሐ. 1:7፤ 1ጴጥ. 1:18-19፤ ራእ. 5:6-10/። የዓለም ማዳኛውም እማናዊ ክቡር ሥጋው ቅዱስ ደሙ ነው፤ ሥጋውን ደሙን፥ ቢያንስ በ40 ቀን ውስጥ የማይቀበል የክርስቶስ ተከታይ ሁኖ ሊቆጠር አይችልም፤ እንደ ክርስቶስና እንደ ሐዋርያት ትምህርት ከሆነም የሕይወት ተስፋም የለውም፤ ሰምን ቢሉ ሥጋውንና ደሙን የሰጠው ለኃጢአት መደምሰሻ ለመንግሥተ ሰማያት መውረሻ ነውና። ሰዚህም በዚሁ ጽሑፍ በመጀመሪያው ገጽ በ4ና በ8 ቁጥር የተሰጡትን ጥቅሶች መላልሶ እንበ መረዳት ያሻል። ጌታችን ቅዱስ ቁርባንን ሲመሠርት <u>ለኃጢአት ማስተስረያ</u> ብሎ ስለሠራው ሳትበቁ በቅታችሁ፥ ሳትነጹ ነጽታችሁ እያሉ ምእመናንን የሚያሰፈራሩ ሁሉ ተሳስተዋል፥ ዐውቀው እንደሆነ ግን የጌታ ጠላቶች ናቸው፤ /ማቴ. 26:26-28/።

ሰምን ቢሉ ጌታ ፈሪሳውያንን፥ እናት ጸሐፍትንና ፈሪሳውያን ወዮላችሁ መንግሥተ ሰማያትን በሰው ፊት ትዘጋላችሁና እናንተም አትገቡባት፥ የሚገቡትንም ትከለክላላችሁ እንዳላቸው እነዚህም ሰው እንዳይጸድቅ ይከለክላሉና /ማቴ. 23:13፤ ሉቃ. 11:52/።

ለእጽንያተ ነገር ያህል ስለ ቁርባን ከቅዱሳት መጻሕፍት የሚከተሉት ጥቅሶች እነሆ፥ /ትርጉማቸውም በቀጥታ ከጽርእ ወደ እማርኛ ነው የተተረጎመው/ ሥጋዬን የበላ ደሜን የጠጣ የሚለው ስሕተት የመጣው በሌም ቋንቋ የግሥ ጊዜ ሁለት ብቻ ስለሆነ ነው እንጂ ጌታ ያለው ሥጋዬን አንድ ጊዜ የቀመስ ሳይሆን፥ ሥጋዬን ሲበላ፥ ደሜን ሲጠጣ የኖረ፥ ሥጋዬን ስትበሉ ደሜን ስትጠጡ ካልኖራችሁ በራሳችሁ

/ክብረቶችሁ/ ምንም ሕይወት የላችሁም ነው፤ በዮሐ. 6:35-60 የተጻፉትን ቁጥሮችም በዚሁ መንፈስ እያቃጠሉ ግንበብ ያስፈልጋል: ጽርአ ለማያውቁም የሚከተሉትን የእንግሊዝ: የፈረንሳይ: የኢጣልያን ትርጉሞች እንጠቅሳለንሐሐሠ[2]፤

1. ከዚህ ውኃ የሚጠጣ ሁሉ እንደ ገና ይጠማል: እኔ ከምሰጠው ውኃ የሚጠጣ ሁሉ ግን ለዘለዓለም አይጠማም። /ዮሐ. 4. 13/።

2. የሕይወት እንጀራ እኔ ነኝ: ወደኔ የሚመጣ ከቶ አይራብም: የሚያምንብኝም ለዘለዓለም አይጠማም...። የሕይወት እንጀራ /ዳቦ: ጎብስት/ እኔ ነኝ: አባቶቻችሁ በምድረ በዳ መና በሉ: ሞቱም: ከሱ የሚበላ እንዳይሞት ከሰማይ አሁን የወረደ እንጀራ ይህ ነው። ከሰማይ የወረደ ሕያው እንጀራ እኔ ነኝ: ከዚህ እንጀራ የሚበላ ሰው ሁሉ ለዘለዓለም ይኖራል። እኔም ስላለም ሕይወት የምሰጠው እንጀራ ሥጋዬ ነው.....። እውነት እውነት እላችኋለሁ የሰውን ልጅ ሥጋ ስትበሉ ደሙንም ስትጠጡ ካልኖራችሁ በራሳችሁ ሕይወት የላችሁም: ሥጋዬን የሚበላ ደሜንም የሚጠጣ የዘለዓለም ሕይወት አለው፤ እኔም በመጨረሻው ቀን እስነሣዋለሁ። ሥጋዬ እውነተኛ መብል: ደሜም እውነተኛ መጠጥ ነውና። ሥጋዬን የሚበላ ደሜንም የሚጠጣ በእኔ ይኖራል: እኔም በእሱ እኖራለሁ። ሕያው አብ እንደላከኝ እኔም በአብ እንደምኖር እንዲሁ የሚበላኝ ደግሞ በእኔ ይኖራል። /ዮሐ. 6:35-69/።

3. ቅዱስ ጳውሎስም ጌታ የተናገረውን መልሶ ከተናገረ በኋላ: ሰው ግን ራሱን ፈትኖ ከእንጀራው ይብላ: ከጽዋም ይጠጣ: የጌታ ሥጋ መሆኑን ሳያውቅ የሚበላና የሚጠጣ ግን በራሱ ላይ ፍርድ ይበላል ብሏል፤ ከዚህ ላይ የጌታ ሥጋ መሆኑን ካላወቀ ከሚለው ላይ እንዳንድ ስዎች የሌለውን እንዲያው እምጎበ አልቦ አምጥተው ወኢኮነ ንጹሐ ነፍሱ ሰውነቱ ንጹሕ ካልሆነ ብለው ይጨምሩበታል: ይህ ግን በፍጹም ስሕተትም ድፍረትም ነው። ቅዱስ ጳውሎስም አላለው: ከጌታችን ትምህርት ጋራም አይስማም: የቅዱስ ቁርባን ዓላማም እይደለም። ቅዱስ ጳውሎስ ወደ ቆሮንቶስ ሰዎች ይህን እንቀጽ የጻፈው: እንደ ሀገራችን የግጎበር ድግስ አድርገው እንደ ዘኬና መክፈልት: በቁርባን ስም የቻሉትን ያህል ዳቦና ወይን አምጥተው: ዳቦአቸውን በወይናቸው እያማጉ እየበሉ ይሰክሩና ወድቀው የሚያድሩ: የሚደባደቡ: የሚጣሉ ሁነዋል: በዚህም እግዚአብሔር ተቆጥቶ ብዙዎቹን ቀሥፏል: የዚህ ወሬ ኤፌሶን ሳለ ለቅዱስ ጳውሎስ ይደርሰዋል፤ ስለዚህ የጌታ ሥጋ መሆኑን ያላወቀ እይቁረብ ብሎ ይጽፍላቸዋል። /1ቆሮ. 11:17-34/።

4. የልጁም የኢየሱስ ክርስቶስ ደም ከኃጢአታችን ሁሉ ያነጻናል፤ ኃጢአት የለንም ብንል ግን ራሳችንን እናስታለን /እናታልላለንና/ እውነትም በእኛ ውስጥ የለም። በኃጢአታችን ብንናዘዝ፥ ኃጢአታችንን ይቅር ሊለን ከፀመግም ሁሉ ሊያነጻን የታመነና ጻድቅ ነው። ኃጢአት አላደረግንም ብንል ሐሰተኛ እናደርገዋለን፥ ቃሉም በእኛ ውስጥ የለም። /1ዮሐ. 1:9-10/

5. የቤተ ክርስቲያን አበውም ከሐዋርያት ጀምሮ በእየቅዳሴያቸው እንደ ተጻፈው ያስተማሩትና የሚሉት የሚከተለው ነው፥

<u>*ለቅዱስ ሥጋው*</u> አምነው ከሱ ለሚቀበሉ ሕይወትና፥ መድኀኒት የኃጢአት ማስተስረያ ሁኖ የሚሰጥ በእውነት ቅዱስ የጌታችን፥ የአምላካችን፥ የመድኀኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ሥጋ ይህ ነው።

<u>ለክቡር ደሙ</u>

አምነው ከሱ ለሚቀበሉ ሕይወት፥ መድኀኒት የኃጢአት ማስተስረያ ሁኖ የሚሰጥ በእውነት ክቡር፥ የጌታችን የአምላካችን፥ የመድኀኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ደም ይህ ነው። /ሐዋ. 41-43፤ 97-101፤ 104፤ 112፤ 115-117፤ ሕር. 108፤ ሠለሰቱ ምእት. 85-87፤ 147፤ አት. 124 ባስ. 119፤ ኤጲ. 60-64፤ ዮሐ. አፈ. 40-42፤ ቄር. 63-65፤ ዲዮ. 29-31፤ 39፤ 43፤ ጎርጎ. 34-35/።

በዚህ ጽሑፍ የተጻፉትን ጥቅሶችና ያልተጻፉትን ደግሞ ቁጥራቸውን እያወጣ ለተመለከተ አስተዋይ አንባቢ፥ ክርስቶስ የሞተው የዓለምን ኃጢአት ለማስወገድ፥ የእኛን በደል ለመሸከም /ኢሳ. 53:4-12/ ደሙም የተሰጠው ለሰው ሰጅ ድኅንነት፥ ለኃጢአት ማስተስረያ፥ ለበደል መደምሰሻ፥ ለአበሳ ማጥፊያ፥ በሌላም አነጋገር ደካማ ጊዜይን /ኃጢአተኛ/ ከደኑ ፈጣሪ ጋራ ማስታረቂያ እንጂ እንዳንድ አላዋቂዎች በሐሰትና በድፍረት <u>ሳትበቁ በቅታችሁ፥ ሳትነጹ ነጽታችሁ</u> ብትቀበሉት ሥጋው እሳት ሁኖ ይበላችኋል፥ ደሙ ባሕረ እሳት ሁኖ ያሰጥማችኋል እንደሚሉት እንዳልሆነ ይረዳል።

አሁንም ከዚህ በፊት ብዙ ተረት ስለሰማ የሚያነበውን የማይረዳ አንባቢ፥ ታዲያ ለመቁረብ የሚያስፈልገው ምንድር ነው? ይል ይሆናል፥ ስለዚህም መልሱ፥ ይህ በኀብስትና በወይን አምሳል የቀረበው መሥዋዕት እግናዊ ሥጋ መለኮት፥ እግናዊ ደመ መለኮት ነው፥ የኔንም ኃጢአት ለማስተስረይ ይችላል ብሎ አፍ ተልብ ግመን፥ ከመቀበል በፊት ደግሞ ኃጢአትን ለካህን መናገር ቂም በቀልን ከኀሊና ማራቅ ነው።

ታዲያ ቁርባን ለምን ይፈራል?

እንዲህ ከሆነ ነገሩ ቀላል ነው፥ ታዲያ ቁርባን ለምን ይፈራል? ለሚል ጠያቂ ደግሞ መልሱን እናስከትላለን፥

1. አሪት በሀገራችን ከወንጌል በፊት ገብታ ስለነበረ፥ ለብቻቸው መሥዋዕት አሪትን የለመዱ፥ ነገሩ ያልገባቸው ካህናት፥ ጥቅማቸው የተነካባቸው መስሏቸው፥ ተረፈ መሥዋዕቱን ለግል ለማድረግ ሕዝቡን እያስፈራሩ ያባርራሉ።

2. ለአንድ ሺህ ሰድስት መቶ ዘመን ግብጻውያን በኢትዮጵያ ሲቀልዱ ኑረዋል። ወንጌል እንዳትስፋፋ የሰብከት ድርጅት ሳያቋቁሙ፥ የተጠመቀውም እንዳይጸድቅ ሳያስተምሩ፥ የተማሩት የሀገራችን ሊቃውንትም እንዳያስተምሩ ትምህርታቸውና ቋንቋቸው ስለማይገባቸው፥ እንዲያው ከጎጋው ሕዝብ ጋራ ሁነው ገዝቻለሁ እያሉ፥ ሊቃውንቱን ሲያስገድሉ፥ በሀገሯ ላይ ድንቁርና ሲዘሩ ኑረው አልፈዋል።

3. ለአንድ ሺህ ዘመን ከሌላው ከክርስቲያኑ ዓለም በመለየታችን፥ ከሦስተኛው የዓለም ጉባኤ በኋላ ከዓለም ጉባኤ እንዳንችም ጉባኤ ሳንቀበል፥ በሀገራችንም ሀገር አቀፍ ጉባኤ ሳይደረግ፥ በእየጊዜው የተነሡት ችግሮችም በሲናዶስ ሳይወሰኑ፥ እንዲያው ከዚህ ግባ የማይባል አንዳንድ ግለሰብ ካሰኘው፥ ሲያሰኘው፥ ከጌታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ ትምህርት ጋራ እንኳ ተፃራሪ የሆነ ሐሳብ እንደ <u>ወኢኮነ ንጹሐ ነፍሱ ሰውነቱ ንጹሕ ካልሆነን</u> የመሳሰለ በሐዲስ ኪዳንና በቅዳሴ ሲጨመር፥ በዚህም አንጻር የጠላውን ሲቀንስ፥ ሲያወጣ፥ የቀረውንም በትርጉም ሰራሱ እንደሚመቸው እያደረገ ሲያጣምም ኑሯል። በዚህም ብዙው ሕዝብ ከፈጣሪው ተለይቶ እንዲሞት፥ ወይም ወደ ሌላ ሃይማኖት እንዲሄድ ሲያደርግ ኑሯል። አሁንም የግብር መሰሉ ያደርጋል።

4. ብዙ ካህናት ካለማወቅ ይሁን ከጥመት አይታወቅም ሕዝቡን አስፈራርቶ ግባረር እንጂ ሰብኮ፥ አደፋፍሮ ወደ ቤተ ክርስቲያን ግቅረብ ደስ አይላቸውምና ንጹሕ ሳትሆኑ አትምጡ እያሉ ያወናብዳሉ፤ ሰው የሚነጻው ወደ ክርስቶስ ሲቀርብ ነበር፤ ግን ሕዝቡ ከጋጢአቱ፥ ክርስቶስ የሰጠውን ጸጋ ተቀብሎ እንዳይነጻ የፈሪሳውያንን ጅራፍ ይዘው ያባርሩታል።

5. መበለታቱ ደግሞ ከአንድም ቁስ ሳይሰሙ፥ ቁሱ እንዲህ ይላል እያሉ የራሳቸውን ፈጠራ ስለሚያወሩ፥ ልጁ አድጎ ተምሮ እንኳ እናትህ የነገረችህ ውሸት ነው ቢሉት፥ ተረቱን እንደ ወንጌል አምኖ

ሌላ ስለማይቀበል፥ በብዙዎች ዘንድ ተረት ሃይማኖት ከሆነ ውሎ አድሯል።

መበለታት ከሚያወሩት መዓትም በጥቂቱ ለመጥቀስ ያህል፤

ሀ. በቅዱስ ጋብቻ የተጋቡትን ሰዎች ከመቁረብ በፊት ሰባት ቀን፥ ከዚያ በኋላ ደግሞ ሰባት ቀን ሩካቤ ሥጋ ክልክል ነው ይላሉ፥ ይህ እውነት ቢሆን ኑሮ ሕጋዊ ካህን አይቀድስ ግለት ነው። ጋብቻንም ማርከስ ነው።

ለ. ከቁርባን በፊትም ሆነ በኋላ ሥራ ክልክል ነው ይላሉ፥

ሐ. ከቆረቡ፥ መትፋት፥ መታጠብ፥ መነጋገር፥ ከሰው ጋር መብላት፥ በልቶ፥ ጠጥቶ ማተረፍ፥ ብቻ መሄድ ክልክል ነው ይላሉ።

መ. የቆረበ ሰው ከተሳሰተ ቁርባኑ ይፈርሳል፥ ንስሓም የለውም ይላሉ፥ ይህን ግን በልጅነታቸው ስለሚሰሙት ብዙ ደብተሮችም እንኳ ያምኑበታል።

በዚህ ዓይነት ከሰባ ዓመቷ በላይ የሚጠይቅት ስታጣ የመነኮሰች መበለት እንኳ እንደ ካህናቱ ሕዝቡን ከአምላኩ ለመለየት ተሳትፎ አድርጋለች።

6. ሊቃውንቱ፥ ደባትሩ፥ የዜማ፥ የቅኔ፥ የመጽሐፍ መምህራኑ ሌሊት ተቀን በያሬዳዊ ጣዕመ ዜማ ቤተ ክርስቲያንን ሲያዳምቁ ኑረዋል፥ አሁንም በእየደብሩ ይዘምራሉ፥ በዝማሬ መሥዋዕታቸው የሥጋውንና ደሙን አዳኝነት ዘወትር ይናገራሉ፥ ግን አይቆርቡም። ከዚህም አልፈው ተርፈው የሚቆርብ ዕጣን ጠባሽ ደንቆሮ ሰሞነኛ ነው ይላሉ፤ ደንቆሮው ግን ማን እንደሆነ ይህን የሚያነብ አስተዋይ አንባቢ አይስተውም። ሲዘምሩ አድረው፥ ጥሩ ጸበል ያየ ሰይጣን ይመስል ቅዳሴ ሲገቡ ከቤተ ክርስቲያን እየወጡ ይሄዳሉ። ታዲያ ከእነዚህ የሚገኘው ምን ዓይነት ምሳሌ ነው?

7. እሱ ራሱ ሕዝቡም ጀሮውን እናቱ በልጅነቱ በሞላችው ተረት ጠቅጥቆ፥ እውነት ለመስማት ባለመፈለጉ፥ ክርስቶስ ያለውን ሲያስተምሩት መናፈቅ እያለ ይደበድባል፥ ከቤተ ክርስቲያንም ያባርራል። ምን ያድርግ ፍርዱ ነው፥ እበት የተሞላ ዕቃ ካልተዋጣ፥ (ካልተገላበጠ) ማር አያስጨምርምና።

8 ውጭ ሀገር ይልቁንም ግብጽና ኢየሩሳሌም ብዙ መነኮሳት፥ ቀሳውስት፥ ምእመናን ይሄዳሉ፥ ከዚያም ክርስቲያን ሁሉ ሲቆርብ ያያሉ፥ ዐይተው ሲመለሱ ግን ቁረቡ ብለው አይሰብኩም፥ አይነግሩም፥

አያስተምሩም። ለምን ቢሉ? ብዙዎች ኢየሩሳሌም ሳሚ በመባል አቦ! አቦ! እየተባሉ ከፍተኛ ሹመት ይዘው ለመኖር ነውና የሚያስቡ: አስተምረው መናፍቅ እንዳይባሉ፥ ጥሪያቸውን ለሹመት፥ ለገንዘብ: ለክብር፥ ለውዳሴ ከንቱ ለውጠው፥ ዐይናቸውን ጨፍነው፥ አፋቸውን ዘግተው በውዳሴ ከንቱ ቅዱስ! ቅዱስ! ሲባሉ ይኖራሉ።

<u>ለመቁረብ የሚችል ማን ነው</u>?

ኢየሱስ ክርስቶስ /መሲሕ/ ነው ብሎ በማመን ከእግዚአብሔር ለተወለደ ክርስቲያን ሁሉ ቅዱስ ሥጋውን፥ ክቡር ደሙን ቢያንስ በአርባ ቀን አንድ ጊዜ መቀበል መብቱም ግዴታውም ነው። ማርቆስ አባታችን፥ እስክንድርያ እናታችን እንላለን፥ ታዲያ ግብጻውያን እንደኛ ሰዎች ናቸው፥ ያውም ከኛ ባይከፉ፥ እኛ የምንሠራውን ሥራ ሁሉ ይሠራሉ፥ ግን በእየጊዜው ኃጢአታቸውን እየተናዘዙ ይቆርባሉ። በዓለም ያሉ ክርስቲያኖች ሁሉ በሥጋውና በደሙ እንደኛ የሚያምኑ ከሆነ ይቆርባሉ። ይህ በጎብስትና በወይን ቅርፅ አምሳል የቀረበው መሥዋዕት እማኖዊ ሥጋ ወልደ እግዚአብሔር እማኖዊ ደመ መለኮት ነው፥ የኔንም ኃጢአት ለማስተሰረይ ይችላል የሚል ከ12 ዓመት በላይ ያለ ሰው ሁሉ መቁረብ ይችላል፥ አለበት፥ ከማኅበረ ክርስቲያን ካልተለየ በቀር። ሥርዓቱም መጀመሪያ ኃጢአት ይሠራል፥ ከአበሳ: ከበደል ለመጣላገል ይቆረባል /ማቴ. 26-26-28፥ (1ዮሐ. 1:7-12/። በሌላም አነጋገር ኃጢአት የሠራና ሥርየት የሚፈልግ ሁሉ መቁረብ አለበት፥ ይቁረብ፥ ወደ አዳኙ ወደ ክርስቶስ እንዳለ እምነቱን ብቻ ይዞ ይምጣ፥ የዓለሙን ኃጢአት ለማስወገድ የሚችል ክርስቶስ ብቻ ነውና። ቁሱም <u>ሳትነጹ ነጽታችሁ</u> በማለት ፈንታ፥ በደላችሁን ተናዛችሁ: ከኃጢአታችሁ እንድትነጹ፥ ቅዱስ ሥጋውን ክቡር ደሙን ተቀበሉ፥ የክርስቶስ ደም ኃጢአታችሁን ያነጻልI እምቢ ብትሉ ግን በአበላችሁ ከሚመጣባችሁ ፍዳ ነጻ ነኝ፥ ጥፋታችሁን ተላልፎ መቀበል የለብኝም ይበል፥ ዲያቆኑም ይህን የቄሱን ቃል የናቀ፥ ያቃለለ ብሎ ይቀጥላል። 12 ዓመት ከሆነው እስኪያገባ ድረስ ከአርስተ ኃጣውእ እንዱን የሠራ እንደሆነ ኃጢአቱን ለካህን ተናግሮ በበነጋው ይቆርባል፥ አግብቶ ከአሚኑ ጋራ ይቆርባልI አሚኑ ብታመነዝር ወይም ብትሞትበት ሌላ እስኪአገባ ድረስ በአመክሮ ቢቀመጥ አሁንም ይቆርባል። ከአመክሮው በኋላ ቢፈልግ ሌላዋን ቁርቦ ለማግባት ይችላል። በምንም ዓይነት ክርስቲያን ሁኖ እየጸመ፥ እየጸለየ ከዓመት በላይ ሳይቆርብ መቆየት የለበትም። /ሮሚ 7:2-3I ቆሮ. 7:39-40/።

ይህ ሐሳብ በግብር አይፈጸምም እንጂ በእኛም ቤተ ክርስቲያን

ይወራልና ለጎጋው ሕዝብ ካልሆነ በቀር በሊቃውንት ደረጃ አያጣላም። በቤተ ክርስቲያን ደረጃ የሚያጋግረው ግን ካላመነዘረ እግኒ ከኢእግኒት፥ እግኒት ከኢእግኒ ጋር እየኖረ ሊቆርብ ይችላል የሚለው ሐሳብ ነው፤ ይህ ግን እንደ ጊዜውና ሀገሩ በቅዱስ ሲኖዶስ እንጂ በግለ ሰብ ደረጃ የሚወሰን አይደለም /1ቆሮ. 7:12-16/።

<u>ክርስቲያን ምንድር ነው</u>? ከዚህ በፊት በእየምክንያቱ ደጋግመን እንደተናገርነው ክርስቶስን የተቀበለ ሁሉ የእግዚአብሔር ልጅ ነው /ገላ. 3:26-29/ የሰው ልጅ ሰው፥ የከብት ልጅ ከብት እንደሆነ ሁሉ ከቅዱስ እግዚአብሔር የተወለዱ ክርስቲያኖችም ቅዱሳን ናቸው። /ዮሐ. 15:12-17፤ 17:20-26፤ 1ጴጥ. 2:5-10፤ ገላ. 3:26-29፤ 2ቆሮ. 9:1፤ ግብ. 9:13፤ 32፤ 41፤ ሮሜ 15:25፤ 1ቆሮ. 16:1/።

እንኳን ሌላ ቅዱሳት ለቅዱሳን የሚለው እንኳ ቢሆን ክርስቲያኖችን ቁርባንን እይከለክልም፤ ጌታ ግን ይህን ንኡስ ሐረግ የተናገረው ስለሃይማኖት ትምህርትና ስለ ሥነ ምግባር እንጂ ለሥጋውና ለደሙ አይደለም፥ መሥዋዕትን ቁርባንማ ለኃጢአት ማስተሰረያ እንደሆነ ፍርጥ አርገጥ አድርጎ ነግሯል።

<u>ታዲያ እንዲህ ከሆነ ከልካይ ማን ነው</u>? ጠያቂ አይታክትምና፥ ብዙ ተረት ስለሰማና አንዳንድ በካህን ስም አወናባጅ ሰዎች እትቁረቡ ሲሉ ሰምቶ፥ ታዲያ እንዲህ ከሆነ ከልካይ ማነው? የኛ ካህናትስ ለምን ይከለክላሉ? ይል ይሆናል። ከክርስቶስም ሆነ ከሐዋርያት ከሠልስቱ ምእት፥ ከሊቃውንት፥ በቤተ ክርስቲያን ሥርዓትም ሆነ ሥሪት፥ ሥጋውን ደሙን ለመስጠት እንጂ፥ ተቀባዩን ለመንቀፍም ሆነ ለመከልከል ፈቃድም ይሉ መብት የተሰጠው አንድም ሰው የለ /ግቴ. 7:1-5፤ ሮሜ 14:4፤ 13/

ይህ ጽሑፍ የሚደርሳችሁ ቀና አስተሳሰብ ያላችሁ የኢትዮጵያ አርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት በዚህ ዐይነት ሰባቱን ሀብታት ጽፌ ለማሳተም ስላሰብሁ፥ የማትስማሙበትን ነጥብ በሚከትለው አድራሻ እንድታስታውቁኝ በትሕትና ትለመናላችሁ፥

ቴሌ. 182320፥ ፖ.ሣ.ቁ. 30143 አ.አ.

በክርስቶስ የእናንተው

ዓለማየሁ ሞገስ

መ ዘ ክ ር

1.1 ዓለማየሁ መገስ፡ የአማርኛ ሐረግ፡ የፍልሰታ ቅዳሴ፡ በአዲስ አበባ አድባራት፡ 1964 ዓ.ም. ትንሣኤ ዘጉባኤ ማ.ቤት፡ አዲስ አበባ፡ 167፡ ገጽ. 43-51

1.2 አዲስ አበባ ስለቅዱስ ቁርባን የቀረበ ሮሮ /የተባዛ፡ ሠኔ.21.1975/

2.1 King James Version, Holy Bible.

2.2 La Bible en Francais Courant 1983.

2.3 La Bible de Jerusalem, /Jeruselem Nouvelle/ 1979.

2.4 La Bibbia di Gerusalemme, Maggio 1974.

2.5 La Sacra Bibbia, Roma, MCM LVIII.

ቁርባንን ለሚከለክሉ ሰዎች የተሰጡ ቅኔያት

የቅዱስ ቁርባን ይዞታ ይህ ሲሆን አንዳንድ ጠማማ ካህናት ጎጋ ሕዝብ ያለበቂ ምክንያት እንዲያው በጥመት ቁርባንን ንጹሓን ምእመናን እንዳይቀበሉ ስለከለከሉ፡ እንዲያውም እንዲማ መሪዎች ነን ከሚሉተ ውስጥ፡ ለዚህ ሁሉ ስንዴ የት ይገኛል ብሎ ዐረፈ። ስለዚህ ነው በንዴት የሚከተሉትን የመሳሰሉ ቅኔዎች የተበተኑት። ይዞታቸውም ጠማሞችንና አላዋቂዎቹን ነው እንጂ ሊቃውንቱንና ደጋጎቹን አይነካም።

ጉባኤ ቃና

መፍትው ትግበር ይሁዳ ውስተ ግብርከ ጎሠማ
እስመ ያወፅእ ሳሕምከ ይእዜ በበዕለቱ ሠላሳ።
እምነ ካህናት እምላክ ረሲእን ይጌይሱክ በጽድቅ
አምጣነ ረሲእን አምላክ ኢይሠይጡ በወርቅ።

ዘአምላኪየ:

ካህነ ሐሰት ቂቁይ ካህነ ዓለም ተከብቶ
ቅዱመ ቅድመ ምእመናን ዐጸወ ኖጎቶ
ለእግዚአብሔር ንጉሥ ስፉሐ ማዕድ አእኮቶ።

ሚበዝኁ

እግዚአብሔር ንጉሥ አበ ወልደ አብ አጽንዕ እስኩ መለኮተከ
ለለዕለቱ ብሩረ እስመ ይሠየጥ ወልድከ
በእንተ ንዋይ ወክብር እምነ ነጋዲ ካህን ዘበላዕለ ሕዝብ ሜምከ።

ሥ ላ ሴ:

ከብረ ድኅረ ሞተ
ወልደ አብ መምህር ዘበትሕትና

ውሉደ አዳም ይባልሕ ኩነኔ ውስተ ከርሠ ብእሲት ጎደረ
ወሐዲበ እግረ አርዳኢሁ ትሕትና መሀረ
ወእምአይሁድ ተሠይጠ ሠለሳ ብሩረ እስራኤል ገብረ፡
ባሕቱ ካህን ዘኢያአመረ
በከሊአ ቁርባን ምእመነ አምላኮ አክበረ
አፉ ሕዝብ ኢይኩን ሕሡረ።

<u>ትርጉም፡</u>

በትሕትና ዓለምን ከኩነኔ ለማዳን ከሴት ግሕፀን ያደረ፡ በአይሁድ ቤት ከትልቅ ውርደት የሚቆጠረውን ትሕትና የደቀ መዛሙርቱን እግር በማጠብ ያስተማረ፡ በመጨረሻውም በርካሹ የእስራኤል ብር በሠላሳ ብር ከአይሁድ የተሸጠ፡ መመምህር ወልደ እብ የሞተ ልጅ አንገቱ ረጅም ነውና ከሞተ በኋላ ከበረ። ምክንያቱም አላዋቂ ካህን ሕዝቡ ቆርበው እንዳያረክሱት ከልክሏልና።

እንዲህ ነው እከባበር ሕዝብን ከእምላክ፡ አምላክን ከሕዝብ ለይቶ ልክ እንደ ዲያብሎስ። ቁርባንን የሚከለክል ካህን ሐዋርያነቱ ለማን ይሆን? ይህንስ ላንባቢ ፈንታ ልተወው።

<u>መወድስ 1.</u>

ለእመ ሐተታ ሐተትን ላዕለ ካህናት
ወግጎበረ አይሁድ ሐሰውት ፈድፋደ ይትሌዐሉ
ግጎበረ አይሁድ ሐሰውት እምነ ካህናት እሉ
አምጣነ አይሁድ ለአድጎና
ዓለመ እምነ ኩነኔ አምለከ ሰቀሉ
ውስተ ዐውደ ፍትሕ ቀራንዮ
ባሕቱ ካህናት ዘውስተ ዐውደ ፍትሕ ብዕሉ
ግብሮሙ ለለዕለቱ እንዘ የሀቡሉ
ክርስቶስ ዘእድጎነ በከሊአ ቁርባን ይቀትሉ።
ወአመ በዕረፍት መዓልተ ምእመናነ ወልድ ወዐሉ
ለቂተለ የዋህ ካህናት ገዳግተ የዐይሉ።

<u>መወድስ 2.</u>

ሕግመነ ቅንዓት ዘቃኤል ወልደ ዐመፃ
ሕግመ ልያ ወራሔል ውሉደ እይሁድ ኮሎሙ
ቅዱሳነ ግብር ቃላተ ጎጡአነ ሠናይት ዳእሙ
ይስቅሉ ወልደ ሥጋ እምላክ
ጎቡራነ እንዘ ይትጋብኡ ውስተ ዐውድ ቆሙ
በትንቢተ ቀደምት ነቢያት

እስመ ለወልደ አብ ቁርባን ይስቅልዎ ሀለዎሙ።
በሳሌም ዐውደ ኩነኔ አመ ተከሥተ ግብሮሙ
ይበልዑ መቅሠፍታተ ወምሕረተ ይጸውሙ
ሥርዓተ መሓሪ አምላክ አምጣነ አልቦሙ
ቤቶሙ ጎልዮተ ወጎሊና ጽድቅ አልቦሙ።

መወድስ 3.

ይሁዳ ይኄይስ እምካህናቲነ
ጸረፍተ ይሁዳ በአፍ ወተለውተ ግብሩ በግብር
እስመ እመ ሜጠ ለወልድ እግዚአብሔር
ለሕዝበ አይሁድ ፍቁራኒሁ
ሰዓተ አሐተ በጎዳጥ ብሩር
ነስሐ እምነ ልቡ
እስክነ ለሞት ጸዋግ በእንተ ዝንቱ ነገር:
ባሕቱ ካህነ ወርቅ በውዳሴ ከንቱ ክቡር
እንዘ ለለጸብሐ ይሠይጠ ለሥጋ መለኮት ኢየኀፍር
ወእንዘ ለሊሁ ክርስቶስ ይጼውያሙ በፍቅር
ጉባኤነ ጽድቅ አባግኢሁ በልብሰ መዳልው ያበርር።

መወድስ 4.

ጽድቀ ኮነ ባህለ አግሌቅ
እኪተ ንግበር ከመ ንርከብ ሠናያተ
እስመ በዘአምጽአ ወልድ ዘለዓለማዊ ሕይወቲ
ህየንተ ስባሔ ወአምልኮ
ረከበ እምነ አይሁድ ላዕለ ዕፅ ስቅለተ።
ወበዘወረየ አንስተ ሮም
ምስለ እደወ ሮም ጴጥሮስ ተሰቀለ ቁልቁሊተ።
በእቅሌያስሂ ህገርነ ለእመ ጉሕሉት ብሕተ
ለረኪበ ሣመት ካህናት ይቀትሉ ሊቃውንተ
ወበውዳሴ ይርከቡ ፍትውተ ዓለም ሣመተ
ያርሕቁ ምእመናነ ሥግወ መለኮተ።

መወድስ 5.

መኑ ይኄይስ በጊዜ ሐተታ
እምነ እኩያነ አብያጽ ግጎበረ አይሁድ ወቀሳውስት
በገቢረ ብዙኀ እከይ መትልወ ጸዋግ ጉሕሉት
እመ ዕሩያነ አምስሎሙ

መቅደስ ዘይሰብስዎ ጸዲሬ ትውፊት?
ይኄይሱ ካህናት
በአኒመ ሐሰት ልብስ እንዘ የአክዩ በትምህርት።
እመ በስሕተት ሕዝበ አይሁድ አምላከ ምሕረት
አግብኡ ለኩነኔ ውስተ ዐውደ ፍትሕ በፍርሃት
እምጣነ በሚመት ሰይፍ ወመጥባሕተ በቀል ቅንዓት
ይቀትሉ ሊቃውንተ ቀታልያነ ጽድቅ ካህናት።

<u>ኩ ል ክ ሙ</u>

ተዋልጦ ብዙኅ ነገር ለእመ ተግብረ
በዘመንነ ሐዲስ ወውስተ ቅድስት ሀገርነ
ለአድኅኖ ዓለም ዘመጽአ መድኅኒትነ
ስርየተ ኃጢአት እመ ወሀበ
ቅዱስ ሥጋሁ ወደሞ እሙነ
ተብህለ ለኮንኖ
ለምእመናኒሁ ዘሠርዐ ማዕደ አምላክ ቁርባነ፡
በእንተ ዝንቱ ቅድመ ቁርባን ያፈርሁነ
በብሂሰ ኩኑ ግብረክሙ ፍጹማነ ቅዱሳነ፡
ከመ ምጽአተ ወልድ ቅዱስ ለጸውዖ ጻድቃን ኮነ
እለ የኅይሱ ክርስቶስሃ ወጳውሎስሃ ካህናቲነ።

ይህ ተግሣጽ ከተበተነ ወዲህ ብዙዎቹ ደጋግ ካህናት ስርብትና ፈርተው እንደዚህ ጽሑፍ ምስጢረ ንስሓን አፍረጥርጠው፡ ግልጥልጥ አድርገው፡ ሰው ገብቶት እንዲቆርብ አድርገው እያስተምሩም፡ አላስተግሩም እንጂ እንዲያው በደፈናው ቁረቡ፡ ቁረቡ፡ ካልቆረባችሁ አትጸድቁም እያሉ መስበክና ማስተግር መጽሐፍም ጀምረዋል፡ ሕዝቡም መጽሐፍ ቅዱስ እያነበበ የዲያብሎስ ሐዋርያ ፀረ ክርስቶስ የሚያወራውን ሳትበቁ በቅታችሁን ጥሶ በገፍ ይቆርብ ጀምሯል፡ በዚህም እግዚአብሔር ይክበር ይመስገን።

ሀ) አባ መልከ ጼዴቅ (አቡን) ትምህርተ ክርስትና 2ኛ መጽሐፍ፡ ትንሣኤ ዘጥባኤ ማተሚያ ቤት አ.አ. 1984 ዓ.ም. ገጽ. 108።
ለ) ዓሥራት ገብረ ማርያም ትምህርተ መለኮት፡ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት አ.አ. 1983 ዓ.ም. ገጽ. 225።
ሐ) አቡነ ገብርኤል የኤርትራ ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ፡ የኦርቶዶክስ ሃይማኖት አንደኛ መጽሐፍ፡ የኢትዮጵያ ጥናቶች ማእከል አሥመራ፡ 1976 ዓ.ም. ገጽ. 43-44።
መ) ሊቀ ካህናት ክንፉ ገብርኤል አልታዩ (እምነ ዝኩር)።

ምዕራፍ 16

ለሥጋህ ወደሙ የሚቀርበው ኅብስትና ወይን

ቁርባን እንዴት እንደሆነ ከነተጋድሎው ካየን: ለሥጋውና ደሙ የሚቀርበው ኅብስትና ወይን የሚዘጋጀው እንዴት ነው? ለሚል ጠያቂ ደግሞ በሚከተለው እንቀጽ ይብራራል።

ጌታችን ቁርባንን በጸሎተ ሐሙስ ሲሠራ ለእራት ካመጡለት ኅብስትና ወይን እንሥቶ ነው የሠራው: ይህንም ቃል ለቃል ተቀብለው አሁንም ከገበያ ኅብስቱንና (ዳቦውን) ወይኑን ገዝተው የሚሠሩ አሉ። አብዛኛዎቹ ምዕራባውያን ደግሞ የሮምን ቤተ ክርስቲያን ተከትለው ለዚህ በተዘጋጀ መሥሪያ እየሠሩ ያድላሉ።

ደም የሌለው ሥጋ የለም ብለው ሥጋውን ብቻ የሚሰጡ አሉ። (መ.ቅ.ገ. 464:52) ወይም እንደ ግሪክ ቤተ ክርስቲያን አደባልቀው ያቀብላሉ። ከኛ ቤተ ክርስቲያን በቀር ምስጢር ነው ብሎ የድብብቆሽ ጭዋት የሚጫወት የለም። ሁሉም በግልጥ ነው። ድብብቆሹ የተጀመረ ግን መቼ እንደሆነ የሚያውቅ የለም። ለዚህም ዕንቋችሁን ከእሪያ ፊት አታስቀምጡ ብለው: ስለ ሃይማኖት የተነገረውን የሚጠቅሱ አሉ: ይህ ግን ያለበታው የገባ ያላዋቂ ጥቅስ ነው። ቀዳሾች በሚቆርቡበት ጊዜ መጋረጃ ገልጠው ለሰው አብነት ለመሆን በግልጥ በመቁረብ ፈንታ ከቅዳሴው የሌለ መልክአ መልክ በመልክአ ቁርባን ስም ያንጎራጉራሉ። ያም ሆነ ይህ በእኛ ቤተ ክርስቲያን ለሥጋው የሚሆነው ኅብስት: ለደሙ የሚሆነው ወይን እንዴት እንደሚዘጋጅ እነሆ:

ንጹሕ ስንዴ ተመርጦ በቅዴታ ተሰፍሮ በጥንቃቄ ይለቀማል: ከዚያ በኋላ በንጹሕ ውኃ ይዘፈዘፍና ይፈተጋል: ተፈትጎ ሲደርቅ ይፈጫል። ከዚያ ለዲያቆን ይሰጣል: ዲያቆኑም መልክአ ኢየሱስ እየደገመ ያቦካዋል: መጣል ይባላል: ጥሎት ውሎ ሲነሣ አሁንም መልክአ ኢየሱስ እየደገመ ያሸዋል: እንዳይዘባ አድርጎ አሽቶ ሲያበቃ ከሦስት ከፍሎ መስቀል ባለው ማኅተም እየረገጠ ከጽዱት በላይ ይደፋዋል: ሲበስል ሦስቱንም አንሥቶ በመሶብ ወርቅ አድርጎ ለአምስተኛው ዲያቆን ይሰጠዋል: ይዞት ወደ መቅደስ ይሄዳል: ከዚያ ገባሬ ሠናዩ ቄስ ቢስማማ ዲያቆኑ እንዳስቀመጠለት የመካከሉን ይወስዳል: ባይስማማ የወደደውን የመምረጥ መብት አለው።

ከመሠረቱ ስንዴውን በገጠር: በድኃ ቤተ ክርስቲያን የሆነ እንደሆነ ዐቃቢት ሴት: የካህን ሚሽት ወይም ከወንድ ያልደረሰች ልጃገረድ: በደብርና በገዳም የሆነ እንደሆነ ቆራቢ ወንድ ወይም መነኮስ: ዲያቆን: ቄስ ነው የሚፈጨው። በጥንቃቄ በኩል በአንድ በኩል ብናጠፋ እንቀሠፋለን ብለው ስለሚፈሩና ቢአለሙ ደግሞ እንጠቀማለን

በእምላካችን ዘንድ ዋጋ እናገኛለን ብለው ስለሚያምኑ የተቻላቸውን ያደርጋሉ። ወይኑን (ዘቢቡን) ደግሞ ገባሪ ሠናዩ ዲያቆን ለቅልቆ ይደፋና ፍሬውን እያወጣ አሽቶ ደም ሲመስል ጎብስቱን የያዘውን ዲያቆን እየመራ መቅደስ ይዞት ይገባል። ወዲያውም ቅዳሴ ይጀመራል። (ማቴ. 26:26-30፤ ማር. 14:22-26፤ ሉቃ. 22:14-20፤ መ.ቅ.ነ. 377:60)

ምዕራፍ 17

ቅዳሴ፤

ቅዳሴ ሥጋውን ደሙን ለማክበር የተሠራ ጸሎት ነው። የቤተ ክርስቲያን አገልግሎት መደምደሚያውም ይህ ነው። በዚህ ጸሎት ጎብስቱ አማናዊ ሥጋ መለኮት ወይኑ አማናዊ ደመ መለኮት በመንፈስ ቅዱስ ሁኖ ስለሚለወጥ፥ ኢየሱስ ክርስቶስ ስለሚሠዋ፥ መንፈስ ቅዱስ መሥዋዕቱን ስለሚለውጥ፥ እግዚአብሔር አብ የልጁን መሥዋዕት ስለሚቀበል፥ ሦስቱም ሥላሴ በልዩ አካኋን ስለሚገኙ ከጸሎት ሁሉ በላይ አድርጎ በፍርሃት፥ በረዓድ፥ በፍቅር በጥንቃቄ ሊያከናውኑት ይገባል። በዚህ ጊዜ ለተልእኮ ከሚንቀሳቀሱት ካህናት በቀር መናገር፥ መንቀሳወስ፥ በጎሊና መዘባረቅ አይገባም።

ይህን ለማከናወን በቀኖና ቤተ ክርስቲያን የታዘዘው አንድ ቄስ ብቻ ነው፥ ካመቼ የሚረዳው አንድ ዲያቆን ቢጨመር አይከፋም። ለዓመት በዓል ጸጸስ ሲቀድስ አንድ ቄስና ዲያቆን ይጨመራል። (መ.ቅ.ገ. 34-36) ይህ የዓለም አብያተ ክርስቲያናት የሚሠሩበት አዳው አውራ ጎዳና ነው። በእኛ ቤተ ክርስቲያን ግን ቀዳስያኑ አምስት ካልሞሉ ይታጎላል። ይህ አጉል ልማድ ከመቼ ጀምሮ ወደ ሀገራችን እንደ ገባ ተጠንቶ ሳይደረስበት ቀርቷል። (መ.ቅ.ገ. 231-112-114) ከዚህም በላይ የተመቻቸው ታላላቁ አድባራት ደግሞ ሰባትም፥ ዐሥራ ሁለትም፥ ዐሥራምስትም፥ ሃያሐንድም፥ ሃያራትም ያደርጋሉ። በጎብረት ለመቁረብ ከሆነ ጥሩ፥ በተቀረ ግን ጭቃ በራይ ነው።

አሁን ወደ ቁም ነገሩ እንመለስና ጸሎቱን የሚሠራውም የሚመራውም ገባሬ ሠናዩ ቄስ ነው፤ ለጭቃ ሹም ጓኝ እንዳለው ለሱም ተራዳኢ ቄስ አሰው፤ ገባሬ ሠናዩ ቄስ ወደ እግዚአብሔር በሚጸልይበት ጊዜ ወደ መንበሩ ይዞራል፥ በተቀረ ግን ሁልጊዜም ግንባሩ ወደ ሕዝቡ ወደ ምዕራብ መሆን አለበት። ገባሬ ሠናዩ ዲያቆን ግን ሁልጊዜም ሕዝቡን ማዘዝ ስለ ሆነ ተግባሩ ከመቅደሱ በር ሁኖ ፊቱን ወደ ሕዝቡ እዙሮ መቆም አለበት፥ ቁሞ፥ ተንሥኡ፥ ጸልዩ እያለ ያዝዛል፥ ያዝዝ። አንዳንድ አላዋቂ ዲያቆን ወደ መንበሩ፥ ወደ ምሥራቅ ዙሮ ስገዱ ይላል፤ ምን ማለቱ ነው? ታቦቱንና መንበሩን ስገዱ ማለቱ እንደሆነ የሚናገረውንና የሚያደርገውን አያውቅም ማለት ነው። ካላወቀስ እንዴት ከዚህ ማዕረግ ደረሰ? የሚል ጥያቄ ያመጣል። መልእክታትና ወንጌልም የሚነበቡ ወደ ሕዝቡ ዙሮ ነው፥ አንዳንድ ቀላውስት ወደ መንበሩ ዙረው የሚያነቡ አሉ፥ አሁንም እነዚህ መንበርና ታቦት ነው ወይስ ሕዝብ የሚያስተምሩ ያሰኛል። ይህም የሚያደርጉትን አለማወቅ ያሰኛል።

የሆነስ ሆነና መቸ ነው የሚለወጠው? አንዳንድ ሰዎች አሐዱ አብ ሲል ነው፡ ሌሎች ደግሞ ይረስዮ ሲል ነው ይላሉ፡ የትኛው ነው እውነት? ለሚል ጠያቂ ደግሞ መልሱ ይረስዮ ሲል ነው፤ ምክንያቱም፤
አንደኛ፡ አሐዱ አብ፡ አሐዱ ወልድ፡ አሐዱ ውእቱ መንፈስ ቅዱስ በማለቱ በአንድ አብ በአንድ ወልድ በአንድ መንፈስ ቅዱስ አምናለሁ ብሎ ይናገራል እንጂ ጎብስቱን ባርከው ወይኑን ለውጠው ብሎ ስላልጠየቀ በዚህ አይለወጥም።
ሁለተኛ፡ ከዚህም በላይ በእየጊዜው ይህን ጎብስት ይህን ጽዋዕ ባርክ እያለ አይባርክም ነበር። ጎብስቱና ወይኑ ተለውጠው አግናዊ ሥጋ ወልደ እግዚአብሔር፡ አግናዊ ደመ ወልደ እግዚአብሔር ከሆኑ በኋላ፡ እግዚአብሔርን ለመባረክ የሚችል ሥልጣን ያለው ቄስም ይሁን ጳጳስ የለምና።
ሦስተኛም፡ አሐዱ ሲል ተለውጦ ቢሆን ኑሮ በኋላ በፍሬ ቅዳሴው ይህን ጎብስትና ጽዋዕ የልጅህን ሥጋና ደም እንዲያደርገው ቅዱስ መንፈስህን ላክ ብሎ አይጸልይም ነበርና።
አራተኛ፡ በአሐዱ አብ ተለውጦ ቢሆን ኑሮ መልእክታትንና ወንጌልን አንቦ አይሰብክም ነበርና።
አምስተኛ፡ እስኪለወጥ የነበሩትን ፃኡ ንኡስ ክርስቲያን ብሎ ለማሰናበት ሥልጣን አይኖረውምና።
ስድስተኛ፡ መጨረሻው ሥርዓተ ቅዳሴ ፍሬ ቅዳሴ ባለመሆኑ መዘጋጃ እንጂ መለወጫ አይደለምና። ይህም ሊታወቅ ቅዳሴው ሁሉ የዐሥራራቱም ይረስዮ የማይል ወይንም ምትኩን የሚይለጥ የለም። ከዚህ ላይ ከሁሉም የሚያሳዝነው ይርስዮ ተብሎ ከተለወጠ በኋላ ወልደ እግዚአብሔር በገሃድ ከመንበሩ ላይ እየተፈተተ ካህናቱ ሲቆርቡ፡ ሰው እንዳያውቅባቸው፡ የሰረቁ ይመስል፡ ሲያኩተመትሙ ወይንም ሃይማኖተ አበውና መልክአ ቁርባን ያለበታው ስለሚሉ፡ ሕዝቡ ሁሉ የግል ድጋሙን ማኩተምተሙ ነው፡ ድጋሙም ከቁርባኑ ጋራ ያልተያያዘ መልክአ መልክ ዳዊት፡ ውዳሴ አምላክ፡ አርጋኖን ወዘተ.ነው።
ሥርዓተ ቅዳሴውስ ይሁን አየን፡ አሠራሩስ እንዴት ቢሆን ይሻላል? ለሚል ጠያቂ የሚከተለው ሐሳብ ቀርቧል፤
የኛ ቄስ በትውፊቱ መሠረት አንዱን ጎብስትና ጽዋዕ በእጁ ይዞ ነው የሚቀድሰበት፡ በ24 ሰዓት ደግሞ አንድ ጊዜ ብቻ ነው የሚቀድሰው፤ ይህ ባለፈው በጥሩ ሁኔታ ሠርቷል፤ ሰምን? ቢሉ በጠቅላላ ሕዝቡ ጥቂት ከዚያውም የሚቆርቡ አምስት ሰሞነኞችና የታመሙ ወይም

ነፍስ የማያውቁ ሕፃናት፥ አእምሮአቸውን የሳቱ፥ ኃጢአት ለመሥራት የሚይችሉ አርጅተው የጃጁ ሽማግሌች ነበሩ። መጠኑም ለማቁረብ ጉንጭ ሙሉ ሳይሆን በአፍ ለመለከክ ያህል ነበር። አሁን ግን ስውም ስለበዛ ብትቆርቡ ትኮነናላችሁ የሚለው ማስፈራሪያ፥ ሁሉም በመማሩ ስለሚነሣ የተጠመቀ ሁሉ ሊቆርብ ነው፥ ክርስቲያን ነውና ስለዚህ ኅብስቱን ሥጋ መለኮት፥ ወይኑን ደመ መለኮት የሚያደርገው መንፈስ ቅዱስ ስለሆነ በብዙው ኅብስቱንም ወይኑንም አቅርቦ መንፈስ ቅዱስ እንዲለውጠው መጠየቅ ነው። ሕዝቡንም ኅብስቱ ከመሠራቱ በፊት እንዲመዘገብ ማስተማር መንገር። የተረፈ መሥዋዕትን (አኮቴትንና የእቶንን ልማድ) መፋቅ ነው። አንዲህ ያለው አሳፋሪ ልማድ ካልተነሣ ቤተ ክርስቲያኗ በቅርቡ ትዘጋለች።

በቅዳሴ ጊዜ ሁሉም የግል ድጋሙን ስለሚያኩተመትም፥ ያውም ደጉ የተቀረው ደግሞ ወሬውን ስለሚጠልዝ፥ ብዙ ጽሑፎች ተበትነዋል፥ ከእነሱም አንዱ እነሆ፥

የፍልሰታ ቅዳሴ 1964 ዓ.ም.

በአዲስ አበባ አድባራት።
ከዓለማየሁ ሞገስ።

ድሮ ድሮ ድሮ በሕፃንነቴ
ትዝ ይለኛል አሁንም ውዬ ማስቀደሴ
ውዬ መቀደሴ
በቀን አኩል ሳዜን ባሥራሐንድ ባሥር
ተጣትሬ ውዬ እያላጋኝ ዕርፉ:
ሳርም ስጎለጉል መሬት ስቆፍር
ከተማ ሳልመጣ ሳለሁ በገጠር:
ያላንዳች ያላንዳች ምድራዊ ደመወዝ: ሰዓታት ቁሜ አድሬ:
ኪዳን አስደርሼ:
ግለዳ ሲነጋ እንደ ሕዝቡ አርሼ:
በሮቼ ሲደክሙ ባሥር ተመልሼ:
ሕዝቡን አቆርብ ነበር ቅዳሴ ቀድሼ
ድሮ በሀገር ቤት በነበርሁኝ ጊዜ ቄስና ገበሬ
ከተማ ሳልገባ ሳለሁ በገጠሬ።
ከጊዜ በኋላ አጠናቀቅሁና ሐዲሱን ትምህርት
በብዙ ደመወዝ ገባሁ መሥሪያ ቤት:
በገጠር ሳለሁኝ በሮቼን ፈትቼ:
አስቀድስ ነበረ: እቀድስ ነበረ ሥራዬን ሁል ትቼ።
ከተማ ስገባ: መሥሪያ ቤት ስቀጠር ይኸ ሁሉ ቀረ
በለዓት ምክንያት ባህል ተለወጠ: ግብር ተቀየረ።
በዘጠኝ ባልገባ ሁሉም ሆነ መና
የማስተማር ኑሮ ኮንትራት ነውና።
ስለዚህ ሲደወል እየሰማሁኝ: እንዳልሰማሁኝ
በሰዓት ምክንያት: በሥራ ምክንያት ዝም ብዬ ናርሁኝ።
ደግሞም አንዳንድ ጊዜ ቅስት የሰው ኑሮ ትዝ ባለኝ ቁጥር
ልጅ ስሆን ልመለስ እቀጥር ነበር።
አጭር ረጅሙን የሕይወት ጎዳና
ሳዘግም ስጣደፍ እያልሁ ደፋ ቀና
በለዓት በሥራ እያመካኘሁ
የሕይወትን መንገድ ዘወር ብዬ ሳላይ ዘመን አሳለፍሁ።
ኑሮዬን ላጠቃ: እሱ ላይጠቃ ገንዘብ ሳሳድድ
በነፍስ መንገድ ሳይሆን በሥጋ መንገድ

በሥራ ምክንያት አለፈ ወራቱ ነጎደ ዘመን
እንዱንም ሳልይዘው በዚሁ አኳኋን።
በዚህ ሁሉ ዘመን በዚህ ሁሉ ጊዜ ሰምን ቀረህ ብሎ
ሰው ሲጠይቀኝ
የትዳሴው ጊዜ ከሥራዬ ጋራ እየሆነብኝ
ለመምጣት አልቻልሁም እየቸገረኝ
እያልሁኝ ስመልስ ሰሚጠይቀኝ ሰው ለጎሊናዬም፥
ጡረታ ስገባ እንደልጅነቴ
ቢቃናልኝ ሀብቴ
አስቀድሳለሁ ስል በፍልስታ ጸም፥
እንዲያው በድንገት
ባልታሰበ ጊዜ ባልታሰበ ዕለት
እንዲያው በድንገት
ከኋላ ቀርቸ ቤተ ክርስቲያናችን ለመጠች ሰዓትI
እንዲያው በድንገት
አንድ ቀን ምሽት
ሳይ ቴሌቪዥን
ለመጠች ጊዜን
የትዳሴውን።
እንዲያው በድንገት
ለመጠች ሰዓት
እንዲያው በድንገት
ጠፉ ምክንያት
ግለዳ ለኪዳን ግታ ለትዳሴ የምቀርበትI
ዐሥር ዐሥራሐንድን እንዳላየ ትቶ
ዘጠኝንም ዘሎ በስምንት ሰዓት
በዕረፍታችን ወቅት
ይፈጸግል ብሎ ሥርዓተ ቁርባን
ቢነገር ዐዋጁ የቤተ ክርስቲያን
ይህን ሁሉ ዘመን የሸፈትሁበቱ
ጠፉ ምክንያቱ
ይሽ ዱር ምክንያት እኔን ብቻ ሳይሆን ብዙ ሰው
ሸፍኖ ይኖር ነበርና
ይሽው ይታይ ገባ ያዳሚ ገመና
የየዋህ ስንፍና።

የኛ ቤተ ክርስቲያን ከኋላ ቀርታለች እየተባለች
ችግሯን በማያውቅ እንዲያ ስትነቀፍ እንዳልነበረች
ሦስቱን ሰዓታት፥ ሦስቱን ዘመናት ባንድ ቀን ሄደች
ነፃ ወጣችና
ምክንያት ከመሆን ላዳሚ ስንፍና
ና ልምራህ ና ልምራህ አሁንስ እንደጥንቱ በሥልጣኔዬ
በሕይወት ጎዳና
ስትለን ሰምቼ
ምክንያቴን ትቼ
ነሐሴ አንድ ቀን ግልፋ ተነሥቼ
ምክንያቴን ትቼ
ሄድሁ ቤተ ክርስቲያን
ግለፋ ለኪዳን
በዚሁ ደስ ብሎኝ በጣሙን ኮርቼ እኔ ስንጠራራ
እንደምነህ አሉኝ ቄስና ደብተራ።
ጸሎቴን ላልጨርስ ዘወር ብዬ ባይ
ድሮ የማውቃቸው
ጓደኞቼ ናቸውɪ
ልዩነቱ ብቻ እኔ ተመልጨ፥ ለውነቴ ከብዶ በብዙ ዱልት
እነሱ ግን ደርቀው በጸም በጸሎት

ፊታቸው እንዳለ፥ ጠጉራቸው እንዳለ እንደ ተፈጠረ
ወዛቸው እንዳለ ጎይላቸው እንዳለ እንደ ጠነከረ
ጥቂት እንዳወራን ምን እመጣህ? አሉኝ
እኔም ምክንያቱን ገልጨ ነገርሁኝ።
አውርቼ እንደጨረስሁ ቄሱ ቀደመና
ጋበዘኝ በነጋው ሰዓታት እንድሰግ
የሌቱን ውዳሴ ግሩሙን ጸሎት
የግይሰለቸውን የግይታክተውን ሁሌ ቢሰሙት
ደብተራውም ጠራኝ ለስብሐተ ነግሁ ለያሬዱ ዜማ።
በዚህ ትሕትናቸው በጣም ተገርሜ
ጣራ ጣራውን ላይ ከሐሳብ ላይ ቁሜ
ቅዱስ ሲል ተሰማ ካህኑ ከሩቅ
ሕዝቡም ተቀበለው ሆነ ድብልቅልቅɪ

በግዕዝ ያዜመውን በአማርኛ ፊቶ ለሕዝብ ያነባል፤
እንደበቱ ርቱዕ ይንበለበላል።
ዕፁብ ነው ግሩም ነው በጣም ይገርማል።
በበነጋታውም በቀጠሯችን
ሰግሁት ሰዓታቱን ሰብሐተ ነግሁን
በጣም ግሩም ነው፥ እጅግ ግሩም ነው
የካህኑ ፊንታ የሕዝብ ተሰጦው
እምሮ ተፈጸመ ሁሉም በተራው።
የሌሊቱን ሰዓታት፥ ያጠባቡ ኪዳን ደስ ቢላት ለነፍሴ
በቀትር ተመለሰሁ ደግሞ ለቅዳሴ።
እንድ ካህን ሰምቼ ከሁለት ወር በፊት
በቅዳሴው ሥርዐት ሰው የሚያሰደስት
ይህን እያወራሁ በሐሳብ ጎዳና
ገባሁ ቤተ ክርስቲያን ጉዞው አለቀና።
እንደበተ ደጉ፥ ጥሁመ ልሳኑ የማልዳው ካህን
ሲያነብ አየሁና ሥርዐተ ግብጹን
የምጸድቅ መሰለኝ እንዲያው በቁመና
ግልዳ ሁኔታውን አይቻለሁና።
ግና ፈጠነብኝ ፈጠነ ፈጠነ እጅግም ሮጠ
በንባብ ፈረሱ በግልቢያ ፈረሱ እየሼመጠጠ።
በረረ በረረ ካህኑ በረረ
ቃላትን በቃላት እያነባበረ
ካህኑ በረረ
'ሰ' ብሎ ሲጀምር ሰላም ለማለት
ምሰለ መንፈሰከን ሕዝቡ ጨረሱት
እንዲሁም ዲያቆኑ 'ተ'ን እንደጀመረ
ሕዝቡ ተሰጦውን ቀድሞ ተናገረ።
ካህኑ ዲያቆኑ ሕዝቡም ቀለጠፈ፥
ሰባት ተኩል ሳይሆን ጨረሰና ዐረፈ።
ጫጫታው ቢበዛ ውቂ ደብልቂው
የማለዳው ካህን መልአክ የማልዳው
የነግሁ ቅዱስ ሕዝብ የነግሁ ብሕትው
አሁን ደርሶ ግታ ምን አሳበደው
ምንድር አሮጠው?
እያለ ጎሊና ልብን ጠየቀው

አልተገኘም መልሱ በልቤ ባወጣ፡ ባንጎሉ ባወርድ
የኋላ የኋላ አስኪገለጥ ድረስ በውድም በግድ።
ቅዳሴው አለቀ በሰባት ተኩል
በስምንት ነበረ ዐዋጁ የሚል
ሰዓት ባያውቁ ነው እንደዚህ የሮጡ
ለነገ ይሉታል ሁሉ በእየፈርጡ
እያልሁኝ በልቤ በሰፈው ሳትት
እስመ ጎይል ብለው ወረዱ ድርገት።
ሰው በሰው ተጋፋ
መቆሚያ ምድር ጠፋ
መጡ ተሰልፈው አእላፍ ሕፃናት
ዳር እስከ ዳር ሆነ ድብልቅልቅ ጩኸት፤
ሕፃናት ሲያለቅሱ ዐዋቂው ሲጋፋ
መተራመስ እንጂ መደግመጥ ጠፋ።
ያ ቀን ተወስኖ ለሴቱ ለብቻ
ይመስል ነበረ የድሮ ዘመን።
ግፊያው ትርምሱ ዕለተ ምጽአት
ይመስላል ይመስላል ይመስላል በውነት
አትለይምና እናት የልጃን ጩኸት።
እንደዚህ እያለ ካምስት መቶ በላይ በቀን ይቆርባል
ሌላ ቀን ቅዳሴ የለ ይመስል
አይቆርብ ይመስል፤
የከተማው ሕፃን ቆጥሮ ፍልሰታን
በዓመት ሦስት ጊዜ በግድ ይቆርባል፤
ሕፃኑ አለቀሰ እንባ እስኪወጣው
እናቱ ሳትቆርብ ቁረብ ብትለው፡
ነክቶት ግያውቀውን ነፍስ ካወቀ አባቱ
ከቅኔ ላይ እርጋ ተቀበል ብትለው የፈራች እናቱ።
እናቱ ስትፈራ
አባቱ ሲፈራ
እንደገና ልጁ፡
ልጁ ምን ይበላ?
ጥንቱን ጥንቱን፡ ኧረ ጥንቱን፡ ጥንቱን፡
ሥጋ መለኮት
ደመ መለኮት

ለዓለም የተሰጠው ለጎጢአት ሥርየት
የልጅ ግሳደጊያ አይደለም ወተት
አይደለም ፍትፍት።
ሰውነት ሲቆሽሽ፥ ልብስ ዕቃችን ሲያድፍ ያሸዋል ሳሙና
ደኅና ሁኖ ታጥቦ እንዲያገኝ ንጽሕና፤
አሁን ግን ብናየው በሀገራችን
በዘመናችን
አባት በቆሸሸ፥ እናት በረከሰች ታጠበ ሕፃን፥
ወልዲ በታመመ ገብሬ ቢታከም
አይለቅም አይለቅም አይለቅም ሕመም።
ስለዚህ ይታከም ያው በሽተኛው
እያጠና ይቆይ ሕፃን ጤነኛው።
እናትና አባቱ እንደነሱ ሳይሆን ሳይሸፍት ብለው
ሕፃኑን አመጡት በእቅፍ አባብለው፤
ሲበሱ ሲበላ፥ ሲጠጡ ሲጠጣ የነበረው ልጅ
ዝም ብሎ አልቆረበም ተፈራገጠ እንጂ።
በውድም በግድም የተሰበሰቡት
ሲቆርቡ ሕፃናት
የተባለው ሰዓት
አሰፈሐን ሰምንት።
ካህኑን ለነቅፍ ፈጥኖ በግንበቡ
ሻግውን ሳሸጋጥጥ ቀለም ሲልስ ሕዝቡ
ሳይገባኝ ጥበቡ
አሁን አገኘሁት ይሄ ነው ለበቡ
ካህኑ ፈጠነ ሕፃን ለማቁረቡ
ይሄ ነው ሰበቡ
ቢገባው ባይገባው ጸሎቱ ለሕዝቡ
ምን ቸገረኝ ብሎ ካህኑ ፈጠነ ሕፃን ለማቁረቡ።
ቀድሞም በግዕዝ ሁኖ አሁንም በፍጥነት
ምንም አልተረዳ የቁርባን ጸሎት
ያውም በፍልሰታ
በሕፃናት ለቅሶ በልጆች ጫጫታ
ያውም በፍልሰታ።

ጎልማሳው ይመከር
ሕፃኑም ይማር
ለሕፃናት ቁርባን ቤተ ስኪያን ትምከር።
በሕይወተ ሥጋ ኢየሩሳሌም
ሲገባ ክርስቶስ ንጉሠ ሰላም፥
ወጥተው ተቀበሉት እዕሩግ ሕፃናት
ጎልማሶች ሲሸሹ ንቀው ጠልተውት
እንደዚሁም ሁሉ በሀገራችን
በዘመናችን
የወንጌሉን ታሪክ ሕዝቡ ሊፈሽም
ወይ ሕፃን ካልሆነ ወይም ካላረጀ ቁርባን አይነካም።
ስለዚህ ስለዚህ ጎልማሳ እንዲመከር እንዲማር ሕፃን
ለምእመናን ትምከር ቅድስት ቤተክሲያን።
ቢመክሩት ካልሰማ ግስተግር ነው መና
በሀገራችን ሁሉም ቄስ ነውና።
የሕፃናት ቁርባን ከዚህ ፊት በሰፈው ሲነገር ኑሯል
ግና ሕዝቡ ሕዝቡ መቸ ይሰማል፥
በዚህኛው ሰምቶ በዚያ ያፈሳል።
በክርስቶስ ዘንዳ ዘር ቆጥሮ ሊድን
ይህ ጥሩት ነው፥ ሲሉት ያሾላል አፉን
ይቆጥራል ዘሩን።
እሁንስ ቅዳሴውን ማነው የጎተተው ቄሱ ነው ካህኑ?
ወይንስ ዲያቆኑ?
ሕዝቡ ነው ሕዝቡ ነው ቄሱን ለመሳደብ ቅልብልብ ልሳኑ
ካህኑ ሲነግረው የማይሰማው በድኑ።
ቤተስኪያን ሚባለው ምእመንና ካህን
ሠልጥኗል ሠልጥኗል ሠልጥኗል ካህን
ግና ገና ገና ገና ነው ምእመን።
ምእመን በሃይማኖት አልሰማም እያለ እንዴት እንደ ቀረ
እንዳልዘረዝረው ጊዜዬም አጠረ።
የሕፃኑን ጩኸት ችላም ብንለው
እላሰማም እለ ሚያነበንበው።
ሕዝቡ በገፍ መጣ ቅዳሴ ሊያስቀድስ ተሰጥም ሊቀበል
መቆሚያ እስኪጠፉ ልክ እንደጥምቀት በዓል

በዚህ መቋሚያውን በዚህ ግድግዳውን ተደግፎ ቁሞ
ትዳሴውን ትቶ፥ ተሰጠውን ንቆ ፈጽሞ ፈጽሞ
ያነበንብ ጀመር የግል ጸሎቱን
እንቅልፉን አቋርጦ፥ ሌሊቱን ተነሥቶ ያልደገመውን።
የግል ጸሎት ልምዱ ግለኛ ነበረ
አሁንስ ተሻሽሎ ለቀትር ተቀጠረ።
ድጋፉን ያዘና ለትዳሴው ቆመ
ውዳሴ ማርያሙን እያኩተመተመ፤
ትዳሴውንና የግሱን ጸሎት
መሀይምን ትጉህ ነው ያዘው እንድነት።
ሁለት የወደደ አያገኝም አንድን ያውቀዋል በቃል፥
ግና ከመጽሐፉ፥ ገና ከመምህሩ እሱ ይበልጣል፥
ትዳሴ እንዳይሰግ በትዳሴ ጊዜ ያነበንባል፤
ከራሱ ከኢየሱስ ከትዱሱ ቁርባን ከሥጋ መለኮት
አቱቱው ተሸሎ ለሥርየተ ኃጢአት፥
እንኳን ሌላውና ቢሆንም ወንጌል
በትዳሴ ሰዓት ጊዜውም አይደል።
ድርገት ወረዱና ዕርገት ወረዱና ክርስቶስ ሲመጣ
ልጆች አስቲቆርቡ መጽሐፉን አወጣ
ያኛው ጎልጎታ ይህኛው ኪዳን
አንዱ መልክአ ኢየሱስ
መልክአ ጊዮርጊስ
መልክአ ማርያምና ውዳሴ ማርያም
ትዳሴ ማርያም
ትምህርተ ጎቡአት
ሰይፈ መለኮት
መልክአ መድኀኔ ዓለም
ለፍልሰታ ጸም
ቁሞ እያስቀደሰ ነገረ ማርያም
ካህኑ ያደምጣል ጭዋው ሲደግም።
ካህኑ ሲቀድስ በሌሎቹ አገር
በጣም ያስደስታል፥ ተሰጠውን ይዞ ሕዝቡ ሲዘምር።
ከዚህ ግን ሁሉ ዐውቆ ሚያስፈልገውን
በስዓታት በኪዳን በጊዜ ቁርባን
ያኩተመትመዋል የግል ጸሎቱን።

ሕም .....ቱቱቱቱቱቱ...ብርድ እንደያዘው
በታዛ በቅድስት በቅጽር በግቢው።
ድንጉላችን ጮኽ ንባችን ተመመ
ድምፁን የግል ጸሎት እያዝመገመ።
አንዱን ቀረብ ብዬ በቅዳሴ ጊዜ የግል ጸሎትህን
እትጸልይ ብለው
ባለመጠምጠሜ በሆዴ መወፈር በጣም ገረመው፤
እንዲህ ያለ ደፋር ከሄት መጣ ብሎ
አስተውሎ ዐየና መልሱን አከታትሎ
ቤተ ክርስቲያን መሄድ ለጸሎት መሆኑን አስረዳኝ በቶሎ።
ወዲያውስ እንዲያውስ፥ እንዲህ የተቆጣህ እኔ ብጸልይ
የሰውን ጎሊና ለማዘዝ ከቻልህ
ሥልጣኑ ካለህ
ከቅድስቱ ቁመው ወሬ የያዙትን አታስተውም ወይ?
ወይስ ከኔ በቀር ሌላው ሚሠራውን ዐይንህም አያይ?
እነዚያማ ረስተው ከየት እንደቆሙ
የወሬ ነጎድጓድ ያዝገመግማሉ
ሰማቸው ሰማቸው ይላሉ ሙሙ!!
ጆሮአቸው ቢቆረጥ ግንንም አይሰሙ
የመጡ ለወሬ፥ አየደል ለቅዳሴ
እነዚያን መምከርስ እትሞክርም ነፍሴ
እሽ በጂ ብለው ላያዳምጡኝ
የተሞኟቸውን ወሬአቸውን ግቂረጥ ደግም አይመስለኝ፤
እንግዲያ እኔን ብቻ በምን ስለልሽኝ
በደኅና ስጸልይ ምታቂርጠኝ?
አለና ቀጠለ ውዳሴ ግርያም
ዝም አልሁኝ እኔም
እኩሉ ሲጸልይ እኩሉ ሲያወራ
የትኛውን ልስማ ልቤን ገባው ግራ።
ታላላቅ መኳንንት ካጠገቤ ያሉ
ምርኳዝ ተገድፈው ሒሳብ ያስባሉ
ያዝመራውን ሽያጭ የቤቱን ከራይ
ብድሩ ተከፍሎ በዚህ ባምስት ዓመት
ያልቅልናል ወይ?

እስመ ጎያል ባዩ ባያለግቸው
ፀያስቸግራቸው
ይናገሩ ጀመር በጣም ጮኽ ብለው።
ፀተ ክርስቲያን ገብቶ ሒሳብ መተሳሰብ ላስተዋለው ሰው
ልክም ቢመስለው
ፀሁል ጊዜ እንግዳ እንደኔ ላለው
አሰናከረው።
ምንጊዜም ተስፋ አይቆርጥ ኤርምያሱ ልቤ
ተናገር ስላለኝ
ኤያመነታሁኝ
ልናገር ወሰንሁኝ ጌቶቼን ቀርቤ፤
ፀለለለ ቃል በረታ እንደበት
አሁን በዚህ ጊዜ ሲወረድ ድርገት
ለኛ ሲፈተት
ሥጋ መለኮት
ተሰጥዎ እነደ ግለት
ግረኝ እንደ ግለት
ስምን ቤተ ስኪያኑን ለሒሳብ ግሰቢያ አረጋችሁት?
ብዩው በትሕትና
ቃሜ ሳል ከፈቱ ዘወር አልሁኝና
ክነገር ያደገ ከሁለት እንዳቸው
ጀርባዬን በቡጢ ጎሶም አረገው
ምንድር ይሆን ብዩ ዘወር ብዩ ባይ
ፈቱ ተጨማዲል ዐይኑም ሁኗል ቀይ፤
ናረ በሙግት ባደባባይ ላይ
ታረቶ ሲገባ ላይነደው ነው ወይ?
ተመክሮ ሲገባ ላይነደው ነው ወይ?
ተከብረ ነክ ቆጥሮ የነገርሁትን
ጅጎነደነደልኝ የሚያስበው
ምንድር ያስኮንናል ሒሳብ ግሰሳሰል
ሌሚትና ቧልታ ሰው ግንኣት ይመስል?
ህንን ብሰማ ገርሞኝ ምክንያቱ
ይገባኝ ሙግቱ
ግስረዳው መስሎኝ አመጣሁ ምሳሌ
ጥሩ እንደ ብርሌ፤

በረቂቁ ንጉሥ ሥጋ መለኮት
በንጉሠ ነገሥት አምላክ አማልክት
በክርስቶስ ፈንታ
ንጉሠ ቢመጡ አሁን በዚህ አፍታ
ንጉሠ ንጉሠ ንጉሠ ምድራዊው
ይናገራሉ ወይ ብዙ ብጠይቀው
አምን አምን ብሎ አዳችም ሳያስብ ሙግቱን ለቀቀው
በቅዳሴ ጊዜ በዚሁ ብገፋ
ወዲያው ስለታየኝ ሰላም እንዲጠፋ÷
ቤተ ክርስቲያኒቱም እንድትሆን ፍርድ ቤት
ውሳኔ በሌለው ለመንቻካ ሙግት
ዝም አልሁኝ ዝም አልሁኝ ሸግዱን አንሥቼ
እሳቸው ረተው እኔ ተረትቼ።
እንዲህ ነው ሙግት እንዲህ ነው ሥርዐት÷
አደባባይ ሳይሆን÷
ቤተ ክርስቲያን ገብቶ÷
በቅዳሴ ጊዜ ያውም በድርገት፤
መልስ በማጣት ሳይሆን ሙግቱን ጠልቼ
ወሬውን ስጠላ ሙግት ብጀምር
ይቆጣል ይቆጣል ይቆጣል እግዜር።
ስለዚህ አልሁና ከምንግሪር
ዝም አልሁኝ ዝም አልሁኝ ሸግዱን አንሥቼ
እሳቸው ረተው እኔ ተረትቼ።
ጫጫታው ደመቀ በሴቱ ነገድ
በቤቱ አስተዳደር በልብሳቸው ሞድ
ጎፈሬ አበጣጠር÷ ጠጉር አሠራር
ምንም ሳይቀራቸው ከዳር እስከ ዳር
ከጎረቤታችን ያለችው ወይዘሮ
አጭር ትለብስና ትመስላለች ዶሮ፤
ወጣቶቹም ደግሞ በዘርፋፋ ቀሚስ
ያች ጎረቤቴ ናት መሬት ምታብስ
የምትጠርግ ጎዳና ልብስ የምትጨርስ
እያሉ ሲያወሩ ወጣት በተራው
ስለኳስ ጭዋታ አወራው አወራው አንድም ሳይቀረው።

ትንሽ ሽግግሎች ሥርዐቱን ያወቁ
ትእዛዘ የጠበቁ
በተመሥጠ ሁነው ቁመው ሲያስቀድሱ
ሕፃናት ተንጫጩ ጀመሩ ያለቅሱ
ጎሊና ሰው ጥሎ ጸሎቱን ተወና ሄደ ገሠገሠ
ቅዳሴውን ትቶ ዓለም አዳረሰ።
ካህኑ ሲቀድስ በተዋበ ድምፁ በረታ አንደበቱ
ዓለሙን ሲጋብዝ፥ ኑ፥ ሰሙኝ እያለ አነበል አቱቱ።
እኩሉ ሲጸልይ እኩሉ ሲያወራ
የትኛውን ልስማ ልቤን ገባው ግራ።

ምዕራፍ 19

አገልግሎት

ዓመት እስከ ዓመት በቤተ ክርስቲያን ዘወትር የሚደረሰው ጸሎት ድጋም ወይም ማሕሌት በአጠቃላይ አገልግሎት ይባላል። ይህ የካህናት አገልግሎት የቀሳውስትና የደባትር ተብሎ ከሁለት ይከፈላል፤ የካህናት ሰዓታት፥ ኪዳን፥ ቅደሴ ይባላል፥ የደባትሩ፥ የማሕሌታውያኑ ደግሞ በአጠቃላይ ማሕሌት ይባላል። ሰዓታትና ኪዳን ከአቡነ ዘሰማያት፥ ከዳዊት፥ ከቅዳሴ በቀር ተወዳዳሪ የሌላቸው ጸሎቶች ናቸው፥ ለሚጸልያቸው፥ በምንገዴ ለተርእዮና ለደመወዝ ካልሆኑ በቀር ለሚደርሳቸውም ጥሩ ጥሩ ድጋሞች ናቸው። ማሕሌትም በጸናጽል፥ በከበሮ በመቋሚያ እየታጀበ የሚደረስ ሰብሐተ እግዚአብሔር ነው። ግዕዝ ለሚያውቅ ሰው ሁለቱም በጣም ይጣፍጣሉ። የኛ ቤተ ክርስቲያን አገልግሎት በጣም ረጅም ነው፤ ቀሳውስቱም ሆነ ደባትሩ ከምሽቱ በአራት ሰዓት ገደማ የተደወለ፥ እስከ በነጋው ዐሥር ሰዓት ቁመው ያገለግላሉ ያውም እህል ሳይቀምሱ፤ አገልግሎቱ ከ14-15 ሰዓት ይፈጃል፥ ያውም ቢያልቅ፥ ግዕዝ ሕያው በነበረበት ጊዜ ምእመናንን ያንጽ ኑሯል። አሁን ግን ወንጌል እንዳትሰብክ፥ ክርስቶስ እንዳይታወቅ፥ ሃይማኖት እንዳይሰፋ ግጭበርበሪያ፥ መጋረጃ ከመሆን በቀር የሚጠቅመው የለም። የግጎበር ጸሎት ነው አይባል ከመዘምራኑ መካከል ፍቅር የት አለና፥ ሕዝቡን ይሰባል አይባል፥ ሕዝቡ ግዕዝ የት ያውቅና።

ከቅዳሴ በቀር ይህንም በእየቋንቋው ተርጉሞ፥ የቀረውን በአጭር ለዘመናዊ ሰው እንደሚመች ተደርጎ፥ ወንጌል ካልተሰበከ፥ ሃይማኖት ካልተነገረ በቀር የዚች ቤተ ክርስቲያን መዘኪያ ቅርብ ነው። ለምን ቢሉ ከደብተራ በቀር ማሕሌት የሚቆም፥ ከቁስ በቀር ሰዓታት የሚቆም ኪዳን የሚያደርስ፥ የሚያስደርሰ የት አለ? እንዲያውም አብዛኛው ክርስቲያን ነኝ ባይ ኢትዮጵያዊ አንዱን ከሌላው ለይቶም አያውቀው፥ እንኳን ለማድረስ ሊመጣ ቀርቶ። በእየዓመትባሉም በዓሉን ለማክበር የመጣው ጭዋ ከውስጥ ሲቀደስ፥ ሲወደስ ከውጭ በቅጽሩ አካባቢ ይዘፍናል፥ ይጯኅታል፥ ይንጫጫል። ይህ እንዳይሆን ከእናንተው በተሻለ ሕዝቡ ሊረዳው የሚችል፥ በሚገባው ቋንቋ አዲስ መዝሙር ተቀበሉ ቢባሉ ከዛሬ 1500 ዘመን በፊት ቅዱስ ያሬድ ከደረሰው በቀር እንቀበልም ብለው ሕዘቡን አደነቆሩ፥ ቤተ ክርስቲያንን ዘጉ፥ የክርስቶስን ስምና ግብር፥ መልክ አጠፉ። እግዚአብሔር መዘምር ቅዱስ ያሬድን፥ ቋንቋም ግዕዝ ብቻ አይደለምና የፊጠረ አገልግሎታችሁን ሕዝብና እግዚአብሔር እንደሚወዱት አድርጉ ቢባሉ

እምቢ አሉ። በዚህም ከትእዛዘ እግዚአብሔር ጋራ መጣላታቸው ነው፤ ይህም ከመዘምራኑ አለቃ ከዳዊት ጀምሮ ሲነገር ኑሯል፤ አያስተውሉትም እንጂ፥ እነሱም በእየዕለቱ ይቀኛሉ፥ የቅኔ ቋንጣ ስለሚባል መድገምም አይችሉ፤

ሰብሕዎ ለእግዚአብሔር ስብሐተ ሐዲስ እግዚአብሔርን በአዲስ ምስጋና አመስግኑ፤ (መዝ. 95፣ 97፣ 32:2-3)

በመዝሙርና በዝማሬ በመንፈሳዊም ቅኔ እስበላችሁ ተነጋገሩ፥ ለጌታም በልባችሁ ተቀኙና ዘምሩ፥ ሁል ጊዜ ስለሁሉ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ስም እምላካችንንና አባታችንን ስለ ሁሉ አመስግኑ። (ኤፌ. 5:19-20)

የእግዚአብሔር ቃል በሙላት ይኑርባችሁ በጥበብ ሁሉ እስበላችሁ አስተምሩና ገሥጹ፥ በመዝሙርና በዝማሬ በመንፈሳዊም ቅኔ በጸጋው በልባችሁ ለእግዚአብሔር ዘምሩ። (ቆላ. 3:16-17)

ቅዱሳት መጻሕፍት በሐዲስ መዝሙር እግዚአብሔር እንደሚደሱት ያስረዳሉ። ግን መንፈስ የሚያነቃቃ አዳዲስ መዝሙር አይወዱም፤ እነሱ በግዕዝ እየዘመሩ፥ በከበሮ ይደልቃሉ፥ በእግራቸው ያሸበሽባሉ፥ በእጃቸው ያጨበጭባሉ፥ ሌላው ግን በአግርኛ ሲዘምር ይቆጣሉ፥ ነገሩ ሁሉ ሰሚውን የሚያስደንቅ፥ አስተዋይ የሚያስገርም ነው። የኛ ካህናት ዳዊት በመድገም ከግንም ይበልጣሉ፥ ግን የሚለውን አይሠሩም፥ ግነብነብ ነው እንጂ አይረዱትም ግለት ነው።

አሕዛብ ሁላችሁ በእጆቻችሁ አጨብጭቡ፥ በደስታ ቃልም ለእግዚአብሔር እልል በሉ፥ (መዝ. 46:1)

ምድር ሁሉ፥ ለእግዚአብሔር እልል በሉ፥ በደስታም ለእግዚአብሔር ተገዙ፥ በሐሤትም ወደፊቱ ግቡ። (መዝ. 99:1-2) ለእግዚአብሔር የሚቀርብ መንፈሳዊ ምስጋና ከሆነ ግሽብሽብ፥ መወዛወዝ፥ በልዩ ልዩ የሙዚቃ መሣሪያ እየታጀቡ ግጨብጨብ እንደ ቅዱሳት መጻሕፍት ይቻላል። መዝሙሩ የሚገመተው በይዘቱ ነው እንጂ በቃናውና በምልክቱ አይደለም።

ምዕራፍ 20

አልዮ ነቢይ ድኅረ ክርስቶስ፡ የትንቢት ሁሉ መፈጸሚያ ክርስቶስ ነው።

የነቢይ መግለጫ፤ የነቢይ ትርጉም የመጣው ነበየ ተነበየ ካለው ግሥ ነው ይሸውም በዕብራይስጥ አንድ ሰው ስለ ሌላ ተናገረ ግለት ነበረ፡ አንደ ጠበቃ፤ ስለዚህ እስራኤል ባጠፉ ቁጥር፡ ነቢያት እየተነሡ በእግዚአብሔር ስም ይገሥጹ ጀመር፡ ሕዝቡም አልሰማ ሲሉ እግዚአብሔር ይቀጣል ሆነ፡ በኋላ ጥቂት በጥቂት የሕዝቡን ጥፋት እያዩ አስቱዋይ ሰዎች ሲገሥጹ፡ እግዚአብሔርም ሲቀጣ ትንቢት አስቀድሞ መናገርን ያሳይ ጀመረ። እየመረጠ ለሕዝቤ እንዲህ በል እያለ ሲያዝዝ፡ ነቢይም ሲላክ፡ ትንቢትም ይደርስ፡ ይፈጸማል ሆነ። አስቀድሞ የተናገረም ነቢይ ተባለ። በዚህ ትርጉም ከነቢያተ እስራኤል ብዙዎች ስለ ክርስቶስ ተናግረዋል። ከዚህም ሌላ አስቀድሞ ለመናገር ተሰጥዎ ያለው ሁሉ ነቢይ ይባላል። ሌሎችም ደግሞ በመንፈስ ይሁን በሕልም አይታወቅም አስቀድመው ይናገራሉ፡ ይደርሳልም፡ እነሱም እነደ ሁኔታው ልዩ ልዩ ስም አላቸው፤ ከዚህም የምናየው ግን ትልቁን ሊቀ ነቢያት፡ ተፍጻሜተ ነቢያት ክርስቶስ ነው። ብዙ ሰርባቶች ነቢይ ነን ከእግዚአብሔር ተልከናል እያሉ ሰውን ያታልላሉ፡ አታለዋልም፤ ከክርስቶስ በቀር የቀሩት ሁሉ ትንቢት የተነገረለትን፡ ሱባኤ የተቆጠረለትን አይሆኑም። ምክንያቱም ለክርስቶስ የተነገሩትን አይፈጽሙምና። ያ ትንቢት የተነገረለት ነቢይ የእግዚአብሔር መልክተኛ፡ ነቢይ ሊቀ ካህናት፡ ሊቀ ሰማዕት፡ ብእሲ መከራ፡ ንጉሥ ወልደ እግዚአብሔር፡ ወልደ ዳዊት፡ ወልደ አብርሃም ነው። የሚወለደውም በድንግልና ነው፤ ከክርስቶስ በኋላ የመጡት ሰርባቶች ሁሉ የተወለዱት በዘርዐ ብእሲ ሲሆን ዘርዓቸው ደግሞ ከአብርሃምና ከያዕቆብ ዘር ውጭ ነው።

የክርስቶስን፡ የኢሳን ነቢይነት የሚቀበል፡ አሪትን፡ ነቢያትን መዝሙርን ወንጌልን የሚያምን ሁሉ እውነተኛ ከሆነ በሌላ አስተዳደግ ስላደገ ባይዋጠውም ይህን ሐቅ መቀበል አለበት። ከሁሉ አስቀድሞ ሙሴ ሊቀ ነቢያት በአሪት ዘዳግም እስራኤልን ሲሰናበት፡ እንዲህ ብሏል፤

አምላክህ እግዚአብሔር ካንተ መካከል ከወገኖችህ እንደኔ ያለ ነቢይ ያስነሣልሃል፡ እርሱንም ስማው፡ እግዚአብሔርም አለኝ፡ የተናገሩት መልካም ነው፡ ከወንድሞቻቸው መካከል እነዳንተ ያለ ነቢይ አስነሣላቸዋለሁ፡ ቃሌንም በአፉ አደርጋለሁ፡ ያዘዝሁትንም ቃል ሁሉ

ይነግራቸዋል፥ በስሜም የሚናገረውን ቃሌን የማይሰማውን ሰው እኔ እበቀልለታለሁ። ነገር ግን ይናገር ዘንድ ያላዘዝሁትን በስሜ በድፍረት የሚናገር ወይንም በሌላ አማልእክት ስም የሚናገር ነቢይ እርሱ ይገደላል። (ዘዳ:16-20)

ይህን ጥቅስ አስተውለን ብናየው ክርስቶስ ወይም ትልቁ ነቢይ ከያዕቆብ ዘር እንጂ ከሌላ እንደማይመጣ ይናገራል። ለምን ቢሉ አንደኛ ከወንድሞቻችሁ መካከል ሲል የሚያሳየው የያዕቆብን ልጆች ብቻ ነው። እስራኤል ከያዕቆብ ከዐሥራ ሁለቱ ልጆች ከነገደ እስራኤል በቀር የተረፉን ወንድማችን አይሉምና። ከዚያ ውጭ የዘለዓለም ጠላት እንጂ ወንድማማች አይደሉምና። ለዚህም የሚከተሉትን ጥቅሶች እናቀርባለን፥ አብርሃም ይሥሐቅን ባረከ፤ ሕፃኑም አደገ ጡትም ጣለ። አብርሃምም ይሥሐቅን ጡት ባስጣለበት ቀን ግብፃ አደረገ። ሣራም ግብጻዊቱ አጋር ለአብርሃም የወለደችለትን ልጅ ሲሥቅ አየችው። አብርሃምንም ይህችን ባሪያ ከነልጅዋ አሳድ፥ የዚች ባሪያ ልጅ ከልጄ ከይሥሐቅ ጋራ አይወርስምና አለችው። ይህም ነገር አብርሃምን ስለልጁ በጣም አስቸገረው። እግዚአብሔርም አብርሃምን ስለ ባርያህና ስለብላቴናው አትዘን፥ ሣራ የምትነግርህን ቃል ሁሉ ስማ፥ በይሥሐቅ ዘርህ ይጠራልና አለው።

ስለዚህም በበነጋው ማልዶ ተነሥቶ ባሪያውን አጋርን ከልጅዋ ከእስማኤል ጋራ አባረታል። (ዘፍ. 21:8-14)

ከዚህ በኋላ ሁለቱ ወንድማማቾች ከልብ አልታረቁም። ከአብርሃምም ሞት በኋላ እግዚአብሔር ይሥሐቅን ባረከውም መረተውም። (ዘፍ. 25:11)

ይሥሐቅም ያዕቆብን ባረከ፥ ይሥሐቅም ስለ ሚስቱ ወደ እግዚአብሔር ጸለየ፥ መካን ነበረችና፤ እግዚአብሔርም ተለመነው፤ ርብቃም ፀነሰች፥ ልጆችም በሆዷ ውስጥ ይታገሉ ነበር። እርስዋም እንዲህ ከሆነ ይህ ለኔ ምኔ ነው? አለች። እግዚአብሔርንም ትጠይቅ ዘንድ ሄደች። እግዚአብሔርም አላት ሁለት ወገኖች በማሕፀንሽ ናቸው። ሁለቱም ሕዝብ ከሆድሽ ይከፈላሉ፤ ሕዝብም ከሕዝብ ይበረታል፥ ታላቁም ለታናሹ ይገዛል። ትወልድ ዘንድ ቀንዋ በተፈጸመ ጊዜ እነሆ በማሕፀንዋ መንታ ነበሩ። በፊትም የወጣው ቀይ ነበረ፥ ሁለንተናውም ጠጉር ለብሶ ነበር፥ ስሙም ኤሳው ተባለ። ከዚያም በኋላ ወንድሙ ወጣ፥ በእጁም የኤሳውን ተረከዝ ይዞ ነበር፥ ስሙም ያዕቆብ ተባለ። (25:21-26) እንዲህም እንደ ይሥሐቅና እስማኤል ለጊዜው ወንድማማቹ ለፍጹሙ ግን ልጆቻቸው ተለያይተው ተቆራርጠው

ቀሩ። ኤሳውስ እንዲያውም ከአሕዛብ ወገን ሁለት ሴቶች አግብቶ ይሥሐቅንና ርብቃን ሲያሳዝናቸው ኖረ እንጂ አልተመረቀም። (ዘፍ. 26:34-35)

ይሥሐቅም ያዕቆብን ዘርህ ይባረክ የእናትህ ልጆች ይስገዱልህ፡ የምድር አሕዛብ ይገዙልህ ብሎ መረቀው፡ (ዘፍ. 27:1-30) ያዕቆብም ይሁዳን ባረከ፡ ያዕቆብም ዕለተ ሞቱ ደርሶ ዐሥራ ሁለቱን ልጆቹን ሲመርቅ ከእሱ ዘር ክርስቶስ የሚወለድበትን ይሁዳን እንዲህ ብሎ መረቀው። ሁሉም በክርስቶስ ደረሰ ተፈጸመ፡

ይሁዳ ወንድሞችህ አንተን ያመሰግኑሃል። እጅህ በጠላቶችህ ደንደስ ላይ ነው፡ የአባትህ ልጆች በፊትህ ይሰግዳሉ፡ ይሁዳ ያንበሳ ደቦል ነው ፡ ልጄ ሆይ! ከደንህ ወጣህ፡ እንደ አንበሳ እሸመቅህ፡ እንደ ሴት አንበሳ አደባህ፡ ያስነሣው ዘንድ ግን ይችላል? በትረ መንግሥት ከይሁዳ አይጠፋም፡ የገዢም ዘንግ ከእግሮቹ መካከል፡ ገዢ የሆነው እስኪመጣ ድረስ፡ የአሕዛብ መታዘዝም ከእርሱ ይሆናል። ውርንጫውን በወይን ግንድ ያስራል፡ የአህያይቱንም ግልገል በወይን ሐረግ፡ ልብሱን በወይን ያጥባል፡ መጎናጸፊያውንም በወይን ደም፡ ዐይኑም ከወይን ይቀላል፡ ጥርሱም ከወተት ነጭ ይሆናል። (ዘፍ. 49:8-12)

ይህን ትንቢት ቃል ለቃል ከክርስቶስ በቀር ከያዕቆብ አሳትም ሆነ ከወንድሙ ልጆች የፈጸመ የለም። እስራኤልም ወንድምህን እንደራስህ ውደድ፡ ጠላትህን ጥላ ሲሉ ወንድም የያዕቆብን ልጅ እስራኤላዊውን፡ ጠላት ደግሞ ከዚያ ውጭ ያለውን ስለሆነ፡ ለእስማኤል ለኤሳው ርግማንና ጠላትነት ማስረጃ እስከዚህ የተጠቀሰው ይብቃንና ወደሌሎች ቃላት እንመለስ።

እግዚአብሔርም አለኝ ከወንድሞቻቸው መካከል እንዳንተ ያለ ነቢይ አስነሣላቸዋለሁ፡ ቃሌንም በአፉ አደርጋለሁ። ይህ ቃል ቃለ እግዚአብሔር ኢየሱስ ክርስቶስ ነው፡ አካላዊ ቃል ሥጋ ለብሶ ትስብእትን ይዋሐዳልና።

ያዘዝሁትን ቃል ሁሉ ይነግራቸዋል፡ በስሜም የሚናገረውን ቃሌን የማይሰማውን ሰው እኔ እበቀልለታለሁ። ይህንም ጣላ በፈለገ ዮርዳኖስ ሲጠመቅ፡ በደብረ ታቦር ብርሃነ መለኮቱን ሲገልጥ የምወደው ልጄ ይህ ነው፡ ስሙት ብሎ አረጋግጦለታል። የሊቀ ነቢያት ሙሴ ትንቢት ክክርስቶስ በቀር ሌላ አለማሳየቱን ካስረዳነ ሌላውን ደግሞ በእየተራው እንይ፡

ከሙሴ በፊት አብርሃም ይሥሐቅን ሊሠዋው ሲል ካዳነው በኋላ እግዚአብሔር ራሱ በመልአክ ሳይሆን፡ ዓለም በዘሩ በነጠላ፡ በብዙ

አይደለም እንደሚድን ነግሮታል፤ የምድር አሕዛብ ሁሉም በዘርህ ይባረካሉ፥ ቃሌን ሰምተሃልና። (ዘፍ. 22:18) በዚህም ሰዓለም ቡራኬ የሚያመጣው ነቢይ ወይም መሲሕ አንድ እንጂ ብዙዎች እንዳልሆኑ እንረዳለን። ብዙዎች መሲሓን ቢል ኑሮ በዘሮችህ ይል ነበርና። ይህንም ቅዱስ ጳውሎስ አብራርቶታል፤ (ገላ. 3:16) ይህንም ያለው በይሥሐቅ መሥዋዕትን ሐሳብ ሰለሆነ፥ ለሌላ አለመሆኑ ግልጥ ነው።

ክርስቶስ ዐምደ ብርሃን ነው፤ የቅዱሳት መጻሕፍት የፒራሚድ ጉልላትም ወንጌል ናት። ወደ ጉልላቱ የማያሳይ ግዕዘን ወይም ጠርዝ የለም። ብሉያት ስለ ክርስቶስ ይመጣል ብለው ትንቢት ይናገሩ፥ ነቢያት ደግሞ ልጅህን ላክልን እያሉ ይጸልዩ ነበር። ሐዲሳት ደግሞ የተነገረውን ትንቢት ሁሉ ክርስቶስ መፈጸሙን ይናገራሉ። በሌላም አንጋገር ነቢያት ክርስቶስ ይመጣል፥ ዓለምን ያድናል እያሉ ትንቢት በእየጊዜው ተናግረዋል፤ ራሱ እኔ ነኝ እያለ ድዉይ እየፈወሰ፥ ሙት እያስነሣ፥ ታምራት እያሳየ በእርግጥ ያምላክ ልጅ መሆኑን በግብር አሰረድቷል። ከእሱ በኋላ ደግሞ ደቀ መዛሙርቱ ሐዋርያት፥ ኦርድእት፥ ሊቃውንት፥ ያ ትንቢት ይነገርለት የነበረ መሲሕ ነቢይ ክርስቶስ መጥቶ ስለእሱ የተነገረውን ትንቢት ፈጽሞ ዓለምን አድኖ ወደ ሰማይ ተመልሶ ዐርጎ በአባቱ ቀኝ ተቀምጧል እያሉ ዓለምን አስተምረዋል። ስለዚህም በሰማዕትን በሀላውያን ነገሥታት ያለቁ ናቸው።

በሙሴ የተነገረው ትንቢት በክርስቶስ መምጣት መፈጸሙን ለማጠየቅ ቅዱስ ጴጥሮስ እንዲህ ብሎ መልሶለታል፤ እግዚአብሔር ከጥንት ጀምሮ በቅዱሳን ነቢያቱ አፍ የተናገረው ነገር ሁሉ አስከሚከናወንበት ዘመን ድረስ ሰማይ ይቀበለው ዘንድ ይገባልና፤ ሙሴም ለአባቶች አለቀች-ጌታ አምላክ እኔን እንዳስነሣኝ ነቢይ ከወንድሞቻችሁ ያስነሣላችኋል። የሚነግራችሁን ሁሉ ስሙት፥ ያን ነቢይ የማትሰማ ነፍስ ሁሉ ከሕዝብ ተለይታ ትጠፋለች አለ። ሁለተኛም ከሳሙኤል ጀምሮ የተነበዩት ነቢያት ሁሉ ስለዚህ ወራት ተነበዩ። እናንተ የነቢያት ልጆችና እግዚአብሔር ለአብርሃም፥ በዘርህ የምድር ወገናችህ ሁሉ ይባረካሉ ብሎ ከአባቶቻችንም፥ ጋራ ያደረገው የኪዳን ልጆች ናችሁ። ለእናንተ አስቀድሞ እግዚአብሔር ብላቴናውን (ልጁን) አስነሥቶ፥ እያንዳንዳችሁን ከክፋታችሁ እየመለሰ ይባርካችሁ ዘንድ፥ ሰደደው። (ግብ. 3:21-26) ዲያብሎስ አዳምን በአባብ አድሮ ስላሳተው፥ ጌታ እግዚአብሔር ዲያብሎስን በሥጋ ገብቶ የሚያሸንፈው ከዘሩ የሚወለደው ከርስቶስ እንደሆነ ተናግሯል፤ ከይሲን ይቀጠቅጣል፥

ተብሏል: እግዚአብሔር እምላክም አባቡን አለው: ይህን ስላደረግህ ከአንስሳት ከምድር አራዊትም ሁሉ ተለይተህ: እንተ የተረገምህ ትሆናለህ: በሆድህም ትሄዳለህ: አፈርንም በሕይወትህ ዘመን ሁሉ ትብላለህ። በእንተና በሴቲቱ መካከል በዘርህና በዘርዋ መካከል ጠላትነትን አኖራለሁ: እርሱ ራስህን ይቀጠቅጣሃል: እንተም ለኮናውን ትቀጠቅጠዋለህ። (ዘፍ. 3:14-15)

ይህም ዲያብሎስን ሥጋ ለብሶ ከአዳም ዘር ተወልዶ በመስቀል ተሰቅሎ ሙቶ ክርስቶስ ድል መንሣቱን ይናገራል። ይህንም ዮሐንስ ወንጌላዊው መልሶታል (ቀልብሶታል): ልጆቼ ሆይ ማንም አያስታችሁ: እሱ ጻድቅ እንደሆነ ጽድቅን የሚያደርግ ጻድቅ ነው: ኃጢአትን የሚያደርግ ከዲያብሎስ ነው: ዲያብሎስ በመጀመሪያ ኃጢአትን ያደርጋልና: ስለዚህ የዲያቢሎስን ሥራ ለማፍረስ የእግዚአብሔር ልጅ ተገለጠ: (1ዮሐ. 3:6-8)

ከድንግል ይወለዳል: እናንተ የዳዊት ቤት ሆይ! ስሙ በውኑ ሰውን ማድከማችሁ ቀላል ነውን? አምላኪየን ደግሞ የምታደክሙ? ስለዚህ ጌታ ራሱ ምልክት ይሰጣችኋል: እነሆ ድንግል ትፀንሳለች: ወንድ ልጅም ትወልዳለች: ስሙንም ዐማኑኤል ትለዋለች። (ኢሳ. 7:14) ይህም በድንግልና ተፀንሶ በድንግልና በመወለዱ ተፈጽሟል: የኢየሱስ ክርስቶስ ልደትም እንዲህ ነበረ: እናቱ ማርያም ለዮሴፍ ታጭታ: ሳይገናኙ በመንፈስ ቅዱስ ፀንሳ ተገኘች። (ማቴ. 1:18-24) እንዲህ ብሎ ማቴዎስ መፈጸሙን ነግሮናል።

ዓለሙን ሁሉ የሚያስተው ዲያብሎስና ሰይጣን የሚባለው ታላቁ ዘንዶ እሱም የቀደመው እባብ ተጣለ: ወደ ምድር ተጣለ: መላእክቱም ከርሱ ጋራ ተጣሉ። ታላቅም ድምፅ ከሰማይ ሰማሁ እንዲህ ሲል--አሁን ያምላካችን ማዳንና ኀይል መንግሥትም የክርስቶስ ሥልጣን ሆነ: ቀንና ሌሊትም በአምላካችን ፊት የሚከሳቸው የወንድሞቻችን ከሳሽ ተጥሏልና: እነሱም ከበጉ ደም የተነሣ: ከምስክራቸውም ቃል የተነሣ: ድል ነሡት (ራእ. 12:9-12) ይህም ዘፍ. 3:15 የተጻፈውን በትክክል ያጥፋል። ስለዚህ መሆኑንም ያስረዳል።

ጳውሎስም የሰላምም አምላክ ሰይጣንን ከእግራችሁ በታች ፈጥኖ ይቀጠቅጠዋል: ብሎ ደግሞታል: (ሮሜ 16:20)

አብርሃምም እግዚአብሔርን እስማኤል በፊትህ ቢኖር በወደድሁ ነበር አለው: እግዚአብሔርም በእውነት ሚስትህ ሣራ ወንድ ልጅ ትወልድልሃለች: ስሙንም ይሥሐቅ ብለህ ትጠራዋለህ: በእርሱ በኋላ በዘሩ የዘለዓለም ቃል ኪዳን ከእሱ ጋራ አቆማለሁ (ዘፍ. 14:19) ይህም

መፈጸሙን ቅዱስ ጳውሎስ በዕብራውያን መልእክቱ በምዕራፍ ሰባት በሙሉ ገልጦታል።
እንደ መልከጼዴቅ ሥርዓት አንተ ለዘለዓለም ካህን ነህ ብሎ እግዚአብሔር ማለ፥ አይጸጸትምም (መዝ. 109:4) ይህም ከላይ በተጠቀሰው ምዕራፍ ተመልሷል።
እግዚአብሔር ጌታዬን ጠላቶችህን- ለእግርህ ዱካ እስካደርግልህ ድረስ በቀኜ ተቀመጥ አለው፤ ይህም (ማቴ. 22:44፤ ማር. 12:36፤ ሉቃ. 20:42፤ ግብ. 2:34፤ 1ቆሮ. 15:25) ላይ ተመልሷል።

<u>ነቢይ ነው</u>፥ በዘዳግም ከ18:15-20 የተነገረው ነቢይ እሱ መሆኑንም ራሱና ደቀመዛሙርቱ አረጋግጠዋል፤ (ማቴ. 13:57፤ 21:11፤ ማር. 6:4፤ ሉቃ. 4:24፤ 7:16 ዮሐ. 1.21፤ 4:19፤ 7:40፥ ግብ. 3:22)
<u>ንጉሥ ነገሥት ነው</u>፥ እኔ ግን ንጉሤን በተቀደሰው ተራራዬ በጽዮን ላይ። (መዝ. 2:6)
እናንተ መኳንንቱ በሮችን ክፈቱ፥ የዘለዓለም ደጆችም ይከፈቱ፥ የክብር ንጉሥም ይግባ። የክብር ንጉሥ ማን ነው? እግዚአብሔር ነው፥ ብርቱና ጎያል እግዚአብሔር ነው፥ በሰልፍ ጎያል፤ (መዝ. 23:6-10)
አምላኪየና ንጉሤ አንተ ነህ፥ ለያዕቆብ መድኀኒትን አዝዝ፤ (መዝ. 43:4)
አቤቱ ፍርድህን ለንጉሥ ስጥ፥ ጽድቅህንም ለንጉሡ ልጅ (71:1)
እስራኤል በፈጣሪው ደስ ይበለው፥ የጽዮንም ልጆች በንጉሣቸው ሐሤትን ያድርጉ። (149:2)
እነሆ ንጉሥ በጽድቅ ይነግሣል፥ መሳፍንትም በፍርድ ይገዛሉ፤ (ኢሳ. 32:1፥ 9:6-7) በሌሊት ራእይ አየሁ፥ እነሆም የሰው ልጅ የሚመስል ከሰማይ ከደመናት ጋራ መጣ፥ በዘመናት ወደ ሸመገለውም ደረሰ: ወደፊትም አቀረቡት። ወገኖችና አሕዛብ በልዩ ልዩ ቋንቋ የሚናገሩ ሁሉ ይገዙለት ዘንድ ግዛትና ክብር መንግሥትም ተሰጠው፥ ግዛቱም የማያልፍ የዘላለም ግዛት ነው፥ መንግሥቱም የማይጠፋ ነው። (ዳን. 7:13-14)
<u>ንጉሠ ሰላም</u> ነው፥
ለዚህም ኢሳይያስ ምዕራፍ ዐሥራ ሐንድን ያነቧል። ከዚህ ቀጥሎም ዘካርያስ እንዲህ ብሏል፤ አንቺ የጽዮን ልጅ ሆይ! እጅግ ደስ ይበልሽ: አንቺ የኢየሩሳሌም ልጅ ሆይ! እልል በይ፥ እነሆ ንጉሥሽ ጻድቅና አዳኝ ነው: ትሑትም ሁኖ በአህያም፥ በአህያይቱ ግልገል በውርጫይቱ ላይ ተቀምጦ ወደ አንቺ ይመጣል (ዘካ. 9:9)

ይህ ሁሉ በሚከተሉት ጥቅሶች እንደ ተፈጸመ ተመልክቷል፥ ታዋቂል፥ ተገርብቷልI (ማቴ. 21:2-12I 25:34I ማር. 11:-1-11I ሉቃ. 19:28-38I ዮሐ. 12:12-19I 1ጢሞ. 1:17) በልብሱና በጭኑም የነገሥታት ንጉሥ የጌቶች ጌታ የሚል የተጻፈ ስም አለው (ራእ. 19:16)

<u>ብእሴ መከራ የመከራ ሰው ነውI</u>

ሲወለድ ጀምሮ ከሙታን ተለይቶ እስኪነሣ ድረስ የዚህን ዓለም ሠላሳ ሦስት ዓመቱን ያሳለፈው በመከራ ነውI ከግርግም ተወልዶ ከእንስሳት ጋራ ስነበተI የኢየሩሳሌምን ንጉሥ ሔሮድስን ፈርቶ ሦስት ዓመት በግብጽ በረሃ ተሰደደI ኋላም ለሦስት ዓመት የራሱ ግሳረፊያ ሳይኖረው ሦስት ዓመት ከሦስት ወር፥ ሀገር ላገር እየተንከራተተ ዙሮ አስተማረI የቀኑ አይሁድ አሰሩት፥ አዳፉት፥ ገረፉት፥ ገፈፉት፥ ገርፈው ሰቅለው ገደሉት። ይህ ሁሉ ገና ከመወለዱ በፊት ተነግሯል። የሰማነውን ነገር ግን አምኖናል? የእግዚአብሔርስ ክንድ ለማን ተገልጧል? በፊቱ እንደ ቡቃያ ከደረቀም መሬት እንደ ሥር አድጓል፥ መልክና ውበት የለውም፥ የተናቀ ከሰውም የተጠላ፥ የሕማም ሰው፥ ደዌንም የሚያውቅ ነው፥ ሰውም ፊቱን እንደሚሰውርበት የተናቀ ነው፥ እኛም አላከበርነውምI በእውነት ደዌያችንን ተቀበለ፥ ሕማማችንንም ተሸክሟል፥ እኛም እንደ ተመታ በእግዚአብሔርም እንደ ተቀሠፈ ቆጠርነው። እሱ ግን ስለመተላለፋችን ቆሰለ፥ ስለ በደላችንም ደቀቀ፥ የድኅንነታችንም ተግሣጽ በእሱ ላይ ነበረ፥ በእሱም ቁስል እኛ ተፈወስን። (ኢሳ. 53:1-12I መዝ. 22:1-31I ማቴ. 27:27-35I ዮሐ. 1:29I 1ጴጥ. 1:19I 2:21-25)

<u>ሰማዕት፥ ሊቀ ሰማዕት ተኣማኒ ሰማዕት ነውI</u>

ስለእባቱ በመመስከሩ፥ እባቱን እባቴ ነው በማለቱ በዐውደ ጲላጦስ ተገርፎ በአይሁድ እጅ ተሰቅሏል።

<u>ኃጢአተ ዓለምን የሚያስተሰርይ መሥዋዕት ነውI</u> (ዮሐ. 1:29I 1ጢሞ. 2:5-6I ራእ. 1:5-6)

ምዕራፍ 21

የሐሳዊ መሲሕን መምጣት ክርስቶስና ሐዋርያት ነገረዋል፤

ከዚህ በላይ እንደ ተገለጠው ትንቢትን ሁሉ ከፈጸመ በኋላ፥ ከኔ በኋላ ሐሳዊ መሰሕ እንጂ ነቢይ የለም እያለ ሰበከ፤ ሐሰውተ መሲሕም እንዴት ያሉ እንደሆኑ ገልጦ ነገረ፥ ማስጠንቀቂያ እየሰጠ አስረዳ። የቤተ መቅደስን መፍረስ፥ የንዋየ ቅድሳትን መዘረፍ፥ የእይሁድን መማረክ የኢየሩሳሌምን መጥፋት አብራርቶ ተናገረ።

እሱም ከመቅደስ ወጥቶ ሄደ፥ ደቀመዛሙርቱም የመቅደሱን ግንቦች ሊያሳዩት ቀረቡ። እሱ ግን መልሶ ይህን ሁሉ ታያላቸሁን? እውነት እውነት እላችኋለሁ ደንጊያ በደንጊያ ላይ ሳይፈርስ በዚህ አይቀርም አላቸው።...እሱም መልሶ እንዲህ አላቸው ግንም እንዳያስታችሁ ተጠንቀቁ፤ ብዙዎች እኔ ክርስቶስ ነኝ እያሉ በስሜ ይመጣሉና ብዙዎችንም ያስታሉ፤...ብዙ ሐሰተኞች ነቢያት ይነሣሉ፥ ብዙዎችንም ያስታሉ፤...እስከ ዓለም መጨረሻ የሚጸና ግን እሱ ይድናል።...ከዚያ ጊዜ እነሆ ክርስቶስ (መሲሕ) ከዚህ አለ ወይም ከዚያ አለ ቢሏቸሁ አትመኑ፥ ሐሰተኞች ክርስቶሶችና ሐሰተኞች ነቢያት ይነሣሉና፥ ቢቻላቸውስ የተመረጡትን እንኳ እስኪያስቱ ድረስ ታላላቅ ምልክትና ድንቅ ያሳያሉና እነሆ፥ አስቀድሜ ነገርኋችሁ።

ወድ እንባቢ በክርስቶስ ወንድሜ ሆይ፤ ይህን ምዕራፍና ጓደኞቹን መላልሰህ እንበህ ከክርስቶስ በኋላ ከመጣውና ከሚመጣው መከራ እንድትድን ትጠቀግለህ። (ማቴ. 24:1-51፤ ማር. 13:14-23፤ ሉቃ. 21:20-24)

በመጨረሻም የመንፈስ ቅዱስን መምጣት ለደቀ መዛሙርቱ ነግሮ ወርዓል። እሱም እሱ በወረገ በዐሥረኛው ቀን በሐዋርያት ላይ በእምላስ ነበልባል ወርዶ በልዩ ልዩ ቋንቋ አናግሮ፥ ደካማ የነበሩትን ጎያላን፥ ፈሪዎች የነበሩትን ጥቡኣን አድርጓል። የመንፈስ ቅዱስን የመምጣት ተስፋ ሰሌላ ነቢይ ነው የተናገረ የሚሉ አሉ። ይህ ፍጹም ስሕተት ነው፥ ምክንያቱም ቢሉ በኢየሩሳሌም ሁነው የአብን ተስፋ እንዲጠብቁ አዘዛቸው፤ ዮሐንስ በውኃ አጠቀመ እናንተ ግን በቅርቡ በመንፈስ ቅዱስ ትጠመቃላችሁ ባላቸው መሠረት በዐሥረኛው ቀን መንፈስ ቅዱስ ወርዶ ተጠምቀዋል። (ግብ. 1:4-6፤ ሉቃ. 24:47:8)

ከዚህ በላይም ሌላ ነቢይ የሚልክ ወይም የሚላክ ቢሆን ኑሮ እውነተኛው ክርስቶስ እስከ ዓለም መጨረሻ አብራእችሁ ነኝ አይልም ነበር። (ማቴ. 28:19)

ደቀ መዛሙርቱም ይህን እምነው ተቀብለው ለዓለም እንዳለ አስተምረዋል እነሱም በተሰጣቸው ህብተ ትንቢት የታያቸውን የሐሳውያን ነቢያትን መምጣት በሰፊው ተናግረው አስጠንቅቀዋል። ነገር ግን በመጨረሻው ቀን የሚያስጨንቅ ዘመን እንደሚመጣ ዕወቅ፤ ሰዎች ራሳቸውን የሚወዱ ይሆናሉና፥ ገንዘብ የሚወዱ ትምክሕተኞች፥ ትዕቢተኞች፥ ተሳዳቢዎች፥ ለወላጆቻቸው የማይታዘዙ፥ የማያመሰግኑ፥ ቅድስና የሌላቸው፥ ፍቅር የሌላቸው፥ ዕርቅን የማይሰሙ፥ ሐሜተኞች፥ ራሳቸውን የማይገዙ፥ ጨካኞች፥ መልካም የሆነውን የማይወዱ፥ ከዳተኞች፥ ችኩሎች፥ በትዕቢት የተነፉ፥ ከእግዚአብሔር ይልቅ ተድላን የሚወዱ ይሆናሉ፤ የአምልኮት መልክ እያላቸው ኀይሉን ይክዳሉ፥ ከእነዚህ ደግሞ ራቅ። ወደ ቤቶች ተሸሉክሉክው እየገቡ፥ ኃጢአታቸው የተከመረባቸውን፥ በልዩ ልዩ ምኞቶች የሚወሰዱትን ሁልጊዜም እየተማሩ እውነትን ወደማወቅ ሊደርሱ ከቶ የማይችሉትን ሞኞችን ሴቶች የሚማርኩ ከእነዚህ ዘንድ ናቸውና። (2ጢሞ. 3:1-7)

መንፈስ ግን በግልጥ በኋለኞች ዘመናት አንዳንዶች የሚያስቱ መናፍስትንና በውሸታሞች ግብዝነት የተሰጠውን የአጋንንት ትምህርት እያደመጡ ሃይማኖትን ይክዳሉ፤ (1ጢሞ. 4:1-3፤ ሮሜ 1:29-31፤ 2ጴጥ. 3:3፤ 1ዮሐ. 2:18፤ ይሁ. 18)

<u>መደምደሚያ</u>፥ ይህ ሁሉ እያለ ነው በእየጊዜው ክርስቶስ (መሲሕ ነቢይ) ነን እያሉ የሚነሡ። ሥልጣንና ገንዘብ ለማግኘት በስርብትና ከሆነ ነገሩ መቸስ ምን ይደረጋል? በሃይማኖት ግን የትም እንደማይሰድ መጻሕፍት ሁሉ ይናገራሉ፥ ተናግረዋል። ስለዚህ በክርስቶስ ወንድሜ አንባቢ! ይህን ምዕራፍ አንበህ ነፍስህን እንድታድን ትጠቅማለህ።



ምስጢረ ትንሣኤ

ክርስቶስ ከሞት ካልተነሣ ፥ የኛም ትምህርት ሆነ ፥ የእናንተም እምነት ከንቱ መሆኑ ነዋ!

ምዕራፍ 22

ምስጢረ ትንሣኤ ሙታን

ሊቀ ነቢያት ወልደ እግዚአብሔር ጌታችን ኢየሱስ ከርስቶስ ስለእሱ በመንፈስ ቅዱስ በነቢያት የተነገረውን ትንቢት ሁሉ በሠላሳ ምስት ዓመት ከምስት ወር ፈጽሞ፥ ከሙታን በተነሣ በአርባኛው ቀን በቅርቡ መንፈስ ቅዱስን እልክልከላቸሁ፥ በኢየሩሳሌም እንድነት ሁናቸሁ ጠብቁ ብሎ እዝዞ እስከ ዓለም ፍጻሜ አብራአችሁ አለሁ ብሎ ተሰፋ ሰጥቶ፥ እንደ ገና በግርማ መለኮት በዓለም ላይ ለመፍረድ የሚመጣ መሆኑን ነግሮ፥ ወደ አባቱ ወደ ሰማይ ዐረገ። ወዲያውም መላእክት እንዲሁ አሁን ሲያደርግ እያያችሁት ይመለሳል ብለው ለሐዋርያት ነገሩ። በዚሁ መሠረት እግዚአብሔር ራሱ በወሰነውና በሚያውቀው ቀን አእላፍ መላእክት ከበውት ይመጣል። (ማቴ. 25:31፤ ግብ 1:11)

የነፍሰን ትርጓሜ ከተራ ሕዋሰ ተነሥቶ እስከ ነባቢት፥ ሰባቂት ሕያዊት ድረስ በልዩ ልዩ ቃላት ትርጉም ምዕራፍ 33 አስረድተናልና በዚያ ግዮት ይቻላል። በዚህ ደግሞ በሥጋ ሁና በሠራችው ሥራ ዋጋዋን ወይም ፍጻዋን የምታገኝ መሆኗን እንደ ቅዱሳት መጻሕፍት እንተነትናለን። ከርስቶስን ለማያምን፥ ሐዋርያትን ለማይቀበል ሰው ካልሆነ በቀር በግያሻግ ትርጉም ትንሣኤ ሙታን እንዳለ በግልጥ ተነግሯል። ትንሣኤ ሙታን አለ፥ ከርስቶስ ዳግመኛ ወደዚህ ዓለም ለቅዱሳን ዋጋ ለመስጠት በጋጥአን ላይ ለመፍረድ ይመጣል። ሲአልና ገሃነመ እሳት ለደይን ለኩነኔ አሉ። ነነት፥ መንግሥተ ሰማያት ደግሞ ዓለም ከመፈጠሩ በፊት ለጻድቃን ማረፊያና ለዘለዓለም ሕይወት ተዘጋጅተው አሉ፥ ይኖራሉ።

ለሁሉም ከዚህ በላይ የተጠቀሰውን ማቴ. 25:31 እስከ መጨረሻው እንየው እሱም፤

የሰው ልጅ በክብሩ በሚመጣበት ጊዜ ከርሱም ጋራ ቅዱሳን መላእክት ሁሉ፥ በዚያን ጊዜ በክብሩ ዙፋን ይቀመጣል፥ አሕዛብም ሁሉ በፊቱ ይሰበሰባሉ፥ እረኛም በጎቹን ከፍየሎች እንደሚለይ እርስ በርሳቸው ይለያቸዋል፥ በጎቹን በቀኙ ፍየሎቹንም በግራው ያቆማቸዋል። ንጉሡም በቀኙ ያሉትን እንዲህ ይላቸዋል፥ እናንተ የአባቴ ቡሩካን! ኑ፥ ዓለም ከተፈጠረ ጀምሮ የተዘጋጀላችሁን መንግሥት ውረሱ፤ ተርቤ አብልታችሁኛልና፥ (35-40) ከዚያ በኋላ በግራ ያሉትን ደግሞ እናንተ ርጉማን! ለሰይጣንና ለመላእክቱ ወደ ተዘጋጀ ወደ ዘለዓለም እሳት ከኔ ሂዱ፥ ተርቤ አላበላችሁኝምና (42-46: አንብ) እነዚያም ወደ ዘለዓለም ቅጣት፥ ጻድቃን ግን ወደ ዘለዓለም ሕይወት ይሄዳሉ።

ወደ ገሃነም ከወረዱ እንደ ደረት ዕንጨት ተቃጥለው የሚያርፉት አዶደለም ዘለዓለማዊ እንጂ። (ማቴ. 8:12፤ 22:13 ማር. 9:44-48፤ 2ተሰ. 1:5-15)

ቅዱስ ጳውሎስም በቀዳማዊ ቆሮንቶስ መልእክቱ ምዕራፍ 15ትን ስለ ትንሣኤ ሙታን ብቻ ጽፏል፥ ምዕራፉን በሙሉ ማንበብ ያሻል። ለመጥቀስ ያህል፥ ክርስቶስ ከሙታን እንደ ተነሣ የሚሰበክ ከሆነ ከእናንተ አንዳንዶቹ ትንሣኤ ሙታን የለም እንዴት ይላሉ? ትንሣኤ ሙታንም ከሌለ ክርስቶስ አልተነሣም። ክርስቶስ ካልተነሣም እንግዲያስ ስብከታችን ከንቱ ነው። እምነታችሁም ደግሞ ከንቱ ናት። በዚች ሕይወት ብቻ ክርስቶስን ተስፋ የምናደርግ ከሆነ ከሰው ሁሉ ይልቅ ምስኪኖች እኛ ነን። በአንደኛ ተሰሎንቄ መልእክቱ ምዕራፍ 4 ከ13 ጀምሮ ደግሞ፥ ነገር ግን ወንድሞቼ ሆይ! ተስፋ እንደሌላቸው እንደሌሎች ደግሞ እንዳታዝኑ፥ አንተላፍተው ስላሉት ታውቁ ዘንድ እንወዳለን። ኢየሱስ እንደሞተና እንደ ተነሣ ካመንን፥ እንዲሁም በኢየሱስ ያንቀላፉትን እግዚአብሔር ከርሱ ጋራ ያመጣቸዋልና። በጌታ ቃል የምንላችሁ ይህ ነውና፥ እኛ ሕያዋን ሁነን ጌታ እስኪመጣ ድረስ የምንቆይ ያንቀላፉትን አንተድምም ጌታ ራሱ በትእዛዝ በመላእክትም አለቃ ድምፅ በእግዚአብሔርም መለከት ከሰማይ ይወርዳልና፥ በክርስቶስም የሞቱ አስቀድመው ይነሣሉ፥ ከዚያም በኋላ እኛ ሕያዋን ሁነን የምንቆይ ጌታን በአየር ለመቀበል ከእነሱ ጋራ በደመና እንነጠቃለን እንዲሁም ሁልጊዜ ከጌታ ጋራ እንሆናለን።

የሚከተሉት አናቅጽም ትንሣኤ ሙታንን ይደግፋሉ፤ (ሮሜ 14:9፤ 1ተሰ. 1:9-10 2ተሰ. 1:5-15)

የሙታን ትንሣኤ መሠረቱና ምሳሌው ክርስቶስ ነው፥ ግን ክርስቶስ በእርግጥ ሙቶ አልተነሣም። አንዳንዶቹ አይሁድ ሊገሉት ሲሉ የእሱን ወዳጅ ዮሐንስን ተክቶ ክርስቶስን ቸሸገው፥ ሌሎቹ ደግሞ ተሠውቶ ሙቶ ለእግዚአብሔር የመጨረሻ መሥዋዕት ሁኖ በመሥዋዕትነት ተታጥቦ ለእግዚአብሔር ተረበና፥ እግዚአብሔርም ይህን መሥዋዕት ተቀብሎ ዓለምን ማረው እንጂ ሙቶ አልተነሣም ይላሉ፤ ይህን የሚሉት ስግቸው ባይጠራም በጎረቤታችን ስላሉ ስም አያስፈልግም። ኢየሱስን የሚያምኑና ቅዱሳት መጻሕፍትን የሚቀበሉ ከሆነ የራሳቸውን ፈጠራ ትተው ቅዱሳት መጻሕፍትን መቀበል አለባቸው። ትንሣኤ ክርስቶስ በነቢያት በመንፈስ ቅዱስ ሲነገር የኖረ፥ ክርስቶስ መጥቶ ራሱ የተነሣው ከትንሣኤው በኋላም ራሱ ያስተማረው ሐዋርያት የሰበኩት ታሪክ ነው። (መዝ. 15:10፤ 77:65፤ 48:15)

በኢሳ ሞት ተተካ የተባለው ወንጌላዊው ዮሐንስም ከትንሣኤ በኋላ ሲሰብክ፥ ሲያስተምር ለብዙ ዘመናት መኖሩን፥ የጻፈው ወንጌልና መልእክታቱ ያስረዳሉ።

ከዕብራይስጡና ከግሪኩ ጋራ የማይስማማ የራሳቸውን መጽሐፍ ቅዱስ ይዘው፥ መጽሐፍ ቅዱስ ነው እያሉ፥ ቤተ ክርስቲያን ሠርተው ሳይሆን፥ ቤት ሰቤት እየተሽሎከለኩ ያልተማሩትን የሚያስቱ መስሕታን አርዮሳውያን አሁን ዘመን ራሳቸውን የጆሐባ ምስክሮች ነን የሚሉ ደግሞ መጨረሻ መሥዋዕት ሁኖ ለያሕቤ ቀረበ እንጂ ክርስቶስ አልተነሣም ስለሚሉ ክርስቶስ ራሱ ከተነሣ በኋላ ትንሣኤውን እንዳስተማረ ሐዋርያትም ዓለምን እየዞራችሁ አስተምሩ ብሎ ባዘዛቸው መሠረት ዓለምን እየዞሩ ትንሣኤውን መስበካቸውን ለማስረዳት የሚከተሉትን አናቀጽ እናቀርባለን።

<u>መጀመሪያ ራሱ ጌታችን መድኀኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከትንሣኤው በኋላ</u>

በመጀመሪያ ከመቃብሩ አጠገብ እሑድ ማለዳ በአጠባብ ለማርያም መግደላዊት ታየ፥ ከዚያ ሲመሽ ማታ በአማሁስ ሰሚሄዱ ሁለት ሰዎች ታይቶ ማዕድ ባረከላቸው፥ ከዚያ በኋላ ዐሥራ ሐንዱ ሐዋርያት አንድነት ተሰብስበው ካሉበት ቤት ገብቶ፥ ሰላም ለእናንተ ይሁን አላቸው። እነሱ ግን ደነገጡና ፈሩ፥ መንፈስም ያዩ መሰላቸው። እሱም ስለምን ትደነግጣላችሁ? ስለምንስ ሐሳብ በልባችሁ ይነሣል? እኔ ራሴ እንደሆንሁ እጆቼንና እግሮቼን ዕዩ፥ በእኔ እንደምታዩት መንፈስ ሥጋና ዐጥንት የለውምና እኔን ዳሳችሁ እዩ አላቸው። ይህንም ብሎ እግሮቹንና እጆቹን አሳያቸው። እነሱም ከደስታ የተነሣ ገና ስላላመኑ ሲደነቁ ሳሉ (መንፈስ አለመሆኑን ለማረጋገጥ) በዚህ አንዳች የሚበላ አላችሁን አላቸው። እነሱም ከተጠበሰ ዓሣ ቁራጭና የማር ወለላ ሰጡት፥ ተቀብሎም ከፊታችው በላ።

ከዚያም ቀጥሎ በሕይወተ ሥጋ አብሯቸው ሳለ ያስተምራቸው የነበረን እንደገና እንዲህ እያለ አብራራላቸው፤ ከእናንተ ጋራ ሳለሁ በሙሴ ሕግና በነቢያት በመዝሙራትም ስለኔ የተጻፈው ሁሉ ይፈጸም ዘንድ ይገባል ብዬ የነገርኋቸሁ ቃሌ ይህ ነው አላቸው።

አብሯቸውም ሲበላ ሲዳስሱትም ነበር፥ ያውም ሴቶች፥ መብላትና መዳሰስ የመንፈስ ተግባር አይደለም። (ማቴ. 28:5-16፤ ማር. 16:1-16፤ ሉቃ. 24:13-49፤ ዮሐ. 20:1:29፤ 1ዮሐ. 1:1፤ 1ቆሮ. 15:1-58፤ 1ተሰ. 4:13-18)

ከቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ ስለትንሣኤ ሙታን የማይናገሩ በጣም ጥቂቶች ናቸው፥ ስለዚህ ያለምንም ችግር ብዙ መጥቀስ ይቻላል፤ በመሆኑም እንባቢ የተጻፈውንና የተጠቀሰውን በደንብ አስተውሎ እንዲረዳ ጠቁመን እንደመድግለን።

ለትንሣኤ ሙታን መደምደሚያ

ነፍስ የሚለው ቃል ብዙ ትርጉም እንዳለው ከአሳየነ በኋላ ሰባቂት፥ ነባቢት፥ ሕያዊት ነፍስ እንዳለችና ዘለዓለማዊ ፍርድ ከዓለም ዳኛ ከጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በዕለተ ምጽአት በሕይወተ ሥጋ ሳለች በሠራችው መሠረት ዋጋ ወይም ፍዳ እንደምትቀበል በዚህ ርእስ ተገልጧል። በዚሁ መሠረት ተዘጋጅቶ መቆዬት ያስተዋይ እንባቢ ፈንታ መሆኑን ገልጠን እናልፋለን።

ምዕራፍ 23

መንፈስ ቅዱስ

መንፈስ ቅዱስ ከሦስቱ አካላት አንዱ አካል መሆኑን በምስጢረ ሥላሴ ተናግረናል። ሦስቱ አካላትም ዕሩያን ናቸው፤ አንዱ ሌላውን አይበልጠውም፤ ላከው፥ አዘዘው ቢባልም በጎብረት በሥምረት በፈቃድ ነው እንጂ አንዱ ሌላውን የሚበልጠው ሁኖ አይደለም፤ በእሱ በአባቱና በመንፈስ ቅዱስ ፈቃድ መጥቶ አዳነን እንደሚለው። ከዚህም መንፈስ ቅዱስን አብ ይልክላችኋል፥ አብ በስሜ የሚልክላችሁ መንፈስ ቅዱስ ይገልጥላችኋል፥ ያስተምራችኋል፤ እኔ መንፈስ ቅዱስን እልክላችኋለሁ፥ መንፈስ ቅዱስ ይመጣል ይላል፥ ሁሉም ያው ነው። መላኩም ሆነ መምጣቱ በምስጢረ ሥላሴ እንደ ተገለጠው ከሁለቱ አካል ጋራ ያለውን ዕሩይነት አያጎድሉበትም። (ዮሐ. 14:26፤ 15:26፤ 16:7)

በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን እንደ መንፈስ ቅዱስ ችላ የተባለ ወይንም ያልታወቀ ከሦስቱ አካላት የለም። ለምሳሌ በአሁኑ ጊዜ በአዲስ አበባ 56 አብያተ ክርስቲያናት አሉ፤ በመንፈስ ቅዱስ ስም የታነጸ ግን አንድም የለም። የሥላሴ ሁለት የእግዚአብሔር አብ ሦስት፥ የመድኀኔ ዓለም ሰባት፥ ይህም ከግርያም ስለተወለደ እንጂ ግን ዙሮ አይቶት አያ! በጠቅላላ በአስግተ ሠለስቱ ሥላሴ አሐዱ አምላክ 10 አብያተ ክርስቲያን አሉ፤ የተቀረው ግን በግረያም፥ በመላእክት በጻድቃን በሰማዕታት ስም ነው፤ ምስኪን የቤተ ክርስቲያን ጠባቂ መንፈስ ቅዱስ ግን አንድም እንኳን የለውም፥ የዓመት እንጂ የወር በዓለም የለው፣ ሰዎች ሲደነግጡ ብስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ ሲሉ በቀር ሰሙን ግን አንሥቶት አያ! ከእነዚህም በላም ካልደነገጡ በስመ አብ ብቻ ብለው ዝም የሚሉ አሉ። የልግዱና የቸልታው ነገር እስከዚህ ይብቃንና በዚህ ርእሰ ስለመንፈስ ቅዱስ ስመጽሐፍ የተነሣንበትን ዋና ጉዳይ እንይ፤

በእርዮሳውያን ምክንያት ስለ አካላዊ ቃል ኢየሱስ ክርስቶስ ወልደ እግዚአብሔርነትና ከአባቱ ጋራ በመለኮቱ ዕሩይ መሆኑን አስረድተን፥ የሥጋውንና ደሙን ሰራዩ ታጢአትነት እንዳስተማርን፥ አሁን ደግሞ አንዳንድ ሰዎች መንፈስ ቅዱስ የሥላሴ ጎይልና ሥልጣን ነው እንጂ አካላዊ አምላክ አይደለም፥ ሌሎች ደግሞ አያግልድም ስላሉ፥ ልክ እንደ ጎደኛው እንደ ወልድ ያስታርቃልም፥ ያግልዳልም የሚለውን የቅዱሳት መጻሕፍ ይዘት ስመግለጥ ነው።

ወአነ እስእሎ ለአብ ይፈኑ ለክሙ ጰራቅሊጦስሃ ካልአ ዘከማየ ዘይሄሉ ምስሌክሙ እስከ ለዓለም=ከእናንተ ጋራ የሚኖር እንደኔ ያለ ሌላ

ጰራቅሊጦስ እንዲልክላችሁ አብን እለምነዋለሁ። በእንድም ቤት ጰራቅሊጦስን መጽንዒ፥ መንጽሒ፥ ናዛዚ፥ ከሣቲ፥ መስተፍሒ፥ መስተስርዪ ግሰት ነው ብለው ይፈቱታልI ሀውቀው ጎጋውን ፈርተውም ይሁን ሳያውቁ ዋናውን ትርጉም ዘለሙታል። ፓራካሊን (መለመን፥ መግለድ) ከሚለው ግሥ የመጣ ስለሆነ ጰራቅሊጦስ አግላጅ ጠበቃ ግስት ነው። ይህም ተግባራቸውን ስለሚገልጥ የወልደ እግዚአብሔር የጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስና የእግዚአብሔር አብ የባሕርይ ሕይወት የመንፈስ ቅዱስ የጋራ ስም ነው።

ደቂቅየ ዘንተ እጽሕፍ ለክሙ ከመ ኢተአብሱ ወእመኒየ ዘአበሰ ጰራቅሊጦስ ብነ ኢየሱስ ክርስቶስ ጻድቅ ኀበ አብ=ልጆቼ! እንዳትበድሉ ይህን እጽፍላችኋለሁ፥ እውነተኛ ጠበቃ (አግላጅ) ኢየሱስ ክርስቶስ ከአብ ዘንድ አለን ብሎ ሐዋርያው ዮሐንስ ገልጧል። (1ዮሐ. 2:1) በዚህም የወልድና የመንፈስ ቅዱስ ስም መሆኑን እንረዳለን።

እግዚአብሔር ወልድ አካላዊ ቃል በመሆኑ የአብም የራሱም የመንፈስ ቅዱስም ቃል ነው፥ በተለየ አካሉ ሥጋ በመልበሱ ደግሞ ከሥሉስ ቅዱስ ያስታረቀን፥ ያማለደን፥ አሁንም በእባቱ ቀኝ ሁኖ ለእያንዳንዳችን የሚከራከርልን እሱ እንደሆነ መንፈስ ቅዱስም አካላዊ መንፈስ ስለሆነ የአብ የወልድ የራሱም እስትንፋስ ነው። መንፈስ ቅዱስ አካል እንዳለው የሚከተሉት ጥቅሶች ያስረዳሉI

1. በአብና በወልድ በመንፈስ ቅዱስም ስም እያጠመቃችሁ (ማቴ. 28-19)። እንደ ሁለቱ አካላት እንደ አብና ወልድ ፍጹም አካል ባይኖረው ኑሮ በመንፈስ ቅዱስም ስም አይልም ነበር።
2. ግን እርሱ የውነት መንፈስ በመጣ ጊዜ ወደ እውነት ሁሉ ይመራችኋልI የሚሰማውን ሁሉ ይናገራል እንጂ ከራሱ አይናገርም እና የሚመጣውንም ይነግራችኋል፥ እሱ ያከብረኛል፥ ለኔ ካለኝ ወስዶ ይናገራልና። ሌሎች እንደሚሉት ጎይልና ሥልጣን ብቻ ቢሆን ኑሮ ይንቀሳቀስ እንጂ ያሰ አካል እንዴት ይናገራል። (ዮሐ. 16:13)

ከአብ የሚወጣ ከአብ ዘንድ የምልክላቸሁ አግላጅ የውነት መንፈስ በመጣ ጊዜ እሱ ስለኔ ይመሰክራልI (ዮሐ. 15:26) አካል ከሌላው እንዴት ይመሰክራል??

የእግዚአብሔር ልጆች መሆናችንን ያ መንፈስ ራሱ ከመንፈሳችን ጋራ ይመሰክራልI (ሮሜ 8:16)

አካል፡ ከሌላው ያ ብሎ እንዴት ቀጸለለት? እንዴትስ ሊመለከር ይችላል?
እንዲሁም ደግሞ መንፈስ ድካማችንን ያግዛል፥ እንዴት እንደምንጸልይ እንደሚገባን አናውቅምና፥ ነገር ግን መንፈስ ራሱ በማይነገር መቃተት ይማልድልናል። (ሮሜ 8:26)
ሥልጣንና ኃይል ብቻ ቢሆን ኑሮ የተላከበትን ይሠራል እንጂ መናገርና መጸለይ፥ መለመን ማማለድ አይችልም ነበር።
ጌታ መንፈስ ነው፥ የጌታ መንፈስ ባለበትም ነጻነት አለ (2ቆሮ. 3:17) አካል ነው እንጂ ጎይል ጌታ አይባልም።
ወቡሩክ መንፈስ ቅዱስ ጸራቅሊጦስ መጽንዒ ወመንጽሔ ኩልነ ይህንም ሲተረጉሙ ሁላችንን የሚያነጻ የሚያጸና መንፈስ ቅዱስ ቡርክ ነው ብለው ጸራቅሊጦስን ትተውታል፥ የሚያግልድ አማላጅ የሚሰውን ቃል ለማድበስበስ። መባል ያለበት ከግዕዙ ጀምሮ፥ ወቡርክ መንፈስ ቅዱስ አማሕፃኒ መጽንዒ ወመንጽሔ ኩልነ=ሁላችንንም የሚያግልድ፥ የሚያጠና፥ የሚያነጻ ወይም በግልስ ቅጽል የሁላችንንም አማላጅ፥ አጥናኝ፥ አንጪ መንፈስ ቅዱስ ቡሩክ ነው ነበር። (መ.ቅ.ገ. 42:20) ገጽ 63 ቁ.10፤ ላይም ወቡሩክ መንፈስ ቅዱስ ጸራቅሊጦስ መጽንዒ ኩልነ=ሁላችንንም የሚያጸና መንፈስ ቅዱስ ቡሩክ ነው ብለው አሁንም አማላጅን እንደ ልማዳቸው ጥለውት ሂደዋል። ወይም በአየቀኑ ሊያነቡ ይዘሉታል።
ወእምዝ ሐመ ወሞተ በሥጋ ወተንሥአ እሙታን በግልስት ዕለት፡ ወወርገ ሰማያተ ጎበ አብ ዘፈነዎ ወነበረ በየማነ ጎይል ወፈነወ ለነ ጸራቅሊጦስሃ መንፈሰ ጽድቅ ዘወፅአ እምአብ ወአድጎነ ኩሎ ዓለመ ዘህልው ምስለ አብ ወወልድ=ከዚህ በኋላ በሥጋ ታመመ፡ ሞተ፡ በሦስተኛው ቀን ከሙታን ተለይቶ ተነሣ ወደ ላከውም አብ ወደ ሰማይ ዐርጎ በቀኝ ጎይል ተቀመጠ። ከአብና ከወልድ ጋራ የሚኖርን፡ ዓለምን ሁሉ ያዳነን፥ ከአብ የወጣ የውነት መንፈስ አማላጅን ላከልን በማለት ፈንታ የግሪኩን ቃል አውነትን ለማጨለም እንዳለ ጸራቅሊጦስን ላከልን ብለው፡ ጥሬውን ተቀብለው አስቀምጠውታል። (መ.ቅ.ገ. 103:32)
ጸራቅሊጦስ መንፈስ ቅዱሳን ላከልን በማለቱም ከላይ ከተጠቀሰው አኔ እልክላችኋለሁ ከሚለው ጋራ ይስማማል።
ወበሐምሳ ዕለት ፈነወ ሎሙ መንፈሰ ቅዱሰ ከመ ዘአሳት=በአምሳኛውም ቀን መንፈስ ቅዱስን በአምሳለ አሳት ላከላቸው። (መ.ቅ.ገ. 215፤ 252፤ 317፤ 378፤ 403፤ 429፤ 462) በጠቅላላው

ስለመንፈስ ቅዱስ (ማቴ. 28:19፤ ሉቃ. 1:35፤ 24:29፤ 12:11-12፤ ዮሐ. 14:15-17፤ 16:7-15፤ 14:25-26፤ 15:26፤ 16:13-15፤ ግብ. 2:17-20)

መንፈስ ቅዱስ በራሱ ፈቃድ በተለየ አካሉ ሰውን ይረዳል ያጽናናል፥ ለጸሎትም ያነቃቃል። አብም ወልድም ይልኩታል፤ ስለዚህ እግዚአብሔር አብንም ሆነ እግዚአብሔር ወልድን ቅዱስ መንፈስህን ላክልን እንዲህ እንዲህ እንዲያደርግልን ብሎ መለመን ይቻላል፥ ፍቅረ መንፈስ ቅዱስ ካደረብንም ራሱን ጌታችን መንፈስ ቅዱስ ሆይ! በእኔ አድረህ ይህን አድርግ ብሎ ወደ ራሱ መጸለይ ይቻላል።

ቅዳሴውም ሰወልጦ ሥጋሁ ወደሙ ርደተ መንፈስ ቅዱስን የሚጠይቀው አንድ ጊዜ አብን በሌላው ጊዜ ደግሞ ወልድን ከዚያም መንፈስ ቅዱስን ነው። (መ.ቅ.ገጽ. 119:ቁ.47፤ ገጽ. 165:ቁ.49፤ ገጽ. 199:ቁ.100-101፤ ገጽ. 267:ቁ. 113፤ ገጽ. 317:ቁ.39፤ ገጽ. 345:ቁ.21፤ ገጽ. 375:ቁ.65፤ ገጽ. 404:ቁ.72-73፤ ገጽ.425:ቁ.69፤ ገጽ.462:ቁ.39)

በእየዕለቱ ከሚደገመው መልክአ መልክም፤

ሰላም ለዕርገትከ ዘኢይትረከብ መጠኑ፥ ወለንብረትከ ሰላም ለአቡከ ውስተ የማኑ። ኢየሱስ ክርስቶስ እሰ ኪያከ ተአመኑ። ቅዱሳነ ዘእምኀቤከ ወንጹሓነ ይኩኑ። ጸራቅሊጦስሃ መንፈስከ ፈኑ። ይላል።

<u>ሰዘህ ርእስ መደምደሚያ</u>፥

መንፈስ ቅዱስ ከሦስቱ ሥላሴ አንዱ አካል አይደለም ኀይል ብቻ ነው፥ አያግልድም፥ ማሕየዊ አይደለም፥ አይላክም እያሉ ስሕተታቸውን ለሚነዙ ቅዱሳት መጻሕፍትን ለሚደልዙና ለሚዘሉ፥ ስለመንፈስ ቅዱስ ብቻ ሌላ ይህን ያህል መጽሐፍ እስከናዘጋጅ ያለፉትን ጥቅሶች ሰጥተናል። እስከዚያው ውድ አንባቢ ሆይ! መንፈስ ቅዱስ ልክ እንደወልድ ይላካል፥ ተልኳል። ያግልዳል ያጥናናል፥ ያነጻል፥ ከሁለቱ ከአብና ከወልድ ጋራ በዕሪና የኖረ ያለ የሚኖር ግሕያዊ አካል ነው ብለህ አምነህ ለመቆየትና ለመጽደቅ የተጠቀሰው ይበቃል።

ምዕራፍ 24

የክርስቶስ ተከታይ ምንድር ነው? ማነው?

የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስንና የመንፈስ ቅዱስን አስታራቂነትና አማላጅነት ታየን የሌሎችን አማላጅነት ልማመቻቸት የክርስቶስ ተከታይ ምን መሆኑን ከግብሩ በፊት እንገልጣለን።

ክርስቶስን የተቀበለ ሁሉ የቅዱስ እግዚአብሔር አብ ልጅ ነው። ልጁም በመሆኑ ከክርስቶስ ጋራ የመንግሥቱ ተወራራሽ ነው። በልጅነት የሚሰያዩትም የክርስቶስ የባሕርይ፥ የተከታዩ የጸጋ በመሆኑ ነው። ልጁን ልኮ ልጆቹ ያደርገን የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ አባት ይመስገን፥ እንደዚሁም ከአባቱ ሳይለይ በትሕትና ሥጋ ለብሶ፥ በትዕግሥት ጸዋትወ መከራን ተቀብሎ በጥንተ ተፈጥሮ የተሰጠንን ልጅነታችንን የመለሰልን ኢየሱስ ክርስቶስ ይባረክ፥ አሜን።

ኢየሱስ ክርስቶስ ነው ብሎ የሚያምን ሁሉ ከእግዚአብሔር ተወልዷል። (1ዮሐ. 5:1)

ወደ ወገናቹ መጣ ወገናቹ ግን አልተቀበሉትም፥ በስሙ ለሚያምኑትና ለተቀበሉት ሁሉ ግን የእግዚአብሔር ልጆች እንዲሆኑ ሥልጣንን ሰጣቸው፤ እነሱም ከእግዚአብሔር ተወለዱ እንጂ ከደም ወይም ከሥጋ ፈቃድ ወይም ከወንድ ፈቃድ አልተወለዱም። (ዮሐ. 1:10-13)

የእግዚአብሔር ልጆች መሆናችንን ያ መንፈስ ራሱ ከመንፈሳችን ጋራ ይመስክራል፤ ልጆች ከሆን ወራሾች ደግሞ ነን፥ ማለት የእግዚአብሔር ወራሾች የክርስቶስ ተወራራሾች። (ሮሜ 8:16-17)

በእምነት ሁላችሁም በክርስቶስ ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጆች ናችሁና፥ ከክርስቶስ ጋራ አንድ ትሆኑ ዘንድ የተጠመቃችሁ ሁሉ ክርስቶስን ለብሳችኋልና፥ በእሱም አይሁዳዊ ወይም ግሪክ፥ ባሪያ ወይም ጭዋ፥ ወንድ ሴት የለም፥ ሁላቸሁም በክርስቶስ ኢየሱስ አንድ ናችሁና፤ (ገላ. 3:26-28)

ከዚህ በላይ በተጠቀሱት በጸጋ የእግዚአብሔር ልጆች መሆናችንን ከተረዳን ክርስቶስ በሰጠን ቃል ኪዳን መሠረት እኛም ተከታዮቹ እንደሱ ግግለድ መቻላችንን በሚከተለው እናያለን።

ምዕራፍ 25

የትዳሳን አማላጅነት

እኛ ደግሞ በሃይማኖት አሱን ካመንን፥ በማብር አሱን ከመሰልን እንደ መምህራችን እንደሱ ወደሱ፥ በእሱ እናማልዳለን። ወደዚህ ዓለም የመጣው እኛን ከአባቱ አማልዶ ለማስታረቅ ነው፤ ስለሆነም ጻድቃን፥ ሰማዕታት ቅዱሳንም ከሱ ጋራ በእሱ ያስታርቃሉ፥ ያማልዳሉ። ድውይ ይፈውሳሉ፥ ዕውር ያበራሉ፥ ለምጻም ያነጻሉ፥ ሽባ ያረታሉ፥ ሙት ያነሣሉ፥ አጋንንትን ያወጣሉ፤ ስለምን? ቢሉ ጌታ ራሱ ቃል ኪዳን ሰጥቷቸዋላ! ብሎ ይመልሷል።

የሚከተሉት ጥቅሶች ጻድቃንና ሰማዕታት በሕይወተ ሥጋም ሆነ በወጸደ ነፍስ (ከሞት በኋላ) ማማለዳቸውን ያስረዳሉ፤

በዚያን ጊዜ ጴጥሮስ መልሶ--እነሆ፥ እኛ ሁሉን ትተን ተከተልነህ፥ እንኪያስ ምን እናገኝ ይሆን? አለው። ኢየሱስም እንዲህ አላቸው፤ እውነት እውነት እላችኋለሁ፥ የተከተላችሁኝ እናንተስ በዳግመኛ ልደት የሰው ልጅ በክብሩ ዙፋን በሚቀመጥበት ጊዜ እናንተ ደግሞ በወሥራ ሁለቱ የእስራኤል ነገድ ለመፍረድ በወሥራ ሁለት ዙፋን ትቀመጣላችሁ።

ምክንያቱስ ቢሉ ጌታ አምላክ ሕያዋን እንጂ አምላክ ሙታን አይደለማ! ቅዱሳን በወጸደ ሥጋም ሆነ በወጸደ ነፍስ ለእሱ አንድ ናቸው። በላይንስ መዣሪያ ከእኛው ሌላ፥ ሌላ ዓለም እንዳለ እየተረጋገጠ በሄደበት ዘመን ይህን ማመን አደጋች አይደለም። (ማቴ. 19:27-28፤ 22:31-32)

ከመንፈስ ቅዱስ በቀር የአማላጅ ሁሉ አለቃ ከእግዚአብሔርና ሰው መካከል የቆመ፥ የሆነ፥ የሚናር ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። እንዲህ ሆኖ፥ ስለሆነ፥ የሚከተለውን ቃል ኪዳን ለተከታዮቹ ሰቅዱሳን ሰጥቷል። ማእከለ እግዚአብሔር መሰብእ መሆኑን ከዚህ በፊት ስላየነው አሁን ወደ ዛሬው ርእሳችን እንመለስ፤ (ዮሐ. 14:6)

እውነት እውነት እላችኋለሁ በኔ የሚያምን እኔ የምሠራውን ሥራ ይሠራል፥ ከዚህም የሚበልጥ ይሠራል፥ (ዮሐ. 14:12) ሥጋን የለበሰ ሰው የሆነ መለኮት ሥራው ምንድር ነው? ቢሉ ማስተማር፥ ማስታረቅ፥ ማማለድ፥ ድውይ መፈወስ፥ ሙት ማንሣት ወዘተ ነዋ! ብሎ ይመልሷል።

ይህንንም ሐዋርያትን ሲልክ በትእዛዝ አረጋግጧል፤

> ሂዳችሁም መንግሥተ ሰማያት ቀርባለች ብላችሁ ስበኩ፤ ድውያንን ፈውሱ፥ ሙታንን አስነሡ፥ ለምጻሞችን እንጹ፥ አጋንንትን አውጡ። (ማቴ. 10:7-9፤ ማር. 6:7፤ ሉቃ. 10:19-20)

እንደሱም ቅዱሳን ካህናት ኃጢአት እንዲያስተሰርዩ ቃል ኪዳን፤ ኃጢአቱን የተዋችሁለት ይተውለታል የያዛችሁበት ግን ይያዝበታል፥ በምድር የፈታችሁት በሰማይ የተፈታ ይሆናል ያሰራችሁትም ይታሰራል፥ ብሎ ሥልጣን ሰጥቷል፥ ቃል ኪዳን ገብቷል፤ (ማቴ. 18:18፤ 16:19፤ ዮሐ. 20:23)

ተስፋውስ በጣም ጥሩ፥ ግን ይህ ተስፋ በተግባር ታይቷል ወይ ተፈጽሟል ይፈጸማል ወይ? ለሚል ጠያቂ እንዲታ ያውም በዕጥፍ ከታሰበውም በላይ ብለን መልስን ለመረጃ የሚከተሉትን እንጠቅሳለን፤ ሐናንያ የተባለ አንድ ሰው፥ ሰጲራ ከተባለች ምሽቱ ጋራ መሬት ሸጠ፥ ምሽቱም ስታውቅ ከሽያጩ አስቀረና አኩሌታውን አምጥቶ በሐዋርያት እግር አጠገብ አኖረው። ጴጥሮስም ሐናንያ ሆይ! መንፈስ ቅዱስን ታታልልና ከመሬቱ ሽያጭ ታስቀር ዘንድ ሰይጣን በልብህ ስለምን ሞላ? ከሸጥኸውስ በኋላ በሥልጣንህ አልነበረምን? ይህን ነገር ስለምን በልብህ አሰብህ? እግዚአብሔርን እንጂ ሰውን አልዋሸህም አለው፤ ሐናንያም ይህን ቃል ሰምቶ ወድቆ ሞተ። በሰሙትም ሁሉ ላይ ታላቅ ፍርሃት ሆነ። ጎበዛዝቱም ተነሥተው ቀበሩት፥ አውጥተውም ቀበሩት። ከሦስት ሰዓት ያህል በኋላም ምሽቱ የሆነውን ሳታውቅ ገባች። ጴጥሮስም መልሶ አስቲ ንገሪኝ መሬታችሁን በዚህን ያህል ሸጣችሁትን? አላት። እስዋም አዎ! ይህን ለሚያህል ነው አለች። ጴጥሮስም የጌታን መንፈስ ትፈታተኑ ዘንድ ስለምን ተስማማችሁ? እነሆ! ባልሽን የቀበሩት ሰዎች እግር በደጅ ነው፥ አንችንም ያወጡሻል አላት። ጎበዛዝቱም ሲገቡ ሙታ አገኟትና አውጥተው ከባሏ ጋራ ቀበሯት። በቤተ ክርስቲያን ሁሉና ይህንም በሰሙ ሁሉ ላይ ታላቅኝ ፍርሃት ሆነ። በሐዋርያትም እጅ ብዙ ተአምራትና ድንቅ በሕዝብ መካከል ይደረግ ነበር። ሁሉም በአንድ ልብ ሁነው በሰሎሞን ደጅ መመላለሻ ነበሩ። ከሌሎችም አንድም እንኳ ሊተባበሯቸው የሚደፍር አልነበረም፥ ሕዝቡ ግን ያከብሯቸው ነበር። የሚያምኑትም ከፊት ይልቅ ለጌታ ይጨመሩለት ነበር። ወንዶችና ሴቶችም ብዙ ነበሩ። ስለዚህም ጴጥሮስ ሲያልፍ ጥላውን እንኳ እንዲጥልበት በሚሄድበት መንገድ ድውያንን አውጥተው በአልጋና በመስካ ያኖሯቸው ነበር። በኢየሩሳሌም ከተማም ዙሪያ ካለችው ከተማ ድውያንንና በርኩሳን መናፍስት የሚሠቃዩትን እያወጡ ብዙዎች ይሰበሰቡ ነበር። ሁሉም ይፈወሱ ነበር። (ግብ. 5:1-16)

ጴጥሮስም በእየስፍራው ሁሉ ሲዞር በልዳ ወደ ሚኖሩ ቅዱሳን ደረሰ። በዚያም ከስምንት ዓመት ጀምሮ በአልጋ ላይ ተኝቶ የነበረውን ኤንያ

የሚሉትን አንድ ሰው አገኘ። እሱም ሽባ ነበረ። ጴጥሮስም ኤንያ ሆይ! ኢየሱስ ክርስቶስ ይፈውስሃል፥ ተነሣና ለራስህም አንጥፍ አለው። ወዲያውም ተነሣ። (ግብ. 9:32-34)

በኢዮጴም ጣቢታ የሚሏት አንዲት ደቀ መዝሙር ነበረች። እሷም መልካም ነገር የሞላባት ምጽዋትም የምታደርግ ነበረች። ታማ ሞተች፥ አጥበውም በሰገነት አኖሯት። ወደ ጴጥሮስም ልከው ጠሩትና መጥቶ ጸልዮ ጣቢታ ሆይ! ተነሽ አላት እሷም ዐይኗን ከፍታ ጴጥሮስን አይታ ተቀመጠች። (ግብ. 9:36-43)

እግዚአብሔርም በጳውሎስ እጅ የሚያስገርም ተአምር ያደርግ ነበር። ስለዚህም ከጨርቁ ቁራጭ ወስደው ከድውዩ ላይ ሲጥሉት ደዌው ይለቀው፥ አጋንንትም ይወጡ ነበር። (ግብ. 19:11-20፤ 20:7-12፤ 28:7-12)


<u>በዐጸደ ሥጋም በዐጸደ ነፍስም</u>

በዐጸደ ሥጋ ሳሉስ አዎ! የክርስቶስ ተከታዮች ብዙ ያስተምራሉ፥ ተአምራትም ያሳያሉ። ክርስቶስ ለሦስት ዓመት ከኢየሩሳሌም እስከ ገሊላ አንዲት ከፍለ ሀገር የግታክል ጠቅላይ ግዛት አስተምሮ ነው የሄደው፥ እነሱ ግን ዓለምን ዙሪው አስተምረዋል፤ በተአምራትም በኩል ጴጥሮስና ጳውሎስ ብቻ እንኳ በጨርቃቸውና ጥላቸው ይበልጥ አሳይተዋል፥ ከሞቱ በኋላስ? ለሚል ጠያቂ ደግሞ፥

አንደኛ ሞት በጻድቃን ዘንድ ከአንድ ጎላፊ፥ ጠፊ ሕይወት ወደ ማይጠፉና ማያልፍ ሕይወት መሸጋገሪያ እንጂ መጥፊያ ስላልሆነ እግዚአብሔርም አምላክ ሕያዋን ስለሆነ፥ ሁለተኛም እግዚአብሔር አንድ ጊዜ ከሰጠ ተጠጥቶ የሰጠውን መልሶ ስለማይቀማ፤ እግዚአብሔር ማሰ አይጠጠትምም እግዚአብሔር ከማለ አይጠጠትም። እግዚአብሔር በጸጋው ስጦታና በመጥራቱ አይጠጠትምና። አንድ ጊዜ ሙት አንሡ ድውይ ፈውሱ ብሎ ቃል ከሰጠ በኋላ ከሞትህስ ሥልጣኔን አምጣ አይልምና፥ (መዝ. 109:4፤ ሮሜ 11:29)

ጻድቃን በዐጸደ ሥጋም በዐጸደ ነፍስም፥ በዚህም በወዲያኛው ዓለምም ያግልጻሉ። ሦስተኛም እንኳንስ ግግለድና በቀልም ያዘከራሉ፥ ያስታውሳሉና፤ ለዚህም፤ አምስተኛውን ግጎተም በፈታ ጊዜ ስለ እግዚአብሔር ቃልና ስለጠበቁት ምስክር የታረዱትን ሰዎች ነፍሳት ከመሠውያው በታች አየሁ፥ በታላቅ ድምፅም እየጮኽ፥ ቅዱስና እውነተኛ ጌታ ሆይ! እስከ መቼ ድረስ አትፈርድም? ደማችንስ በምድር በሚኖሩት ላይ እስከ መቼ አትበቀልም? (መዝ. 131:11፤ ሮሜ 11:29፤ ራእ. 6:9-10)

ለሁሉም የክርስትና ሕይወት አንዱ ለሌላው ግግለድ እንደሆነ በጌታችን ጸሎት ይታወቃል፤ ከዚህ በላይ ብዙ ለግንበብ ለሚፈልግ የሚከተሉትን ጥቅሶች እያወጣ እንዲመለከት እንጠቁግለን፤ (ያዕ. 5:14-16፤ ኤፌ. 1:15-17፤ ቆላ. 1:9-12፤ ፊል. 1:9፤ 1ጢሞ. 2:1-5፤ 4:1-5፤ 2ቆሮ. 5:20፤ ኤፌ. 6:20፤ 1ዮሐ. 5:15-16፤ 2ጢሞ. 3:1-9 ቲቶ. 1:16፤ ዘኁ. 16:47-48፤ 14:13-20፤ መዝ. 105:23፤ ኤር. 27:18)



የመላእክት አግላጅነት

ምዕራፍ 26

የመላእክት አግላጅነት

ግግለድን ለግጠቃለል ስለ መላእክት ህልዎትና ሬድኤትም ከዚ
ቀጥለን እንናገራለን። መላእክት ከእግዚአብሔር በተሰጣቸው ታ
ኪዳን፥ ሥልጣን፥ በእየጊዜውም በሚሰጣቸው ትእዛዝ ተልከው
ሳይላኩም፥ አስበውም ያግልዳሉ፥ ያስታርቃሉ፥ ይቀሥፋሉ፥ ያድናሉ
ይጠብቃሉ። ተፈጥሮአቸውም ከእሳትና ከንፋስ ነው። በዕሩቅ ብእሲ
ዐይን አይታዩም ነበር፥ በዘመናችን ግን የመስኩብና የአሜሪካ ጠበብት
በሕዋው ሲበሩ ዐየናቸው ብለው በፎቶ ግራፍ አንሥተው በመጽሔት
ለዓለም በትነዋል።

መላእክትን እናከብራለን፤ ሰጊድ በሚለው ክፍል አስከናየው ድረስ
እኛም ለመላእክት እጅ እንነሣለን። ይህ ሰጊድ፥ እጅ መንሣት እንጂ
የአምልኮት ሰጊድ አይደለም። ራእየ ዮሐንስ 19:10፤ 22:8-10
የተጻፈውን፤ ይህንም ያየሁትና የሰማሁት እኔ ዮሐንስ ነኝ፤
በሰማሁትና ባየሁት ጊዜ ይህን ባሳየኝ በመልአኩ እግር ፊት አሰግድ
ዘንድ ተደፋሁ። እሱም እንዳታደርገው ተጠንቀቅ፥ ከአንተ ጋራ
ከወንድሞችህም ከነቢያት ጋራ የዚህንም መጽሐፍ ቃል ከሚጠብቁ
ጋራ አብሬ ባሪያ ነኝ፥ ለእግዚአብሔር ስገድ አለኝ የሚለውን ይዘው
ለመላእክት አይሰገድም የሚሉ አሉ፤ ይህ የሆነው ግን ዮሐንስ
ከምዕራፍ 1:12-17፤ እስከ ምዕራፍ 5 ሲያየው የነበረ ጌታችንን
ኢየሱስን ስለነበረ አውንም በብርሃኑ እሱ መሰሎት በአምላክነት
ሊሰግድለት ቢሞክር የአምልኮት ሰጊድ እይገባኝም ሲል ፍጡርነቱን
ገለጠለት እንጂ በመልአክነቱ እጅ መንሣት የለብኝም ግለቱ አይደለም
። እጅ መንሣትስ ለመላእክት እንደሚገባ የሚከተሉት ጥቅሶች
ያስረዳሉ፤

እንዲሁም ሆነ፥ ኢያሱ ብኢያርኮ አጠገብ ሳለ ዐይኑን አንሥቶ
ተመለከተ፥ እነሆም የተመዘዘ ሰይፍ በእጁ የያዘ ሰው በፊቱ ቆሞ
ነበር፥ ኢያሱም ወደ እሱ ቀርቦ፥ ከኛ ወይስ ከጠላቶቻችን ወገን ነህ
አለው። እሱም አይደለሁም፥ እኔ የእግዚአብሔር የሠራዊቱ አለቃ
በመሆኔ አሁን መጥቻለሁ አለ። ኢያሱም ወደ ምድር በግምባሩ ተደፍቶ
ሰገደና፥ ጌታዬ ለባሪያው የሚናገረው ምንድር ነው? አለው።
የእግዚአብሔርም ሠራዊት አለቃ--አንተ የቆምህበት ስፍራ የተቀደሰ
ነውና ጫማህን ከእግርህ አውልቅ አለው። ኢያሱም እንዲሁ አደረገ።
ጫማህን አውልቅ ሲለው አትሰገድልኝ ግን አላለውም፤ ምክንያቱም
መልአኩ የእግዚአብሔር ሠራዊት አለቃ መሆኑን ስለነገረው
በመተዋወቃቸው እጅ ነሣ እንጂ አምላክ ነህ ብሎ አልሰገደምና

አምልኮት ሰጊድም አላቀረበምና ነው። (ኢያ. 5:13-15) ዳዊትም ይኖቹን አነሣ፥ የእግዚአብሔር መልአክ በምድርና በሰማይ መካከል ም፥ የተመዘዘም ሰይፍ በእጁ ይዞ፥ ያም ወደ ኢየሩሳሌም ተዘርግቶ ። ዳዊትና ሽማግሌዎችም ማቅ ለብሰው በግምባራቸው ተደፉ። (1 ን.መዋ. 21:16) ከዚህ ቀጥለው ያሉት ጥቅሶችም ተመሳሳይ ናቸው፤ . 23:20-24፤ መዝ. 33:7፤ ዘፍ. 48:16፤ 19:1-11፤ 2ነገ. 6:15-19፤ . 6:22፤ 10:9-11፤ 9:20-22፤ ሉቃ. 1:18-20፤ ግብ. 5:17-21፤ :6-11)

መላእክት ያድናሉ፥ ይጠብቃሉ፥ ይቀሥፋሉ

መንገድ ይጠብቅህ ዘንድ ወደ አዘጋጀሁትም ስፍራ ያገባህ ዘንድ ዘሥ፥ እኔ መልአክ በፊትህ እሰዳለሁ። በፊቱ ተጠንቀቁ፥ ቃሉንም ድምጡ፥ ስሜም በእሱ ስለሆነ ኃጢአት ብትሠሩ ይቅር አይላቸሁምና ታስመርሩት። አንተ ግን ቃሉን ብትሰማ፥ ያልሁህንም ሁሉ ታደርግ፥ ጠላቶችህን እጣላቸዋለሁ፥ የሚያስጨንቁህንም ስጨንቃቸዋለሁ፥ መልአኬ በፊትህ ይሄዳልና (ዘፀ. 23:20-23) እግዚአብሔር መልአክ በሚፈሩት ሰዎች ዙሪያ ይሰፍራል፥ ድናቸውማል። የእግዚአብሔር መልአክ የሚፈሩትን ሰዎች አደባባይ ክታተማል፥ ተከታትሞስ በዙሪያችው ስፍሮስ ምን ያደርግላቸዋል? ለኝ እንደሆነ ያድናቸዋል እልሃለሁ ይላል፤ (መዝ. 33:7) ሚካኤል፥ ብርኤል፤ ኡራኤል፤ ሚካኤል ጎኛም፥ ግሻ ዐባይ፥ ገብርኤል፥ ቁልቢ ሬር፥ ኡራኤል አዲስ አበባ፥ ጎልቁ ወመሳፍርት የሌለው ተአምራት ሚያሳዩበት ዘመንና ሊቃነ መላእክት ተሰልፈው እንደ ሙሽራ ፎቶ ሚነሡበት ዘመን የመላእክትን ህልውናና ተራደኢነት መካድ ቂልነት ንጂ ዕውቀት አይባልም።

ትንሽነቴ ጀምሮ እስከ ዛሬ የመገበኝ እግዚአብሔር፥ ከክፉ ነገር ሁሉ ዳነኝ መልአክ እነዚህን ልጆች ይባርክ፥ (ዘፍ. 48:16፤ 19:1-11፤ ብ. 12:23)

ና ጎሊና ላለው አንባቢ የመላእክትን ህልውና፥ ረድኤት፥ አማላጅነት ልእኮ፥ አገልግሉት ለመረዳትና ለዚህ ትምህርት መግቢያ የተሰጠው ብቃንና በመጀመሪያ መላእክት ወደሚረዷቸው ወደ ቅዱሳን እንለፍ።

ምዕራፍ 27

ቅዱሳን እነማናቸው?

ቀደሰ፡ ለየ፡ አነጻ፡ ባረከ ማለት ነው። ቅዱስም የዚህ ሳደስ ቅጽል ስለሆነ የተለየ፡ የነጻ፡ የተባረከ ማለት ነው።
ኢየሱስ ክርስቶስ ነው ብሎ ያመነ ሁሉ ከእግዚአብሔር ተወልዷል ብለናል። እግዚአብሔር ቅዱስ ነው፡ በጸጋ በኢየሱስ ክርስቶስ የሚወለደው የኢየሱስ ክርስቶስ ተከታይም ቅዱስ ነው። ቅዱስ እግዚአብሔር ርኩስ አይወልድም። የምንበላለጠውም በግብር እንጂ በመንፈስ ቅዱስ በጥምቀት ከእግዚአብሔር የተወለድነ ሁሉ አንድ ነን። ርግጥ ነው ልጅ ሁሉ ያባቱን ፈቃድ ካልፈጸመ ካስቀየመው ርስቱን አይወርስም፡ ርኩስ የርኩስ ልጅ ግን አይባልም አባቱን መስደብ ነውና። እኔ ቅዱስ እንደሆንሁ እናንተም ቅዱስ ሁኑ (ሌዋ. 11:45) አግዚአብሔር አምላካችሁ ቅዱስ ነኝና እናንተም ቅዱስ ሁኑ (ሌዋ. 19:2)
በእውነት ቀድሳቸው፡ ቃልህ እውነት ነው (ዮሐ. 15:3:17)። ወአውሥአ እናንያ ወይቤ እግዚኦ ሰማዕኩ በእንተ ውእቱ ብእሲ በጎበ ብዙኃን ኮሎ ዘይገብር እኩየ ዲበ ቅዱሳኒከ በኢየሩሳሌም ሐናንያም መልሶ ጌታ ሆይ! በኢየሩሳሌም=በቅዱሳንህ ላይ ስንት ክፉ እንዳደረገ ስለዚህ ሰው ሰምቻለሁ።
ቅዱሳን ያላቸው የኢየሱስን ደቀ መዛሙርት ነው። (ግብ. 9:13) ጴጥሮስም በእየስፍራው ሁሉ ሲዞር በልዳ ወደሚኖሩት ቅዱሳንም ደግሞ ደረሰ። (32) ይህንም በጠቅላላ ለማረጋገጥ የሚከተሉትን ጥቅሶች ያነቧል፤ (ግብ. 9:13፤ 32፤ 41፤ 26:10፤ ሮሜ 1:7፤ 8:27፤ 12:13፤ 15:25፤ 26፤ 31፤ 16:2፤ 15፤ 1ቆሮ. 1:2፤ 6:3፤ 13፤ 14:33፤ 16:1፤ 15፤ 2ቆሮ. 1:1፤ 7:1፤ 8:4፤ 9:1፤ 12-13፤ ኤፌ. 1:1፤ 15፤ 18፤ 2:19፤ 3:8፤ 18፤ 4:12፤ 5:18፤ 6:18፤ ፊል.1:1፤ 1ጴጥ. 1:16)
በዚህ ምንነታቸውን ተመልክቶ አማላጅነታቸውን ደግሞ በአማላጅ ምዕራፍ ያጠናል። ቅዱሳት ለቅዱሳት የሚለው ለትምህርት እንጂ ለሥጋሁ ወደሙ እንዳልሆነ በቦታው ተገልጧል። ለዚህም ቢሆን ኑሮ ቅዱሳን ምእመናን ስለሆኑ ያለምንም ችግር ሥጋውን ደሙን ኃጢአት ለማስተስረይ፡ በክብር ላይ ክብር ለመጨመር የመቀበል መብትና ግዴታ አላቸው።
በጠቅላላ ስለ ቅዱሳን እስከዚህ ይብቃንና ስለ ቅዱሳን አክሊልና ሞገስ፡ ዘውድ ቅድስት ድንግል ማርያም ደግሞ ጥቂት እንይ።



ወሳዲተ አምላክ ፡ ቅድስት ድንግል ማርያም ፡ እጎቶሙ ለመላእክት ፡ እሞሙ ለሰማዕት ፤ ማርያም እምነ ወእሙ ለእግዚእነ።

ምዕራፍ 28

ቅድስት ድንግል ማሪያም

የድንግል ማርያም መገለጫ የኛ የጸጋ እናታችን፡ እመቤታችን፡ የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ወልደ እግዚአብሔር ሕያው የሥጋ እናቱ፡ ወላዲተ አምላክ በቅጽል፡ ወላዲተ አምላክ፡ ቅድስት፡ ድንግል ማርያም መትሕተ ፈጣሪ፡ መልዕልተ ፍጡራን፡ እጎተ መላእክት፡ እመ ሰማዕታት ናት። በዚህም መጻሕፍት ሁሉ ይስማማሉ።

እግዚአብሔር አብ መርጧታል፡ ወዷታል፡ አጽንቷታል፡ እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ቀድሷታል፡ ከርስሐት ሁሉ አንጽቷታል፡ እግዚአብሔር ወልድ ደግሞ በተለየ አካሉ ከሥጋዋ ሥጋ ከነፍስዋ ነፍስ ነሥቶ፡ ሰው ሁኖ ተወልዶባታል፡ ስለዚህ ሁሉም ያመሰግኗታል።

የዚህን መጽሐፍ ደራሲ አተረጓጎም ከማየት በፊት አንባቢ ሁሉ ሉቃ 1:26-55ን መላልሶ አንቦ እንዲረዳ ይጠቁማል።

በስድስተኛው ወር መልአኩ ገብርኤል ከእግዚአብሔር ዘንድ ናዝሬት ወደምትባል ወደ ገሊላ ከተማ፡ ከዳዊት ወገን ለሆነው ዮሴፍ ለሚባል ሰው ወደታጨች ወደ አንዲት ድንግል ተላከ፡ የድንግሊቱም ስም ማርያም ነበረ። መልአኩም ወደእሷ ገብቶ፡ ጸጋ የሞላብሽ ሆይ! ደስ ይበልሽ፡ ጌታ ካንቺ ጋራ ነው፡ ከሴቶች ሁሉ መካከል የተባረክሽ ነሽ አላት።

በዚህም እግዚአብሔር አብ ልኮ፡ አዝዞ፡ ቅዱስ ገብርኤል ሊሳ መላእክት ተልኮ፡ ተአዝዞ አመስግነዋል። እግዚአብሔር አብ ሥላሴን፡ ቅዱስ ገብርኤል መላእክትን ይወክላሉ።

ወዲያውም በምስጋናውና በሰላምታው ተደናግራ፡ ተደናግጣ፡ ይህ እንዴት ያለ ሰላምታ ነው? ብላ አሰበች። እሱም የሚከተለውን መልእ ያረጋጋታል፡ ያረጋግጥላታል፡ ማርያም ሆይ! በእግዚአብሔር ፊት እጅ አግኝተሻልና አትፍሪ። እነሆም፡ ትፀንሻለሽ ወንድ ልጅም ትወልጃለሽ፡ ስሙንም ኢየሱስ ትይዋለሽ፡ እሱም ታላቅ ይሆናል፡ የልዑል ልጅም ይባላል፡ ጌታ አምላክም የአባቱን የዳዊትን ዙፋን ይሰጠዋል፡ በያዕቆብ ቤትም ላይ ለዘለዓለም ይነግሣል፡ ለመንግሥቱም መጨረሻ የለውም ብሎ፡ ማረያምም መልአኩን ወንድ ስለማላውቅ ይህ እንዴት ይሆናል? አለችው። መልአኩም መልሶ እንዲህ አላት፡ መንፈስ ቅዱስ በአንቺ ላይ ይመጣል፡ የልዑል ኀይልም ይጸልልሻል፡ ስለዚህ ደግሞ ከአንቺ የሚወለደው ቅዱስ የእግዚአብሔር ልጅ ይባላል። በዚህም የሁሉም ኀይል መንፈስ ቅዱስ እንደ ሚጸልላት በተለየ አካሉ መንፈስ ቅዱስ ደግሞ በላይዋ ላይ መጥቶ ከርስሐት ሁሉ

እንደሚያነጻት፡ ከእሷ የሚወለደው ደግሞ ቅዱስ የእግዚአብሔር ልጅ መባሉን አብሥሮ፡ የእግዚአብሔር ጸጋ እንዳላት፡ ሥሉስ ቅዱስ በኀብረት እንዳመሰገኗት ነግሮ ተመልሷል።

ቀጥሎም ቁጥር 42 ላይ በኤልሳቤጥም መንፈስ ቅዱስ መላባት በታላቅ ድምፅም እንዲህ ብላ ጮኸች፡ አንቺ ከሴቶች መካከል የተባረክሽ ነሽ፡ የማሕፀንሽም ፍሬ የተባረከ ነው።

በዚህም መንፈስ ቅዱስ ርግጠኛው፡ ዋነኛው አመስጋኝ፡ ኤልሳቤጥ ግኑያ፡ ግራማፍን መሆናቸው ነው። በዚህም መንፈስ ቅዱስና ኤልሳቤጥ (ሰው) ተባብረው ማመስገናቸውን ወንጌሉ ያስረዳል። ይኸው መንፈስ ቅዱስ ካደረባት በኋላ ራስዋ ማርያም ደግሞ እነሆ! ትውልድ ሁሉ ያመሰግኑኛል (ብፅዕት ይሉኛል) ብላለች። ለማረያም ምስጋና በሽ! በሽ! ነው፤ ሥላሴ፡ መላእክት፡ ሰው እንደሚያመሰግኗት በዚህ እንረዳለን። ይህን የተረዳ ቅንዓት ካልያዘው በቀር ለማረያም ምስጋና አይገባትም አይልም።

ለማርያም የታዘዘው ምስጋና ከአምስት አንድ ነው። በእኛ ቤተ ክርስቲያን ግን በጣም በዛና ወንጌል እንዳትሰበክ ከለከለ።

በሰዓታቱ፡ በማሕሌቱ፡ በኪዳኑ በቅዳሴው ሁሉ እሷ ናት፡ ወንጌል እናንብ የተባለ እንደሆነ ታምሯ ሳለች ይባልና የወንጌሉ ነገር ይረሳል። ስለዚህ የኛ ቄሶች ከተአምረ ማርያም ውጭ በማሕሌት፡ በኪዳን፡ በሰዓታት ተወጥረው ሰለተያዙ ይህን የጠቀስነውን ከያዙ ስለሃይማኖት ባያወቁ አይፈረድባቸውም። መልሳቸውንም ከቅዱሳተ መጻሐፍት ጋራ የማይስማማው ገድላገድልና ተአምረ ማርያም ነው። የእኛ የማርያም ወዳጆች፡ ማረያም በሥላሴ ላይ መፈንቅለ መንግሥት ያደረገች አስመስለው፡ ሥላሴን አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስን ትተው፡ ቅዱሳት መጻሕፍት እንዳይሰበኩ ማድረጋቸው ነው እንጂ አንድ አምስተኛ ምስጋናስ ይገባታል፤ እንዴታ! እንዴት ሁኖ ነው አንድ አምስተኛ መሆኑ? ለሚል ለአብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ፡ በዕፀ መስቀል ስም ጌታ በዚህ ዓለም ሁኖ ለተቀበለው ጸዋትወ መከራና ለእሷ።

<u>ሰጊድም</u>፡ በቦታው እንደምናየው፡ የጸጋ ሰጊድም አንድ አምስተኛ አላት። ምስጋና እንደሚገባትና እንደምትመሰገን በትንቢትም ተነግሯል፤ ወትቀውም መንግሥት በየማንከ፡ በአልበሰ ወርቅ ዑጽፍት ወሑብርት=በወርቅ ልብስ ተሸፍናና ተጎናጽፋ ንግሥት በቀኝህ ትቆማለች። ወይዘክሩ ስመኪ በኩሉ ትውልደ=ትውልድ ትውልድ ሁሉ ስምሽን ያስታወሳሉ፤ ስለዚህ አሕዛብ ሁሉ ይገዙልሻል፡ ያገለገሉሻል። (መዝ. 44:9፤ 16-17) ብሏልና።

ድንግል ናት

ቅድመ ፀኒስ፥ ድኅረ ፀኒስ፥ ቅድመ ወሊድ፥ ድኅረ ወሊድ ሁልጊዜም ድንግል ናት። ክርስቶስ ከዚህ በፊት እንዳየነው ከመጣበት አንዱ ዐላማ ትንቢትን ሁሉ መፈጸም ነው፤

ለዚህም የሚከተሉትን ጥቅሶች እነሆ፥

ስለዚህ ጌታ ራሱ ምልክት ይሰጣችኋል፤ እነሆ፥ ድንገል ትፀንሳለች፥ ወንድ ልጅም ትወልዳለች ስሙንም ዐማኑኤል ብላ ትጠራዋለች (ኢሳ. 7:14)

አዎ! በድንግልናስ እንደትንቢቱ ወልዳለች፥ ግን ከወለደች በኋላ ተፈትሖ ማሕፀን ይኖርባት ይሆናል ለሚል ተጠራጣሪ ደግሞ የሚከተለው ጥቅስ ይሰጠዋል፤

ወደ ምሥራቅም ወደሚመለከተው በስተውጭ ወደ አለው ወደ መቅደሱ በር አወጣኝ፥ ተዘግቶም ነበር። እግዚአብሔርም ይህ በር ተዘግቶ ይኖራል እንጂ ሰውም አይገባበትም፥ የአስራኤል አምላክ እግዚአብሔር ገብቶበታልና ተዘግቶ ይኖራል (ሕዝ. 44:1)

በዚህ ትንቢት እንደተነገረው እሷም በድንግልና ስለወለደችና የእግዚአብሔር መልአክም ስላናገራት በመገረም በድንግልና ቀርታለች። በድንግልና ትወልጃለሽ ያለ መልአክ ተመልሶ እገሌን አግቢ አላላትምና። በትንቢቱ በር የተባለችም ድንግል ማርያም እንደሆነች ለማንም ተራ አንባቢ ግልጽ ነው።

እጎቴ ሙሽሪት የተቆለፈ ገነት (ተጋን) የተዘጋ ምንጭ፥ (የታተመ ነቅዕ፥ መሐ. 4:12)

ይህም መግቢያ የሌለው ተጋን (የአትክልት ቦታ ገነት) አፍ የሌለው ምንጭ በማለቱ ዘለዓለማዊ ድንግልናዋን ያሳያል። በሐዲስ ይህ ትንቢት እንዴት እንደ ተፈጸመ የሚከተሉትን ያነቧል፤ (ማቴ. 1:18፤ ሉቃ. 1:26-46)

ይህንም ሲናገር ከሕዝቡ አንዲት ሴት ድምፅዋን ከፍ አድርጋ፥ የተሸከመችህ ማሕፀንና የጠባሃቸው ጡቶችዋ ብፅዓን ናቸው አለችው፤ (ሉቃ. 11:27)

በዚህም እሷ ራስዋ ትውልድ ሁሉ ብፅዕት ይሉኛል ያለቸው ተጀመረ። ድንግልናዋን፥ መመስገኗን፥ ምንነቷን ካየነ አማላጅነቷን ደግሞ በአማላጅ ምዕራፍ ማገናዘብ እንችላለን።

ከጥንተ አብሶ ነጻ ናት ወይ?

በብሥራት ጊዜ መልአኩ ቅዱስ ገብርኤል ጸጋን የተመላሽ ሆይ! ደ ይበልሽ ያለውን ይዘው እመቤታችንን ጥንተ አብሶ አልነካትም፥

ከአዳም ጀምራ ስትወርድ ስትዋረድ የመጣች ንጹሕ ዘር ናት የሚሉ አሉ። ሌሎች ደግሞ ጸጋን የተሞላች ከተወለደች በኋላም፥ መንፈስ ቅዱስ ካነጻት በኋላም ሊሆን ይችላል፤ ዘለዓለማዊ ድንግልናዋም በነቢያት ሲነገር ከጥንተ አብሶ ግን ነጻ ናት ያለ አንድም ነቢይ ስለሌለ፥ መልአኩም መንፈስ ቅዱስ ይጸልልሻል ብሎ እንደሚያነጻት ተናገረ እንጂ እኔ ወንድ አላውቅም እንዴት ይሆንልኛል? ስትለው ሳለ ያለ ጥንተ አብሶ መወለዱን ለመናገር ምቹ ጊዜ ሳለው፥ የመንፈስ ቅዱስን ማንጻት ተናግሮ ነው ያለፈው። የቤተ ክርስቲያን ሊቃውንትም መንፈስ ቅዱስ እንዳነጻት፥ አንጺሖ ሥጋሃ ጎደረ ላዕሌሃ (ሥጋዋን አንጽቶ በላይዋ ላይ አደረ፥ ቅዱስ ያሬድ) ገሊላዊት ሐቀፈተከ፥ ነፍሳ ቀደስከ፥ ወሥጋሃ አንጻሕከ (ገሊላዊት ታቀፈችህ፥ ነፍሷን ቀደስህ፥ ሥጋዋን አነጻሕ መ.ቅ.ገ. 438:21) እያሉ ስለሚናገሩና አብዛኞቹ አባቶችም እንደ ዳዊትንና ሰሎሞንን የመሳሰሉት ወንጀሎኞችና አመንዝሮች ስለነበሩ፥ በየት አልፋ ነው እሷ ከጥንተ አብሶ ነጻ የምትሆነው ይላሉ። ለሁሉም የቅዱሳት መጻሕፍትንና የቅዱሳን አበውን ትምህርት ከዚህ ቀጥለን አቅርበናልና አንባቢ በጥንቃቄ አንቦ እንዲከተለው አደራ እንላለን።

ኢሳኢያስ ም. 61:1-3፥ እግዚአብሔር ለድኆች የምሥራቹን ቃል እንዳበሥር ቀብቶ ስለላከኝ፥ የልዑል እግዚአብሔር መንፈስ በእኔ ላይ ነው። ልባቸው የተሰበረውን እንድፈውስ የተጨቆኑትን ነጻ እንዳወጣና፥ ለተሰበሩትም ነጻነትን እንዳበስር ልኮኛል። እንዲሁም እግዚአብሔር ጠላቶቻቸውን ድል ነሥቶ ሕዝቡን የሚያድንባት የጸጋ ዓመት መድረሷን እንዳውጅ ልኮኛል፥ ያዘኑተን እንዳጽናና በጽዮን ሐዘንተኞች ለሆኑት በሐዘን ፈንታ ደስታን እንድሰጥ በትካዜ ፈንታ የምስጋና መዝሙር እንዲዘምሩ አደርግ ዘንድ ልኮኛል። ይህን ጥቅስ ጌታም ቃል ለቃል ደግሞታል፤ (ሉቃ. 4:18-19)። ይህም ትስብእትን ሲያይ የተነገረ መሆኑን ለሥጋ ለትስብእት የተነገሩ ቃላት በሚለው ምዕራፍ አስረድተናል።

ነቢዩ ቀብቶ ላከኝ ያለውን ሊቁ መልአኩ ቅዱስ ገብርኤል መንፈስ ቅዱስ ወዳንቺ ይመጣል በአንቺም ያድራል፥ ማለት ያነጻሻል ባላት መሠረት አምላክ እንዲፀነስ መንፈስ ቅዱስ በማርያም ላይ ወርዶ ሥጋዋን ባነጻ በመንፈስ ቅዱስ ይተረጎማል፤ ይህችም የቅባት (የማንጻት ትርጓሜ ናት። አምላካዊ ቃል ከሥጋዋ ጋር አንድ እስከሆነ ድረስ በእርስዋ (በሥጋ) አድሮ ድል የነሣቻትንና ያረከሰቻትን የአዳምን ሥጋ አንጽቷታልና ብሏል (ግብረ ሕማማት ገጽ 205)

<u>ቅዱስ ያሬድም</u>፡ እመቤታችንና የድኅነታችን ምክንያት የሆነችው የአምላክ እናት ማርያም ከአዳም ሥር የተገኘች ናት። ነፍሷን አክብረህ ሥጋዋን አንጽተህ ልጅህን በርስዋ እንዲያድር አደረግህ። (የጥር. 21:ዝግሬ)

ያግረ ኮከብ በማርያም አደረ
ሥጋዋን አንጽቶ በማርያም አደረ

ርሷን ቀድሶ መለኮቱን ከሥጋዋ ጋራ አዋሐደ። (ነሐሴ 15 ቀን ዚቅ)

<u>ያዕቆብ ዘሥሩግም</u>፡ ከአብ የማይለይ ረጅም ፈትል ሰማይና ምድርን የፈጠርህ፡ በፈቃድህ ከሰማይ ወረድህ፡ የድንግል ማሕፀን ወሰነህ፡ የድኖች ልጅ ትንሽ ብላቴና አቀፈችህ፡ ነፍሷን አከበርህ፡ ሥጋዋንም አነጻሕ። አጸናሃትም ባንተም አልደነገጠችም። (መ.ቅ. ቁጥር 21 ገጽ. 438)

<u>ጎርጎርዮስ ዘኑሲስም</u>፡ ቃል በግብረ መንፈስ ቅዱስ ሰው ሆነ የሚለው ትርጓሜም ከሐድያንና መናፍቃን እንደሚያስቡት የመንፈስ ቅዱስ ሥጋ ኑሮት ወይም የተፈጠረ ሁኖ ሳይሆን፡ መንፈስ ቅዱስ የማርያምን ሥጋ አነጻ ቀደሰ፡ የአብ አካላዊ ቃልንም ለመፅነስ የበቃች አደረጋት እንጂ ብሏል። (ሃይ. አበ. ገጽ. 125 ቁጥር 19)

በዘመናችንም አቶ ዐሥራት ገብረ ማርያም ትምህርተ መለኮት በሚለው መጽሐፋቸው (ገጽ. 95-6) የገብርኤልን አርኬ ጠቅሰው መንፈስ ቅዱስ ማርያምን ከጥንተ አብሶ እንዳነጻት አብራርተው፡ ገልጸው ጽፈዋል።

ሰላም ለከ ገብርኤል ለማርያም ጎይሰ ልውል ጸለላ
መንፈስ ቅዱስ አንጽሐ ሥጋ አባላ፡ ተፈሥስሒ ሰበ ትቤላ=ገብርኤል ሆይ! ሰላም ላንተ ይሁን፡ ማርያምን ደስ ይበልሽ ባልሃት ጊዜ የልውል ጎይል ጸለላት፡ መንፈስ ቅዱስ ሰውነትዋን አንጽቷታል። ዝቅ ብለውም እነሆኝ የጌታ ባሪያ እንደ ቃልህ ይሁንልኝ ባለች ጊዜ፡ ብላ እምነቷን በእግዚአብሔር ላይ ባሳረፈች ጊዜ ጌታን ከመውለዱ በፊት መንፈስ ቅዱስ እመቤታችንን ቀድሶና አንጽቶ የጥንቱን የአዳምን ኃጢአት አስወግዶላታል ብለው ጥንተ አብሶ ወደ ጌታ ሳይተላለፍ ከማርያም ላይ መቅረቱን አስረድተዋል። እሷም ያው መንፈስ ቅዱስ ከአደረባት በኋላ በአምላኪየ ወመድኀንየ=በአምላኪየና በመድኀኒቴ ብላለች። ከጥንተ አብሶ ነጻ ብትሆን ኑሮ አዳኜና መድኀኒቴ ግለት አያስፈልጋትም ነበር። የቅድስት ድንግል ማርያም ያለ ጥንተ አብሶ መወለድ በሮም ቤተ ክርስቲያን ለብዙ ዘመን ሲያጨቃጭቅ ኑሯል። አሁን ግን ከብዙ ጭቅጭቅ በኋላ የሮማ ቤተ ክርስቲያን ቅድስት ድንግል ማርያም ከጥንተ አብሶ ነጻ ናት ብላ ወስናለች።

ይህ ክርክር በጣም ተባብሶ የነበረው በፍራንሲስካንና በዶሚኒካን መነኮሳት መካከል ነው። የፍራንሲስካን መነኮሳት ድንግል ማሪያም ከጥንተ አብሶ ነጽታ ተወልዳለች ሲሉ ዶሚኒካን ደግሞ ይህን አይቀበሉም ነበር። ይህንም በተመለከተ በትሬንዲንቲኒ ጉባዔ ላይ ከፓፑ ተልከው በሄዱት በሦስቱ ካርዲናሎች መካከል ልዩነት ነበር። ዲሞንቲ የተባለው ካረዲናል ያለ ጥንተ አበሶ ተወለደች ሲል ካርዲናል ሲቲናክሩስ ደግሞ ይህን ሐሳብ የሚቃወም ሲሆን ካርዲናል ቶውሊ ግን ከማንኛቸውም ወገን አልነበረም። ብሎም ካለኃጢአት ተወለደች የሚሉት ወገኖች በመብዛታቸው ከፒየስ ዘጠነኛ ጀምሮ የቅድስት ማርያም ያለጥንተ አብሶ መወለድ በርግ ቤተ ክርስቲያን ተወሰነ። እሱም እንደ ኤ. ስ. በ1854 ዓ.ም. የተደረገው የፓፓው ውሳኔ እንደሚከተለው ነው፤

በኢየሱስ ክርስቶስ ሥልጣን፥ በብፁዓን ጴጥሮስና ጳውሎስ ሥልጣን፥ በሥልጣናችንም ድንግል ማሪያም ከተፀነሰችበት ደቂቃ ጀምሮ ከጥንተ አብሶ የነጻች መሆንዋን የሚያስተምረውን ትምህርት ወስነናል። (ትምህርተ መለኮት 3ኛ መጽሐፍ ገጽ 556-557 በዐረብኛ ቋንቋ)። ስለ እመቤታችን ብዙ መጽሐፍ ይቻል ነበር ግን ወረቀት ስለተወደደና የገንዘብ ዐቅሙም አጭር ስለሆነ ለእስዋ እስክዚህ የተደረገው ይብቃንና እስዋ መመኪያዋ ወፂሆነቸው ሴት በክርስቶስ አደባባይ ወደሚለው ርእስ እንሻገር።

ምዕራፍ 29

ሴት በክርስቶስ አደባባይ፤

ይህ ርእስ በአሰፈው መንግሥት በንግግር ነጻነት ምክንያት ከተከለከለው መጽሐፌ እንዳሰ አንዱ ምዕራፍ የተገለበጠ ነው።

ሴት በሐዲስ ኪዳን

53. የሴት ጠቅላላ አቋም በሐዲስ ኪዳን

ከክርስቶስ ልደት በፊት ሀገር ለመጠበቅም ሆነ ለግስፋፋት የሚያስፈልገው ተባዕታዊ ጎይል ነበር፤ ምክንያቱም የጦር መሣሪያውም ሆነ ፍልስፍናው የተመሠረተው በጡንቻ ብርታት፥ በጉልበት ጥናት ነውና። አሁን ግን ብሉይን አሳልፎ ሐዲስን የተካው፥ ያለፈውን ሁሉ ሥርዓት ሽሮ ሐዲስ ሕግ ደንገገ፤ ሐዲስ አቋም መሠረተ፥ ሥርዓቱ ከቀድሞው ሁሉ የተለየ ሐዲስ መንግሥት ዐወጀ። ይህም ሐዲስ መንግሥትና ሥርዓት መሲሑ ክርስቶስን የመጀመሪያው ሥጋ ሰባሲ አብዮታዊ አደረገው። ክርስቶስ ከሱ በፊት የነበረውን አሕዛብዊና አይሁዳዊ ሥርዓት ሁሉ ተቃወመ። ከዐሠርቱ ቃላት በቀር ሁሉንም ሻረ። ፍልስፍናውና ትምህርቱም ከጎያሉ ደካማውን፥ ከዕቡዩ ትሑቱን፥ ከጻድቁ ኃጥኡን፥ ከወንዱ ሴቱን፥ ከጉልማላው ሕፃኑን ይደግፋል፥ ደገፈ፥ አነቃቃ። (ማቴ. 9:13፤ 11:28-29፤ 18:2-11፤ 19:4-7፤ ማር. 2:17፤ ሉቃ. 5:32)

ቀኝ ጉንጭህን ቢጸፋህ ግራ ጉንጭህን ስጥ፥ አንድ ምዕራፍ አስገድዶ ቢያሸክምህ ሁለት ምዕራፍ ውሰድለት፥ ቀሚስህን ሊቀማህ ለሚፈልግ ጋቢህን ድገመው፥ ክፉን ደግ በግድሪግ አንጂ በክፉ አትቃወም፥ ጠላትህን ውደድ፥ ወዘተ..እያለ አስተግረ። ትምህርቱንም ተአምር እያሳየ፥ በቃሉ ድውይ እየፈወሰ፥ ሙት እያስነሣ፥ ዕውር እያበራ፥ አንካሳ እያበረታ ተከታዮቹ እንዲቀበሉት አሕዛብ እንዲያምኑት አደረገ። ስለዚህ በመንግሥቱ በጎይል የሚሠራ ነገር ሁሉ ለትዕግሥት፥ ለትሕትና ቦታውን ለቀቀ። ወዲያውም ደካማው የጎይለኛውን፥ ትሑቱ የዕቡዩን፥ የዋሁ የጠቢቡን፥ በትምህርት ደካማው የሊቁን፥ ዓጣ አስጋሪው የሊቀ ካህናቱን ቦታ ወሰደ። (ማቴ. 5:39-48፤ 10:1፤ ሉቃ. 6:27-39)

በዚህ ትምህርት ምክንያት ከዚያ በፊት የወንድ ተገዥ ሁና ከማጀት ትኖር የነበረችው ሴት እንደ ወንዶች ክርስቶስን ተከትላ፥ አደባባይ ላደባባይ እየዞረች፥ ሀገር ላገር እየተመላለሰች መጀመሪያም ተማረች፥ በኋላም ከባርነት ነጻ አውጥቶ ከወንድ እኩል ያደረጋትን መምህር፥ ነቢይ፥ አምላክ እያመሰገነች ሐዋርያትን ተከትላ በዓለም እየዞረች ሰበከች። (ሉቃ. 23:49፤ ሮሜ 16:1፤ 12)

ን ታድርግ? ከክርስቶስ በፊት እንኳንስ ሊያስተምራት፥ ሊያስከትላት
ቀ መዝሙሩ ሊያደርጋትና ከጉባኤው የሚያስደርሳት ነቢይም ሆነ
ላስፋ አልነበረም። በግሪክማ ዓለም ከወንድ ስብሰባ መካከል ገብታ
ትገኝ ከኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ገብታ የተገኘች ውሻ ነበረች።
እን. 44)
ብዙ ሽ ዘመን በጸታዋ ምክንያት ከእንስሳትና ከወንድ መካከል ሁና፥
ወንድ ተናጋሪ ጥሪት እየተባለች የኖረችው ሴት ዛሬ ደርሶ
እስራኤል ተራራ፥ ሜዳ፥ ከተማ፥ ገጠር እየዞረ ሴት ከወንድ እኩል
ት እያለ የሚሰብክ ነቢይ በመነሣቱ፥ ራስዋን ሴቲቱን ገረማት፥
ንድን ደነቀው። በዚህ ፈላስፋው ሶቅራጥስ በግሪክ ሕፃናቱን
ያባልግ ነው ተብሎ በመርዝ እንደ ተገደለ ክርስቶስም ሴትም ሰው
ት፥ ከወንድ እኩል ናት በማለቱ ብርቱ ተቃውሞ ተነሣበት፥ ሴት
ግሩን ስታጥበው ዝም በማለቱ፥ ስታነጋግረው በመመለሱ ተነቀፈ፥
ሸሟጠጠ፥ ተጓጠጠ፥ ነቢይ ቢሆን፥ አምላክ ቢሆን መቼ እንዲህ
ደርግ ነበር እየተባለ ተሸረደደ።
ሁን እንጂ ሁሉንም ታግሦ ከባቢሎን፥ ከአሶርያ፥ ከእስራኤል፥
ጽርእ ከሮም ሕግ ነጻ አውጥቶ ከወንድ እኩል እደረጋት። በራስዋ
ንፍናና አካባቢዋ እስራኤላዊና አሕዛባዊ ተጽዕኖ ምክንያት በግብር
ንዳንድ ቦታ ሀገር ስትጨቆን ቆየች እንጂ ክርስቶስ በሕግ ነጻ
ወጣት ከሁለት ሺ ዘመን በፊት ነው። ርግጥ ከስድስተኛው መቶ ዓ.ም
ምራ ሴት በግብጽ ለመብቷ ስትታገል፥ ስትጥልም፥ ስትወድቅም
ራለች፥ ከወንድ በላይም እኩልም የበታችም ስተሆን የኖረችበትም
ዜና ዘመን አለ። በዚያ ጊዜ ሴት የወንድ፥ ወንድ የሴትን ሥራ ይሠራ
ከናውን ነበር፥ ከተፈጥሮ ተግባር በቀር፥ በኋላ ግን ግብጽን፥
ሥራቃውያን ፋርስና ባቢሎን ወግተው በጦር ኀይል ቅኝ ሀገር
ድርገው፥ ልማዷን ሽረው፥ ባህሏን ለውጠው ሥርዓተ መንግሥቷን
ፍርሰው፥ የራሳቸውን ባህል ዘርግተው ለ3000 ዘመን ያህል
ረውባታል ከዚያም በትልቁ እስክንድር መሪነት ጽርእውያን ከፋርስ
ቀብለዋታል፥ ከእነዚህም ሮማውያን ተረክበው አሁንም የራሳቸውን
ግድ ሲዘረጉ የሴትም መብት ከግብጹ ነፃነት ጋራ ተደምሶ እስከ
ርስቶስ ቀዳማዊ ምጽአት ለ500 ዘመን ኑሯል። የሴት መብት በግብጽ
ጥቂት ጊዜም እንኳ ቢሆን በክርስትና ምክንያት ከሞላ ጎደል የብርሃን
ላንጭል ሲያይ የቅብጣውያን ነጻነት ግን እንደ ሞተ ቀርቷል።

ምን ታድርግ? ከክርስቶስ በፊት እንኳንስ ሊያስተምራት፡ ሊያስከትላት ደቀ መዝሙሩ ሊያደርጋትና ከጉባኤው የሚያስደርሳት ነቢይም ሆነ ፈላሰፋ አልነበረም። በግሪክማ ዓለም ከወንድ ስብሰባ መካከል ገብታ ብትገኝ ከኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ገብታ የተገኘች ውሻ ነበረች። (አን. 44)

ለብዙ ሽ ዘመን በጸታዋ ምክንያት ከእንስሳትና ከወንድ መካከል ሁና፡ የወንድ ተናጋሪ ጥሪት እየተባለች የኖረችው ሴት ዛሬ ደርሶ በእስራኤል ተራራ፡ ሜዳ፡ ከተማ፡ ገጠር እየዞረ ሴት ከወንድ እኩል ናት እያለ የሚሰብክ ነቢይ በመነሣቱ፡ ራስዋን ሴቲቱን ገረማት፡ ወንድን ደነቀው። በዚህ ፈላስፋው ሶቅራጥስ በግሪክ ሕፃናቱን ሊያባልግ ነው ተብሎ በመርዝ እንደ ተገደለ ክርስቶስም ሴትም ሰው ናት፡ ከወንድ እኩል ናት በማለቱ ብርቱ ተቃውሞ ተነሣበት፡ ሴት እግሩን ስታጥበው ዝም በማለቱ፡ ስታነጋግረው በመመለሱ ተነቀፈ፡ ተሸሟጠጠ፡ ተጓጠጠ፡ ነቢይ ቢሆን፡ አምላክ ቢሆን መቼ እንዲህ ያደርግ ነበር እየተባለ ተሸረደደ።

ይሁን እንጂ ሁሉንም ታግሦ ከባቢሎን፡ ከአሶርያ፡ ከእስራኤል፡ ከጽርእ ከሮም ሕግ ነጻ አውጥቶ ከወንድ እኩል አደረጋት። በራስዋ ስንፍናና አካባቢዋ እስራኤላዊና አሕዛባዊ ተጽዕኖ ምክንያት በግብር ባንዳንድ ቦታ ሀገር ስትጨቆን ቆየች እንጂ ክርስቶስ በሕግ ነጻ ያወጣት ከሁለት ሺ ዘመን በፊት ነው። ርግጥ ከስድስተኛው መቶ ዓ.ም ጀምራ ሴት በግብጽ ለመብቷ ስትታገል፡ ስትጥልም፡ ስትወድቅም ኑራለች፡ ከወንድ በላይም እኩልም የበታችም ስተሆን የኖረችበትም ጊዜና ዘመን አለ። በዚያ ጊዜ ሴት የወንድ፡ ወንድ የሴትን ሥራ ይሠራ ያከናውን ነበር፡ ከተፈጥሮ ተግባር በቀር፡ በኋላ ግን ግብጽን፡ ምሥራቃውያን ፋርስና ባቢሎን ወግተው በጦር ኃይል ቅኝ ሀገር አድርገው፡ ልማዷን ሽረው፡ ባህሏን ለውጠው ሥርዓተ መንግሥቷን አፍርሰው፡ የራሳቸውን ባህል ዘርግተው ለ3000 ዘመን ያህል ኑረውባታል ከዚያም በትልቁ እስክንድር መሪነት ጽርአውያን ከፋርስ ተቀብለዋታል፡ ከእነዚህም ሮማውያን ተረክበው አሁንም የራሳቸውን ልማድ ሲዘረጉ የሴትም መብት ከግብጹ ነፃነት ጋራ ተደምሶ እስከ ክርስቶስ ቀዳማዊ ምጽአት ለ500 ዘመን ኑሯል። የሴት መብት በግብጽ ለጥቂት ጊዜም እንኳ ቢሆን በክርስትና ምክንያት ከሞላ ጎደል የብርሃን ጭላንጭል ሲያይ የቅብጣውያን ነጻነት ግን እንደ ሞተ ቀርቷል።

54. ሴት በክርስቶስ ዘንድ

ሀ) ከልደት እስከ ሞት

በክርስቶስ ዘንድ ሴትና ወንድ አኩል ናችው፡ የጸታ ልዩነት የለም። ማንኛቸውም ስው ዋጋ የሚያገኘው በሃይማኖቱና በምግባሩ ነው እንጂ በጸታውና በዘሩ አይደለም። ስለዚህ ገና ከመወለድ በፊት፡ ፍጡሩ ናት ከዚያም ሴት ሳይል መልአኩን ልኮ የእናቱን የማርያምን ፊቃድ አስጠየቀ፡ ፊቅዳ ስትስማማ ተፀንሶ ተወልዷል። በብሥራት ጊዜም ለስው ዘር ከመላእክት ተደርጎ የማይታወቀውን ምስጋና በትሕትና ስላምታ ክቡር ሊቀ መላእክቱ ቅዱስ ገብርኤል ሰድንግል ማርያም አቅርቧል። ከዚህ በፊት መላእክት ከአምላክ ወደ ሰው ሲላኩ ጸሎትህን እግዚአብሔር ስለሰማህ እንዲህ አደረግልሃለሁ ትሆናለህ ነው እንጂ የተባረክሽ ነሽ ብፀዕት ነሽ የሚል ድምፅ ተሰምቶም አይታውቅም። ከዚህ በፊት እንዳልነው ክርስትና የነገድና የጸታ ሃይማኖት አይደለም እንጂ ቢሆን ኖሮ ሴቶች በጸታቸው ምክንያት ከወንድ በላይ ይሆኑ ነበር።

1. መልአኩ ወደ እርሷ ገብቶ ደስ ይበልሽ ፀጋ የሞላብሽ ሆይ ጌታ ካንች ጋር ነውና፡ አንቺ ከሴቶች መካከል የተባረክሽ ነሽ አላት። እስዋም ባየችው ጊዜ ከንግግሩ የተነሣ በጣም ደነገጠችና ይህ እንዴት ያለ ሰላምታ ነው? ብላ አሰበች። መልአኩም ማርያም ሆይ በእግዚአብሔር ፊት ጸጋ አግኝተሻልና አትፍሪ፡ እነሆም ትፀንሻለሽ ወንድ ልጅም ትወልጃለሽ፡ ስሙንም ኢየሱስ ትይዋለሽ፡ እርሱም ታላቅ ይሆናል፡ የልዑል ልጅም ይባላል፡ ጌታ አምላክም የአባቱን የዳዊት ዙፋን ይሰጠዋል፡ በያዕቆብ ቤትም ላይ ለዘለዓለም ይነግሣል። ለመንግሥቱም መጨረሻ የለውም አላት። ማርያምም መልአኩን ወንድ ስለማላውቅ ይህ እንዴት ይሆናል አለችው። መልአኩም መልሶ መንፈስ ቅዱስ በአንቺ ላይ ይመጣል፡ የልዑል ኀይልም ይጸልልሻል ስለዚህም ደግሞ ካንቺ የሚወለደው ቅዱስ የእግዚአብሔር ልጅ ይባላል፡ እነሆ ዘመድሽ ኤልሳቤጥ በእርጅናዋ ወንድ ልጅ ፀንሳለች፡ ለእርስዋም መካን ትባል ለነበረችው ይህ ስድስተኛ ወሯ ነው፡ ለእግዚአብሔር የሚሳነው ነገር የለምና አላት። ማርያምም እነሆ የጌታ ባሪያ እንደ ቃልህ ይሁንልሽ አለችው።

ኤልሳቤጥም መንፈስ ቅዱስ ሞላባትና በታላቅ ድምጽም ጮኽ አንቺ ከሴቶች ሁሉ የተባረክሽ ነሽ፡ የማሕፀንሽም ፍሬ የተባረከ ነው፡ የጌታዬ እናት ወደ እኔ ትመጣ ዘንድ እንዴት ይሆንልኛል? እነሆ የሰላምታሽ ድምፅ በጆሮዬ በገባ ጊዜ ሽሉ በማሕፀኔ ዘለለ፡ ከጌታ

የተነገረላት ቃል ይፈጸማል ብላ ያመነች ብፅዕት ናት አለቻት፥ ማርያምም....ከዛሬ ጀምሮ ትውልድ ሁሉ ብፅዕት ናት ይለኛል ....አለች። (ሉቃ. 1:28-49።)

እነሆ! እንደዚህ ጥቅስ ሊቀ መላእክቱ ቅዱስ ገብርኤል አመስግኗል። በማርያምና በኤልሳቤጥ መንፈስ ቅዱስ ካደረባቸው በኋላ፥ የመንፈስ ቅዱስ ማጉያ ሁነው ማርያምን እንቺ ከሴቶች መካከል የተባረክሽ ነሽ፥ የማሕፀንሽም ፍሬ የተባረከ ነው፥ ከዛሬ ጀምሮ ትውልድ ሁሉ ያመሰግኑኛል፥ ብፅዕት ይሉኛል ብለው ማርያምን አመሰግነዋል። በዚህም እግዚአብሔር አብና መንፈስ ቅዱስ ሴቷን ድንግል ማርያምን ማመስገናቸውን እንረዳለን። በጥንቱ ተፈጥሮ ሔዋንን የረገመው እግዚአብሔር በብሥራትና በዘመነ ፅንስ ሴትን አመሰግኗል። በዚህም ርግማኑ በምስጋና ተመልሷል። ሴትም ርግም ናት መባሏ ቀርቷል። እንደዚህ ባለ ሁኔታ ተፀንሶ ከተወለደ በኋላ በሕገ ኦሪት አባትህንና እናትህን አክብር ያለውን ትእዛዝ ለመፈጸም ለእናቱና እንደ አባት በሞግዚትነት ላሳደገው ዮሴፍ እየታዘዘ እያገለገለ አድጓል። የወንድ ዘር ሳይጨመር ከሴት በመወለዱ ሊናገሩት ያሳፍር የነበረውን የሴትን ዝቅተኛነት ከሥሩ መንግሎ ጥሏል።

2. ከእነሱም ጋራ ወርዶ ወደ ናዝሬት መጣ፤ ይታዘዝም ነበር። ሉቃ. 2:51፤ እን. 38።)

ለ. ሲያስተምር፥ ስለሴት ያስተማረው

ባለፈው እንቀጽ እንዳየነው ሴት ከወንድ እኩል ናት ብሎ በማስተማሩ በክርስቶስ ብዙ የተንኮል ፈተና ደርሶበታል፤ ሁሉንም በመርሐ መሠረት በሚገባ መልሶታል። ከዚህ ቀጥለን እንደነገሩ አካሄድ በቅደም ተከተል ስለሴት ባለው አስተያየት ከጸሐፍት፥ ከፈሪሳውያን፥ ከሰዱቃውያን ከሌላም ልዩ ልዩ ሰዎች ለፈተናና ለውጠራ የቀረቡለትን ጥያቄዎች እናያለን፤

1. መጀመሪያ ፈሪሳውያን

3. ፈሪሳውያንም ወደ እሱ ቀረቡና ሊፈትኑት (ሲፈትኑት) ሰው በማንኛቸውም ምክንያት ሁሉ ሚስቱን ሊፈታ ተፈቅዶለታልን? አሉት። እሱም መልሶ፥ ፈጣሪ በመጀመሪያ ወንድና ሴት እደረጋቸው፥ ስለዚህም ሰው አባቱንና እናቱን ይተዋል፤ ከሚስቱም ጋራ ይጣበቃል፥ ሁለቱም አንድ ሥጋ ይሆናሉ የሚለውን ቃል አላነበባችሁምን? እንግዲያስ አንድ ሥጋ ናቸው እንጂ ሁለት አይደሉም፥ እግዚአብሔር ያጣመረውን እንግዲህ

ሰው አይለይ አለ። እነሱም እንግዲያስ ሙሴ የፍቺ ምስክር ወረቀት ሰጥተው እንዲፈቷት ለምን አዘዘ? አሉት። እሱም ሙሴስ ስለልባችሁ ክፋት ምሽቶቻችሁን ትፈቱ ዘንድ ፈቀደላችሁ፥ ከጥንት ግን እንዲህ አልነበረም፥ እኔ ግን እላችኋለሁ ያለዘሙት ምክንያት ምሽቱን ፈቶ ሌላይቱን የሚያገባ ሁሉ ያመነዝራል (አመነዘረ)፥ የተፈታችቱንም የሚያገባ ያመነዝራል አላቸው። ደቀ መዛሙርቱም የባልና ምሽት ሥርዐት እንዲህ ከሆነ መጋባት አይረባም (አይጠቅምም) አሉት። (ማቴ. 19:3-10)

ይህን ጥያቄ ያቀረቡለት ሴትና ወንድ እኩል ናቸው እያለ ስለሚያስተምር በሁለተኛው ምዕራፍ እንደተነገረው በቤተ እስራኤል ወንድና ሴት እኩል ስላልነበሩ፥ ወንድ በፈለገበት ጊዜ ምክንያት ፈጥሮ ሰነፍ ናት፥ ደረቅ ናት፥ ሌባ ናት፥ ወዘተ..በሚል የምስክር ወረቀት ሰጥቶ ይፈታታል። ይህን ምስክር ወረቀት ሳትይዝ ግን ከወንድ ጋራ ብትገኝ በደንቢያ ተወግራ ትገደላለች። ልግዱና ሕጉ ይህ ሲሆን እንኪያ አንተ ሴት ከወንድ እኩል ናት እንዴት ትላለህ? ከምን አገኘኸው እንዲህ ያለውን ትምህርት ለማለት አቅርበውታል፤ እሱም አሪትን ጠቅሶ መልሷቸዋል። ፈሪሳውያን ከሄዱ በኋላ ግን በሴተና ወንድ እኩልነት የተገረሙት ደቀ መዛሙርቱ የጋብቻ ሥርዓት እንዲህ ከሆነ መጋባት አይጠቅምም፥ አይረባም ብለውታል። በዘመናቸው ምሽት ማግባት፥ ባሪያ መግዛት ስለነበረ፥ ሴት ከባሏ አኩል ከሆነችስ? ማግባት ረብም የለው ባይ ናቸውና ቢጠይቁት እንዲያውም ከዚያ በፊት የመፍታት መብት ያልነበራትን እሷም ለመፍታት እንደምትችልና ፈታ ብታመነዝር፥ ወንዱም እሷን ፈቶ ቢያመነዝር ሁለቱም በሕግ ፊት እኩል እንደሆኑ አረጋግጠላቸዋል፤

4. በቤትም ደቀ መዛሙርቱ ስለዚህ ነገር ጠየቁት። እርሱም ምሽቱን ፈቶ ሌላ የሚያገባ ሁሉ በረሰዋ ላይ አመነዘረ (ያመነዝራል) እሷም ባልዋን ፈታ ሌላ በታገባ አመነዘረች (ታመነዝራለች) አላቸው። (ማር. 10:10-12)

2. ሰዱቃውያን፤

ትንሣኤ ሙታን የለም ተሚሉት ፈሪሳውያን ጓደኞች ሰዱቃውያን ደግሞ ባንድ ደንቢያ ሁለት ወፎች ትንሣኤ ሙታንና የሴትን እኩልነት ለመግደል የሚከተለውን ጥያቄ አቀረቡለት፤

5. በዚያን ቀን ትንሣኤ ሙታን የለም የሚሉ ሰዱቃውያን ወደ እርሱ ቀረቡና መምህር ሆይ፤ ሙሴ አንድ ሰው ልጅ ሳይወልድ ቢሞት ወንድሙ ምሽቱን አግብቶ ዘር ይተካለት አለ፥ እነሆ

ሰባት ወንድማማች በአኛ ዘንድ ነበሩ፤ ትልቁ ምሽት አግብቶ ሳይወልድ ሞተ፥ ዘርም ስለሌለው ትንሽ ወንድሙ አገባት፥ እንዲህ እያሉ እስከ ሰባተኛው ድረስ አገቧት። ከሁሉም በኋላ ሴቲቱ ሞተች፥ ሁሉም አግብተዋታልና በትንሣኤ ቀን ለማንኛቸው ምሽት ትሆናለች? አሉት። ኢየሱስም መልሶ፥ መጻሕፍትንና የእግዚአብሔርን ኀይል አታውቅምና ትስታላቸሁ፥ በትንሣኤስ በሰማይ እንዳሉ መላእክት ይሆናሉ እንጂ አያገቡም አላቸው። (ማቴ. 22:23-32፤ ማር. 12:18-27፤ ሉቃ. 20:27-40)

በዚህ ጥያቄ ሰዱቃውያን ሊረዱት የፈለጉት ሴት የወንድ ገንዘብ፥ ተናጋሪ ጥሪት ስለሆነች በዕለተ ትንሣኤ ለማን እንደምትሆን ነው። ጌታ ግን በሰማይ አይጋቡም ብሎ በዚህ ዓለም የሴት ባሪያ እንዳላቸው በወዲያኛውም የሴት አገልጋይ የሚኖራቸው የሚመስላቸውን ሁሉ እንዲያስቡና ሴትና ወንድ በመንግሥተ ሰማያት እኩል መሆናቸውን አስረድቷል። በዚህ በማቴ. ምዕራፍ 5:6:7፤ 15:27፤ በተጻፈው ትምህርቱ ሥርዐተ ረበናትን በፍጹም ደምስሶ አጥፍቷል፤ ለሴት ለደካማ፥ ለኃጥአ መምጣቱንም አስመስክሯል፤ ግልጥ ፍርጥ አድርጎ አረጋግጧል።

3. ወዳጆቹ ሕዝቦች ሁሉ፥

ሌሎች ፈሪሳውያን ሆኑ ተራ ሕዝቦች አንዳንድ ያልተማሩ ሰዎች ዛሬም ሴት መቅደስ ብትገባ፥ ታቦት ብትነካ ታረክሳለች እንደሚሉት፥ ክርስቶስንም ሴት ብትነካው የሚረክስ፥ የምታረክሰው ፥ የምታቆሽሸው፥ ነቢይነቱም የሚነሣው እየመሰላቸው ሴት በነካችው ቁጥር ይደነግጡ ያጉረመርሙ ነበር። (ሉቃ. 7:36-39)

4. የራሱ ደቀ መዛሙርት፥

በአካባቢያቸው ባህልና ልማድ ተወጥረው ደቀ መዛሙርቱም እንኳ ከሴት ጋራ በተነጋገረ፥ ሴት በነካችው ቁጥር የጌታቸው ስም እንዳይጠፋ፥ ዝናው እንዳይጎድፍ፥ ቅድስናው እንዳይረክስ ያስቡ ይሠጉ ነበር። ምን ያድርጉ እንኳንስ የሴት ተማሪና ደቀ መዝሙር ማበጀተና ስለሴት ማውራት፥ ትውልድን በሴት መቁጠር በተከለከለበት ነውር በሚባልበት ዘመንና አካባቢ ነው ተወልደው ያደጉት የኖሩት።

6. በዚያም ጊዜ ደቀ መዛሙርቱ መጡና ከሴት ጋራ በመነጋገሩ ተደነቁ። ነገር ግን ምን ትፈልጋለህ ወይንም ከእሷ ጋራ ለምን ትነጋገራለህ ያለው ማንም አልነበረም። (ዮሐ. 4:27)።

የጠየቀው የለም፥ ብዙ ታምራት ስለሚሠራ ፈርተው፥ ግን ደቀ መዛሙርቱ ምን ጊዜም ሴት ከነካችው፥ ከሴት ጋራ ከተነጋገረ ይደነቁም ያጉረመርሙም ነበር። (ማቴ. 20:20-24፤ 26:6-16፤ ዮሐ. 12:1-5)።

55. ሴቶች ለክርስቶስ ክርስቶስ ለሴቶች

ባሪያ ናችሁ፥ የወንድ ተንቀሳቃሽ ዕቃ፥ ተናጋሪ ላም ናችሁ እየተባሉ ሴቶች በተጨቆኑበት፥ በተረገጡበት ዘመን የሴትን መብት በታምራቱ የሚያስከብር ነቢይ ሲነሣ፥ ተነሣ ሲባል ጊዜ ሴት ሁሉ ቤቷን እየዘጋች፥ ንብረቷን እየሸጠች ትከተለው ገባች፤ ጀመረች፤ ደቀ መዝሙሩም ለመሆን ሀገር ላገር፥ ከተማ ለከተማ ትከተለው፥ ትንከራተት ጀመር። ነቢዩ ላከኝ፥ ክርስቶስ አዘዘኝ እያለች ለመስበክ ታጥቃ ተነሣች። ቤት ያላትም ከቤቷ ተቀብላ ለማስተናገድ በጉጉት አቆብቁባ ትጠበቃለች ሆነ።

ከናዝሬት እስከ ኢየሩሳሌም ሴቶች ሁሉ የሚያወሩት ስለክርስቶስ ሆነ። እሱም ወደዳቸው፥ አፈቀራቸው። ከሕመም ፈወሳቸው፤ ሙት አነሣላቸው። ከመቶ ሃያው ቤተ ሰብእም ሠላሳ ስድስት ሴቶች እንዲቆጠሩ አደረገ። ማንም ሲያጠቃቸው ይሟገትላቸው ነበረ። ሴቶች ያስተናግዱታል፤ እግሩን ያጥቡታል፤ በሽቶ ይመዘምዙታል፤ ይህ ሁሉ የንጹሕ ልባዊ ፍቅራቸው ምልክት ነበረ። ከወንዶች ሐዋርያት ይልቅ በግብራቸው ፍቅራቸውን ገልጠዋል፤ ልጨኛነታቸውን አስረድተዋል፤ ውስታቸውን አሳይተዋል። (ማቴ. 8:14-15፤ 9:19-25፤ 15:21-28፤ 26:6፤14፤ ማር. 16:9፤ ዮሐ. 11:5:1-5፤ 12:1-9)።

<u>በኋላም በዐላውያን አደባባይ ስለወደዳቸው አምላካቸው፥ መጽኀኒታቸው ኢየሱስ ክርስቶስ ሕይወታቸውን በሰማዕትነት አሳልፈዋል።</u>

ይህን ፍቅራቸውን ያዩ አይሁድ ቀንተው ያላደረጉት ተንኮል የለም። ከዚህ በፊት ካየነው ሌላ ብቻዋን እንደምትሠራው ሁሉ ግብረ አበሯን ወንዱን ትተው፥ ይህች ሰው ስታመነዝር ይዘናታል፤ በሕጋችን መሠረት መወገር አለባት፥ አንተስ? ምን ትላለህ? ብለው አንዱን ከፊቱ አቆሟት። እሱ ግን ተንኮላቸውን ዐውቆ ከእናንተ ኃጢአት ያልሠራ (አጠይሞ ለመናገር ነው እንጂ ያላመነዘረ ማለቱ ነው) የመጀመሪያውን ድንጊያ ይጣልባት ብሎ አንገቱን አቀርቅሮ ይጽፍ ጀመር። በዚህ ጊዜ ሁሉም ከሲቀ ካህናቱ ጀምሮ አንድ ባንድ እየወጡ ሄዱ። ሴቲቱንም በነጻ ዳግመኛ እንዲህ ያለ ሥራ እንዳትሠራ መክሮ ሰደዳት።

ለመሆኑ ኃጢአት የሌለበት፥ ወይም ኃጢአት ያልሠራ የተባለው ሰዎቹንም ከአደባባዩ ያጠፋው ምን ዐይነት ወንጀል ይሆን? ለሚል ጠያቂ ያው እሷን የከሰሱበት ወንጀል ማመንዘር ነዋ! ሌላ ምን ይሆናል። ከሴትዬዋ ጋራ ሲያመነዝር የነበረውም ሰው አብሮ መጥቶ ይሆናል። በእንግሊዝ ሀገር እስከ 20ኛው መቶ ዘመን ድረስ፥ ሁለት ሁነው አመንዝረው፥ ሲያመነዝሩ ቢገኙ ወንዱን ለቀው ሴቷን ይቀጡ እንደነበረው ግለት ነው። (ዮሐ. 8:1-11)

ለመሆኑ ለምን ኃጢአት የለብኝም አልሠራሁም ብሎ ከመካከላቸው አንዱ የመጀመሪያውን ደንጊያ አልወረወረባትም? ለዚህማ በቃሉ ብቻ ሙት ሲያስነሣ፥ ድውይ ሲፈውስ፥ ዕውር ሲያበራ፥ ሌላም ብዙ ታምራት ሲያደርግ ዐይተዋልና፥ በታምራት ይገለናል ብለው ይፈራሉ። ይልቁንም እንደራሳቸው ገምተው በአጋንንቱ ጎይል ነው የሚሠራ ብለው ስለሚያወሩ ያንኑ የራሳቸውን ወሬ አምነው ይፈሩታል፤ አይደፍሩትም። ከዚህም ሌላ ወንዶቹ ሐዋርያት ከዮሐንስ በቀር ያልሠሩትን በጌታ ሕማማት ጊዜ በዐጸደ መስቀሉ ሳይለዩ አብረውት አይሁድን ሳይፈሩ ሲያለቅሱ ውለው ኋላም መቃብሩን ዐይተው ሽቶ እንደልማዳቸው ለመቅባት ተሰናድተዋል። እሑድ ሌሊትም በአጠበብ ገሥግሠው ወደ መቃብሩ ቢሄዱ መጀመሪያም መላአክት ተከሥተው ፥ በኋላም ጌታ ተገልጦ የታያቸው፥ ሂዱና ትንሣኤዬን ለደቀ መዛሙርቴ ንገሩ ብሎ ያዘዛቸው ሴቶችን ነው። በዚህም ሴቶችን እንዲያስተምሩ መላኩንና ግዘዙን እንግራለን። ሐዋርያት ግን አላመኗቸውም። ምክንያቱስ ቢሉ ያው ስለሴት ያላቸው አስተሳሰብ ዝቅተኛ ስለሆነ፥ ሳያረጋግጡ ነው መስሏቸው። ማቴ. 27:55-56፤ 61፤ 28:1-10፤ ማር. 15:40-41፤ 47፤ 16:1-12፤ ሉቃ. 23:27-31፤ 49፤ 55:56፤ 24:1-12)።

ከአሪት ለሴት አቅዋም የሚስማማውን እየጠቀሰ፥ የማይስማማውን፥ ሥርዓተ ረበናት ነክ የሆነውን እየሻረ ሴትን ከባርነት ሐራነት፥ ከአገልጋይነት እመቤትነት ከርግምትነት ብፅዕትነትን፥ ከርግማን ቡራኬ ብፅዕና ስጥቷታል። ይህም ከዚህ በፊት በአንቀጽ 53 እንዳየነው፥ መጀመሪያ በመልአኩ በቅዱስ ገብርኤል፥ ቀጥሎ በመንፈስ ቅዱስ ከዚያም በኤልሳቤጥ፥ አራተኛ በድንግል ማርያም፥ አምስተኛ በራሱ በኢየሱስ ክርስቶስ፥ ስድስተኛ፥ በጳውሎስ፥ ሰባተኛ በሌሎች ሐዋርያት ቃላትና መልእክታት ተረጋግጧል።

በግዴ ስም ተሸማም ሆነ ራስዋ ወይም ዘመዶች ለምታገባው ወንድ ገንዘብ ከፍለውላት ወደባሏ ቤት በባርነት፥ በአገልጋይነት፥ ደግሞም

ወንድ ወልዳ የባሏን የጌታዋን ስም ለማስጠራት ወንድ ተከትላ ወደ ወንድ ቤትና ሀገር ትሄድ የነበረቸውን ነጻ አውጥቶ፡ ከወንድ በታች የሚያደርጋትን ሕግና ልማድ ሁሉ ሽሮ፡ ከወንድ አስተካክሎ፡ እንዲያውም በሥልጣኑና በጎይሉ፡ ወንድ ቦታውን አይልቀቅ እንጂ ክርስቶስ ሌትን ትመራ፡ ትከተል የነበረችውን እንድትመራ አድርጓታል።

ከዚህም በላይ ፍች ለመጠየቅ በባቢሎን፡ በአሶርያ፡ በእስራኤል የማትችለውን ብትፈልግ ለመፍታት መቻሏን አረጋግጦላታል፡ ለምን ቢሉ ከወንድ እኩል ናታ! ናትና።

ርግጥ ነው፡ ለሴት መብት፡ ለሴት ክብርና ሥልጣን የተከራከረ፡ ሰሴት መጠቃት፡ መጨቆን የተቆረቆረ፡ ከክርስቶስ በፊት እንደሱ ያለ የለም፡ ግን ሥርዐተ ረበናትን (የአይሁድን ካህናት ልማድ) ጨርሶ መንግሎ ጥሎ በግርዱክ ቤተ መቅደስ በባቢሎን ከ2000 በግሪክ ደግሞ ከ500 ዓመት ከእሱ በፊት የነበራትን ሥልጣን መልሶ፡ ቅስና ሰጥቶ፡ ካህን ብሎ ሹሟት አልሄደም፡ አልሾማትም፤ በቤት ከባሏ ጋራ እኩል ቢየደርጋትም በቤተ መቅደስ እላስተካከላትም ለሚል ጠያቂ አሁንም እንደ ገና የጊዜውን ታሪካዊ አቅዋም ማየት ስለሚያሻ በክርስቶስ ዘመንና እካባቢ ሴት እንዴት እንደነበረች የሚገልጥ ዝርዝር እነሆ!

ፈሪሳዊም ሆነ ጽርእዊ ወይም አይሁዳዊ ማንኛውም ሰው ከሌላው ነገድ የኔ ነገድ ይሻላል፡ ከሌላው ሃይማኖትና ሥልጣን የኔው ይበልጣል የሚል ሁሉ ማለዳ ሲነሣ፡ ግታ ሲተኛ፡ ክበር ተመስገን ጌታዬ! ከኢአማኒ (ከአረማዊ) አማኒ፡ ከሐቃል ሥልጡን፡ ከሴት ወንድ፡ ከባሪያ ሐራ እድርገህ የፈጠርኸኝ እያለ ጌታውን ያመሰግን ነበር፤ ወንዶች እንጂ ሌቶች የአብርሃም ልጆች አይባሉም ነበር፤ እንደ ሥርዓቱ ረበናትም ሴት ከምትነካት አሪት በመላዋ ብትቃጠል ይሻላል፡ ሴት ምስክር አትሆንም፡ ልጆችን አታስተምርም፡ ከማዕድ ላይ አትጸልይም፡ ስለ እሷ አትነጋገርም፤ በምኩራብም በመጋረጃ የተወሰነ ቦታ ተሰጥቷት ቁማ ታዳምጣለች እንጂ እሷ የጸሎት መሪም ሆነ ተካፋይ አትሆንም፡ ማሕሌቱን አትመራም፡ ይህ እስካሁን በእንዳንድ አብያተ ክርስቲያናት ይታየል። የቅስና ሥራ ደግሞ ማስተማር፡ በሕዝብ ፊት ስለሕዝብ መጸለይ፡ ጸሎት ማጎበሩን መምራት፡ ምእመናኑን በእደባባይ በከፍተኛ ቃል መስበክ፡ ጩኸ ማስተማር ስለሆነ ከቤቷ ከማዕድ ላይ እንኳ ጸልያ ማዕድ እንዳትባርክ እንጀራ እንዳትቆርስ የተከለከለችውን ባንድ ጊዜ አውጥቶ ከዚያ ላይ ማድረስ በጊዜው ምክንያት ስላልተቻለ፡ ምንም ትምህርቱ አብዮት

ቢሆንም ከዚህ በፊት እንደተነገረው ክርስትና ታምራት እንጂ የጦር መሣሪያ ስለሌለው የማስተማሩ ዘዴ በመሻሻል፥ በትዕግሥት በመሆኑ ቅስና ቀርቶባታል፥ በሌላም አነጋገር መጀመሪያ የምታስተምረው ሃይማኖት፥ የሴት ጠበቃ የሆነ ትምህርት እንዳይባል ወንዶች ይዘውት ቆይተዋል፤ በኋላ ደግሞ ሲውል ሲያድር ጊዜ በትውፊት ምክንያት ወንዶች የጸታቸው አድርገውት ቀርተዋል።

በቤተ ክርስቲያን አንድ ነገር እንደምንም ብሎ ሁለት ትውልድ ካለፈ ከእምነት ተቆጥሮ ይኖራል፤ ለዚህም መረጃ የሚሆን በሀገራችን ያሉት ግዝረት፥ ቅዳሜን ማክበር፥ ከእንስሳት ርኩሳንና ቅዱሳን መለየትና መለሎቻቸው ናቸው፤ እነዚህ ከነመለሎቻቸው የክርስትና ሕግ እንዳልሆኑ እያወቅን፥ ሰው ምን ይለናል ለማለት ይዝናቸው እንኖራለን[2]።

ከዚህ በላይ ለሁሉም አንባቢ እንደገና በአንቀጽ 54 በንኡሳን ቁጥሮች 3 ና 4 የተሰጡትን ጥቅሶች እንዲመለከት አሳስበን፥ ክርስቶስ ስለሴቶች ስላስተማረው እስከዚህ ይብቃንና ተከታዮቹ ሐዋርያት ደግሞ ያስተማሩተን እንይ።

56. ስለ ሴት መብት የሐዋርያት ትምህርት፥

ሐዋርያት መሪያቸው ክርስቶስን ተከትለው፥ የሴትን መብት ጠብቀው፥ እጎታችን የአብርሃም ልጆች፥ በመንግሥተ ሰማያት መውረስ እኩል ተካፋያችን እያሉ ከወንድ እኩል አድርገው አሙልተው፥ አስፍተው፥ ሰብከዋል፥ አስተምረዋል።

ቅዱስ ጴጥሮስ በበዓለ ጰራቅሊጦስ መንፈስ ቅዱስ የወረደላቸው ሰት ሁኔታቸውን ለማየት ለተሰበሰቡት አሕዛብ በመንፈስ ጎይል ኢዮኤልን ጠቅሶ ባደረገው ስብከት የሴትን ከወንድ እኩልነት በሰፊው ገልጧል።

1. <u>በመጨረሻው ቀን እንዲህ ይሆናል ይላል እግዚአብሔር፤ በሥጋ ሁሉ ላይ ከመንፈሴ አፈሳለሁ። ወንዶችና ሴቶች ልጆቻችሁም ትንቢት ይናገራሉ፥ ጎበዛዝቶቻችሁም ራእይ ያያሉ፥ ሽማግሌዎቻችሁም ሕልም ያያሉ፥ ደግሞም በዚያ ወራት በወንዶችና በሴቶች ባሪያዎቼ ላይ ከመንፈሴ አፈሳለሁ፥ ትንቢትም ይናገራሉ። (ግብ. ሥ. 2:17)</u>

በዚህና ከዚህ በፊት ባየነው በትንሣኤው ጊዜ በተናገረው መሠረት ሴቶች ሊያስተምሩም ሊሰብኩም ታዝዘዋል፤ ትንቢት ለመናገርም ፈቃዱና ሥልጣኑ ተሰጥቷቸዋል።

ቅዱስ ጳውሎስም ሴት ከወንድ እኩል ናት ብሎ፥ እያለ በቃል ሲያስተምር መኖሩን በሚከተሉት መልእክታት እረጋግጠ ጽፏል።

2. በክርስቶስ የተጠመቃችሁ እናንተስ ክርስቶስን ለብሳችኋል፤ በእሱ ዘንድ አይሁዳዊ፥ አረማዊ (ግሪክ)፥ ባሪያ፥ ሐራ፥ ወንድ፥ ሴት የለም። ሁላችሁም በኢየሱስ ክርስቶስ አንድ ናችሁ እንጂ። (ገላ. 3:26-28)።

3. ስለጻፋችሁልኝስ ለሰው ከሴት ባይቀርብ ይሻለዋል፤ ግን እንዳታመነዝሩ ማንኛውም ወንድ ምሽት ይኑረው፤ ማንኛዋም ሴት ባል ይኑራት። ለሴት ባሏ የሚገባትን ያድርግላት፥ እንደዚሁም ሴት ለባሏ፥ ሴት (ምሽት) በራስዋ (በገዛ ገላዋ) ሥልጣን የላትም ወንድዩው እንጂ፥ እንደዚሁም ወንዱ በራሱ ሰውነት (አካል) ሥልጣን የለውም፤ ሴትዩዋ (ምሽትዩዋ) እንጂ (1ቆሮ. 7:1-4)።

ይህ ጥቅስ ባልና ምሽት አንድ ሥጋ፥ አንድ አካል ናቸው ያለውን የጌታን ትምህርት ያጸድቃል። በሴቲቱ አካል ወንዱን፥ ባልዩውን፥ በወንዱ በባልዩው አካል ደግሞ ሴቲቱን ምሽትዩዋን አሠልጥኗል፤ ይህም ከሴትና ከወንድ መካከል የሚያንስም ሆነ የሚበልጥ እንደሌለ ያስረዳል። ዳግመኛም፥

4. ያገቡትን ግን በራሴ ሳይሆን በእግዚአብሔር ትእዛዝ እዝዛቸዋለሁ፥ ሴት ከባሏ አትፋታ፥ ብትፋታ ግን ሳታገባ ትኑር ወይንም ከባሏ ትታረቅ፤ ባልም ምሽቱን አይፍታ። (1ቆሮ. 7:10-11)።

በጠቅላላ የሴትን አቋም በጳውሎስ ዘንድ ለማወቅ የተጠቀሰውን ምዕራፍ በሙሉ ማንበብ ያሻል። እንግዲያ እንዲህ ከሆነ ጳውሎስም ጴጥሮስም ሴቶች ለባሎቻቸው ተገዙ እያሉ ሰምን አስተማሩ፥ ጻፉ ለሚል ጠያቂ ለእንባቢ እንዲመቸው ጥቅሶቹን ከጻፍነ በኋላ ምክንያቱን ከነትርጓሜው እናስከትላለን።

5. ክርስቶስን በመፍራት እርስ በርሳቸው እየተጋገዛችሁ ኑሩ፥ (እየታዘዛችሁ ሁኑ) ሴቶች ሆይ! ለጌታ እንደምትታዘዙ ለባሎቻችሁ ታዘዙ፤ ክርስቶስ የቤተ ክርስቲያን አለቃና የአካሏ አዳኝ እንደሆነ የምሽትም አለቃዋ ባሏ ነውና። ቤተ ክርስቲያን ለክርስቶስ እንደምትገዛ ምሽቶች ሰባሎቻቸው በሁሉም ይታዘዙ። እንደዚሁም ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያንን እንደወደዳትና ራሱንም አሳልፎ እንደ ሰጠላት ወንዶችም ምሽቶቻቸውን ያፍቅሩ። በቃሉና በውኃ ጥምቀት ቀድሶና አንጽቶ እድፍንና ርስሐትን

ከሷ አጥፍቶ እርሷም ንጽሕት ቅድስት ሁና ለእሱ የተገባች ያደርጋት ዘንድ ራሱን አሳልፎ እንደሰጠላት፥ ወንዶችም ምሽቶቻቸውን ይውደዱ። እንዲሁም ወንዶች ምሽቶቻቸውን እንደራሳቸው ይውደዱ። ምሽቱን የወደደ ራሱን ወደደ። የራሱን ሥጋ ሊጠላ የሚችል ከቶ ግንም የለም። ይመግባታል፥ ይንከባከባታል እንጂ፥ ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያንን እንደሚንከባከብ። የሱ አካል አባሎች ነንና። ስለዚህ ሰው አባቱንና እናቱን ትቶ ከምሽቱ ጋራ ይጣበቃል፤ ሁለቱም አንድ ሥጋ ይሆናሉ። ይህ ምስጢር ትልቅ ነው፥ እኔ ግን በክርስቶስና በቤተ ክርስቲያን እመለከዋለሁ። ግን ከእናንተ እያንዳንዱ ምሽቱን እንደራሱ ይውደዳት፥ ሴትም ባሏን ትፍራ። (ኤፌ. 5:21-33)

6. ሴቶችም ለእግዚአብሔር እንደምትታዘዙ ለባሎቻችሁ ታዘዙ፤ ወንዶችም ምሽቶቻችሁን ውደዱ፥ አትንቀፏቸው። (ቆላ. 3:18-19)

7. ሴቶች ግን በቤተ ክርስቲያን (በጉባኤ) እንዲታዘዙ እንጂ እንዲናገሩ አልታዘዘምና ዝም ይበሉ። ኦሪት እንዲህ ብሏልና። ሊማሩ ቢፈልጉ ግን ከቤታቸው ባሎቻቸውን ይጠይቁ። በጉባኤ (በቤተ ክርስቲያን) መናገር ለሴት ውርደት ነውና። (1ቆሮ. 14:34-35)።

8. እንዲሁም ሴቶች በዐይነ አፋራምነት በልባይነት ራሳቸውን ከዝሙት በማንጻት እግዚአብሔርን እንደሚፈሩ ሴቶች ይሸለሙ እንጂ፥ ጠጉራቸውን በመሠራት (ሹሪቤአቸውን በመጎንጎን) በወርቅ ወይም በዕንቁ ወይም ዋጋው እጅግ በከበረ ልብስ አይደለም። ሴት እየታዘዘች በጽሞና ትማር፥ ትኑር እንጂ ልታስተምር ወይም በወንዱ ላይ እንድትሠለጥን አልፈቀድም። ...(1ጢሞ. 2:9-12)።

ቅዱስ ጴጥሮስም በእየሀገሩ በእስጢፋኖስ ሞት ምክንያት ለተበተኑ ደቀ መዛሙርት የሚከተለውን ጽፏል።

9. እንደዚሁም ሴቶች ሆይ፣ በምሽቶቻችው ምግባር ምክንያት ያለ ሌላ ምክንያት የሚክዱ ሰዎች ቢኖሩ በማክበር የምትፈጽሙትን ንጹሕ ምግባራችሁን ዐይተው እንዲመለሱ ለባሎቻችሁ ታዘዙ። ለእናንተ የውጭ ጌጣጌጥ፥ ጠጉርን መሸረብና ወርቅን ግንጠልጠል ወይም ልብስን መጎናጸፍ አፍአዊ ሽልግት አይሁንላችሁ፥ በእግዚአብሔር ፊት ዋጋው እጅግ የከበረ የዋህና የጽሞና መንፈስ ያለውን የማይጠፋውን ልብስ የለበሰ የተሰወረ

የልብ ሰው ይሁንላቸሁ እንጂ። እንዲሁ በቀድሞ ዘመን እግዚአብሔርን ተስፋ ያደረጉት ቅዱሳት ሴቶች ባሎቻቸውን በመታዘዝ ተሸልመዋልና። እናንተም ወንዶች ከምሽቶቻችሁ ጋራ ስትኖሩ ምሽቶቻችሁን አታስተሐቅሩ። ተፈጥሮአቸው ይደክማልና፥ ምሽቶቻችሁን አክብሩ፥ እነሱም ከእናንተ ጋራ ከብርና ሕይወትን ይወርሳሉና። (1ጴጥ. 3:1-7)።

ክርስቶስ ሴትና ወንድ እኩል ናቸው ሲል፥ ደቀ መዛሙርቱ ግን ይህን የመሳሰሰ ጽፈዋልI ይልቁንም ቅዱስ ጳውሎስ ራሱ በክርስቶስ ዘንድ አይሁዳዊ፥ አረማዊ፥ ሐራ፥ ባሪያ፥ ሴት ወንድ የሰም ካለ በኋላ መልሶ ለባሎቻችሁ ታዘዙ ብሏል፥ ይህ ነገር አይጠላምወይ? ቢሉ አይጠላም። ምክንያቱስ ? ምክንያቱግ!

ትምህርት በጀመሩበት ገዜ በሐዲስ አማኝነት ሴትና ወንድ እኩል ናቸው እያሉ አሰተምረዋል፥ በኋላ ግን ሴትን ግዙ ከብቱ፥ ፃማ ንብረቱ ናት ብሎ የሚያምነው የወንድ ዓለም ተነሣባቸውI በዚህም የተነሣ ስደት በዛI የሴት መብት ለክርስተና መስፋፋት ዕንቅፋት ሆነ። ብዙ ሰባክያን ታሰሩI በሚቀጥለው በሰፊው እንደምናየው ከሐዋርያትም በዚሁ ምክንያት ብዙዎቹ በመገረፍ፥ በመታሰር ተሰቃዩ፥ ተሰቅለው፥ ተሰይፈው፥ ተሰቃይተው ሰማዕትነት ተቀበሉ።[3]

ጴጥሮስንና ጳውሎስን የመሳሰሉት እየተገረፉ ከሀገር ወደ ሀገር ተሰደዱ፥ ታሰሩ። ከዚህ በኋላ እምነታቸውን ሳይሆን የስብከት ዘዴአቸውን ለወጡI የትምህርታቸውን አሰጣጥና አቀራረብ ቀየሩ ፥ ሰልታቸውን አሻሻሉ። በእየሀገሩ አይሁድም ሆኑ አሕዛብ ትምህርታቸውን እስኪቀበሏቸው ድረስ የአረማውያን ባህል እንኳ የተቀበሉ መሰለው አስተማሩ።

10. እኔስ ወንድሞቼ ሆይ! በክርስቶስ ሃይማኖት እንደ ሥጋውያን እንደ ሕፃናት እንጂ እንደ መንፈሳውያን ልነግራችሁ አልቻልሁም። ገና አልጠናችሁምና ወተት ጋትጓችሁ እንጂ ጥኑ ምግብ አልሰጠጓችሁም። አሁንም አልቻላችሁም፥ ሥጋውያን ናችሁና።

11. ከሁሉም ነጻ ሳለሁ ብዙዎቹን ለመጥቀም እንደባሪያ ሆኜ አገለገልሁ። አይሁድን ለመጥቀም ለአይሁድ አይሁዳዊ ሆንሁ (መሰልሁ)። ከአሪት በታች ያሉትን ለመጥቀም ከአሪት በታች ሳልሆን ከአሪተ በታች ያለሁ መሰልሁ። ሕግ አልባዎችን ለመጥቀም በክርስቶስ ሕግ ሳለሁ፥ የእግዚአብሔርን ሕግ ሳልረሳ፥ ሕግ ለሌላቸው ሕግ አልባ ሞሰልሁ። አመምተኞችን ለማዳን

ለሕመምተኞች ሕመምተኛ ሆንሁ። ደካሞችንም ለመዋቀም ደካማ ሆንሁ። ሁሉንም ሰማዳን ወደኔ ለመሰብሰብ የሁሉንም ባህልና ልማድ ተከተልሁ። የወንጌል ተካፋይ እንድሆን ሁሉንም ስለወንጌል አደርገዋለሁ። (1ቆሮ. 3:1-3፤ 9:19-23)።

12. እንደኔ ሁኑ፥ እኔ እንደናንተ ሁኛለሁና። (ገላ. 4:12)።

ጌታ ዓለምን ጽንፍ እስከ ጽንፍ ሂዳችሁ አስተምሩ ብሎ ያዘዛቸውን ትእዛዝ ተከትለው የሰብክት ስልታቸውን እያሻሻሉ ሲያስተምሩ ኑረው ሲሰደዱ ወይም ሲታሰሩ ሐዲሳን ምእመናን ብዙ ነገር እየተከራከሩ፥ እየተጣሉ፥ ስለዚህ ባስተማርኽን፥ ባስተማራቸሁን ነገር ተጣልተናልና እውነተኛውን ትምህርትህን ጻፍልን እያሉ መጠይቅ ይጽፍላቸው ጀመር፤ እነሱም እምነታቸውን ሳይለውጡ በዘዴ ይጽፉላቸዋል። ከዚህ በላይ የተጠቀሱት አብዛኞቹ የቅዱስ ጳውሎስ መልእክታት የተጻፉት ቅዱስ ጳውሎስ ታስሮ ሳለ ነው። የቅዱስ ጴጥሮስም እንዲሁ በስደተ ላይ ሳለ ነው[4]። (ኤፌ. 3:1፤ 13፤ 4:1፤ ፊል. 1:13፤ ቆላ. 4:18፤ 2ጢሞ. 2:9)።

በሴት መብት ምክንያት በደብዳቤ መጻጻፍ፥ መሰደብ፥ መገረፍ፥ መታሰር፥ መባረር፥ መሠቃየት፥ መሰየፍ ከመምጣቱ በፊት ያለ ምንም ችግር ሴቶች ከወንዶች እኩል ክርስቶስን ይከተሉም ያስተምሩም ነበር። (ማቴ. 28:7-11፤ ማር. 16:5-12፤ 1ቆሮ. 7:1፤ ፊል. 4:2-2 ሮሜ 16:1:3:7:12:13)።

ለ) እናቴ ሴት ናት ተብሎ በማይነገርበት በሴት በኩል ያለው ትውልድ በማይቆጠርበት፥ ወንዶች ብቻቸውን ሁነው ሲያወሩ እንኳ የሴትን ስም ሆነ ሙያ በማያነሱበት ዘመንና አካባቢ ሴት፥ ከወንድ እኩል ናት፥ ልታስተምር ትችላለች፥ ታስተምራለች፥ ታስተምር እያሉ ሲሰብኩ ጊዜ፥ ኧረ ሴት የምታስተምረው ሃይማኖት መጣብን! አሉና አሕዛብም አይሁድም ተናደዱ። ይልቁንም አይሁድ አርቆ ሰማጠር ሐዋሪያትን ሰምን ለማስተማር ስትሄዱ ሴት ታሰክትላላቸሁ እያሉ ይወቅሷቸው፤ ይከሷቸው፥ ያሸሟጥጧቸው ጀመር። ለማወናበድም የሮም መንግሥት በተዘረጋበት ሁሉ እየተዘዋወረ የሚያስተምረውን ቅዱስ ጳውሎስን ከሴት ጋራ ይውላል፥ ሴት ያስተምራል፥ እንድታስተምርም ያሠለጥናል እያሉ ያሳጡት፥ ይከሱት ጀመረ። ከኢየሩሳሌም እስከ ግሪክ ያለው የርቀትም ስደት ለውሸት ይመቻል እንደሚባለው የሐዋርያትን ኑሮ ለማያውቀው ሕዝብ ለማወናበጃ ተመቻቸው (ረዳቸው)። በዚህም ያስተማራቸው ምእመናን ታውከው ሲጽፉለት ጊዜ ሌሎች ሐዋርያትም፥ በሰብክት ባልንጀራቸውን፥

በክርስቶስ አጎታቸውን ያስከትላሉ፥ በግስተግርም ይረዳዳሉ እያለ ሴት የምትከተለውና የምትረዳው እሱ ብቻ አለመሆኑን ገልጸ ጽፏል።

13. <u>ለሚወቅሱኝ መልሴ ይህች ናት፥ ለመብላትና ለመጠጣት መብት የለንምን? እንደ ሌሎች ሐዋርያት እንደ ጌታ ወንድሞችና እንደ ኬፋ ሴት አጎታችንን ለግስከተል መብት የለንምን? ወይስ እኔና በርናባስ ብቻ መብት የለንምን? (1ቆሮ. 9:3-6)።</u>

ከኢየሩሳሌም ርቀው አሕዛብን በመጀመሪያ ጊዜ እየዞሩ ያስተማሩ ሁለታቸው ጳውሎስና በርናባስ ስለነበሩ፥ ሥራቸውን ለግስናከል ቢጽ ሐሳውያን ሴት ያስከትላል፥ ሐዋርያ አይደለም፥ አልተሾመም፥ ኢየሱስ ክርስቶስን አላየም እያሉ በጳውሎስ ላይ ያወሩበት ነበር። ይህንኑ ለመከላከል ብዙ መልእክት ጽፏል። በዚህም የነበረበትን ዘመንና አካባቢውን ሳያጠኑ፥ ከአሉበት አካባቢና ዘመን ሁነው የክርስቶስን ዘመን ሳያውቁ፥ የጳውሎስን አካባቢ ሳይመረምሩ በሐዋርያት የሚፈርዱ ብዙ ናቸው።[5]

ሐ) ሴቶችም ነጻ ከወጣነ፥ ከወንድ እኩል ከሆንነ፥ ብለው ባንድ ጊዜ የናረውን ሥርዓት ትተዋል፤ ለባሎቻችን አንታዘዝም፥ የግጀት ሥራ አንሠራም ሲሉ ጊዜ ባንድ ጊዜ የመጣ እንግዳ ለውጥ ሆነና፥ የቤተሰቡ ምግብና ልብስ ጎላፊ የባሮቹ የአሽከሮቹ መሪ፥ ትልቋ ባሪያ አልሠራም ስትል ጊዜ ኑሮው ተበላሸ፤ የቤቱ ሥርዓት ተደመሰሰ። ከየቤቱ የሚላስ የሚቀመስ ጠፋ። በክርስትና ምክንያት ባሥር ዓመታት ውስጥ ዓለሙ ከሥሉጥ ኑሮ ወደ ሐቃልነት ተለወጠ። ባንዳንድ ህገርና ዘመን ቂል ቂሉ ለው ለውጥ መጣ ሲሉት፥ ሳልሠራ የምኖርበት ዘመን መጣ ብሎ እንደሚያስብ፥ በዚያ ዘመንም ክርስትናን የተቀበሉ ብዙ ሴቶች ሥራ አንሠራም፥ ይልቁንም ባሌ አያዝዘኝም ሲሉ ጊዜ መግባባት ጠፋና ጋብቻን ሊያከብር፥ ሴትን ነጻ ሊያወጣ የመጣው ክርስትና ራሱም ጠፍቶ ጋብቻንም ሊያጠፋው ሆነ፥ ስለሆነ፥ ክርስትናን የተቀበለ ወንድ ሁሉ ተቸገረ፥ ያልተቀበለውም በዚህ ምክንያት ልቀበል አልቀበል እያለ ይዳዳ ጀመር።

በአሶርያ ሕግ ሳትከናነብ በመንገድ የማትታየው፥ በግሪክ ባህል ከግጀቷ የማትወጣው፥ በሮም ልግድ ሳትታጀብ ከግቢዋ የማትላወሰው ሴት ድሮ ነጻ ወጣችና የትም ትዞር ጀመር።

የንግግር ሥርዓትም ሳትግር ምላስ ካለኝ ብላ ሳይጠይቋት፥ ሳይፈቅዱላት፥ ሳታውቅ አገኝ ባጣውን ትለፈልፍ ገባች። ክንንቧን ጣለች፥ አጭር ለበሰች። ቤተ ክርስቲያኑ ቅጥ፥ ጉባኤው መልክ አጣ። ይህ ነው ከዚህ በፊት ያየናቸውን ጥቅሶች ሐዋርያትን እንዲጽፉ

ያስገደዷቸው። በዚህም የአደባባይ ሕግ አውጥተዋል፤ የቤተ ሰብአ ሥርዓት ሠርተዋል፥ አበጅተዋል። ሴቶች ባደባባይ መናገሩንና መኖሩን ለጊዜው ካላወቁበት በፊት ከቤት ይማሩ ብለዋል። (1ቆሮ. 11:2-16፤ 14:34-40፤ ኤፌ. 5:14-33፤ 1ጢሞ. 2:9-12፤ 1ጴጥ. 3:1:7)።

እሽ! ምክንያቱስ ይሁን ክርስትና የጦር መሣሪያ ስለሌለው አስተምሩ እንጂ አስገድዱ ስለማይል የክርስቶስ ሰባኪዎች አንዱ ዕቅዳቸው ሲበላሽ ሌላ አመጡ እንበል፥ መረጃውንም እንቀበል፥ ግን በዚሁ አንቀጽ እንኳ ስለሴት መብት የተጠቀሱት ጥቅሶች እርስ በርሳቸው አይጣሉም ወይ? ለሚል ጠያቂ፥ መልሱ አሁንም አይጣሉም ነው፤ ሴት ከወንድ እኩል ናት ብለው ነው ሁሉም ያስተምሩ የነበረ። አሁንም ጠያቂ እይለለችምና እንዴት ሁኖ ቢፈታና ቢተኙም ነዋ! ሴትና ወንድ አንድ እካል ናቸው ካለ በኋላ ሴቶች ሆይ! ለባሎቻችሁ ተገዙ ሲል የማይጣላው? ለሚል ጠያቂ ትርጓሜውን እናስከትላለን። እሱን ከመጀመራችን በፊት ግን አንባቢያን ሁሉ ባለፉት ሦስት ምዕራፎች የተጻፉትን ከነጥቅሶቻቸው በደንብ እንዲያነቧቸው እናሳስባለን።[6]

57. በአንቀጽ 56 የተጠቀሱት ትርጓሜያት

ከቁጥር 1-4 ያሉት ጥቅሶች በሴት መብት ምክንያት በሐዋርያት ላይ የደረሰው ችግር ከመምጣቱ በፊት የነበረውን የሴት አቋም በቀጥታ ስለሚገልጹ ትንተናና ትርጓሜ አያሻቸውም። ይህ የሚያሻቸው ለሙግት (ለክርክር)፥ ጆሮ ያለው ይስማ፥ ዐይን ያለው ይይ፥ ልብ ያለው ያስተውል ተበለው የተጻፉት የቀሩት ናቸው።

ቁጥር 5፥ ሴቶች ሆይ! ለጌታ እንደምትታዘዙ ለባሎቻችሁ ታዘዙ፤ ክርስቶስ የቤተ ክርስቲያን አለቃና የአካሏ አዳኝ እንደሆነ የምሽት አለቃዋ ባሏ ነውና። ቤተ ክርስቲያን ለክርስቶስ እንደምትገዛ ምሽቶች ለባሎቻቸው በሁሉም ይታዘዙ፥ እንደዚሁም ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያንን እንደወደዳትና ራሱንም አሳልፎ እንደሰጠላት ወንዶችም ምሽቶቻቸውን ያፍቅሩ፤ ....ወንዶችም ምሽቶቻቸውን ይውደዱ፥ እንዲሁም ወንዶች ምሽቶቻቸውን እንደራሳቸው ይውደዱ፥ ምሽቱን የወደደ ራሱን ወደደ፥ የራሱን ሥጋ ሊጠላ የሚችል ከቶ ግንም የለም፥ ይመግባታል፥ ይንከባከባታል እንጂ፥ ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያንን እንደሚንከባከብ፥ የእሱ እካል አባሎች ነንና፥ ስለዚህ ሰው አባትና እናቱን ትቶ ከምሽት ጋራ ይጣበቃል፥ ሁለቱም አንድ ሥጋ ይሆናሉ፥ ይህ ምስጢር ትልቅ ነው፥ እኔ ግን በክርስቶስና በቤተ ክርስቲያን

እመሰለዋለሁ፥ ግን ከእናንተ እያንዳንዱ ምሽቱን እንደራሱ ይውደዳት፥ ሴትም ባሏን ትፍራ ይላል። ከሰዶት በኋላ በእስር ቤት የተጻፉት የጳውሎስና የጴጥሮስ መልእክታት መንፈስ ይህ ነው። ታዲያ ይህ እንቀጽ ሴት እንደ ቀድሞው ዘመን ለባሏ በጭፍኑ፥ በድፍኑ ትገዛ፥ ትጨቆን ይላል ወይ? የለም፥ አይልም። ሴትንስ ይጨቁናል፤ ይጫናል ወይስ ይረዳል? በዚያን ጊዜም ሆነ ዛሬ ይህ እንቀጽ መላልሶ ላነበበው፥ ሴትን ይረዳል፥ ይደግፋል፤ የወንድን ሥልጣን ገፍ፥ የነበረውን ጌትነት ይቀማል። ሴቶች ለባሎቻቸው ይታዘዙ፤ ሴት ባሏን ታክብር ካለ በኋላ፥ ወንድን ግን መላልሶ ምሽቱን እንደራሱ ይውደዳት አባቱንና እናቱን ትቶ ምሽቱን ይከተል፥ እሷ መሪ፥ እሱ ተመሪ፥ እሷ አዛዥ እሱ ታዛዥ፥ እሷ የተገፋችውን ያህል የበላይ እሱ ደግሞ ብድሩን የበታች ይሁኑ ብሎ ሁኔታውን ሁሉ ለውጧል። ምሽቱን እንደራሱ ወድዶ፥ እንደ ሥጋው ይያት፥ ወርዶ፥ ነዶ፥ በርዶ፥ የቀን ሐሩር፥ የሌሊት ቁር፥ የበጋውን ሙቀት፥ የክረምቱን ቅዝቃዜ ታግሦ፥ ያብላት፥ ያጠጣት፥ ይመግባት ተብሏል። ሴት ባሏን ትፍራ፥ ትታዘዝ ነው የተባለችው፥ ወንድ ግን ክርስቶስ ለቤተ ክርስቲያኑ እንደሞተ ወንድም ለምሽቱ ይሙት ተብሎ በእንቀጽ አቀማመጥ በንግግሩ አካሄድ ታዝሏል። በግብርም በኩል ያየነው እንደሆነ ይህ እንቀጽ ዘለዓለም ሲፈጸም ይኖራል። ክርስቶስ ለቤተ ክርስቲያን ሙቷል፥ ከምእመናን ግን ለክርስቶስ የሚሞት፥ የሞቱት በጣም ጥቂት ናቸው። እንደዚሁም ሴት የላከው ጅብ አይፈረም እያሉ ለምሽቶቻቸው ወይም በምሽቶቻቸው የሚሞቱ ወንዶች ብዙ ናቸው፤ ስለባሏ የምትሞት ሴት ግን ብዙም አይደለች። 6ኛው ቁጥር ደግሞ ሴቶችም ለእግዚአብሔር እንደምትታዘዙ ለባሎቻችሁ ታዘዙ፥ ወንዶችም ምሽቶቻችሁን ውደዱ፥ አትንቀፏቸው ይላል። ይህም ልክ የፈተኛውን መንፈስ ሳይለቅ በመግባባት እንዲኖሩ ያዝዛል እንጂ፥ ወንድን የበላይ ሴትን የበታች አያደርግም፤ ሴት ለባሏ ትታዘዝ፥ ወንድም ምሽቱን እንደራሱ ይውደድ፥ አይንቀፉት ግለት ምን ግለት ነው? ከወደዳት፥ ካልነቀፉት እኩል ናቸው። እንዲያውም እንደነገሩ አካሄድ ከሆነስ ወንዱ ይውደዳት አይንቀፉት ሲባል፥ እሷ አትንቅፈው አትስደበው ስላልተባለች፥ አዲሲቱ ግልብጥ ሴት፥ ባሏን ልትነቅፍም ልትሰድብም ትችላለች ማለት ነው። ባልዩው ግን የመንቀፍም ሆነ የመስደብ ሥልጣን የለውም። 7 ና 8 ቁጥሮች ለጊዜው ክርስትና ያመጣው ለውጥ ለሰብከተ ወንጌል ዕንቅፋት ስለሆነ ለማቆያ ቅዱስ ጳውሎስ የጻፈው ነው። 9ቁጥርን እንደ5 እና 6 አሰግምቶ ይተረጉሟል።

58. <u>ስለሴት መብት የሞቱ ሐዋርያት</u>I

ሐዋርያት ሴትም ሰው ናት፥ ከወንድ እኩል ናት ብለው በግለተግራቸው መሰደድ፥ መታሰር፥ መገረፍ እንደደረሰባቸውና በዚህም የስብከት ስልታቸውን እንደሰወጡ አይተናል። አሁን ደግሞ ስደቱም ቀጥሎ፥ እነሱም በትምህርታቸው፥ በሴት መብት፥ ሥልጣን፥ እኩልነት ምክንያት ሰማዕት የሆኑትን የክርስቶስ ተከታዮች ሐዋርያት በገደለ ሐዋርያትና በስንክሳር መሠረት በቅደም ተከተል እናያለንI

ሀ) <u>ቅዱስ ጴጥሮስ</u>፥ ከብዙ ግለተግርና ስደት በኋላ ቅዱስ ጴጥሮስ ሮም ደርሷል። በዚያም ሴት ከዚህ በፊት በምዕራፍ 3 እንዳየነው ሴት ከሰውና ከአንሰሳት መካከል ባለችበት፥ ከነገንዘቧ ሰባሏ አንጡራ ንብረቱ፥ ግቡ ከብቱ በተባሰችበት፥ ከሆነችበት ሀገርና ዘመን ሴት ከወንድ እኩል ናት፥ አንድ ወንድ ላንድ ሴት፥ አንዲት ሴት ላንድ ወንድ ብሎ አስተካክሎ ሰብኳልI በመስበኩም፥ የሴትን መብት ልክ አንደ ክርስቶስ እንደ መምህሩ በግጋነኑ፥ ሴት ሁሉ የጎሊና ንቃት አግኝቶ ተነቃነቀ። ኧረ! ሴትም ሰው ናት የሚል አስተማሪ መጣ እያለ ሮማዊ ሁሉ ሕም! ሕም! ይል ገባ። ከዚህም የተነሣ የከንቲባው አራት ምሽቶች ትምህርቱን ሰሙና፥ ባላቸውን አክርጴስን ከእንግዲህ ወዲህ የወንድ መቀለጃ ሁነን በዕቁባትነት አንኖርምና የመረጥሃትን አስቀርተህ የቀረነውን ከብታችን ሰጥተህ ስደደን ብለው ወጥረው ያዙት። ምላሌአቸውንም ብዙ ሴቶች ተቀበሉ፥ ተከተሉት። መኳንንቱና መሳፍንቱ ሴትማ! ከወንድ እኩል ከሆነች ማን ሊያገለግለን ነው! ብለው ቅዱስ ጴጥሮስን ለመግደል አድማ አስነሥተው አሴሩ።

ጴጥሮስም ይህን ቢሰማ ከሮም በር ሲደርስ ጌታ ተገልጦ ታየው፥ ጴጥሮስም ደንግጦ ጌታ ሆይ! ወዴት ትሄዳለህ? አሰው፥ ጌታም ልሰቀል ወደ ሮም እገባለሁ ብሎት ተሰወረ። ጴጥሮስም ተመልሰህ ሰማዕት ሁን ማለቱ ነው ብሎ፥ ተመልሶ ገብቷልI የሮም መሳፍንትም ግንን እንፈልጋለን ብሰው በሴት ምክንያት የተጣሉትን ሃይማኖት አልብሰው ሰቀሉት ይላል ገድሰ ሐዋርያቱ።[7]

ስንክሳሩ ደግሞ፥

<u>ምክንያተ ሞቱ ሰጴጥሮስ - የጴጥሮስ የሞቱ ምክንያት</u>፥

14. <u>ወበእንተ ዝንተ ትእምርት አምኑ በዙኃን ሰብእ ወዕቁባቲሁ ሰአክርጴስ መልአክ ሀገር አምና በእደዊሁ ወዐቀባ ንጽሕና ወብዙኃት አንስት ተግሕሣ እምአምታቲሆን በወእንተዝ ነገር ተግከሩ ከመ ይቅትልዎ።</u> ስለዚህ ምልክት ብዙ ሰዎች አመኑI

የህገረ ገኾው የአክርዴስ ዕቁባትም በእጹ አመኑ፥ ንጽሕናም ጠበቁ፤ ብዙ ሴቶችም ከባሎቻቸው ተለዩ። ስለዚህ ነገር ሲገሉት ሞከሩ። (ስንክሳር ሐምሌ 5)

ለ) <u>ቅዱስ እንድርያስ ሐዋርያ</u>፥

የጴጥሮስ ወንድም ሐዋርያው እንድርያስም በሰማዕትነት የሞተበት ምክንያት መነሻው ያው የሴት መብት ነው።

15. <u>ወይቤሉ ለእመ ዝንቱ ነበረ ውስተ ህገርነ ያጠፍአነ በሥራዩ፥ እስመ ውእቱ ይፈልጥ አንስተ እምእምታቲሆን፥ ንዑ ንስድዶ እምህገርነ ከመ ኢይፍልጠነ እም-አንስቲያነ=ይህ ከኛ ጋራ ከቆየ በሥራዩ ያጠፋናል፥ ሴቶችን ከባሎቻቸው ይለያልና፥ ከሴቶቻችን እንዳይለየን ኑ ከህገራችን እናባረው አሉ። በዚህም ገለውታል።</u>[8]

ሐ) <u>ያዕቆብ የጌታችን ወንድም</u>፥

ያዕቆብም ወንድና ሴት አንድ አካል ናቸው ኖሚለውን የጌታን ትምህርት በሰፊው ሲያስተምር ኑሯል። በዚህም አይሁድ ሴት ያስተምራል ብለው እየተነሡ ሲያስቸግሩት ብዙ ዘመን ከቆዩ በኋላ በሕይወቱ መጨረሻ መካን የነበረችውን ያምንዮስን ምሽት ቴዎብስታን ጸልዮ ቢባርካት ወልዳለች፤ ይህን የሰማው ባሏ፥ ሕዝቡን ሰብኮ አሳድሞታል። ያደመው ሕዝብም እሆ! እያለ ካለበት ድረስ ሂዶ ገድሎታል።[9]

መ) <u>ቅዱስ በትረተሎሚዎስ</u>፥

ይህም ሰማዕት የሆነው የአግርጳስን ምሽት አስተምሮ አጥምቋታል። እሷም ተምራ፥ ተጠምቃ ስታበቃ ባሏን ትፈልግ እንደሆነ፥ አንተና እኔ በኩልነት እንኑር፥ በተቀረ ግን ይህን እንሰሳዊና አረማዊ ኑሮ አልፈልግም ብትለው፥ እንዲህ ያለውን ወንጀል ሴት ከወንድ እኩል ናት ብለህ ያስተማርሃት አንተ ነህ ብሎ ገሎታል።[10]

ሠ) <u>ሐዋርያው ፊሊጶስ</u>፥

የዚህም ከክርስቶስ ሌላ የሰማዕትነት ምክንያት የሴቶች መብት ነበር፤

16. <u>ወይቤሉ በበይናቲሆሙ ርእዩ እፎኑ ይሥሕቅ እንዘ ይሳለቅ ወይፈቅድ ያስሕተነ ወይሚጠነ ከመ ሕዝብ እሰ ረስዮሙ ይጎደጉ አግልክቲ ሆሙ ወፈለጠሙ እምእንቲያሆሙ።</u> እርስ በርሳቸው አግልክታቸውን እንዳስተዋቸውና ከምሽቶቻቸው እንደለያቸው ሕዝብ ሊያስተጉና ሊመልሰን ፈልጎ እንዴት እያፌዘብን እንደሚሥቅ ዕዩ ተባባሉ።[11]

ረ) ሐዋርያው ግትያስ፡

ደግስቆን የሰበከው ሐዋርያ ግትያስም ሰግዕት የሆነው በሴት መብትና በሃይማኖት ነው። ትምህርተ ሥሉስ ቅዱስን ካስረዳ በኋላ የሴትን መብት በሰፊው ሰብኳል፡ ሴቶችም ሰምተው ነቅተው ተከትለውታል። ይህም የሞቱ ምክንያት ሁኗል።

17. <u>ወቀዳሚ ዘእኤዝዘክሙ ቦቱ ከመ ትርሐቁ እምኩሉ ርስሐት ወኢታበዝኁ ተደምሮ ምስለ አንስት ከመ ይርአይ እግዚአብሔር ጎበ ንጽሕክሙ ወይባርከ ላዕሌክሙ በበረከት መንፈሳዊት ወበረከት ሰግያዊት ወይምሐርክሙ በዕለተ ኩነኔ ወሶበ ሰምዑ ሰብእ ሀገር በምክንያተ ምግባሩ ወይቤሉ በበይናቲሆሙ እምኔሁ ዘንተ ቦእ ሰይጣን ውሰተ አልባቢሆሙ እግን እሰመ ዝንቱ ብእሲ አሐዱ እም 10 ወ 2 እደው መሠርያን እለ ያንሰስው ጢስተ ኩሉ በሐውርት ወይፈልጡ አንስተ እምአምታቲሆን፡ ርእዩ ዘከመ ትፈስይዎ=ከሁሉ አስቀድሚ እግዚአብሔር ንጽሕናችሁን ዐይቶ በመንፈሳዊትና በሰግያዊት በረከት እንዲባርካችሁና በኩነኔ ቀን እንዲምራችሁ ከሴቶች ጋራ መገናኘት እንዳታበዙና ከርስሐት ሁሉ እንድትርቁ አዝዛችኋለሁ። የሀገሩ ሰዎች ይህን በለሙ ጊዜ፡ ግብረ ክፉው ሰይጣን በልቡናቸው ገባ። እርስ በርሳቸውም በርግጥ ይህ ሰው፡ ሀገር ሰሀገር እየዞሩ በሥራያቸው ሴቶችን ከባሎቻቸው ከሚለዩት ከ12 ሐዋሪያት አንዱ ነው። ስለሆነ ምን እንደምታደርጉት አስተውሉ፡ ምከሩ፡ ተባባሉ። በዚህ ምክር መሠረትም፡ ሴትም ሰው ናት፡ ከወንድ እኩል ናት ካለ ይሙት በቃ ብሰው ፈርደው ገድለውታል።</u>[12]

ሰ) ሐዋርያው ቶማስ፡

ቅዱስ ቶማስም ብዙ ሥቃይ ዐይቶ፡ ቆዳውን ተገፎ የሰግዕትነቱን ክብር ያገኘው ሴትም ከተግረች እንደ ወንድ ልታስብ ትችላለች፡ በሃይማኖትም የፈለገችውን ልትከተል ትችላለች ብሎ ስላስተግረና ስላሠለጠነ ነው።[13]

በዚህ አንቀጽ ከ1-7 የተዘረዘሩት ከ12 ሐዋርያት ሰባቱ የተገደሉት ስለሴት መብት ነው።

59. ፍች በሐዲስ ኪዳን፡

በዚሁ ምዕራፍ በአንቀጽ 53 እንዳየነው በሐዲስ ኪዳን ሴት ከተፈጥሮዋ በቀር በሕግ ከወንድ እኩል ናት። ከክህነት በቀረ ወንድ የሚሠራውን ሁሉ በሕግም በግብርም አግኝታለች። ታስተምራለች፡

ትንቢት ትናገራለች፥ ባደባባይ ሳትከናነብ ትዞራለች፥ የመረጠችውን ነቢይ ትከተላለች፥ የወደደችውን መምህር ትምህርት ትሰማለች፥ መርጣ ታገባለች። ካልተስማማችም በእኩልነት እንዳገባች በባለእኩልነት መብቷ ተጠቅማ ሀብቷን እኩል ተካፍላ ትፋታለች። ባሏ በሰም አለቃዋ በግብር ባሪያዋና አገልጋይዋ ነው። ለግብር ይውጣ ያህል ምሽት ትታዘዝ ተብላለች፥ ባል ግን ምሽቱን እንደራሱ ይውደድ፥ ይመግባት፥ ይቀልባት፥ ከዚያም አልፎ ተርፎ ይሙትላት፥ ራሱን አላልፎ ይሰጣላት ተብሏል። ስለዚህ እንደ ባቢሎን፥ ፋርስ፥ ነነዌ፥ ቤተ እስራኤል ወንድ እንደፈቀደ ለምስክር በፈጠራ ቁራጭ ወረቀት ሰጥቶ ማሰናበቱ ቀረ፤ ሞተ፤ ተከቱተ፤ ስለዚህ ስትፈልግ ትኖራለች፥ ካልፈለገች ግን የጋራ ገንዘቧን ተካፍላ፥ ያመጣችውን ትሎት እንዳለ፥ ተላልታ፥ ተቀብላ፥ ትፋታ ጀመረ። (1ቆሮ. 7:10)[11]

60. <u>ለመስተጋድላን እደው የተደረገው ጸጋ እግዚአብሔር ሁሉ ለቅዱሳት አንስትም ተደርጓል፥ ተፈጽሟል፤</u>

ጌታ ለሐዋርያት ድውይ ፈውሱ፥ ሙት አንሡ፥ ዕውር አብሩ፥ አጋንንትን አውጡ፥ ብሎ በሰጠው ሥልጣን መሠረት፥ ወንዶች ሐዋርያት ሲሠሩበት ኑረዋል። ርቱዓተ ሃይማኖት (ሃይማኖተ ቀናዎች) የሆኑ ሴቶችም ልክ እንደ ሐዋርያት ድውይ እየፈወሱ፥ ሰምጽ እያነጹ፥ ሙት እያስነሡ፥ ገቢረ ታምራት እያሳዩ ሲያስተምሩ ኑረው፥ ስማዕት እየሆኑ ወይንም ተጋድሎአቸውን በሰላም እየፈጸሙ፥ በቅድስና ዐርፈዋል። በዚህ ዐይነት በሃይማኖታቸው ሲጋደሉ ኑረው በአሸናፊነት የሞቱትን ቅዱሳት አንስት ጽፌ እጨርሳለሁ ብሎ መነሣት ጊዜ መፍጀት፥ ወረቀት መጨረስ ስለሆነ ስማስረጃ ያህል ጥቂት መጽሐፍት ጠቅሰን እናልፋለን። (ማቴ. 10፤ 1፤ ሉቃ. 9:1-2፤ ግብ. 5:15 ሮሜ 16:1:3:6፤ 1ቆሮ. 9:3-7፤ ስንክሳር መስከረም 17፤ 28፤ ጎዳር 18፤ ታኅሣሥ 5፤ 10፤ 21፤ ጥር 20፤ 24፤ 26፤ የካቲት 8፤ መጋቢት 5፤ 12፤ 26፤ ሚያዝያ 25፤ ግንቦት 11፤ 28፤ ሠኔ 12፤ ሐምሌ 1፤ 17፤ 23፤ 25፤ ነሐሴ 2፤ 6፤ 15፤ 21)።

ከዚህ በላይ በተጠቀሱት የጳውሎስ መልእክታትና ስንክሳር ሴት በገቢረ ተአምርም ሆነ በተጋድሎ የወንድ እኩያ እንደሆነች ተደጋግሞ በሰፊው ተጽፏል። ለክርስትና ትምህርት ሥቃይዋን ተቀብላለች፤ ድርሻዋን አበርክታለች። እሷም ቀድሞ ከወንድ ግኗን አምና ተናጋሪ እንሰሳ መሆኗን ተቀብላ የኖረችው፥ ክርስቶስ ለው ነሽ ሲላት ጊዜ ታጥቃ ተነሥታ ምንነቷን አስመስክረች።

61. <u>ለመብታቸው የታገሉ ሴቶች</u>I

ለብዙ ሽህ ዘመን ጠፍቶ የኖረው የሴት መብት ክርስቶስ ስላወጀው፥ ሐዋርያት ስለሰበኩት ባንድ ጊዜ አልተቋቋመም፥ በወር ወይም በዓመት ተቃንቶ ከወንድ እኩል አልሆነም። እስኪቃና፥ እስኪሳካ ዘመናት ወስዷል። ብዙ ሰዎች በትግል ስለሴት አቋም ሕይወታቸውን አሳልፈዋልI ደማቸውን አፍስሰዋል። ከሐዋርያት ሰባቱ በዚህ ምክንያት እንደሞቱ በአንቀጽ 58 ተናግረናልI ዐይተናልI እንዳየነው፥ እንደተረዳነ፥ አሁን ደግሞ ስለራሳቸው መብት የሞቱትን ቅድሳት እንስት እንቆጥራለን።

ሀ) <u>ቅደስት ቴክላ</u>፥

ከሐዋሪያት በምን አንሣለሁ ብላ መጀመሪያም የቅዱስ ጴጥሮስ ረድ ሁና እየተከተለች ስትረዳው ኑራ፥ በኋላም ከሱ ተለይታ ራስዋን ችላ ስትሰብክ፥ በአረማውያን ተይዛ የሰማዕትነት መከራ ተቀበላ ልክ እንደ ነቢዩ ዳንኤል ከአናብስት ጉድጓድ ተጥላ አናብስቱ ሳይነኳት ሁለት ቀናትና ሌሊት ቆይታ በደኅና ወጥታ በሐዋርያዊትነት ብዙ ሕዝብ አስተምራ አሳምና በአንጾኪያ አካባቢ በሰላም ዐርፋለች። (ስንክሳር፥ ሐምሌ፥ 25)

ለ) <u>ቅድስት አንስጣስያ</u>፥

ይህች ሰው ከቁስጥንጥንያ መሳፍንት ያንዱ ልጅ ናት። ለዐቅመ ሔዋን ስትደርስ በዘመኗ የነበረው ንጉሥ ብስጥያሄስ ምሽት እያልች ሁለተኛ ምሽቱ አድርጌ ላግባሽ ቢላት የሴትን መብት አዋርጂ ሁለተኛ ተደራቢ ምሽት ሁኜ ከምኖር ምነና ይሻለኛል ብላ፥ ከቁስጥንጥንያ ጠፍታ ወደ ግብጽ ሄዳ ከአስቂጥስ ገዳም ደርሳለች። ከዚያም በአበምኔት በአባ ዳንኤል ፈቃድ ከአንድ በአት ገብታ 28 ዓመት ሙሉ ዘግታ ኑራ፥ በቅታ፥ ዕለተ ሞቷ ሲደርስ፥ መነኮሳቱን ተሰናበታ፥ በሰላም ያለ ደዌ ዐርፋለች። (ስንክሳር ጥር 7)።

ሐ) <u>ቅድስት አውዳክስያ</u>፥

ይህች ቅድስት ሴት በእስክንድርያ ከሚገኙ ሀብታም ነጋዴዎች ተወልዳ፥ ወንዶች ልጆች የሚማሩትንም ከሴትነት ባልትና ጋራ እየተማረች አድጋለች። ቤትመህርት ከወንዶች ጋራ እኩል ስለነበረች የእናቷን ሙያ ትታ የአባቷን ተግባር ለመያዝ ወሰነች። በውሳኔዋም መሠረት ሴትና ወንድ አንድ አካል ናቸው የሚለውን ክርስቶስን ተከተላ እንደወንድ ለማስተማር ቆረጠች። እምነቷንም ለጸታ ጓደኞች በሰፊው አስተማረች። ብዙ ሴቶችም አርኣያዋን ተከተሉ። በኋላ ግን አረማውያን ሴቶቻችንን አነቃችብን ብለው ቀንተው፥ በሌላ ጉድለት

ሳይሆን በሴትነቷ ብቻ ለምን? በራስሽ ወሳኝነት ተጠቀምሽ? መነኮስሽ? ገዳም ገብተሽ በብሕትውና ትኖሪያለሽ? ብለው በጣም እሠቃይተው፥ ብዙ መከራ ካሳዩአት በኋላ ሰይፈው ገድለዋታል። (ስንክሳር መጋቢት 5)

ለአርአያ ያህል ጠቀስን እንጂ እነዚህን የመሳሰሉ ብዙ ተጋዳዮች ሴቶች ስንክሳር ይሠራል። በእንቀጽ 60 የተጠቀሱትን የስንክሳር ዕለታት ማንበብም ስለሴት እቋም የታገሉትን ሴቶች ታሪክ ዘርዝሮ ያሳያል።

62. ሴቶች የሚፈልጓቸውን ወንዶች ለጋብቻ ከመጠየቅ ደረጃ ደርሰዋል፤

ከዚህ በፊት እንዳየነው ክርስቶስ ሴትና ወንድ እኩል ናቸው ካለበት ጊዜ ጀምሮ ይህን የለማች ሴት ሁሉ ዳር እስከ ዳር ትነቃለች፥ ነቅታለች፥ የወንዶች ግዛት የነበረው በአደባባይ መሟገት፥ በቤተ ክርስቲያን መሰበክ፥ ሃይማኖት ማስተማርን የመሳሰለውን አውራጃ ሁሉ ለኛም ይገባናልና እያለች በእየፊናው ወጥራ ያዘች። አድኃሪው አረማዊ ወንድም ሥልጣኔን አልሰጥም፥ መብቴን አለቅም እንዳባቶቻችን እንችም በማጀት እኔም በአደባባይ፥ አንቺ እንደ እናትሽ ተመሪ፥ እኔም እንዳባቴ በአባዋራነት ቤቱን ልምራ፥ አንችን ላዝዝ እያለ ይሟገታል። ሴት ግን እሱን ተወው! ያለፈው ይበቃሃል፥ በሩን ክፈት፥ መንደጉን ልቀቅ እያለች ወጥታ፥ ማጀቱንም፥ አደባባዩንም አጣምራ ከያዘችው ዕድሜ ለሐዋርያት ትምህርትና ገቢረ ተአምር እንጂ ብዙ ቀን ሁኗል።

ሳታገባ ለመኖር የምትፈልገው እምቢ አላገባም፥ ወይንም ይህን ሰውዬ አልወደውም እያለች ወላጆችዋ ያመጡላትን ባል ግባት ከተወች ውሎ አድሯል፥ ጊዜው አልፏል። ሌላዋ ደግሞ ወላጆችዋን ሳትጠይቅ ገዳም ገብታ ማንንም ሳታማክር በራሷ ሐሳብ መንኩሳለች። ይህም በእየሀገሩ ከታወቀ ዋለ እደረ። ለውጡ እየገፋ ሄደ። በዚህ ጊዜ ልታገባ የምትፈልገዋ ደግሞ እስከ መቼ የወደደኝ ብቻ ሲያገባኝ ይኖራል? ከእንግዲህስ እኔ የወደደሁትን ግባት አለብኝ አለችና ወንድ እንደሚያደርገው እሷም እግባኝ ብላ ትጠይቅ ሽማግሌ ትልክ ጀመረች።[14](ታኅሣሥ 5፤ ጥር 27)።

ለሴት አቋም የተጠቀሱ መጻሕፍት፤

1. a) Flinders Petrie, Social Life In Ancient Egypt, (London: Constable and Company Ltd. 1923), pp. 27-28; 23-75;
   b) The Legacy of Egypt, Sec. Edition, Ed. J.R. Haris (Oxford, Clarendon Press, 1971), pp. 170-174.
   c) John Manchip White, Everyday Life in Ancient Egypt, (London: B.T. Bartford, Ltd. 1963), p. 116.

2. Theological Dictionary of the New Testament, (Vol. 1, Trans, and Ed. by Geoffrey W. Bromiley Michigan, Wm. B. Eerdmans Publishing Company, 1972), pp. 776-789.

3. ገድለ ሐዋርያት። Ethiopian Manuscript, Microfilm Project (No. 1482, Xerox, A.A. University Microfilms, 1974), pp. 12-15.

4. a) ግብ. ሐ. ከምዕራፍ 21፥ ቁጥር 27 እስከ ምዕራፍ 28 መጨረሻ ያይቀል፥ መሐሪ ትርፌ (ሊቀ ሊቃውንት፥ በኋላ ሊቀ ጳጳስት ዘጎንደር) የቅዱስ ጳውሎስ መጽሐፍ፥ አዲስ አበባ፥ ትንሣኤ ዘጉባኤ ግ/ቤት፥ 1948/ ገጽ 410.
   b) መጻሕፍተ ሐዲሳት ሦስቱ /አዲስ አበባ፥ አርቲስቲክ፥ 1951/ ገጽ. 197-202/።
   c) The Jerusalem Bible, Ed. by Alexander Jones, (London: Darton, Longman & Todd, 1966), pp. 251-266;
   d) Henry H. Hally, Hally's Bible Handbook, (Michigan: Zondervan Publishing House, 1965), pp. 613, 621, 635;

e) Dictionary of the Bible, Ed. by James Hasings, Edition XII, (Edinburgh: T. & T. Clark, 38 George Street, 1950), pp. 148, 232, 721;

f) The New Bible Dictionary, Ed. by J. D. Douglas, (London: (Inter Varsity Press, 1972), pp. 243, 381.

5. መሐሪ ትርፌ የጳውሎስ መጽሐፍት፡ / 1ቆሮ. 9:3-5።/

6. a) William Barclay, The Daily Study Bible, Letters to Corinthians, (Edinburgh: The Saint Andrew Press, 1975), pp. 151-152;

b) William Barclay, Letters to Galatians, Ephesians, (1965), pp. 198-202;

c) William Barclay, Letters to Philippians, Colossians and Thessalonians, (1974), pp. 191-197;

d) William Barclay, Letters to Timoth, Titus and Philemon (1975) pp. 74-79;

e) William Barclay, Letters of James and Peter, (1975), pp. 258-265.

7. ገድለ ሐዋርያት። Ethiopian Manuscript Microfilm Project; No. 1482, (Xerox, University Microfilms, 1974), pp. 12-15.

8. Ibid., p. 88.

9. Ibid., pp. 21-22.

10. Ibid., p. 45.

11. Ibid., p. 79

12. Ibid., p. 113.

13. Ibid., pp. 125-129.

14. መሐሪ ትርፌ፡ ሠለስቱ መጻሕፍተ ሐዲሳት /አዲስ አበባ፡ ትንሣኤ ዘጉባኤ ማ/ቤት 1951 ዓ.ም./ ገጽ. 236።

ምዕራፍ 30

ሴት በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን

63. ጠቅላላ አቅዋም።

የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ስለሴት አቋም የምትከተለው ከሙሉ በከፊሉ ክርስቶስ ያስተማረውን፥ ሐዋርያት የሰበኩትን በሐዋርያትና በሊቃውንት ሲኖዶስ የተሠራውን ድነጋጌ ነው። በዚህ በኩል ያለው ንጹሑ ይዞታዋ ልክ እንዳዲስ ኪዳን ሲሆን፥ ግን በሀገራችን ሕገ አሪት ስትገባ፥ ሥርዓተ ረበናትም አብሮ ገብቶ ስለነበር፥ አሪትንና ወንጌልን ያልለዩ ሁለቱ ሕግጋትና ሥርዓታት አብረው የሚሄዱ የሚመስላቸው፥ ሥርዓተ ረበናትን እየጠቀሱ ይልቁንም ባልቴቶች ሴትን ከወንድ ያምታንስ አስመስለው የሚያሳዩ አሉ። ይህ ግን ያላዋቂዎች አፈ ታሪክ እንጂ ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን አይደለም።

እውነት በቀር ሴት በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ከወንድ እኩል ናት። ያምትቆመውም በቀኝ ነው። ለብቻዋ ከቆመች ሴት ከወንድ ብታንስ ይሻል የሚሉ አሉ። ቦታ መለየት ቦታ መካፈልን እንጂ፥ መተናነስን ወይም መበላለጥን አያሳይም። እንደ ቀድሞው ኢትዮጵያዊ አስተሳሰብ ትልቁ በቀኝ ትንሹ በግራ ይቆማል፤ በዚሁ መሠረት በቤተ መንግሥትም ቀኛዝማች የቀኝ ክንፍ ኃላፊ በቀኝ፥ ግራዝማች (የግራ ክንፍ ኃላፊ) በግራ ይቆማሉ። ቀኛዘማች ይቀድማል፥ ግራዝማች ይከተላል። እንደዚሁም ከእመቤታችን ወዲህ ሴቶች ከወንድ ለሚበልጡ፥ ሴት በቀኝ ስተቆም ወንድ በግራ ይቆማል።

ሥረጃውም ይኸው መቆሚያቸው ነው። ይህም በሁለቱ መሪዎች በቀኝ በኩታና በግራ ጌታ ይታወቃል። ይህም የተደረገው ቤተ ክርስቲያን ቤተ ክህነት ስለሆነች ሁለቱም ከመተያየት የተነሣ በሐጸ ዝሙት ተነድፈው ቤተ ክርስቲያንን የዳንሰ መቃጠሪያ እንዳያደርጓት ታስቦ እንጂ ጸታ ስለማበላለጥ አይደለም።

ዳግቱም የሴትንና የወንድ ተብለው ተከፍለዋል። ከወንድ ገዳም ሴት ትገባም። እንዲሁም ከሴት ገዳም ወንድ አይገባም፤ ከ70 ወይንም እንደ ገዳሙ ሥርዓት 80 ዓመት በላይ ካልሆነ በቀር። ይኸውም ቀድሶ ቁርቦ ወደ ወንዱ ገዳም ለመመለስ ብቻ። ለዚህም ከትግራይ ደብረ ዳሞን፥ ከጎጃም ውራ ኢየሱስን፥ ጉታ፥ ባሕር ዳር መጥቀስ ይቻላል። በዚህ ሁለቱ ገዳማት የሴትና የወንድ የተለያዩ ገዳማት አሏቸው። ምሥራቅ ሲመጡ የሴቶች ገዳማት በቀኝ ናቸው። ለምን? ቢሉ ክርስቶስ ሲሰቀል ከምሥራቅ ወደ ምዕራብ ስለተሰቀለ የሴቶችን ገዳማት በቀኝ ለማድረግ፤ ሌሎች ደግሞ የለም ይህ የሆነው ሁለቱም ሴት ገዳማት ከወንዞች እጠገብ እንዲሆኑ ታስቦ ነው ይላሉ፤ በምርጫ

ምዕራፍ 30

ሴት በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን

63. ጠቅላላ አቅዋም።

የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ስለሴት አቋም የምትከተለው ከሙሉ በከፊሉ ክርስቶስ ያስተማረውን፥ ሐዋርያት የሰበኩትን በሐዋርያትና በሊቃውንት ሲኖዶስ የተሠራውን ድነጋጌ ነው። በዚህ በኩል ያለው ንጹሑ ይዞታዋ ልክ እንዳዲስ ኪዳን ሲሆን፥ ግን በሀገራችን ሕገ አሪት ስትገባ፥ ሥርዓተ ረበናትም አብሮ ገብቶ ስለነበር፥ አሪትንና ወንጌልን ያልለዩ ሁለቱ ሕግጋትና ሥርዓታት አብረው የሚሄዱ የሚመስላቸው፥ ሥርዓተ ረበናትን እየጠቀሱ ይልቁንም ባልቴቶች ሴትን ከወንድ የምታንስ አስመስለው የሚያሳዩ አሉ። ይህ ግን ያላዋቂዎች አፈ ታሪክ እንጂ ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን አይደለም።

ከክህነት በቀር ሴት በኢትዮጵያ ቤተ ክርሰቲያን ከወንድ እኩል ናት። የምትቆመውም በቀኝ ነው። ለብቻዋ ከቆመች ሴት ከወንድ ብታንስ ነው የሚሉ አሉ። ቦታ መለየት ቦታ መካፈልን እንጂ፥ መተናነስን ወይም መበላለጥን አያሳይም። እንደ ቀድሞው ኢትዮጵያዊ አስተሳሰብ ትልቁ በቀኝ ትንሹ በግራ ይቆማል፤ በዚሁ መሠረት በቤተ መንግሥትም ቀኛዝማች የቀኝ ክንፍ ኃላፊ በቀኝ፥ ግራዝማች (የግራ ክንፍ ኃላፊ) በግራ ይቆማሉ። ቀኛዘማች ይቀድማል፥ ግራዝማች ይከተላል። እንደዚሁም ከእመቤታችን ወዲህ ሴቶች ከወንድ ስለሚበልጡ፥ ሴት በቀኝ ስተቆም ወንድ በግራ ይቆማል።

መረጃውም ይኸው መቆሚያቸው ነው። ይህም በሁለቱ መሪዎች በቀኝ ጌታና በግራ ጌታ ይታወቃል። ይህም የተደረገው ቤተ ክርስቲያን ቤተ ጸሎት ስለሆነች ሁለቱም ከመተያየት የተነሣ በሐጸ ዝሙት ተነድፈው ቤተ ክርስቲያንን የዳንስ መቃጠሪያ እንዳያደርጓት ታስቦ እንጂ ጸታ ለማበላለጥ አይደለም።

ገዳማቱም የሴትንና የወንድ ተብለው ተከፍለዋል። ከወንድ ገዳም ሴት አትገባም። እንዲሁም ከሴት ገዳም ወንድ አይገባም፥ ከ70 ወይንም እንደ ገዳሙ ሥርዓት 80 ዓመት በላይ ካልሆነ በቀር። ይኸውም ቀድሶ አቁርቦ ወደ ወንዱ ገዳም ለመመለስ ብቻ። ለዚህም ከትግራይ ደብረ ዳሞን፥ ከጎጃም ውራ ኢያሱን፥ ጉታ፥ ባሕር ዳር መጥቀስ ይቻላል። እነዚህ ሁለቱ ገዳማት የሴትና የወንድ የተለያዩ ገዳማት አሏቸው። ከምሥራቅ ሲመጡ የሴቶች ገዳማት በቀኝ ናቸው። ለምን? ቢሉ ክርስቶስ ሲሰቀል ከምሥራቅ ወደ ምዕራብ ስለተሰቀለ የሴቶችን ገዳማት በቀኝ ለማድረግ፥ ሌሎች ደግሞ የለም ይህ የሆነው ሁለቱም የሴት ገዳማት ከወንዞች አጠገብ እንዲሆኑ ታስቦ ነው ይላሉ፥ በምርጫ

e) Dictionary of the Bible, Ed. by James Hasings, Edition XII, (Edinburgh: T. & T. Clark, 38 George Street, 1950), pp. 148, 232, 721;

f) The New Bible Dictionary, Ed. by J. D. Douglas, (London: (Inter Varsity Press, 1972), pp. 243, 381.

5. መሐሪ ትርሌ የጳውሎስ መጽሐፍት፡ / 1ቆሮ. 9:3-5ዉ/

6. a) William Barclay, The Daily Study Bible, Letters to Corinthians, (Edinburgh: The Saint Andrew Press, 1975), pp. 151-152;

b) William Barclay, Letters to Galatians, Ephesians, (1965), pp. 198-202;

c) William Barclay, Letters to Philippians, Colossians and Thessalonians, (1974), pp. 191-197;

d) William Barclay, Letters to Timoth, Titus and Philemon (1975) pp. 74-79;

e) William Barclay, Letters of James and Peter, (1975), pp. 258-265.

7. ገድለ ሐዋርያት። Ethiopian Manuscript Microfilm Project; No. 1482, (Xerox, University Microfilms, 1974), pp. 12-15.

8. Ibid., p. 88.

9. Ibid., pp. 21-22.

10. Ibid., p. 45.

11. Ibid., p. 79

12. Ibid., p. 113.

13. Ibid., pp. 125-129.

14. መሐሪ ትርሌ፡ ሠለስቱ መጻሕፍተ ሐዲሳት /አዲስ አበባ፡ ትንሣኤ ዘተባሌ ማ/ቤት 1951 ዓ.ም./ ገጽ. 236ዉ

ምዕራፍ 30

ሴት በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን

63. ጠቅላላ አቅዋም።

የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ስለሴት አቋም የምትከተለው ከሙሉ በከፊሉ ክርስቶስ ያስተማረውን፥ ሐዋርያት የሰበኩትን በሐዋርያትና በሊቃውንት ሲኖዶስ የተሠራውን ድንጋጌ ነው። በዚህ በኩል ያለው ንጹሑ ይዘታዋ ልክ እንዳዲስ ኪዳን ሲሆን፥ ግን በህገራችን ሕገ አሪት ስትገባ፥ ሥርዓተ ረበናትም አብሮ ገብቶ ስለነበር፥ አሪትንና ወንጌልን ያልለየ ሁለቱ ሕግጋትና ሥርዓታት አብረው የሚሄዱ የሚመስላቸው፥ ሥርዓተ ረበናትን አየጠቀሱ ይልቁንም ባልቴቶች ሴትን ከወንድ የምታንስ አስመስለው የሚያሳዩ አሉ። ይህ ግን ያላዋቂዎች አፈ ታሪክ እንጂ ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን አይደለም።

ከክህነት በቀር ሴት በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ከወንድ እኩል ናት። ያምትቆመውም በቀኝ ነው። ለብቻዋ ከቆመች ሴት ከወንድ ብታንስ ነው የሚሉ አሉ። ቦታ መለየት ቦታ መካፈልን እንጂ፥ መተናነስን ወይም መበላለጥን አያሳይም። እንደ ቀድሞው ኢትዮጵያዊ አስተሳሰብ ትልቁ በቀኝ ትንሹ በግራ ይቆማል፤ በዚሁ መሠረት በቤተ መንግሥትም ቀኖዝማች የቀኝ ክንፍ ኃላፊ በቀኝ፥ ግራዝማች (የግራ ክንፍ ኃላፊ) በግራ ይቆማሉ። ቀኖዘማች ይቀድማል፥ ግራዝማች ይከተላል። እንደዚሁም ከአመቤታችን ወዲህ ሴቶች ከወንድ ስለሚበልጡ፥ ሴት በቀኝ ስተቆም ወንድ በግራ ይቆማል።

ሥረዓቱም ይሽው መቆሚያቸው ነው። ይህም በሁለቱ መሪዎች በቀኝ ቆታና በግራ ጌታ ይታወቃል። ይህም የተደረገው ቤተ ክርስቲያን ቤተ ሴት ስለሆነች ሁለቱም ከመተያየት የተነሣ በሐጸ ዝሙት ተነድፈው ቤተ ክርስቲያንን የዳንስ መቃጠሪያ እንዳያደርጓት ታስቦ እንጂ ጸታ ስለበላለጥ አይደለም።

ሥግቱም የሴትንና የወንድ ተብለው ተከፍለዋል። ከወንድ ገዳም ሴት ትገባም። እንዲሁም ከሴት ገዳም ወንድ አይገባም፤ ከ70 ወይንም ከ80 ገዳሙ ሥርዓት 80 ዓመት በላይ ካልሆነ በቀር። ይሽውም ቀድሶ ከቊርቦ ወደ ወንዱ ገዳም ለመመለስ ብቻ። ለዚህም ከትግራይ ደብረ ዳሞን፥ ከጎጃም ውራ ኢየሱስን፥ ጉታ፥ ባሕር ዳር መጥቀስ ይቻላል። በዚህ ሁለቱ ገዳማት የሴትና የወንድ የተለያዩ ገዳማት አሏቸው። ሥራቅ ሲመጡ የሴቶች ገዳማት በቀኝ ናቸው። ለምን? ቢሉ ክርስቶስ ሲሰቀል ከምሥራቅ ወደ ምዕራብ ስለተሰቀለ የሴቶችን ገዳማት በቀኝ ለማድረግ፤ ሌሎች ደግሞ የለም ይህ የሆነው ሁለቱም ሴት ገዳማት ከወንዞች አጠገብ እንዲሆኑ ታስቦ ነው ይላሉ፤ በምርጫ

ምዕራፍ 30

ሴት በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን

63. ጠቅላላ አቅዋም።

የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ስለሴት አቋም የምትከተለው ከሙሉ በከፊሉ ክርስቶስ ያስተማረውን፥ ሐዋርያት የሰበኩትን በሐዋርያትና በሊቃውንት ሲኖዶስ የተሠራውን ድነጋጌ ነው። በዚህ በኩል ያለው ንጹሑ ይዞታዋ ልክ እንዳዲስ ኪዳን ሲሆን፥ ግን በሀገራችን ሕገ ኦሪት ስትገባ፥ ሥርዓተ ረበናትም አብሮ ገብቶ ስለነበር፥ ኦሪትንና ወንጌልን ያልለዩ ሁለቱ ሕግጋትና ሥርዓታት አብረው የሚሄዱ የሚመስላቸው፥ ሥርዓተ ረበናትን እየጠቀሱ ይልቁንም ባልቴቶች ሴትን ከወንድ የምታንስ አስመስለው የሚያሳዩ አሉ። ይህ ግን ያላዋቂዎች አፈ ታሪክ እንጂ ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን አይደለም።

ከክህነት በቀር ሴት በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ከወንድ እኩል ናት። የምትቆመውም በቀኝ ነው። ለብቻዋ ከቆመች ሴት ከወንድ ብታንስ ነው የሚሉ አሉ። ቦታ መለየት ቦታ መካፈልን እንጂ፥ መተናነስን ወይም መበላለጥን አያሳይም። እንደ ቀድሞው ኢትዮጵያዊ አስተሳሰብ ትልቁ በቀኝ ትንሹ በግራ ይቆማል፤ በዚሁ መሠረት በቤተ መንግሥትም ቀኛዝማች የቀኝ ክንፍ ኃላፊ በቀኝ፥ ግራዝማች (የግራ ክንፍ ኃላፊ) በግራ ይቆማሉ። ቀኛዘማች ይቀድማል፥ ግራዝማች ይከተላል። እንደዚሁም ከእመቤታችን ወዲህ ሴቶች ከወንድ ስለሚበልጡ፥ ሴት በቀኝ ስተቆም ወንድ በግራ ይቆማል።

መረጃውም ይኸው መቆሚያቸው ነው። ይህም በሁለቱ መሪዎች በቀኝ ጌታና በግራ ጌታ ይታወቃል። ይህም የተደረገው ቤተ ክርስቲያን ቤተ እሎት ስለሆነች ሁለቱም ከመተያየት የተነሣ በሐጸ ዝሙት ተነድፈው ቤተ ክርስቲያንን የዳንስ መቃጠሪያ እንዳያደርጓት ታስቦ እንጂ ጸታ ለማበላለጥ አይደለም።

ገዳማቱም የሴትንና የወንድ ተብለው ተከፍለዋል። ከወንድ ገዳም ሴት አትገባም። እንዲሁም ከሴት ገዳም ወንድ አይገባም፥ ከ70 ወይንም እንደ ገዳሙ ሥርዓት 80 ዓመት በላይ ካልሆነ በቀር። ይኸውም ቀድሶ አቁርቦ ወደ ወንዱ ገዳም ለመመለስ ብቻ። ለዚህም ከትግራይ ደብረ ዳሞን፥ ከጎጃም ውራ ኢየሱስን፥ ጉታ፥ ባሕር ዳር መጥቀስ ይቻላል። እነዚህ ሁለቱ ገዳማት የሴትና የወንድ የተለያዩ ገዳማት አሏቸው። ከምሥራቅ ሲመጡ የሴቶች ገዳማት በቀኝ ናቸው። ለምን? ቢሉ ክርስቶስ ሲሰቀል ከምሥራቅ ወደ ምዕራብ ስለተሰቀለ የሴቶችን ገዳማት በቀኝ ለማድረግ፥ ሌሎች ደግሞ የለም ይህ የሆነው ሁለቱም የሴት ገዳማት ከወንዞች አጠገብ እንዲሆኑ ታስቦ ነው ይላሉ፤ በምርጫ

ቢሆን ከሁለቱ ሐሳብ ማነን ትመርጣለህ? ብባል ሁለተኛውን እላለሁ። ለምን ቢሉ ከላይ ሴት የምትቆመው ከምዕራብ ሲገቡ በስተቀኝ ነው ብለናልኣ በምርጫ ግን አሁንም ከወራጁ ውኃ አጠገብ ያለው ቦታ ምንም ሐሳቡ ተግባራዊ ቢሆንም፥ ተመርጦ የተሰጠው ለሴት ስለሆነ፥ ቅድሚያውን ሴት ወስዳለች። ለሴት ምርጡ ተሰጥቷልኣ ለወንድ ግን ምራጩ ደርሷል።

በሰግያዊ ክብርም ከፈጣሪ በታች ከሌሎች ፍጡራን ሁሉ ከመላእክትም በላይ ያለውን የክብር ቦታ የያዘችው ቅድስት ማርያም ናት። በበዓላትም የጌታ በዓመት 9 ሲሆን ለእሷ ግን 33 በዓላት አላት። በሚጸለየው ጸሎትና ማሕሌትም ከጌታው የማርያም ይበልጣል።

ከእመቤታችን በታች ያለውን መንፈሳዊ ሰግያዊ ቦታ ቅዱሳንና ሰግዕታት እንደ ሥራቸው በጸጋ አድልዎ ሳይደረግባቸው ይወርሱታል። በመንፈሳዊ ዓለም ለሰው የመጨረሻው ሰግያዊ ክቡር ቦታ በሕይወቱ ባደረገው ተጋድሎና ከሞተ በኋላ በሚያሳየው ታምራት መሠረት በሰሙ ታቦት ሲቀረፅለት፥ ተቀርያለት ለዚህ ታላቅ ማዕረግ ሲደርስ ነው። ከዚህ በላይ ሰው የሚያውቀው መንፈሳዊ ሀብትና ክብር የለም። ከዚህ ማዕረግ የደረሱ ቅዱሳት እንስት በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን እጅግ ብዙ ናቸው። ከክርስትና ጋራ በዓለም አቀፍነት የመጡትን እነግርያምን፥ ሐናን ትተን ኢትዮጵያውያቱን እንኳ ብንቆጥር በኢትዮጵያ ታቦት ከተቀረፀላቸው ሴቶች ይበልጣሉኣ እናቴ ወለቱ፥ መስቀል ክብራ፥ ቅድስት አርሴማ፥ እግዚእ ኀረያ፥ ክርስቶስ ሠምራ ወዘተ..። ለሴቶችም ልክ እንደ ወንዶች ገድልና ታምር ተጽፎላቸው ይነበባል፥ መልክእ ተደርሶላቸው ይደገማል። በሐዲስ ኪዳን (እን. 60) እንዳየነው ወንዶች ሲሠሩት የነበረን ሁሉ በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ሴቶች ሲሠሩ ኑረዋልኣ ይሠራሉ። በጉባኤአቸው ስፋት በዕውቀታቸው ጥልቀት፥ በአእምሮአቸው ርቀት የታወቁ ብዙ መምህራት ሴቶች ነበሩ፥ አሁንም አሉ።

<u>በቅኔ</u>፥ ከእነዚህም በዘመናችን ከሦስቱ የቅኔ ቤቶች ጎንጅ፥ ዋድላ፥ ዋሸራ፥ እንዱን ጎንጅን እየመሩ ለአምሳ ዓመት ያህል የኖሩት ወይዘሮ ገላነሽ ሐዲስ ይገኛሉ።

ይህም በቅኔ ቤት የነበረ ሰው ሁሉ የሚያውቀው ታሪክ፥ ዛሬም ያለ ሐቅ ነው።

<u>በትንቢት</u>፥ በግብረ ሐዋርያትና (2፥ 17) በሐዋርያት ሲኖዶስ ትእዛዝ 40 እንደ ተነገረው ብዙ ሴቶች ጎላፍያትንና መጻእያትን ሲናገሩ ኑረዋል።

ዲያቆናዊት፡ በብዙ አድባራት፡ አብያተ ክርስቲያን ዐቃቢ (ዐቃቢት) በሚባል ስም ለመሥዋዕት የሚሆነውን ቅዱታ የሚያልሙ፡ ግዩን የሚቀዱ ሴቶች መነኩሳት ናቸው።

ከእመቤታችን ወዲህ ሴት በቤተ ክርስቲያን ከገነት አወጣሽን እየተባለች መከሰሷ፡ መወቀሷ፡ መነዝነዟ ቀርቷል፡ በሴት ከገነት ብትወጡ ከሴት ክርስቶስ ተዋልዶ አድኗችኋል፤ ያለኛ አይሆንላቸሁም፤ ብትወጡም፡ ብትወርዱም በእኛው ነው እያሉ ስለሚመልሱ ወቃሻቸው ዝም ይላል። እንዲያውም ይዋደዷል፡ ከግርያም፡ ይሰደዷል ከላም፡ ግርያምን ወዶ ይወዷቷል? ከግንድ የሚጋያጋጭ ልጅ አላት እንጂ እያለ ወደ ውዳሴ ማርያሙ ይመለሳል።[1]

64. የሴት መብት በቤተ ክርስቲያን ሕግ፡

ከምዕራፍ 4 አንቀጽን 54 ተራ ቁጥር 3:5፤ አንቀጽ 56 ተራ ቁጥር ከ1-9 ያሉት ጥቅሶች ከዚህም ይጠቀሳሉ። እንደ ጠቃሹ ስሜት የሴትን እኩልነት፡ የበላይነት፡ የበታችነት፡ ዝቅተኛነት፡ ደካማነት ለማሳየት አርእስቱን ከነጎዳጉ አገናዝቦ አስተውሎ ሳይሆን በጥራዝ ነጠቅነት ዐረፍተ ነገሩን ለእየብቻው እየጠቀሱ ስሜታቸውን ለመግለጥ የሚፈልጉ ብዙ ሰዎች አሉ።

ከዚህ በላይ በቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት ዐይን ነገሩን ለማብራራት ከዚህ በፊት ያየነውን ጥቅስ እንደግማለን፤ በመጀመሪያም የሚጠቀሰው ዝነኛው የኦሪት ቁጥር አዳምም ይህች አጥንት ካጥንቴ ሥጋም ከሥጋዬ ናት፡ እሷም ከወንድ ተገኝታለችና ሴት ትባል አለ። ስለዚህም ሰው አባትና እናቱን ትቶ ከምሽቱ ጋራ ይጣበቃል። ሁለቱም አንድ ሥጋ ይሆናሉ። (ዘፍ. 2:21-24) በጥንተ ተፈጥሮ የምናገኘው ይህ ነው።

በዚህ ጥቅስ መሠረት እነሆ ሴት ከወንድ በመገኘቷ ከወንድ ታንሳለች። ወንድ ደግሞ አባትና እናቱን ትቶ ምሽቱን በመከተሉ ከሴት ያንሳል። ተከተይ ተመሪ፡ አስከታይ መሪ ነውና። የዐረፍተ ነገሩን አቀማመጥ ትተን የሕጉን መንፈስ ብናስተውለው ግን ሴትና ወንድ አለመበላለጣቸውን ቁልጭ አድርጎ ያሳየናል።

አፈጣጠሯንም ሊቃውንት ይህን ቁጥር አስማምተው ተርጉመው ከጥንተ ተፈጥሮ ጀምረው የወንድ፡ የአዳም ባለእኩል አድርገዋታል። ከግራ ጎድኑ ተፈጥራለች ያሉ እንደሆነ፡ ውኃ ወደ ግራ ያደላል፤ ውኃነት በሴቶች ባሕርይ ይበዛል፡ በዚህ ይታወቃል። ከቀኝ ጎድኑ

ተፈጥራለች ያሉ እንደሆነ፥ ጌታ በዕለተ ዐርብ ንቁሕ በመሰከት፥ ንውም በትሰብእት ሁኖ ሳለ ከቀኝ ጎኑ የፈሰሰው የደመ ገቦ ምሳሌ ናት። ዳግመኛም ሴት ተሠርታ፥ ተቀጥታ ካደገች በኋላ ለባሏ ስትሰጥ ባሏን ወደ ግያዊ ግብር ትመራለችና። ስለምን ከጎድኑ? ዝቅ ብሎ ከእግሩ ከፍ ብሎ ከራሱ አይፈጥራትም ኑሯልን? ዝቅ ብሎ ቢፈጥራት የወንድ ተገዥ ሁና ትቀር ነበር፤ ከፍ ብሎ ቢፈጥራትም ወንድን ልግዛህ ባለች ነበርና፥ ከመካከል አካሉ ፈጥሯታል። ተገዥም አለቃም አይደለሽ፥ እኩያው ረዳቱ ነሽ ሲል። ግእከለ ነቂሕወንዋም ሳለ መፈጠሯስ ስለምን ነው? ቢሉ፥ እጅግ ነቅቶ ሳለ ብትፈጠር ይሰግውና ይጠላት ነበር፤ እጅግም ተኝቶ ሳለ ቢሆን ተነሥቶ ባያት ጊዜ ምትሐት ናት ባላት ነበርና። ስለዚህ ተነሥቶ ባያት ጊዜ ዛቲ ዐፅም እምዐፅምየ ወሥጋ እምሥጋየ ለትኩነኒ ብእሲትየ ብሎ በትንቢት አሜት።[2]

ፍትሐ ነገሥቱም የጳውሎስንና የጴጥሮስን መልእክታት እየጠቀሰ ስለ ባልና ምሽት ስለሴትና ወንድ፥ ስለቤተ ሰብእ በጠቅላላ በሰፊው ከተነተነ በኋላ ወንዶች ሴቶችን ተጠንቅቀው፥ ተንከባከበው፥ አክብረው እንዲይዟቸው አዝዟል።[3]

ሴት ከአምስቱም ሕግጋት፥ ከባቢሎን፥ ከአሶር፥ ከእሰራኤል፥ ከጸርእ፥ ከሮም ሁሉ ነጻ ወጥታ ከወንድ እኩል መሆኗን ፍትሐ ነገሥቱ ፍርጥ፥ እርግጥ፥ ግልጥልጥ አድርጎ፥ ወኩሎ ዘአሕረሙ ለዕለ ብእሲቱ ከግሁ ሕሩም ውእቱ ላዕለ ምታኒ፥ ለምሽቱ የተከለከለው ሁሉ ለባሏም ክልክል ነው፥ ብሎ ተናግሯል።[4]

በቤተ ክርስቲያን አገልግሎትም ልክ በቀዳማዊ ጢሞቲዎስ ምዕራፍ 3 ለጳጳሳት፥ ለቀሳውስት፥ ለዲያቆናት የታዘዘውን ትእዛዝ የፈጸሙ፥ ሲፈጽሙ እንዲሾሙ የአመክሮና የፈተና ሕግ ተጽፏል። ፈተናውን ሲያልፉ እመ ምኔትነትና ዐቃቢነት ይሾማሉ። አለቅነት ይሰጣቸዋል።[5]

በሚቀጥለው አንቀጽ እንደምናየው ከባሏ በሕይወቷ እኩል እንደሆነች ስትሞትም በፍትሐትና በሥርዓተ ቀብር እኩል ናት። ክህነት ለሌላቸው ለወንዶች ምእመናን የሚደረገው ሁሉ ያላንዳች አድልዎ ለሴቶች ምእመናትም ይደረጋል፤ ሥርዓተ ጸሎቱም ይደረሳል። በዚህም ከሊቃነ ጳጳሳት፥ ቀሳውስት፥ ዲያቆናት፥ መሃይምናን ጋራ ተራቸውን ይዘው ተሰልፈዋል።[6]

የቄስ የዲያቆን ምሽት (እሚን) ለትምት ሰባሏ የሚደረገው ሁሉ፥ ለእሷም ይደረጋል። ሬሳዋን የሚሸከሙት ልክ እንደባልዋ እንደ ቄሱ መዓርገ ክህነት ያላቸው ካህናት ናቸው።

65. ሴት የወንድ እመቤት ሆነች፥

ከዚህ በፊት ባየናቸው ሕግጋት ሁሉ ሴት መጀመሪያ ለወንድ ተናጋሪ እንስሳ፥ ወንድ ልጅ ተክሎ የሚያሳድግባት ተጋን፥ መብት የሌላት ታዛዥ ባሪያ ነበረች። በኋላም በክርስቶስ መሰላልነት ከባርያነት ወዘቅት ወጥታ፥ ወደ እኩልነት ሰገነት እንገቷን ብቅ አደረገች። በዚህ ዓለም ሲደነቅ በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ሕግጋት ግን ከዓለም ሁሉ አስቀድማ የወንድ የበላይ፥ የወንድ ገዥ ሆነችና ቁጭ አለች።

መጀመሪያ ሁለቱም ታያይተው በፍቅር ተጣምደው ለመጋባት ከተስማሙ በኋላ፥[7] ያለፈው ሥርዓት ሁሉ ተለውጦ ወንድ የበታች ሴት የበላይ ስለሆነች አግላጅ ሽግግሌ ወደ ወላጆችዋ ይልክና ከበዙ መጓደድ በኋላ እሽ ሲሉ፥ እሺ ቢሉ፥ ግጫ ያቀርባል፤ ጥሎሽ ይጥላል፤ እጅ መንሻ ይሰጣል። ለወላጆችዋ ያሳደጉበትን ዋጋ ይከፍላል። ይህ የሙሽራ ዋጋ ባለፈው በባቢሎን፥ በአሶር፥ በእስራኤል እንዳየነው ሴቷን ለባሏ ተገዥ የሚያደርግ አይደለም። በግሪክና በሮም ሴት ትሎት ይዛ መጥታ የወንዱ ተገዥ እንደምተሆነው ሁሉም አይደለም፥ የኢትዮጵያው ቤተ ክርስቲያን ወንድ ግን ገና ሙሽራይቱ ምሽቱ ከመምጣቷ በፊት የበታችነቱን የሚገልጥበት፥ ባርነቱን የሚጀምርበት፥ አገልጋይነቱን የሚያሳይበት ግጫ፥ ጥሎሽ ወይም እጅ መንሻ ይከፍላል። በቀደሙት አሕዛብና እስራኤል ሕግጋት ሴት ግጫ ወይም ጥሎሽ የምትቀበለው ለወደፊቱ ከእርኖዋ ቤት ገብታ በአገልግሎት ዋጋውን ስለምትመልስ ወላጆችዋ ያሳደጉበትን ዋጋ ይቀበሉ ነበር፤ አሁን ግን ከቤቱ ከገባች በኋላ ባለው ንብረት ሁሉ ባለ እኩል ስለምትሆን፥ በገዛ ገንዘቡ ራሱን ሸጦ የምታዝዘው እመቤት ይገዛል፥[8] ይህም በ3ኛው ምዕራፍ በግሪክና በሮም ይፈጸም የነበረው በኢትዮጵያ ተገላብጦ ደረሰ ማለት ነው። ሁለተኛውም እንኳንስ በድሎና ሳይበድል፥ ሳይገፋ ምሽቱ ተቆጥታ፥ ከቤቱ ወጥታ ከሄደች ማሪኝ ብሎ ይለምናል፤ አግላጅ ይልካል፤ ተበድሎ እንደበደለ ይክሣል። ይህን ተከትለው ነው መለለኝ የዘመናችንና የህገራችን ዳኞች ባልና ምሽት ተካለው ሲቀርቡ ገና ነገሩን ላይመረምሩ፥ ጉዳዩን ሳያጣሩ፥ ሙግታቸው እስኪያልቅ ቀለቧን ሰጪት ብለው ከወንድ ደመወዝ አብዛኛውን ጊዜ ከመቶ ሰባውን እንዲሰጣት የሚበይኑት።[9]

እንደ አሕዛብ ልማድ ግጫ ትቀበላለች፥ እጅ መንሻ ትበላለች፥ በጥሎሽ ምክንያት ከእናትና አባቷ ቤት ዐይታው የማታውቀውን ልብስ ትለብሳለች፤ ጌጣጌጥ ታደርጋለች፤ ከወላጆችዋ ቤት ከብት

ትጠብቅ፥ ታርም፥ ትጎለትል፥ ዕንጨት ትለቅም ውኃ ትቀዳ እንዳልነበረች ሁሉ ካማቷ ቤት ሁለት ዓመት እንደጨቅላ ልጅ እየተንደላቀቀች ስትሞሸር ጊዜ የወንድ የበላይ፥ የባል እመቤት ነኝ ብላ እመነችና ስላመነች ገና ስትታጭ ጀምራ መንደላቀቅ ጀመረች። ይህ ሥልጣኗ እያደገ ሲሄድ፥ ሄደና እንዲያውም በዘመናችን በአዲስ አበባስ እጅ መንሻና ማጫ እንደቀድሞው ወላጆችዋ ሳይሆኑ ራስዋ ተቀብላ፥ ከዚያም በፊት ተስማምታ ከተዋዋለች በኋላ ይበልጥ ስታገኝ ቃሏን እየስበረች አረቦኗን ትመልስ ጀመር። ለምን? ቢሉ የምትመልሰው ገንዘብ እንደዚህ በፊቱ አራት ወይም ሦስት ዕጥፍ ሳይሆን ራሱን ብቻ ስለሆነ፥ የመጀመሪያውን እጭተኛ ገንዘብ በልታ ስትፋፋ፥ ስትቆነጅ ለብላ ከተዋበች በኋላ፥ ስትዋብ፥ ስታጌጥ የብዙ ጎበዝ ዐይን ስለምትማርክ ዕጥፍ ገንዘብ ስለምታገኝ ከሁለትኛው ማጪዋ ለፊተኛው ያለምንም ወለድ ቆንጥራ ሰጥታ ያውም ብትራራ፥ በተቀረ ግን ምን እውቅልህ፥ እንጃልህ ብላ በመጨረሻ ብዙ የሰጣትን ታገባለች። የቤተ ክርስቲያኑ ሕግ የተመሠረተው ወንድ ጎይሰኛ ነውና ሴትን እንዳይበድል በሚል ግምትና የሴትን ተንኮል ባለማወቅ ነበር። ግን ሴት፥ ብልኀ ልጅ እየበላ ያለቀሳል እንደሚባለው የተጠቃች፥ የምታለቅስ መሰላ እየታየች፥ በክርስትና ሕግ ተጠልላ፥ ወንድ እያማረጠች፥ በወንድ ትቀልድ ጀመረ። እንዲህም ሁና ገብታ በቤቱ ንብረት ሁሉ ማጀት በጎረሰ፥ ደጃፍ በመለሰ እዛኝ ናዛኝ፥ ፈላጭ ቆራጭ እሷ ሆነች። በዚህም ወንድ ለፍቶ፥ ወጥቶ ወርዶ፥ ነዶ፥ በርዶ፥ ባመጠው ጥሪቱ ለማኝ ሆነ። ፍጹም ለውጥ ሆነና በሕጉም ባይሆን በግብር፥ ሴት እዛኝ፥ ወንድ ታዛኝ፥ ተላኪ፥ ባል ሎሌ፥ ምሽት እመቤት ሆኑ። በዚህ ጊዜ ነው ሴት የላከው ጅብ እይፈራም የሚለው የህገራችን ተረት የተመሠረተው። ይህ ተፅዕኖ ሁለቱም ሳሉ እንኳ ብቻ ሳይሆን ከሞቱም በኋላ ይጠበቃል፤ ይከበራል፤ ምሽቱ የሞተችበት ወንድ ዓመት ሳይቆይ እንዳያገባ ተከልክሏል፥ ባሏ የሞተባት ሴት ግን በዐሥር ወር እንድታገባ ተፈቅዶላታል። ይህንን ሕግ በቀጥታ ሴቶች ወይም የሴት ጠበቆች የሠሩት ነው ለማለት ያስደፍራል። እንደዛሬው ሆቴል ባሌለበት፥ ሠራተኛ እንደልብ በማይገኝበት ዘመን የማጀትን ሥራ የማያውቀው ለዕለት ጉርሱ የሚቸገረው ወንዱ ዓመት ይቆይ ተባለ፥ ሲባል፥ ሴቷ ግን ባሏ ሠርቶላት ከሞቀ ቤቷ ሁና እያበሰለች እየበላች ብዙ ዘመን ለመቆየት የምትቸለው እንዳይበርዳት ብቻ ቶሎ ታግባ ተባለች።[11]

የቀረው ቀርቶ ተፈጥሮ በሚያመጣው መጋነንና መባለቅ እንኳ ወንዱ ተጨቁኗል። የሴት ዐቅመ ሔዋን ማድረሻ ከ12-15 ዓመት ሲሆን የወንዱ ዐቅመ አዳም ማደርሻ ከ20-25 ዓመት እንዲሆን ተወሰናበታል። ከዚያ ቢያንስ ጋብቻው ሕገ ወጥ ነው። ወንድ ከአባቱ ከሰጠው ባላደራ፡ ወይም ሙት ዓመት ጠባቂ ነጻ የሚወጣው ከ20 ዓመት በላይ ሲሆን ሴት ግን በ12 ዓመቷ ነው።[12]

66. ባልና ምሽት በክርስትና፡

ባለፈው አንቀጽ የሴት መብት እየገሠገሠ የወንዱ ለገሥጋሹ ቦታ እየተወ፡ እያፈገፈገ ሂዶ ከምን እንደደረሰ ዐይተናል። ይህ አንቀጽ ደግሞ ባልና ምሽት ከተጋቡ በኋላ እስከ ዕለተ ሞታቸው ለግራ ቀኛቸው ያላቸውን ወይም ያለባቸውን የእምነት ጉዳይ ያብራራልናል። የጋብቻን እምነት አጉድሎ ያመነዘረ ከሁለቱ አንዱ ያላንዳች የጸታ አድልዎ ይቀጣል። ወንድ ነኝ ብሎ ምሽቱን ከቤት አስቀምጦ ያላንዳች ተቆጣጣሪ ቢፈልግ ከውሽማው፡ ከወዳጁ፡ ከዕቁባቱ፡ ቢፈልግ ከገረዱ፡ ከባሪያው ግንኙነንድ ከዚህ በፊት እንዳየነው በባቢሎን፡ በፋርስ፡ በነነዌ፡ በግሪክ፡ በሮም፡ በእስራኤል ቀረ። እንዲህ ያለው ዘላንነት በክርስትና ሞተ፤ ተከተተ። ባሏን ሲያመነዝር ካገኘችው፡ ምሽት ከስላ የምታስቀጣበት ሕግ አገኘች። ዳኛውም እንኳንስ ተበድላ ላትበድልም፡ ከጸታ ጓደኛው ይልቅ ለጸታ ተቃራኒው ለሴት የሚያደላ ሆነ። ሌላው ይቅርና ባሪያውን እንኳ ለግግባት ከፈሰገ፡ መጀመሪያ ነጻ ያውጣትና፡ ግጫ ሰጥቶ፡ ጥሎሽ ጥሎ፡ እጅ መንሻ አቅርቦ በእኩልነት ደረጃ ያግባት ተባለ። ይህ ከሆነ ደግሞ ባሪያው እመቤቱ መሆኗ የታወቀ ነው። ለውጥ ይህች ናት፡ ሴት ባሪያን በጸታዋ ምክንያት በጋብቻ የክርስትና ሕግ የጌታዋ እመቤት አደረጋት።[13]

በምንም ዓይነት ይሁን የቤተ ክርስቲያን ሕግ ስለአውስቦ ያለው ውላኔ አንድ ወንድ ላንድ ሴት ነው። ይህም ሕግ ክርስትና ባለበት ዘመን ሁሉ የሚኖር እንጂ እንደጊዜው የሚሻሻል የሚሰወጥ፡ የሚከለስ አይደለም።[14]

67. ያለፈቃዷ አትዳርም ገንዘቧም አይያዝም፡

ሴት ነጻ ወጥታ ከዚያም አልፋ ብድሯን መግባት እንደጀመረች ከዚህ በፊት ዐይተናል። ስለዚህ ያለፈቃዷ በምንም ምክንያት አትታጭም፡ አትዳርም። ገንዘቧም አይያዝም። ከባሏ ጋራ ሁና በበላችውም ዕዳ አትጠየቅም። ለሁሉም ነገር አስተድሞ በምስክር ፊት መስማማት አለባት። ይህ ካልሆነ ግን ከማናቸውም ዕዳና ነውር፡ ከሰላ ነጻ ናት።[15]

68. <u>መዋዕለ ንጽሕ፡</u>

በክርስትና ሴት በተፈጥሮ በሚያጋጥማት ነገር ሁሉ ንጹሕ ናት። የወር አበባዋ ቢመጣ፡ ብትወልድ፡ ረከሰች፡ ርኩስ ናት አትባልም፤ ግን በዜሌዋውያን ምዕ. 12:1-8፤ 15፤ 19-30፤ የተጻፈውን የሰሙ፡ አሪትና ወንጌል ምን እንደሆኑ ያልለዩ መበለታት ሴት ስትወልድና ስታብብ ትረክሳለችና ጸበል ርጩን፡ የነካነውን ባረኩልን ሰለሚሉ የቆላ ቀሳውስትም መጻሕፍቱን ሳያነቡ፡ የሴት ንስሓ ልጆቻቸውን ትእዛዝ ተከትለው፡ አንዳንድ ነገር አኩተምትመው ውኃ ስለሚረጩ፡ ሕገ አሪት በባልቴቱ አዝማችነት መዋዕለ ንጽሐችሁን አክብሩ እያለች ትሰብካለች። ይህን ሊቃውንቱ በፍጹም አይቀበሉትም።[16]

ቤተ ክርስቲያንም የምታሰተምረው፡ "ጋብቻ በማናቸውም ገጹ ምን ጊዜም ክቡር ነው፤ ለምኝታውም ርስሐት የለውምን" ነው። (ዕብ. 13: 4)።

ዐጼ ገላውዴዎስ ስለግዝረት ቢጠይቋቸው ሰጪናና ለተግባራችን እንጂ ለሃይማኖት ብለን አይደለም የምንገዝረው ብለው እንደመለሱ፡ ሊቃውንቱም ለምን ሴት በወለደች ቁጥር መዋዕለ ንጽሕሽን ጠብቂ እየተባለች ስትረጭ ዝም ትላላቸሁ ሲሏቸው፡ ይህ ምግባር እንጂ ሃይማኖት አይደለም፤ ጎጢአት ሁኖ እያስከንናት፡ ወንጀል ሁኖ አያስቀጣት፡ ከዚያም በላይ ልባልባ የሌላት ሴት ሰውነቷን በማትቆጣጠርበት ጊዜ ቤተ ክርስቲያን ከእነአደቷ ገብታ፡ ተመልካች ከምታሰቀይም መዋዕለ ንጽሕሽን ጠብቂ ብሎ፡ ሰውነቷ ሲጠዳ ከሰው ብትገናኝ ለንጽሕና ጥሩ ነው እንጂ፡ ለሃይማኖትስ አይደለም ብለው ይመልሳሉ። በዚህም የንጽሕና ወራት ለጥዳት እንጂ ለሃይማኖት ምንም እንዳልሆነ የተግረ ሁሉ ያውቀዋል።

እንግዲያ በቤተ ክርስቲያን ሕግ እንዲህ ከሆነች ዛሬ በራድዮ የሚነገረው በአየጋዜጣው የሚጻፈው ሴት ተጨቁናለች፡ ድርብ ጭቆና አለባት የሚባለውሳ እንዴት መጣ? ለሚል ጠያቂ የሚከተለው ምዕራፍ ይቀርብለታል።

ከዚህ የቀረው በሴት አቋም መጽሐፉችን ይቀጥላልና አሁን ግን ወደ ያዝነው ትምህርት ወደ ሰጊድ እንሻገራለን።

ለዚህ ምዕራፍ የተጠቀሱ መጻሕፍት

1. ሀ. Kealy and Sherk OP.cit. P.199,
   ለ. ስንክሳር ነሐሴ 3:15።
   ሐ. ቅዱስ ኤፍሬም ውዳሴ ማርያም፥ አዲስ አበባ፥ ብርሃንና ሰላም፥ 1943/:7.154-5።
2. የሥነ ፍጥረት ምዕላድ ቁ. 729/አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፥ የኢትዮጵያ ጥናትና ምርምር ኢንስቲትዩት ቤተ መጻሕፍት።
3. ፍትሐ ነገሥት፥ አንቀጽ 1፥ ክፍል 2።
4. ከዚያው፥ አንቀጽ 24፥ ክፍል ራብዕ።
5. የሐዋርያት ሲኖዶስ፥ ትእዛዝ 15፥ 19።
6. መጽሐፈ ግንዘት፥ /አዲስ አበባ፥ ትንሣኤ ዘጉባኤ ማ/ቤት፤ 1940፤ ገጽ 3፤ 4፤ 36-81፤ 100፤ 133-143።
7. ፍትሐ ነገሥት፥ አንቀጽ 24፥ ምዕራፍ 1፥ ክፍል 1-3።
8. እምነ ዝኩር፥ አንቀጽ 24፥ ምዕራፍ 3፥ ክፍል 2-3፤ ወንጌል ቅዱስ
   አዲስ አበበ ብርሃንና ሰላም፥ 1917/፥ ገጽ. 280-281
9. ሕርያቆስ/አባ/ ቅዳሴ ማርያም፥ /አዲስ አበባ፥ ብርሃንና ሰላም 1943 /ገጽ 72-3።
10. ፍትሐ ነገሥት፥ 24፤ 3፤ 3።
11. ከዚያው፥ 24፤ 5፤ 3፤ 3።
12. ከዚያው፥ 24፤ 3።
13. ሀ. የሐዋርያት ሲኖዶስ፥ ትእዛዝ 63፥
    ለ. የሠለስቱ ምእት ሲኖዶስ፥ ትእዛዝ 70፥
    ሐ. ፍትሐ ነገሥት 24፤ 5፤ 3፤ 5።
14. ከዚያው፥ 25።
15. ከዚያው፥ 24፤ 1፤ 11፤ 3፤ 3፤ 5፤ 3፤ 5።
16. ዓለማየሁ ሞገስ: ሠርግና ልግድ፥ /አዲስ አበባ: ብርሃንና ሰላም ማ/ቤት 1956/ ገጽ 69-70።

ምዕራፍ 31

ሰ ጊ ድ

የሰጊድ መግለጫ

ሰጊድ ሰንት ዐይነት ነው? ለማንሰ ይጣል? ለጊል ጠያቂ፥ መጀመሪያ ዐይነቱንና ትርጉሙን እናስቀድማለን። በአየቋንቋው ሰጊድ ሁለት ትርጉም አለው። አሱም እጅ መንሣትና የአምልኮት ስግደት ይጣላል። የአምልኮት ስግደት በእኛ የሚደረገው ሰሥላሴ ብቻ ነው፤ ለሦስቱ አካላት፥ ለሦስቱ አሰግት፤ አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ አንድ አምላክ ብቻ። ለቀረው ግን ለማርያም፥ ለመላእክት፥ ለመስቀል፥ ለክቡር ሰው፥ ለጌታ ሥዕል፥ እጅ እነሣለን። እጅ መንሣትና መስገድ በእንቅስቃሴ ቢመሳሰሱም በሐሳብ አንድ አይደሱም። ለአምላክና ለስሙ የሚደረገው አምልኮት ነው፥ የቀረው ግን እጅ መንሣት ነው፤ ሰጋጁ ምንም መሬት ቢስም ከእጅ መንሣት አልፎ አምልኮት አይሆንም። ለታቦትም በላዩ ላይ የእግዚአብሔር ስም ስለተቀረፀ የአምልኮት ሰጊድ እንሰግዳለን። በጽላቱ ላይ ለተጻፈው ለተቀረጸው የእግዚአብሔር ስም እንጂ ለጽላቱ ወይም ለዕንጨቱ እንዳልሆነ ተረድቶ መስገድ ያሻል፤ ያለበለዚያ ግን አምልኮ ጣዖት ይሆናል።

በጽላቱ ላይ ዐሠርቱ ቃላት መቀረጽ አለባቸው፥ ይልቁንም ከግብጽ ምድር ከባርነት ቤት ያወጣሁህ እግዚአብሔር አምላክህ እኔ ነኝ የሚለው መቅረት የለበትም። ወይም በዚህ ተለዋጭ የኢየሱስ ክርስቶስ ስም በጉልህ በሚነበብ አኳኋን መቀረጽ አለበት። ጽላቱ ትልቅ የሆነ እንደሆነ ዐሠርቱ ቃላትን፥ ትንሽ የሆነ እንደሆነ ደግሞ ኢየሱስ ክርስቶስን መያዝ አለበት። እነዚህ ከሌሉበት ግን ፊልጦ ቡና ግፍያ ግድረግ ነው። (ዘፀ. 20:1-17፤ 34:1፤ 28፤ 4:13፤ 10:4፤ ፊል. 2:9-10)

ታቦት፤

ታቦት ሁለቱም ዐይነት ሰጊድ ይገባዋል፤ ለጽላቱ የአምላክ ቅዱስና ክቡር ስሙ እንዲቀረጽበት ተመርጧል በትቷልና የአክብሮት፥ ለአምላክ ስም ያምልኮት ሰጊድ ይገባል። በሁለቱም ዐይነት ለጽላት መስገድ ይገባል።

ጌታ እስራኤልን ከግብጽ ሲያወጣ፥ ከግብጽ አምልኮ እንስሳት፥ ላም፥ በፊ፥ ፍየል፥ በግ ወዘተ..ለመለየት እነዚህን ሁሉ ሠዋልኝ አለው፤ በደረሻ ወደ ስሙ አምልኮት ለመምራት፥ ግን ለሰው ልጅ በረቂት ሰሙ ለማመን ስለራቀበት በጽላት ቀርጾ በግዙፍ ነገር ላይ አስፍሮ ሰጠው፤ ከዚያ ወዲህ ጽላት የሰሙ መያዢያ ሁኖ ሲወርድ ሲዋረድ ከኛ ደረሰ።

የተናገረውን ይዘው ታቦትንም ገሸሽ ለማድረግ የሚፈልጉ አሉ። በዚህ ግን ራሱን የጌታን ቃል እናስተውለው፤ ሴቲቱም፥ ጌታ ሆይ! አንተ ነቢይ እንደሆንህ እያለሁ፥ አባቶቻችን በዚህ ተራራ ሰገዱ፥ እናንተ ግን ሰው ሊሰግድበት የሚገባው ስፍራ በኢየሩሳሌም ነው ትላላችሁ አለችው። ኢየሱስም እንዲህ አላት--አንቺ ሴት! እመኚኝ፥ በዚህ ተራራ ወይም በኢየሩሳሌም ለአብ የማትሰግዱበት ጊዜ ይመጣል። እናንተስ ለማታውቁት ትሰግዳላችሁ፥ እኛ ግን መዳን ከአይሁድ ነውና ለምናውቀው እንሰግዳለን። ነገር ግን በእውነት የሚሰግዱ ለአብ በመንፈስና በእውነት የሚሰግዱበት ጊዜ ይመጣል፥ አሁንም ሁኗል፥ አብ ሊሰግዱለት እንደነዚህ ያሉትን ይሻልና፥ እግዚአብሔር መንፈስ ነው፥ የሚሰግዱለትም በመንፈስና በእውነት ሊሰግዱለት ይገባቸዋል። (ዮሐ. 4:19-24)

አንደኛ ይህ የሚያሳየው ስለቦታና አቀራረብ ነው፥ በመሆኑም በሉዛ (ገርዚን) ወይም በኢየሩሳሌም ብቻ ሳይሆን በመንፈስ የትም ሁኖ ለአብ መስገድ መቻሉን ነው። ሁለተኛም ጌታ ቤተ መቅደስ ገብቶ ነጋዴዎቹን ሁሉ ሲያስወጣ፥ በእምልኮተ እግዚአብሔር በኩል ቆሻሻ የሆነውን ሁሉ ሲያስወግድ ጸሐፍት ፈሪሳውያን የሚያደርጉትን ሁሉ ሲዘልፍ ታቦትን አልነቀፈም፤ ጽላትን አልሰደበም፥ ይህም ቅዱስ መሆኑን ያሳያል። ሦስተኛም ተከታዮቹ በትምርህርቱ ተቸግረው ሲያስቡ እኔ አሪትን (ሕግን) ነቢያትን ለመሻር የመጣሁ አይምሰላቸሁ፥ ልፈጽም ነው እንጂ ለመሻር አልመጣሁም--(ማቴ. 5:17) ብሎ ጽላትን ከነጽሑፉ ወደ ዘመነ ሐዲስ አሻግሮታል።

የአምልኮት ስግደት ለእግዚአብሔርና ለስሙ እንደሚገባ ለመረዳት የሚከተሉትን ጥቅሶች እነሆ፥ (ዘፀ. 20:2-6፥ 34:14፥ ዘዳ. 5:6-8፥ 10:3-5፤ 26:10፥ ኢያ. 7:6፥ 1ዜና.መዋ. 16:29፥ መዝ. 5:7፥ 22:27፥ 96:9፤ 95:6፥ ሳሙ. 1:19፥ ኢሳ. 36:7፥ 45:23-24፥ ማቴ. 4:10፥ ፊል. 2:9-16፥ ዕብ. 1:6)

በክርስትና ሃይማኖት ለሰውና ለመላእክት የጸጋና ያክብሮት ሰላምታ ይሰጣል፥ ለዚህም የሚከተሉት ጥቅሶች ያስረዳሉ፥ (ዘፍ. 49:8፥ 19:14፥ 33:3-8፥ 42:6፥ 43:28፥ ኢያ. 5:14፥ 49:23፥ 2ነገ. 4:36-37፥ 27:28-29፤ 1ዜና.መዋ. 21:21፥ ግብ. 10:5፥ 16:29፥ ራእ. 3:9)

የጽላት ግብሩና ሥራው ይህ ሲሆን መሰወሩ መሸፈኑ ግን ልክ አይደለም። በእያድባራቱ ጽላት የሚሰረቅበትም ምክንያት በመሸፈኑ ነው።

ጽላት ስመ እግዚአብሔር ከሌለበት በነቢያት የተነገሩትን ጣዖታት ይመሰላል፥ እሱስ እንዴት ነው? ለሚል እነሆ፣
(መዝ. 113:10-17፤ 134:15፥ ኢሳ. 44:9-20፤ 40:18-20፥ ኤር. 10:5) በጽላት ላይ በተቀረጸው ስሙ አድሮ እግዚአብሔር ተአምራት እንደሚሠራ ለማወቅም 1ሳሙ. ከምዕራፍ 4-6 አስተውሎ ያነቧል። ስጊድ ምን እንደሆነና ለማን እንደሚገባ ከተረዳን የሚሰገደውስ የት ነው? ለሚል ጠያቂ የሚከተለው መልስ ይቀርባል፣

ምዕራፍ 32

ቤተ ክርስቲያን=ቤተ መቅደስ

ጌታ እግዚአብሔር መንፈስ ነው፥ የሚሰግዱለትም በመንፈስና በእውነት ሊሰግዱለት ይገባል ያለውን ይዘው፥ ቤተ ክርስቲያን አያስፈልግም እያሉ ቤት ለቤት የሚሽሎከለኩ አሉ። ከዚህ ላይ ጌታችን በመንፈስና በእውነት ስገዱ አለ እንጂ ቤተ ክርስቲያን አትሂዱ አላለም። ይህ አባባል የሚያስተምረው የትም ሁን እግዚአብሔርን አፍ ተልብ ሁነህ አገልግል፥ አምልክ ነው፤ ይህ ባይሆንስ ኑሮ የአባቴ ቤት ቤተ ጸሎት ይባላል፥ እናንተ ግን የሌቦች መደበቂያ አደረጋችሁት እያለ አይጠርገውም ነበር። (ማቴ. 21:12-17፤ ማር. 11:15-19፤ ሉ. 19:45-48፤ ዮሐ. 2:13-22)

<u>መቅደስ</u>፥ የሰሎሞን መቅደስ ከመሠራቱ በፊት ጀምሮ በትንቢት የተነገረ፥ የሰሎሞን መቅደስ ታንጾ ሲቀደስም በራሱ በእግዚአብሔር የተባረከና የተቀደሰ፥ በኋላም ክርስቶስ ያስተማረበት ደቀ መዛሙርቱ ሐዋርያት የጸለዩበት፥ የሰበኩበት ነው። ጳውሎስ የአሪትን ከነመሥዋዕቷና ከህጎቷ ግለኗን ሲናገር፥ ግዝረትን በጥምቀት ሲፍቅ መቅደስ ቤተ ክርስቲያን የጉባኤ መሰብሰቢያ አዳራሽ አያስፈልግም አላለም። ይህም ክርስቲያን በእየሀገሩ የሚሠሩትና የሚያገለግሉበት የአብያተ ክርስቲያን ሕንጻ ነው።

ለዚህም የሚከተሉትን ይመለከቷል፤

እግዚአብሔር በተቀደሰው መቅደሱ ነው፥ (መዝ. 10:41)

ሁሉም በመቅደሱ ያመሰግናል (መዝ. 28:9)

እግዚአብሔርን አንዲት ነገር ለመንሁት፤ እርስዋንም እሻለሁ፥ በሕይወቴ ዘመን ሁሉ በእግዚአብሔር ቤት እኖር ዘንድ እግዚአብሔርንም ደስ የሚያሰኘውን አይ ዘንድ መቅደሱንም አገለግል ዘንድ (26:4)

እጆቼን በንጽሕና አጥቤ፥ አቤቱ መሠዊያህን እዞራለሁ፤ የምስጋና ድምፅ እሰማ ዘንድ፥ ታምራትህንም ሁሉ እነግር ዘንድ፥ አቤቱ! የቤትህን ስፍራ፥ የክብርህንም ማደሪያ ቦታ ወደድሁ፥ (25:6-8) ስገዱ ለእግዚአብሔር በዐጸደ መቅደሱ (28:22)

ይህን የመሰለ በመዝሙር ውስጥ ከ40 በላይ ጥቅስ አለ። እግዚአብሔር በገባዖን ለሰሎሞን እንደተገለጠለት ዳግመኛ ተገለጠለት አለው፥ በፊቴ የጸለይሽውን ጸሎትህንና ልመናህን ሰምቻለሁ፥ ለዘለዓለምም ስሜ በዚህ ያድር ዘንድ ይህን የሠራሽውን ቤት ቀድሻለሁ፥ ዐይኖቼም ልቤም በዘመኑ ሁሉ በዚያ ይሆናሉ፥ (1ነገ. 9:3)

የሰሎሞንንማ ቤተ መቅደስ ናቡከደነጸር አፍርሶት የለ? ሰሚል ተከራካሪ ደግሞ የሚከተለውን መልስ እንሰጣለን።
እግዚአብሔር እምላክ ፍቅር ወትሕትና ነው። ካህናቱ ግን: ልክ የኛዎቹ ዛሬ በቂም በበቀል ገብተው እንደሚቀድሱት: በቂምና በተዘሀሮ ስላረከሱት ቤተ መቅደስን በእሕዛብ እጅ እንድትወረርና እንድትመዘበር አደረገ። አድርጎ ግን አልቀረም እስራኤል ንስሓ ሲገቡ: መጀመሪያም በዘሩባቤል: በኋላም በትልቁ ሔሮድስ ተመልሳ እንድትሠራ ፈቀዶ: ተመልሳ ተሠርታለች። ይህም አንድ ቤተ መቅደስ: ቢፈርስ: ቢቃጠል ሌላ ሥሩ ለማለት ምሳሌ ይሆናል: ሆኗልም።
ጌታም ሔሮድስ በሠራው ቤተ መቅደስ ያስተምርም ይሰብክም: ድውያንንም ይፈውስ ነበር። ከዚያም አልፎ ተርፎ ያባቴን ቤት እታቆሽሹ እያለ ያባርር ነበር። በኢየሩሳሌም የነበሩ ሐዋርያትም ሲሆንላቸው ገብተው ሳይሆንላቸው ደግሞ ባካባቢው ሁነው ይጸልዩ ነበር። ይህም ጸሎተ ማኅበራችሁን በቤተ ክርስቲያን እድርጉ ማለት ነው።
በእየቀኑም እንድ ልብ ሁነው: በመቅደስ እየተጉ: በቤታቸውም እንጀራ እየቆረሱ: በደስተና በጥሩ ልብ: ምግባቸውን ይመገቡ ነበር። (ግብ. 2:42)
ዕለት ዕለትም በመቅደስና በቤታቸው ስለ ኢየሱስ እርሱ ክርስቶስ እንደሆነ ማስተማርና መስበክን አይተውም ነበር። (ግብ. 5:42) ከዚህም በላይ እንዳየነው ቤተ መቅደስ በቤተ ክርስቲያን ተተካች እንጂ አላለፈችም አልተፋቀችምና የማኅበር ጸሎታችንና ስብከታችንን በቤተ ክርስቲያን የግል ጸሎታችንን በቤታችን እናድርግ።

ምዕራፍ 33

የልዩ ልዩ ቃላት ትርጉም

አጠቃላይ የቃላት መግለጫ፡
ብዙ ጊዜ በሃይማኖት ጭቅጭቅ ወይም ክርክር የሚነሣው በቃላት አሰመግባባት ነው። ቃላት በእየዘመኑ፡ ሀገሩ፡ ወረዳው፡ አውራጃው ይለዋወጣሉ። ለምሳሌም በሀገራችንና በዘመናችን አሽከር፡ ቆንጆ፡ አቆርቋዥ፡ አብዮት ከምን ተነሥተው የት እንደደረሱ ብናስተውል የቃላት መለዋወጥ፡ የቋንቋን መሳልመሰና ማርጀት ብሎም መሞት እናያለን። ቅዱሳት መጻሕፍት የተጻፉት በብዙ አህጉርና በብዙ ዘመን ነው። ዘመን፡ 1500 ሲሆን፡ አህጉር ደግሞ ከባቢሎን እስከ እስፓኝ፡ ከሮም እስከ ኢትዮጵያ ነው። በዚህ የዘመንና የአህጉር ስፋት ብዙ ባህል ተለዋውጠዋል፡ ብዙ ታሪክም አልፏል። ከዚህም በላይ ቅዱሳት መጻሕፍትን የጻፏቸው ደራሲያን ከ40 በላይ ናቸው። ርግጥ ቅዱሳት መጻሕፍትን የጻፏቸው ደራሲያን በመንፈስ ቅዱስ እየተመሩ ነው። ግን መንፈስ ቅዱስ ዐላማውን ይመራል፡ መንገዱን ያሳያል እንጂ ቃል መርጦ፡ ብዕር ቀርጦ አይጽፍም። ቃላቱም በባህሉ ምክንያት ልዩ ልዩ ትርጓሜ ያሳያሉ፡ ከዚህም ነጻ ሊሆኑ አይችሉም። ስለዚህ መጀመሪያ ያወቁትን ያንድ ቃል ትርጉም ይዞ ሁለተኛውን አልቀበልም ማለት ከሳሹን ሰምቶ ተከሳሹ የሚሰጠውን መልስ አልቀበልም የሚልን ዳኛ ያስመስላል። ይህም ከግይታረም የሰሕተት ጉድጓድ ይጥላል። በመሆኑም ይህ ምዕራፍ እንደ መዝገበ ቃላት ሁኖ የብዙ ቃላትን ትርጉምና ፍች ባይሰጥም በሃይማኖት ችግር የሚያመጡትን ቃላት ከዚህ ቀጥሎ ይዘረዝራል።

አብ=አባት
ከእናት ጋራ ሁኖ፡ ተገናኝቶ በሥጋ የወለደ፡ የሕይወት መገኛ ምንጭ ከዚህ የተነሣ በዘዬ ብዙ ትርጉም አለው፡ (ዘፍ. 2:24)

ሀ) 1. ፈጣሪ፡ ጌታ ሆይ አባታችን አንተ ነህ (ኢሳ. 64:8)
2. በሰማያት የምትኖር አባታችን ሆይ! (ማቴ. 6:9)
3. ሁላችንስ አንድ አባት ያለን አይደለንምን? አንድ አምላክስ የፈጠረን አይደለምን? (ሚል. 2:10፡ ሮሜ 8:14-16)

ለ) መሥራች
ዓዳም የባልን ወለደች፡ አሱም በድንኳን የሚቀመጡት የዘላኖች አባት ነበረ። የወንድሙም ስም ዩባል ነበረ። አሱም በገናንና መለከትን የሚይዙ አባት ነበረ። (ዘፍ. 4:20-21)

ሐ) <u>ታዳጊ፥ ጠባቂ</u>

1. እኔም አባት እሆነዋለሁ አሱም ልጅ ይሆነኛል (2ሳሙ. 7:14)
2. ለዕውር ዐይን፥ ለአንካሳ እግር፥ ለደኃ አባት ነበርሁ (ኢዮ. 29:16)
   <u>አሳዳጊ</u>፥ ልጄ ሆይ! ለምን እንዲህ አደረግህ? እነሆ፥ አባትህና እኔ እየተጨነቅን ስንፈልግህ ነበርን አለችው፤ (ሉቃ. 2:48)

መ) <u>ከአባት በፊት የነበሩና የአባት ጓደኞች ሁሉ፤</u>

1. የአባቶቻቸውንም አምላክ በደሉ፥ እግዚአብሔርም ከፊታቸው ባጠፋቸው በምድሩ አሕዛብ አምላክ አመነዘሩ። (2ዜና.መዋ. 5:25)
2. አቤቱ! በጆሮአችን ሰማን አባቶቻችንም ነገሩን፤ (መዝ. 43:1)

<u>እም = እናት</u>፥ ወላጅ እናት፥ አሳዳጊ በዘይቤ ደግሞ እንደ እናት በውለታዋ የምትቆጠር ሴትና ሀገር።

<u>እኁ = ወንድም፥ እኅት</u>፥

የእናት ልጆች፥ በእናትና አባት የሚገናኙ ብርክና ግሕፀን የሚያገናኛቸው ወይም ከሁለቱ በአንዱ የሚገናኙ ሰዎች እኅትና ወንድም ይባላሉ። ከዚህ የተነሣ አንድ ሃይማኖት ያላቸው፥ አንድ ጽዋዕ የሚጠጡ፤ በአንድ ግጎበር የሚኖሩ፥ ያንድ መምህር ተማሪዎች፥ ያንድ ገዳም መነኮሳትና መነኮሳይያት ወንድም እኅት፥ እኁ እኅት በብዙም አኀው አኀት ይባላሉ።

<u>ተከታይ</u>

1. በዙሪያው ተቀምጠው ወደነበሩት ተመለከተና እነሆ፥ እናቴ ወንድሞቼም፥ የእግዚአብሔርን ፈቃድ የሚያደርግ ሁሉ፥ ወንድሜ ነው፥ እኅቴም እናቴም ነው አለ። (ማር. 3:32-35)
2. ከዚህ በኋላ ከእናቱና ከወንድሞቹ ከደቀ መዛሙርቱ ጋራ ወደ ቅፍርናሆም ወረደ። (ዮሐ. 2:11-12)
3. እነዚህ ሁሉ ከሴቶችና ከኢየሱስ እናት ከማርያምም ከወንድሞቹም ጋራ በአንድ ልብ ሁነው ለጸሎት ይተጉ ነበር። በዚህም ወራት ጴጥሮስ በመቶ ካያ የማኅበሩ ሰዎች መካከል ቁሞ ወንድሞቼ ሆይ!-(ግብ. 1:14-15)

መቶ ካያው ሁሉ የሥጋ ወንድሞቹ ላይሆኑ፥ የክርስቶስ ደቀመዛሙርት፥ የእግዚአብሔር ልጆች ማለቱ ነው።
ወንድሞቼ ሆይ! ስለአባቶች አለቃ ስለዳዊት ....(2:29) አሁንም የመንፈስ ጓደኞቼ ማለቱ ነው። በዚህም መላ ግብረ ሐዋርያት ይቀጥላል፥ (7:1-2፤ 22:1)
<u>በአቋጥሪኝ ዝምድናም በነገድም በሀገርም ወንድም</u> ይባላል፤ ይህም እንደሚከተለው ነው፤
አብርሃም ሎጥን፥ እኛ ወንድማማች ነንና በእኔና በእንተ በረኞቼና በረኞችህ መካከል ጠብ እንዳይኖር እለምናለሁ እለው። (ዘፍ. 13:8) የወንድሙን ልጅ ነው ወንድሜ ያለው።
ወንድሞቼ ሆይ! ይህን ክፉ ነገር አታድርጉ...(19:7) ይህ ደግሞ ሎጥ ነው፤ የሀገሩን ሰዎች ነው ወንድሞቼ ያላቸው።
ወንድሞቹም ይህን ባወቁ ጊዜ ወደ ቂሳርያ ወሰዱት (ግብ. 9:30) ይህም በደግስቶ ያሉት ክርስቲያን ማለት ነው።
ለዚህ ርእስ ብዙ መጥቀስ ይቻላል፤ ይህን የጠቀስነውም ብዙ ሰዎች የክርስቶስ ወንድሞች የማርያም ልጆች የሚል በቅዱሳት መጻሕፍት ካለ፥ ክርስቶስ ወንድሞች ካሉት ለማርያምም ልጆች እሏት ከተባለ ክርስቶስም ወንድሞች አሉት በሥጋ፥ ማርያምም ከክርስቶስ ሌላ ልጆች ካሏት፥ ዘለዓለም ድንግል አይደለችም፥ በሕዝቅኤልና በሰሎሞን የተነገረው ትንቢትም አልተፈጸመም የሚሉ ሰዎች ስላሉ አባት፥ እናት፥ ወንድም፥ እኅት የሚሉ ቃላት ብዙ ትርጉም እንዳላቸው ለማስረዳት ነው።
<u>ነ ፍ ስ</u>፥
ነፍስ ነፈሰ፥ ሸው ሸው አለ ካለው ግሥ የመጣ ዘመድ ዘር ነው፤ መጀመሪያ እንደ መዝገበ ቃላት በዚህ ርእስ በኋላ ደግሞ በምስጢረ ትንሣኤ ያለውን እናላያለን፤ ነፍስ የለችም የሚሉት ወንድሞቻችን እንዲረዱልን።
ነፍስ በቁሙ ረቂቅ አካል፥ የሥጋ ሕይወት፥ የሥጋ ባለቤት፥ ደመ ነፍስ፥ በደመ ነፍስ የሚንቀሳቀስ እንስሳ ሁሉ፥ ነባቢት ሰባዊት፥ ሕያዊት ህልውና ናት፤
ነፍሱ በላዩ ላይ አለች። ነፍሱ ልትወጣ ደረሰች። ተናጋሪ ነፍስ። ከጻድቃን ነፍሳት ጋራ ትካፈላላችሁ። (ግብ. 20:10፤ ዘፍ. 35:18፤ 1ነገ. 17:21)
ትንፋሽ፥ እንስትንፋስ፥ ሕቅታ፤ ሕያው እስከሆንህና ነፍስህ እስካለች ድረስ፥ ነፍሱ (እስትንፋሱ) ፍም ናት። እስከ ነፍስ ደጃሪት፥ እስከ

መጨረሻዋ አስትንፋስ (ሚራ. 30:29፤ ኢዮ. 41:13፤ ቅዳ 112:11)
ልብ፥ ልቡና፥ ኩሉ ነፍስ ይደነግፅ=ልብ ሁሉ ይደነግጣል። በኩሉ ነፍስከ አክብሮ ለአቡከ=በሙሉ ልብህ አባትህን አክብረው። ወዐቅም ምክረ ነፍስከ=የልብህን ምክር ወስን። (ኢሳ. 13:7፤ ሚራ. 6:26፤ 37:13)።
ሰው፥ ለውነት፥
ወተወሰኩ ሠላሳ ምእት ነፍስ 3000=ለዎች ተጨመሩ። ዕቀቡ ነፍስክሙ=ሰውነታችሁን ጠብቁ። የጎሥሥዋ ለነፍሰ ዝ ሕፃን የዚህን ሕፃን ሰውነት ይፈልጓታል። (ግብ. 2:41፤ ዘዳ. 4:15፤ ማቴ. 2:20)
ሕያው ፍጥረት፥
ሕያው ፍጥረት፥ ትንፋሽና ደመ ነፍስ ያለው፥ የሚላወስ፥ ተንቀሳቃሽ፤ ኩሉ ነፍስ ይሴብሑ ለእግዚአብሔር=ነፍስ ሁሉ እግዚአብሔርን ያመሰግነዋል፤ (መዝ. 150:6)
ከለዎቹም፥ ከበሬዎቹም፥ ከአህዮችም፥ ከመንጎችም ከእምስት መቶ አንድ ነፍስ አውጣ፤ ከዚህ ላይ ነፍስ አንድ ስጥ ማለት ነው፤
ከእስትንፋስ ጀምሮ እስከ ሕያዊት ነፍስ ድረስ ማለየቱን ለመረዳት እስከዚህ የተነገረውን እንመልከት።
ገ ነ ት
ገነት ተጋን፥ የተከል ቦታ፥ ብዙ ተክል የሚተከልበት የሚበቅልበት፥ ውኃ ገብ፥ ምንጭ የሚፈልቅበት፥ የታጠረ ለምለም ቦታ። (መሐ. 4:12፤ ዳን. 1:7፤ ዮሐ. 18:1፤ 19:41፤ 20:15፤ ዘፍ. 2:8)
ገሀነም ገሃነም፤
ከኢየሩሳሌም አጠገብ ያለ ሸለቆ፥ ቀድሞ የቆሻሻ መጣያ፥ ቆሻሻውን ለማቃጠልም ሁልጊዜ እሳት ይነድበት ነበር። ስለዚህ የገሃነመ እሳት ምሳሌ ሁኖ በመጻሕፍት ይነገራል።
ቃል ከትንሽ ነገር ይነሣና በምሳሌ፥ በዘይቤ፥ በዘዴ እየገነነ ይሄዳል። ብዙ ቃላት ከመንደር ተነሥተው ሀገራዊ ከዚያም፥ አህጉራዊ ብሎም ዓለም አቀፍ ይሆናሉ። ለምሳሌም ቅዱስ ልዩ ውሱን ነበረ በመጀመሪያ በኋላ ግን እየገነነ ሂዶ በመጀመሪያ ለደጋግ ለዎች በኋላ ግን የራሱ የፈጣሪ ቅጽል ሁኖ ቅዱስ እግዚአብሔር ይባላል፥ እንላለን። ራሱ አግዚአብሔርም ብዙ ሰም ነበረው፤ አምላክ፥ ገዥ፥ ጌታ፥ አምላከ ኩሉ፥ አጋዜ ኩሉ፥ ዐማዴ ኩሉ፥ እግዚአ ኩሉ ይባል ነበር፥ በመጀመሪያ በኋላ ግን የሀገር ጌታ የሚለው ተመረጠና እግዚአብሔር ጠና። ሰው ለአምላኩ ጥሩ ጥሩውን ቃል ስለሚለጥ ቅዱስ፥ ንጉሥ፥ ክቡር፥ ብፁዕ፥ ቡሩክ ወዘተ..የመላለሉትን ቃላት ለጥቶታል።

ምዕራፍ 34

ነፍስ፥ ነነት፥ መንግሥተ ሰማያትI

ይህ ምዕራፍ ነፍስ፥ ነነት፥ መንግሥተ ሰማያት፥ ገሃነም፥ ሲኦል የሉም ለሚሉ ሰዎች ለማስረዳ የቀረበ ነው።

ነ ፍ ስ

ነፍስ የሚለው ቃል ብዙ ትርጉም እንዳለው ባለፈው መፍትሔ ቃላት አስረድተናልI ከዚህ ግን ስለ ነባቢት፥ ለባቢት፥ ሕያዊት ነፍስ እናያለን።

እግዚአብሔር አምላክም ሰውን ከምድር አፈር አበጀው፥ በአፍንጫውም የሕይወት እስትንፋስ እፍ አለበት ሰውም ሕያው ነፍስ ያለው ሆነ። (ዘፍ. 2:7)

እግዚአብሔር አዳምን በፈጠረ ዕለት በእግዚአብሔር አምሳል አደረገውI (ዘፍ. 5:1-21) እግዚአብሔር ሕያው ነው እይሞትም፥ ስለዚህም ሰውን በአምሳሉ ፈጠረው ግለት ሰውም እንደ አምሳሉ እንደ እግዚአብሔር አይሞትም። በምድር ያለውን እንስሳ ሁሉ ሲፈጥር የሕይወት እስትንፋስ ሰጠው፥ ለዘለዓለም ሕያው እንዲሆንም አደረገው አላለም ሰውን ብቻ ነው እንዲህ ያለI ይሽውም በእግዚአብሔር እስትንፋስ በነፍስ ምክንያት ሰው አይሞትም ግለት ነው። ይህ ቁጥር ነፍስ ዘለዓለማዊት መሆንዋን በደንብ ያስረዳል።

እስዋም ስትሞትም ነፍስዋ በምትወጣበት ጊዜ ስሙን ቤንኢ ብላ ጠራችው (ዘፍ. 35:18)

ጳውሎስም ወርዶ በላዩ ላይ ወደቀ፥ እቅፎ፥ ነፍሱ አለችና አትንጫጩ አላችው (ግብ. 20:10)I.

ጌታ በምሳሌ ያስተማረው የአንድ ባለጸጋና የድኃው አልአዛር በሲኦልና በገነት ሁነው የተነጋገሩት ንግግርም እንደኛ ነፍስ፥ ሁለተኛ ሲኦል፥ ገሃነመ እሳት መኖራቸውን ያስረዳልI ይህ አንቀጽ ረጅም ስለሆነ ለእንባቢ ጠቅሰን እናልፋለን (ሉቃ. 16:19-31)

አምስተኛውንም ማኅተም በፈታ ጊዜ ስለ እግዚአብሔር ቃልና ስለጠበቁት ምስክር የታረዱተን ሰዎች ነፍሳት ከመሠዊያው በታች አየሁ። በታላቅ ድምፅም እየጮኽ፥ ቅዱስና እውነተኛ ጌታ ሆይ! እስከ መቼ ድረስ አትፈርድም? ደማችንስ በምድር በሚኖሩት ላይ እስከ መቼ ድረስ አትበቀልም? አሉ። ለእያንዳንዳቸውም ነጭ ልብስ ተሰጣቸው። እንደነሱም ደግሞ ይገድሉ ዘንድ ያላቸው የባሪያዎች ባልንጀሮቻቸውና ወንድሞቻቸው ቁጥር እስኪፈጸም ድረስ ገና ለጥቂት ዘመን እንዲያርፉ ተነገራቸው። ይህስ የነፍስን ሕያውነት አልፎ በወዲያኛው ዓለምም ጸሎትና ሽልማት እንዳለ ያስረዳል።(ራእ.6:9-11)

ሥጋንም የሚገድሉትን፥ ነፍስን ግን መግደል የማይቻላቸውን አትፍሩ፥ ይልቅስ ነፍስንም ሥጋንም በገሃነም ሊያጠፉ የሚችለውን ፍሩ። (ማቴ. 10:28)

ከዚህ ላይ ሊያጠፉ የሚለው ቃል በግሪክ የሚያሳየው ከገጸ እግዚአብሔር ከረድኤተ እግዚአብሔር ሊያርቅ፥ እርቆ በገሃነም ሊኮንን የሚችለውን ፍሩ ማለት እንጂ እሽቶ ብን አድርጎ ሊያጠፉ ማለት አይደለም፤ ማጥፋትማ ቢሆን ኑሮ ዕረፍት ነበር። ማጥፋት እንዳልሆነስ የሚከተሉት ጥቅሶች ያስረዳሉ።

እነዚያም ወደ ዘለዓለም ቅጣት፥ ጻድቃን ግን ወደ ዘለዓለም ሕይወት ይሄዳሉ። (ማቴ. 25:46፤ ማር. 9:48፤ ኢሳ. 66:24) በዚያም ዘመን በመጽሐፍህ ተጽፎ የተገኘው ሕዝብህ ሁሉ እያንዳንዱ ይድናል። በምድርም ትቢያ ውስጥ ያንቀላፉቱ ብዙዎች ይነቃሉ፥ እኩሌቶቹ ወደ ዘለዓለም ሕይወት፥ እኩሌቶቹም ወደ ዕፍረትና ወደ ዘለዓለም ጉስቁልና ጥበበኞቹም እንደ ሰማይ ፀዳል፥ ብዙ ሰዎችንም ወደ ጽድቅ የሚመልሱ እንደ ከዋክብት ለዘለዓለም ይደምቃሉ። (ዳን. 12:1-3)

የሰው ልጅ መላእክትን ይልካል፥ ከመንግሥቱም እንቅፋትን ሁሉ ዐመፅንም የሚያደርጉትን ይለቅማሉ፥ ወደ እቶነ እሳትም ይጥሏቸዋል፥ በዚያ ጥርሰ ግፋጩትም ይሆናል። በዚያን ጊዜ ጻድቃን በአባቶቻቸው መንግሥት እንደ ፀሐይ ያበራሉ። (ማቴ. 8:12፤ 13:50፤ 22:13፤ 24:51፤ 25:30፤ ማር. 9:43፤ 48፤ ሉቃ. 13:28፤ 1ጴጥ. 1:9፤ 2:11፤ 25፤ 4:19)

ከዚህ በላይ በተጠቀሱት ጥቅሶች የነፍስን መኖርና ዘለዓለማዊነት፥ ለባዊትነት፥ ነባቢትነት፥ የገሃነመ እሳትን፥ የገነትን፥ የሲኦልን፥ የመንግሥተ ሰማያትን መኖር ተረድተናል። ይህንም ለመረዳት የተጻፉትን ጥቅሶች መላልሶ ማንበብ ያሻል።

ነፍስ የምግባርና የሃይማኖት ስሜት መኖሪያ ናት። በሥጋ ውስጥ ነባቢት፥ ሕያዊት፥ ለባዊት እካል ነፍስ ስለሆነች የማንኛቸውም ስሜት መኖሪያ ነፍስ ናት። አንጎል የሚሠራውም በነፍስ ኀይል ነው፥ ለዚህም የሚከተሉት ጥቅሶች ይናገሩ፤

እናንተ ደካሞች ሸክሞችሁ የከበደ ሁሉ፥ ወደኔ ኑ እኔም አሳርፋችኋለሁ። ቀምበሬን በላያችሁ ተሸከሙ ከእኔም ተማሩ፥ እኔ የዋህ በልቤም ትሑት ነኝና፥ ለነፍሳችሁም ዕረፍት ታገኛላችሁ=ቀምበሬ ልዝብ ሸክሜም ቀላል ነውና። ከዚህም ነፍስንና መንፈስን ተለዋዋጭ አድርጎ መንፈሳችሁ ይረፍ ማለቱ ነው። ለዚህም የሚከተሉትን ጥቅሶች እነሆ፤ (ማቴ. 11:29፤)

የደከመችውን ነፍስ አርክቻለሁና፥ ያዘንችውንም ነፍስ ሁሉ አጥግቤአለሁና። (ኤር. 31:25)
እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፥ በመንገድ ላይ ቁሙ፥ ተመልከቱም፤ የቀደመችውንም መንገድ ጠይቁ፥ መልካሚቱ መንገድ ወዴት እንደሆነች ዕወቁ፥ በርሷም ላይ ሂዱ፥ ለነፍሳችሁም ዕረፍት ታገኛላችሁ። (ኤር. 6:16)
ያላመኑት አይሁድ ግን የአሕዛብን ነፍስ በወንድሞች ላይ አነሣሡ። (ግብ. 14:2) የሚከተሉት ጥቅሶችም የእነዚህ ጓደኞች ናቸው፤ (ግብ. 14:22፤ 15:24፤ ኤፌ. 6:6፤ ማቴ. 12:18፤ 26:38፤ መዝ. 6:4፤ ሉቃ. 12:19-20)

<u>ገነትና ሲኦል</u>

በፊት ገነትን አይተን ከዚያ ደግሞ ሌሎቹን መንግሥተ ሰማይን፥ ሲኦልን ገሃነመ እሳትን እንመለከታለን፤
ኢየሱስንም ጌታ ሆይ! በመንግሥትህ በመጣህ ጊዜ አስበኝ አለው። ኢየሱስም እውነት አልሃለሁ፥ ዛሬ ከኔ ጋራ በገነት ትሆናለህ አለው። (ሉቃ. 23:42)
እንዲህ ያለውንም ሰው አውቀዋለሁ፥ በሥጋ እንደሆነ ወይም ያ ለሥጋ እንደሆነ አላውቅም፥ እግዚአብሔር ያውቃል፤ ወደ ገነት ተነጠቀ፥ ሰውም ሊናገር የማይገባውን የማይነገረውን ቃል ሰማ። (2ቆሮ. 12:3-4) እናንተ ያባቴ ቡሩካን! ኑ ዓለም ከተፈጠረ ጀምሮ የተዘጋጀላችሁን መንግሥት ውረሱ። (ማቴ. 25:34፤ 6፤ ዮሐ. 5:29፤ ዳን. 12:2-3፤)

<u>መንግሥተ ሰማይ፤</u>

አዲስ ሰማይና አዲስ ምድርም አየሁ፤ የፊተኛው ሰማይና የፊተኛይቱ ምድር አልፈዋልና፥ ባሕርም ወደ ፊት የለም። ቅድስቲቱ ከተማ አዲሲቱ ኢየሩሳሌም፥ ለባልዋ እንደተሸለመች ሙሽራ ተዘጋጅታ ከሰማይ ከእግዚአብሔር ዘንድ ስትወርድ አየሁ--። (ራእ. 21:1-27)
ነገር ግን ጽድቅ የሚኖርባትን አዲስ ሰማይና አዲስ ምድር እንደ ቃሉ ተስፋ እንጠብቃለን፤ (2ጴጥ. 3:13)
እነሆ! አዲስ ሰማይና አዲስ ምድር እፈጥራለሁና፥ የቀደሙትም አይታሰቡም። (ኢሳ. 65:17-19)
በሲኦል በሥቃይ ላይ ሳለ አሻቅቦ አብርሃምን በሩቅ አየ--፤ (ሉቃ. 16:19-31፤ መዝ. 6:4)
ጌታ ሆይ! ጌታ ሆይ! የሚለኝ ሁሉ መንግሥተ ሰማያት የሚገባ አይደለም፤ (ማቴ. 7:21)

ገሃነም፥

ወደ እቶን እሳት (ገሃነመ እሳት) ይጥሏቸዋል፥ በዚያ ልቅሶና ጥርስ ማፋጨት ይሆናል።

ዐይንህ ብታሰናክልህ አውጣት፥ ሁለት ዐይን ኑሮህ ትሉ ወደ ማይሞትበት እሳቱ ወደማይጠፋበት ወደ ገሃነመ እሳት ከመጣል ዐንድ ዐይን ኑሮህ ወደ እግዚአብሔር መንግሥት መግባት ይሻልሃል። (ማር. 9:46-48)

ለዚህ ርእሰ የመደምደሚያ ምክር፤ ወንድሜ አንባቢ ሆይ! የኃጢአትህን ብዛት እያሰብህ ንስሓ በመግባት ፈንታ ራስህን ለግጥናናት ነፍስ የለም፥ ፍርድ የለም፥ ገነት፥ መንግሥተ ስማያት የሉም፥ ገሃነመ እሳት ሲኦል የለም እያልህ ራስህን ስትደልል ኑረህ የማይቀረው ሞት ሲመጣ ከሚፈረድብህ አሁኑኑ ሃይማኖት ከምግባር፥ ምግባር ከሃይማኖት የሚለውን ምዕራፍ አንበህ ፈጣሪህ ያዘጋጀልህን መንግሥት እንድትወርስ ትነገራለህ።

ምዕራፍ 35

ሃይማኖት ከምግባር፥ ምግባር ከሃይማኖት

ለወገበ ነጭና ለጥራዝ ነጠቅ ተግሪ ሃይማኖት ያለ ምግባር ወይም ምግባር ያለ ሃይማኖት የሚያድን ይመስለዋል። ግን ሁለቱም ካልተባበሩ አንዱ ብቻውን አያድንም። ሰባኪ አንድ እሑድ ስለሃይማኖት ይሰብክ ኑሮ እመኑ ትድናላችሁ ሲል የሰማ ምእመን እምነትን ተቀብያለሁ፥ አምኛለሁ መዳኔ ነው ብሎ ተቀምጦ ሳለ፥ በሚቀጥለው እሑድ ደግሞ ያው ሰባኪ ይሁን ወይም ሌላ አልታወቀም ደግ ሥሩ ትጸድቃላችሁ፥ ደግ ሥራ ያጸድቃል ሲል ሰማና የሚከተለውን ተቀኘ፤

አንዱ ይበቃል፥ የወንጌል ቃል
አለ መስጠት ያጸድቃል።

ይበል እንጅ መስጠት ያለ ሃይማኖት ብቻውን አያጸድቅም፤ ግመን መቀበል ጭምር እንጂ ብቻውን ግወቅ አይደለም። ግመን ግወቅ ብቻማ ቢሆን ኑሮ አጋንንት ሁሉ ኢየሱስ ክርስቶስ ወልደ እግዚአብሔር መሆኑን ያውቃሉና በጸደቁ ነበር።

ኢየሱስንም ከሩቅ ባየ ጊዜ ሩጦ ሰገደለትና በታላቅ ድምፅ እየጮኸ፥ የልዑል እግዚአብሔር ልጅ ኢየሱስ ሆይ! ከእንተ ጋር ምን አለኝ? እንዳትሠቃየኝ በእግዚአብሔር አምልሃለሁ አለ፤ በልዩ ልዩ ደዌም የታመሙትን ብዙዎቹን ፈወሰ፥ ብዙወቹንም አጋንንት አወጣ፥ አጋንንትም ክርስቶስ መሆኑን ዐውቀው ነበርና ሊናገሩ አልፈቀደላቸውም፤ (ማር. 1:34፤ 24፤ 5:6:7፤ ማቴ. 8:29፤ ሉቃ. 4:34፤ 8:28)

ይህ አገር አምኗል ሲባል የመንግሥቱን ሕግ፥ አስተዳደር፥ ሥልጣን=ዳኝነት ተቀብሎ እየገበረ ይኖራል ማለት ነው። ክርስቶስንም ማመን ትእዛዙን ተቀብሎ እሱን ተከትሎ መሄድ ነው። ስለዚህም ሃይማኖት ብቻውን እንደማያድን እሱም ተከታዮቹ ሐዋርያትም ፍርጥርጥ፥ ግልጥልጥ አድርገው በማያሻማ አነጋገር አስተምረዋል።

በሰማያት ያለውን ያባቴን ፈቃድ የሚያደርግ እንጂ፥ ጌታ ሆይ! ጌታ ሆይ! የሚለኝ ሁሉ መንግሥተ ሰማያት የሚገባ አይደለም። በዚያ ቀን ብዙዎች ጌታ ሆይ! ጌታ ሆይ! በስምህ ትንቢት አልተናገርንምን? በስምህስ አጋንንትን አላወጣንምን? በስምህስ ብዙ ተአምራት አላደረግንምን? ይሉኛል። የዚያን ጊዜ ከቶ አላውቃቸሁም፥ እናንተ ዐመፀኞች ከኔ ራቁ እላቸዋለሁ። (ማቴ. 7:21-27)

ጽድቃችሁ ከጽሐፍትና ከፈሪሳውያን ካልበለጠ መንግሥተ ሰማያት አትገቡም። (ማቴ. 5:20)

አንቀጸ ብፁዓንም የተነገረው ስለምግባር ነው፤ (ማቴ. ምዕራፍ 5:6:7፤) በጠቅላላ ምግባርና ሃይማኖት ምንና ምን እንደሆኑ ስማወቅ ስሚፈልግ አንባቢ የሚከተሉት ጥቅሶች ቀርበውለታል፤ (ዮሐ. 3:16-19፤ 6:29፤ 14:15፤ 21፤ 23፤ 24፤ ማቴ. 25:31-46፤ ሮሜ 2:6፤ 13፤ 1ዮሐ. 5:1-3፤ ያዕ. 2:17፤ 20፤ መዝ. 62:12፤ 1ጴጥ. 1:17፤ ዮሐ. 5:29፤ ገላ. 6:9፤ 2ተሰ. 2:3-13፤ ዕብ. 13:2፤ ዘፍ. 19:2፤ 1ጢሞ. 1:18፤ ያዕ. 2:14፤ 21፤ 25፤ 17)

<u>ስዚህ ርእስ መደምደሚያ</u>

ውድ በክርስቶስ ወንድሚ አንባቢ ሆይ! ሃይማኖት ከምግባር፥ ምግባር ከሃይማኖት አስተባብረህ ይዘህ ክርስቶስን ተከትለህ መንግሥቱን ለመውረስ ተነሥተሃል፤ ግን ሥርዐተ ረበናት በመንገድህ ዕንቅፋት ስሰሚሆንብህ እሱ ደግሞ በሚከተለው ምዕራፍ ይገለጥልሃልና አሽቀንጥረህ ጥለህ መደኅኒትህ ክርስቶስንና ለዚህ ፀረ ረበናት የሆነውን ዋነኛውን መምህር ቅዱስ ጳውሎስን እንድትከተል ትጠቆማለህ።

ምዕራፍ 36

ረበናት አፅራረ ክርስቶስ

ሥርዓተ ረበናት፤ ረቢ መምህር ሊቅ ማለት ነው፤ የዚህ ብዙ ረበናት ደግሞ መምህራን፥ ሊቃውንት ማለት ነበር። በኋላ ብዙ ጊዜ በስመ ሊቃውንት የራሳቸውን ጥቅም የሚያሳድዱ፥ እስ ከርሦሙ አምላኮሙ ስለበዙበት ይህ ቃል ከሊቅነት ከፀዋቂነት ወደ ፈሪሳዊነት ወደ ግብዝነትና አታላይነት ተሸጋገረ። በኋላም የጸሐፍትና የፈሪሳውያን የግብዞች መግለጫ ተጸውዖ ስም ሆነና ቁጭ አለ። አሁንም ከዚህ የሚቀርበው በዚህ ትርጉም ነው፤ የጌታችን ኢየሱስ ዋና ጠላቶች የነበሩም እነዚህ ናቸው። ፈሪሳዊነት ግብዝነትን ሲፈልግ፤ ጌታ ግን በጸሎት ክፍል እንዳየነው በጎቡአ፥ በስውር ከአምላክህ ጋራ ተገናኝ፥ አምላክህ ኩላሊት ያመላለሰውን፥ ልቡና ያሰበውን ያውቃልና በስውር ሥራ አለና ቁጭ አለ። በዚህም ለብዙ ዘመናት በእስራኤል የተጠራቀመውን ትውፊት (ዘእንበሩ አበው) ናደና ዐረፈ። በዚህም ጥቅማችን ተነካ፥ ዕውቀታችን ተናቀ የሚሉ አይሁድ ተነሡበት። ለጊዜው አይሁድ ያገረማሩ እንጂ፥ ሥርዓተ ረበናት በክርስቶስ ትምህርትና በተከታዮቹ ሐዋርያት ስብከት መናዱ አልቀረም።

ፈሪሳዊነትና ክርስቶስ፤

በቅድሚያ መጀመሪያ ከተከታዮቹ በፊት ራሱ ጌታ ፈሪሳዊነትን ወይም ሥርዓተ ረበናትን ምን እንዳደረገው እናያለን፤ በዚያ ጊዜ ኢየሱስ ለሕዝቡና ለደቀ መዛሙርቱ እንዲህ ብሎ ነገራቸው፥ ጸሐፍትና ፈሪሳውያን በሙሴ ወምበር ላይ ተቀምጠውላችኋል፥ ያዘዙአችሁን ሁሉ አድርጉ፥ ጠብቁም፥ ግን የሚናገሩትን አይሠሩትምና እንደ ሥራቸው አታድርጉ። ከባድና አስቸጋሪ ሸክም ተብትበው በሰው ትከሻ ይጭናሉ፥ እነሱ ግን በጣታቸው እንኳ አይነኳትም ለሰውም እንዲታዩ ሥራቸውን ሁሉ ያደርጋሉ፤ አሸን ክታባቸውን ያሰፋሉ፤ ዘርፉንም ያስረዝማሉ፥ በምሳም የከበሬታ ስፍራ፥ በምኩራብም የከበሬታ ወምበር፥ በገበያም ሰላምታና፥ መምህር ሆይ! መምህር ሆይ! ተብለው ሊጠሩ ይወዳሉ። እናንተ ግን መምህር ተብላችሁ አትጠሩ፥ መምህራችሁ አንድ ስለሆነ፥ እናንተም ሁላችሁ ወንድማማች ናችሁ። አባታችሁ አንዱ እሱም የሰማዩ ነውና በምድር ላይ ማንንም አባት ብላችሁ አትጥሩ። ሊቃችሁ አንድ አሱ ክርስቶስ ነውና። ሊቃውንት ተብላችሁ አትጠሩ። ከእናንተም የሚበልጠው አገልጋያችሁ ይሁን። ራሱን ከፍ ከፍ የሚያደርግ ሁሉ ይዋረዳል፥ ራሱንም የሚያዋርድ ሁሉ ከፍ ይላል።

እናንተ ግብዞች ጸሐፍትና ፈሪሳውያን፥ መንግሥተ ሰማያትን በሰው ፊት ስለምትዘጉ፥ ወዮላቸሁ፥ እናንተም አትገቡ፥ የሚገቡትንም አታስገቡ። እናንተ ግብዞች ጸሐፍትና ፈሪሳውያን በጸሎት ርዝመት እያመካኛችሁ የመበለቶቹን ቤት ስለምትበሉ፥ ወዮላችሁ፤ ስለዚህም የባሰ ፍርድ ትቀበላላቸሁ። እናንተ ግብዞች ጸሐፍትና ፈሪሳውያን፥ አንድ ሰው ልታሳምኑ በባሕርና በየብስ ስለምትዞሩ፥ በአመነም ጊዜ ከእናንተ ይልቅ ሁለት ዕጥፍ የባሰ የገሃነም ልጅ ስለምታደርጉት ወዮላችሁ። እናንተ ዕውራን መሪዎች ትንኝን የምታጠሩ ግመልንም የምትውጡ። እናንተ ግብዞች ጸሐፍትና ፈሪሳውያን በውስጡ ቅሚያና ሥሥት ሞልቶ ሳለ የጽዋውንና የወጭቱን ውጭ ስለምታጠሩ ወዮላችሁ። አንተ ዕውር ፈሪሳዊ ውጭው ደግሞ ጥሩ እንዲሆን አስቀድመህ የጽዋውንና የወጭቱን ውስጡን አጥራ። እናንተ ግብዞች ጸሐፍትና ፈሪሳውያን በውጭ እምረው የሚታዩ በውስጥ ግን በሙታን ዐጥንትና በርኩሰትም የተሞሉ፥ በኖራ የተለሰኑ መቃብሮችን ስለምትመስሉ፥ ወዮላችሁ። በውጭ ለሰው ጻድቃን ትመስላላቸሁ፥ ስትመስሉ፥ በውስጥ ግን ግብዝነትና ዐመፀኝነት ተሞልታችኋል።

እናንተ እባቦች የእፉኝት ልጆች ከገሃነም ፍርድ እንዴት ታመልጣላችሁ? እነሆ፥ ነቢያትንና ጠበብት ጸሐፊዎችንም ወደ እናንተ አልካለሁ፥ ከእነሱም ትገላላችሁ፥ ትሰቅሉግላችሁ፥ ከእነሱም በምኩራባችሁ ትገርፋላችሁ፥ ከከተማም ወደ ከተማ ታሳድዳላችሁ። ጸሐፍትና ፈሪሳውያን ከነግብዝ ትምህርታቸው ምን እንደሆኑ ለማወቅና በዘመናችን ደግሞ እነግንን እንደሚመስሉ ለማስተዋል የሚከተሉትን ጥቅሶች ልብ እድርጎ ያነቧል፤ (ማቴ. 23:1-35፤ 6:1-18፤ ማር. 12:38-40፤ ሉቃ. 11:37-52፤ 2:45-47)

ይህ ለሥራቸው፥ ለእካሄዳቸው ለግብዝነታቸው ሲሆን፥ ለጸሎት ደግሞ፤ (ማቴ. 6:5-14፤ ለጸም 16-18፤ ማቴ. 7:15-19፤ 15:1-20፤ 16:5-12፤ ሉቃ. 12:1-12፤ 11:37-54)

ሥርዐተ ረበናት ከነግሥንግሡ አልፎ፥ ቀላሏ ሕገ ወንጌል ተተክታለች። ክርስቲያን ክርስቶስን በመክተል እንጂ አሪትን በመፈጸም አይደለም። ከአሪት ዐሠርቱ ቃላት ተፈጸሙ እንጂ አልተሻሩም። እነሱም እነግን እንደሆኑ ጌታ ራሱ ተርጉሟቸዋል፤ (ማቴ. 5:17-48) የሐዲሱ መምህር ሊቁ ሊቀ ሊቃውንት መሓሪ ትርፌም (በኋላ የጎንደር ሊቀ ጳጳሳት) የአርቶዶክሳውያን ምእመናን እምነት በሚለው መጽሐፋቸው ዐሠርቱ ቃላትን ተርጉመዋል።

የተቀረውን ግን ሕገ አሪትን ተቀብለው የነበሩ ሰዎች በወግ ጠራቂነት እየተንገታገቱ ያስተላለፉት ነው። ጌታም እንሥቶታል፥ ሐዋርያትም ፍቀውታል፤

እናንተ ደካሞች ሸክማችሁ የከበደ ሁሉ፥ ወደ እኔ ኑ፥ እኔም አሳርፋችኋለሁ። ቀምበሬን በላያችሁ ተሸከሙ፥ ከኔም ተማሩ፥ እኔ የዋህ ልቤም ትሑት ነውና። ለነፍሳችሁም ዕረፍት ታገኛላችሁ፥ ቀምበሬም ልዝብ ሸክሜም ቀላል ነውና። (ማቴ. 11:28-30፤ 19:3-9)

ከእሕዛብ ወደ ክርስትና የገቡት አዲስ አማንያንም ሥርዐተ ረበናትን ካልጠበቁ፥ ቀዳሚትን ካላከበሩ፥ ካልተገዘሩ፥ ሴትም ወልዳ ወይም የወር አበባዋ ሲመጣ ሥርዓተ ንጽሕን ካልጠበቀች አይድኑም የሚል ክርክርና ጭቅጭቅ ሰለተነሣ ሐዋርያት ተሰብስበው የሚከተለውን ውሳኔ ሰጥተዋል፤

እንግዲህ አባቶቻችንና እኛ ልንሸከመው ያልቻልነውን ቀምበር በደቀ መዛሙርት ጫንቃ ላይ በመጫን እግዚአብሔርን አሁን ለምን ትፈታተኑታላችሁ? በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋ እንደነሱ እንድን ዘንድ እንመን እንጂ። (ግብ. 15:10-11)

ስለዚህ ከእሕዛብ ወደ እግዚአብሔር የዞሩትን እንዳናስቸግራቸው፥ ነገር ግን ከጣዖት ርኩሰትና ከዝሙት ከታነቀም ከደምም ይርቁ ዘንድ እንድንጽፍላቸው እመሰናለሁ። (ግብ. 15:19።)

አሪት ከነከህነቷ፥ ሥርዐተ ረበናት ከነዝግንትሉ አልፈዋል፤ ከፈሪሳውያንና ከሰዱቃውያን እርሾ ተጠንቀቁና ተጠበቁ አላቸው፤ እነርሱም ከሰዱቃውያንና ከፈሪሳውያን ትምህርት እንጂ ከእንጀራ እርሾ እንዲጠበቁ እንዳሳሳቸው ያን ጊዜ አስተዋሉ፤ (ማቴ. 16:6፤ 12፤ ግብ. 15:10-35፤ ሮሜ 3:20፤ 28)

እኔንም በክህነት እንዲያገለግሉኝ ትቀድሳቸው ዘንድ የምታደርግባቸው ነገር ይህ ነው፤ ነውር የሌለባቸውን እንድ ወይፈንና ሁለት አውራ በጎች ትወስዳለህ፥ ቂጣ እንጀራ፥ በዘይትም የተሰወሰ የቂጣ እንጎቻ፥ በዘይትም የተቀባ ሥሥ ቂጣ ከመልካም ስንዴ ታደርጋለህ...(ዘፀ. 29:1-46፤ ዘዳ. 24:...)

ከዚህ በላይ የተጠቀሰው ሥርዓተ ክህነት እንደ ተሻረ ሥርዓተ ንጽሕ፥ ሴት ስትወልድ ትረክሳለች የሚለው ሥርዓተ ረበናትም አብሮ በክርስቶስ ሞት አልፏል።

በማቴ. 19:3-11፤ ማር. 10:2-12፤ ላይም የፍችን ሥርዓት ለውጧል። ሐዋርያትም ጌታን ተከትለው ሥርዓተ ረበናትን መንግሰው ሰመጣል ሲጋደሉ እንደኖሩ የሚከተሉት ጥቅሶች ያስረዳሉ። ሰው በኢየሱስ

ክርስቶስ በማመን እንዲጸድቅ እንጂ በአሪት ሥራ እንዳልሆነ ዐውቀን፥ ሥጋን የለበሰ ሁሉ በአሪት ሥራ ስለማይጸድቅ እኛ ራሳችን በአሪት ሥራ ሳይሆን በክርስቶስ እምነት እንጸድቅ ዘንድ በክርስቶስ ኢየሱስ አምነናል። (ገላ. 1:6-10፤ 2:16-21፤ 3:9-14፤ 21-29፤ 6:12-18፤ ዕብ. 7:11-28፤ 8:6-13፤ 9:9-15፤ 10:9)

ለመሆኑ ረበናት (ጻሐፍት ፈሪሳውያን) ምን ይመስላሉ? እነሱማ እነዚህን ናቸዋ!

እንደነዚህ ያሉ ሰዎች የክርስቶስን ሐዋርያት ለመምሰል ራሳቸውን እየለወጡ፥ ውሸታሞች ሐዋርያትና ተንኰለኞች ሠራተኞች ናቸውና፥ ይህም አያስደንቅም ሰይጣን ራሱ የብርሃንን መልአክ ለመምሰል ራሱን ይለውጣልና። (2ቆሮ. 11:13-15) ከውሾች ተጠበቁ፥ ከክፉዎችም ሠራተኞች ተጠበቁ፥ ከሐሰተኞም መገረዝ ተጠበቁ። (ፊል. 3:2)

ቅዱስ አትናቲዎስም በውስጡ ትሕትናና ፍቅር ያለበትን ወንጌልን አንያዝ፥ በውስጡ ስለ ነፍስ የነፍስ ቤዛ የሚሆን የሞት ፍርድ ያለበትን አሪትን ግን አንተው ብሏል።

<u>ግዝረት</u>

ምንም በአምላክ ትእዛዝ ቢመሠረትም በጥምቀት ተተክቶ ግዝረትም ከሥርዓተ ረበናት ጋራ አልፏል፤ ሕገ አሪትንና ልማደ አረማውያንን የሚያከብሩ ሰዎች አሁንም ይገዘራሉ። ለጤናና ለተግባር ጥሩ ነው የሚሉ አሉ። በሃይማኖት ግን ዋጋ የለውም። ጥንቱን በሥርዓቱ የእስራኤላዊነት ምልክት ነበረ፤ ክርስቶስ ከመጣ በኋላ ግን በጥምቀት ተተክቷል። ተግባራዊነቱን የሚፈልግ ከመጠመቁ በፊት ቢገረዝ ምንም አይደል። ከጥምቀት በኋላ ግን የኋሊት መሄድ ስለሆነ ክልክል ነው። ብቻ ለእያንዳንዱ እግዚአብሔር እንደ ከፈለለት፥ እያንዳንዱም እግዚአብሔር እንደጠራው እንዲሁ ይመላለስ። እንዲሁም በአብያተ ክርስቲያናት ሁሉ እደነግጋለሁ። ግንም ተገርዞ ሳለ ተጠርቶ እንደሆነ ወደ አለመገረዝ አይመለስ፤ ግንም ሳይገረዝ ተጠርቶ እንደሆነ፥ አይገረዝ። መገረዝም ሆነ አለመገረዝ ከንቱ ነው፥ የእግዚአብሔርን ትእዛዝ መጠበቅ ነው እንጂ፤ እያንዳንዱ በተጠራበት መጠራት እንዲሁ ይኑር። (1ቆሮ. 7:17-24፤ ገላ. 5:6፤ 6:15፤ ኤፌ. 2:11)

<u>ለዚህ ርእስ መደምደሚያ</u>፥ ውድ እንባቢ ሆይ! የባልቴት ተረት የመሰለ ሥርዓተ ረበናትን አሽቀንጥረህ ጥለህ ክርስቶስን ተከተል።

ምዕራፍ 37

ቅዱሳት መጻሕፍት

ቅዱሳት መጻሕፍት ሁሉ በእግዚአብሔር መንፈስ የተጻፉ ናቸው፤ የእግዚአብሔር መንፈስ ሠራተኛ፥ ደራሲው ምሣር ወይም ግጥያ ሁነው ነው በመላ የተደረሱት። ለእነርሱም ከሰማይ በተላከ በመንፈስ ቅዱስ ወንጌልን በሰበካችሁ ሰዎች አሁን ባወራላቸሁ ነገር እናንተን እንጂ ራሳቸውን እንዳላገለገሉ ተገለጠላቸው፤ ይህንም ነገር መላእክቱ ሊመለከቱ ይመኛሉ። (1ጴጥ. 1:11-12) ይህን በመጀመሪያ ዕወቁ፥ በመጽሐፍ ያለው ትንቢት (አባባል) ሁሉ ከራሱ አይመነጭም፥ ትንቢት ከቶ ከሰው ፈቃድ አልመጣምና፥ ከእግዚአብሔር ተልከው ቅዱሳን ሰዎች በመንፈስ ቅዱስ ተነድተው ተናገሩት እንጂ (2ጴጥ. 1:20-21) በእግዚአብሔር መንፈስ የተጻፈ መጽሐፍ ሁሉ ለእግዚአብሔር ሰው ፍጹምነትና ለበጎ ሥራ የተዘጋጀ ይሆን ዘንድ፥ ለትምህርት፥ ለተግሣጽ ልብን ለማነቃቃት ለማረም በጽድቅ ላለች ሥልጠናና ለደግ ሥራ ሁሉ ይጠቀማል። (2ጢሞ. 3:16-17) በእግዚአብሔር መንፈስስ ተጻፉ ቁጥራቸውና አመጣጣቸውስ እንዴት ነው? ለሚል ጠያቂ፥ ቁጥራቸውን ከዚህ እንቀጥላለን፥ አመጣጣቸው ግን ረጅም ስለሆነ በሌላ መጽሐፍ ይቀርባል። በፕሮቲስታንቱ ዓለም 66፥ በሌሎች አርቶዶክሳውያንና በሮም አብያተ ክርስቲያን 79 በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን እንደ ፍትሐ ነገሥቱ አንቀጽ ደግሞ 81 ናቸው። እነሱም፤

የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት

አሪት ዘፍጥረት	ዕዝራ ሱቱኤል	ሰቆቃወ ኤርምያስ
አሪት ዘፀአት	ዕዝራ ካልዕ	ተረፈ ኤርምያስ
አሪት ዘሌዋውያን	ጦቢት	ባሮክ
አሪት ዘኁልቅ	ዮዲት	ሕዝቅኤል
አሪት ዘዳግም	አስቴር	ዳንኤል
ኢያሱ ወልደ ነዌ	አንደኛ መቃብያን	ሶስና
መሳፍንት	ሁለተኛ መቃብያን	ተረፈ ዳንኤል
ሩት	ሦስተኛ መቃብያን	ሆሴዕ
ቀዳማዊ ሳሙኤል	ኢዮብ	አሞጽ
ዳግማዊ ሳሙኤል	መዝሙር	ሚኪያስ
አንደኛ ነገሥት	ምሳሌ	ኢዮኤል
ሁለተኛ ነገሥት	ተግሣጽ	አብድዩ
አንደኛ ዜና መዋዕል	ጥበብ	ዮናስ
ሁለተኛ ዜና መዋዕል	መክብብ	ዕንባቆም
ኩፋሌ	መሐልየ ሰሎሞን	ሶፎንያስ
ሔኖክ	ሚራክ	ሐጌ
ዕዝራ	ኢሳያስ	ዘካርያስ
ነህምያ	ኤርምያስ	ሚልክያስ

<u>የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት፡</u>

ማቴዎስ	አንደኛ ተሰሎንቄ	ያዕቆብ
ማርቆስ	ሁለተኛ ተሰሎንቄ	ይሁዳ
ሉቃስ	አንደኛ ጢሞቴዎስ	ራእየ ዮሐንስ።
ዮሐንስ	ሁለተኛ ጢሞቴዎስ	
ግብረ ሐዋርያት	ቲቶ	
ሮሜ	ፊልሞና	
አንደኛ ቆሮንቶስ	ዕብራውያን	
ሁለተኛ ቆሮንቶስ	አንደኛ ጴጥሮስ	
ገላትያ	ሁለተኛ ጴጥሮስ	
ኤፌሶን	አንደኛ ዮሐንስ	
ፊልጵስዩስ	ሁለተኛ ዮሐንስ	
ቆላስዩስ	ሦስተኛ ዮሐንስ	

ከቀድሞ ጀምሮ በፍትሐ ነገሥቱ የታዘዘው የ81 መጻሕፍት ቁጥር ይህ ሲሆን አሁን ግን በግዕዝ የተጻፉ አዋልድና ሊቃውንት ሰምን ይቀራሉ ብለው ነው መሰለኝ በ1980 በሲኖዶሱ ፈቃድ በኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር አሳታሚነት በታተመው መጽሐፍ ቅዱስ 93 ደርሷል። በዚሁ እትም ላይም ሌላም አሻሽለን እንጨምራለን ብለው ቃል ሰለገቡ፡ እነሰይፈ መለኮት፡ እነሠኔ ጎልጎታ፡ እነአርጋኖን፡ እነውዳሴ አምላክ ወዘተ..የመሳሰሉት እንደሚጨመሩ ባለሙሉ ተስፋ ነን። መጽሐፈ ባልቴትስ ቢሆን ከልፋፊ ጽድቅ ጋራ በገዛ ሀገሩ ቢጨምር ምንአለበት?

<u>ለዚህ ርእስ መደምደሚያ</u>፡ በደንብ ላጠናትና ለተረዳት ቀና ሰው ለጭቅጭቅ ካልሆነ በቀር ወንጌል ትበቃለች። ደጋፊዎችም 81 መጻሕፍት እንጂ ልፋፊ ጽድቅና አብሮኮሮስ አይደሉም።

ምዕራፍ 38

ሀብተ ክህነት

ካህናት (ቀሳውስት) በሐዋርያት ቀደምትነት ድውይ ፈውሱ፥ ለምጻም እንጹ፥ ሙት አንሡ፥ ኃጢአት አስተስርዩ ተብሎ ከጌታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ ሥልጣን ተሰጥተው ተሹመዋል። ዓለምን እየዞራቸሁ አስተምሩ እኔም እስከ ዓለም ፍጻሜ አብራአችሁ ነኝ፥ አልለያችሁም ብሎም ክህነቱ በእነሱ ከእነሱም በኋላ ለልጅ ልጅ የሚተላለፍ እንዲሆን ተስፋ ተሰጥተዋል። ይህም ዘለዓለማዊ ቃል ኪዳን ነው። እንደ ተስፋውም ዓለምን ዙረው አስተምረው፥ ድውይ ሲፈውሱ ሙት ሲያነሡ ኑረው የቀደሙት አልፈዋል። እንዲሁም እየሆነ ከዘመናችን ሥልጣኑና ሥርዓቱ ደርሷል። ይህንም የሚከተሉት ጥቅሶች ያስረዳሉ። (ማቴ. 10፤ ማር. 3:13-19፤ ሉቃ. 6:12-16፤ 9:11)

ማሰርና መፍታትም እንደሚቻላቸው እነሆ፥ (ማቴ. 16:18-19፤ 18:18፤ ዮሐ. 20:23) የማሰሩንና የመፍታቱ ሥልጣን ግን የተለጠው በጌዶ እንጂ እንዲያው ከቀለሰሁ ብሎ ያለ በቂ ምክንያት አንዳንድ ወፈ ገዝት ቄስ እንደሚያደርገው ደርሶ ለመገዘት አይደለም። ከግዝት በፊት ማስተማር፥ መምከር፥ መነጋገር፥ መከራከር ይቀድማል። ከሃይማኖትና ከወሠርቱ ቃላት ውጭ ያልሆነ ለው ፥ ባዓል ሻርህ፥ ጸም ገደፍህ ተብሎ አይገዘትም። የግዘቱም ሥርዓት የሚፈጸመው በአውራጃው ያሉ ካህናት ተሰብስበው ቢእንስ እንድ ጳጳስ ባለበት ነው እንጂ፥ ግንም አልፎ ሂያጅ ቄስም ይሁን ባሕታዊ ገዝቻለሁ ሊል አይችልም።

ወንድምህም ቢበድልህ፥ ወይም ቢበድል ሂደህ እንተና እሱ ብቻችሁን ሁናችሁ ውቀለው፥ ቢሰማህ ወንድምህን አተረፍህ፥ ባይሰማህ ግን፥ በሁለት ወይም በሦስት ምስክር አፍ ነገር ሁሉ እንዲጸና፥ ዳግመኛ እንድ ወይም ሁለት ከእንተ ጋራ ውሰድ፥ እነርሱንም ባይሰማ፥ ለቤተ ክርስቲያን ንገራት፥ ደግሞም ቤተ ክርስቲያንን ባይሰማት እንደ አረመኔና እንደ ቀራጭ ይሁንልህ። (ማቴ. 18:15-17) ብሎ ነው ሥልጣኑን የሰጠው። ዳግመኛም፥ ወንድምህ ቢበድልህ ገሥጸው፥ ቢጸጸትም ይቅር በለው፥ በቀንም ሰባት ጊዜ እንኳ ቢበድልህ፥ በቀንም ሰባት ጊዜ ተጸጸትሁ እያለ ወደ እንተ ቢመለስ፥ ይቅር በለው። (ሉቃ. 17:3)

ወንድምህን በልብህ አትጥላው፥ በባልንጀራህ ምክንያት ኃጢአት እንዳይሆንብህ፥ ገሥጸው፤ አትበቀልም፥ በሕዝብህም ልጆች ቂም አትያዝ ነገር ግን ባልንጀራህን እንደራስህ ውደድ። (ሌዋ. 19:18)

የግዝት ሥርዓቱ ይህ ከሆነ አንዳንድ ቄሶች በሆነ ባልሆነው ይገዝታሉሳ? ለሚል ጠያቂ፥ እነዚህ የጻሕፍት የፈሪሳውያን የረበናት አንጂ የክርስቶስ ተከታዮች አይደሉም። ፈሪሳዊነትን አንጂ ወንጌልን አያውቋትም ከግለት በቀር ሌላ መልስ የለም። እንዲህ ካለው ቄስ መሸሽ፥ ንስሓ አባት እንደሆነም መሰናበት፥ በእልክ ከእግዚአብሔር ከመለያየት በፊት ያለዚያ ብዙዎች የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተከታዮች የነበሩ እየጠፏት እንደሄዱት ትሆናለህ።

<u>የህብተ ክህነት ውሳኔ</u>

ቤተ ክርስቲያንን ለማገልገል፥ ሕዝቡን፥ መሃይምናኑን ለማስተማር፥ ሰማሪ ለመፍታት ለመቀደስ፥ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለሐዋርያት ከዚያም ለተከታዮቻቸው ካህናት የሰጠውን ሥልጣን የሚያሳየው ትምህርት ህብተ ክህነት ወይም ሥልጣነ ክህነት፥ ምስጢረ ክህነት ይባላል። ማስተማር ኢየሱስ ክርስቶስ ነው ብሎ አምኖ በጸጋ እግዚአብሔር አብ ለተወለደ ሁሉ መብቱም ግዴታውም ነው። ቢያስተምር ዋጋ ያገኛል፥ ባያስተምር ይወቀሳል። ማሰር መፍታት ግን ከላይ እንዳየነው ለካህናት የተሰጠ ሥልጣን ነው። እሱም የሚተላለፈው ከአባት ወደ ልጅ በአንብሮ እድ ነው፥ ይሽም ዘርዐ ክህነት ይባላል። ሕጋዊ ክህነት ከጌታ ጀምሮ እስከ ዘመናችን በመወራረስ መምጣት አለበት። ክህነት በአሪትም ነበር፥ የመጀመሪያው የእስራኤል ሊቀ ካህናትም አሮን ነበረ። ይህም በእግዚአብሔርና በእስራኤል መካከል ያለ አገልጋይ ማለት ነው። እንደ ዘመነ ሐዲሱ ካህን ግን የማሰርና የመፍታት ሥልጣን አልነበረውም፥ ርግጥ የማማለድና የበደል ኃጢአት ቁርባን ያቀርባል፥ ኃጢአትህም ተሰርዮልሃል ይላል። ኃጢአትህን ይቅር ብዬሃለሁ አይልም ነበር። ህብተ ክህነትን ግን ለማን ሰጠ? እንዴት ተጀመረ? ለሚል መልሱ ይከተላል፤ የመሠረተው ራሱ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው፤ መጀመሪያ በቅዱስ ጴጥሮስ እንደራሴነት ለጴጥሮስ፥ ከዚያ ለሐዋርያት፥ ከዚያ ለካህናት፤ እነሆ ላንተ የመንግሥተ ሰማያትን መክፈቻዎች እሰጥሃለሁ፥ በምድር ያሰርኸው በሰማይ የታሰረ ይሆናል፥ በምድር የፈታኸው በሰማይ የተፈታ ይሆናል ብሎ (ማቴ. 16:19፤ 18:18)። ሙቶ ከተነሣ በኋላም ለዐሥሩ ሐዋርያት በተዘጋ ቤት ገብቶ በሰማይና በምድር ሥልጣን ሁሉ ተሰጥቶኛል፥ አብ እንደላከኝ፥ እኔም እናንተን እልካችኋለሁ። ወደ ዓለም አሕዛብ ሁሉ ሂዱና በአብ፥ በወልድ፥ በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቃችሁ የኔ ደቀ መዛሙርት አድርጓቸው፥ ለዚህም መንፈስ ቅዱስን ተቀበሉ ብሎ እፍ አለባቸውና፥

እናንተ የሰዎቹን ኃጢአት ይቅር ብትሉ ይቅር ይባልላቸዋል፥ እናንተ የሰዎቹን ኃጢአት ይቅር ባተሉ ግን ይቅር አይባልላቸውም ብሎ ለመጨረሻና ለዘለዓለም ሾማቸው። (ማቴ. 28:19፤ ዮሐ. 20:19-23) ይህ ትእዛዝ ደስ የማይላቸው ሰዎች እኔ ለምን በቀጥታ ለጌታ አልነግረውም ይላሉ። ሃይማኖት መታዘዝ እንጂ ፍልስፍና ቢሆን ናሮ ደራሲውም በተስማማ ነበር።

<u>ክህነት ሦስት መዓርጋት አሉት</u>፤ ዲቁና፥ ቅስና፥ ጵጵስና። የሚሰጡትም አንድ ጊዜ ብቻ ነው፥ አይከለሱም፥ አይታደሱም። እነዚህ ሦስቱ መንፈሳውያን መዓርጋት ናቸው፥ የሚሰጡትም በአንብሮ እድ ነው። የቀረው ግን ሊቀ ዲያቆን፥ ሊቀ ካህናት፥ ፓትርያርክ ቢባል አስተዳደር እንጂ መዓርገ ክህነት አይደለም።

ዲያቆንና ቄስን አንድ ጳጳስ ብቻ ይሾመዋል፥ ጳጳሱን ግን ሦስት ጳጳሳት መሆን አለባቸው።

ምዕራፍ 39

ሚመተ ምእመናን

በእሪት የክህነት ሥልጣን ከሊቀ ካህናቱ ጀምሮ እስከ ዐቃቤ ኖኅቱ ድረስ በዘር ሊኖሚነቱን ቆጥሮ ነበረ የሚሰጠው፥ በሐዲስ ግን ገና በነቢያት እነደ ተነገረ ክርስቶስን የተቀበለ ሁሉ ካህን ነው። ለማስተዳደር እንዲመች ግን በኋላ በለበው በእንብሮ እድ የሚሰጡ ሦስት መዓርጋተ ክህነት ሰጥታ ቤተ ክርስቲያን እበጅታለች። እነሱም ዲቁና ቅስና ጵጵስና ናቸው። ምንም እነዚህ ለእገልግሎት ዝብርቅርቅ እንዳይል መዓርጋት ይሰጡ እንጂ ማስተግርና መዘመር፥ ማገልገል ኢየሱስን ክርስቶስ ነው ብሎ አምኖ በመቀበል የእግዚአብሔር አብ ልጅ ለሆነ ሁሉ መብቱም ግዴታውም ነው። ተወልዶ ብልጫ እንከሰ ሩጫ የለምና፤

ለዚህም እናንተ ግን የእግዚአብሔር ካህናት ትባላላችሁ፥ ሰዎችም የአምላካችን አገልጋዮች ብለው ይጠሯችኋል። (ኢሳ. 61:6)

ሥራቸውንና አሳባቸውን ዐውቄዋለሁና አሕዛብንና ልሳናትን ሁሉ የምሰብክበት ጊዜ ይደርሳል፥ እነርሱም ይመጣሉ ክብሬንም ያያሉ። በመካከላቸውም ምልክት አደርጋለሁ...። ካህናትና ሌዋውያን እንዲሆኑ ከእነሱ እወስዳለሁ ይላል እግዚአብሔር። (ኢሳ. 66:18-21)

መልእኩም መልሶ ሴቶችን አላቸው፥ እናንተስ አትፍሩ የተሰቀለውን ክርስቶስን እንደምትሹ አውቃለሁና እንደ ተናገረ ተነሥቷልና በዚህ የለም፥ የነበረበትን ስፍራ ኑና እዩ፥ ፈጥናቸውም ሂዱና፥ ከሙታን ተነሣ፥ እነሆም፥ ወደ ገሊላ ይቀድማችኋል፥ በዚያም ታዩታላችሁ ብላቸው ለደቀ መዛሙርቱ ንገሯቸው...። በዚያን ጊዜ ኢየሱስ አትፍሩ፥ ሂዳችሁ ወደ ገሊላ እንዲሄዱ ለወንድሞቼ ተናገሩ፥ በዚያም ያዩኛል አላቸው። (ማቴ. 28:5-10)

በዚህም በነቢዩ በኢሳያስ ትንቢት መሠረት፥ መልእኩም ጌታም ሴቶች እንዲያስተምሩ አዝዘዋቸዋል፥ ሹመዋቸዋል። ከልዩ ልዩ ደዌ የፈወሳቸውንም እየዞሩ እንዲያስተምሩ ይፈቅድላቸው፥ ያዝዛችው ነበር፤ ሂዶም ኢየሱስን እንዴት ያለ ታላቅ ነገር እንዳደረገለት ዐሥር ከተማ በሚባል አገር ይሰብክ ጀመር፥ ሁሉም ተደነቁ (ማር. 5:19-20)

በእምነት በኩል ሁላችሁም በክርስቶስ ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጆች ናችሁና፥ ከክርስቶስ ጋራ አንድ ትሆኑ ዘንድ የተጠመቃችሁ ሁሉ ክርስቶስን ሰብካችኋልና። በእሱም አይሁዳዊ ወይም ግሪክ የለም፥ ባሪያ ወይም ጭዋ የለም፥ ወንድም ሴትም የለም፥ ሁላችሁ በክርስቶስ ኢየሱስ አንድ ናችሁና። (ገላ. 3:26-29)

በጥበብ ሁሉ እርስበርሳቸሁ አስተምሩና ገሥጹ በመዝሙርና በዝማሬ፥ በመንፈሳዊ ቅኔ በጸጋው በልባችሁ ለእግዚአብሔር ዘምሩ፥ እግዚአብሔር አብን በእሱ እያመሰገናችሁ፥ በቃልም ሆነ በሥራ የምታደርጉትን ሁሉ በጌታ በኢየሱስ ስም አድርጉት። (ቆላ. 3:16-17)
ከዚህም ቅዱስ ጳውሎስ እርስበርሳችሁ ተመማሩ፥ በሐዲስ መዝሙር እግዚአብሔርን አመስግኑ ነው የሚለው እንጂ ለተለየ ለው ወይም ነገድ፥ ጸታ የእግዚአብሔርን አገልግሎት አልሰጠም። እግዚአብሔር በመጨረሻው ቀን እንዲህ ይሆናል ይላል፥ ሥጋ በለበሰ ላይ ሁሉ ከመንፈሴ አፈሳለሁ፥ ወንዶችና ሴቶች ልጆቻችሁም ትንቢት ይናገራሉ፥ ጎበዛዝቶቻችሁም ራእይ ያያሉ፥ ሽማግሎቻችሁም ሕልም ያልማሉ፥ ደግሞም በዛች ወራት በወንዶችና በሴቶች ባሪያዎች ላይ ከመንፈሴ አፈሳለሁ፥ ትንቢትም ይናገራሉ፤ (ኢዮ. 2:28-29፤ ግብ. 2:16-17)
ከዚህም ነቢዩ ኢዮኤልና ቅዱስ ጴጥሮስ በእግዚአብሔር ሰዎች መካከል፥ ሴት ወንድ፥ ሽማግሌ ሕፃን ብለው ልዩነት አላደረጉም፥ አላሳዩም።
ዮሐንስ ወንጌላዊም፥ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው ብሎ የሚያምን ሁሉ ከእግዚአብሔር ተወልዷል ብሎ አማኒውን ሁሉ አስተካክሏል። (1ዮሐ. 5:1)
እናንተ ደግሞ እንደ ሕያዋን ደንጊያዎች ሁናችሁ፥ በኢየሱስ ክርስቶስ ለእግዚአብሔር ደስ የሚያሰኝ መንፈሳዊ መሥዋዕትን ለማቅረብ ቅዱሳን ካህናት ትሆኑ ዘንድ መንፈሳዊ ቤት ለመሆን ተዘጋጁ። (1ጴጥ. 2:5-10)
የሚከተሉት ጥቅሶችም ይህንኑ ያረጋግጣሉ፤ (ዮሐ. 1:12-13፤ ሮሜ 8:14-17፤ ያዕ. 4:17)

<u>የዚህ ርእስ መደምደሚያ</u>

ከተጠመቁ ወዲያ በክርስቶስ ዘንድ ልዩነት ስለሌለ፥ ወንድ ሴት፥ ካህን ምእመን ሳትል፥ እንደ ሥራህ ዋጋህን ለመቀበል ተሰለፍ።

ምዕራፍ 40

ያልተማረ ቄስ፥ ሁሉን ያረክስ፥ የተማረ ቄስ ብዙ ሕዝብ ይቀድስ

ምን ርኩስ አለ?

ይህ ርእስ በስመ ቄስ መጠን የሌለው ደበላ ከራሳቸው ላይ አስረው ቄስ መስለው የቅስናው ትምህርቱም ሆነ ሥልጣኑ፥ ዕውቀቱ፥ ላይኖራቸው ገና አቦ! አቦ! እየተባሉ የዋሃኑን ምእመናን ለማታለል፥ እታለው ለመብላት በፈሪሳውያን ጊዜ እንኳ ያልነበረ ነገር፥ ይህን አትበሉ፥ ያን አትንኩ እያሉ ከሚያውኩት አታላዮች ምእመን ሁሉ እንዲጠነቀቅ መረጃውን ለመስጠት ነው የተዘጋጀው። ዋና ዋና ማወናበጃቸውም የሚከተሉት ነገሮች ናቸው፤

ቡና፥ ሲጃራ፥ ጫት፥ ግተብ፥ ዓሣ፥ የሴት ርስሐት፥ የወሲድ መቆጣጠር። ሁሉንም እያንዳንዳቸው ቀጥለን እናያቸዋለን።

ቡ ና ፥

ከዚህ ላይ የተጠቀሱት ቡና፥ ሲጃራ፥ ጫት፥ ቁጥራቸው ከዕፅዋት ነው። ለዕፅ ደግሞ ከአንዲቱ ዕፀ ገነት በቀር መርዝ ካልሆነበት ይህን ብላ ያን አትንካ የሚል ትእዛዝ የለም። መጽሐፍ ላያነቡ፥ ትእዛዙን ላያውቁ፥ ከወዋቂ ላይጠይቁ፥ እንዲያው እነደርሶ ቄስ ቡና ብትጠጡ፥ ሲጃራ ብታጤሱ፥ ጫት ብትቅሙ ገዝቻለሁ ሲሉ ይሰማሉ። ከዚህም አልፈው ተርፈው፥ ከኪሳቸው እውጥተው የቡናና የሲጃራ ታሪክ ይህ ነው ሲሉ ይሰማሉ፤ ቡናና ሲጃራ ከእርዮስ ሽንት ላይ ነው የበቀሉተ ይላሉ። ስለዚህ የሁለቱንም ታሪክ ማየት ያሻል። ሁለቱም፥ እግዚአብሔርም ምድርን ዘርን የሚሰጥ ሣርንና ቡቃያን በምድርም ላይ እንደወገኑ፥ ዘሩ ያለበትን፥ ፍሬን የሚያፈራ ዛፍን ታብቅል አለ፥ እንዲሁም ሆነ። ምድርም ዘርን የሚሰጥ ሣርንና ቡቃያን እንደ ወገኑ፥ ዘሩም ያለበትን ፍሬን የሚያፈራ ዛፍን እነደ ወገኑ፥ አበቀለች። እግዚአብሔርም መልካም እነደሆነ አየ (ዘፍ. 1:11-12) እንዳለው የተፈጠሩ ሲሆን፥ ሰው ግን ለጥቅሙ ያዋላቸው በቅርቡ ነው።

በ10ኛው መቶ ዘመን የዘጌ ሦስት ቅዱሳን ምን እንብላ ብለው ሱባዔ ቢገቡ መልእክ እግዚአብሔር ለጸሎት እንድተጉ ቡና ጠጡ ብሎ ጥቅሙን ከነአሠራሩ ነግሯቸዋል። ከዚያ በኋላ በአየሀገሩ መጠጣት ተጀምሯል። በ11ኛው መቶ ዘመን ደግሞ በከፉ ብዙ ቡና ይጠጣ ስለነበርና የዐረብ ነጋዴዎችና የስልምና ሃይማኖት ሰባኪዎች በዚያ ክፍለ ሀገር በብዛት ስለገቡ ወደ ዐረብ ሀገር ከአውራጃው ስም ጋራ ይወስዱታል፤ በዚህ ምክንያት በብዙ ቋንቋ ካፌ፥ ኮፊ ይባላል።

ዓለምን ንቀው መንነው በረሃ፥ ገዳም የገቡት በቀን አንድ ጊዜ ብቻ የሚበሉት የዋልድባ መነኮሳትም በ9 ሰዓት ያውም በግር ይጠጡታል። የሲኖዶሱ አባላትም በምሳ ጊዜ ይጠጣሉ፥ ለእንግዳም ባርከው ይጋብዛሉ።

ሥጋ በአሪት ዘሌዋውያን ምዕራፍ 11 ተለይቶ ተሰጥቷል፥ በዕፅዋት በኩል ግን መርዝ ካልሆነበት በተቀር ይህን ብላ ያን አትንካ የሚል የለም፥ ሁሉም ቡሩክ ነው። ታዲያ ነገሩ፥ ታሪኩ እንዲህ ከሆነ አንዳንድ ባሕታውያን ቡና አትጠጡ ግዝት ነው፥ ገዝተናል ለምን ይላሉ? ለሚል ጠያቂ መልሱ የሚከተለው ነው፤ ጥፋቱ ከቡናው ሳይሆን ከአደራረጉ ነው፥ አንዳንድ ሰዎች ቡና ሲጠጡ ጨፈ ይጎዙላሉ፥ ዕጣን ያጤሳሉ፥ ጨፈ መጎዝጎዝ ዕጣን ግጤሱም ባልከፋ፥ ከዚያ በኋላ የእናቴ ያባቴ እምላክ እያሉ የብዙ መናፍስት አስማት ይጠራሉ፤ ይህ አምልኮ ባዕድ ነው፥ ክልክል ነው። የእናቴ የአባቴ እምላክ ተብሎ የባዕዳን አማልክት ስም ከተጠራ፥ ተጠርቶ ከታረደ፥ በግም፥ ፍየልም፤ ዶሮም መበላት የለበትም፥ አይበላም በክርስትና እምነት። ማንኛቸውም ነገር በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ ተብሎ ከተባረከ ቅዱስ ነው ያለበለዚያ ግን ርኩስ ነው። ስለዚህ መገዘት፥ መከልከል አቀራረቡን እንጂ ቡናውን አይደለም።

<u>ሲጃራ</u> ደግሞ ከላይ እንደ ጠቀስነው ከእርዮስ ሽንት የበቀለ ሳይሆን፥ እርዮስ የሞተ በ4ኛው መቶ ዘመን በኒቅያ ዛሬ ቱርክ በሚገዛት ክፍለ ሀገር ነው። ትንባሆ ደግሞ ከአዲሱ ዓለም ከአሜሪካ ወደ አሮጌው ዓለም የመጣው ኮሎምበስ አሜሪካን ካገኘ በኋላ በ16ኛው መቶ ዘመን ነው። ከእነሱም ጋራ ብርቱካን፥ ድንች፥ መጥተዋል። ብርቱካንና ድንች ጥሩ ምግቦች ስለሆኑ ተፈቅደዋል፤ ይበላሉ፥ ርግጥ ሲጃራ ሱስ ስለሚያስይዝ ያለምንም ጥቅም ገንዘብ ስለሚያጠፋ፥ ልብስ ስለሚያቆሽሽ፥ አየር ስለሚበክል፥ ለማኅበራዊ ኑሮም ከጥቅሙ ጉዳቱ ስለሚያመዝን ቢከለክል በጣም ጥሩ ነው ባይ ነኝ። ግን ከልካዩ መንግሥት በጤና ጥበቃ በኩል እንጂ በባሕታዊ ነኝ ባይ መነኩስ አይደለም። ከጓደኞቹ ከብርቱካንና ከድንች ልዩነት የለውምና።

<u>ጫትም</u>፥

ለመድኀኒት ገቢረና ለመብል እንበለ አምልኮ ከሆነ ኃጢአት አይደለም።

<u>ግተብ</u>፥

ግተብን ደግሞ መካከለኛውን ምሥራቅ ስልምና ሲወረው ለልዩነት ብሎ ያዕቆብ ዘእንበረደኢን የሚባል ጳጳስ ለወገኖቹ መለያ ብሎ

የፈጠረው ነው የሚባለው። ይህም ምክንያት ዛሬም ሆነ ቀድሞ በፍጹም ቸጋ የሰውም። ለምን ቢሉ? ሃይማኖት ተጠይቆም ሆነ ሳይጠየቁ በእየእደባባዩ የሚመስክሩት የሚያስተምሩት ነው እንጂ በኪስ እንደ ወጣ ክኒን ይዞ የሚውጡት አይደለምና ነው። ተዐቁቡኬ እምሐሳውያን ነቢያት በሚል ርእስ ሐምሌ 4: 1986 ዓ.ም. በወጣው የኢትዮጵያ አርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን መንበረ ፓትርያርክ ማስጠንቀቂያ ገጽ 41 የተጻፈው እንድም እውነት የሌለው ከኪስ እየወጣ የተጻፈ ነው፤ ይህንም እያንዳንዱን እንዘረዝራለን፤

ከሁሉ አስቀድሞ ማተብ የተጠመቁና ያልተጠመቁ መለያ ነው ብለዋል፤ ይህም ፍጹም ውሸት ነው፥ በዓለም ያሉ ክርስቲያኖች ሁሉ፥ ማተብ አያወቁም፥ ከኛም ካልተማረው በቀር አንገቱን በገመድ የሚያንቅ የለም። ደግሞም ጌታ በገመድ ታስሮ ለመሳተቱ ምሳሌ ነው ብለዋል። ዐሥራ አራቱን ጸዋትወ መከራማ በመሸከም የምናሳይ ከሆነ እነአክሊለ ሦክ፥ እነተጸፍየተ ገጽ፥ እነተቀሥፎ ዘባን፥ እነበትረ ሕሰት፥ ኧረ ስንቱን ጓደኞቹን የት ጥለን ነው ከቡትቶ ክር ላይ ብቻ የተጣበቅነው? ከሁሉም የሚያስገርመው የውሼቱ ጥቅስ መንጋጋት ነው። ላም ባልዋለበት ኩበት ለቀማ እንዲሉ፥ እኛ ከተናገርን ማን ያርመናል ተብሎ፥ ላልተማረ ወይም ሥራ ለሚበዛበት ሰው ማታለያ ታስቦ የተደረደረ ጥቅስ ነው እንጂ አንድ እንኳ እውነት የለበትም።

መጀመሪያ <u>ጎደገ ለነ ማዕተቦ ክርስቶስ</u>፥ እንዲህ የሚል ጥቅስ የለም፥ ለማደናገር በግዕዝ ያልጠቀሰውን በአማርኛው፥ ፍለጋውን ትከተሉ ዘንድ ምልክቱን ሊተውላችሁ ስለእናንተ መከራ ተቀብሏል። የጸሐፊውን ሐሳብ ከተረዳነው፥ የግሪክ ፊደል በህገራችን ስለሌ በግዕዝ እንዳለ ተርጉመን ግዕዙን በአማርኛ ፊትተን እናቀርባለን፤

እስመ ለዝንቱ ተጸዋዕክሙ ክርስቶስኒ በእንቲአክሙ ሐመ ይጎድግ ለክሙ ማዕተቦ ከመ ትትልው አሠረ ዚአሁ=ለዚህ ተጠርታችኋልና፥ ክርስቶስም አሩን (ዱካውን) እንድትከተሉ ምሳሌውን ይሰጣችሁ ዘንድ ታመመ ነው፥ የሚለው የእውነተኛው ጥቅስና ይዘት። (1ጴጥ. 2:21)

ሁለተኛው መዝሙር 59:4 የተጠቀሰው ደግሞ፥ ከቀስት ፊት ያመልጡ ዘንድ ለሚፈሩህ ምልክትን ሰጠሃቸው ነው የሚለው፥ ከዚህ ላይ ምልክት ተአምራት ማለት ነው እንጂ ቡትቶ ገመድ ማለት አይደለም። ስለዚህ እግዚአብሔር ክር ካላሰርህ ብሎም አይኮንን፥ ክር እበትህ ብሎም አያጸድቅ፥ በምግባርና በሃይማኖት እንጂ።

ዓሣ፡

ዓሣን ሠለስቱ ምእት ካሣ በቀር ሥጋ በጾም አትብሉ። ዓሣ ስለተበላ ከባሕር የሚገኘውም ሁሉ ሳይሆን ደልፊን በግዕዝ ጋርሣ ቃል የግሣት በአግረኛ አምባዛ (ይህ ግን በዐባይና በጣና አካባቢ የሚገኘው አባብ መሰሉ ዓሣ አይደለም) የሚበላው ነው። ዓሣ ደም ይወጣዋል፡ ለምን ሥጋ አይባልም? ለሚል ጠያቂ መልሱ፡ የሠለስቱ ምእት ጊዜ እንደዛሬው ፍራፍሬ የበዛበት አልነበረም፤ ጤነኛውም፡ በሽተኛውም፡ ልጁም፡ ዐዋቂውም፡ ደካማውም፡ ብርቱውም፡ ሕፃኑም፡ ሽማግሌውም፡ ሌጣውም፡ አመጫቱም ያለ ሥጋና ወተት ዐርባ ቀን ሊጾም ስለማይችል የሥጋ ምትክ ቢፈለግ ዓሣ ሁኖ ተገኘ። በእነሱ ውሳኔ ሥጋ የሚባል መጀመሪያ በሩካቤ የተወለደ፡ ተወለዶ የእናቱን ጡት የጠባ፡ በመጨረሻ ሲያርዱት ደም የሚወጣው እንደሆነ ተወሰነ፤ በዚህ መሠረት ዓሣ የሚወለደው በሩካቤ አይደለም፡ ከውኃ ውስጥ ወንዱም ዘሩን ሴቷም ዕንቁላሏን ይለቃሉ፡ በውኃው ገሬነት ዘርና ዕንቁላል ይገናኛሉ፤ የፅንሱ አጀማመር ይህ ነው፤ ይህም ሕልመ ሌሊትን ይመስላል። በአየር የተገናኘው ልጅም እናትና አባቱን ስለማያውቅ ጡት አይጠባም። ሦስተኛው ደገሞ ደም ነው፤ ዓሣ ሲያርዱት ደም የሚመስል ነገር ይፈሰዋል፡ በዕቃ ሲያቆዩት ግን ውኃ ይሆናል፤ እንደ ደም አይረጋም። ስለዚህ ዓሣ ሥጋ አይደለም። አይደለምና በጾም ይበላል።

ሴት በወር አበባና በወሊድ ትረክሳለች ወይ?

ይህ በሰፊው ሴት በሚሰው አንቀጽ ተዘርዝሯል፤ በሥርዓተ ረበናት እንጂ በወንጌል ሴት ርኩስ ናት አትባልም። ምክንያቱስ? ቢሉ በወንጌል ሰው በሥራው፡ በግብሩ እንጂ በተፈጥሮው ወይም በጥንተ አብሶ አይኮነንም፡ አይፈረድበተምና። ጥንተ አብሶን ክርስቶስ በመስቀሉ ሽሮታል። አሁንም አለ የሚል ፈሪሳዊ ካህን እንዳለ የክርስቶስን ሞት ክንቱ ግድረጉ ነው። እንዲህ ያለው ካህን ከመጠምጠም መግር ይትደም እንዲሉ፡ ከግደንከሩ በፊት ክርስቶስ በሞቱ፡ በመሠዋቱ ጥንተ አብሶን አጥፍቶ ዓለምን እንዳዳነ ግወቅ አለበት። አስካሁን ድረስ ሴት በሥርዓተ ረበናት ቀምበር ሥር ከኖረች ወይም ካለች የክርስቶስ ሞት ግማሹን ዓለም አላዳነም ግለት ነው። ትዱስ ጳውሎስም በእምነት በክርስቶስ ሁላችሁም አንድ ናችሁ፡ በእሱም ዘንድ አይሁዳዊ፡ ግሪክ፡ ሴት ወንድ ቂጥ ባለ፡ የለም ያለውንም ያፈርሳል። ጋብቻ በግንኙቸውም ክቡር ነው፡ የሚተኙበትም ርስሐት የለውም ባለው መሠረት ከዘጠኝ ወር በፊት

ጋብቻ ከቡር ነው ብሎ የባረከው ቄስ ከዘጠኝ ወር በኋላ ጸሎቱ ተሰምቶ ቡራኬው ይዞ ብትወልድ፥ ስትወልድ፥ ረክሰሻል፥ ጸበል ልርጭሽ ማለት ካለመግርም በላይ አስተዋይ አእምሮ የሚሠራው አይደለም። የቆረበች ሴት ከባሏ ጋራ በምታደርገው ግንኙነትም በዚህ ቀን በዚህ ሌሊት የሚል ነገር የለባትም። የሁለቱንም ጋብቻ ሥጋውና ደሙ የቀደሰው ሰለሆነ ሩካቤአቸውም እንደመጸዳዳትና እህል ውኃ እንደ መመገብ እንጂ፥ በዓል ስለዚህ እከብሩ በጸም አትገናኙ የሚል ሕግም ይሉ ትእዛዝ የለም። መጽሐፉስ የሚለው እንዲያውም ሰይጣን እንዳይፈታተናችሁ ለጸሎት ካልሆነ በቀር እትለያዩ፥ ለጊዜው ለጸሎት ብተለያዩም ጸሎታችሁ ሲያልቅ ተመልሳችሁ አብራችሁ ተኙ ነው። ከዚህም በላይ እግዚአብሔር ያጣመራቸውን፥ ማለያየት ለይጣንነት ሲሆን፥ እግዚአብሔር የቀደሰውን ማርከስ ደግሞ እግዚአብሔርን መንቀፍ ነው፤ (ማቴ. 19:4-7፤ 1ቆሮ. 7:1-5፤ ዕብ. 13:4)
ኃጢአትን ነው እንጂ ተፈጥሮንና ሕገ እግዚአብሔርን መቃወም አላዋቂነት ብቻ ሳይሆን ትዝዛዘ አምላክን የካህን ልብስ ለብሶ በመዋጋት የሳጥናኤል ውሳጣዊ እርበኛነት ነው።

ጫ ግ፥

መቼም ብዙ አላዋቂዎች፥ ወይም ምቀኞች፥ ወይም የእኩይ ውሳጣውያን እርበኞች ለውን ከእግዚአብሔር ለማራቅ፥ ቤተ ክርስቲያን መጥቶ ጸሎተ ማኅበር እንዳይካፈል፥ በዚህም ሃይማኖታዊ ተግባሩን እንዳይፈጽምና እምነቱን እንዳያጠና አድርገው ሰይጣናዊ ተልእኮአቸውን ለመፈጸም ነውና ብርድ የማይችለውን ሽማግሌና ድውይ ጫማ ካላወለቅህ ቤተ ክርስቲያን እትገባም እያሉ፥ ይገዝታሉ፥ እንዲያም ሲል በጎይል ያባርራሉ። ለዚህም የሚጠቅሱት ጌታ በሲና በረሃ ለሙሴ ሲታይ ሳለ የቆምህባት መሬት የተቀደሰች ናትና ጫማህን አውልቅ ብሎታል ይላሉ። ይህም ሆነ ለኢያሱ የተገለጠው መልአክ ጫማህን አውልቅ ያሉበት ምክንያት በአካባበያቸው የነበሩት አሕዛብ እንደኛ ሀገር እጉሪዎች ጫማ አውልቁ ስለሚሉ፥ ይህም ለማስፈራራት፥ ይህንም ሙሴ ከእግቱ ቤት ያውቅ ስለነበረ የተገለጠለትን እንዲፈራ ተልእኮውን በትሕትና እንዲቀበል ነበረ። ይህማ ባይሆን ኑሮ ከቤተ ክርስቲያን በፊት ዮተሠራች ቤተ መቅደስ፥ ከዚያም በፊት ደብተራ አሪት ናት። በሁለቱም ጫማ አውልቁ የሚል ትእዛዝ ወይም ትውፊት የለም። ሲቀ ካህናቱም ለዕጣንም ሆነ ለመሥዋዕት በመሠዊያው አጠገብ ሲቆም፥ ቤተ መቅደስ ሲገባ ጫማውን እያወልቅም። ሕዝቡም እንኳንስ ያወልቅና ጫማ ካላደረገ ከቅድስቱ አይገባም። በእየምኩራቡ

ደግም ሜግና ባርኔጣ ካላደረገ አይገባም። ራሱና እግሩ አይገለጥም። ከዚያም በመላ አብያተ ክርስቲያን ስለሜግ የሚጨቃጨቅ የለም፤ ቢነግም ልብስ ለብስ ለብስህ ቤተ ክርስቲያን አትግባ እንደግለት ነው የሚታየው። የእኛዎቹም ከአዶ ከብራ፡ ከዛር፡ ከእጉሪ ቤት ያዩትን ልግድ ለግንጸባረቅ ሴት ስታብብና ከባሏ ጋራ ስታድር፡ ትረክሳለች፡ ሜግ ቤተ ክርስቲያን አይገባም እያሉ ስለአምልኮ ባዕድ ይከራከራሉ፤ በዚህም አምላክን ከግገልገል ይልቅ ሰውን ያደናግራሉ። ለዚህም መረጃውን ጌታ ለኃጢአት ግስተሰረያ ብሎ የሰጠውን ሥጋውን ደሙን ብትቀበሉ ሥጋው እሳት ሁኖ ይፈጃችኋል፡ ይበላችኋል ደሙ ባሕረ እሳት ሁኖ ያሰጥግችኋል እያሉ ከኪሳቸው አውጥተው ሕዝቡን ምእመናኑን ያስፈራራሉ። የተሰሳተ ሰው ወደ ፈጣሪው ሲመለስ በቁድር እንደገና ያጠምቃሉ። ቅዱስ ጋብቻን ያረክሳሉ፤ ምን ብለው? ምን አድርገው? ለሚል ጠያቂ በቁርባን ከተጋቡ በኋላ ዐርብ ረቡዕ፡ እሁድ ቅዳሜ በበዓላት የወርም እንኳ ቢሆን ወሲብ ክልክል ነው ይላሉ። እነሱ ግን አይጠብቁትም። ከመባቻ እሰከ 30 ያለው ቀን ሁሉ ያውም በድርብርብ በዓል ግጥም ብሎ ተይዝዋል። የእነዚህ ሰዎች ግብር የሚያደላው ከግነጹ ይልቅ ወደ ግፍረሱ ነው። ኃጥእን አስተምሮ ንስሓ እንዲገባ ከግድረግ ይልቅ በግባረሩ የሚደሰቱ ብዙዎች ናቸው። አንድ ሊቀ ጳጳስ ከጠቀላይ ገዥ ጋራ ይጣላሉ፡ ጠቅላይ ገዥውም ተቆጥተው ከቤተ ክርስቲያን ይቀራሉ። ታዲያ ብፁዕ ሊቀ ጳጳሱ በደስታ ፈንድቀው ሲሞቱ። እንዲህ ነው ሰባኪ ከሆኑ ላይቀር፡ ለማን? ግን አሁንም ለማን? አሁንስ አንባቢ ሆይ! ይህስ ለአንተ ፈንታ ይሁን መለለኝ።

ሥርዐተ ጸሎት እያስተምሩም፡ ከዚያም አልፈው ተርፈው በቅዳሴ ጊዜ ያውም እግዚኦ ሲባል ዳዊታቸውን አውጥተው ወይም መልክአ መልኩን በፊት መቋሚያቸውን በኋላ ግድግዳቸውን ይደገፉና ሲያነበንቡ ከገባሬ ሠናዩ ቄስ ጋራ ለመወዳደር የተሰለፉ ይመስላሉ።

<u>የወሊድ መቆጣጠር</u>፡

በጥንተ ተፈጥሮ በሕጋዊ መንገድ ብዙ ተባዙ ብሎ ጌታ ግዘዙን የግያውቅ አይሁዳዊ፡ ክርስቲያን፡ ሰላም የለም። ይህም በምኩራብ በቤተ ክርስቲያን በመሰጊድ ይሰበካል። በሦስቱም ታላላቅ ሃይግኖቶች አትግደል ይከበራል። አትግደልም የሚሠራው የወንድና የሴት ዘር ተገናኝተው ፍሬ ከሆኑበት ጊዜ ጀምሮ ነው እንጂ ከዚያ በፊት አይደለም። ሁለቱ ዘሮች ከመገናኘታቸው በፊት ግን ግንም ተጠያቂ አይደለም። ይህ ባይሆን ግን ደናግል ነን እያሉ በሕልመ ሌሊት (ብሪቱ

አጨላ) የሚያፈሱ ሁሉ ንሃነም መውረዳቸው ነው። ከቅድስት ማርያም በቀር ከዚህ ንጹሕ የለምና። ቤተ ክርስቲያንም ሆነች መስጊድ ማስጨንገፍን ይከለክላሉ፥ መከላከልም አለባቸው፥ ስለ እግዚአብሔር፥ አትግደል ስለሚለው ትእዛዝ። ከወሲብ በፊት ስለሚያዝ፥ የሚዋጥ ነገር ግን አምላካዊ ትእዛዝ የለምና ባይጨነቁ ጥሩ ይመስለኛል። ሃይማኖትን እንጂ የራስን ልብ ወለድና ልማድ በአዲስ ትውልድ ላይ ካልጫንሁ ብሎ መንገዳገድ ጥሩ አይደለምና አስተውሎ አጥንቶ መናገር ይገነባል፤ እንዲያው ሳያጠኑ ሳይረዱ መለፍለፍ ግን ይንዳል፥ ያፈርሳል።

የሰላም ሥጋ

ክርስቲያኑ የሰላም ፣ ሰላሙ የክርስቲያን ሥጋ አንበላም የሚሉ ሰዎች በሀገራችን በኢትዮጵያ ብቻ እንዳሉ የታወቀ ነው። ይህም ለመለያ ፣ ለመለያያ ለመጣያ ብለው ሰርዓቶች የፈጠሩት እንጂ በሐዲስ ኪዳንም ሆነ በቅርአን ክርስቲያን ያረደውን ሰላም ፣ ሰላም ያረደውን ክርስቲያን አይበላም የሚል የለም። ምንም እንኳ ቅዱስ ጳውሎስ ጎሊናው ደካማ የሆነን ሰው ላለማዳከም ለጣዖት የታረደ ለደካማው ወንድማ ጎሊና ስትል አትብላ ቢልም ፣ ክርስቲያንና ሰላም ለጣዖት በሰማያርዱ ወይንም ስለማይሠው የሰላም ሥጋ አትበሉም ብሎ ማወጁ ልክ አይደለም ፤ (1 ቆር· 8 ፤) ስለዚህም አንዳንድ ሰዎች መላ ምት የመሰለ ተረት ይሰጣሉ ፤ ሰልምና ወደ ኢትዮጵያ ከመግባቱ በፊት ክርስትና በደጋው ኢትዮጵያ ነበረች። ሰልምና ቄላ ቄላውን እየሰበከ ወደ ደጋዋ ኢትዮጵያ ወደ ትግሬ ፣ ወደ አጋሚ ፣ እነ መሐመድ ነጋሽ ወደሚገዙት ብቅ ሲል ፣ በቄላው ለቆሌ ፣ ለአድባር ፣ ለአውሊያ ፣ ለዛር ፣ ለጋኔን የሚታረደውን አንበላም እያሉ እንደመጡ ፣ አጋሚም ሲደርሱ እናንት ያረዳችሁትን አንበላም ብለዋል። ክርስቲያንም እኛማ ለቆሌ ፣ ለአድባር አንሠዋም ፣ የምንባርከውም በስመ እግዚአብሔር ነው ብለዋል ፣ ቢሆንም መሐመድን ካልተቀበላችሁ ያረዳችሁትን አንበላም ብለው ሰላሞች እምቢ ስላሉ ፣ ክርስቲናችም ግም ሊሉት ጥምብ አይል የለምና እኛም የእናንተን አንበላም በማለታቸው መለያያ ሁኖ ቀርቷል። በኋላም ገዥዎች ለማለያያ ይረዳናል ብለው ስለደገፉት በጎጋው ሕዝብ ዘንድ ጸድቆ ቀርቷል።

ሃይማኖቱ ጽኑ የሆነ ክርስቲያን ሁሉ ግንም ይረደው ፣ ያዘጋጀው ሳይጠይቅ በስመ አብ ወወልድ መመንፈስ ቅዱስ ተባረክ ፣ ሊቀ ካህናት ኢየሱስ ክርስቶስ ባርክልን ብሎ መብላት ፣ ይችላል። ይህ ካልሆነ ግን የሚበላው እህል ፣ የሚለብሰው ልብስም ሊያረክሰው ስለሚችል ሰላም የነካውን ፣ የሠራውን ፣ ክርስቲያን ፣ ክርስቲያን ያበጀውን ሰላም መልበስ መብላት የለበትም።

እዚህ ላይ የሚገርመው ፣ የኛ ጳጳሳት ፣ መነኩሳት ፣ ሽሆች በዓለም ሲዞሩ ያነጉትን ሳይጠይቁ እየባረኩ ይበላሉ ፣ ሰላሙም ክርስቲያኑም ስመ እግዚአብሔር እየጠራ ሲበላ ያያሉ። ወደ ሀገራቸው መጥተው ግን ሽሁም ፣ ጳጳሱም በዚህ አንጣላም አትጣሉ ብለው እያውቁም። በልግድና በማይረባ ተረት መጣላት ግንንም አይጠቅምም።

ምዕራፍ 41

ልዩነት ለሹመት

የክርስቶስ ተከታይ ክርስቲያን ነኝ የሚል ሁሉ ምልክቱ መፋቀር ነው። ግን አሁን እንደምናያቸው ክርስቲያን ይፋቀራሉ ወይ? ወይስ በየቤተ ክርስቲያኑ እየተከፋፈሉ፥ ስም እየተወጣጡ ሲጣሉ፥ ሲሰዳደቡ ፥ እየሞሉ ጠላታቸውን ዲያቢሎስን ያስደስታሉ? ለባንጎሮቻቸው መሣቂያ ሁነዋል ወይ፤ የቤተ ክርስቲያናችን መሥራች ክርስቶስ የሰጠን ምልክት ሰንደቅ ዓላማችን ፍቅር ነበረች፤

እኔ እንዳፈቀርኋችሁ እናንተ ደግሞ እርስ በርሳችሁ ትፋቀሩ ዘንድ አዲስ ትእዛዝ እሰጣችኋለሁ። እርስበርሳችሁ ብትፋቀሩ የኔ ደቀ መዛሙርት መሆናችሁን ሰዎች ሁሉ ያወቃሉ። (ዮሐ. 13:34:35) ብሎ ለደቀ መዛሙርቱ ትእዛዝ ሰጠ፥ ወደ አባቱም አባ! ቅዱስ! ዕቀበሙ በስምክ ዘወሀብከኒ ከመ ይኩኑ አሐደ ከማነ=ቅዱስ አባት ሆይ! በሰጠኸኝ ስምህ እንደኛ አንድ ይሆኑ ዘንድ ጠብቃቸው ብሎ ለመነ ጸለየ፥ በዘመናችን ግን ትእዛዙም ተቀባይ ጸሎቱም መልስ ያገኘ አይመስልም።

በእየዘመኑ አንዳንድ ክርስቲያኖች፥ አንዳንድ ጠግግ ልጅ አባቱ ያሰውን ትቶ ሌላ እንደሚሠራ፥ የክርስቶስን ትዝዛዝ ተቃራኒ ሲሠሩና ሲያደርጉ ይታያሉ። መካከለኛውን ምሥራቅ ስላሞች ሲወሩት እኔን ጳጳስ ታደርገኛለህ ወይ እያሉ በወንድሞቻቸው ክርስቲያኖች ላይ የስላም ወታደር ሰላይ እየሆኑ መንገድ የሚመሩ በጣም ብዙዎች ነበሩ። ይህም ለሥጋዊ ሹመት የተስገበገቡ ሰርባቶች የሚያደርጉት እንጂ መንፈሳውያን አልነበሩም። በሙያ፥ በሊቅነት፥ በደግነት በትሩፋት የሚበልጣቸው መስሎ የሚታያቸውን ሰው ሁሉ ከቤተ ክርስቲያን እንዲለይ የሚጥሩም በጣም ብዙ ናቸው። የቤተ ክርስቲያንን መለያየት ያበዛውም የሃይማኖት ልዩነት ሳይሆን የራስን ጥቅም ለማመቻቸት ሲባል የሚውጠነጠን ፈጠራ ነው። ለዚህም ምሳሌ የሚከተሉት ታሪኮች ያገለግላሉ፤

አንድ ጳጳስና ጠቅላይ ገዥ ካንድ ቤተ ክርስቲያን ይሰማሉ። ብዙው ሕዝብ ጠቅላይ ገዥን እጅ ይነሣል፥ ብፁዕ አባታችን ይቀኑና ለንጉሡ እጅ ያስነሣል፥ ሐሳቡ ሌላ ይመስላል ብለው ይጠቁማሉ፥ ዐዜውም ሥልጣን ያንገበገባቸው ስለነበሩ፥ ቤተ ክርስቲያን የጳጳስ እንጂ ያንተ አይደለችም፥ እንዳትደርስባቸው ብለው ትዝዛዝ ያስተላልፋሉ፥ ታዲያማ! አባታችን ፈንድቀው ሲሞቱ፥ ለምን ቢሉ፥ አንድ ምእመን ሲቀር ያውም ሠራዊት ያለው፥ ለጊዜው ቤተ ክርስቲያን ለፍጻሜው ግን መንግሥተ ሰማያት ይሰፋሉና፥ መምህር ይሉሃል ይህ ነው።

ሁለተኛ ደግሞ ምስካየ ሕዙናን መድኀኔ ዓለም ተምሮ ግስተግር የሰንበት ትምህርት ቤት አለ፥ ከዚያ ከልጅነታቸው የሚተዋወቁ ሁለት ሰዎች ቆርበው ይጋባሉ። ተጋብተው በእያመቱ በተጋቡበት ቀን የሙሽራ ልብሳቸውን ለብሰው በአንድነት ቆርበው የጋብቻቸውን በዓል ያከብራሉ። በዚህ ሊኖሩ፥ አጅሬ ደርግ ሥር ነቀል ለውጥ አመጣሁ ባዩ በጠቋሚ ሰውዬውን በሥራ አመካኝቶ አሜሪካ ይልከዋል። በዚህ ጊዜ ብዙ ሰዎች ፈተና ደርሶባቸው እንደነበረ ያይን ምስክር ነን። በዚህ ጊዜ ሴቶች የመግር መጎበር አቋቁመው አንድ መምህር ይዘው በሳምንት አንድ ምሽት ይግራሉ። በዚህ መሃል ባሏ የተጠቀሰችው ሴትዮ በሌለበት የሠርጓ በዓል ይደርስባታል እንዳትቆርብ ባሏ የለ፥ ዝም እንዳትል በዓሉ ደረሰ፥ ምንታድርግ? ሰለዚህ መምህራቸውን ሊቁን፥ ትጠይቀዋለች። አንባቢ ሆይ ምን ብሎ ይመልስ ይመስልሃል? ሙያውንና ባሕርዩ የመምህሩ ምንድር ነው? ግብሩና ተግባሩ ከተጠየቀግ፥ ሰብኮ ወደ ክርስቶስ መጥራት ሳይሆን፥ እስበርጎ ግባረር ስለሆነ ሙያው የእጅሬ ካድሬ፥ በንጽሕና የተቀመጠችውን ሰውብቻሽን ባልሽ አሜሪካ ኼንቺ ከዚህ ሁነሽ ልትቆርቢ አትችይም፥ ሥጋ መለኮት ዋዛ አይደለም አላትና ወረፈ። ከብዙ ጊዜ በኋላ ቀድሞ በተምሮ ግስተግር ይሰብኩ የነበሩ በዚያ ጊዜ ሊቀ ጳጳስ ሰሲናዶስ ስብሰባ አዲስ አበባ ሲመጡ ሴትዮዋን ያገኝዋትና ስለደኅንነቷና ስለባሏ ከጠየቋት በኋላ፥ ዘመኑ አጠራጣሪ ስለሆነ፥ አሁንም እንደድሮአችሁ ትቆርባላቸሁ ወይ ይሏታል፥ ባሌን መንግሥት አሜሪካ ላከው ትላቸዋለች፥ ታዲያ የባልሽ አሜሪካ መሄድ ከቁርባን ይከለክላል ወይ? ይሏታል። አምን አለቃ የሴቶች ግኅበር መምህር ሥጋሁ ወደሙ መቀለጃ አይደሰም፥ ብቻሽን አትቁረቢ ስላሉኝ፥ ባሌ እስኪመጣ ለመድኀኔ ዓለም እየነገርሁ አለሁ፥ አለችኝ ብለው ነገሩኝ። እኔም ከአፋቸው ቀበል አድርጌ፥ እንዴት? የምን ፍርድ ነው? ብላቸው፥ የዕውር ፍርድ! ብለው መለሱ፥ ይበል ኅብር ቅኔ፥ እንደዚያን ዕለት ቱግታ፥ ኅብር ቅኔ በሕይወታቸው የሚያጋጥግቸው አይመስለኝም። እንዲህግ ቢሆን እንዳለቃ ገብረ ሐና ስግቸው በቀልድ በተነግ ነበር።

ሁለተኛም ይህ ዕውር የተባለ እደናቂ፥ በ1975 ዓ.ም. ስለቁርባን 3 ክታባት ተበተኑና፥ ቢበተኑ ቁርባን የሚያስቀሥፍ መስሎን ነው እንጂ የሚያድንግ ከሆነ ብሎ ሕዝቡ ለመቁረብ ቢሰለፍ፥ ሊቃውንቱ ረበናት፥ በስም ካህናት፥ በግብርም የዘመናችን ጸሐፍት ፈሪሳውያንም ግራ ገብቷቸው የተዝህሮእቸው አምባ በመሰበሩ፥ ሕዝቡ ሁሉ ከእነሱ ጋራ እኩል በመሆኑ ሲሸበሩ፥ የአጥፊዎች አለቃ ስለሆነ፥ ሠራዊቱ በመነካቱ

ተናዶ፡ ጌታ ሥጋውንና ደሙን የሰጠው ሦስት ጊዜ ብቻ ነው፡ ሲመለዱ፡ ሲያገቡ፡ ሲሞቱ እያለ ሲሰብክ ከረመ። የዚህን ሰው ስም መጥራትን ፈርቼ ምስክርም አጥቼ ሳይሆን፡ ከዚህ የተጋደሉ መጽሐፍ ስሙ እንዳይገባ ዘልየዋለሁ።

ያለፉት የቤተ ክርስቲያኒቱ መሪም የሕይወት ምንጭ ክርስቶስ ነው በተበተነበት ጊዜ ለዚህ ሁሉ ስንዴ የት ይገኛል? ብለዋል። ሰው (ክርስቲያን ሁሉ) ይቁረብ በመባሉም ተንተው ሰባኪውን ለመንግሥት ሰላውደው አሳስረዋል። የሚፈልጉት የክርሰቶስን መንጋ መበተን እንጂ መጠበቅንና መሰብሰብን አይደለምና። በዚህም የግን ካድሬ መሆናቸውን ገልጠዋል። ለሥራቸውም በትርቡ የጋቸውን አጎኝተዋል። እግኳንስ ለራስህ ቤተ ክርስቲያን አባልና ለሌላውም ቢሆን፡ አግናዊ ሥጋ ወልደ እግዚአብሔር፡ አግናዊ ደመ ወልደ እግዚአብሔር ነው፡ የኔንም ኃጢአት ማስተሰረይ ይችላል፡ ከኃጢአቴም መላቀቅ እፈልጋለሁ ብሎ ለቀረበ አግኝ ኃጢአተኛ ሁሉ ያለ ጭቅጭቅ ማቁረብ እንጂ ጠያቂ ይሉ ከልካይ የለም፡ ይህም በምስጢረ ቁርባን ተገልጧል። ለምን ቢሉ ጌታ ለኃጢአት ማስተሰረያ ብሎ ነውና የሰጠው፡ የእኩይ ካድሬዎች ግን እንደገና ዓለሙን ያስታረቀውን መሥዋዕት ይከለክሉና አምባገር ይጀምራሉ። በዚህም አለታቸው ግን እንደሆነ አስታውቃለኢ በግብራቸው ማንነታቸውን ገልጠዋል።

በዘመናችን የዓለም ሊቃነ ጳጳሳት፡ አርእስተ ሊቃነ ጳጳሳት፡ መንፈላውያን መሪዎችና የክርስቶስን ትእዛዝ እንከተላለን ዲሚሉ ቄደጋግ ሰዎች ሁሉ መዳንድነት እንመለሰ እያሉ፡ ይሰብካሉ፡ ያስተምራሉ፡ ግን የፍቅር በሯ በጣም ጠባብና አጭር ስለሆነች በመፍራሙ የተሠራውን የሹመት ካባ ላንቃ አውልቆ ዝቅ ብሎ ለመግባት የደፈረ፡ የጨከነ፡ የለም። ለምን ቢሉ ትሕትና ብርድን፡ ልቡናው ገባ አለመዳትግ! መለያየት የሚገባው በሃይማኖት ብቻ ነውኢ አሱም በሚከተሉት አርእስትኢ

1. አምስቱ አዕማደ ምስጢርኢ ምስጢረ ሥላሴ፡ ምስጢረ ሥጋዌ፡ ምስጢረ ጥምቀት፡ ምስጢረ ቁርባን፡ ምስጢረ ትንሣኤ ሙታን ኢ
2. ሰበዓቱ ሀብታተ ቤተ ክርስቲያንኢ ሀብተ ጥምቀት፡ ሀብተ ሜሮን (ቅብዓት)፡ ሀብተ ቁርባን፡ ሀብተ ክህነት፡ ሀብተ ንስሓ፡ ሀብተ ተክሊል፡ ሀብተ ቀንዲል ናቸው።

በእነዚህ የሚስማሙ ሁሉኢ የኢትዮጵያ አርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን፡ የግብጽ፡ የሶርያ፡ የግሪክ፡ የሮም፡ የእንግሊካን ቸረች

አንድ ናቸው።
የሥላሴን ሦስትነት አንድነት፥ ዕሩያን (እኩል) መሆን የሚያምን፥ ከሦስቱ አካል አንዱ አካል ወልድ በተለይ አካሉ ሥጋ ለብሶ ዓለምን ማዳኑን የሚቀበል፥ በጥምቀትና በመስቀል ጥንተ አብሶ መወገዱን፥ በቁርባን ኃጢአት መስተሰረዩን፥ በትብዐ ሚሮን ጸጋ መንፈስ ቅዱስ መሰጠቱን፥ በተክሊል ባልና ሚሽት አንድ አካል መሆናቸውን፥ በንስሓ ጊዜያዊ ኃጢአት መስተሰረዩን፥ በቀንዲል ህብተ ፈውስ መገኘቱን የሚያምን ሁሉ ወንድም ነው። በየትም ቤተ ክርስቲያን ሥጋውንና ደሙን መቀበል ይችላል።
ከፕሮቴስታንት አብያተ ክርስቲያንም የሥላሴን አኩልነት፥ የወልድን አማላጅነት፥ አስታራቂነት፥ ጥምቀትን፥ ሥጋውንና ደሙን ከተቀበሉ ወንድሞቻችን ናቸው። ወልደ አብ በመለኮቱ፥ ወልደ ማርያም በትስብእቱ፥ ኢየሱስ ክርስቶስ፥ መድኀኔ ዓለም፥ የቤተ ክርስቲያን መሥራች፥ በመለኮቱ ከአብ ጋራ አኩል ነው የሚል ክርስቲያን ሁሉ በክርስቶስ ወንድሜ ነው፥ ይህንም የአባታችንን ጸሎት የሚጸልይ ሁሉ መቀበል አለበት።
ፍቅረ ሚመት ባይኖር ኑሮ የታላላቁ አብያተ ክርስቲያናት ስለ ክርስቶስ ሥጋዊ ያላቸው አስተያየት አንድ መሆኑ ከታወቀበት ጊዜ እስከ ዛሬ የጎብረትን ብዙ ጎዳና መሄድ ይቻል ነበር።
ከዚህ ደረጃ ለመድረስ ያልተግረ ካህን በአየሰበካው፥ ባል ሚራችሁ፥ ጸም ገደፋችሁ እያለ የሚገዝተውን ሁሉ ግቶም አለበት። ጸም ጹሙ፥ በዓል አክብሩ ብሎ መምከርና ማስተግር ሥራውም ግዴታውም ነው። በዚህ የተነሣ ሥጋውና ደሙን መከልከልና መገዘት ግን አይችልም። አብረውት የሚኖሩት የንስሓ ልጆቹን የሚያባርር፥ የሩቅ ወንድሙን የሚወድበትና የሚያይበት ዐይን ይሉ ልቡና፥ ችሎታ የለውም።

ምዕራፍ 42

ተግሩ፥ ተዘጋጁ፤

ግስተግር ጦርነት ነው፥ በእየጊዜው ዐቅዱን ይለውጣል። እንግዳ ባይመጣ ሁሉ ሴት፥ ዝናብ ባይመጣ ሁሉ ቤት እንደሚባለው የውጭ ሚሲዮናውያን ወደ ሀገራችን ከመግባታቸው በፊት ቅዱሳት መጻሕፍት በእየአንዳንዱ ምእመን እጅ ባለመገኘታቸውና ሕዝቡም ካህናቱ እንጂ ሌላው ያልተግረ ስለነበረ፤ አብዛኛው ቁስም ግንበብ እንጂ በግዕዝ የሚያነበውን የግይረዳ ስለነበረ፥ የባልቴቱ ተረት እንደ እውነት ተአምና ነበር፥ በአለፈው በደጉ ዘመን። ትልቁ ቁም ነገርም ቅኔና ዜማ መማር ነበር። አሁን ግን ቅዱሳት መጻሕፍት በእየሰው እጅ ገቡና እንዲህ ግለት ምንድር ነው? የሚል ጠያቂ (እንቦም ሆነ ከውጭ ሰባኪ ሰምቶ) ስለበዛ እንደ ቀድሞው በግሕሌት ርዝማኔ ሕዝቡ ስለግይረካ፥ ምንም በግያውቀው ቋንቋ ከ14-18 ሰዓት ግሕሌት ቢያደርሱ፥ ሰዓታት ቢቆሙ፥ ቅዳሴ ቢቀድሱ በሚያውቀው ቋንቋ ለ20 ደቂቃ ስለአንድ ርእስ ቢሰግ ስለሚሻለው፥ ሕዝቡ በጠቅላላ ወጣት ሽማግሌ ሳይል፥ ወደ ሌላ ቤተ ክርስቲያን እየሄደ ነው። ስለዚህ ካህን ሲጠይቁት ለመመለስ በዜማና በቅኔ የሚያሳልፈውን ረዥም ዘመን ቀንሶ ለጥቂት ዘመን መጽሐፍ ግጥናት አለበት። ይህም በቅዱሳት መጻሕፍትም ሆነ በፍትሐ ነገሥቱ የታዘዘ ነው፤

ስለትሩፋታችሁ (ሃይማኖታችሁ) ምክንያትን ለሚጠይቁ ሁሉ መልስ ለመስጠት ዘወትር የተዘጋጃችሁ ሁኑ። (1ጴጥ. 3:15)፤

ኢየሱስም መልሶ እንዲህ አላቸው፥ መጻሕፍትንና የእግዚአብሔርን ኃይል አታውቁምና ትሰሳታላቸሁ። (ማቴ. 22:29፤ 12:3፤ 19:4፤ ግብ. 13:27፤ 2ቆሮ. 3:15፤ ኤር. 5:4፤ አሞ. 3:10፤ ሚክ. 4:12፤ ሮሜ 10:3፤ ኤፌ. 4:18፤ 1ጴጥ. 1:14፤ 3:15፤ ቆላ. 4:6፤ 1ጴጥ. 3:14-15)

ከዚህ በላይ የተጻፉት ጥቅሶች ሁሉ የሚያሳዩት ካለመግር የሚመጣውን ስሕተት ነው። ስለዚህ መጀመሪያ ደጎና አድርጎ ግጥናት በኋላ መወገን ነው የሚገባው። ካህን ከተግረ ግንኛውም መናፍቅ ቢጠይቀው ወዲያው ለመመለስ ዝግጁ ነው። ዝግጅቱ ግን በዜማና በቅኔ ብቻ ሳይሆን በቅዱሳት መጻሕፍትም ጭምር ነው። መጀመሪያ ሃይግናት በኋላ ሰዓታት፥ ኪዳን፥ ግሕሌት ቅዳሴ ይሁን።

ምዕራፍ 43

አጠቃላይ ምክር ለካህናት

ዜማዋንና ቅኔዋን እንደምትማሩት መጻሕፍትንም በተና ልቡና አጥኑ። መጻሕፍትን ሳያጣምም ከሚተረጉም ጋራ ተሰማሙ። ስትረቱ ደስ እንደሚላቸሁ ስትረቱም እውነት ከሆነ ያሰምንም ክርክር ሰመተበል ዝግጁ ጎሊና ይኑራችሁ። ሃይማኖት ተረድቶ ግመን እንጂ የእስጥ አገባ ሙግት አይደለም። መጀመሪያ የራሳችሁን ሃይማኖት ደኅና አድርጋችሁ ተማሩ። ከዚያ በኋላ የተሻለ ከተገኘ ሰመተበል ጥቅም ፈልጋችሁ አትናደዱ። ቅዱሳት መጻሕፍትን በመጽሐፈ ባልቴት አትሰውጡ። እውነት ለጊዜው መራራ ናት፥ በእንጻሩ የመበለት ተረት ግን ጣፋጭ ነው፤ ፍጻሜው ግን ከንቱ ነው። ወዲያኛው ዓለምም እንደዚህ ጠባብ መስሏቸሁ፥ የሰው ልጅ መንግሥተ ሰማይ እንዳይገባ እትመቅኙ፥ እግዚአብሔር ሀብታም ነው፥ ለሁሉም ይበቃል፥ ሰለዚህ ወደ ሰራው መንግሥተ ሰማያት ሰው እንዳይገባ መመቅኘት ከንቱ ነው። ከዚህ በራት እንደ ተገለጠው የክርስትና ሃይማኖት መሥራች ክርስቶስ ነው። ከእሱ ጋራ የሚጣላ ትምህርት ሁሉ ምንጩ ያው የእውነት ጠላት፥ የሐሰት አባት፥ የሰው ዘር ባላንጋራ ዲያብሎስ መሆኑን አውቃቸሁ ተጠንቀቁበት፥ ንቁበት። ግንኛቸውንም የሃይማኖት ጠላታቸሁን አሳፍሮ ለመመለስ ቅዱሳት መጻሕፍትን ሌት ተቀን አጥኑ፥ አንቡ። የዘመኑ ተከራካሪዎች የሚተበኋቸውን ቅዱሳት መጻሕፍት በራት አጥኑና ከዚያ ተጥላቸው መጻሕፍተ ሊቃውንትን ለቅዱሳት መጻሕፍት መተርጎሚያና ግንዛቢያ አስተውሉ። ይህ ሁሉ ከተዘጋጀ በኋላ ጊዜ ካለ አዋልድንም ግንበብ ይጠቅማል።

የአዋልድ መጻሕፍት በቅዱሳት መጻሕፍት አይጠቀሱም፥ ቅዱሳት መጻሕፍት ደግሞ ለግብራሪያ ከአልሆነ በቀር በመጠቅል ላይ አይጠቀሱም። የመጻሕፍት ሁሉ ቁንጮ፥ ዘውድ፥ ከራስ ላይ የምትቀመጥ አክሊል መጠቅል ናቸው።

ምዕራፍ 44

መጠይቅ ለጠያቂና ተመራማሪ

ጋብቻ በግንኙቸውም መልኩ ክቡር ቅዱስ ነው፡ ሁለቱን ተፈቃቃሪዎች የሚያጣምርም እግዚአብሔር ነው፡ ተብሎ በተክሊልና በቁረባን ይጋባሉ። ከተጋቡ በኋላ በዘጠነኛው ወር ጸሎቱ ሠምሮ፡ ቀኗ ደርሶ ትወልዳለች፡ ስትወልድ እንኳ ደስ አለሽ በመባል ፈንታ ረከሽ፡ የነካሽ፡ ያተበሽ ቤተ ክርስቲያን አይገባም፡ ቅዱስ ነገር አትነኪም። እንኳንስ አንቺና ምንም ያልሠራው የተወለደው ልጅም በመወለዱ ርኩስ ነው ትባላለች በረበናት ልማድ። የሚገርመው ደግሞ አብሯት የሠራው፡ ለመውለዷ ምክንያት የሆነው ወንዱ ርኩስ አይደለም። መውለዱ የጋርዮሽ ሲሆን መርከሱ ግን የሴቷ ነው። ዋንተ አብሶ ያመጡት ሁለቱም አዳምና ሔዋን ናችው፤ እሱንም በጥምቀተና በመስቀል ጌታ አጥፍቶታልና እያለች ቤተ ክርስቲያን ታተሰተምራለች፡ ሕዝቡም ክርስቲያን ሁሉ ያምናል፡ በወር አበባና በወሊድ ምክንያት አሁንም ሴት የምትረክስ ከሆነ የክርስቶስ ሞት ከንቱ ሆነ።

ዋንተ አብሶ በግማሹ ሰው በሴት አሁንም አለ ወይ? በክርስቶስ ሞት አልተፋቀም ወይ? ከዐሠርቱ ቃላት ሌላ ከአሪት ወደ ክርስትና የተላለፈ አሁንም አለ ወይ? መሥዋዕተ አሪት ከህነተ አሮን፡ በዓላተ አሪት አሁንም ይከበራሉ ወይ? ግዝረት አሁንም በጥምቀት አልተተካም ወይ? ለሥጋዊ ተግባር ሳይሆን ፡ ለጽድቅ ያስፈልጋል ወይ? ይህን የመሳሰለውን ከመመለስ በፊት ገላትያን ከነቁራኛው ግንበብ ያሻል።

ያለ ቁርባን አንዳንድ አፅራረ ወንጌል ወጽድቅ እንደሚሉት በትሩፋት ብዛት መጽደቅ ይቻላል ወይ? (ማቴ. 26:26-28፤ ዮሐ. 6:27-69) ማስተማር ወይስ ማወናበድ? ወይስ አደናግሮ ምእመናኑን ለማባረር የተዘጋጀ ወጥመድ?

በቤተ ክርስቲያን ቅዱሳት መጻሕፍት የሚሉትን ተመርኩ፡ ቃለ እግዚአብሔር ከማስተማር ይልቅ የባልቴት ተረት የሚሰብኩ ብዙ ካህናት መሳዮች አሉ። ተረታቸው እንዳይሻርባቸውም ቅዱሳት መጻሕፍት ወደ ቤተ ክርስቲያን እንዳይገቡ ይከለክላሉ፡ በሩን ይዘጋሉ። ገብተውም እንዳይነበቡ በምሕላ፡ በእግዚአታ ጊዜውን ያሳልፋታል። ለምሳሌ ደርጉ ከወደቀ ወዲህ ምእመኑ ወደ አምላኩ ተመልሶ አስተምሩን ብሎ በ11 ሰዓት ወደ ቤተ ክርስቲያን ይመጣል። በስመ ካህናት የወንጌል ጠላቶች ግን፡ ከአምላክ የሚጠይቁት አንድ ዓላማ ሳይኖራቸው፡ የሚግለለውን ሕዝብ ሳያስታርቁ፡ ወንጌል

እንዳይሰማ በምሕላና በእግዚኦታ ጊዜውን አሳልፈው ይበትኑታል። በምሕላውም የጸሎቱ፥ የሰእሰቱ፥ የልመናው የጥያቄው ርእስ ስለሌለው እግዚአብሔር አይመልስም፤ ባለፈውም አልመለሰም። ለምን ቢሉ ያለ ዓላማ የተሰበሰበ ሕዝብ ነውና። አንዱ ገብረ ክርስቶስን እንሣልኝ፥ ሁለተኛው ደግሞ ጠብቅልኝ፥ ሦስተኛው ሀገራችን በእየነገዱ ስለተከፋፈሰች የእኛን ነገድ ርዳ፥ ሌላውን አውድም ነው የሚሰው በልቡ፥ ታዲያ አምላክ የቱን ይሰማ?

በመጀመሪያ በሥርዓተ ጸሎት እንደተነገረው በዚህ ሱባዔያችን፥ እግዚአብሔርን ይህን እንዲሰጠን እንጠይቃለን፥ እንለምናለንና፥ ለመለመን ፈቃደኛ የሆናችሁ ከተጣላቸሁት ታርቃቸሁ ኑ ተብሎ አልታወጀም፤ አልተነገረም፥ አይነገርም፥ አይታወጅም። ይህም ባለመሆኑ የትግራኛ ተረት እናትና አባቱ ጸሎታቸው እየብቻቸው እንደሚሰው ሁሉም መልስ የለሽ ልመናውን ያቀርባል፥ ጩኸቱም ያህያ፥ ጸሎቱም የእሽኮኮ ሆኖ ይቀራል።

ይህን ዓለም በመልክተኛ ለማዳን ስላልተቻለ፥ ራሱ ወልደ እግዚአብሔር ኢየሱስ ክርስቶስ ሥጋ ለብሶ አስተማረ፥ በእኔ ያመነም ይድናል ብሎም ዐወጀ። ታዲያ የባልቴት ተረት ተተግኖ፥ ሥርዓተ ረበናትን ለብሶ ክርስቶስን ያልተቀበለ ይድናል ወይ? ተረት ነው ወይስ ቃለ እግዚአብሔር የሚያጸድቀው?

ከዚህ በፊት እንደ ተነገረው በወንጌል፥ በቅዱሳት መጻሕፍት ላይ ሊቅ፥ በሊቅ ላይ አዋልድና ተረት አይጠቀስም ነበር፤ ለብዙዎቹ ግን ወንጌላቸው ምንጩ የማይታወቅ ተረት ነው። በትርጓሜ ወንጌል ግቴ. 7:6 ላይ እንዳለው ያለ ተረትና ግምት ከቤተ ክርስቲያን መውጣት አለበት። (ወንጌል ቅዱስ ንባቡና ትርጓሜውን እይ)

ለዚህ መጽሐፍ መጻፍ ምክንያት በሆነው ተዐቀቡኬ እምሐሳውያን መምህራን በሚለው ክታብ 23 ገጽ፥ ጻድቃን በዐጸደ ሥጋም በዐጸደ ነፍስም ያግልዳሉ። ተብሏል። በውዳሴ ማርያም ትርጉም ደግሞ ለእሊ ለነ ቅድስት ስትተረጎም፥ ልመናስ ከዚህ በኋላ እንኳን በእሷ በሌሎችም የለባቸውም፥ በቀደመ ልመናዋ የምታስምር ስለሆነ እንዲህ አለ እንጂ ብሎ በዐጸደ ነፍስ መለመንዋን ይክዳል፥ ግምቱንና ተረቱን በቅዱስ ኤፍሬም ላይ ጠቅሶ ታዲያ የተኛው ነው እውነት? ጻድቃን ከሞቱ በኋላ ያግልዳሉ ወይስ አያግልዱም፥ አንዱን ያዝ ያስኛል። የዐርብ ውዳሴ ማርያም ማርያም ንጽሕት! ለእሊተ ምሕረት ለውዱደ ሰብእ! ለእሊ ለነ ኀበ ክርስቶስ ወልድኪ ይስረይ ኃጢአተነ=ለሰው ልጅ ምሕረት ለማኝ ቅድስት ማርያም ሆይ! ኃጢአታችንን ያስተሰርይልን

ዘንድ ከልጅሽ ከወዳጅሽ ለምኝልን ይላል፤ በቀን ከ10 ጊዜ በላይ የሚደግሙት በሰላመ ቅዱስ ገብርኤል መልአክም....ከተወደደ ልጅሽ ከጌታችን ከመድኀኒታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ ዘንድ ኃጢአታችንን ያስተሰርይልን ዘንድ ለምኝልን ዛሬም ለዘለዓለሙ አሜን ብሎ ይዘጋል። ይህን የመሰለ ሌሊቱን ቁመውት በሚያድሩ በሰዓታት: በስብሐተ ፍቁር: በማሕሌት: ሞልቷል: ታዲያ የትኛው ነው ስሕተቱ ወይስ እውነቱ? እንዲህ ያለውን ሲያዩና ሲያነቡ : የአኛ ካህናት አፋቸው የሚለፈልፈውን ጆሮአቸው የሚሰማውና ልቡናቸው የሚረዳው ስለማይመስል ትንቢተ ኢሳያስ ደርሶባቸው ነው ያለኛል።

የእሑድ ውዳሴ ማርያም የለኪ ይደሱ መጨረሻም ስለሊ ለነ ኅበ እግዚእነ ወመድኀኒነ ኢየሱስ ክርስቶስ ከጌታችን=ከመድኀኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ዘንድ ለምኝልን ይላል። አሁንስ?

መጽሐፉ አርጋኖንና ኖኅተ ብርሃንም ምስጋናና ልመና አኩቴት ናቸው። አመስግኖ ሲያበቃ ከጠላቴ አድኝኝ: ጠብቂኝ: የዕለት ሲሳየን ስጭኝ እያለ ነው የሚለምን: ይልቁንም ከ360-371 ባሉት ገጾች። ታዲያስ ያለእናንተ ማን ያያል? ማንስ ያነባል? በመላ ሰዓታትም ማሕሌትም ስለሊ ለነ ማርያም: ስለሱ ለነ ሚካኤል ወገብርኤል ሲባል ነው የሚያድረው: ታዲያ እንዴት ሁኖ ነው ሲነጋ ደርሶ በቃል ኪዳኗ ነው እንጂ: አሁንስ አታማልድም: አትጸልይም የሚባለው? አስተዋይ ኅሊና ያሻል። ቤተ ክርስቲያንን የመሠረተ ዓለምን ያዳነ መድኀኔ ዓለም ክርስቶስ ነው: ሲሆን ፈጣሪ ዓለም እግዚአብሔር አብ: መድኀኔ ዓለም መንፈስ ቅዱስ የማርያምን ያህል: ይከበራሉ: ይመሰገናሉ ወይ? ሁሉም በእየመጠናቸው ቢመሰገኑና ቢከበሩ ጥሩ አይደለም ወይ? ማርያም አትመስገን: አታማልድም አላልሁም: አልልምም ከሥላሴ በኋላ ትሁን እንጂ።

ምዕራፍ 45

ለማስታወቅ ያህል፥

ይህ አጭር ምዕራፍ የኢትዮጵያን ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የጵጵስና ታሪክ ባጭሩ ይገልጣል። የተደረገውም አንድ ምሽት ከግብዣ ላይ ከአንድ ግብጻዊ ካህን ጋራ በጭውውት መልክ ነው።

አባ! ለምድንድር ነው? ለዓለም አብያተ ክርስቲያናት የኢትዮጵያ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ከቅዱስ ቴዎፍሎስ ወዲህ በአበው ቀኖና መሠረት የማትሄድ፥ ኢቀኖናዊት ናት ብላችሁ፥ ከአብያተ ክርስቲያን የለያችሁን? አልሁት፥ በጥያቄዬ የወጠርሁተና መልስ አሳጥቼ ያሳፈርሁት መስሎኝ፥ ለካስ ካህኑ እንደኛ ካህናት ቅዳሴ ብቻ ሳይሆን ታሪክም ያውቅ ኑሮ እንደሚከተለው በእንግሊዝኛ በዝርዝር መለሰ።

ውድ ወንድሜ ሆይ! የራሳችሁን ታሪክ ከኔ ይልቅስ ለስርብትና ካልሆነ በቀር አንተ እንደምታውቅ አምናለሁ። ከጠየቅሽኝ ግን የማውቀውን እነግርሃለሁ። እንደምታውቀው ከአቡነ ሰላማ ከሣቴ ብርሃን እስከ አቡነ ማቴዎስ እስከ 1922 ዓ.ም. የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ጳጳሳት ግብጻውያን ነበሩ። በዚህ ረጅም ዘመን አባቶቻችን አጠፉ፥ አላጠፉም፥ አለሙ፥ አላለሙም የሚለውን ጥያቄ ለጊዜው ወደ ጎን እንተውና ጵጵስናን ከኛ ከተረከባችሁ ወዲህ ምን እዳደረጋችሁ እንተርክ፥

በ1922 ዓ.ም. ለመጀመሪያ ጊዜ አምስት መነኮሳት ላካችሁ። እኛም ግብጻዊውን አቡነ ቄርሎስን ሊቀ ጳጳስ አድርገን አምለቱንም መነኮሳት አጳጵሰን ላክንላችሁ። ከእነዚህም በዕድሜ በትምህርት በዕውቀት በሊቅነት፥ ይልቁንም ከቅባት ጋራ በሚደረገው ከርከር ተወዳዳሪ የላቸውም ስለተባለ ከሁሉ አስቀድመን አቡነ አብርሃምን ሹመን ላክነላችሁ። በሕገ ሢመተ ጳጳሳት መሠረት የመጀመሪያው ኢትዮጵያዊ ጳጳስ ስለሆኑ ተቀዳሚው እሳቸው ነበሩ። ጳጳሳቱ ሲቀመጡም፥ በሊቀ ጳጳሱ ቀኝ የሚቀመጡ፥ ጉዞም ሲሆን ተከታዩ እሳቸው ነበሩ። ህገረ ስብከታቸውም፥ አቡነ አብርሃም ጳጳስ ዘምዕራብ ኢትዮጵያ ተብለው ጎጃምና ጎንደር ነበር። እንዲሁ ሁነው ሲሠሩ በ1928 ዓ.ም. ጣሊያን መጣ። በዚህ ጊዜ እንደልማዱ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ከመንግሥት ጋራ ሁና የህገሯን ጠላት ትዋጋ ነበርና ሃይማኖትህን የሚያስክድ፥ ግተብህን የሚያስቆርጥ፥ ሰማያዊይና ምድራዊ ርስተህን የሚቀማ ጠላት መጥቶብሃልና ለጦር የደረስህ ወንድ ልጅ ሁሉ ደንቀዝና ዳባት እጁን ያልያዝሽኝ እንደሆነ ጥቁር ውሻ ውለድ ብለው በእየአድባራቱ፥ ገዳማቱ፥ ገጠሩ፥ በእየገበያው፥ ከተማው በተኑ። በዚህ ምክንያት በሸዋ አገዛዝ ተናዶ፥

እንውረድ አሉኝ ሰቲት
እኔስ አልወድም ሰቲት
ሸዋ እንደበላ ይሙት።
ገብሬ ገብሬ ነጭ ዐጥንቴ ወጣ
በገንዘቡ አዳሪ መለሎኒ መጣ።
ገብር! ገብር! ዝንጀሮም ገብር፡
ኧረ እንደምን ሁኜ ልገብር?
አዳሬ ከዋሻ ኑሮዬ ከዱር?
ኧረ እንደምን ሁኜ ልገብር?
ገብር!!

የንጉሥ አይደለም ወይ የምትጭረው ምድር?

እያለ ያጉረመርም የነበረው የጎጃምና የቤጌምድር ነበዝ ለሀገር ፍቅርና ለንጉሡ ክብር ሳይሆን የጳጳሱን ግዝት ፈርቶ፡ የክርስቲያን ሀገር ስለሆነ በነቂስ ወጣ። ንጉሡ ግን መጀመሪያ ይገዝቱ ብለው ገፋፍተው አስገዝተው ሊያበቁ፡ ንስሓ አባታቸውና ከሚወዱት ጠቅላይ ግዛት ስላልሆኑ፡ ጦሩ መውጣቱን ከተረዱ በኋላ ድል አድርገው ሲመለሱ ጳጳሱም ንጉሡም ሸምች ነበሩ ለማለት፡ የሸዋ ጀግና ከጎጃሚ ጳጳስ ፊት እንዳይፈክር፡ ወጣቱን አቡነ ጴጥሮስን ይዘን፡ በዚሁ በወሎ ወደ ትግራይ እንዘምታለን፡ ስለዚህ እስኮ ባሉበት ጎንደር ይቀመጡ ብለው ቴሌግራም አደረጉላቸው፡ እሳቸው ግን በሹመትም ሆነ በዕድሜ ተቀዳሚው፡ ቀዳሚው እኔ ነኝ፡ ከዚህም በላይ ለለማዕትነት ሞት በሽምግልና የመጣልኝን አይንፈጉኝ፡ እግዚአብሔር አይበለው እንጂ ድል ብንሆንም ወጣት ነውና ሀገር ላገር እየዞረ ሊያስተምር ይችላል ብለው ቢመልሱላቸው፡ ንጉሡ ከመኳንንታቸው ጋራ መክረው የሠሩት ስለሆነ፡ በጦርነት ጊዜ ሁለት አለቃ የለም፡ እርስበርሳችን ልንዋጋ ነው ወይ? ይመለሱ ብለው ስላዘዟቸው፡ በቀና ልቡና፡ በድብትርና፡ በምንኩስና በትሕትና ሁኜ ያገለገልሁህ አምላኬ የዚህን ሰው ፊት አታሳየኝ ብለው ከጸለዩ በኋላ የሚያምኗቸውን ሲቃነ ካህናት አማከረው ቀሩ። ጣልያን ድል አድርጎ ሲገባ አቡነ ቄርሎስ ንጉሠን ተከትለው ሸሹ። ቤተ ክርስቲያንዋ መሪ አጣች። ምርጫ ተደረገ፡ ሕዝቡም በዕድሜም፡ በሊቅነትም በዝናም፡ በደግነትም የሚያውቃቸውን አቡነ አብርሃምን መረጠ። አሳቸውም የጎይለ ሥላሴ መንግሥት፡ የለማዕትነት ሞት በመከልከሉ ረግመውት ነበርና ምርጫውን ተቀበሉ። ይደልዎ ተብሎ ከዚሁ ቅድስት ማሪያም በሊቀ ጳጳስነት ተሾሙ። ይህም የአሁኑ ፓትርያርክ የሚለው ቃል

ስላልተለመደ ነው እንጂ ፓርያርክ ማለት ነው። የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ከግብጽ ነጻ የወጣችው በዚህ ጊዜ ነው። የዚህም መረጃ አቡነ አብርሃም ቀዳሚ ሊቀ ጳጳሳት በኢትዮጵያ የሚል ጽሑፍ ቅደስት ማርያም ቤተ ክርስቲያን ይገኛል: ሂደህ ዕይ። በሹመታቸውና በቀብራቸው ጊዜ የወጡ ጋዜጦችም አለ። አቡነ አብርሃም ሁለት ዓመት ቆይተው ሲሞቱ አቡነ ዮሐንስ በኃይለ ሥላሴ ጊዜ የአዲስ ዓለም ንቡረ እድ የነበሩት ተመርጠው በሥነ ሥርዓት ነገሡ። በዘመናችው ንጉሡ ተመለሱ። ወዲያውም የቤተ ክርስቲያኒቱም ገዥና ጳጳስ እኛ ነን ስለሚሉ አቡነ ዮሐንስን ከሥራ አገዱቸውና እንደገና ከግብጽ ቤተ ክርስቲያን ጋራ ውዝግብ ተጀመረ። ከብዙ ጭቅጭቅ በኋላ እንደገና አምስት ሊቃነ ጳጳሳት ተሾሙ። አቡነ ቄርሎስ እስኪሞቱ ተብሎ። በኋላ አቡነ ቄርሎስ ሲሞቱ የግብጽ ቤተ ክርስቲያን የኢትዮጵያን ቤተ ክርስቲያን ለተማሩት ለአቡነ ቴዎፍሎስ መንፈሳዊ መሪነቱን ሰጠች። ጃንሆይ ግን ለወዳጃቸው ለአቡነ ባስልዮስ እንዲሰጡላቸው ስለፈለጉ: በስው ሀገር አገዛዝ የግብጽ ቤተ ክርስቲያን የማዘዝ ሥልጣን ስለሌላት አቡነ ባስልዮስ ለሥጋዊ አስተዳደር ተሾሙ። ከአቡነ ባስልዮስ በኋላ ደግሞ ለሥጋዊው አመራርም ቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ ተተኩ። እስከዚህ ከሞላ ጎደል ሕጋዊ ነው እንበል። በሥርዓተ መንግሥት ሁለተኛው በቀኖና አራተኛው ከሞቱ ወዲህ ግን ቤተ ክርስቲያኒቱ ሕጋዊት ናት ለማለት በጣም አስቸጋሪ ነው። አንደኛ በሲኖዶሱ ታሉት አበው ጳጳሳት የምትሏቸው በእየጋዜጣው እንደታየው አባታቸውን ከአረመኔ መንግሥት ጋራ ተባብረው ያስገደሉ ወንጀለኞች ናቸው።

ሁለተኛ ተክለ ሃይማኖትና መርቆርዮስ ከነሲኖዶሶቻቸው አባታቸውን ለሹመት ብለው ያስገደሉ የወንበዴ ጥርቅሞች እንጂ ጳጳሳት አይደሉም። ከቁጥርም አይገቡም።

ሦስተኛ: አምስተኛው ፓትርያርክ አቡነ ጳውሎስም: እሳቸውን ሦስት አድርገው የሾሟቸው ሕጋዊው ቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ ቢሆኑም: የራሳቸው ሥልጣን ልክ ቢሆኑም: ሌሎቹን አሷሷግቸው ግን ቀኖናዊ አይደለም። አሰኝና ዐረፉ። እኔም ምነው ለዚህማ በትግር ጊዜ አንድ ጳጳስ ብቻውን ሁኖ ሊሾም ይችላል ይል የለም ወይ በእየቤተ ክርስቲያኑ ያለው የቀኖና መጽሐፍ? አልሁና ወጠርሁ።

እሱም እሱማ በትግር ጊዜ ነው: የአሁኑ ፓትርያርክ ግን ለስርብትና ብለው ነው እንጂ ከግብጻውያን ወንድሞቻቸው አንዱን ጠርተው ሊያሽሹግቸው ይችል ነበር። ለመሆኑ ቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ የሾሟቸው ሕጋውያኑ: ከደግቸውም ያልገቡ ሊቃነ ጳጳሳት ባስልዮስ:

ጴጥሮስ አልነበሩም ወይ? ሰምን አነሱን ይዘው አልሸሙም አሰና ጠየቀኝ: እኔም አቡነ ጴጥሮስ ፈቃደኛ ሰላልሆኑ ነው ብዬ እውነቱን መለሰሁለት። እሱም የእናንተ ጳጳሳት ቀኖናውን ለሹመት: ለደመወዝ: በነገድና በጥቅም እየተገፋፉ: ቀኖና ቤተ ክርስቲያንን እያጥመሰመሱ ይሄዳሉና በሐሰት ሰዓለም አብያተ ክርስቲያን: ዓለም በጋዜጣ: በራዲዮ: በቴሌቪዥን ያወቀውን ስሕተቷን የግብጽ ቤተ ክርስቲያን ልክ ናት ብላ ጽፋ መሣቂያ እንድትሆን ነው ወይ የምትፈልገው? አለና ፈንታውን ወጠረኝ።

እንዲያውም አሁንማ ለሹመት ስትሉ በአየመንደሩ አንዳንድ ፓትርያርክ አበጃችሁና ዐረፋችሁ፤ የኢትዮጵያ ፓትርያርክ: የኤርትራ ፓትርያርክ: በአሜሪካ ያሉት የሦስቱ ክፍሎች ፓትርያርኮች: በጠቅላላ አምስት ፓትርያርኮች አሏችሁ። ከዚህም ሌላ በአየመንደሩ: ገጠሩ: ከተማው በባሕታዊ ስም የሚያስተምሩት የአነአባ መሸ በከንቱ ስብከት ከቅዱሳት መጻሕፍትም ሆነ ከወንጌል ትምህርት ጋራ አይገናኝም። ታዲያ በዚህ መካከል የትኛው ሥራችሁ ነው ልክ ነው ተብሎ የሚመሰክርላችሁ? ይህም ዓለማውያን ሰስርብትና ብለው ከሚያደርጉት ትግል ጋራ ቢመሳሰል እንጂ መነኮስ ከሚያደርገው ተጋድሎ ጋራ አይዛመድም። ብሎ ዐይኑን አፈጠጠብኝ። እንዴ! ታዲያ ምን ይሁን ማለትህ ነው? ብለው እንደገና ሀ ብላችሁ ካልጀመራችሁ በዘርዐ ክህነት ልክ ናችሁ አትባሉም አለኝና ወጉን ቀጠለ።

ከዚህም በላይ በጉባኤ ሊቃውንት ስም ቅኔና ዜማ እንጂ መጻሕፍት የት እንደዋሉ የማያውቁ ሰዎች አስቀምጣችሁ በኬልቂዶን ዲዮስቆሮስ የተወገዘው በሥነ ሥርዓት እንጂ በሃይማኖት አለመሆኑ እየታወቀ ለስርብትና ለሹመት ተብሎ የተነዛ ፕሮፓጋንዳ ይዘው ውሸት የሚነዙ ሰዎች ይዛችሁ የምትግበሰበሱ: ከሥርዓተ ረበናት ያልወጣችሁ: ክርስቶስን ከጳውሎስ ጋራ በደንብ ያልተቀበላችሁ: ክርስቲያን ስታዩ አመለጥነ መስኗችው አንድ ጊዜ እግዚአብሔር አብ የኢየሱስ ክርስቶስ በሥጋው የባሕርይ አባቱ ነው ብላቸሁ: አምቅደመ ዓለም ከአብ ያለ እናት: ድኅረ ዓሰም ከአመቤታችን ያለ አባት የሚለውን ክርስቲያናዊ ትምህርት የምታፋልሱ። አሁን ደግሞ መጻሕፍትን በሙሉ ፍቃችሁ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከፈጣሪያችን ከአግዚአብሔር አብ ጋራ አላስታረቀንም: አላግለደንም: አያስታርቀንም: አያግልደንም ብላችሁ የምትቀደዱ። ሳትነቁ ነቅታችሁ: ሳትበቁ በቅታችሁ ብትቆርቡ ሥጋው አሳት ሁኖ ይፈጃችኋል: ደሙ ባሕረ አሳት ሁኖ

ያሰጥግችኋል ብላችሁ ከቅዱሳት መጻሕፍት የወጣ ክሕደት የምትሰብኩ። አምስት ወይም አራት ውሉድ ሰእግዚአብሔር አብ አለው የሚል ክርስቲያን እንዳለ ሁሉ፥ ወልድ ዋሕድ ብላ የምታምን የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ብቻ ናት እያላቸሁ የምትዋሹ፥ ሌሎች አብያተ ክርስቲያናት የማይሉትንና የማያደርጉትን ስለርብትና ብላችሁ እንዲያው ከኪሳችሁ እያወጣቸሁ ሐሰት የምትበትኑ፥ ቂም ዘርታችሁ በቀል የምትሰበስቡ፥ ዛሬ ዓለም ሁሉ በቀድሞ ዘመን ባለመግባባት የተነጣጠሉት አብያተ ክርስቲያናት ሁሉ በሃይማኖት ካልሆነ በሥርዓት የተለያዩት ሁሉ ለመገናኘት በሚጥሩበት ጊዜ በሁለት ባሕርይ ምክንያት ያልነበረ እያወራቸሁ ልዩነትን በልብ ንጹሓን የምትተክሉ፥ ሰግኒያ አሐዱ መጻሕፍትን ገድላገድሉን ሁሉ ጨምራቸሁ ከ81:93 ያገባችሁ፥ ቃለ እግዚአብሔርን ከእናንተ ሐሳብ ጋራ ካልተስማማ ስትደልዙና ስትሰርዙ የማታፍሩ ሰዎች ምናችሁ ክርስቲያን ናችሁ ተብሎ ይመስከርላችኋል? ዲዮስቆሮስ የተወገዘው አንድ ባሕርይ በማለቱ ነው እያላቸሁ ያለምንም ኀፍረት ታወራላቸሁ፥ ታስተምራላቸሁ፥ ይህ ውሸት መሆኑን ግሪክ የተማሩ ልጆቻችሁ ከነገሯቸሁ ዘመናት አልፈዋል። እናንተ ግን አሁንም ሳናውቅ የምናወራው እኛ ነን እውነተኞች እያላቸሁ የሐሰት ፕሮፓጋንዳችሁን ትነዛላችሁ። የኬልኬዶን ጉባኤ የተደረገው በግሪክ ነው። ቃለ ጉባኤውም አለ፥ በዚህ ቃለ ጉባኤ ላይ ዲዮስቆሮስ የተገዘተው በሁለት ባሕርይ ምክንያት ነው የሚል ብታሳዩ የቀረው ዓለም ውሸታም እናንተ እውነተኛ ትሆኑ ነበር። ግን በኋላ የተፈጠረ የስርብትና ውሼት ስለሆነ እንደ ልግዳችሁ፤ የመላእክት ቋንቋ ግዕዝ ነው፥ ወልድ ዋሕድ የምትል ኢትዮጵያ ብቻ ናት፥ ቁርባን እያጸድቅም፥ እንዲያውም ያስቀሥፋል፥ ኢየሱስ ክርስቶስ ከእባቱ ጋራ አላስታረቀንም፥ እያስታርቀንም፥ ጓዴው መንፈስ ቅዱስም እያግልደንም፥ እይጸልይልንም እያላቸሁ እንደምትዘላብዱት ያለ ነው፤ ብዙ ሰዎች ሲግሩ ይህም ስሕተት መገለጡ አይቀርም። እንዲያውም ስለመንፈስ ቅዱስማ ያላችሁ ጥላቻ ከመቅዶንዮስ የባሰ ነው። ለዚህም ግስረጃ በመላ አዲስ አበባ ከሚገኙት 57 አብያተ ክርስቲያናት አንድ እንኳ በመንፈስ ቅዱስ ወይም ጸራቅሊጦስ የተሰየመ የለም፥ የእብና የወልዱን፥ የግርያምና የሚካኤል የገብርኤሉን እንተወውና ከእቦና ከቅዱስ ያሬድ ከዮሴፍ እንኳ እንሶ ይሆን? ይህን ሲያዩት እነዚህ ሰዎች እውነተኛ ክርስቲያኖች ናቸው ወይ? የሚል ጥያቄ ያሳድራል። እንኳንስ በቀናና ነው የሚሄዱ ብሎ ለመመስከር ይቅርና።

እምቅድመ ዓለም ከአብ ያለናት፡ ድኅረ ዓለም ከእመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ያለአባት ተወለደ፡ ወልደ አብ በመለኮቱ፡ ወልደ ማርያም በትስብእቱ ሁለት ልደት በተዋሕዶ ከበረ፡ ኢየሱስ ክርስቶስ ወልደ እግዚአብሔር አብ ሰው የሆነ አምላክ ነው፡ አምላክም ሰውም ነው የሚል፡ ብሎ የሚያምን ሰው ሁሉ ክርስቲያን ነው። ከዚህ የሚለይ ሁሉም የዲያብሎስ ወገን ነው። ሚናውን ይለይ፡ በግልጥ ይወግን።
ስለዚህ በትውፊት ምክንያት የሰበሰባችሁትን ተረት ትታችሁ ከዓለም አብያተ ክርስቲያናት ጋራ ተገናኙ። ጠላቶቻችሁን ለዩ፡ ወዳጆቻችሁንም ዕወቁ።
እንኳን በአለፈው ይቅርና አሁንም ክርስቶስ እንዳይታወቅ ወንጌል እንዳትሰበክ፡ ሰው ትምህርት ፈልጎ በ11 ሰዓት ሲመጣ በማይገባው ቋንቋ በግዕዝ እየዘመራቸሁ ጊዜውን አሳልፋችሁ ትሰዱታላችሁ። በመካከለኛው ዘመን የምዕራብ ካህናት ያደርጉት እንደነበረ። አሁንም እነደፈሪሳውያን ስድብ እንጂ ሃይማኖት እንደማታስተምሩ፡ አማረኛ የሚያውቅ አንድ ወዳጄ በአየደብሩ የሚሰጠውን ትምህርት ለሁለት ወር ከተከታተለ በኋላ ነግሮኛል። ብዙ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ተከታዮች ወደ ሌሎች ሰባክያን የሚሄዱበትም ምክንያት አሁን እናንተ የምትሰጡት ትምህርት ከመዝሙሩ ጀምሮ አፍራሽ እንጂ ገምቢ ስላልሆነ ነው፤ ርትዕት የተዋሕዶ ሃይማኖትን ያለምንም ስርብትና እየሰበኩ መናፍቃንን የሚመልሱትን ስላምን የሚያጠምቁትን እውነተኞችን፡ ሐቀኞችን ሰባክያን እነ አባ ገብረ መስቀልን በሸዋ እነ አምኃ ኢየሱስን በጎንደር ሌሎችንም በእየአውራጃው እንዳይሰብኩ ከልክላችኋል፡ ትክለክላላቸሁ። ሃይማኖተ አበውን ያለምንም ምክንያት ዘግታችኋል። አንተም በተለይ የንግግር ነጻነት ይስጡ የጋላ ገበር መሬት የምትሉትን ለሕዝቡ ይልቀቁ እያልህ በስውር እየጻፍህ ከአቤ ጉበኛ ጋራ የንግግር ነጻነት ባልነበረበት ዘመን እንደነ <u>ሀገር ምንድር ናት</u>? ያሉትን ጽሑፎች ትበትን እንዳልነበረ፡ አሁን እንደገና ስትታገልላት የኖርህ የንግግር ነጻነት ስትመጣ ዝም አልህ። ይህም በጠቅላላ ትግላችሁ ሁሉ ለምድራዊ ጥቅም እንጂ ለሰማያዊ ክብር አይደለም ማለት ነው አለና ዕቀጩን ነገረኝ።
በዘርዐ ክህነት በኩል ስላለው ቀኖና ለጊዜው እስከዚህ የተነገረው ይብቃንና በቀሩት በሰባቱ ሀብታት ደግሞ እንዴት እንደምትቀልዱ ባጭሩ ልናገር እፈልጋለሁ። ገንዘብ ካገኛችሁ በምስጢራተ ቤተ ክርስቲያንም ትነግዳላችሁ፡ ትለውጣላችሁ።

ለምሳሌ፡

አንደኛ፡ ያለ ቁርባን ተክሊል እንደሌለ እየታወቀ በሥርዓተ ተክሊል ስም ገንዘብ ተቀብላችሁ አገኝ ባጣውን ቀባጥራችሁ፡ ተክሊል አደረስንላችሁ ብላችሁ፡ ፎቶ ታስነሡና ትለቃላችሁ። ይህንም የጀመራችሁት ዐጤው ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ለልዑል ራስ መንገሻ የልጅ ልጃቸውን ልዕልት አይዳን ሲድሩ ነው።

ሁለተኛ፡ ጋብቻ ከስባቱ ሀብታተ ቤተ ክርስቲያን አንዱ ነው፡ ቅዱስ ነው ብላችሁ በቁርባን በሥርዕተ ተክሊል ካጋባችሁ በኋላ በውጤቱ ገዜ የቆረበች ሴት ስትወልድ፡ ራሰዋም ልጅዋም ርኩስ ናቸው ብላችሁ ጸበል ትረጫላችሁ። በዚህም ከክርስትና ይልቅ ራሱ ክርስቶስ ያወገዘውን ሥርዓተ ረበናትን፡ ከወንጌል አሪትን፡ ከክርስቶስ ጸሐፍት ፈሪሳውያንን ስታከብሩ ትታያላችሁ።

ሦስተኛ፡ በአርቶዶክሳውያን አብያተ ክርስቲያን ሁሉ ጥምቀት አንድ ጊዜ ብቻ መሆኑ እየታወቀ፡ እናንተ ግን በቁድር እያመካኛችሁ፡ የስላም ሥጋ በልተሃል፡ ከማንም ጋራ ተዳድፈሃል፡ ወድቀሃል፡ ረክሰሃል እያላችሁ ሰው ለንስሓ በተመለሰ ቁጥር ታጠምቃላችሁ።

አራተኛ፡ ምስጢረ ንስሓንም በስም እንጂ በግብር አታውቁትም ወይም ዐውቃችሁ፡ ለራሳችሁ ሐሳብ ስላልተስማማ ታጣምሙታላችሁ። ካረጁ ከጃጁ፡ ኃጢአት ለመሥራት ካቃተ በኋላ የሚደረግ አስመስላችሁ ስለምታቀርቡት፡ ምእመኑ በሙሉ ኃጢአት ለመሥራት ችሎታ ካለው፡ ነገ ብሰሳት እያለ ሳይናዘዝ በኃጢአቱ ተጠቅሎ ይሞታል፡ በዚህም ብታውቁም ባታውቁም ከፍርድ አትድኑም።

አምስተኛ፡ ጌታ ሥጋውንና ደሙን የሰጠው ለኃጢአት ማስተስረያ መሆኑን እያወቃችሁ፡ ሳትበቁ፡ ሳትነቁ ብትቀበሉት ሥጋው እሳት ሁኖ ይፈጃችኋል፡ ደሙ ባሕረ እሳት ሁኖ ያሰጥማችኋል እያላችሁ ታውጃላችሁ። ይህን ዐዋጃችሁን ተራምዶ፡ ፈጣሪዬ እንደ ምሕረትህ እንጂ እንደ አበሳዬ አይደለም፡ አድርግልኝ እንጂ አታድርግብኝ ብሎ በጥቡዕ ልቡና የቀረበውን ሰው ደግሞ፡ አስብበት በልጅነት ቁርባን ጥሩ አይደለም እያላችሁ በማስፈራራት ታባርራላቸሁ።

ስድስተኛ፡ ከዐሠርቱ ቃላትም ኃጢአት መስሎ የሚታያችሁ አታመንዝር ብቻ ነው እንጂ የተቀሩትን ግን ካህናቱም እንኳ ትተላለፏቸዋላችሁ። አትሰረቅ ትላላችሁ፡ ራሳችሁ ትሰርቃላችሁ። ያውም ታቦትና ጽላት፡ ሌላም ንዋየ ቤተ ክርስቲያን፡ ንዋየ ቅድሳት። ጥብቅና ትቀጥራላችሁ፡ ይህንም ለመረዳት በእየጊዜው በመገናኛ ብዙኃን የሚነገሩትን መከታተል ይበቃል። ለሹመት፡ ለገንዘብ፡ ለክብር

ስትሉ ሐሰት ፈጥራችሁ ታወራላችሁ፡ አባታችሁን በአድማ፡ በውሸት መስክራችሁ ታስገድላላችሁ። በትምህርት በችሎታ በዕውቀት በማስተዋል የሚበልጣችሁን ሀሉ፡ እንዳያስተምር፡ እንዳይሾም፡ እንዳይሸለም መናፍቅ ነው ትሉና በሐሰት ስሙን ታጠፋላችሁ። ከምእመናንም ጋራ ትሰያዩታላችሁ።

<u>ሰባተኛ</u>፡ በቀን የፈለጋችሁትን ያህል ለመባረክ ስትችሉ ታቦትም፡ ጽላትም ትሰርቃላችሁ።

<u>ስምንተኛ</u>፡ ከቃልቻና ከአጉሪ ቤት የመጣ ልማድ ይዛችሁ፡ ቤተ ክርስቲያን ስትገቡ ጫማ አውልቁ እያላችሁ ምእመናኑ በብርድ ለቁርጥማት ትዳርጋላችሁ።

<u>ዘጠነኛ</u>፡ የተበላው ሁሉ በስድስት ሰዓት እንደሚጠፋ እየታወቀ ከቁርባን በፊት 18 ሰዓት ካልጸማችሁ አትቆረቡም እያላችሁ ምእመኑን በረኃብ ታሰቃያላችሁ።

<u>ዐሥረኛ</u>፡ የጸሎትም ሕግና ሥርዓት ስለሌላችሁ ቤተ ክርስቲያን የገባ ምእመን ሁሉ በቃል ያጠና በቃሉ የተቀረጡም ደግሞ መጽሐፍ መጽሐፉን ይዞ ስለሚያኩተመትም፡ ቤተ ክርስቲያን ይሁን ምኩራብ አይታወቅም። ገባሬ ሠናይን ቄስ ከተራው ሕዝብ መለየትም አይቻልም። ሥራቸሁ ሁሉ ጨቂ ደብልቂ ነው። ለማስተማር ቢሞከርም ሁሉም ከቄስ አላንስም ስለሚልና ሃይማኖት በትምህርትና በእምነት መሆኑ ቀርቶ ዘሩን ስለሚቆጥር፡ ከጉንጭ አልፋ ጭቅጭቅ በቀር የምትማሩም ሆነ የምተረዱ አይደላችሁም።

<u>ዐሥራ ሐንደኛ</u>፡ ትገዘራላችሁም ትጠመቃላችሁም። መገዘሩስ ከጥምቀት በፊት ከሆነ ለተግባርና ለጤና ጥሩ ነው ትሉ ይሆናል። የሚያሳዝነው ግን ከጥምቀት በኋላ መገዘራችሁ ነው።

<u>ዐሥራ ሁለተኛ</u>፡ በዓለም አብያተ ክርስቲያን የማይደረግ በሳምንት ሁለት ሰንበት ታከብራላችሁ።

<u>ዐሥራ ሦስተኛ</u>፡ የቆረበ ሁሉ ሕጉ ወይም አሚኑ ብትሞት መመንኮስ እንጂ ሌላ ቆርቦ ማግባት አይችልም እያላችሁ ሕዝቡ እንዳይቆርብ ታስፈራራላችሁ።

<u>ዐሥራ አራተኛ</u>፡ በጠቅላላ የምታምኑትም የምታከብሩትም ከወንጌል ይልቅ ያለፈችውን አሪትን፡ ከቅዱሳት መጻሕፍት ተረትን፡ ከሃይማኖት ስርብትናን፡ ከሊቃውንት ባልቴትን ነው።

<u>ዐሥራ አምስተኛ</u>፡ በጥንታውያን፡ ምሥራቃውያን፡ አርቶዶክሳውያን አብያተ ክርስቲያናት ከታወቁት ሰባቱ ምስጢራተ ቤተ ክርስቲያን ከአምስቱ አዕማደ ምስጢር ጋራ አማታችሁ ወይም ተማቶባችሁ ሀብተ ከህነትንና ሀብተ ተክሊልን ትፍቃላችሁ።

0ሥራ ስድስተኛ፡ መጽሐፉ ግብዣ ስታደርግ ሀብታሞችን፡ ጓደኞችህን አትጥራ ምንአልባት እነሱም ብድር ለመመለስ ይጠሩህና ብድር እንዳይሆን እያለ፡ በዋስና በሙሴ (በዳኛ በሊቀ መንበር) የሚበላ፡ የሚጠጣ ማጎበር ያጸድቃል እያላችሁ ትሰብካላችሁ፡ ትባርካላቸሁ።

ሌላም ሌላም ብዙ ጉድለት አለ። ይህን ሁሉ ዛሬ ያለው በሰም ጉባኤ ሊቃውንት ሳይሆን በእርግጥ የተማሩ፡ ለስርብትና ሳይሆን ለሃይማኖት የሚያደሉ ሊቃውንት ሰብስባችሁ፡ የሮም ቤተ ክርስቲያን በሁለተኛው የባቲካን ጉባኤ ሥርዓቷን ሁሉ እንዳስተካከለች፡ እናንተም ማስተካከል አለባችሁ። ራሳችሁንም ካረማችሁ፡ ሥርዓታችሁን ካስተካከላችሁ፡ ሥራችሁ ስለሚመሰክር ከማንም ምስክር አያስፈልጋችሁም። እኛ ግን በዚህ ሁሉ ጉድለት መካከል እንዴት አድርገን ነው ይህች ቤተ ክርስቲያን ቀኖናዊት ናት ሥርዓቷም ትክክል ነው ብለን ለእነቶቻችን አብያተ ክርስቲያናት የምንመሰክረው? አለኝና ዐረፈ።

እኔም ይህን ሁሉ ሐቅ ለማስተባበል ብሞክር እንደ ተሟጋች ውሸታም ስለምሆን፡ ንዴቴን በልቤ አምቄ፡ እንዳልዋሽ ፈርቼ ዝም አልሁ። ወይ ነዶ! ህገርህና ሃይማኖትህ እንዲህ ሲዋረዱ እያዩ እንዳላዩ፡ እየሰሙ እንዳልሰሙ ዝም ማለት ምን ይደረግ? ዕቅም የለ? ማስተማሪያ ሚዳ የለ? አስተምራለሁ ብትል ጥቅማቸው የተነካ የሚመስላቸው አጭበርባሪዎች ሕዝቡ እንዳይጠጋህ፡ ከዚህ በፊት በብዙ ሊቃውንትና በእኔም እንደደረሰው በጥሩው ሰባኪ ላይ የመናፍቅ ስም ያወጡለታል: ሕዝቡም ያንን ይዞ ስለሚያዋክበው ትምህርቱም ጥረቱም ከንቱ ሁኖ ይቀራል እያልሁ ዝም ብዬ ሳስላስል፡ ወንድሜ! ከዚህ በፊት መረጃ በሌለው ነገር፡ በስርብትና የተወራውን ሁሉ እንዳንዳንድ ውሸታም ጋዜጣ ቆጥረን እገሌ ነው እንጂ እኔ አላጠፋሁም፡ ልክ ነኝ ማለቱን ትተን፡ ጉንጭ አልፋ ንትርክን ትተን፡ በቅዱሳት መጻሕፍት ብቻ ተነጋግረን አንድ እንሁን፡ ይህ ካልሆነ ሁሉም ወገኑን ለማጽደቅ: ሌላውን ስመኮነን በሚፈጥረው ተረት ክርስቲያናች የወገናችን ጠላት፡ የጠላታችን ረዳት ሁነን እንቀራለን። ይህ እንዳይሆን ጸሎታችንም እምነታችንም የሚከተለው ይሁን አለና ጸለየ፤ <u>አቤቱ አምላካችን ሆይ! የአንተን በልጅህ ፈጣሪ ዓላማትነት፡ የልጅህን አምላክነትና ሰውነት፡ መላኩቱንና ትስብእቱን፡ በመስቀሉ ዓለሙን ማዳኑን፡ የመንፈስ ቅዱስን ሕይወትነት፡ የመላእክትን ተራዳኢነት፡ የሰማዕታትን፡ የጻድቃንን አማላጅነት፡ የልጅህን ሥጋና ደም መስተስርዩ ኃጢአትነት የምናምን ክርስቲያን ሁሉ በፍቅረ ንዋይና በሹመት</u>

ምክንያት ከሚመጣብን መለያየት ድነን፥ በአንድነት ኑረን መንግሥትህን እንወርስ ዘንድ ቅዱስ መንፈስህን ላክልን ብሎ ጸለየ። እኔም በጸሎቱ ተስማምቼ ውይይታችንን ፈጸምን።

አሁንም አምላካችን ሆይ! በዚህ መጽሐፍ አነሣሽነት አብያተ ክርስቲያናትን የሚያገናኝ የፍቅር መንፈስህን ላክልን። አሜን።

መፍትሔ ታላት

ሕልመ ሌሊት	=	ብሪቱ አጨላ፥ የሕልም ወሲብ። ተጸብአ።
መሥዋዕት	=	የደም ቁርባን፥ የእህል ለአምላክ የሚቀርብ ገጸ በረከት ነው። ስበደል ግስተሰረያም ለአኩቴትም ይቀርባል። ስሰ አዳም ኃጢአት ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በዕፀ መስቀል ላይ ራሱን መሥዋዕት አድርጎ ለእግዚአብሔር አብ ለአባቱ አቅርቧል። በዚሁ አርአያም ዘለዓለም በተቀደሰ ቁጥር ሊሠዋ ይኖራል።
መቅደስ	=	መቀደሻ ቦታ ነው። የእኛ ቤተ ክርስቲያን በሦስት ትከፈላለች፤ ቅኔ ግሕሌት፥ ቅድስት፥ መቅደስ። በኦሪት ቅድስተ ቅዱሳን ይባል ነበር። ታቦቱን የያዘው መንበር የሚገኘውም በዚህ ውስጥ ነው። መቅደስ ቤተ ክርስቲያን ማለትም ነው። ስሎሞን የሠራው ቤተ መቅደስና የአይሁድ ምኩራብም መቅደስ ይባላሉ።
መቅድመ መቅድም	=	የመቅድም መቅድም፤ ይህ ውሳኔ የተሰጠው ለመጀመሪያ ገዜ በዚህ መጽሐፍ ነው። እሱም ከመቅድሙ በፊት መጥቶ ብዙ ይናገራል።
ግዕረገ ክህነት	=	የክህነት መዓረግ ወይም ግዕረግ፥ የክህነት መዓርጋት ሦስት ናቸው፤ ዲቁና፥ ቅስና፥ ጵጵስና። የተቀሩት ሊቀ ዲያቆናት፥ ሊቀ ካህናት፥ ሊቀ ጳጳሳት ወዘተ የአስተዳደር አስማት ናቸው።
ምስጢር አየ	=	ለመጀመሪያ ጊዜ አዲስ የተካነ ዲያቆን ቤተ ልሔምና መቅደስ ገብቶ ቀሳውስት በሽሽግ የሚሠሩትን ግብረ መሥዋዕት አየ፥ ተግረ፤ የቅዳሴ ሽፋንፋን ሥራ ተገለጠለት። ይህ መጽሐፍ ሁሉንም ስሰተናገረ ይህ የድብብቆሽ ሥራ አክተመ።
ሠራዒ ዲያቆን	=	ገባሬ ሠናይ ዲያቆን፥ ዋናው ዲያቆን።
ሥጋ መለኮት	=	የመለኮት ሥጋ፥ የቅዱስ ልጅህን ሥጋ

ሠራዒ ዲያቆን = ገባሬ ሠናይ ዲያቆን፥ ዋናው ዲያቆን።

ሥጋ መለኮት = የመለኮት ሥጋ፥ የቅዱስ ልጅህን ሥጋ ያደረገው ዘንድ ቅዱስ መንፈስህን በዚህ ጎብስት ላይ ላክ ብሎ ካህኑ ሲጸልይበት በጎይለ መንፈስ ቅዱስ ጎብስቱ ተለውጦ ፍጹም የመለኮት ሥጋ ይሆናል። ከዚህ በኋላ ሥጋ መለኮት ይባላል። ጌታ ሥጋዬን ብሉ ያለውም ይህንን ነው።

ረቢ = ረበነ አስተማረ ካለው ግሥ የመጣ ሣልስ ቅጽል ስለሆነ አስተማሪ ማለት ነው። በመጀመሪያ ሊቅ፥ ዐዋቂ፥ አስተማሪ ማለት ነበረ፥ በኋላ ግን ዐዋቂ ነን ባዮች በግብራቸው እየተንጠረዘዙ በአመላቸው ከጸሐፍትና ፈሪሳውያን ጋራ በግብዝነት ስለተገናኙ የግብዝነት፥ የከንቱነት ትርጉም ተሰጥቷቸው በነጠላ ረቢ በብዙ ረበናት ይባላሉ፥ ክብሉይ ኪዳን የሌለ ለራሳቸው ተከብሮ የሚመች የመሰለ ብዙ ሥርዓት ፈጥረዋል።

ስርየት = ይቅርታ፥ ማጥፋት፥ መፋቅ፥ ድምሳሴ።

ቅድስት = ከቅኔ ማሕሌትና ከመቅደስ መካከል ያለው ቦታ፥ በክብ ቤተ ክርስቲያን ሁለተኛው ዙር።
የተቀደሰች፥ የተለየች ሳድስ ቅጽል፤ የዐቢይ ጾም መጀመሪያው ሳምንት።

ቁርባን = ለእግዚአብሔር የተሰጠ። ሥጋውና ደሙ። በዘመነ አሪት የእህል ውሃ መሥዋዕት። ዛሬ ለሙት ፍትሐት የሚደረገው ሁሉ፥ መሐራው፥ ዘኬው፥ መክፈልቱ፥ የአባታችን ሙት ዓመት አስቆረብነ እንዲሉ።

ተጸብኦ = ሕልመ ሌሊት፥ ብሪቱ አጨላ።

ተረፈ መሥዋዕት = አኮቴትና እቶን፥ ከመሥዋዕት የተረፈ።

ታቦት = የጽላት ማኅደር፥ በስመ ኀዳረ ይጼዋዕ ማኅደር= በአዳሪ ሁኖ በጽላት ስም ታቦቱ ገባ፥ ታቦቱ ወጣ ይባላል፥ ጽላቱ ግለት ነው።

ትሩፋት = ከታዘዘው በላይ እጸድቅ ብሎ የሚሠሩት ምግባረ ሠናይ ሁሉ።

ትውፊት = ዘአንበሩ አበው፥ ከአባት ወደ ልጅ ሲወርድ ሲዋረድ የመጣ። በቤተ ክርስቲያን ከዮሐንስ ወንጌላዊ ጎልፈት ወዲህ ያለው፥ በታል የመጣው ሥርዓት ሁሉ ትውፊት ወዲህ ነው።

ንስሓ = ጸጸት፥ በሠራው ኃጢአት ማዘን፥ መጸጸት። ንስሓ ገባ፥ በሠራው ኃጢአት ተጸጽቶ ኃጢአቱን ለካህን ነግሮ፥ ጹም ጸልዮ ሰርየት ተቀበለ። ከክፉ ሥራው ተመለሰ።

የንስሓ ልጅ = የነፍስ ልጅ

የንስሓ አባት = የነፍስ አባት፥ አበ ነፍስ፥ መምህረ ንስሓ።

ንፍቅ ቄስ = ረዳት ቄስ፥ ግማሽ ቄስ።

ነፍቅ ዲያቆን = ረዳተ ዲያቆን፥ ግማሽ ዲያቆን

አማናዊ = እውነተኛ፥ እርግጠኛ።

አምልኮት = ግምለክ፥ አምላክ ነህ፥ ነው ብሎ ማመን፥ ለፈጣሪ ለአምላክ የሚገባ አምልኮት መስጠት፥ ማቅረብ፥ ጓደኛው አክብሮት ነው፥ ስለዚህ ስግደት በሁለት ይከፈላል፤ የአምልኮትና የአክብሮት ተብሎ፤ የአምልኮት ስግደት ለአምላክ ብቻ፥ የአክብሮት ግን እጅ መንሣት ነው፥ በዕድሜም በማዕረግም ለሚበልጥ ሁሉ ይደረጋል፥ ስግይበልጥ ለስትሕትናና ፍቅር ይሰጣል።

አግለደ = አግላጅ፥ ተግላጅ፥ በዳይና ተበዳይን፥ ተበዳዩን ለምና ግለታረቅ ነው። በዚህም አግላጅ ከተግላጅ በክብር የማያንስበት ነገር የለም። እኩል ናቸው። እንዲያውም

አግላጅ የሚያጸፍበት ጊዜም ይኖራል። ስለዚህ ነው ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በዳዩን አዳምን ከጌታው ከእግዚአብሔር አብ ከተበዳዩ ጋራ አግለደው፥ አስታረቀው የሚባለው።

አክብሮት = ግክበር፥ የአክብሮት ሰጊድ አምልኮትን ፅይ።

አኩቴት = ለሥጋው የሚቀርበውን ጎብስት ለመምረጥ ተብለው የሚሠሩት ሦስቱ አምባሻ መሳይ ጎብስቶች አኩቴት ይባላሉ። ከሦስቱ አንዱ ተመርጦ ይቀደስበትና ፈኑ መንፈሰ ቅዱሰ ይረስዮ ሥጋ ወልድከ ሲል መንፈስ ቅዱስ ይሰውጠውና ሥጋ ወልደ እግዚአብሔር ይሆናል።

የቀሩትን ሁለቱን ግን አምስቱ ቀዳስያን ይካፈላቸዋል፥ እንደ መቁረር ግገልገላቸው ነው።

አውሰቦ = ጋብቻ፥ ሰብሳብ፥ ከብካብ፥ ወሲብ፥ ሕገ ሰብሳብ።

እቶን = ታል ለታል ምድጃ፥ ግዕድ ቤት፥ ግብሰያ፥ መጋገሪያ ግለት ነው። በኋላ ግን በቅዱታ የተሰፈረው ስንዴ ከሦስቱ አኩቴት ሲተርፍ እያደቦለቦሉ ይሠሩና ምስጢር ያዩ ሁሉ ይካፈሉታልI ያነሡታል ነው የሚባለው።

ካንቻ = መመንጥር፥ ካንቻ መታ ዱሩን መነጠረ፥ ደኑን ጨፈጨፈ።

ዐቅመ አዳም ደረሰ፥ አደረሰ ለጋብቻ ደረሰ።

ዐቅመ ሔዋን ደረሰች = ባለቀች

ዐውደ ምሕረት = ከቤተ ክርስቲያን በስተ ምዕራብ የሚገኘው አደባባይ።

ዐውድ = አደባባይ። የጻሕል ግስተመጫ።

ዕርቅ = ዐረቀ፡ አዕረቀ፡ ታረቀ፡ ተራረቀ፡ አስታረቀ፡ አስተራረቀ፡ ሁለት የተጣሉትን ወገኖች አንተም ተው አንተም ተው ብሎ አስታረቀ፡ አስማማ ማለት ነው። ማስታረቅ የሚያሳየው የሦስቱንም እኩልነት ነው። በቋንቋው አስታራቂም ተራራቂም እኩል ናቸው፤ ስለዚህ በጌታ አማኝነት ከአስታረቀ ይልቅ አማለደ ይመረጣል፡ ሰለምን ቢሉ አዳም ፍጡር ነውና ከፈጣሪው ከጌታው አማላጅ ያሻዋል፡ አስታራቂም ያስፈልገዋልና። አስታራቂውም አማለደውም ይባላል።

ዘርዐ ክህነት = ከጌታ ጀምሮ እስከ ዓለም ፍጻሜ ከጳጳስ ወደ ጳጳስ ሲወርድ የሚኖረው ሀብተ ክህነት ዘርዐ ክህነት ይባላል።

ዘአንበሩ አበው = ትውፊት

ገባሬ ሠናይ = ሠራዒ ቄስ ይባላል፡ መሪው ቄስ፡ በቅዳሴ ጊዜ።

ጌዶ = ውል፡ እንዲህ ቢሆን፡ እንዲህ ባይሆን ተብሎ። ሕፃን ልጅ በጌዶ ትዳራለች። እስከ 12 ዓመቷ ላይነካት ቃል ገብቶ፡ ከአግቷ ቤት ልታድግ፡ አንደኛ ሌላ እንዳይወስዳት ሁለተኛ የአግቷን ጠባይና ሙያ ለምዳ እንድታድግ።

ጥንተ አብሶ = የበደል መጀመሪያ፡ አዳም ጌታችን አትብላ ያለውን ዕፀ በለስ በልቶ ያመጣው መቀጮ፡ ጥፋት፡ ኃጢአት፡ በደል። ይህ በክርስቶስ ሞት፡ በዕለተ ስቅለት፡ በላዕለ መስቀል ጠፍቷል። ከዚያ ወዲህ ክርስቶስን የተቀበለ ሁሉ፡ ሁሉም አዲስ ፍጥረት ነው።

ጸሎተ ማኅበር = የማኅበር ጸሎት የኅብረት ጸሎት። በጸሎተ ማኅበር የሚሳተፉ ሁሉ ሰላምና ኅላግ

ሊናራቸው ያሰፈልጋል፡ ያለዚያ ጸሎቱ ሁሉ ያህያ ጩኸት የእሽኮኮ ጸሎት ይሆናል።

ጳሕል = በመጀመሪያ ጎብስቱ በኋላ ሥጋው የሚቀመጥበት ዝርግ ሳህን።

ጽላት = ዐሠርቱ ቃላት የተጻፈበት ሰሌዳ፡ ከዕፀዋትና ከአእባን ዐይነት ተመርጦ ይቀረጻል። የሚከበረውም በላዩ ላይ ስመ እግዚአብሔር ስለተጻፈበት ነው። የእግዚአብሔር ስም ከሌለበት ግን ተራ ዕንጨት ወይም ደንጊያ ነው።

ጽዋዕ = ከልዩ ልዩ ብረታ ብረትና ሸክላ የሚሠራ የፈሳሽ መያዣያ ዕቃ። በቅዳሴ ግዜ በመጀመሪያ ወይኑን በኋላ ደሙን ቀላውስት የሚያስቀምጡበት ዕቃ።

ስዚህ መጽሐፍ አስትዋፅኦ ያደረጉ መጻሕፍት መጀመሪያ በግዕዝና በአማርኛ ከዚያ በሌሎች ቋንቋዎች፤

1. ሃይማኖተ አበው በኢትዮጵያ አረቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን፥ ትንሣኤ ዘጉባኤ ማ/ቤት፥ አ.አ
2. አቡነ መልከ ጼዴቅ፥ ትምህርተ ክርስትና 2ኛ መጽሐፍ፥ ትንሣኤ ዘጉባኤ ማ/ቤት አ.አ. 1984 ዓ.ም.
3. መሓሪ ትርፌ (ሊቀ ሊቃውንት በኋላ የጎንደር ሊቀ ጳጳሳት) የአርቶዶክሳውያን ምእመናን እምነት ፥ አርቲስቲክ ማ/ቤት አ.አ. 1951 ዓ.ም.
4. መኩሪያ አብዩ ሆይ (ንቡረ እድ) መዝገበ ሃይማኖት ወጸሎት ፥ ብርሃንና ሰላም ማ/ቤት አ.አ. 1969 ዓ.ም.
5. መዝገበ ሃይማኖት በመንበረ ጸባዖት ቅድስት ሥላሴ ካቴድራል የድርሰት ክፍል ተዘጋጀ። 1959 ዓ.ም.
6. ምስጢረ ሥላሴ፥ በብፁዕ ሊቀ ጳጳሳት አቡነ ማቴዎስ ዘመንግሥተ ኢትዮጵያ ፈቃድ የታተመ በ1903 ዓ.ም.
7. ሞገሰ ዕቁባ ጊዮርጊስ (ሊቀ መዘምራን) ኮከበ ጽባሕ ማ/ቤት አሥመራ፥ 1958 ዓ.ም.
8. ሰማንያ አሐዱ መጻሕፍት በሞላ፥ ቅዱስ ወንጌል ንባቡ ከነትርጓሜው ብርሃንና ሰላም ማ/ቤት፥ አ.አ. 1959 ዓ.ም.
9. ሰዓታት ዘሌሊት መዘነግሀ፥ ተሰፋ ገብረ ሥላሴ ማ/ቤት፥ አ.አ. 1960 ዓ.ም.
10. ስለሁለተኛው የባቲካን ጠቅላላ ጉባኤ፥ ብርሃንና ሰላም ማ/ቤት፥ አዲስ አበባ፥ 1954 ዓ.ም.
11. በፈቃዱ የተመኘ፥ አርቶዶክሳዊት ቤተ ክርስቲያን 7ቱ ምስጢራተ ቤተ ክርስቲያን፥ ተሰፋ ማ/ቤት አ.አ. 1948 ዓ.ም.
12. የባቲካን 2ኛ ጠቅላላ ጉባኤ ደንብ፥ ብርሃንና ሰላም ማ/ቤት አ.አ. 1955 ዓ.ም.
13. ተአምረ ማርያም፥ ትንሣኤ ዘጉባኤ ማ/ቤት አ.አ. 1976 ዓ.ም.
14. ተዐቀቡኬ እምሐሳዊያን ነቢያት፥ ከኢትየጵያ አርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን መንበረ ፓትርያርክ ለምእመናን የተዘጋጀ ትምህርት፥ አልቦ ማ/ቤት፥ 1986 ዓ.ም.
15. አባ ቴዎፍሎስ ሊቀ ጳጳሳት ዘሐረር ወዘኩሉ አድያሚሃ፥ መዝሙረ ዳዊት ንባቡና ትርጓሜው፥ አርቲስቲክ ማ/ቤት አዲስ አበባ፥ 1950 ዓ.ም.

16. አየለ ተክለ ሃይማኖት (ዶክተር አባ) የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ስለክርስቶስ ባሕርያት አካላዊ ተዋሕዶ የምታምነው ትምህርት፡ ኢጥርስ ሲላ ግ/ቤት አሥመራ 1951 ዓ.ም.
17. አምስቱ አዕማደ ምስጢር፡ ተስፋ ገብረ ሥላሴ ግ/ቤት አ.አ. 1975 ዓ.ም.
18. የኢትዮጵያ አርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን መንበረ ፓትርያርክ፡ ተወቀቡኬ እምሐሳውያን ነቢያት አ.አ. ሐምሌ 4 ቀን 1986 ዓ.ም.
19. ክንፉ ገብርኤል አልታየ (ሊቀ ካህናት) ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን ትንሣኤ ዘጉባኤ ግ/ቤት አ.አ. 1983 ዓ.ም.
20. ወልደ ሚካኤል ብርሃነ መስቀል (መምህር) ገብረ ሕግግት፡ አርቲስቲክ ግ/ቤት አ.አ. 1942 ዓ.ም.
21. ወደ ዘላለም ሕይወት የሚመራው እውነት።
22. ውዳሴ ግርያምና ቅዳሴ ግረያም፡ ብርሃንና ሰላም ግ/ቤት አ.አ. 1943 ዓ.ም.
23. ዓለማየሁ ሞገስ፡ ሠርግና ልግድ፡ ብርሃንና ሰላም ግ/ቤት አ.አ. 1956 ዓ.ም.
24. የሴት አቅኖም በክርስቲያን ኢትዮጵያ፡ ከሐሙራፒ እስከ 1967 ዓ.ም. የ4000 ዘመን የታሪክ ሂደት በ1969-71 በእጅ ጽሑፍ ተባዝቶ የተበተነ።
25. ያሬድ (ቅዱስ) መጽሐፈ ድጓ፡ ብርሃንና ሰላም ግ/ቤት፡ አዲስ አበባ፡ 1954 ዓ.ም.
26. ይሁ ነው ዘለዓለማዊ ሕይወት፡ (በግሪክ) Brooklyn, New York, U.S.A. 1953.
27. ሠራዊተ ክርስቶስ ግጎበር፡ የይሐዋ ምስክሮችና ሃይማኖታቸው፡ አርቲስቲክ ግ/ቤት፡ አ.አ. 1984 ዓ.ም.
28. ገብረ እግዚአብሔር (አባ) መጽሐፈ ብርሃን፡ ኮከበ ጽባሕ ግ/ቤት፡ አሥመራ፡ ዓ.ም.
29. አቡነ ገብርኤል ሊቀ ጳጳሳት ዘኤርትርያ፡ የአርቶዶክስ ሃይማኖት አንደኛ መጽሐፍ፡ የኢትዮጵያ ጥናቶች ማእከል፡ አሥመራ፡ 1976 ዓ.ም.
30. ፍትሐ ነገሥት፡ ሮማ፡ 1897 ዓ.ም.

Books referred to in Foreign Languages

Aeschliman, Professor Carlos, The Faith of Jesus, Central American Union.
Bancroft, E.H., Teologia Elementare, Seconda Editione, Editione Centro Biblice, Napoli, Italia, 1977.
Bible Readings for the Home, Review and Herald Publishing Association, Washington D.C. 1972.
Charles Caldwell Ryrie, A Survey of Bible Doctrine, Moody Press, Chicago, 1972.
Kautsby, Karl, Foundations of Christianity. Orbach and Chambers, London, 1925.
Let God be True, Brooklyn, New York, U.S.A 1953.
Make Sure of All Things, Brooklyn, New York, U.S.A. 1953.
O'Brien, John A., Ph.D., LL.D., The Faith of Millions, London, W.H. Allen 1952.
Owen, John, D.D., The Holy Spirit, KREGEL Publications, Grand Rapids, Michigan, U.S.A. 1973.
Pesch, Otto, Hermann, Breve Catechismo Cattolico, Terfa Editione, Queriniana, Brescia, 1976.
Pope John, Sunday Missal, Buckley, Michael, Revin Mayhew Publications, 1978.
The Illustrated Catechism, A Redemptorist Publications G.B. 1980.
Hammovd, T.C., In Undertaking Be Men, Inter Varsity Press, Great Britain, 1971.
Sheed, F.J., Theology and Sanity, New England Edition, Sheed & Ward, London, 1978.
SCHLEIERMACHER, FRIEDRICH, The Christian Faith, T & T. Clark, 38 George Street, Edinburgh, 1976.
Tucber, Ruth, Strange Gospels, Marshal Pickering, U.S.A. 1991.

	ገጽ
መቅድመ መቅድም	4
1. እኛስ የተሰቀለውን ክርስቶስን እንሰብካለን	"
2. የክርስትና መሥራች	"
3. ይህን መጽሐፍ ዳር እስከዳር	"
4. ወደኔቅረቡ መጨረሻቸው ጥፋት	5
6. የበሰበሰ ዝናብ አይፈራም	"
7. ትምህርት ቀናን ያሻሽላል	"
8. ክርስቲያን ምንድር ነው?	"
9. በእምነት ሁላችሁም	"
10. በእግዚአብሔር መንፈስ የሚመሩ	6
11. የልጅነቱና የወንድምነቱ ቃል ኪዳን	"
12. በእግዚአብሔር መንፈስ የተጻፈ	"
መቅድም፡	7
መግቢያ	20
ምዕራፍ 1፡	23
ምስጢረ ሥላሴ	"
1. የሥላሴ አንድንት ሦስትነት	"
2. ምስጢረ ሥላሴ በሐዲስኪዳን፡ በጌታትምህርት	"
3. ምስጢረ ሥላሴ በሐዋርያት	24
4. ምስጢረ ሥላሴ በመዝገበ ሃይማኖት	"
4.1 መዝገበ ሃይማኖት በግዕዝ	"
4.1 መዝገበ ሃይማኖት በአማርኛ2	6
5. ጸሎተ ሃይማኖት	28
5.1 ጸሎተ ሃይማኖት በግዕዝ	"
5.1 ጸሎተ ሃይማኖት በአማርኛ	29
6. ጸሎተ ሃይማኖት የት መጣ?	30
7. ሥላሴ በብሉይ ኪዳን	31
8. ሥላሴ በሊቃውንት	32

		ገጽ
9.	ሥላሴ በጠቅላላ በቅዱሳት መጻሕፍት	33
9.1	ኢየሱስ ክርስቶስ ከሦስቱ አካላት አንዱ ነው	"
9.2	ኢየሱስ ክርስቶስ ወልደ አምላክ ነው	"
9.3	ወልድ ከአብ ጋራ በመለኮቱ ዕሩይ ነው	"
9.4	የእግዚአብሔር አብ ምስክርነት	34
9.5	በጊዜ ጥምቀት"	
9.6	የራሱ የጌታችን ኢየሱስ ምስክርነት	"
9.7	እውነት እውነት እላችኋለሁ	35
9.8	በእግዚአብሔር ልጅ ታምናለህ?	"
9.9	እኔን የሚጠላ አባቴን ይጠላል	"
9.10	አብ ሙታንን እንደሚያስነሣ	"
9.11	እኔ ራሴን ባከብር ...	"
9.12	ዮሐንስ መጥምቅ	"
9.13	ዮሐንስ ወንጌላዊ	"
9.14	ቅዱስ ጳውሎስ3	6
9.15	ሌሎች ሐዋርያት	"
9.16	መናፍስት	37
9.17	ነቢያት	"
10.	ሥላሴ በመናፍቃን	"
11.	የምስጢረ ሥላሴ መደምደሚያ	40
ምዕራፍ 2፥		43
ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ አግላጅም ተግላጅም ነው፤		"
ክርስቶስ እላግለደም ለምን ተባለ?		
በእየጊዜው የመጡትን ስሕተቶች መግለጫ፥		
አላዋቂዎች እንደ ሥጋውና ደሙ ይቆጠራሉ የሚሏቸው፥		
ስለአብና ግርያም የጋብቻ ሮሮና መወድስ።		
የግስታረቅና የግግለድ መግለጫ		47
የክርስቶስን አግላጅነት ለመካድ የተበተነ ክታብ፥		48
የክርስቶስ ወልደ እግዚአብሔር አግላጅነት ምስክሮች፤		50
እግዚአብሔር አብ አባቱ፥		"
ራሱ ኢየሱስ ክርስቶስ ወልደ እግዚአብሔር		"
ነቢያት		51
ሐዋርያት		"
ሊቃውንት		52

	ገጽ
ምዕራፍ 3፡	55
ጎሩይ ማእከለ እግዚአብሔር ወሰብእ ከለውና ከእግዚአብሔር መካከል ያለ ጎሩይ።	"
የጎሩይነት ምስክሮች	"
ነቢያት	"
ራሱ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ	"
ቅዱስ ጳውሎስ	"
ምዕራፍ 4፡	56
ሥጋ ለብሏልI	"
ሥጋ በመልበሱም ምክንያት ከአባቱ የሚያንስ የሚያስመስሉ ጥቅሶችI	"
ምዕራፍ 5፡	59
አዳምን ሰማዳን፡ ከአብ ተልኮ መጥቷል፡ ታዝዟል።	"
ከአብ መላኩን የሚያስረዱ ጥቅሶች	"
ራሱ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስI	61
ቅዱስ ጳውሎስ	62
ቅዱስ ዮሐንስ ወልደ ነጎድጓድ (ሐዋርያ)	"
ቅዳሴን የጻፉ ሊቃውንት	"
ምዕራፍ 6፡	66
ክርስቶስ ቤዛና መድኀኒታችን ነውI	"
የቤዛና የመጽኀኒት ልዩነት መግለጫ፡	"
ጌታችን ወደዚህ ዓለም የመጣበት ምክንያት፡	"
ምዕራፍ 7፡	68
የዓለም ብርሃን ክርስቶስ፡	"
የዓለም ብርሃንነቱን የሚመሰክሩ ጥቅሶች	"
እሱ፡ ራሱ ኢየሱስ ክርስቶስ	"
ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ አርአያና መምህር ነውI	69
የጌታችንን አርአያነትና መምህርነት የሚመሰክሩ፡	
ምዕራፍ 8፡	72
ጥምቀት፡	"
ምዕራፍ 9፡	74
ሜሮን	"
ምዕራፍ 10፡	75
ተክሊል	"

	ገጽ
ምዕራፍ 11፡	76
ህብተ ቀንዲል	"
ምዕራፍ 12፡	78
ጸም፡ ጸሎት፡ ምጽዋት፤	"
ጸም፡ ጸሎት፡ ምጽዋት ከጌታ በፊትም ነበሩ።	82
የጌታው ትሩፋት ከሌሎች በምን ይለያል?	"
ምዕራፍ 13፡	84
ጸሎት	"
ጸሎት ከሦስት ይከፈላል፡	85
የጸሎት ቦታ፡	86
ጸሎት በግልም በመግነበርም፡	"
ጸሎት እንዴት ነው የሚጸለየው?	"
ምዕራፍ 14፡	87
ንስሓ	"
ንስሓ መቼ? እንዴት? ለማን? ለምን?	"
ምዕራፍ 15፡	90
ቁርባን፡	"
ሕዝብ ሁሉ እንዲቆርብ የተደረገ ተጋድሎ፡	"
ካህናቱ ሕዝብ አይቆርብም ስላሉ የተበተነ ክታብ፡ (ከብዙው አንዱ)	"
ቁዱስ ቁርባንን ሰሚሸጡ ሰዎች የተሰጡ ቅጄያት።	103
ምዕራፍ 16፡	107
ለሥጋው ደሙ የሚቀርበው ኅብስት፡ መይን፡ ቅዳሴ፡	"
አሠራሩ፡ ዐይነቱ፡	"
ምዕራፍ 17፡	109
ቅዳሴ	"
የቀዳስያን ቁጥር	"
ኅብስቱ ሥጋ መለኮት፡ ደሙ ደመ መለኮት የሚሆነው ምንጊዜ ነው?	"
ምእራፍ 18፡	112
የፍልሰታ ቅዳሴ በአ.አ. አድባራት።	"
ምዕራፍ 19፡	124
አገልግሎት	"

ገጽ
ምዕራፍ 20፡ 126
ሱባዔ የተቆጠረለት፡ ትንቢት የተነገረለት ነቢይ ክርስቶስ ነው። "
ከክርስቶስ በኋላ ነቢይ የለም፤ "
የነቢይ መግለጫ "
ቡራኬ ከአብርሃም ወደ ይሥሐቅ፡ ያዕቆብ ነው የወረደው፡
ከያዕቆብ ወደ ይሁዳ እንጂ ወደ አጎቱ ልጆች አልሄደም።
ነቢያት የተናገሩትን ሁሉ የፈጸመ ነቢይም ክርስቶስ ብቻ ነው።
ክርስቶስ ነቢይ ነው፤ 131
ንጉሠ ነገሥት ነው፡ ንጉሠ ሰላም ነው፡
የመከራ ሰው ነው፡ 132
ሰማዕት ሊቀ ሰማዕት ነው፡
ኃጢአተ ዓለምን የሚያስተሰርይ መሥዋዕት ነው። "
ምዕራፍ 21፡ 133
የሐሳዊ መሲሑን መምጣት ክርስቶስና ሐዋርያት ነግረዋል "
ምዕራፍ 22፡ 136
ምስጢረ ትንሣኤ ሙታን፡ "
የነፈስ ትርጓሜ ከተራ ሐዋስ "
የሰው ልጅ በክብሩ ሲመጣ፡
የሙታን ትንሣኤ ምሳሌው ክርስቶስ ነው፡
ክርስቶስ ተነሥቶ ብዙ ጊዜ ታይቷል፡
የዚህ ርእስ መደምደሚያ 139
ምዕራፍ 23፡ 140
መንፈስ ቅዱስ፡ ከሦስቱ አካላት አንዱ አካል፡ "
መንፈስ ቅዱስን እብም ወልድም ይልኩታል፡
መንፈስ ቅዱስ እኛን ይረዳናል፡ ያጸናናል፤
ስለዚህ ርእስ መደምደሚያ 143
ምዕራፍ 24፡ 144
የክርስቶስ ተከታይ ምንድር ነው? "
ምዕራፍ 25፡ 145
የቅዱሳን አማላጅነት፡ "
በዐጸደ ሥጋም በዐጸደ ነፍስም 147
ምዕራፍ 26፡ 150
የመላእክት አማላጅነት "
መላእክትን እናከብራለን፡ በአክብሮትም እጅ እንሣለን፤

	ገጽ
ምዕራፍ 27፦	152
ቅዱሳን እነማናቸው?	"
ምዕራፍ 28፦	154
ቅድስት ድንግል ማርያም፦	"
የቅድስት ድንግል መግለጫ፦	"
ድንግል ናት	156
ምዕራፍ 29፦	160
ሴት በክርስቶስ አደባባይ፦	"
ምዕራፍ 30፦	185
ሴት በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን፦	"
63 ጠቅላላ አትኖም	"
ምዕራፍ 31፦	194
ሰጊድ፦	"
የሰጊድ መግለጫ	"
ታቦት	"
ምዕራፍ 32፦	197
ቤተ መቅደስ፦ ቤተ ክርስቲያን	"
ምዕራፍ 33፦	199
የልዩ ልዩ ቃላት ትርጉም፦	"
አጠቃላይ የቃላት መግለጫ	"
አብ፦	"
እም፦ እጉ፦ እጎት፦	200
ነፍስ፦	201
ገነት፦ መንግሥተ ሰማያት፦	202
ገሀነም፦ ገሃነም	"
ምዕራፍ 34፦	203
ነፍስ፦ ገነት፦ መንግሥተ ሰማያት	"
ነፍስ፦	"
ገነትና ሲኦል፦	205
ገሃነም፦	206
ምዕራፍ 35፦	207
ሃይማኖት ከምግባር ምግባር ከሃይማኖት፦	"
ለዚህ ምዕራፍ መደምደሚያ፦	208

	ገጽ
ምዕራፍ 36፡	209
ረበናት አፅራረ ክርስቶስ	"
ሥርዓተ ረበናት	"
ፈሪሳዊነትና ክርስቶስ	"
ግዝረት፡	212
ምዕራፍ 37፡	213
ቅዱሳት መጻሕፊት፡	"
ምዕራፍ 38፡	215
ሥልጣን ወሚመተ ክህነት፡	"
ምዕራፍ 39፡	218
ሚመተ ምእመናን፡	"
ምእመን ሁሉ የሃይማኖት መምህር ነው።	"
ምዕራፍ 40፡	220
ያልተማረ ቄስ ሁሉን ያረክስ፡ የተማረ ቄስ ብዙ ሕዝብ ይቀድስ፡	"
ምን ርኩስ አለ?	"
ቡና	"
ሲጃራ	221
ግተብ	"
ዓሣ	223
ሴት በወር አበባና በወሊድ ትረክሳለች ወይ?	"
ጫማ፡	224
የወሊድ መቆጣጠር፡	225
ምዕራፍ 41፡	227
ልዩነት ለሹመት፡	"
ምዕራፍ 42፡	231
ተግሩ ተዘጋጁ	"
ምዕራፍ 43፡	232
አጠቃላይ ምክር ለካህናት፡	"
ምዕራፍ 44፡	233
መጠይቅ ለጠያቂና ተመራማሪ፡	"
ምዕራፍ 45፡	236
ለማስታወቅ ያህል	"
ምዕራፍ 46፡	247
መፍትሔ ቃላት	247

ማ ረ ሚ ያ

ገጽ	መሥመር	ግድፈት	እርማት
13	15	ክተብ	ክታብ
13	33	የዕለት—	ጉርስ ሳላጣ እስካሁን አለሁየለም
17	1	በሉ በኢትዮጵያ ሥነ ጹሑፍ ውስጥ የነበሩት መምህራን ሁሉ ከኔ በቀር	ተደግሟል
18	9	በአድማቸው	በዕድሚያቸው
20	33	ይጠቁማል	ይጠቁማል
28	34	ወዘበምድርኒ	ዘበሰማይኒ ወዘበምድርኒ
29	6	ወይሴብሕኩረ	ወሴባሕ ኅቡረ
35	29	ሀሉ	ሁሉ
38	31	ወእስከ ዓለም	ወእስከ ለዓለም
40	1	ረ) ፈጠረ።	የዚህ ትርጉም በሐ የተነገረው ወለደ ነው
41	12	መንፈስ ቅዱስ	መንፈሰ ጽድቅ
44	20	ይጸድቃል	ያጸድቃል
46	8	አኅፍር	አኅፍር
48	27	በግደየለሽእነት	በግድየለሽነት
52	9	ኢያስዐር	ኢይሰዐር
55	5	በግሩክ	በግሪክ
59	2	አልፈልግም	አልፈለገም
59	25	ይጠቅሳል	ይጠቀሳል
63	4	ወለኮሎሙ·	ወለኩሎሙ·
63	27	ማሕያዊ ክመንፈስ	ማሕያዊ ክመ መንፈስ
64	22	መንፈስ ቅዱስ	መንፈሰ ቅዱስ
76	29	ምስጢር ቀንዲል	ምስጢረ ቀንዲል
80	7	ል	ለ
80	9	ሐረ እኅሁ· መወንድሙ·	ሐረ እኅሁ· ከወንድሙ·
81	18	ብቻን	ብቻ ን
85	22	የሽኮኮ	የእሽኮኮ
90	12	ጅጀ	ጅጁ
93	23	12 ጴጥ 1፡4)	2 ጴጥ
93	29	ይጽፏል	ይጽፋል
97	4	እንጠቅሳለን ሐሐሠ	እንጠቅሳለን
	16	እስነግዋለሁ·	አስነግዋለሁ·
	18	አኔም	እኔም
103	28	አእኮዩ	አእዙዩ
104	2	ወሐዲበ	ወሐዲበ
104	27	ሕማመነ	ሕመ·ማነ
	2	በሳሌም	በሰሌምሂ

ከደራሲው የታተሙ

1. ቀዳማዊ ምንባበ ግዕዝ
2. ሰዋስወ ግዕዝ
3. ግዕዝና አማርኛ መጽሔት
4. መልከዐ ኢትዮጵያ
5. ሀገር ምንድር ናት?
6. ጋብቻ ለምን ይጠላል?
7. 1ኛ ሰምና ወርቅ
8. 2ኛ ሰምና ወርቅ
9. ኢትዮጵያዊ ቅኔ
10. ያማርኛ ግጥምና ቅኔ ማስተማሪያ
11. ገብረ መስቀል ባሪያው
12. የድርሰት አጠነት
13. እኔስ ሰው አልሆንም
14. ሠርግና ልማድ
15. የአማርኛ ሐረግ
16. የግዕዝ ቅኔዎች (በአ. አ. ዩ. የኢ. ጥ. ቁ. 6:)
17. የግዕዝ ቅኔዎች (በአ. አ. ዩ. የኢ. ጥ. ቁ. 32:)
18. 46 አናቅጽ (በእየ መጽሔቱና ጋዜጣው የወጡ)
19. ወይዘሮ ዓለሚቱ
20. የግዕዝ ቅኔ ዜማ
21. ሁሉም ሁሉን ይወቅ

የተዘጋጁ

1. ሁለት ወር በዋሽራ 24,733 የቅኔ እንግልጋ፤
2. የሴት አቋም በክርስቲያን ኢትዮጵያ (693 ገጽ)

የባህል ሐኪሙና የደራሲው አድራሻ

ፖ.ሣ.ቁጥር 30143፡ አ.አ. ቴሌ. 18-23-20።

የቤት ቁ. 442፡ ቀበሌ 10፡ ከፍተኛ 16፡ የካ፡ አ.አ.